@BOOKALEM

ሲድኒ ሼልደን

የፍርድ ቀን ዘመቻ

ትርጉም ብስራት አጥላባቸው

@BOOKALEM

ሲድኒ ሼልደን

የፍርድ ቀን ዘመቻ

ቡክዓለም በቴሌግራም የቀረበው መጽሐፍ
@BOOKALEM
ይቀላቀሉን

Sidney Sheldon
The Doomsday Conspiracy

ትርጉም– ብሥራት አጥላባቸው ኃይሌ

ሰኔ 2012 ዓ.ም

@BOOKALEM

"በሚያጓጓ ጊዜ ውስጥ ያኑርህ!"

(ጥንታዊ የቻይናዎች ርግማን)

<u>መታሰቢያ</u>

ለወይዘሮ ጽጌ ኃይሌ ደስታ

አንደኛ እትም– ሐምሌ 1986 ዓ.ም
ሁለተኛ እትም–ግንቦት 1998 ዓ.ም
አሥራ አንደኛ እትም–ሰኔ 2007 ዓ.ም

<u>ሌሎች ሥራዎች</u>

አፐሬሺን መቅደላ– ድርሰት
ሌላው ገጽታዬ– ሲድኒ ሼልደን
ባልተኛው– ጀምስ ፓተርሰን
ተለዋጭ ሰላይ– ፍሬደሪክ ፎርሲዝ
ግዙፍ የስኬት እርምጃዎች– አንቶኒ ሮቢንስ
የስኬት ጉዞ–

<u>በቅርብ የሚወጡ</u>

የቤይሩቱ ፍንዳታ -ድርሰት
ሞሳድና ዘመቻ ሙሴ– እውነተኛ ታሪክ
የዘመናት እንቆቅልሽ– ዘጋቢ
ጠቢቧ የወሲብ መምሕርት-ሥነ-ወሲብ
የሕልም መፍቻ ከነትርጉሙ
ብሰል ጥቅሶች

@BOOKALEM

ክፍል አንድ

አዳኙ

እሁድ ጥቅምት አሥራ አራተኛ ቀን

2100 ሰዓት

አስቸኳይ መልዕክት

በጣም ከፍተኛ ምሥጢር

ኤን.ኤስ.ኤ. ለ–ኮምሴክ ምክትል ዳይሬክተር

ዐይኖች ብቻ

ግልባጭ የለውም

አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ

መልዕክት– ይጀመር

አስታውቁ ለፊረንሳይ፤ ጣሊያን፤ ጀርመን፤ ስዊዘርላንድ፤ እንግሊዝ፤ ካናዳ፤ ሩሲያ የመረጃ ድርጅቶች።

እሁድ ጥቅምት አሥራ አራተኛ ቀን

አስቸኳይ መልዕክት

በጣም ከፍተኛ ምሥጢር

ኤን. ኤስ.ኤ ለ–አሥራ ሰባተኛው ቀጣና የባሕር ኃይል መረጃ ጽሕፈት ቤት

ምክትል ዳይሬክተር

ዐይኖች ብቻ

አርእስት–ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ

ወደ ኤጀንሲው በጊዜያዊነት እንዲዛወር አስፈላጊው ሁሉ ይዘጋጅ።

ወዲያውኑ ተግባራዊ የሚሆን!

ከላይ በተጠቀሰው ላይ የምታደርጉት ትብብር ይጠበቃል።

@BOOKALEM

ኡተንዶርፍ ሰዊዘርላድ

እሁድ ጥቅምት ኣሥራ ኣራተኛ ቀን

1500 ሰዓት

እመስኩ ጠርዝ ቆመው የነበሩት ምስክሮች ሽብር በተሞላበት ፀጥታ ደንዝዘውና ኣፍጥጠው እየተመለከቱ ነበር። እፊታቸው የተጋደመው ትዕይንት ኣስቂኝ የሆነ ብልሹ ቅርጽ ያለው ከጥንታዊው ሰው ጥልቅና ጨለማ ገና ያልበሰለ ሕሊና ወስጥ የተቡተነ ቅዠት ነበር። እያንዳንዱ ምስክር የተለያየ የስሜት መለዋወጥ ነበር የደረሰበት። ኣንዱ ሕሊናውን ሰቶ ወደቀ። ኣንድ ሌላ ሰው ኣስመለሰው። ኣንዷ ሴት ከቁጥጥር ውጭ ሆና ትንዘፈዘፍ ነበር። ሌላ ሰው ደግሞ የልብ ደካም ሊይዘኝ ነው!' ሲል ኣሰበ። ኣዛውንቱ ካህን ደግሞ መቁጠሪያቸውን ጨምድደው ያዙና ኣማተቡ። "ኣባት ሆይ እርዳኝ! ሁላችንንም እርዳን! ከዚህ ሰው ከመሰለ እርኩሰ መንፈስ ተከላከልልን። በመጨረሻም የሰይጣኑን መልክ ተመልክተናልና። ይህ የዓለም መጨረሻ ነው። የዳኝነት ቀን መጥቷል። የፍጻሜው ጦርነት ኣዚህ ነው። ኣርማጌዶን! ኣርማጌዶን! ኣርማጌዶን!"...

@BOOKALEM

ምዕራፍ አንድ

አንደኛ ቀን

ሰኞ ጥቅምት አሥራ አምስት

ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ኩ.ቺ. ቬትናም በሚገኘው የተጣበበ ሆስፒታል ውስጥ ተኝቶ በመታከም ላይ ነው። ሱዛን በሚያምረው ነጭ የነርሶች የደምብ ልብስ ሆና ወደ ራሱ ዘንበል በማለት "ንቃ! ባሕረኛው። አትሞትም!" ስትለው ይሰማዋል። እሱም ምትሃታዊ ድምጿን ሲሰማ የሚቆጠቁጠውን ሕመሙን ረሳው። አንድ ነገር በጆሮው ስታንሾካሹከለት ይሰማዋል። እጁን ወደ ላይ ላከና ሊጎትታት ሞከረ። ነገር ግን የጨበጠው ባዶውን አየር ነው።

ሮበርት ቤላሚ ሙሉ በሙሉ ከእንቅልፉ የነቃው በሚያቃጭለው የስልክ ጥሪ ነው። ሕልሙ እንዳያመልጠው ቀስ ብሎ ዐይኖቹን ገለጣቸው። አልጋው አጠገብ ያለው ስልክ ይጮሃል። ሰዓቱን ሲመለከት ከለሊቱ አሥር ሰዓት ይል ነበር። ከሕልሙ በመደናቀፉ በጣም ተበሳጭቶ ስልኩን ምንጭቅ አድርጐ አነሳና....."ለመሆኑ ስንት ሰዓት እንደሆነ ታውቃለህ?" አለ።

"ኮማንደር ቤላሚ?" ሲል ጥልቅ የወንድ ድምፅ ጠየቀ።

"አዎን።"

"ኮማንደር አንድ መልዕክት አለኝ። ... ልክ በ0600 ሰዓት ፎርት ሚድ በሚገኘው የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል መሥሪያ ቤት ጄነራል ሒሊያርድ ቢሮ ሪፖርት እንድታደርግ ታዘሃል። መልዕክቱ ግልጽ ነው ኮማንደር?"

"ነውም አይደለምም!" አለ ሮበርት። "በይበልጥ አይደለም!"... አለና ቀስ ብሎ ስልኩን ዘጋው። መልዕክቱ ግራ አጋብቶታል። የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ከሱ የሚፈልገው ምንድነው? የተመደበው በባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ነው። ታዲያ ከማለዳው 12 ሰዓት እሱን ስብሰባ ለመጥራት የሚያጣድፋቸው ምንድነው? እንደገና ጋደም አለና ሕልሙን ለማስታወስ ሞከረ። ፍጹም ገሐድ የሆነ ሕልም ነበር። ሕልሙ ለምን እንደታለመው ገብቶታል። ባለፈው ምሽት ሱዛን ስልክ ደውላለት ስለነበር ነው።

"ሮበርት"... አለችው።

ድምጿን ሲሰማ ሁሌም እንደሚሆነው ድምጹ እየተንቀጠቀጠበት "ሄሎ ሱዛን?" አላት።

"ደህና ነህ ሮበርት?"

"በእርግጥ ደህና ነኝ። የገንዘብ ከረጢትስ ደህና ነው?" አላት።

"እባክህ ሮበርት እንደዚህ አትበል።"

@BOOKALEM

"እሺ ሞንቴ ባንከስ ደህና ነው?"

ባለቤትሽስ ደህና ነው ወይ? ለማለት ፍጹም አይቻለውም። ሞንቴ ባንክስ የሱዛን ባል ነው።

"በጣም ደህና ነው" አለች ሱዛን። "ለጥቂት ጊዜ ርቀን ለመሄድ ስለፈለግን እንዳትጨነቅ ይህንኑ ልነግርህ ፈልጌ ነው" አለችው።

የድምጹን ቃና ለመመለስ እየጣረ "ወዴት?" ሲል ጠየቃት።

"ወደ ብራዚል ልንበር ነው።"

'በግንዘብ ከረጢት የግል ቦይንግ 727' ሲል አሰበ።

"ሞንቴ ብራዚል ውስጥ የሚያከናውነው አንዳንድ የንግድ ሥራዎች አሉት።"

"በርግጥ?" አለ ሮበርት። ቀጠለናም "እኔ ያገራቱ ባለቤት ነበር የሚመስለኝ።"

"ሮበርት እባክህ ይህን ንግግርህን አቁም።"

"አዝናለሁ ሱዛን።"

"አንዲት ሴት ፈልገህ በመጎዳኘት ደስተኛ እንድትሆን እፈልጋለሁ።"

"አንዲት ሴት አግኝቼ ነበር ሱዛን። ግን ምን እንደተፈጠረ ታውቂያለሽ? እንደገና ተለያየን።"

"እንደዚህ የምታደርግ ከሆነ ሁለተኛ አልደውልልህም!" አለች ሱዛን።

ሮበርት ሆዱን ባር ባር አለውና "እባክሽ እንደዚህ አትበይ ሱዛን" አላት። ሱዛን ለእርሱ የሕይወት እስትንፋሱ ናት። የእርሷ እርሱን ያለማነጋገር ጉዳይ እንኳን ሊቀበለው ሊያስበውም የማይችለው ነገር ነው።

"አንዲት ሴት እንድትይዝ እሻለሁ" አለችው ደገመችና።

"እሺ ሱዛን ቃል እገባልሻለሁ!" አላት

"ስላንተ በጣም አስባለሁ የኔ ፍቅር።"

"እኔ በጣም ደህና ነኝ" አላት። ግን 'እውነተኛውን ጉዳይ ብትረዳውስ?' ሲል አሰበ። ነገር ግን እንኳንስ ለእርሷ ለማንም ሊያሳውቅ ወይም ከማንም ጋር ሊወያይበት የማይሻው ምሥጢር ነው። የሮበርትን እውነተኛ ችግር በመረዳት የሚደርስባትን ሐዘን ፈጽሞ ሊቋቋመው አይችልምና።

"ብራዚል እንደደረስኩ እደውልልሃለሁ" አለች ሱዛን።

በመካከላቸው ረዘም ያለ ፀጥታ ሰፈነ።

"አሁን ልለይህ ነው.....መሐድ አለብኝ" አለችው።

"ሱዛን....."

"አቤት"

"እወድሻለሁ። ምን ጊዜም አፈቅርሻለሁ።"

"አውቃለሁ ሮበርት እኔም አፈቅርሃለሁ።"

@BOOKALEM

ይህ ነበር በጣም የሚያስገርመው ጉዳይ። ፍቅራቸው ጣፋጭና መራራ.....እስካሁን ድረስ በጽናት ይዋደዳሉ።

"ሁለታችሁም ትክክለኛ የሆናችሁ ግሩም የትዳር ጓደኛሞች ናችሁ!" ይሏቸው ነበር ጓደኞቻቸው ሁሉ። ታዲያ በመኻላቸው ምን ስህተት ተፈጠረ?

ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ከመኝታው ተነሳና በባዶ እግሩ ወደ ሳሎን ሄደ። ቤቱ በሙሉ "የሱዛን ያለህ!" እያለ ይጮሃል። ሳሎኑ ውስጥ በደርዘን የሚቆጠሩ ሮበርትና ሱዛን አብረው የተነሷቸው ፎቶግራፎች ተደርድረዋል። በስኮትላንድ ደጋማ ሥፍራዎች ዓሣ ሲያጠምዱ፤ ታይኮንግ የቡድሃ ጣዖት ሐውልት ፊት ቆመው፤ ሮም በበርጌስ የአትክልት ሥፍራ፤ በዝናብ ውስጥ በጋሪ ሲንሸራሸሩ። ሁለት በፍቅር የሰከሩ ሴትና ወንድ ሲስቁ ሲቦርቁ የሚያሳዩ ፎቶግራፎች።

ወደ ምግብ ማብሰያው ክፍል ገባና ቡና በጀበና ጥዶ የማዕድ ቤቱን ሰዓት ሲመለከት ከለሊቱ 10፡15 ይል ነበር። ጥቂት ካወላወለ በኋላ ስልኩን አነሳና የተወሰኑ ቁጥሮች መታ መታ አደረገ። ከስድስት ጥሪዎች በኋላ "ሄሎ....." የሚለውን የአድሚራል ዊታከርን ድምፅ ሰማ።

"አድሚራል?"

"አዎን።"

"ሮበርት ነኝ አድሚራል። በዚህ ሰዓት ስለቀሰቀስኩዎት በጣም አዝናለሁ። ከብሔራዊ የፀጥታ ወኪል አንድ እንግዳ የሆነ የስልክ ጥሪ ደርሶኝ ነበር።"

"ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ካንተ የሚፈልገው ምንድ ነው?"

"አልገባኝም። በ12፡00 ሰዓት ጄነራል ሒሊያርድ ጽሕፈት ቤት እንድቀርብ ታዝዣለሁ።"

"ምናልባት ወደዚያው ተዛውረህ እንዳይሆን።"

"ሊሆን አይችልም። ፈጽሞ ስሜት አይሰጥም። ለምን ብለው?"

"በግልጽ አንድ አስቸኳይ የሆነ ጉዳይ አለ ማለት ነው ሮበርት። ለምን ስለውጤቱ ከስብሰባው በኋላ አትደውልልኝም?"

"እደውልልዎታለሁ አድሚራል። አመሰግናለሁ" አለና ስልኩን ዘጋው።

'ሽማግሌውን ባላስቸግረው ይሻል ነበር' አለ ሮበርት። አድሚራሉ ከሁለት ዓመት በፊት ከባሕር ኃይል የመረጃ ጽሕፈት ቤት ኃላፊነታቸው በጡረታ ተገልለው ነበር። እንዳውም ጡረታ እንዲወጡ ተገደዱ ማለት የበለጠ ተስማሚ ነው።

ስለአድሚራሉ ውስጥ ውስጡን የሚናፈሰው ወሬ ባሕር ኃይሉ ለአድሚራሉ አንድ አልባሌ ቢሮ ሰጥቷቸው መርከብ ስር የሚጣበቁ የባሕር ነፍሳትን የመቁጠር ዐይነት ተራ ሥራ እንደሚሠሩ ነው።

@BOOKALEM

አድሚራሉ ስለወቅታዊ የመረጃ ጉዳዮች ምንም ግንዛቤ አይኖራቸውም። በዚህ ዓለም ላይ ከሱዛን ሌላ ሮበርትን በሚገባ የሚያውቀው ሰው ቢኖር አድሚራሉ ብቻ ናቸው። እጅግ በጣም ነበር ሮበርትን የሚቀርቡት።

ሮበርት ከሱዛን ከተለየ በኋላ ከሰው ጋር መነጋገር በጣም ነበር የሚናፍቀው። ልክ በጊዜ እስር ቤት ውስጥ የተከረቸመ ሆኖ ነበር የሚሰማው። በሌላ ጊዜ በሌላ ዓለም ውስጥ አሁንም ከሱዛን ጋር የደስታና የፍስሐ የጋብቻ ኑሮ የሚኖር መስሎ ይታየዋል።

ተንተከተኮ የፈላውን ቡና በስኒ ቀድቶ መታጠቢያ ቤት ገባና የፊቱን ገጽታ በመስታወት ይመለከት ጀመር። በመጀመሪያዎቹ አርባ ዓመታት ውስጥ የሚገኝ፤ ዘለግ፤ ቀጠን ያለና አካላዊ ብቃት ያለው ሰው ተመለከተ። ደረቱ ላይ ጥልቅና ሰፊ ጠባሳ አለው። ጐላ ጐላ ያሉ ጥቋቁር ዐይኖች፤ ጠንካራ አገጭና ጥቁር ፀጉር ያለው ሰው። ደረቱ ላይ ያለው ጠባሳ ከአውሮፕላን አደጋው የወረሰው ቅርስ ነበር። ጠባሳውና ሱዛን የትላንት ናቸው። ይህ ግን ሱዛን የሌለችበት ዛሬ ነው። ጢሙን ተላጭቶ ገላውን ከታጠበ በኋላ ወደ ልብስ መስቀያው አመራ። ጥቂት አሰብ አደረገና ግራጫማ ሙሉ የሱፍ ልብስ ከነጭ ሸሚዝ ጋር ለብሶ ግራጫማ ከራቫት አሰረበት።

ስለብሔራዊ የፀጥታ ወኪል መሥሪያ ቤት የሚያውቀው ነገር በጣም ውስን ነበር። ድርጅቱ "የእንቆቅልሽ ቤተ መንግሥት" በሚል የቅጽል መጠሪያ ከመታወቁም በላይ መላውን የአሜሪካ የስለላና የመረጃ ድርጅቶች የሚተካ ከሁሉም በላይ ደግሞ እጅግ ምሥጢራዊ የሆነ መሥሪያ ቤት ነው።

'ከኔ የሚፈልጉት ምን ይሆን? ግድ የለም በቶሎ እደርስበታለሁ' አለ።፣

ምዕራፍ ሁለት

የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል (ናሽናል ሴኩሪቲ ኤጀንሲ) ፎርት ሚድ ሜሪላንድ ውስጥ በ82 ኤከር መሬት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ሁለቱም ሕንፃው በአንድ ላይ ተዳምሮ ላንግሌይ ቨርጂኒያ ከሚገኘው የሲአይኤ ዋና መሥሪያ ቤት የበለጠ ነው።

የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል የተቋቋመው ለዩናይትድ ስቴትስ በመገናኛ አውታር መረጃ (ዳታ) ለመሰብሰብ ሲሆን በሺህ የሚቆጠሩ ተቀጣሪ ሠራተኞች ያሉት፤ በሚያደርገውም እንቅስቃሴ በጣም በርካታ የሆነ መረጃ የሚያመነጭ፤ ከነዚህም መረጃዎች በየቀኑ ከአርባ ቶን በላይ የሆነ የወረቀት ሰነድ የሚከመርበት የስለላና የመረጃ ድርጅት ነው።

@BOOKALEM

ሮበርት የመጀመሪያው መግቢያ በር ላይ ሲደርስ ገና በሚገባ አልነጋም ነበር። ባለስምንት ጫማ ከፍታ ወዳለውና በእሾሃማ ሽቦ ወደታጠረው አጥር መኪናውን እያሽከረከረ ሄደ። በሩ ላይ አንድ የዘቦች ቤት ሲኖር ሁለት የታጠቁ ዘቦች አካባቢውን በንቃት በመቃኘት ላይ ነበሩ። ሮበርት በሩ ላይ ሲደርስ አንዱ ዘብ በቦታው ሲቆይ አንደኛው ከዘብ ቤት ወጣና ወደ ሮበርት መጥቶ "ምን ልርዳህ?" ሲል ጠየቀው።

"ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ነኝ። ጄነራል ሒሊያርድን ለማየት ነው የመጣሁት" አለ።

"እባክህን መታወቂያህን ብታሳየኝ?"

ሮበርት ቤላሚ ከቦርሳው ውስጥ የአሥራ ሰባተኛውን ቀጣና የባሕር ኃይል መረጃ ጽሕፈት ቤት አባልነት የሚያሳይ መታወቂያ ካርድ አወጣና ለዘቡ ሰጠው።

ዘቡም መታወቂያውን በጥንቃቄ ከመረመረው በኋላ "አመሰግናለሁ ኮማንደር!" ብሎ መለሰለት። ቀጠለና ዘብ ቤት ውስጥ ለቆመው ባልደረባው ምልክት ሲሰጠው የመግቢያው በር ወለል ብሎ ተከፈተ። ሮበርት ወደ ውስጥ መንገዱን ሲጀምር ዘብ ቤት የቆመው ጠባቂ ሰልኩን አነሳና "ኮማንደር ቤላሚ በመንገድ ላይ ነው" ሲል አሳወቀ።

ከአንድ ደቂቃ በኋላ ሮበርት አንድ ሌላ የኤሌክትሪክ ኃይል ያለው አጥር ላይ ደረሰ።

አንድ ዘብ ወደ ሮበርት ጠጋ አለና "ኮማንደር ቤላሚ?" ሲል ጠየቀው።

"አዎ ነኝ።"

"እባክህን መታወቂያህን ብታሳየኝ።"

ሮበርት ለመቃወም ጀመረና ተወው። 'ምን ዋጋ አለው? ይህ የተከለለ የአራዊት ሥፍራ ነው።'

ከቦርሳው ውስጥ እንደገና የመታወቂያ ካርዱን አወጣና ለዘቡ ሰጠው።

ዘቡ መታወቂያውን በሚገባ ከተመለከተ በኋላ "አመሰግናለሁ" ብሎ መለሰለትና ለሌላው ዘብ የሚታይ ምልክት ሲሰጠው በሩ ወለል ብሎ ተከፈተለት።

ሮበርት ጥቂት እንደነዳ ሌላ ሽምጥ የታጠረ አጥር አጋጠመው። 'ያምላክ ያለህ! በአራዊት ሥፍራ ውስጥ ነው ያለሁት!' አለ ለራሱ። የመታወቂያ ካርዱን ለማውጣት ኪሱ ሲገባ ሲል ዘቡ የመኪናውን ሰሌዳ ቁጥር ተመለከተና "እባክህ ኮማንደር መኪናህን በቀጥታ ወደ አስተዳደር ሕንፃው ንዳ። እዚያም አንድ የሚቀበልህ ሰው ታገኛለህ" አለው።

"አመሰግናለሁ።"

@BOOKALEM

ሮበርት የመግቢያው በር ሲከፈትለት በቀጥተኛው መንገድ ላይ እየነዳ አንድ ነጭ ግዙፍ ሕንፃ ፊት ሲደርስ ሕንፃው በር ላይ አንድ የሲቪል ልብስ የለበሰ ሰው በጥቅምቱ የንጋት ውርጭ እየተንቀጠቀጠ ቆሞ ሲጠብቀው አየ።

"መኪናህን እዚያው አቁማት። እስፈላጊውን ጥንቃቄ እናደርግላታለን" አለው። ሮበርት ቤላሚ ቁልፉን መኪናው ላይ ትቶ ወረደ። ቆሞ ይጠብቀው የነበረው ሰው በሠላሳዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ፤ ቀጠን ዘለግ ያለ፤ የቆዳው ቀለም የገረጣ ሰው ነበር። ለዓመታት ያህል ፀሓይ ፈጽሞ የነካው አይመስልም።

"ሐሪሰን ኬለር እባላለሁ። ወደ ጄነራል ሒሊያርድ ቢሮ ወስድሃለሁ" አለው።

ሁለቱ ሰዎች ተያይዘው ጣራው በጣም ከፍ ያለ ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ገቡ። በአዳራሹ ውስጥ አንድ የሲቪል ልብስ የለበሰ ሰው ከጠረጴዛ ኋላ ተቀምጧል።

"ኮማንደር ቤላሚ!" የሚል ጥሪ ሰማ።

ሮበርት በፍጥነት ዘወር ሲል የተቀመጠው ሰውዬ የያዘው ካሜራ "ቀጭ!" ሲል ተሰማው። "አመሰግናለሁ ጌታዬ!" አለ ሰውዬው።

ሮበርት ቤላሚ ወደ ኬለር ዘወር አለና "ምንድነው ጉዳዩ?" አለው።

"ይህ ጉዳይ አንድ ደቂቃ ብቻ ይፈጃል" አለ ኬለር።

ከሰልሳ ሴኮንድ በኋላ ሮበርት ቤላሚ ፎቶግራፉ የተለጠፈበት ባለሰማያዊና ነጭ ቀለም በደረት ላይ የሚደረግ መታወቂያ (ባጅ) ተሰጠው።

"እባክህ ኮማንደር እዚህ ሕንፃ ውስጥ እስካለህ ድረስ ይህን የመታወቂያ ባጅ በደረትህ ላይ አንጠልጥለው።"

"እሺ!"

ሮበርት በረዥም ነጭ ኮሪደር ውስጥ መራመድ እንደጀመረ በየሃያ ጫማው ርቀት ላይ የፀጥታ መቆጣጠሪያ ካሜራዎች መተከላቸውን ለማስተዋል ቻለ።

"ይህ ሕንፃ ምን ያህል ትልቅ ነው?" ሲል ጠየቀ።

"ከሁለት ሚሊዮን እስኩዌር ጫማ ትንሽ ከፍ ይላል ኮማንደር።"

"ምን?"

"አዎን። ይህ የምንራመድበት ኮሪደር እንኳ በዓለም ላይ የመጨረሻ ረዥሙ ኮሪደር ሲሆን ርዝመቱም ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ጫማ ነው። ሙሉ በሙሉ ራሳችንን የሚያስችለን ሕንፃ ነው። የገበያ ማዕከል፤ ካፌቴሪያ ፣ የተሟላ ሱቅ፤ ስምንት ሻይ ቤቶች፤ የተሟላ የቀዶ ጥገና ሕክምና መስጫ ክፍል ያለው ሆስፒታል፤. የጥርስ ሕክምና መስጫ ክፍል፤ የሎሪስ ስቴት ቅርንጫፍ ባንክ ቤት፤ የልብስ ንጽሕና መስጫ፤ የጫማ ሱቅ፤ የፀጉር ማስተካከያ ሱቅና ሌሎችም ጥቂት ለየት ያሉ ነገሮች አሉን።"

'ይህማ ከመኖሪያ ቤት የራቀ የመኖሪያ ቤት ነው!' አለ ሮበርት በሐሳቡ።

@BOOKALEM

ቀጥሎም እጅግ በጣም ሰፊና ሥፍር ቁጥር በሌለው ኮምፒውተር የተሞላ አዳራሽ ውስጥ ሲገቡ ሮበርት እጅግ በጣም ከመደነቁ የተነሳ ባለበት ቦታ ፈዞ ቀረ።

"ያስደንቃል አይደለም?" አለ ኬለር። ይህ አንዱ የኮምፒውተር ክፍላችን ሲሆን የሦስት ቢሊዮን ዶላር ዋጋ ያለው የምሥጢር ቃላት መፍቻ መሣሪያና አያሌ ኮምፒውተሮችን ያካተተ ቤት ነው።"

"እዚህ ድርጅት ውስጥ ምን ያህል ሠራተኞች አሉ?"

"አሥራ ስድስት ሺህ ያህል ይሆናሉ።"

'ታዲያ ከኔ የሚፈልጉት ምን ይሆን?' አለ በሐሳቡ።

ኬለር ሮበርትን እየመራ ይዞት ሄደና ሌሎች ሠራተኞች የማይጠቀሙበት አንድ የግል አሳንሱር (ሊፍት) ውስጥ ይዞት ገባ። ኬለር በያዘው ቁልፍ አሳንሱሩን ካንቀሳቀሰው በኋላ አንድ ፎቅ ወደ ላይ ተጉዘው ከአሳንሱሩ ወጡ። እንደገና በአንድ ረዥም ኮሪደር ውስጥ ተራምደው የኮሪደሩ መጨረሻ ላይ የሚገኝ አንድ ቢሮ ፊት ሲደርሱ ቆሙ።

ኬለር ሮበርትን እየመራ አንድ ሰፊ የእንግዳ መቀበያ ቢሮ ውስጥ ይዞት ገባ። ቢሮው የአራት ጸሐፊዎች ጠረጴዛ ሲኖረው በዚያ ሰዓት ሁለቱ ጸሐፊዎች ማልደው ጠረጴዛቸው ላይ ለሥራ ተገኝተዋል።

ሐሪሰን ኬለር ለጸሐፊዋ ምልክት ሲሰጣት ጸሐፊዋ ጠረጴዛዋ ላይ አንድ ቁልፍ በጣቷ ስትጫን የውስጠኛው ቢሮ በር በኤሌክትሪክ ኃይል ተከፈተ። "ከቡራን እባካችሁ ወደ ውስጥ ግቡ። ጄነራል ሒሊያርድ እየጠበቋችሁ ነው!" አለቻቸው።

ሮበርት ቤላሚ ሐሪሰን ኬለርን ተከትሎ ወደ ውስጥ ገባ። ቢሮው በጣም ሰፊ ከመሆኑም በላይ ግድግዳውና ኮርኒሱ ድምጽ እንዳያስገባና እንዳያስወጣ ሆኖ የተሠራ ነው። ክፍሉ ምቾትና ቅንጦት ባላቸው ዕቃዎች፤ በፎቶግራፎችና የግል ስብስብ በሆኑ ዕቃዎች ተሞልቷል።

ባጠቃላይ የጽሕፈት ቤቱን አደረጃጀት ሲመለከቱት እዚህ ቢሮ ውስጥ ተቀማጭ የሆነው ሰው ጠረጴዛው ላይ ብዙ የሥራ ሰዓታት እንደሚያሳልፍ ያስረዳል።

የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል መሥሪያ ቤት ምክትል ዳይሬክተር የሆነው ጄነራል ማርክ ሒሊያርድ በመካከለኛ ሃምሳዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ፤ ፊተ ገጹ እንደብረት የጠነከረ፤ ሁኔታው እንደበረዶ የቀዘቀዘ፤ ብረት መሰል ዐይኖች ያሉትና ቁመናው ቀጥ ያለ ሰው ነው። ግራጫማ ሙሉ ልብስ በነጭ ሸሚዝ ለብሶ ግራጫ ክራቫት አሥሯል። ሮበርት የጄነራሉን አለባበስ መልከት አደረገና በሐሳቡ 'እኔም ጥሩ የአለባበስ ቀለም መርጫለሁ' አለ።

"ጄነራል ሒሊያርድ.....ይህ ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ነው!" አለ ኬለር።

@BOOKALEM

"እዚህ ድረስ ስለመጣህ አመሰግንሃለሁ ኮማንደር!" አለ ጄነራሉ ልክ የሻይ ግብዣ ጥሪ ይመስል።

ጄነራሉና ሮበርት እጅ ለእጅ ከተጨባበጡ በኋላ ጄነራሉ ሮበርትን "ተቀመጥ ኮማንደር ቤላሚ! አንድ ስኒ ቡና እንደምትጠጣ እርግጠኛ ነኝ" አለው።

'ሰውዬው የሰውን አዕምሮ ያነባል ማለት ነው' "አዎን ጌታዬ!" አለ ሮበርት። "ሐሪሰንስ?" ሲል ጄነራሉ ጠየቀ።

"የለም አልፈልግም" አለና ሐሪሰን ወደ ጥግ አንድ ወንበር ላይ ተኮፈሰ።

ጄነራሉ መጥሪያ ተጭኖ በሩ ሲከፈት አንድ የሩቅ ምሥራቅ ተወላጅ የሆነ ሰው የምግብ ቤት ኮት ለብሶ በማቅረቢያ ትሪ ላይ ቡናና የዳኒሽ ጣፋጭ ብስኩቶች ይዞ ገባ። ሮበርት አስተናጋጁ ሰው ምንም ዐይነት የመታወቂያ ባጅ እንዳላደረገ አስተዋለ። ቡናው ሲቀዳ ግሩም የሆነ አስደሳች መዓዛ ነበረው።

ሁለቱ ሰዎች በምቹ ለስላሳ የቆዳ ወንበር ላይ ፊት ለፊት እየተያዩ ነበር የተቀመጡት። "ዳይሬክተሩ ካንተ ጋር እንድንገናኝ ጠይቀውኝ ነበር" አለ ጄነራሉ።

ዳይሬክተሩ ኤድዋርድ ሳንደርሰን.....በስለላው ዓለም ከበብ ውስጥ ብሩህ አዕምሮ ያላቸው ዝነኛ ሰው ናቸው። ርሕራሄ የለሽ፤ ጥብቅ የሆኑ የጭፍሮቻቸው አለቃ ከመሆናቸውም በላይ በመላው ዓለም የተለያዩ የመፈንቅለ መንግሥት ሴራዎችን ያቀነባበሩ፣ በሕዝብ መሰብሰቢያ ሥፍራዎች እጅግ በጣም በጥቂቱ የሚታዩ ሰው ሲሆኑ ውስጥ ውስጡን በሹክሹክታ ብዙ ይነገርላቸዋል።

"በአሥራ ሰባተኛው ቀጣና ባሕር ኃይል መረጃ መሥሪያ ቤት ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ቆይተሃል?" ሲል ጄነራሉ ሮበርትን ጠየቀው።

"ለአሥራ አምስት ዓመታት" ሲል መልስ ሰጠ። ጄነራሉ ሌላው ቀርቶ ሮበርት የባሕር ኃይሉን የመረጃ ጽሕፈት ቤት መች በአባልነት እንደገባ እንኳ እንደሚያውቅበት ይገባዋል።

"ከዚህ በፊት ቬትናም ውስጥ አንድ የባሕር ኃይል የአየር ተዋጊ ስኳድሮን አዛዥ እንደነበርክ አምናለሁ።"

"አዎን ጌታዬ!"

"ተመትተህ ከነአውሮፕላንህ ተከስክሰህም ነበር። ማንም ትተርፋለህ ብሎ የገመተ አልነበረም" አለ ጄነራሉ።

"አዎን! ተመትቶ ወድቄ ነበር። በአደጋው የደረሰበት ሕመም እጅግ በጣም የሚቆጠቁጥ ከመሆኑ የተነሳ ሮበርት ሞትን በእጅጉ ነበር የተመኘት። ዶክተሩ አጠገቡ ቆሞ "የእርሱን ነገር እርሱት ፈጽሞ አይድንም" ሲል ሱዛን ደግሞ ወደ ራሱ ዘንበል ብላ "ዐይኖችህን ግለጥ አትሞትም!" ስትለው ይሰማዋል። አስከፊውን ሕመም ተቋቁሞ ዐይኖቹን ሲገልጥ የእንቁላል ቅርጽ ያለው ገጽታ፤ ወፍራም ጥቁር ፀጉር፤ የሚያንፀባርቁ ቡናማ ዐይኖች ያላት እጅግ በጣም የተዋበች

@BOOKALEM

ሴት አጠገቡ ቆማ ማራኪ ፈገግታ ስትመግበው አየ። ሊያናግራት በሞከረ ጊዜ የጠየቀው ብርታት ቀላል አልነበረም"።

ጄነራል ሒሊያርድ እያነጋገረው ነበር። ነገር ግን ሮበርት በራሱ ሐሳብ ተውጦ አልሰማውም።"

"ይቅርታ ምን አሉኝ?" አለ ሮበርት።

"አንድ ችግር ገጥሞናል። ዕርዳታህን እንፈልጋለን ኮማንደር።" ጄነራሉ ከመቀመጫው ተነሳና መንጐራደድ ጀመረ። "አሁን የምነግርህ ጉዳይ በጣም ከፍተኛ ምሥጢር ነው። እንዲያውም እጅግ በጣም የከበደ ምሥጢር ነው።"

"አዎን ጌታዬ!"

"በትናንትናው ዕለት በስዊስ የአልፕስ ተራራ ላይ አንድ የናቶ (የሰሜን አትላቲክ መከላከያ ድርጅት) ንብረት የሆነ የአየር ንብረት መመርመሪያ ባሉን ተከስክሷል። በባሉኑም ውስጥ እጅግ በጣም ምሥጢራዊ የሆኑ መሣሪያዎች ለሙከራ ተገጥመው ነበር። የስዊስ መንግሥት በወቅቱ ነቃቅሎ አውጥቷቸዋል። ታዲያ እንደአለመታደል ሆኖ ባሉኑ ሲከሰከስ በሥፍራው ተገኝተው የተመለከቱ ጥቂት የዐይን ምስክሮች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በወቅቱ ስለተመለከቱት አደጋ ለማንም ሰው ምንም ነገር አለማውራታቸው ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው። ለአንዳንድ አገሮች ትልቅ መረጃ ሊሰጥ ይችላልና። እየተከተልከኝ ነው?"

"ይመስለኛል ጌታዬ። እነዚህን ምስክሮች ፈልጌ አግኝቼ ስለተመለከቱት ጉዳይ ለማንም ምንም እንዳያወሩ እንዳስጠነቅቃችው ነው የፈለጉት?"

"በትክክል ወይም ሙሉ በሙሉ ለዚህ አይደለም የፈለግንህ።"

"ታዲያ ለምን እንደሆነ አልገባኝ....."

"አንተ እንድታደርግ የምፈልገው ምስክሮቹን ፈልገህ እንድታገኝ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ የዝምታውን አስፈላጊነት ጉዳይ ሌሎች እንዲያነጋግሯቸው ይደረጋል።"

"ገባኝ። ለመሆኑ ምስክሮቹ በሙሉ ስዊዘርላንድ ውስጥ ናቸው?"

ጄነራል ሒሊያርድ መንጐራደዱን ተወና ሮበርት ፊት ቆመ። "አየህ ኮማንደር። ይህ ነው ዋናው ችግራችን። እነዚህ ምስክሮች እነማን እንደሆኑ ምንም የምናውቀው ነገር የለም።"

ሮበርት አንድ የሳተው ወይም በደንብ ያልተረዳው ነገር ያለ መስለው። "ይቅርታ ምን አሉኝ?" ሲል ጠየቀ።

"ያገኘነው ብቸኛ መረጃ ቢኖር የአየር ንብረት ባሉኑ በተከሰከሰበት ወቅት ምስክሮቹ በአንድ አነስተኛ የቱሪስቶች አውቶቡስ ተሳፍረው እ.....ቦታው ምን ነበር?" ብሎ ወደ ኬለር ዘወር ሲል ኬለርም ፈጠን አለና "ኡተንዶርፍ ስዊዘርላንድ" አለው። "አዎን! ኡተንዶርፍ ሲደርሱ የደረሰውን አደጋ መመልከታቸውን ብቻ ነው የምናውቀው" አለና ጄነራሉ ንግግሩን በመቀጠል "መንገደኞቹ ከአውቶቡሱ

@BOOKALEM

ወርደው አደጋውን ከተመለከቱ በኋላ ጉዞቸውን ሲጨርሱ በየአቅጣጫው ተበተኑ።"

"ሮበርትም በዝግተኛ ድምፅ "ጄነራል ሒሊያርድ! እነዚያ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ወይም ወዴት እንደሄዱ የሚያሰረዳ ሪኮርድ የለም ነው የሚሉኝ?" ሲል ጠየቀ።

"ትክክል!" አለ ጄነራሉ።

"እና ወደዚያው ሄጄ ምስክሮቹን እንድፈልግ ነው የሚሹት?"

"በትክክል እንደሱ እንድታደርግ ነው የፈለግንህ" አለና ጄነራሉ ንግግሩን በመቀጠል "በከፍተኛ ደረጃ የተመረጥከው አንተ ነህ። ግማሽ ደርዘን የሚሞላ የተለያዩ አገሮች ቋንቋዎችን እንደምትናገርና የበሰለ የመሰክ ሥራ ልምድ እንዳለህ ተነግሮኛል። ዳይሬክተሩም በጊዜያዊነት ወደዚህ ወደ ብሔራዊ የፀጥታ ወኪል መሥሪያ ቤት እንድትዘዋወር ሁኔታዎችን አመቻችተዋል።"

"በዚህ ጉዳይ ላይ ከስዊስ መንግሥት ጋር በመተባበር ሠራለሁ ብዬ ገምታለሁ" አለ ሮበርት።

"የለም! ብቻህን ነው የምትሠራው" አለ ጄነራሉ።

"ብቻህን?" ሮበርት ጠየቀ።

"በዚህ በተሰጠህ ተልዕኮ ውስጥ ማንንም ጣልቃ ማስገባት የለብህም። በዚያ በተከሰከሰ ባሉን ውስጥ ተገጥሞ ስለነበረው መሣሪያ ጠቃሚነትና ምሥጢራዊነት በበቂ ሁኔታ የማስረዳበት ቋንቋ የለኝም። የጊዜ ጉዳይ ደግሞ በጣም አጣዳፊ ሲሆን ስለምታደርገው ከትትልና ውጤት በቀን በቀን ለኔ ሪፖርት ታደርጋለህ።" ይህንን ተናገረና ጄነራሉ አንድ አነስተኛ ማስታወሻ ወረቀት ላይ የስልክ ቁጥር ጫር...ጫር አድርጉ ለኮማንደር ሮበርት ቤላሚ እያቀበለው "በዚህ ቁጥር ቀንም ሆነ ሌሊት ልታገኘኝ ትችላለህ። ወደ ዙሪክ የምትበርበት አውሮፕላን ተዘጋጅቶ የሚጠብቅህ ሲሆን ከዚህ እንደወጣህ ወደ መኖሪያ አፓርትመንትህ ታጅበህ ትሄድና የምትፈልጋቸውን ዕቃዎችና አልባሳት በሻንጣህ ሸክፈህ ወደ አየር ማረፊያ ትወሰዳለህ።"

ሮበርትም በሐሳቡ 'እኔ ወደ ተልዕኮዬ ከተሰማራሁ በኋላ ወርቃማ ዓሣዎቼን ማን ይመግብልኛል?' ብሎ ለመጠየቅ ፈለገና ተወው። መልሱ "ወርቃማ ዓሣዎች የሉህም" እንደሚሆን ያውቀዋልና።

"በባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤት (ኦፊስ ኦፍ ናቫል ኢንተሊጀንስ) ውስጥ በሠራህበት ዘመን በስለላው ዓለም በርካታ ወዳጆች እንዳፈራህ አምናለሁ" አለ ጄነራሉ።

"አዎን ጌታዬ! ሊረዱኝ የሚችሉ ጥቂት ሰዎች....."

"ከአንዳቸውም ጋር ዕርዳታ ለመፈለግ ግንኙነት አታደርግም!" አለ ጄነራሉ አቋረጠውና። "ከማናቸውም ጋር እንድትገናኝ አይፈቀድልህም።"

@BOOKALEM

“የምትፈልጋቸው ወይም የምትከተላቸው ምስክሮች መቼም የልዩ ልዩ አገሮች ዜጐች መሆናቸው አያጠራጥርም” አለና ፊቱን ዘወር አድርጎ “ሐሪሰን.....” ሲል ተጣራ።

ሐሪሰን ኬለር ወዲያው ከመቀመጫው ዘሎ ወደ ሰነድ ማስቀመጫው ቁም ሳጥን ሄደና መሳቢያውን ስቦ ከፈተው። ከውስጡም አንድ ትልቅ ኤንቬሎፕ አውጥቶ ለሮበርት እየሰጠው “በዚህ ኤንቬሎፕ ውስጥ ሃምሳ ሺህ ዶላር ዋጋ ያላቸው የተለያዩ የአውሮፓ አገሮችን የገንዘብ ምንዛሪዎች እንዲሁም ሌላ ሃያ ሺህ የአሜሪካን ዶላር በጥሬው ታገኛለህ። ከገንዘቡም በተጨማሪ ሌሎች በርካታ የተለያዩ የሐሰት መታወቂያዎችን ታገኛለህ” ሲል አስረዳው።

ጄነራል ሒሊያርድ ደግሞ አንድ ነጭ መስመር ያለበት ጥቁር አንፀባራቂ የፕላስቲክ ካርድ አውጥቶ ለሮበርት እየሰጠው “ይህ ደግሞ የዱቤ መሸመቻ (ክሬዲይት ካርድ) ሲሆን እሱም.....”

ሮበርት የጄነራሉን ገለጻ አቋረጠና...“አስፈላጊነቱ ያጠራጥረኛል ጄነራል። ጥሬ ገንዘቡ በቂ ከመሆኑም በላይ የባሕር ኃይል መረጃ ጽሕፈት ቤት የዱቤ መሸመቻ ካርድ አለኝ” አለው።

“ተቀበለኝ! ውሰድ!” አለ ጄነራሉ።

“በጣም ጥሩ!” ሮበርት ካርዱን ከጄነራሉ እጅ ተቀበለውና በትኩረት አጠናው። ከዚህ በፊት ስሙን ሰምቶት በማያውቀው ባንክ ስም የተዘጋጀ ካርድ ነው። የካርዱ ጠርዝ ላይ የስልክ ቁጥር ተጽፎበታል። “በካርዱ ላይ ምንም ስም አልተጻፈበትም” አለ ሮበርት።

“ካርዱ የባንክ ቼክ ያህል ዋጋ አለው” አለ ጄነራሉ። “በካርዱ ለመጠቀም መታወቂያ ማሳየት አያስፈልግህም። የምትሸምትበት ሱቅ በካርዱ ላይ የተጠቀሰውን ስልክ ቁጥር ደውሎ እንዲያረጋግጥ ማድረግ ብቻ ነው ያለብህ። ከዚህ ባሻገር በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሁሉ ካርዱን ካንተ ሳትለይ ይዘህ መገኘት አለብህ!” ሲል አስጠነቀቀው።

“እሺ ጌታዬ።”

“እና ኮማንደር?”

“አቤት ጌታዬ?”

“እነዚህን ምስክሮች ፈልገህ ማግኘት አለብህ። እያንዳንዳቸውን። ግዳጅህን መጀመርህን ለዳይሬክተሩ አሳውቃቸዋለሁ” ሲል ጄነራል ሒሊያርድ ማብራሪያውን ፈፀመ።

ሐሪሰን ኬለር ሮበርትን ከጄነራሉ ቢሮ እየመራ ይዞት ሲወጣ ከውጭ ኮሪደሩ ውስጥ አንድ የባሕር ኃይል መኮንን ተቀምጦ እየጠበቃቸው ነበር። ሁለቱ ሰዎች ብቅ ሲሉ የባሕር ኃይሉ ባልደረባ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ተቀበላቸው። “ይህ ሻምበል ዱገርቲ ይባላል። እሱም ወደ አየር ማረፊያ አድርሀህ ይሄዳል።

@BOOKALEM

እንግዲህ መልካም ዕድል ይግጠምህ!" ሲል ኬለር ተሰናበተው። ሮበርትና ኬለር እጅ ለእጅ ተጨባብጠው ሲያበቁ ኬለር ወደ ጄነራሉ ቢሮ ተመልሶ ገባ።

"ዝግጁ ነህ ኮማንደር?" ሲል ሻምበል ዱገርቲ ጠየቀ።

"አዎን ዝግጁ ነኝ!" አለ ሮበርት። በሐሳቡ ደግሞ 'ዝግጁ ለምን?' ሲል ራሱን ጠየቀ። ባለፉት ዓመታት እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ የመረጃ ሥራ ተልዕኮዎችን ተወጥቷል። ነገርግን አንዱም ተልዕኮው እንደዚህ የተቃወሰና አስቸጋሪ የሆነ የለም። ቁጥራቸው፤ ማንነታቸው፤ ዜግነታቸውና የሚኖሩበት አገር ያልታወቀ የዐይን ምስክሮችን ፈልጎ የማግኘት ተልዕኮ ተሰጥቶታል። ከግዳጁ ፀባይ ዐይነት ሲመለከተው የሚገጥመው ዕድል ወይም ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል በእጅጉ አስገራሚ ሆነበት።

ሻምበል ዱገርቲ ከተመሰጠበት ሐሳብ እንዲህ በማለት አነቃው። "ከዚህ በቀጥታ ወደ መኖሪያ አፓርትመንትህ ከዚያም እንድሪውስ የአየር ኃይል ጣቢያ ላይ ወደሚጠብቅህ አውሮፕላን እንድወስድህ ታዝዣለሁ።"

ሮበርት በእምቢታ ራሱን ነቀነቀና "መጀመሪያ ቢሮዬ መድረስ አለብኝ" አለው።

ዱገርቲ ጥቂት ካቅማማ በኋላ "በጣም ጥሩ! ወደ ቢሮህ አብረን እንሄዳለን" አለ።

ሮበርት በጣም ተገረመ። ከዕይታቸው ቢሰወር ፈጽሞ የማያምኑት መስሎ ታየው። ግን ለምን? አንድ ባሉን መከስከሱን ስለተረዳ? ፈጽሞ ስሜት የማይሰጥ ጉዳይ ሆነበት። ከእንግዳ መቀበያ ባንኮኒው ሲደርስ ከፀሐፊው የእጅ ሻንጣውን ተቀብሎ በሻምበሉ ታጅቦ ከአዳራሹ ሲወጣ የሚያንዘፈዝፈው ብርድ ተቀበለው። የግል መኪናው ደግሞ ከቆመበት ቦታ ላይ ተወስዳ በምትኩ አንድ ማራኪ ሸንጠረዥም አውቶሞቢል (ሊሙዚን) ቆሞ አገኘ።

"እንተ እስክትመለስ ለመኪናህ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እናደርግላታለን። እኛ በዚህኛው እንሄዳለን" አለ ሻምበል ዱገርቲ።

ሮበርት ነገሩ ሁሉ የሚረብሽ ሆነበት።

ወደ ባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤት በአውቶሞቢል መንገዳቸውን ቀጠሉ። ደካማዋ ፀሓይ ዝናብ ባዘሉ ጥቋቁር ደመናዎች ውስጥ እየጠለቀች ነው። 'በብዙ መልኩ ይህ የዛሬው ቀን አስከፊ ሊሆን ነው!' ሲል ሮበርት በሐሳቡ ደመደመ።

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሦስት

ኦታዋ ካናዳ 2400 ሰዓት

የምሥጢር (ኮድ) መጠሪያው ጃኑስ ይባላል። በከፍተኛ ደረጃ የተጠናከረ የፀጥታ ጥበቃ በሚደረግለት አንድ ወታደራዊ ጦር ሰፈር በሚገኝ አዳራሽ ውስጥ ለተሰበሰቡ አሥራ ሁለት ሰዎች ማብራሪያ እየሰጠ ነው።

"ሁላችሁም እንደተነገራችሁ ""የፍርድ ቀን ዘመቻ"" ተጀምሯል! በከፍተኛ ፍጥነትና በጥብቅ ምሥጢር ተፈልገው መገኘት ያለባቸው የዐይን ምስክሮች አሉ። ሊደርስ በሚችል የምሥጢር መባከን ምክንያት በተለመደው የስለላ መዋቅር ለመጠቀም አልተቻለም።"

"ለመሆኑ ለዚህ ሥራ የምንጠቀምበት ሰው ማነው?" ግዙፍና ትዕግስት የለሽ የሆነ ሩሲያዊ።

"ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ይባላል።"

"ኮማንደሩ የተመረጠው እንዴት ነው?" ጨካኝና የገዢነት ሥልጣን የሚታይበት ጀርመናዊ።

"ኮማንደሩ የተመረጠው የሲ.አይ.ኤ. የኤፍ.ቢ.አይ እና የሌሎችም ከግማሽ ደርዘን በላይ የሚሆኑ የስለላና የመረጃ ድርጅቶች የኮምፒውተር ፋይል ፍተሻ ከተደረገበት በኋላ ብቃቱ ስለታመነበት ነው።"

"እባክዎን የሰውየው ብቃትና ችሎታ ምን እንደሆነ ለመጠየቅ እችላለሁን?" ትሁትና ምሥጢራዊ የሆነው ጃፓናዊ።

"ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ በመስክ ሥራ ከፍተኛ የሆነ ልምድ ያለውና ስድስት የተለያዩ ቋንቋዎችን አጣርቶ እንደ ተወላጆቹ ለመናገር ከመቻሉም በላይ መረጃን ፈልፍሎ የማውጣት ብቁነቱን በተደጋጋሚ ያስመሰከረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በሕይወት የሚገኝ ምንም የሥጋ ዘመድ የለውም።"

"የጉዳዩን አስቸኳይነትስ ተገንዝቧል?" አደገኛውና ንቀት የሚታይበት እንግሊዛዊ።

"አዎን! ሁሉንም ምስክሮች በአስቸኳይ አድኖ የማግኘቱን ጉዳይ ተረድቶታል። ይጠበቅበታልም።"

"የተልዕኮውን ተግባርስ ተረድቷል?" ጨቅጫቃና ደረቅ ፈረንሳዊ።

"የለም አልተረዳም።"

"ምስክሮቹን ፈልጎ ካገኛቸው በኋላስ?" ትዕግስተኛና ቀልጣፋው ቻይናዊ።

"ጣፋጭ የሆነ ሽልማት ይሸለማል!" ሲል ጃኑስ ጥያቄና መልሱን ደመደመ።

@BOOKALEM

ምዕራፍ አራት

የባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤት ጠቅላይ መምሪያ በዓለም ትልቁ የሚባለውን የአሜሪካ መከላከያ ሚንስትር ሕንፃ "ፔንታጎን" አምስተኛውን ፎቅ አጠቃሎ የያዘ ነው። ፔንታጎን በአጠቃላይ ሕንፃው ውስጥ የሚገኘው ኮሪደር ቢቀጣጠል አሥራ ሰባት ማይልስ ያህል ርዝመት ሲኖረው ሃያ ዘጠኝ ሺህ ሠራተኞችን የያዘ በዓለም ላይ ትልቁ ተብሎ የሚገመት የጦር መሥሪያ ቤት ነው።

ፔንታጎን አምሥተኛው ፎቅ ላይ የሚገኘው የባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤት ውስጣዊ አደረጃጀት የባሕሩን ባሕርይ የሚያንፀባርቅ ይመስላል። ጠረጴዛዎችና የሰነድ መያዣ ቁም ሳጥኖች በሁለተኛው ዓለም ጦርነት የነበረውን የጦሩን ተሸከርካሪዎች ወይራማ አረንጓዴ ቀለም ወይም በቬትናም ጦርነት ወቅት የጦር መርከቦቹ ተቀብተውት የነበረውን ግራጫማ ቀለም የተቀቡ ሲሆን ግድግዳዎቹና ኮርኒሶቹ ደግሞ ነጣ ያለ ቢጫ ቀለም የተቀቡ ናቸው። ይህን ቀለም ሮበርት ባይወደውም ከተላመደው ሰንብቷል።

ሮበርት ሕንፃው ውስጥ ገብቶ ወደ እንግዳ መቀበያው ዴስክ ሲቀርብ ሁሌም የሚገኘው የተለመደው ዘብ "እንደምን አደርክ ኮማንደር! እባክህ የይለፍ ፈቃድህን ብታሳየኝ?" አለው።

ሮበርት እዚህ ቦታ ለሰባት ዓመታት ሲሠራ በቀን በቀን የይለፍ ፈቃዱን እያሳየ ነው ቢሮው የሚገባው። ደንቡ አይለወጥም። ፈቃዱን አወጣና ለዘቡ አሳየው። ዘቡም ይለፉን አየና "አመሰግናለሁ ኮማንደር" አለ።

ሮበርት ወደ ቢሮው በማምራት ላይ እያለ በወንዙ በኩል ባለው መግቢያ ላይ በሚገኘው የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ ሆኖ ወደ ስዊዘርላንድ የሚበርበት አውሮፕላን ድረስ ሊያድበው የሚጠብቀውን ሻምበል ዱገርቲንን አስታወሰ። ወደማይቻለው ግዳጁ የሚሸኘውን። ሮበርት ቢሮው ሲገባ ጸሓፊው ባርባራ ቀድማው በሥራ ገበታዋ ላይ ተገኝታ ነበር።

"እንደምን አደርክ ኮማንደር ተጠባባቂ ዳይሬክተሩ በጽሕፈት ቤታቸው ሊያዩህ ይፈልጋሉ" አለችው።

"ሊጠብቅ ይችላል! በመጀመሪያ ከአድሚራል ዊታከር ጋር በስልክ አገናኝኝ።"

"እሺ ጌታዬ።"

ከአንድ ደቂቃ በኋላ ሮበርት ከአድሚራሉ ጋር እየተነጋገረ ነበር።

"ሮበርት ስብሰባውን እንደጨረስክ እገምታለሁ።"

"አዎን ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ጨረስኩ።"

@BOOKALEM

“አካሄዱ እንዴት ነበር?”

“የ.....የሚማርከ ነበር። ቁርስ አብረውኝ ሊመገቡ ይችላሉ አድሚራል?”

“አዎን እችላለሁ። እዚያው እንገናኝ” አሉ አድሚራሉ። ያለማመንታት።

“መልካም። የይለፍ ወረቀት እተውልዎታለሁ” አለ ሮበርት።

“በጣም ጥሩ ከአንድ ሰዓት በኋላ አገኝሃለሁ።”

ሮበርት ስልኩን ዘጋው። ለአንድ አድሚራል የይለፍ ፈቃድ ሲሰጥ አይገርምም? ከጥቂት ዓመታት በፊት አድሚራሉ እዚህ ቦታ የባሕር ኃይሉ መረጃ ጽሕፈት ቤት ኋላፊ ነበሩ። ‘አሁን ከሥልጣን በመውረዳቸው ምን ይሰማቸው ይሆን?“ ሲል አሰበ።

ሮበርት ከጸሓፊው ጋር የሚገናኝበትን የውስጥ መስመር (ኢንተርኮም) ተጫነው።

“አቤት ኮማንደር?”

“አድሚራል ዊታከርን ስለምጠብቅ የይለፍ ፈቃድ አዘጋጂላቸው።”

“አሁኑኑ አዘጋጃለሁ።”

አሁን ደግሞ የባሕር ኃይል መረጃ ጽሕፈት ቤት ተጠባባቂ ዳይሬክተር የሆነው ደስቲን ቶርንቶን ዘንድ ሪፖርት ማድረጊያ ሰዓት ነው።

ምዕራፍ አምስት

የባሕር ኃይል መረጃ ጽሕፈት ቤት ተጠባባቂ ዳይሬክተር የሆነው ደስቲን ቶርንቶን ወደ ዝነኛነቱ ደረጃ ሊወጣ የቻለው አናፓሊስ ያፈራችው ታላቅ አትሌት በመሆኑ ነው። በእግር ኳስ (አሜሪካን ፉት ቦል) በትከከል ለመናገር ደግሞ በባሕር ኃይልና በጦር ሰራዊት ቡድን መካከል በተደረገው ግጥሚያ ምክንያት ነው። አንድ ግዙፍ ማማ የሚያክለው ቶሮንቶን ለባሕር ኃይሉ ቡድን በግጥሚያ ላይ እጅግ ወሳኝ የሆነ ሚና ነበር የተጫወተው። በአራተኛው ሩብ የጨዋታው ጅማሬ ላይ የጦር ኃይሉ ቡድን ባሕር ኃይሉን አሥራ ሦስት ለሁለት በሆነ ነጥብና ሁለት ጊዜ የባሕር ኃይሉን የግብ ክልል በመንካትና በአንድ ለውጥ እየመራ ነበር። በዚህ ወቅት እዚህ ጨዋታ ላይ መልካም ዕጣ ጣልቃ ገባችና የደስቲን ቶርንቶንን ሕይወት ለወጠችለት።

ቶርንቶን የጦሩ ቡድን የሚቀባበላትን ኳስ ጣልቃ ገብቶ በመቀማት በቁጥጥሩ ስር አዋለ። ኳሷን እንደያዘ ዙሪያውን ከተጠማዘዘ በኋላ የተቀናቃኙን የግብ ክልል በኳስ ለመንካት በተከላካዮች ውስጥ ተወረወረ። ባሕር ኃይሉ በተጨማሪው ነጥብ ላይ ሌላ ነጥብ ቢያጣም አንድ የመስክ ጎል (ግብ)

@BOOKALEM

ለማስመዘገብ ቻለ። ኳስ ከተሊጋች በኋላ የጦሩ ቡድን መሬት ለማስነካት አልቻለም።

ወደ ባሕር ኃይሉ ግብ ኳስ ተጠለዘች። ሰዓቱ እየከነፈ ነው። ነጥብ አሥራ ሦስት ለዘጠኝ ሆነ። ጨዋታው ሲቀጥል ኳስ ለቶሮንቶን ደረሰችው። ቶርንቶን ኳሷን እንደያዛት በቅጽበት የጦሩ ተከላካይ ተጫዋቾች እንደቋጥኝ ተከመሩበት። ከወደቀበት ለመነሳት የወሰደበት ጊዜ አያሌ በመሆኑ የቡድኑ ሐኪም ለዕርዳታ እየሮጠ መጣለት። በዚህ ጊዜ ደስቲን በቁጣ በእጅ ምልክት ሐኪሙን ወይድልኝ ብሎ አባረረው።

ጨዋታው ሊፈፀም ጥቂት ሴኮንዶች ሲቀሩት ቶሮንቶን የተወረወረችለትን ኳሷ ቀለባትና ወደ ጠላቱ ግብ እንደ አንበሳ ተወረወረ። በዚህ ወቅት ማንም ሊያቆመው የቻለ አልተገኘም። ከፊቱ የተጋረጡትን ዕድለ ቢስ ተከላካዮች ሁሉ እንደ ታንክ እየጠራረገ መሬት ለማስነካት የግቡን መስመር አቋርጦ ሸመጠጠ። በአራት ዓመታት ውስጥ የባሕር ኃይሉ ቡድን ለመጀመሪያ ጊዜ ሻምፒዮን ሆነ።

በቶርንቶን ሕይወት ውስጥ ይህ ዕለት መልካም አጋጣሚ ሊሆን የቻለው በከብር እንግዳው ሥፍራ ላይ ዊላርድ ስተንና ሴት ልጁ ኤሊኖር ስተን በመገኘታቸው ነበር።

በስቴዲየሙ ሙሉ የታጨቀው ሕዝብ በተጋጋለ ስሜት ከመቀመጫው ተነስቶ ለቶርንቶን በከፍተኛ ጭብጨባና ጩኸት አድናቆቱን ሲገልጽለት ኤሊኖር ወደ አባቷ ዘወር አለችና በለሆሳስ ድምጽ "ይህን ሰው ላገኘው እሻለሁ!" አለችው።

ኤሊኖር ስተን ፍላጐተ ሰፊና ስሜቷ በቀላሉ የማይረካ ሴት ናት። ቅባትና ሰው ሠራሽ ጌጣጌጥ ያላበላሸው ማራኪ ውብ ገጽታ፤ ፈጽሞ የማይረካ አካላዊ ስሜት ያላት ወጣት ሴት ናት። ቶሮንቶን በግዙፍ ሰውነቱ ኳስ ሜዳውንና ኳስ ተጫዋቾቹን እንደእርሻ በሬ እያረሳቸው ሲሄድ 'ይህ ሰው አልጋ ውስጥ ሲገባ ምን ይመስል ይሆን?' ስትል በሐሳቧ ምራቋን ዋጠች። 'እንደ ሰውነቱ እንትኑም ትልቅ ከሆነ።'"

ከስድስት ወራት በኋላ ኤሊኖር ስተንና ደስቲን ቶርንቶን በሰማንያ ተፈጣጠሙ። ጅማሪው ይህ ነበር። ደስቲን ከዚህ በፊት በገሃድ አለ ብሎ በማይገምተው ዓለም ውስጥ ገብቶ ለአማቱ ይሠራ ጀመር።

የቶርንቶን አማት ዊላርድ ስተን ፍጹም እንቆቅልሽ የሆነ ሰው ነበር። በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከኃያል የፖለቲካ ባለሥልጣናት ጉድኝት ጋር አለው። ስላለፈው ሕይወቱ ምንም የማይታወቅና በዓለም ላይ ከደርዘን በላይ በሚሆኑ አገሮች ውስጥ ድሩን ያደራ ሰው ነው።

ዕድሜው ከሰልሳ አምስት በላይ ሲሆነው በጣም ዘዴኛ፤ እያንዳንዱ እንቅስቃሴውና እርምጃው በዘዴ የተቀነባበረች እንከን የለሽ የሆነ ሰው ነው።

@BOOKALEM

ገጽታው እንደ ምላጭ የሰላ፤ ዐይኖቹ ውስጣዊ ስሜቱን የማያስነብቡ፤ የሚናገራቸውን ቃላትና ሰብአዊ ስሜቱን የማያባክን ሰው ከመሆኑም በላይ ለማግኘት የከጀለውን ነገር በእጁ ለማስገባት በሚወስደው እርምጃ ከቶም ቢሆን ርሕራሄ የለሽ የሆነ ሰው ነበር።

ስለርሱ የሚነገሩት ሹክሹክታዎች ሁሉ የሚያስገርሙ ነበሩ። በማሌዢያ ውስጥ የንግድ ተፎካካሪውን እንዳስገደለ ይወራበታል። እንዲሁም የአንድ ኤሚር ሚስት ያማግጥ እንደነበርም ይነገራል። ከዚህም በላይ በናይጄሪያ ድል ለመምታት የበቃ አብዮት በገንዘብ እንደደገፈና በኋላም መንግሥት በርካታ ክሶችን ቢመሰርትበትም በረቀቀ ምሥጢራዊ ዘዴና ተንኮል የተመሰረተበትን ክስ ውድቅ ለማድረግ እንደ ቻለም የሚተረከለት ጉዳይ አለ።

ዊላርድ ስተን መደለያ በመስጠት እንደራሴዎችን በጉቦና በምልጃ የማሳሳት ተግባር በመፈፀም የሚታማ ሰው ሲሆን የፕሬዚደንቶችና የነገሥታት አማካሪ ለመሆንና ጆሮአቸውን ለማግኘት የበቃ ሰው ሆኗል። በአጠቃላይ ዊላርድ ስተን ኃያል ሰው ነው። ከዊላርድ ስተን ንብረት ውስጥ በኮሎራዶ ተራሮች መኻል የሚገኝ ብቸኛ የሆነ በየዓመቱ ሳይንቲስቶች፤ የኢንዱስትሪ ባለቤቶች እንዲሁም መራሔ መንግሥታት ለስብሰባና ለሴሚናር የሚገኙበት በታጠቁ ዘቦች በጥብቅ የሚጠበቅ ሰፊ ርስት አለው።

ዊላርድ ስተን የልጁን ጋብቻ ማጽደቅ ብቻ ሳይሆን እንዳውም ይገፋፋትና ያደፋፍራትም ነበር። የልጁ ባል ብሩህ አዕምሮ የታደለ፤ እንደፈለጉ የሚጠመዝዙትና የሚመሩት ከመሆኑም በላይ በምኞትና በተስፋ የተሞላ ሰው ነው።

ከጋብቻቸው አሥራ ሁለት ዓመታት በኋላ ዊላርድ ስተን ለልጁ ባል ለቶርንቶን አስፈላጊ ሁኔታዎችን አመቻችለትና በደቡብ ኮሪያ አምባሳደር ሆኖ እንዲሾም አደረገው። ከበርካታ ዓመታት በኋላ ፕሬዚደንቱ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አምባሳደር አድርገው ሾሙት። በመጨረሻም አድሚራል ዊታከር ከሥልጣናቸው በመነሳታቸው የባሕር ኃይል መረጃ ጽሕፈት ቤት ተጠባባቂ ዳይሬክተር ተብሎ ተሰየመ።

ቶርንቶን የተሾመ ዕለት ዊላርድ ስተን አስጠራውና እንዲህ አለው። “ይህ ገና ጅማሬው ነው። ስላንተ የወደፊት ዕጣ ትልቅ በጣም ትልቅ የሆነ ዕቅድ አቅጀልሃለሁ!” ብሎ ቃል ገባለት። የገባውንም ቃል ተራ በተራ ተግባራዊ ማድረግ ቀጠለ።

ከሁለት ዓመታት በፊት ሮበርት ከባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤት ተጠባባቂ ዳይሬክተር ጋር በተገናኘበት ጊዜ ደስቲን ሻካራ የሆነ አቀባበል ነበር ያደረገለት።

@BOOKALEM

"ተቀመጥ ሮበርት። ከግል ማሕደርህ እንረዳሁት አንድ የሆነ ጥሩ ነገር ነህ!" አለው።

'ምን ማለቱ ነው?' ሲል ሮበርት ተገረመና አፉን ዘግቶ መቀመጡን መረጠ።

ቶሮንቶን ቀና ብሎ ሮበርትን ከተመለከተ በኋላ "አድሚራል ዊታከር ኋላፊ በነበረበት ጊዜ ይህንን ጽሕፈት ቤት እንዴት ይመራው እንደነበር አይገባኝም። ካሁን በኋላ ግን ማንኛውንም ሥራ የምናከናውነው ደምቡ በሚያዘው መሠረት ይሆናል። ትእዛዜ ሁሉ እንዲከበር እፈልጋለሁ። ግልጽ ነው?"

'የከርስቶስ ያለህ እዚህ የተቀመጥነው ለምንድነው?' አለ ሮበርት በሐሳቡ። "ንግግሬ ግልጽ ነው ኮማንደር?"

"አዎን ግልጽ ነው" ሲል መልሰ ሰጠ። 'ሰላምታ መስጠት ይኖርብኝ ይሆን?' አለ በሐሳቡ።

ነገር ግን ይህ ብቻ አልነበረም። ከአንድ ወር በኋላ ሮበርት አንድ አገሩን ለመከዳት የሚፈልግ ሳይንቲስት ለማስኮብለል ወደ ምሥራቅ ጀርመን ተሳከ።

"ስታሲ" በመባል የሚታወቀው የምሥራቅ ጀርመን ማዕከላዊ የደሕንነት ፖሊስ የታቀደውን የኩብለላ ሴራ ቀደም ብሎ ስለደረሰበትና ሳይንቲስቱን በቅርብ ይከታተለው ስለነበር የሮበርት ግዳጅ አደገኛ የሆነ ገጽታ ነበረው።

ነገር ግን የቱን ያህል ግዳጁ አደጋ የሰፈነበት ቢሆንም ሮበርት ሳይንቲስቱን ድንበር አሻግሮ አንድ አስተማማኝ የሆነ ቤት ውስጥ ሊያሳርፈው ቻለ። ከዚህም በመቀጠል ሊቁን ወደ ዋሺንግተን ለማሻገር አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ሳለ ከደስቲን ቶሮንቶን ሁኔታው መለወጡንና ሳይንቲስቱን ባለበት ቦታ ትቶት ወደ ዋሺንግተን እንዲመለስ የሚል ትዕዛዝ ደረሰው። ሮበርትም "ፊጽሞ እዚህ ልንተወው አንችልም። ከዚህ በኋላ በምሥራቅ ጀርመን የመረጃ ሰዎች እጅ ተመልሶ ከገባ ያለጥርጥር ይገድሉታል" ሲል ተቃውሞውን ሰነዘረ።

"የተሰጠህ ትዕዛዝ በቀጥታ ወደ አገርህ እንድትመለስ ነበር!" ሲል ደስቲን በጥብቅ አዘዘው።

ሮበርት የመጨረሻውን ትዕዛዝ ከሰማ በኋላ 'እኔ ደግሞ በፍጹም አልተወውም' ብሎ ወሰነና የእንግሊዝ የመረጃ ድርጅት (ኤምአይ.ሲክስ) ባልደረባ ለሆነ አንድ ወዳጁ ስልክ ደውሎ ሁኔታውን ሁሉ አብራራለት።

"አየህ! ወደ ምሥራቅ ጀርመን ተመልሶ ከሄደ እንደአሳማ አፍነው ነው የሚገድሉት። አናንተ ለምን አትወስዱትም?" ሲል ሮበርት ጠየቀው።

"ሊሆን የሚችለውን ጉዳይ እናያለን። ለማንኛውም ሰውዬውን አምጣው!" አለ እንግሊዛዊው ሰላይ።

በመጨረሻም ሳይንቲስቱ በእንግሊዝ አገር ገነታዊ አቀባበል ተደረገለት።

@BOOKALEM

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ደስቲን ትእዛዙ ባለመከበሩ ሮበርትን ነክሶ ያዘው። በሁለቱ ሰዎች መካከል ግልጽ የሆነ ጥላቻ ተመሠረተ። ቶሮንቶን ስለሁኔታው ከአማቱ ጋር ተነጋገረበት።

"እየህ?" አለ ዊላርድ ስተን። "የሮበርት ዐይነት መረን የተለቀቁ የመድፍ አረሮች እጅግ አደገኞች ናቸው። የፀጥታ መዛባትም ምክንያት ናቸው። የዚህ ዐይነት ሰዎች እስከ መጨረሻው "መወገድ" አለባቸው!" ሲል አስጠነቀቀው። ቶርቶንም የአማቱን ምክር ከማስታወስ አልተቆጠበም።

ሮበርት ደስቲንን ለማነጋገር ወደ ቢሮው በሚያመራበት ወቅት በአድሚራል ዊታከርና በደስቲን መካከል ስላለው ልዩነት ከማሰብ ሊቆጠብ አልቻለም።

በስለላው ዓለም ውስጥ ሰው ማመን ማለት በራስ ላይ የሞት ፍርድ አሳልፎ መስጠት ነውና ደስቲንን ከቶም ቢሆን አያምነውም።

ሮበርት ቢሮው ሲገባ ደስቲን ከጽሕፈት ጠረጴዛው ኋላ ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ነበር።

"ሊያነጋግሩኝ ፈልገው ነበር?"

"አዎን! ተቀመጥ ኮማንደር" አለው። ግንኙነታቸው ሻካራ ስለሆነ "ሮበርት" ብሎ በስሙ አይጠራውም።

"ወደ ብሔራዊ የፀጥታ ወኪል በጊዜያዊነት እንደምትዛወር ተነግሮኛል። በምትመለስበት ወቅት አንድ....."

"አልመለስም! ይህ የመጨረሻው ተልዕኮዬ ይሆናል።"

"ምን አልከ?"

"ሥራውንም አልፈልግም!"

ነገሩ ካለፈ በኋላ ሮበርት ሁኔታውን መለስ ብሎ ሲገመግመው በወቅቱ ደስቲን ምን ዐይነት ስሜት አድሮበት እንደነበረ ለመገመት አልቻለም። አልተቆጣም አልተደናገጠም። ትኩር ብሎ ተመለከተውና "ውሳኔህ ይኸው ነው። አይደለም?" ብቻ ነበር ያለው።

ሮበርት ወደ ቢሮው እንደተመለሰ ፀሐፊው ባርባራን "ርቄ መሔዴ ስለሆነ ከአንድ ሰዓት በኋላ እወጣለሁ" አላት።

"ልትገኝ የምትችልበት አድራሻ ይኖራል?"

የጄነራል ሒሊያርድን ትዕዛዝ አስታወሰና....."የለም። ምንም አድራሻ አይኖረኝም" አላት።

"የምትሳትፍባቸው አንዳንድ ስብሰባዎች....."

"በሙሉ ሰርዣቸው" አለና የእጅ ሰዓቱን ተመለከተ። አድሚራል ዊታከርን የሚገናኝበት ሰዓት ደርሷል።

@BOOKALEM

ሮበርትና አድሚራሉ ቁርሳቸውን "ባዶ ምድር" የሚል መጠሪያ በተሰጠውና በፔንታጐን ማዕከላዊ ሥፍራ በሚገኝ ቡና ቤት ተመገቡ። ምግብ ቤቱ ይህንን መጠሪያ ሊጎናጸፍ የቻለው ፔንታገን የመጀመሪያው ፀረ ዩናይትድ ስቴትስ የኒውክሊየር ጥቃት የሚያርፍበት ቦታ ነው ተብሎ ስለሚገመት ነው። ሮበርትም ከሰሚ ጆሮ ራቅ ብለው በምሥጢር ለመወያየት እንዲችሉ ገለልተኛ የሆነ ቦታ አስቀድሞ አስይዞ ነበር።

አድሚራሉ ልክ በቀጠሮው ሰዓት ነበር የደረሰው። አድሚራሉ ከሥልጣኑ በግማሽ ጡረታ መልክ መገለሉ በአካሉ የመሚሸሸና የመሸምገል ጥላ ጥሎበታል። ከዓመታት በፊት ማራኪ ገጽታ፤ ጠንካራ ቁመትና ብርማ ጸጉር ነበረው። ሮበርት የአድሚራሉ ጭፍራ በመሆን በአንድ ወቅት ቬትናም ቀጥሎም በባሕር ኃይል የመረጃ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ሠርቷል። አድሚራሉን ልክ እንደወላጅ አባቱ ነበር የሚመለከተው። አድሚራል ዊታከርም ለሮበርት ምትክ አባቱ ነው።

"እንደምን አደርክ ሮበርት። ወደ ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ድርጅት አዛወሩህ እንዴ?" አለ አድሚራሉ ወንበር ስቦ እየተቀመጠ።

ሮበርት ራሱን በአዎንታ እየነቀነቀ "በጊዜያዊነት አዛውረውኛል" ሲል መልስ ሰጠ።

የቡና ቤቱ አስተናጋጅ ትዕዛዝ ለመቀበል አጠገባቸው መጥታ ቆመች። አድሚራል ዊታከር የምግብ ዝርዝሩን እየተመለከተ "እዚህ ቦታ ምግባቸው ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ ዘንግቼዋለሁ" አለና ዙሪያ ገባውን በፈገግታ መቃኘት ጀመረ።

'እዚህ ቦታ እንደገና ለመመደብ (ለመመለስ) በጣም ይመኛል። ምነው በቀናው!' ሲል ሮበርት በልቡ ተመኘ።

ምግባቸውን ካዘዙና አስተናጋጇ ርቃ ከሄደች በኋላ ሮበርት ውይይቱን ጀመረ። "አንድ የአየር ንብረት መመርመሪያ ባሉን ሲከሰከስ የተመለከቱ የዐይን ምስክሮችን እንዳድን የሦስት ሺህ ማይልስ ርቀት ጉዞ የሚሸፍን ተልዕኮ ሒሊያርድ ሰጥቶኛል። ስለዚህ ጉዳይ አንድ በጣም እንግዳ የሆነብኝ ነገር አለ። የጊዜ ጉዳይ በጣም አስፈላጊ (አስቸኳይ) ነው ብሎኛል ጄነራሉ። ሆኖም ግን በውጭ አገር የሚገኙ በስለላው ዓለም ውስጥ የማውቃቸውን ባልንጀሮቼን ዕርዳታ ፍለጋ እንዳልገናኛቸው ታግጃለሁ" አለው።

አድሚራሉ ሮበርትን ግራ በመጋባት ተመለከተውና..... "ምናልባት ጄነራል ሒሊያርድ የራሱ የሆነ ምክንያት ሊኖረው ይችላል" አለው።

አድሚራል ዊታከር ሮበርትን በጥሞና ያጠናው ጀመር። ኮማንደር ቤላሚ በእርሱ ስር ሆኖ ቬትናም ውስጥ ከማገልገሉም በላይ ቤላሚ በስኳድሮኑ ውስጥ አሉ ከተባሉት ምርጥ ተዋጊ ፓይለቶች አንዱ ነበር።

@BOOKALEM

የአድሚራሉ ልጅ ኤድዋርድ ደግሞ ሮበርት በሚያበረው የጦር አውሮፕላን ላይ ቦንበኛ (ቦንብ ጣይ) በመሆን ተመድቦ ነበር።

በዛች በመጨረሻዋ አሳዛኝ ዕለት የሮበርት አውሮፕላን ተመትቶ ሲወድቅ ኤድዋርድ በአደጋው ተገደለ። ሮበርትም ከአደጋው በሞትና በሕይወት መኻል ተርፎ ሆስፒታል በተኛበት ወቅት አድሚራሉ ሊጎበኘው መጥቶ ነበር። ዶክተሮቹ ሮበርት በፍጹም እንደማይድን ተነበዩ። ሮበርት ደግሞ ሕሊና በሚያስተው ሕመሙ እየተሰቃየ "ስለ ኤድዋርድ አዝናለሁ! በጣም አዝናለሁ!" ሲል እየቃተተ ተናገረ።

አድሚራሉም የሮበርትን እጅ ጠበቅ አድርጐ ያዘና "አይዞህ ሮበርት። ማድረግ የሚገባህን ነገር ሁሉ ማድረግህን አውቃለሁ!" በማለት አጽናናው። አድሚራሉ ሮበርት እንዲድንለት ድኖ ልጁን ኤድዋርድን እንዲተካለት በጥልቅ ሕሊናው በጽኑ ተመኘ። ከዚህ ጊዜ በኋላ አድሚራሉ ሮበርትን እንደምትክ ልጁ ይመለከተው ጀመር። አትሙት ያለው ሮበርትም ዳነ።

"ሮበርት!"

"አቤት አድሚራል?"

"የስዊዘርላንድ ተልዕኮህ የተሳካ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።"

"እኔም እንደዚሁ። ይህ ደግሞ የመጨረሻው ተልዕኮዬ ይሆናል።"

"አሁንም ሥራውን ለመተው እንደቆረጥክ ነው?"

"አዎን ይበቃኛል።"

"በቶርንቶን ምክንያት ነው?"

"የለም በእርሱ ሳይሆን በራሴ ምክንያት ነው የምተወው። በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ መግባቱ ታክቶኛል። እብለቱና ማጭበርበሩ ሁሉ ታክቶኛል። ከቶም ቢሆን የማይፈጸመው ሰባራ ቃል ኪዳንና ተስፋ ሁሉ ታክቶኛል። በሰዎች መጠቀምና እኔም የሰዎች መጠቀሚያ መሆኔ ሁሉ ታክቶኛል። በምወደው ነገር ሁሉ ዋጋ አስከፍሎኛልና።"

"ከዚያ በኋላስ ምን እንደምትሠራ አውቀሃል?"

"ለሕይወቴ አንድ ጠቃሚና አስፈላጊ የሆነ ሥራ እፈልጋለሁ።"

"ምናልባት ስንብት ባይሰጡህስ?" አለ አድሚራሉ።

"ይሰጡኛል። ምርጫ አይኖራቸውም። ይኖራቸዋል?"

@BOOKALEM

ምዕራፍ ስድስት

ሸንጠ ረዥሙ አውቶሞቢል በወንዙ በኩል ባለው የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ ቆሞ እየጠበቀው ነበር።

"ኮማንደር ዝግጁ ነህ?" ሲል ሻለቃ ዱገርቲ ጠየቀው።

'ከምንጊዜውም የበለጠ' ሲል አሰበና....."እዎን ዝግጁ ነኝ" አለ።

ሮበርት የሚፈልጋቸውን ዕቃዎች እንዲያዘጋጅ ሻምበሉ አጅቦት ወደ መኖሪያ ኢፓርትመንቱ ወሰደው።

ተልእኮው ለምን ያህል ጊዜ ከመኖሪያ ቤቱ አርቆ እንደሚያቆየው ባያውቅም ለአንድ ሳምንት ያህል የሚሆን ቅያሪ ልብስ በሻንጣው ካሸገ በኋላ በመጨረሻዋ ደቂቃ አንድ በፍሬም የታሸገ የሱዛንን ፎቶግራፍ በሻንጣው ጨመረ። 'ይህን ጊዜ ብራዚል ውስጥ ራሷን እያስደሰተች ይሆን? ምነው አስደሳች ጊዜ ባልሆነላት!' አለና እንደገና በራሱ መጥፎ ሐሳብ ሐፍረት ተሰማው።

አውቶሞቢሉ አንድሪውስ የአየር ኃይል ጣቢያ ሲደርስ ሲ.20ኤ የተባለ የአየር ኃይል ጄት ዝግጁ ሆኖ በመጠባበቅ ላይ ነበር። ሻምበል ዱገርቲ እጁን እየዘረጋለት "መልካም ዕድል ኮማንደር!" ሲል ተሰናበተው።

"አመሰግናለሁ!" አለ ሮበርት።

ሮበርት በደረጃዎቹ ላይ እየተረማመደ አውሮፕላኑ ውስጥ ሲገባ የአውሮፕላኑ የበረራ ሠራተኞች አስፈላጊ የሆነውን የቅድመ በረራ ፍተሻ ሁሉ በማጠናቀቅ ላይ ነበሩ። ፓይለት፤ ረዳት ፓይለት፤ ተቆጣጣሪና አንድ አስተናጋጅ የአየር ኃይሉን የደምብ ልብስ ለብሰው አውሮፕላኑ ላይ ሥራቸውን ጀምረዋል። ሮበርት አውሮፕላኑን በሚገባ ያውቀዋል። እጅግ በጣም የተራቀቁ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ተገጥመውለታል። በውጭ በኩል ወደ ጅራቱ አካባቢ ትልቅ ዓሣ ማጥመጃ የመሰለ ባለከፍተኛ ሞገድ የራዲዮ መገናኛ አንቴና አለው። በውስጥ ግድግዳው ላይ ደግሞ በተለያዩ ርቀቶች አሥራ ሁለት ቀይ ቴሌፎኖችና አንድ መደበኛ ነጭ ቴሌፎን ተሰቅለዋል። የራዲዮ ግንኙነት የሚደረገው በምሥጢር ቃል ሲሆን ራዳሩም በወታደራዊ ፍሪኩዌንሲ የተስተካከለ ነው።

ይህ የአየር ኃይል ጄት ውስጡ ሰማያዊ ቀለም የተቀባ ሲሆን በጣም ሰፊ በሆነ የክበብ ዐይነት ወንበሮች ተደራጅቷል።

ሮበርት ራሱን ብቸኛው መንገደኛ ሆኖ አገኘው። ፓይለቱ መጥቶ ሰላምታ ሰጠውና "እንኳን በደህና ለመሳፈር በቃህ። አሁን የደህንነት ቀበቶህን ካሰርክ የበረራ ፈቃድ ስላገኘን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እንበራለን" አለው።

@BOOKALEM

ሮበርት የመቀመጫ ቀበቶውን ከወገቡ ጋር ጠበቅ አድርጎ አሰረና ወደ ኋላው ዐይኖቹን ጨፍኖ ጋለል ሲል አውሮፕላኑ ምድር ለመልቀቅ ማኮብኮብ ጀመረ። ከአንድ ደቂቃ በኋላ አውሮፕላኑ ምድር መልቀቅ ሲጀምር ሮበርት የተለመደው የመሬት ስበት ኃይል ተሰማው። ሮበርት ተዋጊ አውሮፕላኑ ተመትቶ ከተከሰከሰ በኋላ አብርሮ አያውቅም። ካሁን በኋላ ማብረር አትችልም ተብሎ ተነግሮታል። ምን ይህ ብቻ በሕይወት አትተርፍም ተብሎስ አልነበረም? ግን ተዓምር ነው። የለም ተዓምር አልነበረም ያዳነው። ሱዛን እንጂ።

ቬትናም የተላከው በምክትል ኮማንደርነት ማዕረግ ሬንጀር በተባለችው አውሮፕላን ተሸካሚ ጦር መርከብ ላይ በታክቲክ መኰንንነት ሲሆን የሥራ ድርሻው ተዋጊ ፓይለቶችን ማሠልጠንና የውጊያ ስልት ማቀነባበር ነበር።

"ኤ.6.ኤ ኢንትሩደር" የተባሉ አውሮፕላኖች ያሉበት አንድ ተዋጊ ስኳድሮን አዛዥ ሆኖ ሲሠራ ከውጊያ ተጽእኖ ነጻ የሆነበት ጊዜ በጣም ጥቂት ነበር። ነጻ በሆነው የረፍት ጊዜው አንዴ ወደ ባንኮክ ለሽርሽር ተጓዘ። በዚህ የሽርሽር ጊዜው ውስጥ ፈጽሞ እንቅልፍ ለመተኛት አስቦም አያውቅም ነበር።

የባንኮክ ከተማ በተለይ ለወንዶች የመደሰቻ ሥፍራ እንድትሆን ተብላ የተቆረቆረች ትመስላለች። ሮበርት አንዲት ውብ የታይ ልጃገረድ አገኘ። እርሷም በባንኮክ ከተማ ቆይታው ሁሉ አልተለየችውም ነበር። ጥቂት የታይ ቃላቶችንም አስጠናችው።

"እንደምን አደርክ?.....አሩን ሳዋሲ።"

"ከየት ነው የመጣህው?.....ኩን ማቻክ ኖይ።"

ወዴት ነው የምትሄደው?..... ኩን ካምራንት ቼን ናይ።

ሌሎችም ትርጉማቸውን ያልነገረችውን ጥቂት ቃላቶች እንዲደግም ትነግረውና ሲናገራቸው በሳቅ ትጉተከተካለች።

ሮበርት ወደ ምድብ ሥራው ሲመለስ ከኋላው ትቷት የመጣው ባንኮክ የሩቅ ሕልም ሆነችበት። አሁን ከፊቱ የተደቀነው ገሃዱ እውነታ ጦርነት ነው። ጦርነቱ ደግሞ እጅግ አሰቃቂ ነበር። አንድ የባሕር ኃይል ወታደር ለሮበርት ያሳየው በራሪ ወረቀት እንዲህ ይነበብ ነበር።

"ውድ የቬትናም ዜጐች!"

የቬትናምን ሕዝብ ሥጋት ረሐብና ስቃይ የሌለበት ደስተኛ ሕይወት እንዲኖር ለማስቻል የዩናይትድ ስቴትስ ባሕር ኃይል ከቬትናም መንግሥት ወታደራዊ ኃይል ጎን በመሰለፍ በዱ.ከ.ጠ ከፍለ ግዛት ውስጥ በመፋለም ላይ ይገኛል። ነገር ግን ብዙ የቬትናም ዜጎች የቬት ኮንግን ኃይል በመርዳታቸው ምክንያት ሕይወታቸውን ከመከፈላቸውም በላይ የመኖሪያ ጐጆዎቻቸውም ወድመዋል።

@BOOKALEM

የሀይ ምን፤ ሀይ ታን፤ ሳ.ቢ.ንህ፤ ታ.በንህ እና ሌሎችም በርካታ መንደሮች ከጠላት ጋር በማበራቸው ወድመዋል። የቬትናም መንግሥትና የኢጋሮቹ ውሕደት የሆነውን ግዙፍ ወታደራዊ ኃይል ለመፋለም የማይቻላቸውን የቬት ኮንግ ኃይሎችን የሚረዱትን ሁሉ ለመደምሰስ ከቶም ቢሆን አናመነታም። ምርጫው የናንተው ነው። የቬት ኮንግ ኃይሎች መንደራችሁና ቤታችሁ ከጥፋት ይድናል!"

'እምን ሕይወታቸውን እናተርፋለን። አገራቸውን ግን እናወድማለን!' አለ ሮበርት በሕሊናው።

"ሬንጀር" የተባለችው የጦር አውሮፕላን ተሸካሚዋ መርከብ ዘመናዊ ጥበብ ባፈራው ቁሳቁስ የተሞላች ናት። አርባ መኮንኖችንና ሦስት መቶ ሃምሳ ወታደሮችን በምቾት የምትይዝ የጦር ካምፕም ናት። የውጊያ በረራ ፕሮግራሞች ምንጊዜም ከሦስት ወይም ከአራት ሰዓታት ቀደም ብሎ ይዘጋጁና ለአብራሪዎቹ ይታደላሉ።

በመርከቧ የውጊያ እቅድ ማውጫና የመረጃ ማዕከል ውስጥ የተዋጊ ቦምብ ጣይ ምድብተኞቹ የበረራ ቅደም ተከተላቸውን እንዲያዘጋጁ ለማስቻል ከአየር የተነሱ ፎቶግራፎችና መረጃዎች ቀደም ብሎ ይታደላቸዋል።

"የእየሱስ ያለህ! ዛሬስ የሰጡን ግዳጅ እጅግ በጣም ውብ ነው" አለ ኤድዋርድ። የአባቱ ግልባጭ ቢሆንም በባሕርይ ግን ፍጹም የተለየ ሰው ነበር። አድሚራሉ አስፈሪ፤ አስደንጋጭና እጅግ ኩሩ የሆነ የሥነ-ምግባር ጥብቅነት ሲታይበት ልጁ ኤድዋርድ ደግሞ መሬት የሆነ የወዳጅነትና የተግባቢነት ባሕርይ የተላበሰ ሰው ነበር። በዚህ ተፈጥሮአዊ ቅን ባሕሪው የተነሳ በጓደኞቹ ዘንድ "ከልጆቹ አንዱ" የሚል የቅጽል መጠሪያ ከማፍራቱም በላይ የአየር ኃይል ባልደረባ የሆኑት ባልንጀሮቹ ኤድዋርድ የአዛዣቸው ልጅ መሆኑን ረስተውለታል። ኤድዋርድ በስኳድሮኑ ውስጥ ምርጥ ከተባሉት ቦምበኞች አንዱ ሲሆን ከሮበርት ጋር በፍጥነት ሊወዳጁ ቻሉ።

"ወዴት ነው የምናመራው?" አለ ሮበርት።

ለኃጢአታችን ግዳጅ "ጥልቅ ስድስት" ተሰጥቶናል። አለ ኤድዋርድ።

ከግዳጅ ሁሉ የላቀ አደገኛ ተልዕኮ ነበር። ይህም ማለት ለውጊያ የሚበሩት ወደ ሆናይ፤ ሀይ ፖንግና ጥልቅ ወደሆነው የቀዩ ወንዝ ሰሜናዊ ደለላማ ክፍል ነበር። ሲቪሎች የሚኖሩበትን አካባቢ በቦምብ እንዳይደበድቡ ታግደዋል። ሆኖም ግን ብልጣ ብልጦቹ የሰሜን ቬትናም ተዋጊዎች በሲቪሎች መኸል መሸጉ። በወታደራዊው ኃይል ውስጥ የተቃውሞ ጉርምርምታ ቢሰማም ዋሺንግተን ውስጥ በሰላምና በደሕንነት ውስጥ ከጦርነት ርቀው የተቀመጡት ፕሬዚደንት ሊንደን ጆንሰን ትእዛዛቸውን ያሹጐደጉዱት ነበር።

አሜሪካ ለረዥም ጊዜ ጦርነት ውስጥ የተዘፈቀችበት ጊዜ ቢኖር የአሜሪካን ጦር ኃይሎች ቬትናም ውስጥ ለአሥራ ሁለት ዓመታት የተዋጉበት ጊዜ

@BOOKALEM

ብቻ ነው። ሮበርት ቤላሚ ወደ ቬትናም የመጣው ባሕር ኃይሉ ከፍተኛ ችግር ውስጥ በነበረበት ጊዜ ዘግየት ብሎ በ1962 ዓ.ም. ነው።

ኤፍ.4. የተባሉት የአሜሪካ ተዋጊ ጄቶች ኃይለኛ የሆነ ጥቃት እየደረሰባቸው የነበረበት ወቅት ነው። ኤፍ.4. ጄቶች ከሩሲያዎቹ ሚግ ጄቶች በሥነ–ጥበብ ደረጃቸው የላቁ ቢሆኑም በውጊያ ላይ ሁለት የሩሲያ ሚግ ሲመታ ከአሜሪካ ባሕር ኃይል በኩል ደግሞ አንድ ኤፍ.4. ይወድቅ ነበር። ይህ ደግሞ ፈጽሞ የማይቋቋሙትና የማይቀበሉት ምጥጥኖሽ ነበር።

ሮበርት ወደ አድሚራል ዊታከር ቢሮ ተጠርቶ ገባ። "ፈልገውኝ ነበር አድሜራል?"

"የጐበዝ ፓይለትነት ዝና አለህ ሮበርት። ዕርዳታህን እፈልጋለሁ።"

"አቤት ጌታዬ?"

"እነዚህ የተረገሙ ጠላቶቻችን እያወደሙን ነው ሮበርት። ሁኔታው በጥልቀት እንዲጠና አድርጌ ነበር። በጀቶቻችን በኩል ምንም ዐይነት ችግር እንደሌለ አረጋግጠናል። ችግሩ ወይም ስህተቱ ያለው ጀቶቻችንን የሚያበሩት ፓይለቶች ላይ ነው። ልምድ ያንሳቸዋል። ገባህ ሮበርት?"

"አዎን ጌታዬ!"

"ወደ ሥራችን እንመለስ።"

"እሺ ጌታዬ!"

ሮበርት ከሬንጀር የጦር መርከብ ላይ ሠላሳ አራት የውጊያ በረራዎችን ያላንዳች አደጋና እንከን አከናውኗል።

ሠላሳ አምስተኛው ግዳጁ "ጥልቅ ስድስት" ተብሎ የተሰየመው ነበር።

ሐኖይን አልፈው ወደ ሰሜን–ምዕራብ ፋቶ እና ዬን-ባይ በረሩ። የወንዙ ደላላማ ተረተር ርዝመት ማለቂያ የለሽ ነው።

ቦምብ ጣዩ ኤድዋርድ ከሮበርት በስተቀኝ ተቀምጦ ራዳሩን ሲቆጣጠር የጠላት ራዳር የነሱን ጀቶች ለማየት ሰማዩን በሞገዱ ሲያስስ የሚያሰማውን ድምጽ ያዳምጣል። ሰማዩ ከጠላት በሚተኮሰው ባለሃምሳ አምስት ሚሊ ሜትር የአየር መቃወሚያ መትረየስ ጢስና በቀይ አመልካች ጥይት ተጥለቅልቋል።

"ወደ ዒላማችን እየቀረብን ነው ሲል!" ኤድዋርድ ተናገረ።

"ሰምቻለሁ!" አለ ሮበርት በመገናኛ ማይክሮፎኑ ውስጥ።

ቦምብ ጣዩ አውሮፕላናቸው ኤ.6.ኤ. በአራት መቶ ሃምሳ ኖት ፍጥነት እየበረረ ነው። ከአጠቃላዩ የቦምብ ጭነት ከብደት አንፃር ፈጣንና ለጠላት ዕይታ አስቸጋሪ የሆነ ግሩም ፍጥነት ነበር።

ሮበርት የመሣሪያ መተኮሻ መቆጣጠሪያውን ቁልፍ በጣቱ ተጫነው። አሁን እያንዳንዳቸው 500 ፓውንድ ክብደት ያላቸው ቦምቦች ወደ ምድር ለመራገፍ የተዘጋጁ ሲሆን አውሮፕላኑም በቀጥታ ወደ ዒላማው እየበረረ ነው።

@BOOKALEM

“ሮሜዎ!” የሚል ድንገተኛ የራዲዮ ጥሪ ተሰማ። “ልክ በአራት ሰዓት ላይ ለስላሳ አፈር አለልህ!”

ሮበርት ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ሲመለከት አንድ የሩሲያ ሚግ ተዋጊ ጄት በከፍተኛ ፍጥነት እየተምዘገዘገ ሲመጣባቸው አየ።

ሮበርት አውሮፕላኑን አዘቀዘቀውና ቁልቁል ወደ ምድር ተወረወረ። ሚጉም ከኋላው ተከትሎት እየተወረወረ አንድ ሚሳይል ተኮሰበት። ሮበርት የጠላት ተኩስ መቆጣጠሪያ መሣሪያውን ሲመለከት ሚሳይሉ በከፍተኛ ፍጥነት እየቀረበው መሆኑን ተረዳ። አንድ ሺህ ጫማ ርቀት.....ስድስት መቶ ጫማ.....አራት መቶ ጫማ.....“አረ ምንድን ነው የምንጠብቀው?” ሲል ኤድዋርድ ጮኸ።

ሮበርት የመጨረሻዋን ሰከንድ ጠበቀና ከአውሮፕላኑ የብረት ቁርጥራጮችን ለቆ በድንገትና በቀልጣፋ ፍጥነት አውሮፕላኑን በቀጥታ ወደ ሰማይ ቀልበሶ አወጣው። ሚሳይሉ ግን ምንም ጉዳት ሳያደርስ ከሮበርት አውሮፕላን የተለቀቀውን ብረት ተከትሎ መሬት ላይ ተከስክሶ ፈነዳ።

“ተመስገን አምላኬ! አንተም ጓደኛዬ!” አለ ኤድዋርድ።

“በጣም ግሩም የሆነ አስደሳች ሥራ!” የሚል መልዕክት በራዲዮኑ ደረሳቸው።

አሁን አውሮፕላኑ በሚላማቸው ላይ እያንጣበበ ነው። ኤድዋርድ ሚላማው በትክክል ሲገባለት.....“እዚህ ላይ ነን!” ብሎ ጮኸና ቦምቦቹን የሚለቀውን ቀይ ቁልፍ ተጫነው። ቦምቦቹ ቁልቁል ወደታለሙበት ሚላማ እየተምዘገዘጉ ወረዱ። ግዳጁ ተፈፀመ! ሮበርት ቦምብ ጣዩን አውሮፕላን አዞረና ወደ ተሸካሚዋ የጦር አውሮፕላን ያበራት ጀመር።

ልክ በዚህች ቅጽበት የነሮበርት አውሮፕላን ኃይለኛ የሆነ መናጋት ደረሰበት። ፈጣኑና ባለግርማ ሞገሱ አውሮፕላን በድንገት በደረሰበት የተኩስ ምት ቀርፋፋና ዝግተኛ ሆነ።

ኤድዋርድ “ተመትናል!” ሲል ጮኸ።

የእሳት መቆጣጠሪያ መብራቶቹ ቀይ ሲያበሩ አውሮፕላኑ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ መዋዠቅ ጀመረ።

“ሮሜዎ! ሽፋን እንድንሰጥህ ትፈልጋለህ?” የሚል መልዕክት በራዲዮኑ ተሰማ።

ሮበርት ፈጣን ውሳኔ ሰጠ። “የለም አልፈልግም። ወደ ሚላማችሁ ብረሩ። እኔ እንደምንም ብዬ አውሮፕላኑን መርከቧ ላይ ለማሳረፍ ሞክራለሁ” ሲል መልስ ሰጠ።

ቦምብ ጣዩ ግን ፍጥነቱ በጣም ቀንሶ ዝግተኛ ከመሆኑም በላይ ለመቆጣጠር ፈጽሞ አስቸጋሪ ሆነ።

@BOOKALEM

ሮበርት የከፍታ መቆጣጠሪያ መሣሪያውን ሲመለከት ወደ መሬት እያዘቀዘቁ መምጣታቸውን ተገነዘበ። ወዲያው የመገናኛ ራዲዮኑን ተጫነና....."ሮሜዎ ለጠቅላይ ሠፈር! ተመተናል!" አለ።

"ጠቅላይ ሠፈር ለሮሜዎ! ጉዳቱ ምን ያህል ነው?"

"እርግጠኛ አይደለሁም። ቢሆንም ግን አሳርፈዋለሁ ብዬ እገምታለሁ።" መልዕክት ተቀባዩ "ጠብቀኝ!" ሲል አዘዘና ለተወሰኑ ሴኮንዶች ግንኙነቱ ተቋረጠ።

ከጥቂት ቆይታዎች በኋላ ደግሞ ግንኙነቱ እንደገና ተከፈተ።

"ሮሜዎ! ማረፊያ በምትደርስበት ጊዜ ጥሪህ ቻርሊ ይሁን!" አለው። ይህም በአስቸኳይ መርከቡ ላይ ለማረፍ ትችላለህ ማለት ነበር።

"ሮጀር! ተቀብያለሁ" አለ ሮበርት።

"መልካም ዕድል!"

አውሮፕላኑ ይበልጥ ሚዛኑን ስቶ ይገለባበጥ ጀመር። ሮበርት ደግሞ ፊቱ ተኮማትሮ አቅጣጫውን ለማስተካከልና ከፍታውን ለመጨመር ይታገላል።

"ምን ያህል ርቀት ይቀረናል?" አለ ሮበርት።

ኤድዋርድ ቻርቱን ተመለከተና "ሰባት ደቂቃዎች" አለው።

"ለትኩስ ምሳ እንደርሳለን!" አለ ሮበርት።

ሮበርት ባለው ችሎታ ሁሉ መሪውንና ፍጥነት መቆጣጠሪያውን በመጠቀም በቀጥታ መስመር ለመብረር ታገለ። ቢሆንም ግን ከፍታቸውን በሚያስደነግጥ ሁኔታ እያጡ ሲሆን በመጨረሻም የሚያንፀባርቀውን ሰማያዊ የቶንኬን ባሕረ ሰላጤ ውሃ ለማየት በቁ።

ሮበርትም ጮክ ብሎ "ወደ ሠፈራችን ለመድረስ ጥቂት ማይሎች ብቻ ይቀሩናል" አለ።

እናም በድንገት ከየት መጡ ሳይባል ሁለት ሚግ ተዋጊ ጄቶች እንደነጐድጓድ በሚያስተጋባ ድምጽ እየበረሩ መጥተው በነሮበርት አውሮፕላን ላይ ጥይት እንደዝናብ አወረዱበት።

"ውጣ!" ሲል ሮበርት ጮኸና ወደ ኤድዋርድ ዘወር ብሎ ተመለከተ።

ኤድዋርድ በታሰረበት ቀበቶ ውስጥ እንዳለ ወንበሩ ላይ ተንጋሏል። የሰውነቱ ቀኝ ጐን በጥይት ሲበጣጠስ የአውሮፕላኑ በረራ መቆጣጠሪያ ክፍል በኤድዋርድ ደም ጨቀየ።

"አይሆንም!" ሲል ሮበርት በሰቆቃ ጮኸ።

ከሴኮንዶች በኋላ ሮበርት የሚቆጠቁጥ ሕመም ተሰማው። የበረራ ልብሱ በራሱ ደም ተጨማለቀ። ቁልቁል ሲወረወር ሕሊናውን እየሳተ መሄዱ ተሰማው። ሮበርት በመጨረሻዋ ቅጽበት የቀረችውን የኃይል እንጥፍጣፊ በመጠቀም ቀበቶውን ፈታና ወደ ኤድዋርድ ሙት አካል ዘወር ብሎ....."አዝናለሁ!" ሲል አንሾካሾከ። ከዚህ በኋላ ግን እንዴት ከተመታው አውሮፕላን ውስጥ

@BOOKALEM

እንደተወረወረና በጃንጥላ (ፓራሹት) ባሕር ላይ ሊወርድ እንደቻለ ፈጽሞ አያስታውስም።

ወዲያው የአደጋ ጥሪ ተላለፈ። ሲኩርስኪ ኤስ.ኤች.3.ኤ የባሕር ንጉሥ የተባለ አሳሽ ሄሊኮፕተር "ዩ.ኤስ.ኤስ. ዮርክ ታውን" ከተባለች የጦር መርከብ ላይ ተነስቶ ዙሪያውን እያንዣበበ ሲጠብቅ በርቀት ደግሞ የቻይና የጦር ጀልባዎች ግዳይ ለመጣል በከፍተኛ ፍጥነት የባሕሩን ውሃ እየሰነጠቁ ሲመጡ ታዩ። ቢሆንም ግን በጣም ዘግይተው ነበር። ሮበርትን ሄሊኮፕተሩ ላይ እንደጫኑት አንድ ሐኪም ተመለከተውና "የክርስቶስ ያለህ! ሆስፒታል እንኳ አይደርስም!" ሲል ተናገረ።

ሮበርት የማደንዘዣ መርፌ ተወግቶ ዙሪያ ደረቱ በፋሻ ከተጠቀለለ በኋላ ወደ ኩ.ቺ ጊዜያዊ ሆስፒታል ተወሰደ።

አራት መቶ አልጋዎች ያሉት ይህ ሆስፒታል አገልግሎት የሚሰጠው ለኩ.ቺ ታይጊንህና ድ.ቲንግ ለተባሉት ክልሎች ሲሆን በጐጆ ቤቶች የተከበበ የቀዶ ጥገና ሕክምና መስጫ ክፍል ያለው ጊዜያዊ ሆስፒታል ነበር። እንደዚሁም ለከፍተኛ የቃጠሎ አደጋ ዕርዳታ የሚሰጡ ሁለት የሕክምና ክፍሎች ሲኖሩት ሁለቱም ከሚገባው በላይ በበሽተኛ የተጣበቡ ናቸው። ሮበርትን ወደሆስፒታሉ በሚወስዱበት ወቅት በሆስፒታሉ ወለል ላይ ደሙን እያስመረ ነበር የተወሰደው።

አንድ ዶክተር እየተጣደፈ መጣና ቁስሉ የታሰረበትን ፋሻ በመቀስ ቆርጦ የጉዳቱን መጠን በአንክሮ ከተመለከተ በኋላ "ፈጽሞ አይድንም! ውሰዱና ማቀዝቀዣ ውስጥ አስቀምጡት!" ሲል ተናገረ።

'አትሞትም ባሕረኛው! ዐይኖችህን ግለጣቸው!'

ዐይኖቹን ሲገልጥ ነጭ የነርሶች ዩኒፎርም የለበሰች ሴት አጠገቡ ቆማ ብሩህ ፈገግታ ስትመግበው ተመለከተ። አንድ ነገር እየተናገረችው ነው። ግን ምንም አይሰማውም። የሆስፒታሉ ክፍል በሕመም ስቃይ ተይዘው በሚያቃስቱ፤ በሚጮሁ፤ በሚጓጉሩ ሰዎች፤ እንዲሁም በጩኸት ትእዛዝ በሚሰጡ ዶክተሮችና እንደእብድ እየተራወጡ ቁስለኞችን ለመርዳት በሚጥሩ ነርሶች ተሞልቷል።

በቀጠሉት አርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ሮበርት የማስታወስ ችሎታው ልክ በሕልም ዓለም ውስጥ እንደነበረ ዐይነት ሆኖ ነው የሚታየው።

በመጨረሻ ነርሷ ሱዛን ዋርድ አንድ ዶክተር በብዙ ጥረት አግባብታ ቀዶ ጥገና እንዳደረገለትና ሕይወቱን ለማትረፍ የራሷን ደም እንደለገሰችለት ሊረዳ ችሏል።

ቀዶ ጥገናው ከተከናወነ በኋላ ዶክተሩ "አሥር ከመቶ እንኳ የመትረፍ ዕድል የለውም። ጊዜያችንን በከንቱ ነው ያባከንው" ሲል ተናገረ።

ነገር ግን ዶክተሩ ሮበርት ቤላሚንና ሱዛን ዋርድን በሚገባ አላወቃቸውም ነበር። ሮበርት ዐይኖቹን በገለጠ ቁጥር ሱዛን እጆቹን ይዛ ግንባሩን እያሻሸችለት ሕክምና እያደረገችለት ወይንም እንዲድን እየተመኘች ምንጊዜም

@BOOKALEM

አጠገቡ ትገኛለች። ይህም አልበቃ ብሏት ሌሊቱን በሙሉ ቅዠቱን እያዳመጠች ታድራለች።

"……በቀጥተኛ አቅጣጫ ለመብረር አትችልም……ወንዙ ላይ ትወድቃለህ……በረራቸውን ከሚላማቸው በጥቂት ማዕዘን ዘንበል እንዲያደርጉ ንገሪያቸው።"

"እነግራቸዋለሁ!" አለችና ሱዛን ላቡን ጠራረገችለት።

"አምስቱንም የመጠበቂያ ቅርቃሮች ካልነቀላችሁ በስተቀር መቀመጫው ከአውሮፕላኑ ውጭ ሊወረውራችሁ አይችልም።"

"….የመተኮሻ መሣሪያው አይሠራም። ቦምቦቹ ሁሉ የት እንደሚያርፉ አይታወቅም።" ግማሽ በግማሽ ሱዛን በሽተኛዋ ምን እንደሚያወራ አይገባትም ነበር።

ሱዛን ዋርድ የቀዶ ጥገናው ሕክምና ክፍል ኃላፊና ምርጥ የተባለች ነርስ ነች። አመጣጧ ኢዳሆ ከተባለች አነስተኛ ከተማ ሲሆን ያደገችው ፍራንክ ፕሪስኮት ከተባለ የከተማዋ ከንቲባ ልጅ ጋር ነው። የከተማው ሰው በሙሉ አንድ ቀን ትዳር ይመሠርታሉ እያለ ይጠብቃቸው ነበር።

ሱዛን ሚካኤል የተባለ እጅግ በጣም የምትወደው ታናሽ ወንድም ነበራት። ወንድሟ ሚካኤል አሥራ ስምንተኛ ዓመቱን ሲደፍን ወደ ቬትናም ጦርነት በመዝመቱ በቀን በቀን ደብዳቤ ትጽፍለት ነበር።

ሚካኤል በወደ ዘማችነት ከተመዘገበ ከሦስት ወራት በኋላ ቤተሰቦቹ ቴሌግራም ደረሳቸው። ቴሌግራሙ ከመከፈቱ በፊት ነበር ሱዛን መልዕክቱ ምን እንደሆነ የገባት።

ፍራንክ ፕሪስኮት ዜናውን እንደሰማ ሱዛንን ያዝ አደረጋትና "በእውነት ሚካኤልን በጣም እወደው ነበር። በጣም አዝናለሁ!" ሲል ተናገረና አንድ ስህተት ሠራ። "በይ አሁኑኑ እንጋባ ሱዛን!" አላት።

ሱዛን በመገረም ቀና ብላ ተመለከተችውና ውሳኔዋን ወሰነች። "የለም አይሆንም። አሁን በሕይወቴ ውስጥ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነ ሥራ ለመሥራት መነሳቴ ነው!" አለችው።

"ስለእግዚአብሄር! እኔን ከማግባት የበለጠ ምን ጠቃሚ ነገር ይኖራል?"

የሱዛን መልስ……"ቬትናም!" ነበር።

ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ በተሸከርካሪ አልጋ እየተገፋ ወደ ሆስፒታሉ ሲገባና እንዲሞት ሲፈረድበት ሱዛን ዋርድ ለአሥራ አንድ ወራት ያላንዳች ድካምና መሰልቸት በማገልገል ላይ ነበረች። "ሙከራ" የሚሉት አሠራር በድንገተኛ ዕርዳታ መስጫ ሆስፒታሎች ውስጥ የተለመደ አሠራር ነው። ዶክተሮች ሁለት ወይም ሦስት በሽተኞችን ከተመለከቱ በኋላ የትኛውን ማዳን እንደሚችሉ ይወስናሉ።

@BOOKALEM

ምክንያቱ ምን እንደሆነ ባታውቀውም የጨረተውን የሮበርት አካል ተመለከተችና አሳልፋ ልትተወው እንደማይገባት ወሰነች። ለማዳን የምትጥረው ወንድሟን ነው? ወይስ ሌላ ሰው? እስኪያቅለሸልሻት ድረስ ትሠራለች።

ሱዛን የበሽተኛውን ማሕደር ተመልከታ ማንነቱን በትክክል ተገንዝባለች። የባሕር ኃይል መሰቀል ተሸላሚ የሆነ የባሕር ኃይል ፓይለትና አስተማሪ ሲሆን የተወለደው ሐርቬይ ኢሊኖይስ በተባለች ከሺካጐ በስተደቡብ በምትገኝ አነስተኛ የኢንዱስትሪ ከተማ ነው።

በባሕር ኃይሉ ውስጥ የተመዘገበው የኮሌጅ ትምህርቱን አቋርጦ ሲሆን የሰለጠነው ፔንስኮላ በተባለ ሥፍራ ነው። ያላገባ ብቸኛም ነው።

በየዕለቱ ሮበርት ቤላሚ በሕይወትና በሞት መኻል ባለችው ጠባብ መስመር ውስጥ በሚዋልልበት ወቅት ሱዛን አጠገቡ ቆማ "ንቃ ባሕረኛው! እየጠበኩህ ነው!" ትለዋለች።

ሆስፒታል በገባ በስድስተኛው ቀን በቅዠት ሲወራጭ ውሎ በድንገት አፈፍ ብሎ ተነስቶ አልጋው ላይ ቁጭ አለ። ግልጽ በሆነና በጠራ ድምጽ....."ለካስ በሕልሜ አይደለም። አንቺ በእውን በገሃድ ያለሽ ሴት ነሽ!" አላት። "በገነት ውስጥ ያለሁና አምላክ አንቺን ለኔ የላከልኝ መስሎኝ ነበር።"

ልቧ ሲዘል ተሰማት። "እውን ነኝ!" አለችው። ሱዛን የሮበርትን ዐይኖች ትኩር ብላ ተመለከተችውና "መቼም ሞተህ ቢሆን ኖሮ እኔ ራሴ እንደገደልኩህ እቆጥረው ነበር" አለችው።

ሮበርትም ዙሪያ ገባውን በዐይኖቹ ተመለካከተና "ለመሆኑ የት ነው ያለሁት?" ሲል ጠየቃት።

"በአሥራ ሁለተኛው የድንገተኛ ሕክምና መስጫ ሆስፒታል ውስጥ።"

"ምን ያህል ጊዜ ቆየሁኝ?"

"ለስድስት ቀናት።"

"ኤድዋርድ.....እሱ....." "አዝናለሁ ሮበርት።"

"ለአድሚራሉ መንገር አለብኝ።"

እጆቹን በእጆቿ ጠበቅ አድርጋ ያዘችና ለስለስ ባለ አንደበት "አድሚራሉ የልጃቸውን መሞት ያውቃሉ።

እዚህ ድረስ ተመላልሰው ጎብኝተውህ ነበር" አለችው።

የሮበርት ዐይኖች በእምባ ተሞሉ። "ይሀን የተረገመ ጦርነት እጅግ በጣም ነው የጠላሁት። ምንያህል እንደጠላሁት ልናገር እልችልም!" አላት።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ዶክተሮቹ እስኪገረሙ ድረስ የሮበርት ቁስል እየሻረና ጤንነቱ እየተሻሻለ መጣ። "በቅርቡ ከሆስፒታል እናስወጣዋለን" ብለው ሐኪሞቹ ለሱዛን ሲነግሯት መቋቋም ያልቻለችው ሐዘን ተሰማት።

@BOOKALEM

ሮበርት መቼ ከሱዛን ጋር በፍቅር እንደወደቀ አያውቅም። ምናልባት የቁስሉን ጨርቅ እየለወጠችለት በነበረበት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። በቅርብ ርቀት ላይ ቦምብ ሲጣል ተሰማቸው። ሱዛን ወደ ጆሮው ጠጋ አለችና.....“መዝሙር እየዘመሩ ነው!”” አለችው።

በመጨረሻም ሮበርት ዋሺንግተን ወደሚገኘው ዋልተር ሪድ ሆስፒታል እንደሚዛወር ተነገረው። በዚህ ጊዜ ሱዛን ጠጋ አለችውና “ለመሆኑ ይህንን ሰውነትህን ለሌላ ነርስ አሳልፈሬ የምሰጥ ይመስልሃል? ካንተ ጋር አብሬ ወደ ዋሺንግተን ለመዛወር የማልመዘው ገመድ አይኖርም!” ባለችው ጊዜም ይሆናል ከእርሷ ጋር በፍቅር የወደቀው።

ከሁለት ሳምንት በኋላ የጋብቻቸው ሥነ–ሥርዓት ተፈፀመ። ሮበርት ሙሉ በሙሉ ከቁስሉ ለመሻር አንድ ዓመት ሲፈጅበት በዚህም ጊዜ ውስጥ ሱዛን አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ ቀንም ሆነ ሌሊት ታሚላለት ነበር። የሱዛን ዐይነት ሴት አጋጥሞት አያውቅም። የእርሷን ያህል ማንንም ለማፍቀርም አይችልም። ለሰው ልጆች ስቃይ የሚሰማትን ሐዘኔታ በጣም ይወድላታል። ስሜታዊነቷንና የተፈጥሮ ቅንነቷን ይወድላታል።

አንደኛውን ዓመት የጋብቻ በዓላቸውን ባከበሩበት ወቅት እንዲህ አላት። “በዚህ ዓለም ላይ የመጨረሻዋ ቆንጆ፤ እፁብ ድንቅ የሆነሽ፤ ለሰው ልጆች በጣም የምታስቢ፤ እንዳንቺ ብሩህ አዕምሮና ትኩስ መንፈስ ከቆራጥነት ጋር የተላበሰች ሴት ፈጽሞ የለችም።”

ሱዛንም በደስታ ስሜት እቅፍ አደረገችውና በዘማሪያን ሙዚቃዊ ድምጽ “አንተም ልክ እንደዚሁ እንደሆንክ እርግጠኛ ነኝ!” አለችው።

ከፍቅር በላይ ያለውን ሁሉንም ነገር የሚካፈሉና እርስ በእርሳቸው የሚከባበሩ ከመሆናቸውም በላይ ወዳጆቻቸው ሁሉ የሚቀኑባቸው ስለመልካም ትዳር በአርአያነት የሚጠቅሷቸው በሕይወት የተዋሃዱ የትዳር ጓደኛሞች ናቸው።

አንዳቸው ሌላውን በመንካት ወይም በጥቂት ቃላት ብቻ ስሜቱን ወይም ስሜቷን እንደእሳት ለማሞቅ መቻልን ያውቁበታል። አንድ ቀን ባልና ሚስቱ የተከበረ የራት ግብዣ ተጠርተው ለመሄድ በሚዘጋጁበት ወቅት ሮበርት ዘግይቶ ኖሮ ገና መታጠቢያ ቤት ውስጥ እንዳለ ሱዛን የሚያምር የራት ልብሷን ለብሳ መታጠቢያ ቤት ውስጥ ገባች።

“ያምላክ ያለህ! ፍጹም በወሲብ የተሞላሽ ሴት መስለሻል። ትንሽ እንኳ ጊዜ ስለሌለን በጣም ያሳዝናል” አላት።

“ግዴለም! ስለጊዜ ማነስ አትጨነቅ” አለችና የግብዣ ልብሷን አወላልቃ መታጠቢያው ገንዳ ውስጥ ተቀላቀለችው። ወደ እራት ግብዣው ሳይሄዱ ቀሩ።

ሱዛን ሮበርት ምን እንደሚፈልግ ለራሱ ከማወቁ በፊት እርሷ አስቀድማ ተገንዝባ ፍላጎቱ መሟላቱን ታረጋግጣለች። ሮበርትም እንደዚሁ የእርሷን ፍላጐት

@BOOKALEM

ይከታተላል። የፍቅር ማስታወሻዎች በመልበሻ ክፍሏ ጠረጴዛና በጫማዎቿ ውስጥ ተቀምጠው ታገኛለች። አበቦችና አነስተኛ ስጦታዎች በበዓላትና በመታሰቢያ ቀናት ሁሉ ያበረክትላታል።

ፍፁም ደስታ የተሞላበት ሳቅና ቡረቃ ይጋሩ ነበር።

"በአሥር ደቂቃዎች ውስጥ ዙሪክ አየር ማረፊያ እናርፋለን!" ሲል የፓይለቱ ድምጽ በማይክራፎኑ ላይ አምባረቀ። የሮበርት ቤላሚ የትዝታ ጉዞው ተቋረጠና ወደ ወቅታዊ ተልዕኮው ተመለሰ።

በባሕር ኃይል የመረጃ ጽሕፈት ቤት ባልደረባነት ባሳለፋቸው አምስት ዓመታት ውስጥ እጅግ ፈታኝ የሆኑ የምርመራና የክትትል ሥራዎች ቢገጥሙትም አሁን እንደ ተላከበት ዐይነት ግዳጅ እንግዳ የሆነና መጨበጫ የሌለው ተልዕኮ ግን ገጥሞት አያውቅም። ወደ ቀጭን አየርነት የተለወጡ አንድ አውቶቡስ ሙሉ ምስክሮች ፈልጎ ለማግኘት ወደ ስዊዘርላንድ ተላከ።

"እባክህ የመቀመጫ ቀበቶህን ብታጠብቅ?"

ግዙፉ ሲ.20.ኤ. አውሮፕላን በጥቅጥቅ ጨለማ በተዋጠ ደን ላይ ሲያንጎራብብ ከቆየ በኋላ በአየር ማረፊያው አስፋልት መብራቶች እየተረዳ በዙሪክ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ላይ አረፈ።

ፓይለቱ ተግባሩን ፈጽሞ የአውሮፕላኑን ሞተር ካጠፋ በኋላ ወደ ሮበርት መጣ። "እዚህ አገር አየሩ የተቃወሰ ነው። ትናንት እሁድ ሙሉ ቀን ፀሓያማ ሆኖ ዋለ። ዛሬ ደግሞ ሙሉ ቀን ሲዘንብ ውሎ ማምሻውን ደመናው ገለጠ። እዚህ አገር የሚያስፈልግህ የእጅ ሰዓት ሳይሆን የዝናብ መጠን መለኪያ መሣሪያ ነው። በነገራችን ላይ መኪና እንዲዘጋጅልህ ትፈልጋለህ ኮማንደር?" አለው።

"የለም አልፈልግም" አለ ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ። ምክንያቱም ካሁን በኋላ ያለማንም እገዛ ብቻውን መንቀሳቀስ አለበትና። ሮበርት ከአውሮፕላኑ እንደወረደ አንድ አነስተኛ አውቶቡስ ተሳፈረና ወደ አየር ማረፊያ ሆቴል አመራ። እዚያም አንድ ክፍል ከተከራየ በኋላ ጭልጥ ያለ ሕልም አልባ እንቅልፍ ውስጥ ሰጠመ።

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሰባት

በማግስቱ ጠዋት ሮበርት ወደ መኪና አከራይ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ሄደ።

"እንደምን አደርክ ጌታዬ?"

"እንደምን አደርክ። የሚከራይ መኪና ይኖራችኋል?"

"አዎን ጌታዬ። ለምን ያህል ጊዜ ነው የሚፈልጉት?"

'ለአንድ ቀን? ለአንድ ሳምንት? ለአንድ ወር? ወይስ ለአንድ ዓመት?' ሲል ሮበርት በመደነቅ አሰበና ጸሓፊውን "ለምን ያህል ጊዜ እንደምፈልገው እርግጠኛ አይደለሁም" አለው።

"በጣም ጥሩ! እነዚህን ወረቀቶች ቢሞሉልን?"

ሮበርት ፎርሙን ሞላና የመኪናውን ኪራይ ዋጋ ለመክፈል ጄነራል ሒሊያርድ የሰጠውን ልዩ ጥቁር የዱቤ መሸመቻ (ክሬይዲት ካርድ) ለጸሓፊው ሰጠው።

ጸሓፊው ክሬዲት ካርዱን ተመለከተና "አንድ ጊዜ ይቅርታ" ካለ በኋላ ይዞት ሌላ ቢሮ ገባ። ከደቂቃዎች በኋላ ተመልሶ ሲወጣ "ሮበርት ችግር አለ?" ሲል ጠየቀው።

"የለም። ምንም ችግር የለም ጌታዬ።"

የተከራያት መኪና ግራጫማ ቀለም የተቀባች አፔል አሜጋ ነበረች። ሮበርት በአየር ማረፊያው በኩል አድርጉ ወደ ታችኛው የዙሪክ ክፍለ ከተማ ከነፈ። ስዊዘርላንድ ሮበርትን በጣም የምታስደስተው አገር ከመሆኗም በላይ ብዙ የሰለላና የመረጃ ሥራ አከናውኖባታል። ሮበርት በሰለላው ዓለም ዙሪክ ውስጥ አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ ወዳጆችንም ለማፍራት በቅቷል። ቢሆንም ከአንዳቸውም ጋር ግንኙነት እንዳታደርግ ተብሎ በጄነራል ሒሊያድር ታዟል።

በተከራያት መኪና ለሃያ ደቂቃዎች ያህል ከተጓዘ በኋላ በአረንጓዴ ዕጽዋት የተከበበው ዶልደር ግራንድ ሆቴል ደረሰ። ሆቴሉን ልክ ከዚህ በፊት እንደሚያስታውሰው ነበር ያገኘው። መኪናውን አቁሞ ከወረደ በኋላ በእንግዳ መቀበያው አዳራሽ ውስጥ በስተቀኝ በኩል ወደሚገኘው የእንግዳ መቀበያ ባንኪኒ (ዴስክ) አመራ።

"እንደምን አደሩ ጌታዬ?"

"እንደምን አደርክ! የማረፊያ ክፍል እፈልግ ነበር።"

"አዎን! በቅድሚያ ይከፍላሉ።"

ጄነራል ሒሊያርድ የሰጠውን ክሬይዲት ካርድ አቀበለው።

@BOOKALEM

ሮበርት የስዊዘርላንድን ካርታ ጠይቆ ከተሰጠው በኋላ በሆቴሉ አስተናጋጅ እየተመራ አዲስ በተሠራው የሆቴሉ ህንፃ ውስጥ ወደሚገኘው ምቹ የመኝታ ክፍሉ አመራ። መኝታ ቤቱ ውስጥ ባለው ሐይቁን በሚያሳየው ሰገነት ላይ ቆሞ ከፊቱ ስለሚጠብቀው ግዳጅ ማሰላሰል ጀመረ። ከትትሉን ለመጀመር የሚያስችለው ምንም ጭብጥ ወይም ፍንጭ የለውም። ስሌቱ ሁሉ እንደጉም የማይጨበጥ ደብዛው የጠፋ ነው። አስጎብኚው የአውቶቡስ ኩባንያና የመንገዶቹ ስምና አድራሻ አይታወቅም። ስለመንገደኞቹ ያለው ብቸኛ መረጃ ቀንና ቦታ ብቻ ነበር። እሁድ ጥቅምት አሥራ አራት ቀን ሥፍራው ኡተንዶርፍ።

አንድ ጭብጥ ለማግኘት ሲያሰላስል አንድ ነገር ትዝ አለው። ሁሉም አስጎብኚ አውቶቡሶች የሚነሱት ከሁለት ከተሞች ማለትም ከዙሪክና ከጄኔቫ ነው። ሮበርት የጠረጴዛውን መሳቢያ ሳበና አንድ ግዙፍ የስልክ ቁጥር ማውጫ አወጣ። ከግማሽ ደርዘን በላይ የሚሆኑ አስጎብኚ የአውቶቡስ ድርጅቶች ማውጫው ላይ ተመዝግበዋል።

ሰን ሻይን ቱር.....ቱር አልፒኖ.....ስዊስ ቱር.....ፑሪዝማ ራይዘን ቱር ሰርቪስ.....

እያንዳንዱን አስጎብኚ ድርጅት ተዘዋውሮ ማነጋገርና ማረጋገጥ አለበት። ስማቸውንና አድራሻቸውን በሙሉ ማስታወሻ ደብተሩ ላይ ከገለበጠ በኋላ ቱር ሰርቪስ ወደሚባለውና ከሁሉም ቅርብ ወደሆነው አስጎብኚ ድርጅት ለመጀመር ወደዚያው ጉዞውን ቀጠለ።

ከረዥሙ የእንግዳ መቀበያ ባንከኒ በስተኋላ ቱሪስቶችን በማስተናገዱ ሥራ ላይ ሁለት ጸሐፊዎች ተገኝተዋል። ከሁለቱ አንዱ ነፃ ሲሆንለት ሮበርት ጠጋ አለና.....“ይቅርታ አድርግልኝ። ባለቤቴ በናንተ አውቶቡስ ተሳፍራ በነበረበት ጊዜ የገንዘብ ቦርሳዋን ረስታው ወርዳ ነበር። ይህን ያደረገችው ምናልባት ኡተንዶርፍ ላይ በተከሰከሰው ባሉን በመደንገጧ ሳይሆን አይቀርም” አለው።

ጸሐፊው ግራ ገብቶት ሮበርትን መልከት አደረገውና “ተሳስተዋል ጌታዬ! የኛ አውቶብሶች ፈጽሞ ወደ ኡተንዶርፍ አካባቢ አይደርሱም” አለው።

“አ! አዝናለሁ” አለና ሮበርት ከቢሮው ወጣ። ‘አንድ ወደቀ!’ የሚቀጥለው ሙከራው ፍሬያማ ነበር።

“አዎን ጌታዬ! የኛ አውቶቡሶች ስዊዘርላንድ ውስጥ የማይረግጡት ሥፍራ የለም።”

“በዕለተ ሰንበት የተከሰከሰውን ባሉን ለማየት የቆመ አውቶቡስ ነበር?”

“በማስጎብኘት ሥራችን ከፍተኛ ኩራት ይሰማናል። ቢሆንም ግን ከፕሮግራማችን ውጭ አውቶቡሶቻችን የትም ቦታ አይቆሙም።”

“ስለዚህ ከአውቶቡሶቻችሁ ውስጥ አንድም አደጋውን ለማየት አልቆመም?”

@BOOKALEM

“በፍጹም የቆመ የለም።”

“አመሰግናለሁ።”

የሚቀጥለው ሙከራው ባንሆፍ ስትራዝ በተባለ ሥፍራ የሚገኘውና "ሰን ሻይን ቱር" የተባለው ኩባንያ ነበር።

“እንደምን ዋልክ?” አለ ሮበርት ጸሓፊውን። “ከአውቶቡሶቻችሁ ስለአንዱ ልጠይቅ እፈልግ ነበር። ኡተንዶርፍ አካባቢ ባሉን በተከሰከሰበት ወቅት ከሹፌሮቻችሁ አንዱ ቱሪስቶች የወደቀውን ባሉን ለማየት እንዲችሉ አውቶቡሱን ለግማሽ ሰዓት ያህል አቁሞ ነበር።”

“የለም አይደለም” አለ ጸሓፊው። “ለአሥራ አምስት ደቂቃዎች ብቻ ነበር የቆመው። ጥብቅ የሆነ የመነሻና የመድረሻ ሰዓት የማከበር ደንብ ነው ያለን። ለመሆኑ እርስዎ ለማወቅ የፈለጉት ምንድነው?”

ሮበርት በሸክም ከተሰጡት መታወቂያዎች ውስጥ አንዱን አወጣና ለጸሓፊው እያሳየ “እኔ ጋዜጠኛ ነኝ” አለው። “ትራቨል ኤንድ ሌዠር ለተባለው መጽሔት የስዊዘርላንድ አስጎብኚ አውቶቡሶች ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነጻፀር ምን ያህል ብቃት እንዳላቸው ለመጻፍ ነው የምፈልገው። ሾፌራችሁን ቃለ መጠይቅ ላደርግለት እችላለሁ?”

“መቼም ማራኪ የሆነ አንቀጽ እንደሚጽፉ አምናለሁ። እኛ ስዊሶች በማስገመበኘት ብቃታችን ከፍተኛ የሆነ ኩራትና ክብር ይሰማናል።”

“ይህ ኩራታችሁና ክብራችሁም ተገቢ ነው!” ሲል ሮበርት አረጋገጠለት።

“የኩባንያችን ስምስ በመጽሔቱ ላይ ይጠቀሳል?”

“በጥሩ ሁኔታ።”

ጸሓፊው ፈገግ አለና “በጣም ግሩም! ምንም ጉዳት የማያስከትል መሆኑ ይታየኛል” አለ።

“አሁን ላነጋግረው እችላለሁ? አለ?”

“ዛሬ የእረፍት ቀኑ ነው” አለና ጸሓፊው አንድ ወረቀት ላይ በእስክሪፕቶ ስምና አድራሻ ጫር ጫር አድርጎ ለሮበርት አቀበለው።

ሮበርት ማስታወሻ ወረቀቱን ተቀበለና አነበበው። ሐንስ ቤከር ማን። ከዙሪክ ከተማ አርባ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኝ ካፔል የተባለች መንደር ውስጥ ነዋሪ የሆነ።

“በነገራችን ላይ.....” አለ ሮበርት። “ለዚህ ጉዞ ምን ያህል ቲኬት እንደሸጣችሁ የሚያስረዳ ሪኮርድ ይኖራችሁ ይሆን?”

“በርግጥ አለን” አለና ጸሓፊው መዝገብ አውጥቶ ማገላበጥ ጀመረ። “አምን ይኸው። ዕለተ እሁድ፤ ሀንስ ቤከርማን ሰባት ተሳፋሪዎች፤ ኢይሼኩ መለሰተኛ አውቶበስ (ሚኒባስ)” ሲል ዘረዘረለት።

@BOOKALEM

"'ሰባት ያልታወቁ ተሳፋሪዎችና አንድ ሾፌር።' "ለመሆኑ የመንገደኞቹ የስም ዝርዝር ይኖራችሁ ይሆን?"

"ጌታዬ! ሰዎች ከመንገድ ይመጡና ቲኬት ገዝተው ተሳፍረው ይጓዛሉ። መንገደኞቻችንን የመታወቂያ ወረቀት እንጠይቃቸውም።"

በጣም ግሩም! አመሰግናለሁ!" አለና ሮበርት ወደ መውጫው በር ሲያመራ ጸሓፊው ከኋላው ጠራውና "ጽሑፍህ ሲወጣ የመጽሔቱን አንድ ኮፒ እንደምትልክልኝ ተስፋ አደርጋለሁ!" አለው።

"በሚገባ እልክላችኋለሁ" አለው ሮበርት።

የታሪኩ እንቆቅልሽ የሚጀመረው ከራሱ ከአውቶቡሱ ነው። ስለሆነም ሮበርት ታል ስትራስ ወደሚገኘው የኩባንያው አውቶቡስ የስምሪት ሥፍራ አመራ። ሥፍራውም ሲደርስ አውቶቡሶቹ በረድፍ ተደርድረዋል። ወደ ኡተንዶርፍ ሰባቱን ጐብኚዎች ያጓጓዘው አውቶቡስ ብርማና ቡናማ ቀለም የተቀባ አይቪኮ ሲሆን ገደላማና በረዷማ የሆነውን የአልፕስን ተራራ ለመዝለቅ የሚችል አነስ ያለ ተሽከርካሪ ነው። 'ለመሆኑ ሰባቱ ምስክሮች እነማን ናቸው? ወዴትስ ተሰወሩ?' ሮበርት ራሱን በራሱ እየጠየቀ ወደተከራያት መኪና አመራ።

የመንገድ ካርታውን አጥንቶ ምልክት ካደረገበት በኋላ መኪናውን አስነስቶ የአልፕስ ተራራ መነሻ ወደሆነችው ካፔል ከተማ ነጐደ። የዙሪክን ከተማ የከበቡትን ኮረብታዎች፤ የአልፕስ ተራራ መነሻ የሆኑትን ሰንሰለታማ ጉብታዎች፤ በልዩ ልዩ ሕብረ ቀለማት ያሸበረቀውን የአካባቢውን የተፈጥሮ ውበት እያደነቀ ለአንድ ሰዓት ያህል ከተጓዘ በኋላ ካፔል የተባለችው አነስተኛ መንደር ደረሰ። ትንሿ መንደር አንድ ቤተክርስቲያን፤ አንድ ሬስቶራንት፤ አንድ ፖስታ ቤትና በደርዘን የሚቆጠሩ በተንተን ብለው የሚታዩ የመኖሪያ ቤቶችን ስታካትት ዙሪያዋን በኰረብታዎች ተከባለች።

ሮበርት መኪናውን አቁሞ ሬስቶራንቱ ውስጥ ሲገባ አስተናጋጇ በሩ አካባቢ በጽዳት ሥራ ተጠምዳ አገኛት። "ጤና ይስጥልኝ ወይዘሪት። የአቶ ሐንስ ቤከርማን መኖሪያ ቤት ወዴት እንደሆነ ታውቂያለሽ?"

"እንዴታ!" አለችና አስተናጋጇ መንገዱን አመለከተችው።

ሮበርት ቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ሲደርስ ወደ ቀኝ ታጠፈና ቁልቁል መንገዱን ይዞ ከወረደ በኋላ አንድ ከድንጋይ የታነፀ ዘመናዊ ባለ ሁለት ፎቅ ህንፃ ፊት ለፊት መኪናውን አቁሞ ወደ ግቢው በር አመራ። በሩ ላይ የመጥሪያ ደወል ስላልነበረ በእጁ መቆርቆር ጀመረ።

አንዲት ወፈር ያለችና ሰሰ ጢም የሚታይባት ሴት ወይዘሮ በሩን ከፈተች።

"ስላስቸገርኩሽ አዝናለሁ። ሐንስ ቤከርማን ይኖር ይሆን?"

"ከእርሱ ምን ትፈልጋለህ?" አለች በጥርጣሬ እያየችው።

@BOOKALEM

ማራኪ የሆነ ፈገግታውን መገባትና የመታወቂያ ካርዱን አወጣ። "ወይዘሮ ቤከርማን መሆን አለብሽ። እኔ ለአንድ ታዋቂ መጽሔት ስለስዊስ የአውቶቡስ ሹፌሮች ብቃትና ችሎታ አንድ ዘገባ ለመጻፍ ስለምፈልግ ያንቺ ባለቤት ደግሞ በጣም ግሩም የሆነ ሪኮርድ እንዳለው ስለተጠቆምኩ ነው የመጣሁት።"

አሁን ገና ፊቷ በፈገግታ ፀዳል በራ። "አዎን የኔ ሐንስ የመጨረሻው ድንቅ ሾፌር ነው" አለችው።

"አዎን ሰው ሁሉ የሚነግረኝ ይህንኑ የባልሽን ችሎታ ነው ወይዘሮ ቤከርማን። አሁን ቃለ መጠይቅ ላደርግለት እችላለሁ?"

"ከኔው ሐንስ ጋር ቃለ መጠይቅ?" ስትል በጣም ተደነቀችና "ወደ ቤት ግባ። በጣም የሚያስደንቅ ነው። እባክህ ግባ!" ስትል ጋበዘችው።

ሮበርትን በጥንቃቄ የተያዘና የተደራጀ የእንግዳ ማረፊያ ክፍል ውስጥ አስገባችውና "እባክህ እዚህ ተቀመጥና ጠብቅ። ሐንስን አሁን ይዤው እመጣለሁ" ብላው ሄደች። የእንግዳ ማረፊያው ክፍል አጠር ያለ ጣሪያ ያለውና ጠቆር ያለ የእንጨት ወለል የተነጠፈበት ሲሆን ብዙም ውድ ባልሆኑ የቤት ዕቃዎች ተደራጅቷል። ከክፍሉ ራቅ ያለ ሥፍራ ላይ ከጥርብ ድንጋይ የተገነባ የእሳት ማንደጃ አለው።

ሮበርት ቆም ብሎ ስለሁኔታው ማንሰላሰል ጀመረ። "ሰዎች ከመንገድ ወጥተው ቲኬታቸውን ገዝተው ይጓዛሉ። ማንነታቸውን አንጠይቃቸውም።" ከዚህ በኋላ የምሄድበት ሥፍራ አይኖርም አለ በሐሳቡ። ያሁኑ ሙከራዬ ካልሠራ በጋዜጣ ማስታወቂያ አወጣለሁ።

አንድ ቀጭን ራስ በራ ሰው ብቅ አለ። ፊቱ እንደበሸተኛ የገረጣ ሲሆን ከአጠቃላይ ተክለ ሰውነቱ ጋር የማይመጣጠን ትልቅ ጢም አብቅሏል።

"እንደምን ዋልክ አቶ....." አለ ቤከርማን።

"ስሚዝ!" አለ ሮበርት የውሸት መታወቂያው ላይ የተጻፈውን ስም። በእርግጥ ካንተ ጋር ለመገናኘት እፈልግ ነበር።"

"ባለቤቴ ስለአውቶቡስ ሹፌሮች አንድ ዘገባ በማዘጋጀት ላይ መሆንህን ነግራኛለች" አለ በጀርመኖች የእንግሊዘኛ አነጋገር ስልት።

ሮበርት የአድናቆት ፈገግታ አሳየውና "አዎን በጣም ትክክል ነህ" አለው። የኔ መጽሔት አሳታሚ ስለስዊስ አውቶቡስ ሹፌሮች የማወቅ ከፍተኛ የሆነ ዝንባሌ አለው።

ቤከርማን የሮበርትን ንግግር ሥነ–ምግባር በጐደለው ሁኔታ አቋረጠው። "ለማወቅ የምትፈልገው እሁድ ዕለት ስለተከሰከሰው ነገር ነው። አይደለም?" አለው።

ሮበርት ሃፍረት የተሰማው ለመምሰል እየሞከረ "አዎን በእርግጥ ስለሱም ጉዳይ ለመነጋገር እፈልጋለሁ " አለ።

@BOOKALEM

"ታዲያ ለምን በቀጥታ እንደዚያ ብለህ አትናገርም? በል ተቀመጥ።"

"አመሰግናለሁ" አለና ሮበርት ወንበር ላይ ተቀመጠ።

"የሚጠጣ ነገር ላስተናግድህ ባለመቻሌ በጣም አዝናለሁ። ሺናፕስ እንኳ ቤታችን አናስቀምጥም" አለና ሆዱን መታ መታ እያደረገ....."አልሰር!" አለው ሮበርትን። "ሌላው ቀርቶ ሐኪሞች የሕመም ማስታገሻ እንኳ ሊሰጡኝ አልቻሉም። ለመድኀኒት አለርጂ ነኝ። ነገሬን በዚህ ላቁመው። አንተ ስለኔ ጤንነት ለመወያየት አልመጣህምና። አይደለም? ምንድነው የምትፈልገው?"

"እሁድ ዕለት ኡተንዶርፍ አካባቢ የአየር ንብረት መመርመሪያ ባሉን በተከሰከሰበት ወቅት በአውቶቡስህ ተሳፍረው ስለነበሩት ሰዎች ልጠይቅህ እፈልጋለሁ ።"

ሐንስ ቤከርማን ሮበርትን በመገረም ትኩር ብሎ ተመለከተው። "የአየር ንብረት ባሉን? የምን ባሉን ነው የምታወራው?"

"የተከሰከሰውን ባሉን....."

"የጠፈር መንኮራኩሩን ማለትህ ነው?"

አሁን ደግሞ የመገረሙና የመደናገሩ ተራ የሮበርት ሆነ። "የጠፈር መንኮራኩር?" ሲል ሮበርት ጠየቀ።

"አዎን በራሪው ዲስክ!" አለ ቤከርማን።

ሮበርት ቤከርማን የተናገራቸውን ቃላቶች አጣጥሞ ለመዋጥ የተወሰኑ ደቂቃዎች ወሰደበት። "በራሪ ሳህን (ዲስክ) የመሰለ ነገር አየሁ ነው የምትለው?"

"እንዴታ! የአብራሪዎቹን ሙት አካል እንደያዘ።"

የጄነራል ሒሊያርድ ንግግር ትዝ አለው። "ትናንት በሰዊስ የአልፕስ ተራራዎች አካባቢ አንድ የአየር ንብረት ባሉን ወድቆ ተከስክሷል። በውስጡም እጅግ በጣም ምሥጢራዊ የሆኑ መሣሪያዎች ለሙከራ ተገጥመውበታል።"

ሮበርት በተቻለው መጠን ራሱን ለማረጋጋት ሞከረ። "ሚስተር ቤከርማን! በእርግጥ ያየህው ነገር በራሪ ዲስክ ነው?"

"በእርግጥ እሱን ነው። ዮፎ ወይም ዩ.ኤፍ.ኦ. እያሉ የሚጠሩትን።"

"እናም በውስጡ የሞቱ ሰዎች ነበሩበት?"

"ሰዎች አይደሉም። የሆኑ "ፍጡራን" ናቸው። ስለነሱ ለመግለጽ በጣም ያዳግተኛል። ቤከርማን የተመለከተው ነገር ትዝታው መጣበትና ሰውነቱን አንቀጠቀጠው። አካላቸው በጣም ትንንሽ ሲሆን እንግዳ የሆኑ ትላልቅ ዐይኖች አሏቸው። ብረታማ ብር መልክ ያለው ልብስ ለብሰዋል። እጅግ አሸባሪ የሆነ ትዕይንት ነበር።"

ሮበርት አዕምሮው እየተበጠበጠ ነበር የሚያዳምጠው። "ለመሆኑ መንገደኞችህ ይህንን ነገር ተመልክተዋል?"

@BOOKALEM

“አዎን ተመልከተዋል። ሁላችንም ተመልከተናል። ሥፍራው ላይ ለአሥራ አምስት ደቂቃዎች አውቶቡሱን አቁሜ ስለነበር ተሳፋሪዎቹ ብዙ እንዲቆዩ ቢፈልጉም ኩባንያችን ሰዓትን በተመለከተ ጥብቅ የሆነ ደምብ ስላለው አልቻልኩም።”

ሮበርት ጥያቄውን ከመሰንዘሩ በፊት መልሱ ምን ሊሆን እንደሚችል ቢያውቀውም ከመጠየቅ አልታቀበም። “አቶ ቤከር ማን! መንገደኞቹን ታውቃቸዋለህ?”

“እኔ የአውቶቡስ ሾፌር ነኝ። መንገደኞቹ ደግሞ ዙሪክ ውስጥ ቲኬት ገዝተው ተሳፈሩ። ከዚያ ወደ ደቡብ-ምዕራብ ኢንተርላከንና ስሜን-ምዕራብ በርን የጉብኝት ጉዟችንን ቀጠልን። በርን ከተማ ስንደርስ መንገደኞቼ ተበታትነዋል። አልያም ወደ ዙሪክ ተመልሰዋል። ማንም ስሙን አልተናገረም።”

ሮበርት በጣም ተጨንቆ “እንዳቸውን እንኳ ለመለየትና ለማስታወስ አትችልም?” ሲል ጠየቀው።

ሾፌሩ ጥቂት ጊዜ ያህል አሰበና.....“ደህና! አለ። በጉዞው ላይ ምንም ዐይነት ህፃናት እንዳልነበሩ ላስረዳህ እችላለሁ። ትላልቅ ሰዎች ብቻ።”

“ሰዎች ብቻ?”

አሁንም ቤከርማን ጥቂት አሰበና.....“የለም! የለም! አንዲት ሴት ነበረች” አለ ቤከርማን።

‘በጣም አስደንጋጭ ጉዳይ። ከጅምሩስ ይህን ግዳጅ ለመቀበል ለምን ተስማማሁ?’ አለ ሮበርት በሐሳቡ።

“አቶ ቤከርማን! አንድ የቱሪስቶች ቡድን ዙሪክ ውስጥ ባንተ አውቶቡስ ተሳፍረው የጉብኝት ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ከዚያም በርን ከተማ ስትደርሱ ቱሪስቶቹ ከአውቶቡሱ ወርደው ተበታተኑ ነው የምትለኝ?”

“አዎን። ትክክለኛው ጉዳይ ይህ ነው አቶ ስሚዝ።”

“ስለመንገደኞቹ የምታስታውሰው ምንም ነገር የለም? ያደረጉት ወይም የተናገሩት?”

“አየህ ሚስተር ስሚዝ! አንድ ሰው እንደዚያ ጀርመናዊ የሆነ ችግር ካልፈጠረ በስተቀር ልታተኩርበት አትችልም።”

ሮበርት ፀጥ ብሎ ተቀመጠና “የምን ጀርመን?” ሲል ጠየቀ።

“ከጀርመኑ በስተቀር መንገደኞቹ በሙሉ በራሪውን ዲስክና በውስጡ የነበሩትን ፍጡራን በማየታቸው በከፍተኛ ስሜት ተውጠው ነበር። ጀርመናዊው ግን በፍጥነት ተነስተን መሄድ እንዳለብን ምክንያቱም በርን ከተማ በማግስቱ ዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለሚሰጠው ሌክቸር መዘጋጀት እንዳለበት ሲወተውት ነበር።”

‘ተጀመረ.....’ “ስለ ሰውዬው የምታስታውሰው ነገር አለ?”

“የለም።”

@BOOKALEM

"በአጠቃላይ ምንም አታስታውስም?"

"ጥቁር ካፖርት ለብሶ ነበር።"

"አቶ ቤከርማን አንድ ውለታ እንድትውልልኝ እፈልጋለሁ ። ከኔ ጋር ወደ ኡተንዶርፍ ብትጓዝስ?"

"ይህ የእረፍት ቀኔ ነው። ሥራ በጣም....."

"በደስታ እከፍልሃለሁ።"

ቤከርማን ማሰብ ጀመረ። 'ለምን አልሄድም? በመኪና ለመጓዝ ቀኑም ደስ የሚል ነው። አይደለም?'

ውቦቹን የኢመንዝ፣ ሜከንና ሉዛን መንደሮችን እያቋረጡ ወደ ደቡብ ተጓዙ። መንገድ ላይ የሚታየው የተፈጥሮ ውበት ትንፋሽ የሚያሳጥር አድናቆት ቢያሳድርም በሮበርት አዕምሮ ውስጥ ግን ሌሎች ብዙ ጉዳዮች ነበሩ። ሳርነን እና ብሩኒግ የተባሉ መንደሮችን አቋርጠው እንደተጓዙ "ምን ያህል ይቀረናል?" አለ ሮበርት።

"ቶሎ እንደርሳለን" ሲል ቤከርማን ቃል ገባለት። "የሚቀጥለው ከተማ ቱን ይባላል። እሱን አለፍ ካልን ደረስን ማለት ነው።"

የሮበርት ልብ መዝለል ጀመረ። አንድ ከግምት በላይ ስለሆነ ነገር ከሌላ ሥርዓተ–ከዋክብት ዓለም ስለመጡ ያልታወቁ ጉብኚዎች ሊመሰክር መቃረቡ ተሰማው።

ቱን ከተማን አቋርጠው ትንሽ እንደተጓዙ ቤከርማን ወደ አንድ አቅጣጫ በእጁ አመለከተና....."እዚያ አካባቢ ነው!" ሲል ተናገረ።

ሮበርት መኪናውን ቀዝቀዝ አደረገና ከመንገድ ዳር አቆማት።

"አውራ ጎዳናውን ተሻግሮ ከዛፎቹ በስተኋላ!" ሲል ቤከርማን ተናገረ። ሮበርት በውስጡ የመጓጓትና የመነሳሳት ስሜት ተሰማው። "እስቲ እንመልከት!" አለና መንዳቱን ጀመረ።

አንድ የጭነት መኪና አሳልፈው መንገዱን ከተሻገሩ በኋላ ሮበርት ሾፌሩን ተከትሎ ዛፎች ወዳሉበት ከፍ ያለ ሥፍራ አመራ።

ከሥፍራው ሲደርሱ ፊታቸው የተጋደመው የአየር ንብረት ባሉን ክስካሽ ብቻ ነበር!

@BOOKALEM

‘በጣም እያረጀሁ መጣሁ ማለት ነው። ለዚህ በራሪ ዲስክ ለሚባል ተረት ልታለል ትንሽ ነበር የቀረኝ’ አለ ሮበርት በሐሳቡ።

ሐንስ ቤከርማን እጅግ በጣም ግራ ተጋብቶ ፊቱ የተጋደመውን ብረት መሰል ነገር ትኩር ብሎ ተመለከተና “ይህ አይደለም!” ሲል ተናገረ።

“ይህ አይደለም?” አለ ሮበርት ደገመና።

ቤከርማን ራሱን እየነቀነቀ “ትናንት እዚህ ነበር” አለ።

“ትንንሾቹ አረንጓዴ ሰዎችህ ምናልባት መልሰው አብርረውት እንዳይሆን” አለ ሮበርት በማፌዝ።

“የለም! የለም! ሁለቱም ትንሽ ሞተው ነበር።”

“ትንሽ” ሞተው ነበር!”

‘ይህ ደግሞ ግዳጄን በጣም ያሳምረዋል። የደረስኩበት ፍንጭ ቢኖር’ አለ ሮበርት በሐሳቡ ‘የጠፈር መንኮራኩር ያየ አንድ ወፈፌ ሽማግሌ ነው።’

ሮበርት ወደ ባሉኑ ተጠግቶ በጥንቃቄ ይመረምረው ጀመር።

ዙሪያ ክቡ አሥራ አራት ጫማ ሆኖ ከአልሙኒየም የተሠራ ከረጢት መሰል ቅርጽ ሲኖረው መሬት ላይ በተከሰከሰበት ወቅት ጠርዙ ተሰንጥቆ ተከፍቷል። ውስጡ የነበሩት መሣሪያዎች በሙሉ ጄነራል ሒሊያርድ እንደተናገረው ተነቃቅለው ተወስደዋል። ‘በውስጡ ስለነበረው መሣሪያ ጠቃሚነት ከብደት ልሰጠው አልቻልኩም’ አለ ሮበርት በሐሳቡ።

ሮበርት በዝናብ ውሃ በበሰበሰው ሳር ውስጥ ጫማውን እያራሰ ምናልባት አንድ ጭብጥ ባገኝ ብሎ ዙሪያውን መዞር ጀመረ። ግን ምንም ፍንጭ አላገኘም። ባለፉት ዓመታት ካያቸው የአየር ባሉኖች ጋር ምንም ልዩነት የሌለው ፍጹም ተመሳሳይ ነበር።

ሽማግሌው ሰውዬ ደግሞ የሚበገር አልሆነም። በጀርመናዊ የግትርነት ፀባዩ ድርቅ ብሎ ይሚገት ጀመር። “አየህ? እነዚያ የጠፈር ፍጡራን ምንም የሚሰናቸው ነገር የለም። ልክ እንደዚህ አስመሰለውት ነው” አለ። ካሁን በኋላ እዚህ ምንም የምሠራው ጉዳይ የለም’ አለና ሮበርት ለመሄድ ፊቱን ዘወር አደረገና እንደገና ተመለሰ። አንድ ሐሳብ ጭንቅላቱን መታው። “ከአንደኛው ጠርዝ በኩል ብድግ አድርግልኝ!” አለው ቤከርማንን።

“እንዳነሳው ትፈልጋለህ?” አለ ቤከርማን እየተገረመ።

“አዎን።”

@BOOKALEM

ቤከርማን ትከሻውን በግዴለሽነት ከፍ ዝቅ አደረገና ከአንድ በኩል ቀላል ክብደት ያለውን ብረት ብድግ ሲያደርግ ሮበርት ደግሞ ከሌላው ማዕዘን በኩል ወደ ላይ አነሳው።

ሮበርት ቀላሉን የአልሙኒየም ብረት ከራሱ በላይ ከፍ አድርጎ ያዘና ወደ መኻል ተራምዶ ገባ። "ባሉኑ ያረፈበት መሬት እርጥብ ነው!" ሲል ሮበርት ጮክ ብሎ ተናገረ።

"እዎን ትላንት ሙሉ ቀን ሲዘንብ ነው የዋለው። ቦታው በሙሉ እርጥብ ነው!" ሲል ሽማግሌው ሾፌር መልስ ሰጠ።

ሮበርት ከባሉኑ ስር ተንሷቆ ወጣ። መንፈሱ በሐሳብ ተውጧል። ባሉኑን የሸፈነው መሬት ደረቅ መሆን ነበረበት። ፓይለቱ ምን ነበር ያለው? "'የተቃወሰ አየር። እሁድ ፀሓያማ።" (ባሉኑ የወደቀበት ዕለት።)'

'ዛሬ ሙሉ ቀን ሲዘንብ ውሎ ምሽት ላይ ገለጠ። እዚህ አገር የሚያስፈልግህ ሰዓት ሳይሆን የዝናብ መጠን መለኪያ መሣሪያ ነው።'

"ምን?"

"በራሪውን ዲስክ ያየህ ዕለት አየሩ እንዴት ነበር?"

ቤከርማን ጥቂት አሰብ አደረገና "ግሩም ተሲያት ነበር" አለ።

"ፀሓያማ?"

"እዎን ፀሓያማ።"

"ትናንት ግን ሙሉ ቀን ሲዘንብ ነበር?"

"እዎን!" አለ ቤከርማን ግራ እየተጋባ።

"ስለዚህ....." አለ ሮበርት። "ስለዚህ ባሉኑ ትናንት ሙሉ ሌሊት እዚህ ቢሆን ኖሮ ከሥሩ የነበረው መሬት ደረቅ መሆን ነበረበት። ወይም ደግሞ በውጭው ዝናብ ምክንያት መጠነኛ እርጥበት ብቻ ሊኖረው ሲገባ አሁን ግን ሙሉ ለሙሉ በስብሷል።"

"ምን ማለትህ እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም" አለ ቤከርማን።

"የሆነ ሰው ዝናቡ መዝነብ ከጀመረ በኋላ አንተ ያየህውን ነገር አንስቶ ይህንን ባሉን በምትኩ አስቀምጧል ማለት ነው።"

"እንደዚህ ዐይነቱን የእብደት ሥራ ማን ሊፈጽም ይችላል?"

'ይህ የሕልም ወይንም የእብደት ሥራ አይደለም' አለ ሮበርት በሐሳቡ። የስዊስ መንግሥት አንዳንድ አትኩሮ ተመልካቾችን ለማሳሳት ሲል ይህንን ባሉን ተክቶት ሊሆን ይችላል። የመጀመሪያው ሽፋን የሐሰት መረጃ መስጠት ነው። ሮበርት በራሱ ሞኝነት ራሱን እየተራገመ በረጠበው ሳር ላይ ወዲህ ወዲያ እያለ አካባቢውን በደምብ ይመረምር ጀመረ።

ሐንስ ቤከርማን ሮበርትን በጥርጣሬ እየተመለከተው "ለመሆኑ ለየትኛው መጽሔት ነው እጽፋለሁ ያልከው?" ሲል ጠየቀው።

@BOOKALEM

“ጉዞና የእረፍት ጊዜ ለተሰኘው።”

“እ! ልክ ያኛው ግለሰብ እንዳደረገው ፎቶግራፍ ታነሳኛለህ ብዬ እገምታለሁ” አለ ቤከርማን ፊቱ በፈገግታ ፀዳል እየበራ።

“ምን?” አለ ሮበርት ደንግጦ።

“ምስላችንን እንዳነሳው ፎቶግራፍ አንሺ።”

ሮበርት ባለበት ሥፍራ ደንዝዞ ቀረ። “ስለማን ነው የምታወራኝ?”

“ስለዚያ ፎቶግራፍ አንሺ ግለሰብ። የጠፈር መንኮራኩሩ ስብርባሪ አጠገብ ፎቶ ስላነሳን ሰውዬ። ከመንገደኞቹ ውስጥ ደግሞ ሌሎች ጥቂቶችም ካሜራ የያዙ ነበሩ።”

“አንድ ጊዜ!” አለ ሮበርት ቀሰ ብሎ። አንድ ሰው በተከሰከሰው ያልታወቀ በራሪ ነገር ፊት ለፊት ፎቶ አነሳን ነው የምትለው?”

“አዎን። እሱን ነው የምነግርህ።”

“እናም ለእያንዳንዳችሁ ፎቶውን እንደሚልክ ቃል ገባላችሁ?”

“በትክክል።”

“ስለዚህ ስማችሁንና አድራሻችሁን ወስዷል ማለት ነዋ?”

“ያለዚያማ እንዴት አድርጎ ሊልክልን ይችላል?”

‘አንተ ዕድለኛ የውሻ ልጅ!’” አለ ሮበርት ራሱን መላ አካላቱ በደስታ እየጋለ። የማይቻለው አስቸጋሪ ተልዕኮ በድንገት ወደ ለስላሳ ኬክነት ተለወጠ። ካሁን በኋላ ማደን ያለበት ሰባት ሰዎችን ሳይሆን የሰባት ሰዎችን ስምና አድራሻ የያዘ አንድ ፎቶግራፍ አንሺ ብቻ ነው።

“ለምንድን ነው ቀደም ብለህ ይህንን ያልነገርከኝ ሚስተር ቤከርማን?”

“የጠየከኝ ስላሳፈርኳቸው መንገደኞች ብቻ ነው።”

“ፎቶ አንሺው ግለሰብ ከመንገደኞችህ አንዱ አልነበረምን?”

ቤከርማን አንገቱን በአሉታ እየነቀነቀና በእጁ ከመንገዱ ባሻገር እያመለከተ.....“አይደለም!” አለ። “መኪናው እዚያ ማዶ ተበላሽታ ቆማ ነበር። አንድ የተበላሸ መኪና መጐተቻ ካሚዎን እየጐተተ ሊወስዳት ሲጀምር ይህ ድንገተኛ የመከስከስ አደጋ ተፈጠረ። ሰውዬውም የደረሰው አደጋ ምን እንደሆነ ለማወቅ እየሮጠ መጣ። ነገሩ ምን እንደሆነ በተመለከተም ጊዜ ተመልሶ እየሮጠ ወደ መኪናው ሄደና ካሜራውን ይዞ እየበረረ ተመልሶ መጥቶ ከተከሰከሰው በራሪ ዲስክ ፊት ለፊት እንድንደረደር ጠየቀን።”

“ለመሆኑ ይህ ፎቶግራፍ አንሺ ሰሙን ነግሯችኋል?”

“አልነገረንም።”

“ስለሰውየው ምን የምታስታውሰው ነገር አለ?”

ቤከርማን ለጥቂት ሴኮንዶች አንሰላሰለና “የውጭ አገር ዜጋ ነው። ምናልባት አሜሪካዊ ወይንም እንግሊዛዊ ሳይሆን አይቀርም” አለ።

@BOOKALEM

"አንድ ጎታች ካሚዎን መኪናውን እየጎተተለት ነበር ነው ያልከኝ?"

"በትክክል።"

"ጎታቹ ካሚዎን ወዴት እንዳመራ ታስታውሳለህ?"

"በስተሰሜን በርን ወደ ተባለች ከተማ ነው እየጐተተ የወሰደለት። ቱን ቅርብ ነበረች። ነገር ግን ቱን ውስጥ ያሉት ጋራጮች አሁድ ዕለት በሙሉ ዝግ ነበሩ።"

ሮበርት በደስታ ፈገግ አለና....."አመሰግናለሁ ሚስተር ቤከርማን፣ እጅግ በጣም ነው የረዳህኝ" አለው።

"ዘገባህን ጽፈህ ስትጨርስ አንድ ኮፒ እንደምትልክልኝ አትረሳም አይደለም?" አለ ቤከርማን።

"በፍጹም አልረሳም" አለና ሮበርት የተዋዋልንው የድካምህ ዋጋ ይኸውልህ። በተጨማሪም አንድ መቶ ማርክ ጉርሻ ይኸው ውሰድ። አሁን መኖሪያ ቤትህ አደርስሃለሁ።"

ሁለቱም አካባቢውን ለቀው ወደ መኪናቸው አመሩ። መኪናዋ አጠገብ እንደደረሱ ቤከርማን በሩን መክፈት ጀመረና ወደ ሮበርት ዘወር ብሎ....."አንተ በጣም ለጋስ ሰው ነህ" ብሎ ካመሰገነው በኋላ ከኪሱ አንድ የሲጋራ መለኪያ ላይተር የምታክል የሬክታንግል ቅርጽ ያላት ከሪስታል የያዘች ብረት ነገር አውጥቶ ለሮበርት አቀበለው።

"ምንድን ነው?" አለ ሮበርት።

"በራሪውን ዲስክ ተመልክተን ወደ አውቶቡሳችን ከመመለሳችን በፊት ከመሬት ላይ ያገኘሁት ነገር ነው።"

ሮበርት ከዚህ በፊት ዐይቶት የማያውቀውን እንግዳ ዕቃ በትኩረት ይመረምረው ጀመር። ክብደቱ እንደወረቀት የቀለለ ሲሆን አሸዋማ ቀለም ነበረው። ከአንድ በኩል ሻካራማ አካላቱ ተገጣሚ ነገር እንደነበረው ያመለክታል። "በባሉኑ ውስጥ የነበረ መሣሪያ ነው? ወይስ ከበራሪው አካል የወደቀ ነገር?"

ቤከር ማን ገንዘቡን ኪሱ እያጨቀ "አንድ ዕድል ሊያስገኝልህ ይችላል። ለኔ በእርግጥ ሠርቶልኛል" አለና ፈገግ አለ።

አሁን አስቸጋሪውን ጥያቄ ራሱን የሚጠይቅበት ጊዜ ነው።

'ዩ.ኤፍ.አ የሚባሉ ከሌላ ዓለም በሚመጡ በራሪ ዲስኮች መኖር በእርግጥ አምናለሁኝ?' በራሪ ዲስኮችን አየን፤ አስደናቂ የሆነ ገጠመኝ ደረሰብን ስለሚሉ አንዳንድ ሰዎች በየጋዜጦቹ አስደናቂ የሆኑ ዘገባዎችን አንብቧል። ሆኖም ግን እንደዚህ ዐይነት ሰዎችን የመገናኛ ብዙሃንን ዝና የሚሹ ወይንም ራሳቸውን ለሥነ-ልቡና ሕክምና ጠበብት አሳልፈው የሰጡ በሽተኞች ናቸው ይል ነበር። ነገር ግን ባለፉት ዓመታት በቀላሉ ሊታለፉ የማይችሉ የበራሪ ዲስኮች ዕይታ ዘገባዎች ቀርበዋል። የነዚህ ያልታወቁ በራሪ ነገሮች ዕይታ ሪፖርቶች በጠፈርተኞች፤ በአየር

@BOOKALEM

ኃይል ፓይለቶች፤ ተአማኒነት ባላቸው ግለሰቦች፤ እንዲሁም በፓሊስ ባለሥልጣናት ጭምር ከመቅረባቸውም በላይ በሮዝዌል ኒው ሜክሲኮ የአንድ በራሪ ዲስክ ወድቆ መከሰከሰና በውስጡም የአብራሪዎቹ በድን አካል መገኘትን የሚገልጽ አሸባሪ የሆነ ዘገባም ነበር። የአሜሪካ መንግሥትም ማስረጃውን ሁሉ በምሥጢር ማስወገዱ ይነገራል።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ፓይለቶች ያልታወቁ በራሪ ነገሮችን መመልከታቸውንና እነሱም በላያቸው ላይ በከፍተኛ ፍጥነት እየበረሩ መሰወራቸውን አመልክተዋል። የአንድ ከተማ ነዋሪዎች በሙሉ ከሌላ ዓለም የመጡ በራሪ የጠፈር መንኮራኩሮችን ማየታቸውን መስክረዋል።

'በርግጥ ከሌላ ሥርዓተ–ከዋክብት (ሶላር ሲስተም) በበራሪ ዲስኮች የሚመጡ ያልታወቁ ፍጡራን ቢኖሩስ? ዓለማችንን እንዴት ያደርጓት ይሆን?'

በአንድ በኩል ደግሞ 'ይህ ቤከርማን የተባለ ሰው ለፍላፊ የአዕምሮ በሽተኛ ወይም ወፈፌ መሆን አለበት' ሲል አሰበ። 'በርግጥ ተከስክሶ የተመለከተው ነገር የአየር ንብረት ባሉን መሆን አለበት' ብሎ ተስፋ ያደርጋል። የቤከርማን ታሪክ የማይታመን ቢመስልም ሮበርትን የሚከነክኑት ነገሮች አሉ። ነገሩ የአየር ንብረት ባሉን ከሆነ ከንጋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ወደ ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ተጠርቶ ምስክሮቹን በአስቸኳይ እንዲፈልግ ለምን ታዘዘ? ነገሩ የማስመሰያ ወይንም የሸፋን ታሪክ ይኖረው ይሆን? ከሆነስ ለምን?

ምዕራፍ ዘጠኝ

በዚሁ ዕለት ረፋዱ ላይ በስዊስ መንግሥት የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስትር ሕንፃ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ጋዜጣዊ መግለጫ እየተሰጠ ነበር። አዳራሹ ውስጥ ከሃምሳ የሚበልጡ ጋዜጠኞች ከመታጨቃቸውም በላይ እውጭ ኮሪደሩ ውስጥ ደግሞ አያሌ የጋዜጠኛ መንጋ ተከማችቷል። የቴሌቪዥን የራዲዮና የጋዜጣ ወኪሎች ከፊልም ማንሻና ከድምጽ መቅጃ መሣሪያዎቻቸው ጋር በተጠንቀቅ ሲገኙ ሁሉም በአንድነት የሚያወሩ ይመስሉ ነበር።

"የአየር ንብረት መመርመሪያ ባሉን አይደለም የሚል ዘገባ ሰምተናል። ያልታወቀ የጠፈር መንኮራኩር ነው የሚባለው እውነት ነው?"

"በመንኰራኩሩ ውስጥ ሞተው የተገኙ የሌላ ዓለም ፍጡራን አሉ የሚባለው እውነት ነው? ከፍጡራኑ ውስጥ በሕይወት የተገኙ አሉ?"

"መንግሥት እውነተኛውን ዜና ከሕዝብ ጆሮ ለመደበቅ ይሞክራል?"

የስዊስ መንግሥት ቃል አቀባይ ሁካታውን ለማስቆም ድምጹን ከፍ አድርጉ "ክብሯንና ክቡራት! አንድ በጣም ቀላል የሆነ አለመግባባት አለ። ብዙ

@BOOKALEM

ጊዜ የስልክ ጥሪዎች ይደርሱናል። ሰዎች በራሪ ኮከቦችን ይመለከታሉ። ታዲያ ስላልታወቁ በራሪ ዲስኮች እይታ የሚቀርቡ ዘገባዎች ሳይታወቁ ወይም ሳይረጋገጡ መቅረታቸው አያስደንቅም? ምናልባት ይህን የስልክ ጥሪ ያደረገው ሰው የተመለከተው ነገር ያ.በ.አ. (ያልታወቀ በራሪ አካል) ነው ብሎ አምኖ ሊሆን ይችላል። እውነታው ግን በተጠቀሰው ሥፍራ የተከሰከሰው ነገር የአየር ንብረት መመርመሪያ ባሉን መሆኑ ብቻ ነው። ወደ አደጋው ሥፍራም ሄዶ በዐይን ተመልክቶ ለማረጋገጥ እንዲቻል አስፈላጊው የመጓጓዣ አውቶቡስ የተዘጋጀ ስለሆነ እባካችሁ ሁላችሁም ብትከተሉኝ።" ከአሥራ አምስት ደቂቃዎች በኋላ በሁለት አውቶቡሶች የታጨቁ ጋዜጠኞችና የፊልም ማንሻ ካሜራዎች ወደ ኡተንዶርፍ ጉዞ ቀጠሉ። ከሥፍራው እንደደረሱ በዝናብ በራሰው ሜዳ ላይ ቆመው የተፈረካከሰውን ብረታማ ከረጢት ይመለከቱ ጀመር።

"እነሆ ይኸውና የበራሪ ዲስኩ እንቆቅልሽ!" አለ የዜና ወኪል (ቃል አቀባይ) የሆነው መኮንን። "ቬቬይ ከሚገኘው የአየር ጣቢያችን የተላከ ከመሆኑም በላይ እኛ እስከምናውቀው ድረስ ስላልታወቁ በራሪ ዲስኮች ወይንም ከሌላ ዓለም ስለሚመጡ ጐብኚዎች መንግሥታችን በበቂ ማስረጃ ሊያረጋግጥ የሚችለው ምንም ነገር የለም። በዚህ ጉዳይ ላይ በቂ የሆነ ማስረጃ ካገኘን ዜናውን በመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ይፋ እንደምናወጣ የመንግሥታችን ግልጽ የሆነ ፖሊሲ ነው። እንግዲህ ሌላ ጥያቄ ከሌለ.....።"

ምዕራፍ አሥር

ላንግሌይ ቨርጂኒያ የሚገኘው አሥራ ሰባተኛው የአውሮፕላን ማቆሚያ ሕንፃ (ሀንጋር) እጅግ በጣም ጥብቅ የሆነ የፀጥታ ጥበቃ እየተደረገለት ነው። ከውጭ አራት የታጠቁ የባሕር ኮማንዶ ወታደሮች የሕንፃውን ዙሪያ ሲጠብቁ ከውስጥ ደግሞ ሦስት የጦር ሰራዊት ከፍተኛ መኮንኖች በየስምንት ሰዓቱ እየተለዋወጡ ሀንጋሩ ውስጥ የሚገኝ አንድ የተዘጋ ክፍል ይጠብቃሉ። ግን አንዳችውም ምን እንደሚጠብቁ የሚያውቁት ነገር የለም። የተዘጋው ክፍል ውስጥ ከሚሠሩት ሳይንቲስቶችና ዶክተሮች ሌላ ይህን ክፍል ለመጐብኘት የተፈቀደላቸው ሦስት ጎብኚዎች ብቻ ነበሩ። አራተኛው እንግዳ ገና መድረሱ ሲሆን የፀጥታ ጥበቃ ኋላፊ በሆነው በጀነራል ፓከስተን አቀባበል ተደረገለት።

"ወደ አራዊት መሰብሰቢያ ሥፍራችን እንኳን ደህና መጡ።"

"ይህንን ሥፍራ ለማየት በጣም እፈልግ ነበር።"

"በመምጣትዎ በፍጹም አያዝኑም። እባክዎን በዚህ በኩል ይምጡ።"

@BOOKALEM

ከተዘጋው ቤት ውጭ ከረቂቅ ህዋሳት ሙሉ በሙሉ ነፃ የሆኑና መላ ሰውነትን ከላይ እስከታች የሚሸፍኑ አራት ነጫጭ ልብሶች ተሰቅለዋል።

"እባክዎን አንዱን ልብስ ይልበሱ።"

"መልካም!" አለና ጃኑስ አንዱን ቱታ አንስቶ አጠለቀው። ከመስተዋት በተሠራው ጭምብል ውስጥ ፊቱ ብቻ ይታያል። በጣም ትልልቅ የሆኑ ጫማዎች ተሰጡትና በራሱ ጫማ ላይ ደርቦ አጠለቃቸው። ከዚህ በኋላ ጃኑስ በጀነራሉ መሪነት ወደ መግቢያው በር ሲወሰድ የባሕር ኃይሉ ዘብ ወደ ጐን ራመድ አለና በሩን ለቀቀላቸው። ጀነራሉ በሩን ከፈተው።

ጃኑስ እንደገባ ከፍሉን መቃኘት ጀመረ። በከፍሉ መካከለኛ ሥፍራ ላይ አንድ የጠፈር መንኮራኩር አለ። ከሌላው ጥግ ደግሞ አንድ ነጭ የአስከሬን መመርመሪያ ጠረጴዛ ላይ ሁለት ከሌላ ዓለም የመጡ ፍጡራን አስከሬኖች ተጋድመው አንድ የሬሳ ምርመራ ጠቢብ እየመረመራቸው ነው።

ጀነራል ፓከስተን የጃኑስን ትኩረት ወደ መንኩራኩሩ ወሰደው።

"እዚህ ላይ ቃኚ ወይም ግልገል መንኮራኩር ነው ብለን የምንገምተውን በራሪ ዲስክ እየመረመርን ነው። ይሆች ግልገል መንኮራኩር ከዋናዋ እናት የጠፈር መንኮራኩር ጋር ግንኙነት የምታደርግበት መንገድ አለ ብለን እናምናለን።"

ሁለቱም ሰዎች በጣም ተጠግተው በራሪውን ዲስክ ይመለከቱ ጀመር። ሠላሳ አምስት ጫማ ዙሪያ ከብ ያለው፤ ውስጣዊ ከፍሉ በሉል ቅርጽ የተሠራና ጣሪያው ሊሰፋ የሚችል ሲሆን ልክ ማረፊያ መኝታ የሚመስሉ ሦስት ምቹ ወንበሮች አሉት። ግድግዳው በሙሉ በሚርገበገብ ብረታማ ሽፋን ተሸፍኗል። "እዚህ ውስጥ ምን እንደሆነ እንኳ ያላወቅንው ብዙ ነገር አለ!" ሲል ፓከስተን ተናገረ። "ቢሆንም ግን እስካሁን ብዙ አስደናቂ የሆኑ ነገሮችን ለማወቅ ችለናል።" ቀጠለና ጀነራሉ አንድ በስፋት የተዘረጋ የመቆጣጠሪያ መሣሪያ ቅንብር በእጁ እያመለከተ "ይህ የተያያዘና የተገናኘ ባለሰፊ ማዕዘን የመመልከቻ መሣሪያ ነው።

መሣሪያው ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ለመመልከት የሚያስችል ይመስላል። ሌላው ደግሞ የድምፆችን ምንነት ለማሳየት የሚያስችል መሣሪያ ሲሆን ገና በደምብ ልንነነዘበው ያልቻልንው የበረራ መቆጣጠሪያ መሣሪያ አለው። ይህም መሣሪያ በአንድ ዐይነት አሌክትሮ-መግነጢሳዊ ኃይል ይሠራል ብለን እናምናለን።"

"መንኮራኩሩ ላይ አንዳች ዐይነት የጦር መሣሪያ የለም?" ሲል ጃኑስ ጠየቀ።

ጀነራል ፓከስተን በሸንፈት እጆቹን አወናጨፈ። "እዚህ መንኮራኩር ውስጥ ሙሉ በሙሉ ልንረዳው ያልቻልንው ብዙ ነገር አለ።"

"የኃይል ምንጩስ ምንድነው?"

@BOOKALEM

"ከፍተኛው ግምታችን በተዘጋ ብረታማ ሳጥን ውስጥ የተቀመጠና ቅሪቱ ውሃ የሆነ ውሃውንም ወደ ሒይድሮጂን የኃይል ምንጭነት የሚለውጥ ባለአንድ አቶም ወይንም ሞኖ አቶሚክ ሒይድሮጂን የኃይል ምንጭ ይጠቀማል የሚል ነው። ይህ መንኮራኩር ይህን ሁሉ ተለዋዋጭ የሆነ የኃይል ምንጭ በመጠቀም ጠፈር (ሕዋው) አቋራጭ የሆነ በረራ ለማድረግ ይችላል። እዚህ መንኮራኩር ውስጥ ያለውን የተራቀቀ ቴክኖሎጂ ሙሉ በሙሉ ለመረዳትና ለመፍታት ብዙ ዓመታት ሊፈጅብን ይችላል። ሌላው ግራ የሚያጋባ ነገር ደግሞ ሁለቱ አብራሪዎች ወንበራቸው ላይ በደህንነት ቀበቶአቸው እንደታሰሩ ሲገኙ አንዳንድ መረጃዎች ደግሞ ሦስተኛው ወንበር ላይም ሌላ ተሳፋሪ እንደነበረበት ያመለክታሉ።"

"እንተ የምትለው....." አለ ጃኑስ በጣም ቀስ ብሎ። "ሌላ ሦስተኛ ያልተገኘ ፍጡር ወይም ተሳፋሪ ነበር ነው?" ሲል ጠየቀ።

"አዎን ልክ እንደሱ ነው የምለው።"

በመቀጠል ሁለቱ ሰዎች እንግዳ የሆኑት ከሌላ ዓለም የመጡ ፍጡራን ወደተጋደሙበት የአሰከሬን መመርመሪያ ጠረጴዛ አመሩ። ጃኑስ ቆም ብሎ ሁለቱን ፍጡራን በትኩረት መመልከት ጀመረ። ለሰው ልጅ እንደነዚህ ዐይነት ያልታወቁ እንግዳ ፍጡራን አሉ ብሎ መገመት እጅግ አስቸጋሪ ነው። የፍጡራኑ ግንባር ከተለመደው በላይ ትልቅ ሲሆን የራስ ቅላቸው ሙሉ በሙሉ ፀጉር የለሽ የሆነ በራ ነው። የጠረጴዛ ኳስ (ፒንግ ፖንግ) የመሰለ ቅንድብም ሆነ ሽፋፋል የሌለው ትልልቅ ዐይኖች አሏቸው።

የአንዱ ፍጡር እጅ በአደጋው የተቆረጠ ሲሆን ምንም ዐይነት የደም ምልክት የለበትም። ነገርግን አረንጓዴ ቀለም ያለው ፈሳሽ የሚተላለፍበት የደም ሰር ሲኖረው አብዛኛው ተንጠፍጥፎ ፈሷል።

"አረንጓዴ ፈሳሽ?" አለ ጃኑስ።

"አዎን!" አለ ዶክተሩ። ለጥቂት ጊዜ ሲያቅማማ ቆየና "ሕይወት ያላቸው የእጽዋት ዐይነት ፍጡራን ናቸው ብለን እናምናለን።"

"የእጽዋት ፍጡራን? ከልብህ ነው?"

"እሰቲ ይህንን ይመልከቱ!" አለና ዶክተሩ አንድ የአትክልት ማጠጫ የሆነ የውሃ ቆርቆሮ አነሳና በተቆረጠው እጅ ላይ ውሃ አንቆረቆረበት። ለተወሰኑ ደቂቃዎች ምንም አዲስ ነገር አልተፈጠረም። ከዚያም በድንገት አረንጓዴ ፈሳሽ ከተቆረጠው እጅ ጫፍ ላይ እየፈሰሰ ወጣና የእጅ ቅርጽ መያዝ ጀመረ።

ሁለቱ ሰዎች ተሸብረው ይመልከቱ ጀመር።

"እየሱስ! እነዚህ ሰዎች ሞተዋል ወይስ አልሞቱም?"

"ማራኪ የሆነ ጥያቄ ነው። ከሰብአዊ ፍጡራን አኳያ ሞተዋል ለማለት ይቻላል። ነገርግን ሞት የሚለውን ቃል ሁለቱም ፍጡራን ገና አላሟሉም። እንቅስቃሴ አልባ ሆነዋል ወይም ፈዘዋል አላለሁ።"

@BOOKALEM

ጃኑስ አሁንም አዲስ የበቀለውን እጅ እየተመለከተ ነው።

"ብዙ እጽዋት የተለያየ የማሰብ ችሎታ እንዳላቸው ያሳያሉ።"

"ያስባሉ?"

"አዎን! ራሳቸውን የሚከላከሉና የሚያስቡ የእጽዋት ዐይነቶችም አሉ" በማለት ዶክተሩ ንግግሩን ቀጠለ። "በአሁኑ ጊዜ በእጽዋት ላይ አስደናቂ የሆኑ ሙከራዎችንና ምርምሮችን በማድረግ ላይ ነን።"

"እነዚህን ሙከራዎች ለማየት እወዳለሁ" አለ ጃኑስ።

"በርግጥ ለማሳየት ደስተኛ ነኝ!" አለ ሳይንቲስቱ።

ግዙፉ የአረንጓዴ እጽዋት ቤተ ሙከራ ከዋሺንግተን ዲ.ሲ. ሠላሳ ማይልስ ርቀት ላይ በሚገኝ አንድ ግዙፍና ውስብስብ የመንግሥት ሕንፃ ውስጥ ሲገኝ ግድግዳው ላይ እንዲህ የሚል ጥቅስ ተሰቅሏል።

"ማፕልና ፈርን የተባሉት የእጽዋት ዝርያዎች ገና ያልተበላሹ ናቸው። ማሰብ ከጀመሩ ግን እነሱም መሳደብ፤ መራገምና መማል እንደሚጀምሩ አያጠራጥርም።" ራልፍ ዋልዶ ኤመርሰን። (ተፈጥሮ 1836)

የምርምር ማዕከሉ ኋላፊና የበላይ መሪ ፕሮፌሰር ራችማን የተሰማራበትን ሙያ የሚወድ ኮስታራ ሰው ሲሆን አነስተኛ ሪዝ አብቅሏል።

"እጽዋት ያስባሉ የሚለውን ጽንሰ–ሐሳብ ለማብቀል የመጀመሪያው ሰው ቻርለስ ዳርዊን ነበር። ሎተር በርባከ ደግሞ ከእጽዋት ጋር ግንኙነት ለመፍጠር በመቻል ተከታይ ሆነ።"

"ይህ በእውነት የሚሆን ነው ብለህ ታምናለህ?"

"የሚቻል እንደሆነ እናምናለን። ጆርጅ ዋሺንግተን ካርበር ከእጽዋት ጋር እጅግ የቀረበ ግንኙነት በመፍጠሩ በመቶ የሚቆጠሩ ውጤቶችን ሰጥተውታል። "አበቦችን ስነካ መጨረሻ የለሽነትን እነካለሁ። አበቦች ከሰው ልጅ መፈጠር እጅግ ብዙ ቀድመው የተፈጠሩ ከመሆናቸውም በላይ ከሰው ልጅ በኋላም ለብዙ ሚሊዮን ዓመታት መኖራቸውን ይቀጥላሉ.....።" ብሏል ካርቨር።"

ጃኑስ የማይቋቋሙት የሸቶ መዓዛ ያወደውን ግዙፍ አረንጓዴ የእጽዋት ቤት (ግሪን ሃውስ) ዙሪያውን ይቃኝ ጀመር። በእጽዋትና ማራኪ በሆኑ አበቦች ተሞልቷል።

"እዚህ ቤት ውስጥ ሁሉም ነገር ሕያው ነው!" አለ ፕሮፌሰር ራችማን። "እጽዋት ልክ እንሰሳት እንደሚያደርጉት ሁሉ ፍቅር፤ ጥላቻና ደስታ ይሰማቸዋል። ሰር ጃጋዲስ ቻንድራ ለሰው ልጅ ድምጽ ቅን መልስ መስጠት እንደሚችሉም አረጋግጧል።"

"የዚህ ዐይነት ነገርን አንድ ሰው እንዴት ማሳመን ይቻለዋል?" አለ ጃኑስ።

@BOOKALEM

“ይህንን ለማሳየት ደስተኛ ነኝ” አለና ፕሮፌሰር ራችማን በእጅዋት ወደተሸፈነ አንድ ሰፊ ጠረጴዛ አመራ። ከጠረጴዛው አጠገብ አንድ የፖሊግራፍ ማሺን ተቀምጧል። ራችማን አንዱን ኤሌክትሮድ አንስቶ ከተከሉ ጋር አያያዘው። የፖሊግራፉ አመልካች መርፌ እንቅስቃሴ አልባ ነበር። “ተመልከቱ!” አለ ፕሮፌሰሩ።

ወደ እጽዋቱ ዘንበል አለና “በጣም ውብ ነህ!” ሲል በለሰለሰ ድምፅ አንሾካሾከለት።

አመልካቹ መርፌ በጣም ዝግ ብሎ ሲንቀሳቀስ ጃኑስ አስተዋለ።

ፕሮፌሰር ራችማን በድንገት በከፍተኛ ድምፅ.....“አንተ አስቀያሚ ነህ! ልትሞት ነው! ትሰማኛለህ? መሞትህ ነው!” ሲል ጮኸበት።

ጠቋሚው መርፌ ተንቀጠቀጠና ቀጥ ብሎ ተነሳ።

“ያምላክ ያለህ! ይህንን አላምንም” አለ ጃኑስ።

“ይህ የተመለከቱት.....” አለ ፕሮፌሰር ራችማን “.....ከሰው ልጅ ጩኸት ወይንም ዋይታ ጋር አንድ ዐይነት ነው።

ናሺናል ሜጋዚን የተባለው መጽሔት ስለዚህ ሙከራ ተከታታይ እትሞችን አውጥቷል። አስደናቂ ከሆኑት ፍተሻዎች አንዱ በስድስት ተማሪዎች የተከናወነው ነበር። አንድ በሌሎች የማይታወቅ ተማሪ ተመረጠና ሁለት እጽዋት አንደኛው ከፖሊግራፍ ማሽን ጋር የተገናኘ ይዞ አንድ ክፍል ውስጥ ገባና ከፖሊግራፉ ጋር ያልተገናኘውን ተክል ሙሉ በሙሉ ደምስሶ ወይም በጣጥሶ ጣለው። ቀጥሎ ተራ በተራ ተማሪዎቹ በእጽዋቱ አጠገብ እንዲያልፉ ተደረገ። ልክ ጥፋተኛው ተማሪ ክፍሉ ውስጥ ሲገባ የፖሊግራፉ አመልካች ወደ ላይ ተወርውሮ ቀጥ አለ!”

“ይህ የማይቻል ነው።”

“ግን እውነት ነው። እንደዚሁም ደግሞ እጽዋት ለተለያዩ የሙዚቃ ቅኝቶች መልስ እንደሚሰጡም አረጋግጠናል።”

“ለተለያዩ የሙዚቃ ዐይነቶች?”

“አዎን። ዴንቨር በሚገኘው የቴምፐል ቡል ኮሌጅ በተደረገ ጥናት ጤናማ አበቦች በሦስት የተለያዩ የመስተዋት ሳጥኖች ውስጥ እንዲቀመጡ ተደረገና ፈጣን የሮክ ሙዚቃ በአንደኛው ሳጥን፣ የምሥራቅ ለስላሳ ስታር ሙዚቃ በሚቀጥለው ሳጥን እንዲንቀረቀርላቸው ተደረገና ሦስተኛው የመስታዋት ሳጥን ውስጥ ያሉት አበቦች ያለምንም ሙዚቃ ተተው። የሲ.ቢ.ያ ካሜራ ሠራተኞች የጊዜን ልዩነት የሚሳይ ፎቶግራፍ በማንሳት ይከታተሉት ነበር። በሁለተኛው ሳምንት መጨረሻ ላይ ለፈጣን ሮክ ሙዚቃ የተጋለጡት አበቦች ሲሞቱ ለስላሳ ሙዚቃ የተንቀረቀረላቸው አበቦች ቅጠላቸውና ግንዳቸው ወደ ሙዚቃው ምንጭ እየተመዘዘ በመምጣት እጅግ ተውበውና ደምቀው ሲፀድቁ ሙዚቃ

@BOOKALEM

ያልተደረገባቸው አበቦች ደግሞ የተለምዶውን አስተዳደግ አደጉ። ዋልተር አሮንካይት ጥቅምት 26 1970 ዓ.ም በዜና ፕሮግራሙ ላይ አሳይቶታል።"

"ተክሎች ንቃተ–ሕሊና አላቸው ነው የምትለው?"

"ይተነፍሳሉ፤ ይመገባሉ፤ ይዋለዳሉ፤ ሕመም ይሰማቸዋል እንዲሁም ራሳቸውን ከአደጋ ይከላከላሉ። ለምሳሌ አንዳንድ እጽዋት በዙሪያቸው ያለውን አፈር ለመመረዝና ተፎካካሪ እጽዋትን ለማጥፋት በተርፐኖች ይጠቀማሉ። አንዳንድ እጽዋት አልካላይድን በመጠቀም በነፍሳት ከመጠቃት ሲድኑ እንደዚሁም ፔሮምነስ በተባለ ዘዴ እርስ በእርሳቸው እንደሚገናኙ አረጋግጠናል።"

"አዎን ስለሱ ነገር ሰምቻለሁ" አለ ጃኑስ።

"አንዳንድ እጽዋት ሥጋ በሎች ናቸው። ለምሳሌ አንዳንድ የተክል ዐይነቶች ወንዴ ንቦችን ለማጥመድ ልክ ሴቴ ንቦችን ይመስሉና የነሱን ዐይነት ጠረን ያመነጫሉ።

ሌሎች እጽዋት ሴቴ በራሪ ነፍሳትን በመምሰል ወንዴዎቹን እያማለሉ በማምጣት እንዲነበኙዋቸውና "ፖለን" የተባለውን ዱቄት እንዲያነሱላቸው ያደርጋሉ። ሌሎች እጽዋት ደግሞ የበሰበሰ ሥጋ ዐይነት ጠረን በማመንጨት ዝንቦችን እየሳቡ ያመጣሉ።

ጃኑስ እያንዳንዷን ቃል በተመስጦ እያዳመጠ ነው።

"ሌይዲስ ፊገር የተባለው ባለሮዝ ቀለም ተክልም ንቦች በላዩ ላይ በሚያርፉበት ጊዜ ተወርውሮ የሚይዝ ከናፍር አለው። ብቸኛው የንቢቱ ማምለጫ መንገድ ከተክሉ ከንፈር በስተኋላ ያለ ጠባብ መተላለፊያ ሲሆን ንቢቱ በዚያ መንገድ ነጻ ለመሆን ስትታገል የፖለኑን ዱቄት እንድታነሳ ትገደዳለች። በሰሜናዊ ምሥራቅ ንፍቀ–ክበብ የሚበቅሉ አምስት ሺህ የተለያዩ ባሕርይና ዝርያ ያላቸው እጽዋት አሉ። ሕይወት ያላቸው እጽዋት የማስተዋል ችሎታ እንዳላቸው በተደጋጋሚ ተረጋግጧል።"

ጃኑስ በሐሳብ እየነጐደ ነበር። '.....እናም ያልተገኘው የሌላ ዓለም ፍጡር የሆነ ቦታ አለ ማለት ነው።'

@BOOKALEM

ምዕራፍ ኢሥራ አንድ

ሥስተኛ ቀን

በርን ረቡዕ ጥቅምት ኢሥራ ሰባት

ለሮበርት ተወዳጅ ከሆኑ ከተሞች አንዲ በርን ነች። በውብ ሐውልቶች የተሞላችና በኢሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን በተሠሩ ሕንፃዎች የታጀበች እፀ-ብ ድንቅ ከተማ ከመሆኗም በላይ በአንድ ወቅት የስዊዘርላንድ ዋና ከተማም ነበረች። ሮበርት 'መንግዱን የሞሉት ተሽከርካሪዎች ቀለም አረንጓዴ መሆን ከገንዘብ ቀለም ጋር ተዛምዶ ይኖረው ይሆን?' እያለ ይደነቃል። ሮበርት የበርን ከተማ ነዋሪዎችን ከሌላው የስዊዘርላንድ ክልል የበለጠ ተግባቢዎች፤ በጥንቃቄ የሚንቀሳቀሱ፤ በዝግታ የሚናገሩና በአጠቃላይ ፀጥተኞች ሆነው ነው ያገኛቸው። ባለፉት ጊዜያት በተደጋጋሚ በርን ውስጥ ከስዊስ የፀጥታ አገልግሎት ጋር ዌሰን ሆስ ፕላዝ በተባለ ቦታ ከዋናው መሥሪያ ቤት ውጭ ሠርቷል። በዚያም ውስጥ ሊረዱት የሚችሉ ወዳጆችን አፍርቷል። የተሰጠው መመሪያ ግን ግልጽ ነው። ግራ የሚያጋባ ግልጽ።

ሮበርት የተበላሸውን መኪና የነተሎውን ጋራዥ ለማግኘት ኢሥራ አምስት የስልክ ጥሪዎች ማድረግን ጠይቆታል። ፍሪበርስትራስ በተባለ ቦታ የሚገኝና ፍሪትዝ ማንዴል በተባለ መካኒክ ባለንብረትነት የተያዘ ጋራዥ ነው። ማንዴል በሠላሳዎቹ መጨረሻ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ፊቱ በብጉር የተጠበሰ ከመሆኑም በላይ አካለ ቀጭንና በቢራ የተንዘረጠጠ ቦርጭ ያለው ሰው ነው። ሮበርት በደረሰበት ሰዓት ሰውዬው በግሪስ ማጠጫው ጉድጓድ ውስጥ ሆኖ ሥራውን እየሠራ ነበር።

"እንደምን አረፈድክ!" ሲል ሮበርት ተጣራ።

ማንዴል ቀጥ አለና "እንደምን ዋልክ ምን ልርዳህ?" አለ።

"እሁድ ዕለት ስለሳብከው መኪና ለማወቅ እፈልጋለሁ ።"

"ይቺን ሥራ እስክጨርስ ትንሽ ደቂቃ።" ከኢሥር ደቂቃ በኋላ ፍሪትዝ ማንዴል በቁሻሻ ጨርቅ እጆቹን እየጠራረገ ከጉድጓዱ ወጣ። "ዛሬ ጠዋት ስልክ የደወልከው አንተ ነህ። ስለመጎተቱ ሥራ አቤቱታ ካለህ እኔ ኃላፊ አይደለ....."

"የለኝም!" አለ ሮበርት። ምንም ዐይነት። እኔ አንድ ጥናት በማድረግ ላይ ስሆን ስለአሽከርካሪው ነው ለማወቅ የፈለኩት።

"ወደ ጽሕፈት ቤቴ ና" አለው።

ሁለቱ ሰዎች ትንሿ ጽሕፈት ቤት ውስጥ እንደገቡ ማንዴል የሰነድ መያዣ ሳጥን ከፈተና "እሁድ ዕለት ነው ያልከኝ?" አለ።

"ትክክል።"

@BOOKALEM

ማንዶል አንድ ካርድ ከማህደሩ ውስጥ አወጣና "አዎን ዮፎው ፊት ለፊት ምስላችንን ያነሳው ፎቶግራፍ አንሺ እሱ ነው!" አለ።

ሮበርት ድንገት የውስጥ እጁን ሲያልበው ተሰማው።

"ዩፎውን አይተህዋል?"

"አዎን።"

"ስለሱ መግለጽ ትችላለህ?"

ማንዶል አንቀጠቀጠው። "በራሪው ዲስክ ልክ በሕይወት ያለ ይመስላል።"

"አልገባኝም"

"ማለቴ አንድ የሆነ ሙበራት ዙሪያውን ነበረው። ቀለሙን ይለዋውጣል። አንዴ ስማያዊ አንዴ አረንጓዴ ይመስላል። እኔ አላውቅም። ለመግለጽ በጣም አስቸጋሪ ነው። እናም እነዚህ ኢምንት ፍጥረታት እውስጡ ነበሩ። ሰብአዊ ሰዎች አይደሉም። ግን....." አለና አቋረጠ።

"ስንት?"

"ሁለት።"

"በሕይወት ነበሩ?"

"ለኔ ሙታን መስለውኛል።" የቅንድቡን ላብ ጠራረገ። "ስላመንከኝ በጣም ተደስቻለሁ። ለባልንጀሮቼ ልነግራቸው ስሞክር ሳቁብኝ። ሌላው ቀርቶ ባለቤቴ እንኳ የጠጣሁ ነው የመሰላት። ግን ምን እንዳየሁ አውቃለሁ።"

"ስለጐተትከው መኪናስ?" አለ ሮበርት።

"አዎን ያቺ ሬኖልት የዘይት መፍሰስ ችግር ነበረባት። ስለዚህ ኩሽኔቶቿ ተቃጠሉ። የመጎተቱ ሥራ አንድ መቶ ሃምሳ ፍራንክ አስከፍሎታል። እሁድ እሁድ የምጠይቀው ዋጋ እጥፍ ነው።"

"አሽከርካሪው በቼክ ነው ወይስ በዱቤ ካርድ የከፈለው?"

"በቼክና በካርድ ክፍያ አልቀበልም። ስለዚህ በጥሬው ነው የከፈለኝ።"

"በስዊስ ፍራንስ?"

"በፓውንድ።"

"እርግጠኛ ነህ?"

"አዎን። የምንዛሪውን መጠን ማረጋገጥ ነበረብኝ።"

"ሚስተር ማንዶል የመኪናው ሰሌዳ ቁጥር ይኖርህ ይሆን?"

"እርግጥ!" አለና ማንዶል ካርዱን መልከት አለና "አቪስ የመኪና አከራይ ኩባንያ ሲሆን የተከራያትም ከጀኔቫ ነው" አለው።

"የሰሌዳ ቁጥሩን ብትሰጠኝ ቅር ይልሃል?"

"በሚገባ! ለምን አልሰጥህም?" ቁጥሩን አንድ ወረቀት ላይ ጫር ጫር አደረገና ለሮበርት አቀበለው። "በነገራችን ላይ ይህ ሁሉ ለምንድነው? ስለ ያ.ቢ.አው (ዩ.ኤፍ.አ) ነገር ነው?"

@BOOKALEM

ሐቀኛ በሚመስል ድምጽ "አይደለም" አለና ሮበርት ከኪሱ የመታወቂያ ወረቀት እያወጣ "ከዓለም አቀፍ የአውቶሞቢል ክለብ ነው የመጣሁት። ኩባንያዬ ስለተበላሹ መኪናዎች ማንሻ ካሚዎኖች ጥናት እያደረገ ነው።"

"እ...ሃ...!"

ሮበርት በሐሳብ እንደ ተመሰጠ ከጋራዡ ወጣ። 'ያ.ቢ.ኢ. (ዩ.ኤፍ.አ) ከሁለት ሙታን የሌላ ዓለም ፍጡራን ጋር በእጃችን የገባ ይመስላል።' ታዲያ መሬት ላይ የተከሰከሰው በራሪ ዲስክ መሆኑን እንደሚደርስበት እያወቀ በምን ምክንያት ነው ጄነራል ሒሊያርድ የዋሸው? አንድ ብቸኛ ምክንያት አለው። እናም ሮበርት በድንገት ሰውነቱ ሲቀዘቅዝ ተሰማው።

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

ግዙፏ እናት የጠፈር መንኮራኩር ድምጽ ሳታሰማ ከመሬት ምሕዋራዊ መሽከርከሪት ጋር በተመሳሰለ ሁኔታ በሰዓት ሃያ ሁለት ሺህ ማይልስ ፍጥነት በጨለማው ጠፈር ውስጥ በመብረር ላይ ናት። በራሪዋ መንኮራኩር ውስጥ ያሉት ስድስት እንግዳ ፍጡራን የመንኮራኩሯን አንድ ሙሉ ግድግዳ የሚሸፍነውን ልዩ ማዕዘነ–ሦስት የመመልከቻ መሣሪያ በማጥናት ላይ ናቸው። መሬት በምሕዋርዋ ላይ የምታደርገውን መሽከርከር ቁጥር አንድ የኤሌክትሮኒክ ስፔክትሮ ግራፍ መሣሪያ የምስሎቹን ኬሚካላዊ ውሁዶችና ምንነት እየተነተነ አመልካች መሣሪያቸው ላይ ያሳያቸዋል። እየበረሩ የሚያልፉት የምድር ከባቢ አየር በከፍተኛ ሁኔታ የተበከለ ነበር። ግዙፍ ፋብሪካዎች አየሩን በጥቁርና ወፍራም መርዛማ ጋዞች እየበከሉት ሲሆን ሕይወት ሊያጠፉ የሚችሉ ፍሳሾች ደግሞ በምድር ውስጥና ወደ ባሕር ውሃዎች እየተጨመሩ ነው።

በአንድ ወቅት ንጹሕና ሰማያዊ የነበሩት አሁን ግን በቆሻሻ ዘይት የጠቆሩትንና በኬሚካል ቅሪቶች ወደ ቡናማ ቀለም የተለወጡትን ውቅያኖሶች ተመለከቷቸው። ታላቁ የባሕር ዳርቻ የዓለት ግድግዳ በመርዛማ ኬሚካል ምክንያት ወደ ነጭነት ተለውጧል። በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዓሦችም በሞት እያለቁ ነው።

የአማዞን የዝናብ ደን አሁን መሃን ምድረ በዳ ሆኗል። የጠፈር መንኮራኩራቸው ላይ ያለው መሣሪያ ምድርን ከጐበኙ ከአምስት ዓመት በኋላ የመሬት የሙቀት መጠን ከፍ እያለ መሄዱን ያመለክታል። በመሬት ላይ ጦርነቶች ሲፋፋሙና አዳዲስ መርዛማ ኬሚካሎች በከባቢው አየር ውስጥ ሲታከሉ እየተመለከቱ ነው።

@BOOKALEM

ፍጡራኑ "ቴሌ ፓቲ" በተባለ በአዕምሮ ብቻ የመነጋገር ጥበብ እየተወያዩ ነው።

"በምድራዊያን ዘንድ የተለወጠ ነገር የለም።"

"በጣም ያሳዝናል! ምንም የተማሩት ነገር የለም።"

"እኛ እናስተምራቸዋለን።"

"ሌሎቹን ለማግኘት ሞክራችኋል?"

"አዎን። አንድ የተፈጠረ ስህተት አለ። ምንም መልስ አላገኘንም።"

"ሙከራችሁን ቀጥሉ። መንኮራኩሯን ማግኘት አለብን።"

.....

መሬት ላይ ደግሞ ከጠፈር መንኮራኩሯ ምሕዋር ብዙ ሺህ ማይሎች ዝቅ ብሎ ሮበርት በአንድ አስተማማኝ (ያልተጠለፈ) ስልክ ለጄነራል ሒሊያርድ ጥሪ እያደረገ ነበር። ጄነራሉ ወዲያውኑ ቀረበ።

"እንደምን ውለሃል ኮማንደር። የምትዘግበው ነገር አለህን?"

'አዎ። ውሸታም የውሻ ልጅ ስለመሆንህ ሪፖርት ላደርግ እፈልጋለሁ !'ሲል አሰበና ድምፁን ከፍ አድርጎ "ያ የአየር ንብረት ባሉን ወደ ያ.ቢ.ኢ. የተለወጠ ይመስላል!" አለና መልስ ጠበቀ።

"አዎን አውቃለሁ። ሁሉንም ነገር ቀደም ሲል ያልነገርኩህ አንዳንድ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ምሥጢራዊ የፀጥታ ምክንያቶች ስላሉኝ ነው።"

'ቢሮክራሲያዊ ጥምር አነጋገር' አለ ሮበርት በሐሳቡ።

ከተወሰነ የዝምታ ጊዜ በኋላ "ኮማንደር! በጣም ጥብቅ በሆነ ምሥጢር አንድ ነገር ልነግርህ ነው" አለ ጄነራል ሒሊያርድ።

"የኛ መንግሥት ከሌላ ዓለም ፍጡራን ጋር ከሦስት ዓመት በፊት ግንኙነት አድርጎ ነበር። ፍጡራኑ በአንድ አየር ኃይል ጣቢያችን ላይ ባረፉበት ወቅት ግንኙነት ለመፍጠር ችለን ነበር።"

ሮበርት ልቡ በፍጥነት ሲመታ ተሰማው። "ምን.....ምን ነበር የሚሉት?"

"ሊደመስሱን እንደተነሱ ነበር የነገሩን።"

"እኛን ሊደመስሱ?" ሰውነቱ ሲነዝር ተሰማው።

"በትክክል ተመልሰው መጥተው መሬታችንን እንደሚይዙ እኛንም ባሮቻቸው እንደሚያደርጉንና እነሱንም የምንከላከልበት ችሎታ እንደሌለን ነበር የተናገሩት። እስካሁን አላደረጉትም። እኛ ግን እነሱን የምናቆምበትን መንገድ እየፈለግን ነው። ለዚህም ነው ጊዜ ለማግኘት ሲባል ሕዝባዊ ሽብርን ማስወገድ ያስፈለገው። አሁን እነዚያ ምስክሮች ያዩትን እንዳያወሩ ማስጠንቀቅ ለምን እንዳስፈለገ ሳይገባህ አልቀረም። የፍጡራኑ አንድ ወሬ እንኳ ቢሰማ ዓለም አቀፋዊ ጥፋት ደረሰ ማለት ነው።"

@BOOKALEM

"ሕዝቡን ማዘጋጀት ጠቃሚ መስሎ አይ....."

"ኮማንደር! በ1938 ዓ.ም. አርሰን ዌልስ የተባለ ወጣት ከያኒ "ዋር ኦፍ ዘ ወርልድስ" በሚል ርዕስ የሌላ ዓለም ፍጡራን ምድራችንን ስለመውረራቸው ልቦለድ የራዲዮ ፕሮግራም አሰራጭቶ ነበር። በደቂዎች ውስጥ በመላው ዩናይትድ ስቴትስ ከተሞች ከፍተኛ ሽብር ተነሳ። በፍርሃት የተሸበሩ ሕዝቦች ይመጣል ተብሎ ከተገመተው «ወረራ» ለማምለጥ ሞከሩ። የስልክ መስመሮች በሙሉ በጥሪ ተያዙ። አውራ ጎዳናዎች ተጨናንቀው ሰዎች ተገደሉ። ባጠቃላይ ሽብርና ዋይታ ሆነ። የለም! የለም! ለሕዝቡ መግለጫ ከመስጠታችን በፊት መዘጋጀት አለብን። እነዚህን ምስክሮች ለራሳቸው ደህንነት ሲባል ፈልገህ አግኝተህ ሁኔታውን በቁጥጥር ስር ማድረግ አለብን።"

ሮበርት ነገሩ እየሳበው መሆኑ ገባው። "አዎን ገብ.....ቶኛል።"

"ጥሩ! ከምስክሮቹ አንዱን አነጋግረሃል ብዬ አምናለሁ።"

"ሁለቱን አግኝቻለሁ።"

"ስማቸውስ?"

"ሐንስ ቤከርማን የተባለ የአውቶቡስ ሾፌር።"

"ሌላውስ ምስክር?"

"ፍሪትዝ ማንዴል። በርን ውስጥ የራሱ ጋራዥ አለው። የአንድ ሌላ ሦስተኛ ምስክር መኪና ጎትቶ ያነሳ መካኒክ ነው።"

"የምስክሩ ስምስ?"

"እስካሁን የለኝም። እየተከታተልኩት ነው። ምስክሮቹን ለማንም ሰው ስለዩፎዎቹ እንዳያወሩ ማስጠንቀቂያ እንድሰጣቸው ይፈልጋሉ?"

"ተቃራኒውን። ያንተ ተልዕኮ ምሥክሮቹን ፈልጎ ማግኘት ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ የራሳቸው የተከበሩ መንግሥታት ስለዝምታው ያነጋግሯቸዋል። ምን ያህል ምስክሮች እንዳሉ ተረድተሃል?"

"አዎን! ሰባት መንገደኞችና ሾፌሩ። እንዲሁም መካኒኩና አንድ አልፎ ሂያጅ ሞተረኛ ናቸው።"

"ሁሉንም ማግኘት አለብህ። እያንዳንዱን የመከሰከስ ትዕይንት የተመለከተ ምስክር ፈልገህ ማግኘት አለብህ! ገብቶሃል?"

"አዎን ጄነራል።"

ሮበርት ስልኩን ሲዘጋው አዕምሮው እየዞረበት ነበር። ያልታወቁ በራሪ አካላት ወይም ዩፎዎች እውን ናቸው። እንግዳዎቹ ፍጡራን ጠላት ናቸው። የሚያሸብር ሐሳብ ነበር።

ሮበርት ጠዋት ድንገት ተሰምቶት የነበረው አካላዊና የስሜት መሸበር አሁን በሙሉ ኃይልና ብርታት ተተካ። ጄነራል ሒሊያርድ ይህንን ተልዕኮ ቢሰጠውም ሁሉንም ነገር አልገለጸለትም። 'የሚደብቁት ምን ነበር?'

@BOOKALEM

አቪስ የተባለው የመኪና አከራይ ኩባንያ 40.ሩ.ዲሉሰር በተባለ የጀኔቫ ከተማ ማዕከላዊ ሥፍራ ላይ ይገኛል። ሮበርት ወደ ኩባንያው ገባ።

"ምን ልርዳዎት?"

"የሬኖልቷ መኪና ሰሌዳ ቁጥር የተጻፈበት አንድ ወረቀት ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠና "ባለፈው ሳምንት ይህን መኪና አከራይታችሁ ነበር። እኔ የተከራየውን ሰው ስም ለማወቅ እፈልጋለሁ !" አለ በንዴት እየጮፈ።

"ጸሓፊዋ ወደ ኋላዋ ለጠጥ አለችና "አዝናለሁ! የዚህ ዐይነት መረጃ ለመስጠት አይፈቀድልኝም" አለችው።

"በጣም ጥሩ!" አለ ሮበርት። "መልሱ ይህ ከሆነ ድርጅታችሁ በጣም ከፍተኛ የሆነ ካሳ እንዲከፈለኝ ልከሰው ነው" አለ።

"አልገባኝም ችግርህ ምንድን ነው?"

"ችግሩ ምን እንደሆነ እነግርሻለሁ ወይዘሮ። ባለፈው አሁድ ዕለት ይህ መኪና ከአውራ ጎዳናው ላይ መኪናዬ ላይ ወጣባትና ከፍተኛ ደረጃ የሆነ የግጭት ጉዳት አደረሰብኝ። እኔም ሰውዬውን ከማስቆሜ በፊት ቢያመልጠኝም ሰሌዳ ቁጥሩን ለመያዝ ቻልኩ።"

"አሃ! ገባኝ" አለችና ጸሓፊዋ ሮበርትን ትኩር ብላ ተመልከታው "አንድ ግዜ ጠብቀኝ!" አለችና ጥላው ሄደች። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሰነዶች ይዛ ተመለሰች። "ሰነዳችን እንደሚያስረዳው ከሆነ መኪናው የሞተር ችግር እንደነበረበት ተጠቅሷል። ነገር ግን ስለግጭት አደጋ የቀረበ ምንም ዘገባ የለም።"

"በጣም ጥሩ! እኔ ደግሞ ድርጅታችሁን በተጠያቂነት እከሳለሁ። የመኪናዬን ማስጠገኛ ዋጋ ትከፍላላችሁ። ገና አዲስ የሆነ ፖርሽ መኪና ስለሆነ አያሌ ገንዘብ ያስወጣችኋል።"

"እጅግ በጣም አዝናለሁ። አደጋው እስካልተመዘገበ ድረስ በኋላፊነት ልንጠየቅ አንችልም።"

"ተመልከች!" አለ ሮበርት ድምጹን የበለጠ ለስላሳና ምክንያታዊ ለማድረግ እየሞከረ። "ኩባንያችሁን በኋላፊነት ለመያዝ አልፈልግም። እኔ የምፈልገው አደጋውን ያደረሰብኝ ሰው መኪናዬን እንዲያሠራልኝ ብቻ ነው። ፖሊስ መጥራትም አያስፈልገኝ ይሆናል። አንቺ የሰውየውን ስም ከሰጠሽኝ እኔ አነጋግረውና ችግሩ በኔና በሰውዬው ብቻ እንዲፈታ አደርጋለሁ። ይህ በቂ አይመስልሽም?"

ጸሓፊዋ ቆማ ማሰብ ቀጠለች።

"አዎን! እኛም ይህን እንመርጣለን" አለችና መዝገቡን መመልከት ቀጠለች። "መኪናውን የተከራየው ሰው ስም ሌስሊ ማዘርሼድ ይባላል።"

"አድራሻውስ?" አድራሻው፡...

@BOOKALEM

"213 ኤ.ግሩቭ ጎዳና ዋይት ቻፕል ለንደን ምሥራቅ -3-" አለችና ቀና ብላ ሮበርትን እየተመለከተች "ይህን ጉዳይ በተመለከተ ኩባንያችን በሕግ እንደማይጠየቅ እርግጠኛ ነህ?" አለችው።

"ቃሌን እሰጣለሁ!" አለ ሮበርት። "የኔና የማዘርሼድ የግል ጉዳይ ነው።" ኮማንደር ቤላሚ በሚቀጥለው የስዊስ ኤር አውሮፕላን ወደ ለንደን ተጓዘ።

በጨለማው ክፍል ውስጥ ብቻውን ተቀምጦ ያወጣው እቅድ ምን ያህል እንከን የለሽ መሆኑን በጥሞና እየመረመረ ነበር። በዚህ ወቅት ከሰጠመበት የሐሳብ ባሕር በስልኩ ተቀሰቀሰ።

"ጃኑስ ነኝ!" አለ ስልኩን አነሳና።

"ጃኑስ ጄነራል ሒሊያርድ ነኝ!" አለ ደዋዩ።

"ቀጥል።"

"ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ምስክሮች አግኝቷል።"

"በጣም ጥሩ! አስፈላጊውን ጉዳይ በአስቸኳይ አስፈጽም።"

"እሺ ጌታዬ!"

"ኮማንደሩ አሁን የት ነው የሚገኘው?"

"ወደ ለንደን በመጓዝ ላይ ነው። ሦስተኛውን ምስክር በአጭር ጊዜ ውስጥ ያገኘዋል እላላሁ።"

"ጥሩ! እኔም ኮማንደሩ ስለደረሰበት ዕድገት ለኮሚቴው አሳውቃለሁ። በተጨማሪም የዚህ ዘመቻ ምሥጢራዊነት የተጠበቀ ሆኖ ይቀራል።"

"ይገባኛል ጌታዬ። የማቀርበው ሐሳብ....."

የስልኩ መስመር ተዘጋ።

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ለ–ቡንዴሳን ዋልተስቻፍት
ምክትል ዳይሬክተር ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም።
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ

1. ሐንስ ቤከርማን – ካፔል
2. ፍሪትዝ ማንዴል – በርን።

የመልዕክት መጨረሻ

@BOOKALEM

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ከኡተን ዶርፍ ሃምሳ ማይሎች ራቅ ብሎ የሌጀንፊልድ ቤተሰብ ሌሊት ባልተለመደ እንግዳ ነገር ሲረበሽ ነበር ያደረው። ተለቅ ያለው ህፃን ልጅ በመኝታ ቤቱ መስኮት የገባ የሚብረቀረቅ ቢጫ መብራት ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው። ሁኔታውን ለማጣራት ሲነሳ ብርሃኑ ተሰወረበት። ግቢው ውስጥ ቶዚ የተባለው የጀርመን ሼፐርድ ውሻቸው እንደዕብድ እየጮኸ ሽማግሌውን ሌጀንፊልድን ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው። ነገሩ ምን እንደሆነ ለማጣራት ሽማግሌው ወጣ። በጎቹም ተሸብረው እርስ በራሳቸው ይጋጫሉ። የውሃ መጠጫ ገንዳቸው በትናንትናው ዝናብ ሞልቶ እንዳልነበረ ሁሉ አሁን እንደ አጥንት ደርቆ አገኘው።

ቶዚ እየሮጠና በፍርሃት እያላዘነ ሽማግሌው ስር ሲወሸቅ ሽማግሌው በሐሳብ ተውጦ ውሻውን እየደባበሰ አረጋጋው።

ልክ በዚህ ወቅት የቤቱ መብራት በሙሉ ድርግም ብሎ ጠፋ። ሽማግሌው ወደ ቤቱ ተመለሰና የመብራት ኃይል ኩባንያውን በስልክ ለመጠየቅ ሲሞክር ስልኩ የማይሠራ ሆኖ አገኘው። መብራቱ ለትንሽ ጊዜ ሳይጠፋ ቢቆይ ኖሮ አንዲት እጅግ በጣም የተዋበች ሴት ከመጋዘኑ ውስጥ ወጥታ ከቤቱ ማዶ ወዳለው ሜዳ ስትሄድ ማየት በቻለ ነበር።

ምዕራፍ አሥራ አራት

ቡንዴሳን ዋልትስቻፍት ጀኔቫ 1330 ሰዓት

ሚንስትሩ በስዊስ የመረጃ ድርጅት ሕንፃ አንድ ቢሮ ውስጥ ተቀምጠው የመረጃ ድርጅቱ ምክትል ዳሬክተር መልዕክቱን አንብቦ እስኪጨርስ ያዳምጡ ነበር። ትዕዛዝ አዘሉን ወረቀት ማጎደሩ ውስጥ አስቀምጠ ማጎደሩን መሳቢያ ውስጥ ከከተተ በኋላ መሳቢያውን ቆለፈው።

"ሐንስ ቤከርማንና ፍሪትዝ ማንዴል።"

"አዎን።"

"ይወገዱ!"

"ምን?"

"ይገደሉ! በአስቸኳይ!"

@BOOKALEM

በማግሥቱ ጠዋት ሐንስ ቤከርማን ወደ ሥራው ሲጓዝ የአልሰር ሕመሙ እያሰቃየው ነበር። "ያጋዜጠኛ ከመሬት ላይ አግኝቼ ለሰጠሁት ነገር በቂ ገንዘብ እንዲከፍለኝ ማድረግ ነበረብኝ.....እነዚህ የሚጋዚን አሳታሚዎች በሙሉ በጣም ከበርቴዎች ናቸው። ምናልባት ጥቂት መቶ ማርክ ማግኘት ችዬ አንድ መልካም ሐኪም ዘንድ በመሄድ የአልሰር በሽታዬን መታከም በቻልኩ ነበር።'"

የቱሪልን ሐይቅ አለፍ ብሎ ጥቂት እንደነዳ አንዲት ሴት እጇን እያወዛወዘች ሊፍት ስትጠይቀው ተመለከተ። መልኳን በደምብ ለማየት ብሎ መኪናዋን ዝ....ግ አደረጋት። ወጣትና ማራኪ ነበረች። መኪናውን ወደ መንገዱ ጠርዝ ጠጋ አድርጎ ሲያቆማት ሴትዮዋ መኪናውን ተጠጋች።

"እንደምን አደርሽ? ምን ልርዳሽ?" አለ ቤከርማን። 'ከቅርብ ደግሞ በጣም ታምራለች።'

"ደህና!" አለችው በሰዊስ አነጋገር ዘይቤ። "ከወንድ ፍቅረኛዬ ጋር ስለተጣላን እዚህ ባዶ ሜዳ ላይ ጥሎኝ ሄደ።"

"በጣም መጥፎ ነገር ነው አላት ቤከርማን።"

"ዙሪክ ድረስ ሊፍት ልትሰጠኝ ትችላለህ?"

"ግቢ! እባክሽን ግቢ!"

ሊፍት ጠያቂዋ በሩን ከፍታ አጠገቡ ተቀመጠች። "በጣም ቅን ሰው ነህ። ስሜ ካረን ይባላል።"

"ሐንስ እባላለሁ" አለና መኪናውን ማሽከርከር ጀመረ።

"አንተ ባትደርስልኝ ኖሮ ምን ማድረግ እንደምችል አላውቅም ነበር ሐንስ።"

"አው! እንዳንች ዐይነቷን ቆንጆ ልጅ አንዱ እንደሚወስዳት እርግጠኛ ነኝ።"

ወደ ሐንስ ጠጋ አለች። "ግን ካንተ የተሻለ መልከ መልካም እንደማይሆን እርግጠኛ ነኝ።"

ወደ ልጅቷ ገልመጥ ብሎ ተመለከተ። "እውነት?"

"በጣም ቆንጆ ነህ ብዬ እገምታለሁ።"

ፈገግ አለና "ይህንን ለባለቤቴ መንገር አለብሽ" አላት።

"አው! አግብተሃል?" አለች የብስጭት ቃና ባዘለ ቅላጼ። "ለምንድን ነው ሁሉም እጹብ ድንቅ ሰዎች የሚያገቡት? ደግሞ ብሩህ አዕምሮ ያለህ ትመስላለህ።"

ቀጥ ብሎ ተቀመጠ።

"እውነቱን ለመናገር ከወንድ ጓደኛዬ ጋር ግንኙነት በመፍጠሬ በጣም አዝናለሁ" አለችና የአቀማመጥ አቅጣጫዋን ስትቀይር ቀሚሷ ተሰብስቦ ከጭኗ በላይ ወጣ። ሐንስ ላለማየት ሙከራ አደረገ። "ተለቅ ያሉና የበሰሉ ሰዎችን ነው

@BOOKALEM

የምወደው። ከወጣቶች የበለጠ የወሲብ ፍላጎት አላቸው ብዬ እገምታለሁ።" እላዩ ላይ ለጠፍ አለችና "ወሲብ ትወዳለህ ሐንስ?" ስትል ጠየቀችው።

ጉሮሮውን እያጸዳ "እወድ.....እወድ ይሆን? ደህና ታውቂያለሽ? እኔ.....እኔ....."

"አውቃለሁ!" አለችና ጭኑን መዳሰስ ጀመረች። "አንድ ነገር ልንገርህ? ከወንድ ጓደኛዬ ጋር ያደረኩት ጸብ ስሜቴን አግሎታል። ካንተ ጋር ፍቅር ብሠራ ትወዳለህ?"

ዕድሉን ለማመን አልቻለም። እጅግ በጣም ውብ ከመሆኗም በላይ ማራኪ የሆነ ሰውነት አላት። ምራቁን እየዋጠ "እወዳለሁ! ግን ወደ ሥራ በመሄ....."

"ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነው የሚወስደው። ወደ ጫካው የሚወስድ አንድ ተገንጣይ መንገድ አለ። እዚያ ለምን አናቆምም?"

ስሜቱ ሲነሳሳ ተሰማው። "'ቢሮ ደርሼ ይህንን ጉዳይ ለጓደኞቼ ስነግራቸው መቼም አያምኑኝም። በእርግጥ ለምን አልናረገውም?'

ሐንስ መኪናውን ወደ አቧራማው መንገድ ጠመዘዘና በተላላፊ መኪኖች የማይታይበት ቦታ አመራ።

ጭኑን በዝግታ መዳሰስ ቀጠለች። "የኔ ፍቅር በጣም ጠንካራ እግሮች አሉህ።"

"ወጣት በነበርኩበት ጊዜ ሯጭ ነበርኩ!" ሲል ጉራውን ነዛ።

"ሱሪህን እናውልቀው።"

ቀበቶውን ፈታችና ሱሪውንና የውስጥ ሙታንታውን ዝቅ አደረገችው። ዝግጁ ነበር።

"በጣም ግሩም ነገር!" እያለች ታሻሸው ጀመር። በስሜት ቃተተ።

"እዚህ ላይ ብትሳም ትወዳለህ?"

"አዎን!" ሚስቱ እንኳን ይህንን አድርጋለት አታውቅም።

"እሺ አሁን ዘና በል።"

ቤከርማን ቃተተና ዐይኖቹን ጨፈናቸው። በለስላሳ እጆቿ ዳሰሰችው። ወዲያው አንድ ሹል መርፌ ጠ.....ቅ! አድርጎ ሲወጋው ተሰማውና ዐይኖቹን ከፈታቸው።

"ምን?"

ሰውነቱ ሽምቅቅ አለና ዐይኖቹ ተጎልጉለው ወጡ። መተንፈስ እስኪያቅተው ድረስ ታፈነ። መኪናው መሪ ላይ ድፍት ሲል ሴትየዋ ፀጥ ብላ ተመለከተችው። ከመኪናው ውስጥ ወርዳ ሬሳውን ወደ ተሳፋሪው ወንበር ላይ ገፋ አደረገችውና ሹፌሩ መቀመጫው ላይ ቁጭ ብላ መኪናውን ወደ ዋናው መንገድ እየነዳች ወሰደችው። ልክ የገደሉ ጫፍ ላይ ስትደርስ በሩን ከፈት አድርጋ የነዳጅ

@BOOKALEM

መስጫውን በኃይል ረግጣው ከመኪናዋ በፍጥነት ወጣች። መኪናዋ ከተራራማው መንገድ ወደ ጥልቁ ገደል እየተገለባበጠች ስትወርድ በዝምታ ተመለከተቻት።

ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ ጥቁር ሽንጠ ረዥም መኪና አጠገቧ መጥቶ ቆመ።

"ምንም ችግር አልገጠመሽም?"

"ምንም።"

ፍሪትዝ ማንዴል ልክ በሩን ሊዘጋ ሲል ሁለት ሰዎች ወደ እርሱ መጡ።

"እዝናለሁ። ልዘጋ ስለሆነ ልረዳች....."

አንደኛው አቋረጠውና "መኪናችን ከአውራ ጎዳናው በታች ቆማለች። እንዲጎተትልን ፈልገን ነበር።"

"ሚስቴ እየጠበቀችኝ ነው። አብረን ነው የምናመሸው። የሌላ ኩባንያ ስም ልስጣ....."

"ሁለት መቶ ዶላር እንከፍላለን። በጣም እንቸኩላለን።"

"ሁለት መቶ ዶላር?"

"አዎን። መኪናችን በመጥፎ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ስለዚህ መኪናችንን እንድትጠግንልን እንፈልጋለን። ይህም ምናልባት መቶ ወይም ሦስት መቶ ዶላር ሊያስከፍለን ይችላል።"

ማንዴል ሁኔታው አጓጓው።

"አቤት?"

"ሮልስ ሮይስ ነች" አለ አንደኛው ሰው። "እስቲ ለማንኛውም ምን ዐይነት የመጠገኛ መሣሪያ እንዳለህ እንመልከት!" አለውና ወደ ጋራዡ ተያይዘው አመሩ። ጋራዡ ውስጥ እንደገቡ የመኪና ማንጠልጠያ ማሺን ያለው ጉድጓድ ጠርዝ ላይ ቆሙ። "በጣም ግሩም የሆነ መሣሪያ ነው።"

"አዎን ጌታዬ! በጣም ምርጥ የሆነ ነው" አለ ማንዴል በኩራት።

እንግዳው ሰው ቦርሳውን ከኪሱ አወጣና "አሁን ጥቂት ገንዘብ በቅድሚያ ልሰጥህ እችላለሁ" አለውና ጥቂት ገንዘብ ከቦርሳው አውጥቶ ለማንዴል ሲያቀብለው የገንዘብ ቦርሳው ከእጁ አምልጦት ጉድጓዱ ውስጥ ገባ።

"አይጨነቁ! እኔ አወጣዋለሁ" አለና ማንዴል ወደ ጉድጓዱ ወረደ። ማንዴል ጉድጓዱ ውስጥ እንደገባ አንደኛው ሰው ወደ ላይ የተመዘዘውን ኃይድሮሊክ ሊፍት ወደሚቆጣጠረው መሣሪያ ሄዶ አንዱን ቁልፍ ተጫነው። የመኪናው ማንጠልጠያ ሊፍት ወደ ታች መውረድ ጀመረ።

ማንዴል ወደ ላይ ተመለከተ። "ተጠንቀቅ ምንድነው የምታደርገው?"

በጉድጓዱ አንድ ጠርዝ በኩል ለመንጠላጠል ሞከረ። በዚህ ጊዜ አንደኛው ሰው የማንዴልን እጅ በእርግጫ ሲጨፈልቀው ተመልሶ ጉድጓዱ ውስጥ

@BOOKALEM

ወደቀ። ማንዴል ጩኸቱን አቀለጠው። ከባዱ የሃድሮሊክ ሊፍት ወደ ማንዴል መውረዱን ቀጠለ።

"እባካችሁ አውጡኝ! እባካችሁ!"

ሊፍቱ ትከሻው ላይ ያዘውና ወደ ሲምንቶው ወለል እየጨፈለቀ አወረደው። የሚዘገንነው የማንዴል ዋይታ ፀጥ ካለ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንደኛው ሊፍቱን ወደ ላይ የሚያነሳውን ቁልፍ ተጫነው። ሌላው ደግሞ ወደ ጉድጓዱ ወረደና ደሙ ሰውነቱንና ልብሱን እንዳይነካካው ተጠንቅቆ የገንዘብ ቦርሳውን ካወጣ በኋላ በጭለማው ውስጥ እየነዱ ተሰወሩ።

አሰቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
አብቴሉንግ የስለላ ማእከል ምክትል ዳይሬክተር
ለብሔራዊ ፀጥታ ወኪል (ኤንኤስኤ)
ምክትል ዳይሬክተር ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት..."የፍርድ ቀን ዘመቻ"
1. ሐንስ ቤከርማን–ተወግዷል
2. ፍሪትዝ ማንዴል–ተወግዷል
የመልዕክት መጨረሻ።

ኢታዋ ካናዳ

2400 ሰዓት

ጃኑስ ለአሥራ ሁለት ሰዎች ንግግር እያደረገ ነው። "እጥጋቢ የሆነ ዕድገት ተደርጓል። ሁለት ምስክሮች እንዲገደሉ ሲደረግ ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ የሦስተኛውን ጭራ በመከተል ላይ ነው።

"እስካሁን ድረስ በጠፈር መከላከያ መረጃ በኩል የተገኘ ውጤት አለን?" ትዕግስት የለሹና ተለዋዋጩ ኢጣሊያዊ።

"እስካሁን ምንም የለም። ነገር ግን የስታር ዋር (የከዋክብት ጦርነት) ቴክኖሎጂ እንደሚያልቅና በቶሎ ሥራውን የሚጀምር ለመሆኑ እንተማመናለን።"

"ሥራውን ለማፋጠን የሚቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን። የገንዘብ ጥያቄ ከሆነ....." ፀጥተኛውና በቶሎ የማይረዱት የሳውዲ ዜጋ።

"የለም ሌላ በተጨማሪ መደረግ ያለበት ሙከራ አለ።"

"መቼ ነው የሚቀጥለው ሙከራ የሚደረገው?" ልባዊውና ቀልጣፋው አውስትራሊያዊ።

"በአንድ ሳምንት ውስጥ። ከአርባ ሰምንት ሰዓት በኋላ እንደገና እዚህ ቦታ እንሰበሰባለን።

@BOOKALEM

ምዕራፍ አሥራ አምስት

አራተኛ ቀን

ለንደን ሐሙስ ጥቅምት አሥራ ስምንት

የሌስሊ ማዘርሼድ ሞዴል ዝነኛና ባለፀጋ ሰዎችን በስስትና በጉጉት የሚያስመለከተው የቴሌቪዥን ፕሮግራም አዘጋጅ ሮቢን ሊች ነበር።

ሌስሊ ማዘርሼድ የሮቢን ሊች ፕሮግራም እንግዶችን አለባበስ፤ አረማመድና አነጋገር በጥንቃቄ ያጠናል። ምክንያቱም አንድ ቀን እርሱም በዚህ ፕሮግራም ላይ እንደሚቀርብ እርግጠኛ ነበርና። ሕፃን ከነበረበት ዘመን ጀምሮ አንድ ቀን ሀብታምና ዝነኛ ለመሆን ዕጣው እንደተፃፈለት ይሰማው ነበር።

"አንተ በጣም የተለየህ ነህ የኔ ህፃን። አንድ ቀን በመላው ዓለም ታዋቂ ትሆናለህ....." ትለው ነበር እናቱ።

ወጣቱ ልጅ የእናቱ ንግግር በአዕምሮው ጠልቆ እስኪያምንበት ድረስ በጆሮው እያቃጨለበት ወደ መኝታው ይሄዳል።

ማዘርሼድ እየጎለመሰ ሲመጣ አንድ ችግር እንዳለበት ተገነዘበ። በምን ዐይነት ዘዴ ሀብታምና ዝነኛ ለመሆን እንደሚችል ሊገባው አልቻለም። በአንድ ወቅት ሲኒማ ተዋናይ ለመሆን ሞከረ። ግን ራሱን መቆጣጠር እስኪሳነው ድረስ ሰዎች ፊት ለመጫወት ፈሪ ሆኖ ተገኘ። ለአጭር ግዜ የእግር ኳስ ጨዋታ ኮከብ ለመሆን አሰበ። ግን የስፖርተኛ ተክለ–ሰውነት አልነበረውም። ዝነኛ ሳይንቲስት ወይም ታላቅ የሕግ ሰው ለመሆንና ባለብዙ ንዋይ ለመሆን አሰበ። ግን የትምሕርት ውጤቱ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ወደ ማንኛውም ዐይነት ዝና ከመጠጋቱ በፊት ከትምሕርት ዓለም ተሰናበተ። በቀላል አባባል ሕይወት አግባብ አልነበረችም። ቀጫጫ አካል፤ የወየበ የበሸተኛ ገፅታና አምስት ጫማ ከአምስት ኢንች ብቻ ከፍታ ያለው ድንክዬ ነው። በአንድ በኩል ደግሞ 'ብዙ ዝነኛ ሰዎች አጫጭሮች ናቸው' ሲል ራሱን አሳመነ። ዱድሌይ ሙር፤ ደስቲን ሆፍማን፤ ፒተር ፎከ.....ስንቱ ተቆጥሮ።

ስሜቱን የሚስበው ብቸኛ ሙያ ቢኖር ፎቶግራፍ አንሺነት ነው። ምስሎችን ማንሳት በጣም ቀላል ሥራ ነው። ማንም ሰው ያደርገዋል። በቀላሉ ቁልፉን መጫን ብቻ ነው። የስድስተኛ ዓመት ልደቱን ሲያከብር እናቱ አንድ ካሜራ ገዝችለት። ሌስሊ የሚያነሳቸውን ፎቶዎች ሁሉ እናቱ ከሚፈልገው በላይ ግሩም ድንቅነታቸውን ታረጋግጥለት ነበር።

@BOOKALEM

ዕድሜው የአሥረኛውን ክልል እንደገባም ማዘርሼድ 'የመጨረሻው ድንቅ ፎቶግራፍ አንሺ ነኝ!' ሲል ራሱን አሳመነ።

ልክ እንደነአንሴል አዳምስ፤ ሪቻርድ ኤቤዶን፤ ወይም ማርጋሬት ቡርክዋይት 'ግሩም ፎቶግራፍ አንሺ!' ብሎ ለራሱ ካረጋገጠ በኋላ ከእናቱ ገንዘብ ተበድሮ ዋይት ቻፐል በሚገኘው አፓርታማው ውስጥ አንድ የፎቶ ስቱዲዮ መሠረተ። እናቱ "በትንሹ ጀምር። ግን ወደ ትልቅነት አስብ" አለችው። ሌሲሊ ማዘርሼድም በትክክል ያደረገው ይህንኑ ነበር። እንደ አለመታደል ሆነና የፎቶግራፍ አንሺነት ችሎታ ግን አልነበረውም። የበዓላት ሠልፈኞችን፤ እንሰሳትን፤ አእዋፍን ሁሉ ፎቶግራፍ ካነሳ በኋላ በሙሉ እምነት ወደ ሜጋዚንና ጋዜጣ አሳታሚዎች ፎቶውን ቢልክም እንደገና ተመልሰው ይላኩለት ነበር።

ሳያስበው በድንገት አንድ ዕድል አጋጠመው። ሐርገር ኩሊንስ ለተባለ የእንግሊዝ አሳታሚ ኩባንያ የሚሠራ የአጎቱ ልጅ ስለስዊዘርላንድ የሚያወሳ አንድ የቡና ጠረጴዛ መጽሐፍ ለማዘጋጀት እንደሚሹ ገለጸለት።

"እስካሁን ድረስ ፎቶ አንሺ አልመረጡም ሌሲሊ። ስለዚህ ከፈለክ ወደ ስዊዘርላንድ ተጉዘህ ጥቂት ታላላቅ ምስሎችን አንሰተህ ከመጣህ የመጽሐፉ ኮንትራት ያንተ ሆነ ማለት ነው።"

ሌሲሊ ማዘርሼድ በአስቸኳይ ካሜራዎቹን ሸክፎ ወደ ስዊዘርላንድ ተጓዘ። ጀኔቫ ውስጥ መኪና ተከራይቶ በመዞር የውሃ ፏፏቴዎችን፤ የፀሓይ አጠላለቅን፤ የፀሓይ አወጣጥን፤ የበረዶ ልብስ ያላቸውን ከፍተኛ ሥፍራዎች ሁሉ ምስላቸውን በካሜራ ቀረጸ። እናም በዚህ ሁሉ መኻል ዕጣ እጁ ላይ ወደቀችለትና ሕይወቱን ለወጠችው። መኪናው ስትበላሽ ወደ በርን ከተማ በማምራት ላይ ነበር። መኪናውን ወደ መንገዱ ዳር አወጣና "የዚህ ዐይነት ነገር ለምን ሁሌ በኔ ላይ ይደርሳል?" ሲል አምርሮ ተበሳጨ። ስለሚባክንበት ጊዜና መኪናውን ለማስጎተት ስለሚያወጣው ወጪ በምሬት እያንሰላሰለ መኪናው ውስጥ ተቀመጠ። አሥራ አምስት ማይሎች ያህል ራቅ ብሎ የቱን ከተማ ትገኛለች። 'እዎን ከዚያ ሄጄ ጎታች ካሚዎን ባስመጣ ወጪው ብዙ አይሆንም።'

አንድ የነዳጅ መጫኛ ቦቴ መኪና አስቆመና "የተበላሸ መኪናዬን የሚጎትትልኝ ካሚዮን አፈልጋለሁ። እባክህን ቱን ከተማ ጋራዥ ቆም ብለህ ጎታች ካሚዎን እንዲልኩልኝ ብታደርግ?"

የካሚዎኑ አሽከርካሪ አንገቱን ነቀነቀና "ዛሬ ሰንበት ነው ሚስተር! የቱን ከተማ ጋራዦች ዝግ ናቸው። ዛሬ የሚሠሩት የበርን ከተማ ብቻ ናቸው።"

"አያሌ ንዋይ ያስወጣኛላ!"

ሹፈሩ ሳቅ ብሎ አንገቱን ነቀነቀና መንገዱን ሲጀምር "ቆይ!" ለመናገር በጣም እየተቸገረ....."ከበርን ለሚመጣ ጎታች መኪና እከፍላለሁ።"

"ጥሩ! አንድ ሰው እንዲልኩልህ አደርጋለሁ።"

@BOOKALEM

ማዘርሼድ እየተበሳጨ መኪናው ውስጥ ተቀመጠ። ለፊልም ብዙ ገንዘብ አውጥቷል። አሁን ደግሞ መኪናውን ወደ ጋራዥ ለማስጎተት ለማንም ሌባ ሊከፍል ነው። ጎታቹ ካሚዎን እስኪደርስለት ድረስ ሁለት ሰዓት ነው የፈጀው። መካኒኩ መኪናውን ከጎታች ካሚዎኑ ጋር ማቆራኘት ሲጀምር ከአውራ ጎዳናው ባሻገር የከፍተኛ ብርሃን ብልጭታ በከፍተኛ ፍንዳታ ታጅቦ ሲሰማ ማዘርሼድ ብሩህ የሆነ ነገር ከሰማይ ወደ መሬት ሲወርድ ተመለከተ። በአውራ ጎዳናው ላይ የነበረው ከኋላው መጥቶ የቆመ አንድ የቱሪስቶች አውቶቡስ ብቻ ነበር። የአውቶቡሱ መንገደኞች ወደተከሰከሰው ነገር እየተጣደፉ ሲሄዱ ማዘርሼድ ወሬውን ለማየት በመጓጓትና ጉዞውን በመቀጠል መኻል አመነታና የአውቶቡሱን ተሳፋሪዎች ከአውራ ጎዳናው ባሻገር ተከትሎ ሄዶ። አደጋው የደረሰበት ሥፍራ እንደደረሰ ባየው ነገር መብረቅ እንደመታው ሰው ደርቆ ቀረ። 'ቅዱስ አምላክ!' ሲል አሰበ። በራሪ ዲስክ እየተመለከተ ነበር። ሌሰሊ ማዘርሼድ ስለበራሪ ዲስኮች አንብቧልም ሰምቷልም። ነገር ግን በፍፁም በእውን አሉ ብሎ አያምንም ነበር። አስፈሪውንና እንቆቅልሽ የሆነውን ዕይታ በመደነቅ አፉን ከፍቶ ተመለከተ። የመንኮራኩሯ ቅርፊት ተበርግዶ ተከፍቷል። አካላቸው ትንንሽ፤ ዐይኖቻቸው የሰመጡ፤ ጆሮ የለሽ፤ ትልልቅ የራስ ቅል፤ ሊጠፉ የደረሰ አገጭ ያላቸው፤ ብርማ ቀለም ያለው ብረታማ የበረራ ሙሉ ልብስ የለበሱ ሁለት ሙታን ፍጡራን እየተመለከተ ነው።

የቱሪስቶቹ ቡድን በሌሰሊ ዙሪያ ቆሞ በተሸበረ ፀጥታ ትዕይንቱን እየተመለከተ ነበር። አጠገቡ የነበረው ሰው ጎሊናውን ሰቶ ወደቀ። ሌላ ሰው ፊቱን አዙሮ አስመለሰ። አንድ ሽምገል ያሉ ቄስ ደግሞ በማይገባ ቋንቋ ያጉረመርሙ ነበር።

"እምላኬ በራሪ ዲስክ ነው!" አለ አንድ ሰው።

ተዓምር ነበር እጆቹ ላይ የወደቀለት። እርሱ ሌሰሊ ማዘርሼድ የከፍለ ዘመኑን ታሪክ ለመመዝገብ ከነካሜራው ልክ በቦታው ላይ ነበር። አሁን የሚያነሳውቸውን የእርሱን ፎቶግራፎች የማይወስድ የሜጋዚንም ሆነ የጋዜጣ ሕትመት ድርጅት በዓለም ላይ አይኖርም። 'ስለስዊዘርላንድ የቡና ጠረጴዛ መጽሐፍ' ገና ሲያስበው ሳቁ መጣ። መላውን ዓለም ሊያስደንቅ ነው። ሁሉም የቴሌቪዥን ጣቢያዎች እንዲታይላቸው ይለምኑታል። እርሱ ግን መጀመሪያ የሚቀርበው በሮቢን ሊች ጣቢያ ነው። ፎቶግራፎቹን ለለንደን ታይምስ፤ ዘ ሰን፤ ዘ ሜይል፤ ዘ ሚረር...ለሁሉም የእንግሊዝኛ ሜጋዚኖች ይሸጣል። ሌ ፊጋሮና ፓሪስ ማች፤ አጊ እና ዴር ታግ፤ ታይምና ዩ.ኤስ.ኤ. ቱደይ...በመላው ዓለም ያሉ የሕትመት ድርጅቶች በሙሉ የእርሱን ፎቶግራፎች ለማግኘት ይለምኑታል።

ጃፓንና ደቡብ አሜሪካ፤ ሩሲያና ቻይና እና.....ምንም ማለቂያ የለውም። የማዘርሼድ ልብ በጉጉት እየመታ ነበር። 'ለማንም ቀደምትነትን አልሰጥም።

@BOOKALEM

እያንዳንዱ በተናጠል ይከፍለኛል። በአንድ ፎቶ አንድ መቶ ሺህ ምናልባትም ሁለት መቶ ሺህ ፓውንድ ማስከፈል ጀምራለሁ። እናም በላይ በላዩ ፎቶዎቼን መሸጥ እቀጥላለሁ።' የሚያገኘውን የገንዘብ መጠን ቢጋለ ስሜት ማሰላት ቀጠለ። ሌስሊ ማዘርሼድ የሚያገኘውን ገንዘብ በሐሳቡ ሲደምር ማንሳት የሚገባውን ምስል ጨርሶ ረስቶት ነበር።

"አ! አምላኬ! ይቅርታ አድርጉልኝ" አለና ጎዳናውን አቋርጦ ወደ ካሜራው በረረ።

መካኒኩ የተበላሸችውን መኪና ከካሚዎኑ ጋር አያይዞ ጨርሶ ለመነሳት ተዘጋጅቶ ነበር። "ምንድነው እዚያ ማዶ የተፈጠረው?"

ማዘርሼድ ካሜራውን ለመያዝ እየተጣደፈ "ራስህ መጥተህ ተመልከት!" አለው።

ሁለቱ ሰዎች ጎዳናውን አቋርጠው ዛፍ ብቻ የሆነው ክልል ውስጥ እንደደረሱ ማዘርሼድ በቱሪስቶቹ መኻል ተሸሎክሉኮ "ይቅርታ! ይቅርታ! አርጉልኝ!" እያለ ብቅ አለ።

ካሜራውን አስተካክሎ ዝግጁ ካደረገ በኋላ የዩፎውንና የአሸባሪዎቹን አብራሪዎች ምስል ማንሳት ቀጠለ። ምስሎቹን በባለቀለምና ጥቁርና ነጭ ፊልም ደጋግሞ አነሳ።

ማዘርሼድ የካሜራው መዝጊያ ቀጭ! ባለ ቁጥር 'አንድ ሚሊዮን ፓውንድ.....ሌላ ሚሊዮን ፓውንድ.....ሌላ ሚሊዮን ፓውንድ.....' እያለ ያሰላ ነበር።

ቄሱ እያማተቡ "በስመ አብ! የራሱ የሰይጣን ፊት ነው!" ይላሉ።

'ሰይጣን? ገሀነም? ይህ የገንዘብ ፊት ነው!' ሲል በደስታ አሰበ። 'በራሪ ዲስኮች ስለመኖራቸው የሚያረጋግጠው የመጀመሪያው ፎቶግራፍ ይህ የኔ ይሆናል!' ድንገት ደግሞ አንድ አሸባሪ ሐሳብ ጭንቅላቱን መታው። ሚጋዜኖቹ በሙሉ ያነሳቸውን ምስሎች የተጭበረበሩ ናቸው ብለው ቢገምቱስ? ሌሎች ብዙ የተጭበረበሩ የያ.በ.አ. (ዩ.ኤፍ.ኦ) ፎቶግራፎች አሉ።

ደስታው ሁሉ ተበተነ። 'ባያምኑኝስ?' በዚህ ወቅት ነበር ሌስሊ ማዘርሼድ ሁለተኛው ሐሳብ ብልጭ ያለለት። ዘጠኝ ምስክሮች ዙሪያውን ከበውታል። እነሱም ሳያውቁት የግኝቱን እውነትነት ሊያረጋግጡለት ነው። ፊቱን ወደ ተመልካቾቹ አዞረና "ከቡራንና ከቡራት! ፎቶግራፍ እዚህ ቦታ ላይ መነሳት ከፈለጋችሁ በመደዳ ቁሙልኝ። ከዚያም ለያንዳንዳችሁ አንዳንድ ፎቶ በነፃ እልክላችኋለሁ።" ወዲያውኑ የአድናቆት ምላሽ ነበር ያገኘው።

በደቂቃዎች ውስጥ ከቄሱ በስተቀር የአውቶቡሱ ተሳፋሪዎች በያ.በ.አ.ው ሰብርባሪ ፊት ተሰለፉ።

@BOOKALEM

ቄሱ ፈቃደኛ አልሆኑም ነበር። "አልችልም። ይህ ራሱ ሰይጣን ነው!" አሉ።

ማዘርሼድ ደግሞ በይበልጥ ቄሱን ነበር የፈሊጋቸው። ከሁሉም የበለጡ አሳማኝ ምስክር ናቸውና።

"ዋናው ነጥብ ይህ ነው" አለ ሌስሊ በመገፋፋት። "ይህ በቀጥታ እርኩሳን መናፍስት ስለመኖራቸው በቂ ማሳመኛ ይሆንዎታል።" እና በመጨረሻም ቄሱ ተስማሙ።

"ትንሽ ሰፋ ሰፋ ብላችሁ ቁሙ!" አለ ማዘርሼድ። ምስክሮቹ አቋቋማቸውን ለወጡ።

"ይሄ ነው! በጣም ጥሩ! አሁን ፀጥ ብላችሁ ቁሙ።" ግማሽ ደርዘን ፎቶዎችን ካነሳ በኋላ እርሳስና ወረቀት አወጣ። "ስማችሁንና አድራሻችሁን እዚህ ላይ ከፃፋችሁልኝ እያንዳንዳችሁ ፎቶው እንዲደርሳችሁ አደርጋለሁ።" ምስሎቹን የመላክ ፍላጎት የለውም። እርሱ ተባባሪ ምስክሮች ብቻ ነው የሚፈልገው።

ከዚህ በኋላ በድንገት አንዳንድ መንገደኞች ካሜራ መያዛቸውን አስተዋለ። ከራሱ ከሌስሊ ማዘርሼድ ፎቶዎች በስተቀር ማንም ያነሳው ምስል እንዲኖር አይፈቀድም።

"ይቅርታ።" ካሜራ የያዛችሁ ሰዎች ካሜራችሁን ብታቀብሉኝ ጥቂት ፎቶ አነሳላችሁና በራሳችሁ ካሜራ የተነሳ ፎቶ ሊኖራችሁ ይችላል።"

ካሚራዎቹ በአስቸኳይ ለሌስሊ ማዘርሼድ ተሰጡት።

ማዘርሼድ በርከክ ብሎ የመጀመሪያን ምስል ማንሳት እንደጀመረ በአውራ ጣቱ የፊልም ማንሻውን ሳጥን ከፍቶ ለብርሃን ሲያጋልጠው ማንም አልተመለከተውም ነበር። 'ያሳዝናል ባልንጀሮቼ! ፕሮፌሽናሎች ብቻ ናቸው ታሪካዊ ወቅትን መጨበጥ የተፈቀደላቸው' አለ በሐሳቡ።

ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ማዘርሼድ የሁሉንም ሰዎች ስምና አድራሻ የተፃፈበትን ወረቀት ይዞ ለመጨረሻ ጊዜ በራሪውን ዲስክ ዞር ብሎ ተመለከተው። 'አዎን! እማዬ ትክክል ነበረች። ሀብታምና ዝነኛ ልሆን ነው' ሲል አሰበ። አሁን ወደ ለንደን ተመልሶ ብርቅዬ ፎቶዎቹን ለማሳደግ ጊዜ ማባከን የለበትም።

"ምን እየተፈጠረ ነው?"

በኡተንዶርፍ ዙሪያ የሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች ሌሊቱን በሙሉ በስልክ ጥሪ ሲጣደፉ ነው ያደሩት።

"አንድ ሰው በቤቴ አካባቢ እያደባ ነው!"

"እንግዳ የሆኑ መብራቶች ከውጭ ይታያሉ!"

"የቤቴ እንሰሶች በፍርሃት ሊያብዱ ነው። ተኩላዎች ሳይመጡ አይቀርም!"

@BOOKALEM

"አንድ ሰው የአትክልት ውሃዬን በሙሉ አድርቆታል።"

ከሁሉም የበለጠ ግራ የሚያጋባው ጥሪ ደግሞ "አዛዥ! በርካታ የመኪና መንተቻ ካሚዮኖች ወደ ዋናው አውራ ጎዳናው ቢልኩ ይሻላል። ነገሩ እንደቅዠት ነው። መኪኖቹ በሙሉ ቆመዋል!"

"ምን? ለምን?"

"ማንም አያውቅም።"

የመኪኖቹ ሞተር በድንገት ፀጥ አለ። በፍፁም ሁሉም የማይረሱት ምሽት ነበር።

ምዕራፍ አሥራ ስድስት

'ይህ ተልዕኮ ምን ያህል ጊዜ ይፈጅ ይሆን?' ሮበርት እየተገረመ ነበር ከስዊስ አየር መንገድ አውሮፕላን አንደኛ ማዕረግ ወንበር ጋር ወገቡን ሲያስር። አውሮፕላኑ በግዙፍ የሮልስ ሮይስ ሞተሮቹ የምሽቱን ቀዝቃዛ አየር እየተስገበገበ በመዋጥ በአስፋልቱ ላይ ሲያኮበኩብ ሮበርት ቀና ብሎ ዐይኖቹን ጨፈናቸው። 'ከጥቂት ዓመታት በፊት ከሱዛን ጋር ወደ ለንደን የበረርነው ነበር? አይደለም። ከአንድ ሰው ዕድሜ በፊት ይመስላል።'

አውሮፕላኑ ልክ በሰዓቱ ከንጋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ከሃያ ዘጠኝ ደቂቃ ላይ ለንደን ሒትሮው አየር ማረፊያ አረፈ። ሮበርት በታክሲ ተሳፍሮ ወደ መኻል ከተማ ተጓዘ። የሚያውቃቸውን ትዕይንቶች እየተመለከተ ሲያልፍ የሱዛንን የቡረቃ ድምፅ እየሰማ ነበር። በዚያን ወቅት የትም ሆነ የት ዋናው ነገር አብረው መሆናቸው ነበር። ልዩ ፍስሐቸው የመልካም ጋብቻቸው መፈጸም ነበር።

በመካከላቸው ችግሩ የተከሰተው ታይላንድ ውስጥ ጉብኝት በማድረግ ላይ እንዳሉ አድሚራል ዊታከር ባደረገው አገር አቋራጭ የስልክ ጥሪ ነው። ሮበርት ከባሕር ኃይሉ ከተሰናበተና አድሚራሉንም ካነጋገረ ስድስት ወራት ሆኖት ነበር። ባንኮክ ኦሪየንታል ሆቴል የተቀበለው የስልክ ጥሪ ያልታሰበ ነበር።

"ሮበርት? አድሚራል ዊታከር ነኝ።"

"አድሚራል ድምጽዎን መስማቴ በጣም ጥሩ ነው።"

"አንተን መፈለግ ቀላል አልነበረም። ምን እያደረክ ነበር?"

"ብዙም ነገር የለም። የተራዘመ የጫጉላ ሽርሽር በማድረግ ላይ ነበርኩ።"

"ሱዛን እንዴት ናት? ሙሽራዋ ሱዛን ናት አይደለም?"

"አዎን ደህና ናት አመሰግናለሁ።"

"በምን ያህል ጊዜ ወደ ዋሺንግተን ትመለሳለህ?"

"ይቅርታዎን!"

@BOOKALEM

"እስካሁን ይፋ ባይሆንም አዲስ ኃላፊነት ተሰጥቶኛል።" የአሥራ ሰባተኛው ቀጣና የባሕር ኃይል መረጃ ጽሕፈት ቤት ዳይሬክተር አድርገውኛል። አንተም እንድትቀላቀለኝ እሻለሁ።"

ሮበርት ያልጠበቀው ጉዳይ ነበር። "የባሕር ኃይል መረጃ? አድሚራል ስለ መረጃ ምንም አላውቅም" አላቸው።

"ልትማር ትችላለህ። ለአገርህ አንድ አስፈላጊ የሆነ ሥራ ልትሠራ ትችላለህ። ሮበርት መጥተህ ስለጉዳዩ ከኔ ጋር ትወያያለህ?"

"ደህና።"

"ሰኞ ጠዋት በ0900 ሰዓት ቢሮዬ ውስጥ አይሃለሁ። ሱዛንን ሰላም በልልኝ።"

ሮበርት ውይይቱን ለሱዛን ደገመላት።

"የባሕር ኃይሉ መረጃ? የሚያጓጓ ይመስላል።"

"ምናልባት" አለ ሮበርት በማመንታት። "ምን እንደምናገር ሐሳብ የለኝም።"

"ማወቅ አለብህ።"

ለደቂቃዎች ያህል አጠናትና "ሥራውን እንድቀበል ትፈልጊያለሽ አይደለም?"

እጆቿን ጠመጠመችበት። "ማድረግ የምትፈልገውን ነገር እንድታደርግ እሻለሁ። ወደ ሥራ ለመመለስም ዝግጁ ትመስለኛለህ። ባለፉት ሳምንታት ውስጥ ምን ያህል አረፍት የለሽ እንደሆንክ አስታውሳለሁ።"

የጫጉላው ሽርሽር ተፈፀመ። "ልታሰናብቺኝ የፈለግሽ ይመስለኛል" ሲል አሸሚጠጣት።

ብዙ ዘግይቶ ሮበርት ስለሁኔታው ሲያስታውስ የጋብቻቸው የፍጻሜ መጀመሪያ እንደነበር አስታወሰ። በወቅቱ የሥራው በረከት እፀብ ድንቅ ይመስል ነበርና። አድሚራሉን ለማየት ወደ ዋሺንግተን ተጓዘ።

"ይህ ሥራ አዕምሮን፤ ድፍረትንና ፈጠራን ይፈልጋል ሮበርት። ሦስቱም ችሎታዎች አሉህ።"

"አገራችን የኬሚካል መሣሪያዎችን ማምረት በቻሉና አሸባሪዎችን ማርባት ለቻሉ፤ ኢምንት፤ ቀጭን ቀንዳም አምባ ገነን መንግሥታት ሚላማ እየሆኑች መጥታለች። የዚህ ዐይነት ግማሽ ደርዘን አገሮች በመያዣ ሊይዙን እንዲችሉ አቶሚክ ቦምብ ለማምረት በመሞከር ላይ ናቸው። የኔ ሥራ አንድ የመረጃ ድር ዘርግቶ ምን ለማድረግ እንደሚፈልጉ ማወቅና ይህንንም ለማስቆም መቻል ነው። አንተም እንድትረዳኝ እፈልጋለሁ ።"

በመጨረሻም ሮበርት ሥራውን ሲቀበል ያስገረመው ነገር ለሥራው የተፈጥሮ ተሰጥኦ ያለውና በሥራውም ሊደሰት መቻሉ ነበር።

@BOOKALEM

ሱዛንም ሮዝሊን ቨርጂኒያ ውስጥ አንድ ማራኪ አፓርትመንት ሮበርት የሚሠራበት አካባቢ ከተከራየች በኋላ ቤቱን በማስጌጥ ሥራ ራሷን ጠመደች። ሮበርትም የሲ.አይ.ኤ ወኪሎች ወደሚሰለጥኑበት "እርሻ" ተላከ።

እጅግ በጣም ከባድ የሆነ ጥበቃ የሚደረግለትና በቨርጂኒያ ገጠራማ ክልል የተዋቀረው "እርሻ" በአብዛኛው ጥቅጥቅ ባለ ደን በተሸፈነ ሃያ ስኩዌር ማይልስ ስፋት ባለው መሬት ላይ ይገኛል። ማዕከላዊው ሕንፃ ከዋናው የመግቢያ በር ሁለት ማይሎች ራቅ ብሎ በተመነጠረ የአሥር ኤከር መሬት ላይ ተሠርቷል። አዋራማ መንገዶች፤ የተዘጉ ተውረግራጊ መሰናክሎች፤ መግባት ክልክል ነው! የሚሉ ምልክቶች ተዘጋጅተዋል። አንድ አነስተኛ የአየር ማረፊያ ላይ ምንም ዐይነት ምልክት ያልተደረገባት አውሮፕላን በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ ታርፋለች ትነሳለች። "እርሻው" ኢታላይ ውጫዊ ገጽታ አለው። ቅጠላማ ዛፎች፤ ሜዳው ላይ የሚሯሯጡ አጋዘኖችና በተንተን ያሉ ሕንፃዎች ይታያሉ። ግቢው ውስጥ ግን ፍጹም የተለየ ዓለም ነበር።

ሮበርት ከሌሎች የባሕር ኃይሉ ባልደረቦች ጋር አብሮ እንደሚሠለጥን ነበር የጠበቀው። ሆኖም ግን ሥልጠናውን አብረው የሚካፈሉት የባሕር ኃይል፤ የአየር ኃይል፤ የጦር ሠራዊት ባልደረቦችና የሲ.አይ.ኤ. ምልምሎች ሆነው አገኛቸው። እያንዳንዱ ተማሪ የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር ተሰጥቶ ከጡብ በተሠሩትና ባለሁለት ፎቅ ከሆኑት ሕንፃዎች ውስጥ ለያንዳንዱ የመኝታ ክፍል ተሰጠው። ለሮበርት የባችለር መኮንኖች ሕንፃ ውስጥ አንድ የመኝታ ክፍል ተሰጠው። እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ የግል መኝታ ክፍል ሲሰጠው የመታጠቢያ ክፍል ለሁለት ይጋራል።

ሮበርት ወደ ማሠልጠኛው ካምፕ በደረሰበት ዕለት ሌሎች ሠላሳ አዲስ መጦች ወደተሰበሰቡበት አዳራሽ ተወሰደ። አንድ ረዥም ግዙፍና ጠንካራ ቁመና ያለው ጥቁር ኮሎኔል ለአዲስ ገቦቹ ንግግር አደረገላቸው። ሰውዬው በመካከለኛው ሃምሳ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ረጋ ያለና የአዕምሮ ብስለትም ይታይበታል። በፍጥነትና በግልጽነት ቃላቶችን ሳያባክን ፍሬ ነገሩን ነበር የሚናገረው።

"ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን እባላለሁ። እንኳን በደህና መጣችሁ። በቆይታችሁ ጊዜ ሁሉ የመጀመሪያ ስማችሁን ብቻ ነው የምትጠቀሙት። ከአሁኑ ወቅት ጀምሮ ሕይወታችሁ የተዘጋ መጽሐፍ ማለት ነው። ምሥጢር ለመጠበቅ ቃለ መሐላ ፈጽማችኋል። ይህንንም ቃል ኪዳናችሁን በጣም በጣም ከልብ እንድትጠብቁት ስል እመክራችኋለሁ። ስለምታከናውኑት ሥራ ከማንም ሆነ ከማን፣ ከሚስቶቻችሁ፤ ከቤተሰቦቻችሁ፤ ከጓደኞቻችሁም ጋር ቢሆን መወያየት ወይም መነጋገር በፍጹም አትችሉም። ወደዚህ እንድትመጡ የተመረጣችሁት ልዩ የሆነ ብቃት እንዳላችሁ ስለታመነበት ሲሆን ይህንን ችሎታችሁን ለማዳበር በጣም

@BOOKALEM

በርካታ የሆነ ሥራ ከፊታችሁ ተደቅኖ ይጠብቃችኋል። ታዲያ ሁላችሁም አይሳካላችሁም።

ከዚህ በፊት ከቶም ቢሆን ሰምታችሁ የማታውቋቸው ነገሮች ውስጥ ትገባላችሁ። እዚህ የሚሰጣችሁን ትምሕርትና ሥልጠና ከጨረሳችሁ በኋላ ስለምታከናውኑት ሥራ ጠቃሚነትና አስፈላጊነት በበቂ ሁኔታ ለመግለጽ አልችልም። በአንዳንድ ገለልተኛ በሆኑ ክበቦች ዘንድ የመረጃ ድርጅቶቻችን ላይ የባሕር ኃይል፤ የአየር ኃይል፤ የጦር ኃይሉን የመረጃ ድርጅቶችም ሆኑ ራሱን ሲ.አይ.ኤ.ንም ቢሆን አንዳንድ የጥቃት ሁኔታዎችን መሰንዘር የተለመደ ዘመናዊ ተግባር እየሆነ መጥቷል። ከቡራን ሠልጣኞች! አንድ የማረጋግጥላችሁ ነገር ቢኖር እንደናንተ ዐይነት ቆራጥና ለሙያው ከልብ የተሰለፉ ሰዎች ባይኖሩ ይህች አገራችን ገሃነም ሙሉ መከራ ውስጥ እንደምትዘረፈቅ ነው። ይህም ችግር በአገራችን ላይ እንዳይደርስ በመከላከሉ ተግባር ላይ ዕርዳታችሁን ወይም እገዛችሁን መሰንዘሩ የናንተ ተግባር ይሆናል። ትምሕርቱን የምታልፉ ሁሉ "የጉዳይ መኮንኖች" ትሆናላችሁ። ነገሩን በቀላሉ ለማስቀመጥ "የጉዳይ መኮንን" ሰላይ ማለት ነው። እሱም በማስመሰያ ሽፋን የሚሠራ ይሆናል።

እዚህ ቦታ በምትቆዩበት ጊዜ በዓለም ላይ አለ የተባለው ምርጥ ሥልጠና ሁሉ ይሰጣችኋል። ስለላና የፀረ ስለላ ሥራ (counter inteligence)፣ የራዲዮ መገናኛ ጥበብ፤ የምሥጢር ቃላት አፈታት፤ የጦር መሣሪያዎች አጠቃቀምና ካርታ የማንበብ ትምሕርት ሁሉ ይሰጣችኋል። ከሰዎች ጋር የመገናኘት ጥበብ፤ ዘገባዎችን የማቀናበር፤ የሰዎችን ፍላጎቶች ማግኘትና ማነሳሳት፤ ዒላማችሁ ለሆነ ሰው የስሜት አፎይታ የማሳደር ትምሕርት ሁሉ ትከታተላላችሁ።"

ክፍሉ በሙሉ ኮሎኔሉ በሚናገረው በያንዳንዷ ነጠላ ቃል ላይ ልቡ ተንጠልጥሏል።

"የስለላ ወኪልን እንዴት መገናኘትና መመልመል እንደምትችሉም ትሠለጥኑበታላችሁ። ከመረጃ አቀባይ ጋር የሚደረጉ ስብሰባዎች የሚከናወኑበትን አስተማማኝ ቤት (safe house) የመምረጥ ትምሕርትም ታገኛላችሁ።

ስለምሥጢራዊ መረጃዎች መቀባበያ ሥፍራና ወኪሎቻችሁን እንዴት በሽፋን ለመገናኘት እንደምትችሉም ትማራላችሁ። በምታከናውኑት ተግባር ላይ ብቃት የምታሳዩ ከሆነ ተልዕኮአችሁን ሁሉ ማንም ሳያስተውላችሁና ሳትታወቁ ለመወጣት ትችላላችሁ።"

አየሩን የወጠረው የጉጉት ስሜት ሮበርት ይሰማዋል። "አንዳንዶቻችሁ በኦፊሴላዊ ሽፋን ስር ስትሠሩ ይህ ወታደራዊ ወይም ዲፕሎማቲካዊ ሽፋን ሊሆን ይችላል። ሌሎች ደግሞ ያለምንም ኦፊሴላዊ ሽፋን ይሠራሉ። ይህም የንግድ ሰው፤ ነፃ ግለሰብ፤ የታሪክ ቅርስ ተመራማሪ፤ ጸሓፊ በመምሰል ወይም ለማግኘት ወደምትፈልጉትና ወደምትቃርሙት የምሥጢር መረጃ ሊያቀርባችሁ የሚችል

@BOOKALEM

ማናቸውም የማስመሰያ ሽፋን ሊሆን ይችላል። አሁን ወደ አሰልጣኞቻችሁ መልካም ዕድል ይግጠማችሁ እያልኩ አስተላልፋችኋል።"

ሮበርት ሥልጠናውን እጅግ የሚያስደስት ሆኖ አገኘው። አሠልጣኞቹ በመስክ ሥራ ላይ ተሠማርተው የነበሩ ፕሮፌሽናል ባለሙያዎች ነበሩ። ሮበርት ቴክኒካዊ የሆኑ ሥልጠናዎችን በቀላሉ ከመቀበሉም በላይ ከሚሰጡት ኮርሶች በተጨማሪ ኮሎኔል ጆንሰን ደግሞ በተለያዩ ልሳኖች የማሻሻያ ትምሕርትና የምሥጢር ቃላት አጠቃቀም ትምሕርትም እንደሚኖር ይነግራቸዋል።

ሮበርት ኩሎኔል ጆንሰንን ፍጹም እንቆቅልሽ ሰው ሆኖ ነበር ያገኘው። ስለኩሎኔሉ ውስጥ ለውስጥ የሚወራው ሹክሹክታ ሰውዬው በዋይት ሐውስ ጠንካራ የሆነ ግንኙነት እንዳለውና እጅግ ከፍተኛ በሆነ ምሥጢራዊ ሥራዎች ውስጥ እንደሚሳተፍ ነበር። ለአያሌ ቀናት ከማሠልጠኛው ሰፈር አልም ብሎ ይጠፋና ሳይታሰብ ከች ይላል።

ሮን የተባለ የስለላ ወኪል ለክፍሉ ሌክቸር እየሰጠ ነበር። "በምሥጢራዊ የስለላ ሥራ ውስጥ ስድስት ዐይነት ቅርንጫፎች አሉ።

የመጀመሪያው መለየት ወይም ለይቶ ማወቅ ነው። ለምትፈልጉት መረጃ ቀረቤታ ያለውን ግለሰብ መለየት ነው። አንድ ጊዜ ዒላማችሁ የሚሆነውን ሰው ካነጣጠራችሁበት የምትፈልጉትን መረጃ ሰውየው ማግኘት ይችላል ወይም አይችልም ብላችሁ ትወስናላችሁ። ለምልመላም ተገቢ መሆኑ ታረጋግጣላችሁ።

ሰውዬውን ያነሳሳው ምንድን ነው? በሥራው ደስተኛ ነው ወይ? ከአለቃው ጋር አለመግባባት አለበት ወይ? የገንዘብ እጥረት አለበት ወይ? ተስፋው የሚያስተማምን ከሆነና ሰውየውን ለስለላ ወኪልነት የሚያነሳሳው ልትጠቀሙበት የሚያስችል በቂ ምክንያት ካለ ወደ ሦስተኛው ደረጃ ትሻጋራላችሁ።

ሦስተኛው ደረጃ "ዕድገት" ነው። ከታሳቢው ሰው ጋር መልካም ግንኙነት መመሥረት። በተቻለ መጠን ቶሎ ቶሎ ከሰውዬው ጋር በድንገት የመገጣጠም ወይም የመገናኘት ሁኔታ መፍጠርና ዘገባ ማዘጋጀት። የሚቀጥለው ደረጃ ደግሞ "ምልመላ" ይሆናል። ሰውየው ለሥራ ዝግጁ ነው ብላችሁ ስትገምቱ የሥነ–ልቦና ቅየሳ ታደርጉበታላችሁ። ገንዘብና በገንዘብ የሚገኝ ፍሰሐ፤ አለቃውን መበቀል፤ ወይም ማናቸውንም ያላችሁን የሥነ–ልቦና መሣሪያ ሁሉ በተመልማዩ ላይ ትጠቀማላችሁ። የጉዳይ መኮንኑ ተግባሩን በብቃት ካከናወነ ታሳቢው ምንጊዜም በመመልመሉ ይስማማል። እስካሁን በጣም ጥሩ። አሁን ለናንተ የሚሠራ ሰላይ አገኛችሁ ማለት ነው። የሚቀጥለው ደረጃ የሰላዩ አያያዝ ሁኔታ ነው። ከማንኛውም ችግርና አደጋ ራሳችሁን ብቻ ሳይሆን ሰላያችሁንም ጭምር ነው መከላከል የሚኖርባችሁ። ምሥጢራዊ ስብሰባዎችን ታዘጋጃላችሁ። በማይክሮ ፊልማና በምሥጢር አጠቃቀም ላይ ሥልጠና ትሰጡታላችሁ። ስለላን

@BOOKALEM

ስለማከናወንና ተይዞ ሲጠይቅ ምን መልስ መስጠት እንዳለበት ታስተምሩታላችሁ።

የመጨረሻው ተግባር "መለያየት" ይሆናል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሰላያችሁ ወደ ሌላ ሥፍራ ለሌላ ሥራ ይዘዋወርና እናንተ ከምትፈልጉት መረጃ ጋር ይለያያል። ወይም ደግሞ ሊያቀብላችሁ የሚችለው የመረጃ ዐይነት አስፈላጊነት ወይም ጠቀሜታ ሊያበቃ ይችላል። በማንኛውም ምክንያት ግንኙነታችሁ ያበቃል። ታዲያ ግንኙነታችሁ ማብቃት የሚኖርበት ከሆነ ሰውዬው በመሣሪያነት እንደተጠቀማችሁበት እንዳይሰማውና ለብቀላ እንዳይነሳሳ በሚሆን ጥበብ መከናወን አለበት።"

ኮሎኔል ጆንሰን የተናገረው ትክክል ነበር። ሁሉም ሠልጣኞች ኮርሱን መወጣት አልቻሉም። የተለመዱ ፊቶች በግቢው ውስጥ ከመታየት ጠፉ። ለምን እንደሆነ ማንም አላወቀም አልጠየቀምም።

አንድ ቀን ቡድኑ ለክትትል ትምሕርት ወደ ሪችመንድ ለመሄድ በሚዘጋጅበት ጊዜ "ምን ያህል ግሩም ሰላይ እንደ ሆንክ ለማየት ተዘጋጅተናል ሮበርት" አለው አሠልጣኙ። አንተን የሚከታተል አንድ ሰው ልልከብህ ነው። እንድትሰወርበት እፈልጋለሁ ። የምታደርገው ይመስልሃል?

"አዎን ጌታዬ!"

"መልካም ዕድል።"

ሮበርት ወደ ሪችመንድ በአውቶቡስ ከተጓዘ በኋላ የከተማው አውራ መንገዶች ላይ በእግሩ መዘዋወር ጀመረ። የሚከተሉት ሰዎች (አጥሊዎች) ሁለት ነበሩ። አንዱ በእግሩ ሲሆን አንደኛው በአውቶሞቢል ነበሩ። ሮበርት ቡና ቤቶችና ሬስቶራንቶች ውስጥ ዘው ብሎ ገብቶ በኋላ በር ለመጥፋት ቢሞክርም ተከታታዮቹን ከላዩ ላይ ሊያራግፋቸው አልቻለም። በጣም የሠለጠኑ ነበሩና። አሁን ወደ ካምፕ የመመለሻው ሰዓት እየደረሰ ሲሆን ሮበርት ግን ከሰዎቹ ተሰውሮ ለመጥፋት አልቻለም። በቅርበት እየተከታተልኩት ነው። ሮበርት አንድ የገበያ አዳራሽ ውስጥ ሲገባ ሰዎቹ የሕንፃውን መግቢያና መውጫ ሊቆጣጠሩ የሚችሉበትን ሥልታዊ ሥፍራ ሲይዙ ሮበርት በኤሌክትሪክ የሚሠራውን ተንቀሳቃሽ ደረጃ በመጠቀም ወደ ወንዶቹ የገበያ ፎቅ ወጣ። ከሠላሳ ደቂቃዎች በኋላ ተመልሶ ሲወርድ ሌላ ሙሉ ልብስ ለብሶ፤ ባርኔጣ አድርጎ፤ ሕፃን ልጅ ታቅፎና ከአንዲት ሴት ጋር እያወራ ወጣ። አሳዳጆቹ ልብ ሳይሉት በአጠገባቸው አለፈ።

በዕለቱ የአጥሊዎቹን ክትትል ሊያመልጥ የቻለ ብቸኛ ሰው ሮበርት ብቻ ነበር። በካምፑ ውስጥ የቋንቋ ትምሕርትም ይሰጥ ነበር።

@BOOKALEM

“ምናልባት እነዚህን ቃላት ላትጠቀመባቸው ትችሉ ይሆናል። ቢሆንም ግን ብታውቋቸው አይከፋም” አለ አስተማሪው። ሁለት ዐይነት ወኪሎች አሉ። “የተጽእኖ ወኪል” እና “አበሳጭ ወኪል” ይባላሉ።

“የተጽእኖ ወኪል” በሚሠራበት አገር ውስጥ ያለውን አስተሳሰብ ለመለወጥ ይሞክራል። “አበሳጭ ወኪል” ደግሞ በተሠማራበት አገር ውስጥ ረብሻና ብጥብጥ እንዲፈጠር ያደርጋል። “የሕይወት ታሪክ ምሣር” (ባዮግራፊክ ሌቨሬጅ)” ማለት ደግሞ ሰዎችን በደካማ ጎናቸው ማጥመድ ወይም ምርኮኛ የማድረግ የሲአይኤ. ምሥጢራዊ ቃል ነው። እንደዚሁም “የጥቁር ከረጢት” (ብላክ ባግ ጆብ) ሥራዎች አሉ። እነዚህም ጉቦ ወይም መደለያ ከመስጠት ጀምሮ እስከ ቤት ሰርሰራ ድረስ ይለያያሉ። ዋተር ጌት “የጥቁር ከረጢት” ሥራ ውጤት ነበር።”

ከፍሉ በትኩረት ይከታተለው እንደሆን ለማረጋገጥ ቃኘት አደረገው። ልባቸው ቆሞ ነበር።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥቂቶቻችሁ “ጫማ አዳሽ” ልትፈልጉ ትችላላችሁ። ይህ ደግሞ የሐሰት ፓስፖርት ሊያዘጋጅላችሁ የሚችል ሰው ማለት ነው።

ሮበርት ‘ጫማ አዳሽ መጠቀም የምሻበት ወቅት ይመጣ ይሆን?’ ሲል አሰበ። “በኢያሌው ማውረድ–መሻር” (ቱ ዴሞት ማከሲማሊ) የሚለው ሐረግ ደግሞ አልባሌ አባባል ነው። ይህም "በግድያ ማስወገድ" ማለት ነው። “ተርሚኔት” (ማስወገድ) የሚለው ቃልም ትርጉሙ ተመሳሳይ ነው። አንድ ሰው “ድርጅቱ” “(ዘ ፈርም)” ሲል ከስማችሁ የእንግሊዝ የመረጃ ድርጅትን ማለቱ እንደሆነ እወቁ። አንድን ቢሮ “በጢስ” እንዲታጠን እንድታደርጉ ብትጠየቁ የምትፈልጉት ነገር ምስጥ ሳይሆን “የምሥጢር ማዳመጫ መሣሪያዎችን” ይሆናል።

ገለፃው ሮበርትን እጅግ እያስደነቀው ነበር። “ወይዛዝርት” የሚለው ሐረግ ቅራኔን ለመጨማመር የሚላኩ የሴት ወኪሎችን ይመለከታል። “አፈ–ታሪክ “(ሌጅንድ)” የሚለው ቃል የተቀነባበረ የሰላይ የሐሰት የሕይወት ታሪክ” ማለት ነው። “በግል መሄድ” (ጎይንግ ፕራይቬት)” ማለት ደግሞ የሥለላውን ድርጅት መተው ማለት ነው።

አስተማሪው ከፍሉን መልከት አደረገና.....“እንበሳን ማልመድ” ማለት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?” ሲል ጠየቀ። መልስ ጠበቀ። ግን አንዳችም አልነበረም።

“እንድ ወኪል ከሥራ በሚሰናበትበት ጊዜ ብስጭት ያድርበትና የሚያውቀውን ነገር ሁሉ ይፋ አወጣለሁ ሲል ያስፈራራል። ጡንቻማ ሰው”ወይም "እንበሳ አልማጅ"”ይላከና ሰውየው ከቁጣው እንዲበርድ ይደረጋል።

“እርግጠኛ ነኝ አንዳችሁም ከእንበሳ አልማጅ ጋር አትደራደሩም!” ይህ ንግግሩ ውጥረት የመላበት ሳቅ አስከተለ።

@BOOKALEM

"ኩፍኝ" የሚሉትም ቃል አለ። አንድ ሰው በ "ኩፍኝ" ሞተ ማለት አገዳደሉ በጣም የተራቀቀና ብቃት ያለው ከመሆኑ የተነሳ አሟሟቱን ድንገተኛ አደጋ ወይም የተፈጥሮ አሟሟት ለማስመሰል ተችሏል ማለት ነው። የኩፍኝ ግድያ ከሚደረግባቸው ነገሮች አንዱ "ታቡን" የተባለ መርዝ ነው። ይህ ኬሚካል ቀለም የለሽ ወይም ቡናማ መልክ ያለው ፈሳሽ ውሁድ ሲሆን በሰውነት ቆዳ ውስጥ ዘልቆ ሲገባ የነርቭ አውታሮችን በመበከል ይገድላል። አንድ ሰው "የሙዚቃ ሳጥን" ከሰጠህ "እሳላፊና ተቀባይ ራዲዮ" ሰጠህ ማለት ነው። የራዲዮ አፕሬተሩ "ሙዚቀኛ" ይባላል። ወደ ፊት ጥቂቶቻችሁ እርቃናችሁን" ትሠራላችሁ። ልብሳችሁን ለማወላለቅ አትጣደፉ! "እርቃን" ማለት ያላንዳች ዕርዳታና ድጋፍ ብቻችሁን ግዳጃችሁን መወጣት ማለት ነው።

በዛሬው ዕለት ላወያያችሁ የምፈልገው አንድ ተጨማሪ ነገር አለ። "አጋጣሚ"። በኛ ሥራ ውስጥ "አጋጣሚ" ሁልጊዜ አደጋ ማለት ነው። አንድን ሰው አሁንም አሁንም ብታገኙት ወይም በእንቅስቃሴ ላይ እያላችሁ አንድ መኪና በተደጋጋሚ ብታዩ ራሳችሁን ደብቁ። ምናልባት አደጋ ላይ ትሆናላችሁና። ለዛሬ ይበቃናል ከቡራን! ነገ ካቆምንበት እንቀጥላለን።"

ከጊዜ ወደጊዜ ኮሎኔል ጆንሰን ሮበርትን ቢሮው ይጠራዋል። "እንድናወጋ" ነበር የሚለው ኮሎኔሉ። ውይይቱ በሚያታልል ሁኔታ የተለምዶ ቢመስልም ሮበርት ግን ከንግግራቸው ጀርባ አንድ የተደበቀ ነገር እንዳለ ነቅቷል።

"በደስታ ተጋብተሃል ብዬ አምናለሁ ሮበርት።"

"ትክክል።"

ለሚቀጥለው ግማሽ ሰዓት ስለጋብቻ ታማኝነትና እምነት ተጨዋወቱ። ሌላ ጊዜ ደግሞ "አድሚራል ዊታከር እንደ ልጁ ነው የሚያይህ። ይህን ታውቃለህ ሮበርት?"

"አዎን። የኤድዋርድ ሞት ሐዘን የሚረሳ አይደለም።"

"ሞትን ከአንድ ጊዜ በላይ ተጋፍጠህዋል። መሞት ትፈራለህ ሮበርት?"

"የለም።" 'ግን ለጥሩ ዐላማ መሞት' ሲል አሰበ።

ውይይታቸው ሁሉ ሮበርትን ያሸብረው ነበር። ልክ በማሳሳቻ መስተዋት ውስጥ የሚመለከተው ይመስለዋል። ኮሎኔል ጆንሰን ሮበርትን ግልጽ አድርጎ ሊያየውና ሊረዳው ሲችል ኮሎኔሉ ግን ለሮበርት እንደ እንቆቅልሽ ሰውር የሆነ ምሥጢራዊ ሰው ሆነበት።

ኮርሱ አሥራ ሰድስት ሳምንታት የፈጀ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ አንዱም ሠልጣኝ ከውጭው ዓለም ጋር ግንኙነት እንዲፈጥር አይፈቀድለትም ነበር። የናፈቁት አራቱ ወራት እንደተገባደዱ ኮሎኔል ጆንሰን ሮበርትን ወደ ጽሕፈት ቤቱ አስጠራው።

@BOOKALEM

"ያሁኑ ጥሪ ስንብት ነው። በጣም እጅግ በጣም ግሩም የሆነ ሥራ ነው ያከናወንከው ኮማንደር ቤላሚ። የወደፊት ዕጣህ በጣም ማራኪ ሆኖ ታገኘዋለህ ብዬ አስባለሁ።"

"አመሰግናለሁ ጌታዬ! እኔም እንደሱ አስባለሁ።"

"መልካም ዕድል።"

ኮሎኔል ጆንሰን ሮበርት ከቢሮው ወጥቶ ሲሄድ በፀጥታ ተመለከተው። ወንበሩ ላይ ለአምስት ደቂቃዎች ያህል በማሰብ ሲቆዝም ከቆየ በኋላ አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ። ስልኩን ብድግ አደረገና ጥሪ አደረገ።

ሱዛን እየጠበቀችው ነበር። የአፓርትመንቱን በር ስትከፍትለት መላ አካሏን ግልፅ አድርጉ የሚያሳይ ስስ ልብስ ለብሳ ነበር። እላዩ ላይ ተቀመጠችበትና ጥብቅ አድርጋ ያዘችው።

"እንደምን ነህ ባሕረኛው! ጥሩ ጊዜ ለማሳለፍ ትሻለህ?"

"አንቺን በማቀፌ አንድ ጥሩ ጊዜ ይዣለሁ" አለ በደስታ አነጋገር።"

"በጣም ጥሩ! በጣም ነበር የተለየሽኝ። ካሁን በኋላ አንድ ነገር ቢደርስብህ እሞታለሁ።"

"ምንም ነገር አይመጣብኝም።"

"ቃል ትገባለህ?"

"ቃል እገባልሻለሁ።"

ለደቂቃዎች ያህል በትኩረት አጠናችው። "የደከመህ ትመስላለህ።"

"በጣም ጥልቅና አድካሚ ኮርስ ነበር" ሲል አረጋገጠላት። "መጠናትና መነበብ ከሚገባቸው ጽሑፎችና ከተግባራዊው ልምምድ አኳያ እያንዳንዱ ምልምል በአንድ ምሽት ከጥቂት ደቂቃዎች በላይ ለመተኛት አይችልም ነበር። ይህ የሚሰጣቸው ትምሕርትና ሥልጠና አንድ ቀን ሕይወታቸውን እንደሚያድንላቸው ጠንቅቀው ያውቃሉና።"

"ምን እንደምትሻ በትክክል አውቃለሁ!" አለች ሱዛን።

ሮበርት ሳቅ አለና ተጠጋት።

"ቆየኝ አምስት ደቂቃ ብቻ ሰጠኝ። ልብሶቼን ላወላልቅ።"

ጥላው ስትሄድ ተመለከተና 'አንድ ሰው ከዚህ የበለጠ እንዴት ዕድለኛ ሊሆን ይችላል?' ሲል አሰበና ልብሱን ማወላለቅ ጀመረ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሱዛን ተመልሳ መጣች። "እራቁትህን ስትሆን እንዴት እወድሃለሁ?" አለችው።

የአሠልጣኙ ድምጽ ተሰማው። 'ጥቂቶቻችሁ ራቁታችሁን ትሠራላችሁ። ይህም ያለምንም ዕርዳታ ብቻችሁን ማለት ነው። ራሴንና ሱዛንን እምን ውስጥ ነው የከተትኩት?'

@BOOKALEM

ወደ መታጠቢያ ቤት እየመራች ወሰደችው። የመታጠቢያ ገንዳው በሙቅ ውሃ የተሞላ ሲሆን ገንዳው ጠርዝ ላይ ከተቀመጡት አራት ሻማዎች በስተቀር ክፍሉ በጨለማ ተውጧል።

"እንኳን በደህና ወደ ቤት መጣህ ፍቅሬ!" አለችና ሰስ ፒጃማዋን አውልቃ ገንዳው ውስጥ ገባች። እሱም ተከተላት!

"ሱዛን....."

"ምንም አትናገር። ገንዳው ላይ ጋለል በል።" ትከሻውን ጀርባውን ስታሻሸው ይሰማዋል። ለስላሳ ገላዋ ሲዳስሰው ምን ያህል ደክሞት እንደነበር ዘነጋው። የሞቀው ውሃ ውስጥ ፍቅር ሠሩ። ጨራርሰው ገላቸውን ሲያደራርቁ "ይህ ቅድመ ጨዋታ ነው። አሁን ወደ አልጋችን እንሂድ" አለችው።"

በድጋሚ ፍቅር ሠሩ። ሮበርት ሱዛንን በክንዶቹ እቅፍ አድርጓት እንደተኛ 'ሁልጊዜም እንደዚህ ይሆናል። ለዘለዓለም!' ሲል አሰበ።

ምዕራፍ አሥራ ሰባት

በማግስቱ ጠዋት ሮበርት ሥራውን ለመጀመር ፔንታገን በሚገኘው አሥራ ሰባተኛው ቀጣና የባሕር ኃይል መረጃ ጽሕፈት ቤት ሪፖርት አደረገ።

"እንኳን ደህና መጣህ ሮበርት። ኮሎኔል ጆንሰን ባንተ በጣም ነው የተመሰጠው።"

ሮበርት ፈገግ አለና "ኮሎኔል ጆንሰን በራሱ በጣም የሚመስጥ ሰው ነው" አለ።

ቡና እንደቀረበም "ሥራህን ለመጀመር ዝግጁ ነህ?" አለ አድሚራሉ።

"በጣም ጓጉቻለሁ።"

"ጥሩ! ሮዴሺያ ውስጥ አንዳንድ ሁኔታዎች አሉን....."

ሮበርት በባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤት ውስጥ መሥራትን ከጠበቀው በላይ በስሜት የሚሞላ ነው የሆነበት። እያንዳንዱ ተልዕኮ የተለያየ ከመሆኑም በላይ ለሮበርት የሚሰጠው ግዳጅ ደግሞ "እጅግ በጣም ምሥጢራዊ" ከሚባሉት ውስጥ ነበር። ከፓናማ የኖሪጋን አደንዛዥ እጽ አመላላሽ ቡድን ያጋለጠ ሰው አስመልጦ አምጥቷል። ማኒላ በሚገኘው የአሜሪካ ቆንስላ ውስጥ ለማርቆስ የሚሠራ ወንጀለኛን አጋልጧል። ሞሮኮ ውስጥ የምሥጢር ማዳመጫ መሣሪያ ለመጥለፍ ችሏል። ወደ ምሥራቅ ኢንዲስና ደቡብ አሜሪካ ለግዳጅ ተልኳል። በዚህ ሁሉ መኻል በጣም የሚረብሸው ነገር ከሱዛን ጋር መለየቱ ነው። ከእርሷ መለየት በጣም ነበር የሚጠላው። ከሥራው የሚያገኘው የስሜት እርካታ ሲኖረው

@BOOKALEM

ሱዛን ግን ምንም የላትም። የሮበርት ተልዕኮ እየጨመረ በመጣ ቁጥር ከቤት የሚያሳልፈው ጊዜ እጅግ በጣም ትንሽ ነበር።

እናም በዚህ ወቅት ነው ከሱዛን ጋር ያለው ችግር እየጠነከረ የመጣው።

ሮበርት ወደ ቤቱ ተመልሶ በመጣ ቁጥር ሁለቱም በተራበ ሰሜት ሮጠው ይተቃቀፋሉ። ጣፋጭ ፍቅርም ይሠራሉ። ግን እንደዚህ ዐይነቶቹ ጊዜያት በጣም በጣም እየራቁ ሲመጡ ለሱዛን ሁኔታው የሚታያት ሮበርት ከተላከበት ተልዕኮ ቶሎ መመለስ እንደማይችል ነው።

ሁኔታውን በጣም አስከፊ የሚያደርገው ደግሞ ሮበርት ስለሥራው ከሱዛን ጋር አለመወያየቱ ነው። ወዴት እንደ ሄደና ምን እንደሚሠራ ሱዛን የምታውቀው ነገር የለም። የምታውቀው ነገር ቢኖር ምንም ዐይነት ነገር ውስጥ ይኑር አደጋ ውስጥ እንዳለ ነበር የሚሰማት። እናም አንድ ቀን እንደወጣ ይቀራል ብላ ትሸበር ነበር። ጥያቄ ልትጠይቀው ግን ከቶም ቢሆን አትቃጣም። በሕይወቷ ውስጥ አስፈላጊ የሆነው ምዕራፍ እንደተዘጋባትና ፍፁም እንግዳ ሰው ሆኖ ነበር የሚታያት። አንድ ቀን 'በዚህ ሁኔታ ልቀጥል አልችልም!' ስትል ወሰነች።

ሮበርት በማዕከላዊ አሜሪካ አራት ሳምንት ከፈጀበት ግዳጅ እንደ ተመለሰ "ሮበርት...ስለሁኔታዎች ብንነጋገር የተሻለ ይመስለኛል" አለችው።

"ችግሩ ምንድነው?" አለ ሮበርት። ችግሩን ምን እንደሆነ ግን በሚገባ ያውቀዋል።

"እጅግ በጣም ፈርቻለሁ። አንዳችን አንዳችንን እያመለጥን ነው። እናም እንድንተጣጣ አልፈልግም። ፍጹም ልቋቋመው አልቻልኩም።"

"ሱዛን"

"ቆየኝ ልጨርስ። ባለፉት አራት ወራት ውስጥ ምንያህል ጊዜ አብረን እንዳጠፋን ታውቃለህ? ከአራት ሳምንታት በታች። ወደ ቤት በተመለስክ ቁጥር እንደባሌ ሳይሆን እንደእንግዳ ሆነህ ነው የምትታየኝ።"

ሱዛንን ወደ ራሱ ጥብቅ አስርጎ አቀፋትና "ምን ያህል እንደማፈቅርሽ ታውቂያለሽ" አላት። ራሷን ትከሻው ላይ ጣል አደረገችና "እባክህ አንድም መጥፎ ነገር እንዳይደርስብህ አድርግ" አለችው።

"አደርጋለሁ። አድሚራል ዊታከርንም አነጋግረዋለሁ።"

"መቼ?"

"አሁኑኑ!"

"አድሚራሉ አሁን ሊያዩህ ይፈልጋሉ ኮማንደር።"

"አመሰግናለሁ።"

@BOOKALEM

ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ወረቀቶች ይፈራረም የነበረው አድሚራል ዊታከር ቀና ብሎ ሮበርትን ተመለከተና ፈገግ አለ። "እንኳን በደህና ወደ ቤትህ መጣህ። እንኳንም ደስ ያለህ። ኤልሳልቫዶር ውስጥ ያከናወንከው ተግባር እጅግ በጣም ድንቅ ነበር።"

"አመሰግናለሁ ጌታዬ።"

"ተቀመጥ። ጥቂት ቡና ይሰጥህ?"

"የለም አልፈልግም። አመሰግናለሁ አድሚራል።"

"ልታነጋግረኝ ትፈልጋለህ? ጸሓፊዬ ጉዳይህ አስቸኳይ እንደነበረ ነግራኛለች። የማደርግልህ ነገር አለ?"

ለመጀመር አስቸጋሪ ሆነበት። "አዩ ጌታዬ? ይህ የግል ጉዳይ ነው። ካገባሁ እነሆ ሁለት ዓመታት ሊሆነኝ ነው እናም....."

"በጣም ድንቅ ምርጫ ነው ያደረከው ሮበርት። ሱዛን መልካም ሴት ናት።"

"አዎን እስማማለሁ። ችግሩ ታዲያ ብዙ ጊዜ ከቤት መራቄ ነው። በዚህ ሁኔታ አልተደሰተችም።" ፈጠን አለና "ይህ ደግሞ መብቷ ነው። ጤናማ ሁኔታ አይደለምና" አለ።

አድሚራል ዊታከር ወደ ወንበሩ መደገፊያ ጋለል አለና ቢሐሳብ ተመሰጠ። በእርግጥ የምትሠራው ሥራ የተለመደ አይደለምና አንዳንድ ጊዜ መስዋእትነትንም ይጠይቃል።"

"አውቃለሁ" አለ ሮበርት ድርቅ ብሎ። "ትዳሬን መስዋዕት ለማድረግ ግን ገና ዝግጁ አይደለሁም። ትዳሬ ለኔ በጣም ብዙ ነገር ማለት ነው።"

አድሚራሉ በትኩረት እያጠናው "ገባኝ" አለ። አዎ ገባኝ! ምንድን ነው የምትጠይቀው?"

"ከቤት ብዙ አርቆ የማይወስደኝ ሥራ እዚሁ ሊሰጡኝ ይችላሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ሥራችን በጣም ሰፊ ስለሆነ በቤቴ አቅራቢያ ሆኜ ልሠራ የምችለው በመጻ የሚቆጠር ሥራ ይኖር ይሆናል።"

"በቤትህ አቅራቢያ?"

"አዎን።"

"አንድ ተሰጥቶሃል! ይህን ዐይነቱን ሥራ የማታገኝበት ምክንያት አይታየኝም።"

ሮበርት በእፎይታ ተነፈሰ። "በጣም ጥሩ ሰው ነዎት አድሚራል። ይህንንም ውሳኔዎን በጣም አደንቅልዎታለሁ።"

"አዎን! ይህንን ማቀናበር እንችላለን ብዬ አስባለሁ። በል ሮበርት ችግሩ መወገዱን ሰሉዛን ንገርልኝ።"

@BOOKALEM

ሮበርት ፈገግታ ተላብሶ ብድግ አለ። "እንዴት እንደማመሰግንዎ" አላውቅም።

አድሚራሉ በስንብት እጁን እያወናጨፈ "ለኔ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለህ አንድም ነገር እንዲደርስብህ የማልሻ ሰው ነህ። አሁን ወደ ቤትህ ለሙሽራህ ሂድላት" አለው።

ሮበርት ዜናውን ለሱዛን ሲነግራት እጅግ በጣም ነበር የተደሰተችው። እጆቿን ጠመጠመችበትና "አ! ፍቅሬ ይህ እጅግ በጣም ድንቅ ነው!" አለችው።

"የሁለት ሳምንታት ያህል እረፍት እጠይቀውና ወደሆነ ቦታ እንጓዛለን። ይህም ደግሞ የጫጉላ ሽርሽራችን ይሆናል" አላት።

"የጫጉላ ሽርሽር ምን እንደሆነ ዘንግቼው ነበር አሳየኝ" አለችው። ሮበርትም አሳያት።

በማግስቱ ጠዋት አድሚራል ዊታከር ሮበርትን አስጠራው። "በትናንትናው ዕለት ስለተነጋገርንበት ጉዳይ አንዳንድ ዝግጅቶችን እንዳደረኩ ላሳውቅህ እሻለሁ።"

"አመሰግናለሁ ጌታዬ!" ሮበርት 'አሁን ነው ፈቃድ የመጠየቂያው ሰዓት!' ሲል አሰበና "ጌታዬ....."

"ግን አንድ ነገር ተፈጥሯል ሮበርት!" አለና አድሚራሉ አቋርጦት መንገራደድ ጀመረ። በሚናገርበት ጊዜ በድምፁ ውስጥ ጥልቅ የሆነ ስሜት ይደመጥበታል። "ሲ.አይ.ኤ ውስጥ ሰርጎ የመግባት ችግር እንዳለ ተነግሮኛል። በጣም ከፍተኛ የሆነ የምሥጢር መባከን ተፈጥሯል። ስለሰላዩ የሚያውቁት ነገር ቢኖር የምሥጢር ስሙ "ቀበሮው" መሰኘቱን ብቻ ነው። አሁን የሚገኘው አርጀንቲና ውስጥ ነው። ተልዕኮውን ለማከናወን ከሲ.አይ.ኤ ውጭ የሆነ ሰው ይፈልጋሉ። ሰውየውን አድነህ እንድታመጣላቸው ይፈልጋሉ። ውሳኔውም ያንተ ብቻ መሆኑን አሳውቄአቸዋለሁ። ተልዕኮውን ልትረከብ ትችላለህ?"

ሮበርት አቅማማ። "ይህንን ማለፍ ይገባኛል እላለሁ ጌታዬ።"

"ውሳኔህን አከብራለሁ ሮበርት። በተከታታይ ለግዳጅ ከመጓዝህም በላይ ተልዕኮ አልቀበልም ብለህ አታውቅም። ከትዳርህ አንፃር ቀላል ጉዳይ እንዳልሆነ አውቃለሁ።"

"ይህንን ሥራ ለመቀበል እሻለሁ ጌታዬ! ነገር ግን....."

"ይህን መናገር አይገባህም ሮበርት። ስለሥራህና ቆራጥነትህ ያለኝ አመለካከት ምንጊዜም አይለወጥም። አንድ የምጠይቅህ ውለታ አለ።"

"ምን ይሆን አድሚራል?"

"የሲ.አይ.ኤ ምክትል ዳይሬክተር ውሳኔህን በሚመለከት ሊያይህ ይፈልጋል። ቅር ይልህ ይሆን ሮበርት?"

በማግስቱ ሮበርት በማለዳ ተነስቶ ወደ ላንግሌይ ለስብሰባው አመራ።

@BOOKALEM

"ተቀመጥ ሮበርት!" አለ ምክትል ዳይሬክተሩ ትልቁ ቢሮ ውስጥ እንደገባ። "ስላንተ ብዙ ነገር ሰምቻለሁ ኮማንደር። በእርግጥ ሁሉም ጥሩ የሆነ ነገር።"

"አመሰግናለሁ ጌታዬ!"

"ምክትል ዳይሬክተሩ ከሥልሳዎቹ ዓመታት ከፍ ያደረገ ሲሆን መልካም ነጭ ፀጉር ያለውና ፒፓውን በማገ ቁጥር ከፍ ዝቅ የሚል ራዝ ያለው ሰው ነው። የ የል ዩኒቨርስቲ ምሩቅ ከመሆኑም በላይ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ኤ.ኤስ.ኤስ ይባል በነበረው የመረጃ ድርጅት ሲሠራ ቆይቶ ጦርነቱ እንዳበቃ ሲ.አይ.ኤ ሲመሠረት ወደዚያው ተዛወረ። በተከታታይም በመላው ዓለም ኃያል በሆነው የመረጃ ድርጅት ውስጥ በማዕረግ እያደገ ወደ ላይ ወጣ።

"ኮማንደር ውሳኔህን ከልብ እንደማከብር እንድታውቅልኝ እሻለሁ።"

"አመሰግናለሁ ጌታዬ።"

"ላሳውቅህ የሚገባኝ አንድ ሐቅ አለ እላለሁ።"

"ምንድን ነው ጌታዬ?"

"ቀበሮውን" በማጋለጡ ዘመቻ ፕሬዚዳንቱ ራሳቸው በግል እየተሳተፉ ነው።"

"ይህን አላውቅም ነበር ጌታዬ።"

"ይህን"ቀበሮውን የማደን ተግባር ሲ.አይ.ኤ ከምሥረታው ጀምሮ ካከናወናቸው ተልዕኮዎች ሁሉ የመጨረሻው ጠቃሚና ከፍተኛው አድርገው ነው የሚመለከቱት።"

"እኔም እንደዚሁ።"

"እቤትህ ውስጥ ያለህበትን ችግር አውቃለሁ። ፕሬዚዳንቱም ሁኔታህን ያስተዛዝናሉ። እውነተኛ የቤተ ሰብ ሰው ናቸው። ነገር ግን በባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤትና በኢድሚራል ዊታከርም ላይ ዳመና ሊያዳምንበት ይችላል።"

"ኢድሚራሉን ከኔ ውሳኔ ጋር የሚያገናኘው ጉዳይ የለም ጌታዬ።"

"ይህ ለኔ ይገባኛል ኮማንደር። ነገር ግን ፕሬዝዳንቱ ይገባቸዋል?"

'የሜጉላ ሽርሽሩ መራዘሙ ነው!' ሲል ሮበርት አሰበ።

ሮበርት ወደ ቤቱ እንደተመለሰ ዜናው ለሱዛን ሲያበሥራት በለስለስ አንደበት እንዲህ አላት። "ይህ ውጭ አገር የምላክበት የመጨረሻው ተልዕኮ ነው። ከዚህ በኋላ ግን የኔ ነገር እስኪሰለችሽ ድረስ ለብዙ ጊዜ ከቤቴ አልለይም።"

ፈገግ አለችና "በዓለም ላይ አንተን እንድሰለች የሚያደርገኝ ብዙ ጊዜ አይኖርም። እንግዲህ ለዘለዓለም አብረን መሆናችን ነው!" አለችው።

ቀበሮውን" በማሳደድ ተግባር የሮበርት ልምድ ሁሉ አስከፊ ነበር። አርጀንቲና ውስጥ ጭራውን ደርሶበት ነበር። ሆኖም በአንድ ቀን ደብዛው ጠፋበት። አደኑ ወደ ቶኪዮ፤ ቻይናና ማሌዢያ አመራ። "ቀበሮው ማንም ሆነ ማን

@BOOKALEM

የት እንደነበረ የሚያመለክት ዱካ ትቶ ያልፋል። የት እንደሆነ ግን ፍንጭ አይተውም።

ቀናት ወደ ሳምንታት ሳምንታት ወደ ወራት ተለወጡ። ሮበርት ሁሌም "ከቀበሮው" ኋላ ከመሆኑም በላይ ለሱዛን ስልክ ሲደውልላት "በጥቂት ቀናት ውስጥ ወደ ቤቴ እመጣለሁ የኔ ፍቅር" በሚል ነበር የጀመረው። ቀጥሎም በሚቀጥለው ሳምንት ወደ ቤት ሳልመለስ አልቀርም!" ሆነ ጥሪው።

በመጨረሻም....."መቼ እንደምመለስ እርግጠኛ አይደለሁም!" ሲል ማከተሚያውም የስልክ ጥሪ ማድረጉን ማቆም ሆነ። ያለምንም ውጤት ለሁለት ወር ተኩል የቀበሮውን ጭራ ተከታተለ።

ወደ ሱዛን በተመለሰበት ወቅት የተለወጠች ትመስል ነበር። በመጠኑም ቀዝቀዝ ብላለች።

".....ግን ይቅርታ ጠይቃለሁ የኔ ፍቅር። ይህን ያህል ረዥም ጊዜ ይፈጃል። የሚል ሐሳብ አልነበረኝም። ነገሩ....."

"ከአሁን በኋላ አይልኩልህም። ይልኩልሃል ሮበርት?"

"ምን? በእርግጥ አይልኩኝም።"

"አይመስለኝም!" አለች ራሷን እያወዛወዘች። "በዋሺንግተን መታሰቢያ ሆስፒታል ውስጥ የነርስነት ሥራ ይዣለሁ።"

በጣም ደነገጠ። "ምን?"

"እንደገና ወደ ነርስነት ልመለስ ነው። እዚህ አካባቢ ተወዝፌ ካሁን አሁን ወደ ቤት መጣህልኝ እያልኩ መጠበቅ አልችልም። የት እንደሆንክ ምን እንደምታደርግ ሞተህ ይሆን ወይም በሕይወት አለህ? እያልኩ ማውጣት ማውረድ አልችልም።"

ለዚህም ንግግሯ ሮበርት መልስ አልነበረውም።

የተልዕኮውን ውድቀት ለአድሚራል ዊታከር ሪፖርት ሲያቀርብ አድሚራሉ በማስተዛዘን ስሜት ነበር የተቀበለው።

"እንድትሄድ በመስማማቴ ስህተት የፈፀምኩት እኔ ነኝ። ከአሁን በኋላ ግን ሲአይኤ የራሱን ችግር ራሱ መወጣት ይችላል።"

ሱዛን የነርስነት ሥራ መውሰዷን ለአድሚራሉ ነገረው። "ይህ ምናልባት ጥሩ ሐሳብ ሳይሆን አይቀርም" አለ አድሚራሉ በሐሳብ ተመስጦ። "ግፊቱን ሁሉ ከትዳርህ ላይ ያስወግድልሃል። የውጭ አገር ተልዕኮ አልፎ አልፎ ብትወስድ ብዙም ችግር አይፈጥርም ብዬ እገምታለሁ።"

አልፎ አልፎ ወደ ተከታታይ ተለወጠና የጋብቻው መነጣጠል ጅማሪ ሆነ።

@BOOKALEM

ሱዛን በዋሺንግተን መታሰቢያ ሆስፒታል ውስጥ በቀዶ ጥገና ክፍል በነርስነት ስትሠራ ሮበርት ወደ ቤት በተመለሰ ቁጥር ፈቃድ ለመውጣት ትሞክራለች። ቢሆንም ግን በአብዛኛው በሥራዋ ከመጠመድ አልዳነችም።

"በሥራዬ በጣም እየተደሰትኩ ነው የኔ ፍቅር። በጣም ጠቃሚ ተግባር እንደማከናውን ይሰማኛል።"

ስለበሽተኞቿ ታወጋዋለች። ምን ያህል ተንከባካቢ እንደሆነች ወደ ጤንነትና ወደ ሕይወት እንደመለሰችው እሱም ያስታውሳል። የሚያስደስታትን ሥራ በመሥራቷ በጣም ቢደሰትም ሐቁ ግን የሚተያዩበት ጊዜ እያነሰ እያነሰ መምጣቱ ነው።

በመካከላቸው ያለው የስሜት መራራቅ እየሰፋ ከመምጣቱም በላይ ከዚህ በፊት ያልነበረ ችግርም ተፈጠረ። ሌላው ቀርቶ ውይይት ማድረግ እንኳ አስቸጋሪ ሆኖባቸው ተገኘ።

ሮበርት ስድስት ሳምንት ከፈጀበት የቱርክ ተልዕኮ እንደተመለሰ ሱዛንን ወደ ሳንሱዚ ለእራት ወሰዳት።

"ሆስፒታላችን ውስጥ አንድ በሽተኛ አለን" አለች ሱዛን። "በጣም መጥፎ የሆነ የአውሮፕላን አደጋ ስለደረሰበት ዶክተሮቹ ይተርፋል ብለው አይገምቱም። እኔ ግን ሕይወቱን የማትረፉን ጉዳይ አጥብቄ እከታተላለሁ!" ይህን በምትናገርበት ጊዜ የዐይኖቿ ፀዳል እየተንቦገቦገ ነበር።

ለእርሱም እንዲህ እንደነበረች አስታወሰ። "ወደ በሽተኛው ራስ ዘንበል ብላ.....ንቃ! ደህና ሁን እየጠበኩህ ነው" ትለው ይሆን? ይህን ሐሳብ ከጭንቅላቱ አወጣው።

"በጣም ግሩም ሰው ነው ሮበርት። ነርሶቹ በሙሉ ያብዱበታል።"

'ነርሶቹ በሙሉ?' ተገረመ።

በቀጣዩ ቅዳሜ ሮበርት ወደ ፖርቹጋል ተጓዘ። ከስድስት ሳምንት በኋላም ሲመለስ ሱዛን በጣም ቢጋለ መንፈስ ነበር የተቀበለችው።

"ለመጀመሪያ ጊዜ ሞንቴ ዛሬ ቆሞ መራመድ ቻለ!" አለችው። አሳሳሚ ግድ የለሽና ስሜት የለሽ ዐይነት ነበር።

"ሞንቴ?"

"ስሙ ሞንቴ ባንክሰን ይሰኛል። እየተሻለው ነው። ዶክተሮቹ ለማመን ቢያቅታቸውም ተስፋ ግን አንቆርጥም።"

"እስቲ ስለ ሰውየው አጫውችኝ።"

"በእውነት የሚወደድ ሰው ነው። ሁል ጊዜ ስጦታዎችን ያበረክትልናል። በጣም ባለፀጋ ሰው ሲሆን የራሱን አውሮፕላን ሲያበር መጥፎ የመከስከስ አደጋ ነበር ደረሰበት። እኔም....."....

"ምን ዐይነት ስጦታዎችን?"

@BOOKALEM

አህ! ታውቃለህ ትንሽ ነገሮችን። ከረሜላዎችን፤ አበባዎችን፤ መጽሐፍት፤ የሙዚቃ ቅጅዎችን፤ የመሳሰሉና በጣም ውድ የሆኑ የእጅ ሰዓቶችን ሊያበረክትልን ቢሞክርም እኛ ግን አንቀበልም ማለት ይገባን ነበር።"

"ይገባችኋል።"

"ትልቅ የሞተር ጀልባ አለው።"

ሮበርት ሰውዬውን "የገንዘብ ከረጢት" እያለ መጥራት የጀመረው ከዚህ ዕለት ጀምሮ ነበር።

ሱዛን ከሆስፒታል በተመለሰች ቁጥር ስለሰውዬው ታጫውተዋለች።

"በእውነት ውድ ሰው ነው ሮበርት!"

'ውድ አደገኛ ቃል ነው' አለ በሐሳቡ።

በጣም አሳቢ ነው። ዛሬ ምን እንዳደረገ ታውቃለህ ሮበርት?' ፎቅ ላይ ላሉት ነርሶች በሙሉ ከጆኪ ክለብ ምሳ አስመጣላቸው።"

'ሰውዬው የሚያሳምም ነው' ሲል አሰበ።

ሮበርት መናደዱ ተሰማው። "ይህ ግሩም በሽተኛሽ አግብቷል?"

"አላገባም። ግን ለምን ሮበርት?"

"እንዲያው እየደነቀኝ ነው።"

ሳቀች። "ስለመንግሥተ ሰማያት ብለህ! መቼም አልቀናህም። ቀንተሃል?"

'መራመድ በመለማመድ ላይ ስላለ ሽማግሌ?' በእርግጥ አልቀናም። ቢሆንም ግን "አልቀናሁም" በማለት ሱዛንን ሊያረካት አልፈለገም።

ሮበርት ቤት በሚኖርበት ጊዜ ሱዛን ስለበሽተኛዋ ማውራት አቆመች። እሷ ባታነሳም ርዕሱን ሮበርት ያነሳው ነበር።

"ሽማግሌው አቶ የገንዘብ ከረጢት እንዴት እየሆነ ነው?"

"ስሙ የገንዘብ ከረጢት ሳይሆን ሞንቴ ባንከስ ነው።"

'የፈለገው ቢሆን ይህ የውሻ ልጅ በአደጋው አለመሞቱ በጣም መጥፎ ነው!' ሲል አሰበ።

ተኪታዩ ቀን የሱዛን የልደት ቀን ነበር።

"የምነግርሽ ምን መሰለሽ?" አለ ሮበርት በደስታ ተውጦ። "ልደትሽን ለማክበር ወጣ ብለን ምርጥ በሆነ እራት እንደሰታለን። እናም....."

"ሆስፒታሉ ውስጥ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት መሥራት አለብኝ።"

"ጥሩ! ከዚያው መጥቼ እወስድሻለሁ።"

"መልካም። ሞንቴም ካንተ ጋር ለመገናኘት ይጓጓል። ስላንተ ሁሉንም አጫውቼዋለሁ።"

"እሺ። ሽማግሌውን ሰው ለመገናኘት እሞክራለሁ" ሲል አረጋገጠላት።

ሮበርት ሆስፒታሉ እንደደረሰ እንግዳ ተቀባይዋ "እንደምን አመሸህ ኮማንደር?" ስትል ተቀበለችው። "ሱዛን በሦስተኛው ፎቅ ላይ በሚገኘው የአካል

@BOOKALEM

መጠገኛ ከፍል ውስጥ ስትሆን በአሁኑ ወቅት እየጠበቀችህ ነው” አለችውና ስልኩን ብድግ አደረገች።

ሮበርት ከአሳንሰሩ ሲወጣ ሱዛን ነጭ የነርሶች የደምብ ልብሷን እንደለበሰች ተቀበለችው። ልቡ ዘለለ። ‘አ! እጅግ በጣም ውብ ናት!’

“ሄሎ ውዴ!”

ሱዛን ሳቅ አለች። እንግዳ የሆነ ጭንቀትና መረበሽ ይታይባታል። “ሄሎ ሮበርት። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከሥራ ነፃ እሆናለሁ ተከተለኝ። ሞንቴን ላስተዋውቅህ።”

ወደ አንድ በጣም ትልቅ የሆነ በመጽሐፍት፤ በአበቦችና ቅርጫት ውስጥ በተቀመጡ ፍራፍሬዎች በተሞላ የግል ከፍል መራችው። “ሞንቴ ይህ ባለቤቴ ሮበርት ነው።”

ሮበርት ሦስት ወይም አራት ዓመታት ብቻ የሚበልጠውን አልጋ ላይ የተኛውን ሰው ቆሞ አፍጥጦ ይመለከተው ጀመር። እናም ገና እንዳየው ሰውዬውን አምርሮ ጠላው።

“በእርግጥ ላይህ በመቻሌ ተደስቻለሁ! ኮማንደር። ስላንተ ሱዛን ሁሉንም ነግራኛለች።”

‘አልጋው አጠገብ ሆና በእኩለ ሌሊት የሚያወሩት ስለኔ ነው’ አለ በሐሳቡ።

“በጣም ትኮራብሃለች ሮበርት።”

ሱዛን ሮበርት ትህትና እንዲያሳይ በመሻት ታየው ነበር። እሱም ጥረት አደረገ።

“ከዚህ ቦታ በቶሎ ድነህ እንደምትወጣ ይገባኛል።”

“አዎን ለባለቤትህ ምስጋና ይግባትና ፍፁም ተዓምር የምትሠራ ናት።”.....

“አዎን የእርሷ ልዩ ችሎታ ይህ ነው።” ሮበርት ምሬቱን ከድምፁ መሸሸግ አልቻለም።

የልደት እራታቸው ውድቅ ነበር የሆነው። ሱዛን የምታወራው ሁሉ ስለበሽተኛዋ ብቻ ሆነ።

“ሞንቴን ስታየው የሚያስታውስህ ሰው አለ?”

“ቦሪክ ካርሎፍን።”

“ለምንድነው እንደዚህ ባለጌ የሆንክበት?”

“ትሁት የሆንኩለት ነበር የመሰለኝ። ለማንኛውም ግን ሰውዬውን ልወደው አልቻልኩም” አላት ቀዝቀዝ ብሎ።

“ሌላው ቀርቶ አታውቀውም። ስለሰውዬው ያልወደድከው ነገር ምንድነው?” አለችው አተኩራ እያየችው።

@BOOKALEM

‘አንቺን የሚያይበትን ዐስተያየት አልወደድኩትም፤ አንችንም የምታይውን ዐስተያየት አልወደድኩልሽም፤ ትዳራችን ወደ ገሐነም የሚጓዝበትን ጎዳና አልወደዱኩም፤ አምላኬ! ላጣሽ አልፈልግም!” አለና በሕሊናው ድምፁን ከፍ አድርጎ “አዝናለሁ ደክሞኛል ብዬ እገምታለሁ” አለ።

እራታችውን በዝምታ ተሸብበው ጨረሱ።

በማግስቱ ጠዋት ሮበርት ወደ ቢሮው ለመሄድ ዝግጅቱን እንደጨረሰ “ሮበርት...አንድ የምነግርህ ነገር አለ” አለችው ሱዛን።

እናም ልክ እምብርቱ ላይ ከፍተኛ ዱላ እንደወረደበት ነበር የተሰማው። እየተፈጠረ ያለውን ጉዳት በቃላቶቿ ስታቀናብራቸው ለመስማት መጃጃም አይችልም።

“ሱዛን.....”.....

“እንደማፈቅርህ ታውቃል። ምንጊዜም አፈቅርሃለሁ። አስከዛሬ የማውቀው ምርጥና ውድ ሰው ቢኖር አንተ ብቻ ነህ።”

“እባክሽ.....”

“የለም ልጨርስ። ይህ ለኔ በጠም አስቸጋሪ ነው። ባለፈው ዓመት እኔና አንተ በጣም ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነው አብረን ያሳለፍነው። ከአሁን በኋላ የጋብቻ ሕይወት የለንም! ተራርቀናል።“

እያንዳንዷ የምትናገራቸው ቃላቶች ልክ እንደስለታም ቢለዋ እየሰነጠቁት ነበር።

“ትክክል ነሽ” አላት ተስፋ በቆረጠ ድምጽ። “ይህንን ሁኔታ አለውጣለሁ። የመረጃ መሥሪያ ቤቱን ሥራ አተዋለሁ። አሁኑኑ! ዛሬወኑ! የሆነ ቦታ እንጓዝና.....”

ሱዛን ራሷን ነቀነቀችና.....“የለም ሮበርት። ይህ እንደማይሠራ ሁላታችንም እናውቃለን። መሥራት የምትፈልገውን ሥራ በመሥራት ላይ ነህ። በእኔ ምክንያት ሥራህን ብታቆም ምንጊዜም እንደጠላህኝ ትኖራለህ። ይህ የማንኛችንም ስህተት አይደለም። አንዴ ሆኗል። አሁን እኔ የምፈልገው ፍቺ ነው!”

ዓለም ተደርምሳ የዋጠችው ነበር የመሰለው። ሆዱ በሕመም ሲተራመስ ተሰማው።

“ከልብሽ አይደለም ሱዛን። ይህን ችግር ለመፍታት አንድ መንገድ ፈልጌ.....”

“በጣም ዘግይቷል ሮበርት። በዚህ ጉዳይ ላይ ለረዥም ጊዜ አስቤበታለሁ። አንተ ውጭ በነበርክበት ጊዜ እቤት ተቀምጬ ያንተን መመለስ እየተጠባበኩ አስቤበታለሁ። የተነጣጠለ ሕይወት ነበር የኖርነው። ልትሰጠኝ የማትችለውን ነገር ነው የምሻው።”

@BOOKALEM

ስሜቱን ለመቆጣጠር እየታገለ ቆሞ ቀረ። "ይህ.....ይህ.....ከገንዘብ ከረጢት ጋር ግንኙነት ያለው ጉዳይ ነው?"

ሱዛን አመነታች። "ሞንቴ እንዳገባው ጠይቆኛል!"

ሆድ ዕቃው በውሃ ሲሞላ ተሰማው። "እናስ ልትሄጂለት ነው?"

"አዎን!"

ሁኔታው ልክ እንደተቃወሰ ቅዠት ነበር። 'ይህ ነገር በመሆን ላይ አይደለም ሊሆን አይችልም' ሲል አሰበ። ዐይኖቹ እንባ አቀረሩ።

ሱዛን እጆቿን ትከሻው ላይ ጣለችና ጠጋ አድርጋ አቀፈችው። "ስላንተ የሚሰማኝን ዐይነት ስሜት ከቶም ቢሆን ሌላ ሰው ላይ ሊያድርብኝ አይችልም። በሙሉ ልቦናዬና ነፍሴ አፈቅርሃለሁ። ፍጹም ውድ ጓደኛዬ ነህ።" ወደ ኋላው ገፋ አደረጉችውና ዐይኖቹን ትኩር ብላ ተመለከተቸው። "ግን ይህ ብቻ በቂ አይደለም። ተረዳህ?

ሊገባው የቻለው ነገር ቢኖር ለሁለት እየሰነጠቀችው እንደሆነ ብቻ ነው። እንደገና ልንሞክረው እንችላለን። እንደገና እንጀምርና....."

"አዝናለሁ ሮበርት" አለች በታፈነ ድምጽ። "በጣም አዝናለሁ። አክትሟል!" አለችው።

ሱዛን ለፍቺ ወደ ሪኖ ስትበር ሮበርት ደግሞ ለሁለት ሳምንታት ያለማቋረጥ ሰከረ።

ሮበርት ኤፍ.ቢ.አይ (የፌደራል ወንጀል ምርመራ) ለሚሠራ ጓደኛው ሰልክ አደረገ። አል ትሬይኖር በሮበርት ጎዳና ከግማሽ ደርዘን በላይ ያቋረጠ ሰው ስለሆነ ሮበርት በሚገባ ያምነዋል።

"ትሬይ አንድ ውለታ እንድትውልልኝ እፈልጋለሁ ።"

"አንድ ውለታ? ሳይካትሪስት ያስፈልግሃል። እንዴት ቢደረግ ነው ሱዛንን ያባረርካት?"

"ዜናው ምናልባት ከተማውን ሰይሞላው አልቀረም። በጣም ረዥም ታሪክ ነው።"

"በእውነት አዝናለሁ ሮበርት። ሱዛን በጣም ታላቅ ወይዘሮ ነበረች። ምን ልርዳህ?"

"አንድ ሰው ላይ የኮምፒዩተር ማጣራት እንድታደርግልኝ እፈልጋለሁ ።"

"ይደረገልሃል። የሰውዬውን ስም ሰጠኝ።"

"ሞንቴ ባንክስ" ይባላል። የተለመደውን የማጣራት ተግባር ዐይነት።

"ትክክል። ምንድንነው ማወቅ የምትሻው?

"ምናልባት ባንተ ኮምፒተር ፋይል ውስጥ ላይኖር ይችላል። ከሆነ ግን መኪናውን በተከለከለ ሥፍራ በማቆሙ ተከሷል? ቀይ መብራት ጥሷል? የመሳለሉትን የተለመዱ ዐይነት ማጣራቶች።

@BOOKALEM

"በእርግጥ ይቻላል።"

"እናም ገንዘቡን ከምን እንደሚያገኝ ለማወቅ እፈልጋለሁ ። ስለሕይወት ታሪኩም ዝርዝር ዘገባ እሻለሁ።"

"አሃ! የተለመደውን ማጣራት እ....."

"እናም ትሬይ!" ይህ የግል ጉዳይ ስለሆነ ነገሩ በኔና ባንተ መካል ብቻ ይቅር።

"ምንም ችግር የለም። ነገ ጠዋት ውጤቱን በስልክ አሳውቅሃለሁ።"

"አመሰግናለሁ። ብድሩን ምሳ እጋብዝሃለሁ።"

"የለም እራት ይሻላል።"

"ትጋበዛለህ።"

ሮበርት በሐሳብ ተውጦ ስልኩን አስቀመጠ። ገለባ በእጆቹ የጨበጠ ሰው ምስል ታየው። ይህ ሰው ወንጀለኛ ሆኖ እንደሚገኝና ሱዛንም እጆቿን ዘርግታ እየበረረች ስትመጣ ታየው።

በማግስቱ ጠዋት ደስቲን ቶርንቶ ሮበርተን ቢሮው ድረስ አስጠራው።

"ምንድነው በመሥራት ላይ ያለህው ኮማንደር?"

'ምን እንደምሠራ በትክክል ያውቃል' ሲል አሰበና....."የሲንጋፖሩን ዲፕሎማት ዶሴ በመመርመር ላይ ነኝ እናም....."

"ይህ ብዙውን የሥራ ጊዜህን እንዳልያዘብህ አውቃለሁ!"

"ይቅርታ አልገባኝም።"

"ምናልባት ስተኸው እንደሆነ ኮማንደር? የባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤት አሜሪካዊያንን የመሰለል ሥልጣን አልተሰጠውም።"

ሮበርት ግራ ገብቶት ሰውዬውን እያየው ነበር። 'ምንድነው... ያ ትሬይኖር የሚሉት የውሻ ልጅ ከድቶኛል ማለት ነው? የጓደኝነት ውጤት!'

"ነገሩ እንኳ የግል ጉዳይ ነበር። እኔ....." ብሎ ሲጀምር ደስቲን አቋረጠው።

የኤፍ.ቢ.አይ. ኮምፒተር እዚያ የተቀመጠው ላንተ አመቺ በሆነ ሁኔታ ግለሰብ ዜጎችን እንድታጠቃበት እንድታስጨንቅበት ወይም እንድታበሳጨበት አይደለም። ራሴን ግልጽ እያደረኩልህ ነው?

"በጣም!"

"ይኸው ነው!"

ሮበርት እየከነፈ ወደ ቢሮው ሄደና ቁጥር 202-324-30300 ስልኩን አንስቶ ሲደውል ጣቶቹ እየትቀጠቀጡ ነበር።

ወዲያው "ኤፍ.ቢ.አይ" የሚል መልስ መጣለት።

"አል ትሬይኖር?"

"ጥቂት ይጠብቁ እባክዎ።"

@BOOKALEM

ከአንድ ደቂቃ በኋላ በመሰመሩ ላይ ድምጽ መጣ።

"ሄሎ ምን ልርዳዎት?"

"አል ትሬይኖርን እፈልጋለሁ ።"

"እዝናለሁ አል ትሬይኖር ካሁን በኋላ እቢሮው አይገኝም።"

ሮበርት ሰውነቱን ሲነዝረው ተሰማው። "ምን?"

"ወኪል (ኤጀንት) ትሬይኖር ተዛውሯል።"

"ተዛውሯል?"

"አዎን።"

"ወዴት?"

"ወደ አውሎ ነፋስ! ለማንኛውም ረዘም ላለ ጊዜ እዚህ አይገኝም ብዬ እሰጋለሁ።"

"ምን ማለት ነው?"

"ትናንት ምሽት ላይ ሮክ ሬክ መናፈሻ ሥፍራ ውስጥ ሲዘዋወር በመኪና የመገጨት አደጋ ደርሶበታል። ማመን ትችላለህ? አዕምሮውን እስኪስት ድረስ የጠጣ አሽከርካሪ ሳይሆን አይቀርም እግረኛ መረማመጃው ጠርዝ ላይ ወጥቶ ገጨው። ትሬይኖር በደረሰበት ግጨት ከአርባ ጫማ በላይ ነው የተወረወረው። በፍፁም አይተርፍም።"

ሮበርት አዕምሮው እየዞረበት ሰልኩን አስቀመጠው። 'ምንድነው እየተካሄደ ያለው? ባለሰማያዊ ዐይኖቹ ሁለመናው አሜሪዊ የሆነው ልጅ ሞኑቴ ባንክስ የመከላከል ጥቃ እየተደረገለት ነው። ማን ከምን? በማን? የእየሱስ ያለህ! ሱዛን ራሷን እምን ውስጥ ነው የጨመረችው?' ሲል አሰበ።

ከቀትር በኋላ ሊጎበኛት ሄደ።

በ ኤም ጎዳና ላይ በሚገኘው አዲሱ ውብ አፓርትመንቷ ውስጥ ነበረች። 'አቶ የገንዘብ ከረጢት ከፍሎበት ይሆን?' ሲል ተገረመ። ሱዛንን ካያት ሳምንታት አልፈውት ነበርና አሁን ሲያያት ትንፋሽ አጠረው።

"በዚህ ሁኔታ ስለመጣሁብሽ አዝናለሁ ሱዛን። እንዲህ ላለማድረግ ቃል ገብቼ ነበር።"

"በጣም ከፍተኛ ጉዳይ ነው ብለኸኝ ነበር።"

"ነው!" አላት። አሁን አጠገቧ ነው። እንዴት እንደሚጀምርላት ማወቅ አልቻለም። "ሱዛን ላድንሽ ነው የመጣሁት" ይበላት? ዓለም ፊቱ ላይ ትስቅበታለች።

"ምን ተፈጠረ?" ስትል ጠየቀችው።

"ስለሞኑቴ ነው" አላት።

"ስለእርሱ ምን ተፈጠረ?"

@BOOKALEM

አስቸጋሪው ክፍል ይህ ነበር። ራሱ በትክክል ያልተረዳውን ነገር ምን ብሎ ያስረዳት? የሚያውቀው ነገር ቢኖር አንድ በከፍተኛ ሁኔታ የተበላሸ መጥፎ ነገር እንዳለ ነው። ስለሞንቴ ባንክስ በኤፍ.ቢ.አይ. ኮምፒተር የሰነዘረው ጥያቄ ለባሕር ኃይሉ መረጃ ጽሕፈት ቤት ተላለፏል። 'ለምን?'"

"መስሎ ለመታየት የሚሞክረውን ዐይነት ሰው አይመስለኝም" አላት በመጨረሻ።

"አልገባኝም።"

"ሱዛን....." ገንዘቡን ከየት ነው የሚያገኘው?

በጥያቄው ድንገት መገረም ያደረባት መስላ ታየች። "ሞንቴ በጣም የተዋጣለት የአስመጪና ላኪ ንግድ አለው።"

'በዓለም ላይ የሰነበተ ወይም ያረጀ የሸፋን ዘዴ' ሲል አሰበ። ከግማሽ መላምት ይልቅ የበለጠ አውቆ በመጣ ይሻል ነበር። ልክ እንደሞኝ መሆኑ ተሰማው። ሱዛን መልስ እየጠበቀች ሲሆን እሱ ደግሞ ምንም አልነበረውም።

"ለምንድነው የጠየከኝ?"

"እ.....እኔ.....እሱ ላንቺ ትክክለኛው ሰው መሆኑን ለማረጋገጥ ስለፈለኩ ነው።"

"አሃ!" ሮበርት አለች ሱዛን። ድምጿ የብስጭት ቃና ይሰማበታል።

"መምጣት አይገባኝም ነበር አዝናለሁ።"

ሱዛን ወደ ሮበርት ተራምዳ አቀፈችውና ለስለስ ባለ ቅላጼ "ይገባኛል ሮበርት" አለችው።

ግን ምንም ነገር አልገባትም። ስለሞንቴ ባንክስ የተደረገ ቅን የማጣራት ጥያቄ በድንገተኛ ግድግዳ መዘጋቱ፤ ወደ ባሕር ኃይሉ መረጃ ጽሕፈት ቤት መዛመቱንና መረጃውንም ለማግኘት የሞከረውን ሰው ወደ ሞት እንዳሸጋገረ ፍጹም አልገባትም ነበር።

ሌሎች መረጃ የማግኛ መንገዶች ነበሩ። እናም ሮበርት በከፍተኛ ጥንቃቄ ይሞክራቸው ጀመር። "ፎርቤስ ሜጋዚን" ለሚባል መጽሔት ለሚሠራ አንድ ጓደኛው ስልክ ደወለ።

"ሮበርት!" ለረዥም ጊዜ አላየሁህም። ምን ላድርግልህ?

ሮበርት ጉዳዩን አስረዳው።

"ሞንቴ ባንክስ?" በፎርቤስ ዝርዝራችን ላይ ከአራት መቶዎቹ ከፍተኛ ከበርቴዎች እንደአንዱ መመዝገቡን እንገነዘባለን። ግን ስለሱ ሰውዬ ሌላ ምንም ዐይነት ጠጣር መረጃ ለማግኘት አልቻልኩም። ስለሰውዬው ለኛ የሚሆን ነገር አለህ?

"ባዶ።"

@BOOKALEM

ቀጥሎም ሮበርት ወደ ሕዝብ መጽሐፍት ቤት ሄደና "ሁ ኢዝ ሁ" (ማን ማን ነው?) የተባለውን መጽሐፍ አገላበጠ። ሞንቴ ባንክስ የለበትም። ወይም አልተመዘገበበትም።

የብዙ ዓመታት የጋዜጣና የመጽሔት እትሞችን በፊልም መልክ በጣም ትንሽ በሆነ የመቅጃ መሣሪያ ላይ አከማችቶ በቴሌቪዥን ስክሪን ላይ ለማስነበብ የሚችለውን "ማይክሮ ፊሽ" የተባለውን መሣሪያ በመጠቀም ዋሽግተን ፖስት ሞንቴ ባንክስ የአውሮፕላን አደጋ በደረሰበት ሰሞን የዘገበውን ዘገባ ሲመለከት ሞንቴ ባንክስን "የንግዱ ዓለም አንቀሳቃሽ" ሲል የጠቀሰውን በጣም አጭር ዜና ብቻ አገኘ።

'ሁሉም ነገር ፍጹም ጤናማና ንጹሕ ይመስላል። ምናልባት ተሳስቼ ይሆናል። ሞንቴ ባንክስ ነጭ ባርኔጣ ያጠለቀ (ንጹሕ) ሰው መሆን አለበት። ሞንቴ ባንክስ ስላይ፤ ወንጀለኛ ወይም የአደንዛዥ እጽ ነጋዴ ቢሆን ኖር መንግሥታችን ይህን ሁሉ የመከላከል ተግባር ባላደረገለት ነበር። ሐቁ ሱዛንን እንደገና ለማግኘት መፈለጌ ነው' ሲል ከሕሊናው ጋር ተሟገተ።

ወደ ወንደ ላጤነት በመመለሱ ብቸኛና ፍጹም ባዶ ከመሆኑም በላይ በሥራ የተወጠረ ቀንና እንቅልፍ የለሽ ምሽት ብቻ ነበር የገጠመው። ያላንዳች ማስጠንቀቂያ የብስጭት ማዕበል ይውጠውና እንባውን ያነባል። ለራሱና ለሱዛን ሁለቱም ስላጧቸው ነገሮች ያነባል።

ሱዛን በሁሉም ሥፍራ ነበረች። ኢፓርትመንቱ እሷን በሚያስታውሱ ነገሮች ተሞልቷል። ሮበርት እርሷን በማስታወስ ተሰቃየ። እያንዳንዱ የኢፓርትመንቱ ክፍል የሱዛንን የደስታ ሳቅ፤ የሱዛንን ድምጽ፤ የሱዛንን ሙቀት እያስታወሰው ሕሊናውን አሰቃየው። እርሱን እየጠበቀች እርቃኗን አልጋው ላይ ጋለል ስትል፤ የገላዋን ለስላሳ ሽለቆዎችና ጫጥኞች ሲያስታውስ የትዝታዋን ሕመም ሊቋቋመው አልቻለም። ባልንጀሮቹም የሁኔታውን መለወጥ እያዩ ያስቡለታል።

"ብቻህን መሆን አይገባህም ሮበርት" ይሉታል እየተሸቀዳደሙ።

"ሮበርት አንዲት ምርጥ ልጅ አገኘሁልህ" ይሉትም ጀመር። የሚያስመጡለትም ሴቶች ረዣዥምና ቆንጆጅት፤ አጫጭርና ወሲባሞች ሲሆኑ የፋሽን ሞዴሊስቶች፤ ሴክሬታሪዎች፤ የማስታወቂያ ድርጅት ባለሥልጣናት፤ ጋለሞታዎችና ጠበቆችም ይገኙባቸው ነበር። ግን አንዳችውም ሱዛንን አልነበሩም። አዲስ ከሚተዋወቃቸው ሴቶች ጋር ምንም ዐይነት የጋራ ስሜት ሊኖረው ካለመቻሉም በላይ ካንዳንዶቹ ጋር አጠር ያለ ጭውውት ወይም ወሬ ለማውራት በሞከረ ቁጥር የበለጠ ብቸኝነት ይሰማው ጀመር። እናም ከአንዳቸውም ጋር አልጋ ላይ የመውጣት ፍላጎት ሊኖረው ስላልቻለ ብቸኝነትን መረጠ። ያለፈውን ፊልም እንደገና ወደ ኋላ አጠንጥኖ ለማየት ሲሞክር ስህተቱን ለመረዳት ቀላል ሆኖ

@BOOKALEM

አገኘው። ከአድሚራል ዊታከር ጋር የተደረገው የድብብቆሽ ጨዋታ እንደምን እንደተካሄደ ተመለከተ።

'ሲ.አይ.ኤን አንድ "ቀበሮው" የተባለ ሰላይ ሰርጎ ገብቶበታል። ምክትል ዳይሬክተሩም አድነህ እንድትይዘው ጠይቀዋል።'

"የለም አድሚራል ባለቤቴን ለጫጉላ ሽርሽር ይዣት ለመሄድ እፈልጋለሁ ።"

ሕይወቱን እንደገና ለማተምና የደስታ የፍሰሐ ፍፃሜ ሊሰጠው ፈለገ። ነገር ግን እጅግ በጣም ዘግይቶ ነበር። ሕይወት ደግሞ ሁለተኛ ዕድል አትሰጥምና ብቻውን ቀረ። ሸቀጡን ራሱ ይሸምታል ምግቡን ራሱ ያበስላል። በሳምንት አንድ ቀን ጎረቤቱ ወደሚገኘው የልብስ ንጽሕና መስጫ ጎራ ይላል።

በሮበርት ሕይወት ውስጥ ይህ አስከፊ የብቸኝነትና የብሶት ወቅት ቢሆንም የመጨረሻው አሰከፊ ገጽታ ገና እየመጣ ነበር። አንዲት ዋሽንግተን ውስጥ ያገኛት ውብ የፋሽን ንድፍ አውጪ እራት ካልጋበዝኩህ ብላ ደጋግማ ስልክ ደወለችለት። ሮበርት በመጀመሪያ ቸልተኛ ቢሆንም በመጨረሻ ግብዣዋን ተቀበለ።

በጣም ግሩም መዐዛ ያለው በሻማ ብርሃን የታጀበ እራት አዘጋጅታ ነበር።

"በጣም ግሩም ባለሙያ ነሽ" አላት።

"በሁሉም ነገር በጣም ጥሩ ነኝ!" አለችው።

አባባሏም ስህት አልነበረም። "ላረጋግጥልህ!" አለችና ተጠጋችው። እጆቿን ጭኖቹ ላይ ጣል አደረገችና ዙሪያ ከንፈሩን በምላሷ ዳሰሰችው። ወደ መኝታ በሄዱበት ወቅት ሮበርት ውድቀት ነበር የጠመው። በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በሽብርና በውርደት ብልቱ የማይሠራ ሙት አካል እንደሆነበት ተረዳ።

"ፍቅሬ አትጨነቅ ይሻሻላል" አለችው።

ተሳሰታ ነበር።

ሮበርት ተሸማቆና አካለ ስንኩል የመሆን ስሜት እየተሰማው ወደ ቤቱ ተመለሰ። ከሌሎች ሴቶች ጋር ፍቅር መሥራት ሱዛንን መክዳት መሆኑ ተሰማው። አንዲት የባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤት ጸሓፊ አስተኝታ ሰውነቱን እየዳሰሰችና በአፏ እየደባበሰች ሞከረች። ዋጋ አልነበረውም። ሱዛን ብቻ አስፈለገችው። ከዚህ በኋላ ፍቅር የመሥራት ሙከራውን አቆመ። የሕክምና ባለሙያ ለማነጋገር ሲያስብ ከፍተኛ ውርደት መሆኑ ተሰማው። የችግሩ መፍትሄ ምን እንደሆነ በሚገባ ቢያውቅውም መፍትሄውን የሚያገኝበት ዘዴ አልነበረውምና ያለውን የኃይል እንጥፍጣፊ ሁሉ መደበኛ ሥራው ላይ አዋለ።

ሱዛን ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን ስልክ ትደውልለታለች።

@BOOKALEM

"ሽሚዞችህን ከላውንደሪ ቤት ማውጣት አትርሳ! ይሆን ጊዜ ቤትህ አህያ የወለደችበት መስሏል" ትለዋለች። እያንዳንዱ ጥሪዋ ብቸኝነቱን የሚያቃልልመው አደረገበት። በስርጓ ዋዜማ ጥሪ አድርጋለት ነበር።

"ሮበርት በነገው ዕለት የማገባ መሆኑን ላሳውቅህ አፈልጋለሁ ።"

ትንፋሽ እያጠረው "ሱዛን....."ሲል ጀመረ።

"ምኑቴን አፈቅረዋለሁ። አንተንም በጣም አፈቅርሃለሁ። እስከ ዕለተ ሞቴ ድረስ አፈቅርዋለሁ። ይሆንን ፍጹም እንድትረሳው አልፈልግም።"

'ለዚህ ምን የሚሰጥ መልስ አለ?' ሲል አሰበ።

"ሮበርት ደህና ነህ?" አለችው ድምጹ ሲጠፋባት። "ሮበርት? ሮበርት አለህ?"

በራሱ አካላዊ ችግር ሊቀጣት አልፈለገም። "እባክሽ አንድ ውሊታ ብቻ እንድትውይልኝ ልጠይቅሽ?"

"ምንም ነገር! የምችለውን ሁሉ!"

"እባክሽን ለሜጉላ ሽርሽራችሁ እኔ ወደ መሰድኩሽ ሥፍራዎች እንዲወስድሽ አታድርጊ!" አለና ስልኩን ዘጋው።

ስልኩንም ዘጋና ጥንብር ብሎ ለመስከር ወደ ውጭ ወጣ። ይህ ከሆነ አንድ ዓመት ያለፈው ታሪክ ነበር። አሁን ሱዛን የሌላ ሰው ንብረት የመሆኗን ዕውነታ ለመቀበል ተገደደ። ባለፈው ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ ውስጥ መኖር አለበት። መሥራት የሚገባውም ሥራ አለ። አሁን ወቅቱ የምስክሮቹን ስምና አድራሻ እንዲሁም ፎቶግራፍ የያዘውን ሌስሊ ማዘር ሼድን የመጨረሻው በሆነው ተልዕኮው የሚንጋገሪያው ጊዜ ነው።

@BOOKALEM

ምዕራፍ አሥራ ስምንት

ሌስሊ ማዘርሼድ ከደስታና ፈንጠዝያ በላይ በሆነ ደረጃ ላይ ነበር። ወደ ለንደን እንደተመለሰ ወዲያውኑ ወደ ፊልም ማጠቢያነት ወደለወጠው የጭለማ ክፍል ብርቅዬ የሆነውን ፊልሙን ይዞ ገብቶ ሁሉም አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ መኖሩን አረጋገጠ። የሙቀት መጠን መለኪያ፤ እርጥብ ፊልም ማንጠልጠያ የሚሆን መቆንጠጫ፤ የፊልም ማሳደጊያ፤ ማጥቆሪያ፤ ማሳደጊያ ኬሚካልና ማተሚያው ሁሉ መኖራቸውን አረጋገጠ። ከዚያም የክፍሉን መብራት አጠፋና አንዲት አነስተኛ ቀይ የጠረጴዛ መብራት አበራ። የካሜራውን ክዳን ከፍቶ ፊልሙን ሲያወጣ እጁ ይንቀጠቀጥበት ነበር። ራሱን ለመቆጣጠር በጥልቀት ተነፈሰ። ቡክኣለም በቴሌግራም ያቀረበው መጽሐፍ-@BOOKALEM

በጥንቃቄ ጥቅሉን ፊልም ዘረጋና ዝርጉን ፊልም ማጠቢያ ገንዳ ውስጥ ከትቶ ገንዳውን በፊልም ኬሚካል ሞላው። ይህ ኬሚካል ያለማረቋጥ በየ68 ዲግሪ ፋራናይት በተወሰነ ጊዜ አንዴ መነቅነቅን ይፈልጋል። ከአሥራ አንድ ደቂቃ በኋላ ሁለተኛውን ኬሜካል ወይም ፊክሰር ዝርጉ ፊልም ላይ ጨመረበት።

ሁለተኛው ላይ ስህተት እንዳይሠራ ሲል ጭንቀትና ሽብር አደረበት። ለሁለተኛው ደረጃ እጥበት ፊክሰሩን አንጠፍጥፎ አፈሰሰና ለአሥር ደቂቃዎች ያህል ፊልሙን በንፁህ ውሃ ዘፈዘፈው። ከዚህ ቀጥሎ በማንጪያ ኬሜካል ለሁለት ደቂቃ መታውና ለአሥራ ሁለት ተጨማሪ ደቂቃዎች በንፁህ ውሃ ነከረው። በሚቀጥለው ፎቶሶሉሽን ኔጋቲቩ ምንም ዐይነት ጭረት ወይም ሰህተት እንደሌለው አረጋገጠ። በመጨረሻም በከፍተኛ ጥንቃቄ ፊልሙን አወጣና ማድረቂያው ላይ በመቆንጠጫ አንጠልጥሎ እስኪደርቅለት ድረስ ትዕግስት አጥቶ ይጠባበቅ ጀመር።

አሁን ትንፋሹን ዋጠና ልቡ በፍርሃት እየዘለለበት ኔጋቲቩን መብራት ላይ ሰቅሎ ተመለከተው። ፍጹም የተዋጣለት ነበር። እያንዳንዱ ፊልም የመላው ዓለም ፎቶግራፍ አንሺ ሁሉ ለማግኘት የሚኮራበት ነው የሚሆነው። እያንዳንዱ ያልታወቀው የበራሪ ዲስክ አካል ጉልህ ሆኖ ወጥቷል። በተጨማሪም የሙታን ፍጡራኑ አካል በውሰጡ እንደተጋደመ ይታይ ነበር።

መጀመሪያ ፎቶውን ሲያነሳ ያልተመለከታቸው ሁለት ነገሮች በማግኘቱ ጠጋ አድረጎ ተመለከታቸው። የጠፈር መንኮራኩሩ ተከስክሶ በሚታይበት የውሰጠኛው አካል ውስጥ ሦስት ወንበሮች ይታያሉ። የሙታኑ አካል ግን ሁለት ብቻ ነበር። ሌላው እንግዳ ጉዳይ ደግሞ ከሙታኑ ፍጡራን የአንደኛው እጅ የተቆረጠ ሲሆን በአካባቢው ግን አይታይም ነበር።

@BOOKALEM

‘መናልባት ፍጡሩ ባለአንድ እጅ ብቻ መሆን አለበት’ ሲል አሰበ።

‘የአምላክ ያለህ! እነዚህ ፎቶግራፎች ፍጹም የተዋጣላቸው ናቸው!’ አለ በሐሳቡ። ‘እናቴ ትክክል ነበረች። ፍጹም ብሩህ ሰው ነኝ!’ በጣም ትንሽ የሆነችውን የፊልም ማተሚያ ከፍሉን ተመለከታት። ‘አምን በሚቀጠለው ጊዜ ፎቶግራፎቼን የማትመው ኢቶን አደባባይ በምከፍተው በጣም ትልቅና ቆንጆ ጨለማ ክፍል ውስጥ ይሆናል።’

ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣውን ንብረቱን እንደወርቅ በጣቶቹ እየደባበሰ ቆሞ ቀረ። በመላው ዓለም ላይ የእርሱን ፎቶግራፎች ለማግኘት የማይገል ወይም የማይሞት የጋዜጣና የመጽሔት ድርጅት አይኖርም። ለዚህ ሁሉ ዓመታት እነዚህ ዲቃላ አሳታሚዎች የሚያቀርብላችውን ፎቶግራፎች ከሰድብ ማስታወሻ ጋር ሲመልሱለት ኖረዋል። “በአሁኑ ጊዜ ወቅታዊ ፍላጎታችንን ሊያሙዋሉ የማይችሉትን አሁን መልስን የላክልንህን ፎቶግራፎች ስላቀረብክልን እናመሰግናለን። ሽንፈትህን በመቀበልህም እናመሰግናለን። እሰካሁን ድረስ ካሳተምናቸው ፎቶግራፎች ጋር በጣም ተመሳሳይ ናቸውና በቀላል አነጋገር የላክልንን ፎቶ ግራፎች መልስን ልከንልሃል።””

ለዓመታት ሥራ ሲለምናቸው ኖሯል። ዛሬ ደግሞ እነርሱ በደረታቸው እየተሳቡ እንዲለምኑትና ላደረሱበትም ውርደት ብድሩን እንዲከፍሉ ሊያደረጋቸው ነው።

ይህንን ለማድረግ መቆየት አይችልም። በአፋጣኝ መጀመር አለበት። የቴሌፎን ሒሳቡን ለመክፍል ጥቂት ሳምንት ብቻ በመዘግየቱ የብሪቲሽ ቴሌኮም ድጅት መስመሩን ስለቆረጠው ስልክ ለማግኘት ወደ ውጭ መውጣት ነበረበት። በግብታዊነት “ላንጋሳ” በመባል ወደሚታወቀው የዝነኛና ሀብታም ሰዎች መመገቢያ ሄዶ የገጠመውን ዕድል በመልካም ምሳ ለማክበር ወሰነ። ላንጋሳ ከአቅሙ በላይ ቢሆንም አሁን እሱም ወደ ባለፀጋነቱና ወደ ዝነኛነቱ መድረክ በመውጣት ላይ ነው።

አስተናጋጁ ማዘርሼድን በምግብ ቤቱ ጥግ ላይ አንድ ጠረጴዛ እንዳሰያዘው ከተቀመጠበት ሥፍራ አሥር ጫማ ያህል ራቅ ብሎ የተቀመጡ ሁለት የሚያውቃቸውን ሰዎች ተመለከተ። በድንገት እነማን እንደሆኑ ሲያስታውስ የደስታ ሙቀት በመላ አካላቱ ተሰራጨበት። ሚካኤል ካኒና ሮጀር ሙር! በአካል ተቀምጠዋል። ‘ምነው እናቴ በሕይወተ ሥጋ በኖረችና ይህን ታሪክ ባጫወትኳት’ ሲል ተመኘ። ስለፊልም ተዋናዮች ማንበብ በጣም ትወድ ነበር። ሁለቱ ሰዎች በዙሪያቸው ያለውን ዓለም ችላ ብለው እየሳቁና እያወካኩ ሲጫወቱ ማዘርሼድ ዐይኖቹን ከላያቸው ላይ ለመንቀል አልቻለም።

በዐይኖቻቸው ማዘርሼድን አልፈውት ሄዱ። ‘እነዚህ ዲቃሎች!’ አለ ማዘርሼድ በንዴት። ‘ወደነርሱ ሄጄ የተከበረ ፊርማቸውን እንድጠይቃቸው

@BOOKALEM

ይጠቢቃሉ። ግዴለም በጥቂት ቀናት ውስጥ እነርሱ የኔን ፈርማ ጠያቂ ይሆናሉ። እኔን ከጓደኞቻቸው ጋር ለማስተዋወቅ ይረባረባሉ። ሌስሊ! ቻርልስንና ዲንን እንድትተዋወቅልን እንፈልጋለን። እነዚህ ደግሞ ሬጊና አንድሪው ናቸው። ይህ ደግሞ ያንን ዝነኛውን የዩፎዎች ፎቶ ግራፍ ያነሳው ሌስሊ ነው!'

ማዘርሼድ ምሳውን ተመግቦ እንደጨረሰ ሁለቱን የፊልም ተዋናዮች አልፎ ፎቁ ላይ ወደሚገኘው የስልክ ሳጥን አመራ። ከቁጥር ማውጫው መጸሐፍ ላይ "ዘ ሰን" የተባለውን መጽሔት ቁጥር አገኘ።

"የፎቶግራፍ አታሚያችሁን ለማነጋገር እፈልጋለሁ ።"

"ይህ ቻፕማን ነው" አለ የወንድ ድምጽ።

"አንድ በራሪ ዲስክን ከሁለት ሙታን አብራሪዎቹ ጋር የሚያሳይ ፎቶግራፍ ለማግኘት ምን ያህል ትከፍላለህ?"

"ስዕሎቹ በበቂ ሁኔታ ጥሩ ካልሆኑ ምናልባት ለቀልጣፋ ማታሊያነታቸው በምሳሌነት እናቀርባቸዋለን። እናም....."

"ይህ የማታሊያ ዘዴ አይደለም። የዚህን ጉዳይ እውነትነት ማረጋገጥ የሚችሉ አንድን ቁስ ጨምሮ የዘጠኝ ታዋቂ ምስክሮችን ስም ማቅረብ እችላለሁ።"

የሰውየው ድምጽ ተለወጠ። "አ! እነዚህ ስዕሎች የተነሱት የት ቦታ ነው?"

"ስለሱ ግድ የለም" አለ ማዘር ሼድ። ምንም ዐይነት መረጃ በመስጠት እንዲያሞኙት አያደርግም። "ፍላጎት አላችሁ?" አለ።

"በከፍተኛ ጥንቃቄ ስዕሎቹ የሚታመኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ ከቻልክ በጣም ፍላጎት ይኖረናል።"

'አዎን በሚገባ ትፈልጋለህ!' ሲል ማዘርሼድ አሰበና "ተመልሼ እመጣለሁ" ብሎ ስልኩን ዘጋው።

የሚቀጥሉት ሁለት የስልክ ጥሪዎችም አጥጋቢዎች ነበሩ። 'የምስክሮቹን ስምና አድራሻ መውሰዴ ፍጹም ብልህነት ነበር' ሲል ለራሱ አመነ። ማንም ሰው ካሁን በኋላ እርሱን በአጭበርባሪነት ሊከስ የሚችልበት መንግድ የለም። እነዚህ ፎቶግራፎቹ በመላው ዓለም ሜጋዚኖችና ጋዜጦች በመጀመሪያ ገጽ ላይ ይታተማሉ። "ፎቶግራፎቹ በሌስሊ ማዘርሼድ" ከሚል መግለጫ ጋር።

ማዘርሼድ ሬስቶራንቱን ጥሎ ለመውጣት ሁለቱ የፊልም ተዋናዮች በተቀመጡበት በኩል እያለፈ አጠገባቸው ሲደርስ..... "ስላስቸገርኳችሁ ይቅርታ አዝናለሁ! ፊሪማችሁን ልትሰጡኝ ትችላላችሁ?" አላቸው።

ሮጀር ሙርና ሚካኤል ሱይን በደስታ ሳቅ ብለው ስማቸውንና ፊርማቸውን ትንሽ ወረቀት ላይ አስፍረው ሰጡት።

"አመሰግናለሁ!" ማዘርሼድ ከሬስቶራንቱ እንደወጣ ወረቀቱን በጭካኔ በጣጥሶ ጣለው። "'እኔ ከነርሱ የበለጠ ጠቃሚ ነኝ!' ሲል አሰበ።

@BOOKALEM

ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

ሮበርት በታክሲ ወደ ዋይት ቻፕል ተጓዘ። ዋይት ቻፕል የንግድ ማዕከል የሆነ የለንደን ክፍለ ከተማ ነው። ይህ አካባቢ ከአንድ ምዕተ ዓመት በፊት በወንጀለኛው ጃክ ዘ ራይፐር ዝናው የጎደፈ ነበር። በዋይት ቻፕል ጎዳና ዳርቻዎች ላይ ከልብሳ-ልብስ እስከ ትኩስ ሊታክልት ድረስ የማይሸጥ ነገር አልነበረም።

ታክሲው ወደ ማዘርሼድ አድራሻ እየተቃረበ በመጣ ቁጥር አካባቢው በፈራረሱ አሮጌ ሕንፃዎች፤ በአሮጌና ስብረባሪ ዕቃዎች እየተበከለ መጣ። አንድ አነስተኛ መጠጥ ቤት አለፍ ሲል 'ይህ የማዘርሼድ መደበሪያ" መሆን አለበት' ሲል አሰበ። "ቱላ ዎከር ቡት ሜከር" የሚል ጽሑፍ ሲያይ ደግሞ ምናልባት 'ማዘርሼድ የፊረስ እሽቅድድምን በተመለከተ የገንዘብ ውርርድ የሚያደርገው እዚህ መሆን አለበት' አለ።

በመጨረሻም 213 ኤ ግሩቭ ጎዳና ደረሰ። ሮበርት ታክሲውን ካሰናበተ በኋላ ማዘርሼድ የሚኖርበትን ሕንጻ ማጥናት ጀመረ። ወደ አነስተኛ የመኖሪያ ክፍሎችነት የተለወጠ አሮጌና አስቀያሚ ባለሁለት ፎቅ ሕንፃ ነበር። በዚህ ሕንፃ ውስጥም ሮበርት አንዲከታተላቸው የተላከባቸውን አጠቃላይ የምስክሮች አድራሻና የስም ዝርዝር ያለበት ሰነድ የያዘ ሰው መገኛ ነው።

ማዘርሼድ የበሩ ደወል ሲደወል ሳሎኑ ውስጥ ተቀምጦ መጠጡን እየቀዳ ነበር። በድንገተኛ ፍርሃትና ድንጋጤ ቀና ብሎ ተመለከተ። ደወሉ ተደገመ። ማዘርሼድ ድንቅዬ ስዕሎቹን ሰበሰበና ወደ ጨለማው ቤት ገባ። ፎቶዎቹን በአሮጌ የፎቶግራፎች ክምር ውስጥ ደበቀና ከጨለማው ክፍል ወጥቶ የሳሎኑን በር ሲከፍት አንድ የማያውቀው እንግዳ ሰው ተመለከተ።

"አቤት?"

"ሌስሲ ማዘርሼድ?"

"ትክክል። ምን ላድርግልህ?"

"ወደ ውስጥ ልግባ?"

"ይህ ሁሉ ለምንድነው?"

"ሮበርት የመከላከያ ሚንስትር መታወቂያ ካርድ ከኪሱ አወጣና አሳየው። ሚስተር ማዘርሼድ እዚህ የመጣሁት ለኦፊሴላዊ ሥራ ነው። እዚህ ቤት ውስጥ ወይም ደግሞ ሚንስትሩ መሥሪያ ቤት መነጋገር እንችላለን!" አለው። ነገሩ ውሸት ቢሆንም በፎቶግራፍ አንሺው ፊት ላይ ድንገተኛ ፍርሃት ለመመልከት ቻለ።

@BOOKALEM

ማዘር ሼድ ምራቁን ዋጠና.....“ምን እንደምታወራ አላውቅም። የሆነው ሆኖ መግባት ትችላለህ” አለው። ሮበርት ያልጠበቀው ክፍል ውስጥ ገባ። ቆሻሻ፤ ውዳቂ፤ በሚገባ ያልተያዘና ማንም ሰው በምርጫው የማይኖርበት ክፍል ነበር።

“እዚህ ምን ለማድረግ እንደመጣህ በትክክል ልትገልጽልኝ ትችላለህ?” አለ ማዘርሼድ በተቻለ መጠን ድምፁን የየዋህነት ቃና ለማስያዝ እየተጣጣረ።

“እዚህ የመጣሁት አንተ ስላነሳሃቸው ጥቂት ፎቶግራፎች አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቅህ ነው።

አወቆታል! ልክ የበሩ ደውል እንደተደወለ ነበር ያወቀው። እነዚህ ዲቃሎች አዱኛውን ከጆቹ ሊወስዱበት ነው። ይህንን እንዲያደርጉ አይፈቀድላቸውም።

“ስለምን ፎቶዎች ነው የምታወራው?” ሲል ጠየቀ።

ሮበርትም በትዕግስት “በተከሰከሰው ዩፎ አካባቢ ሰላነሳህው ፎቶ” አለው።

ማዘርሼድ ድንገት የደነገጠ በማስመሰል ሮበርትን ተመለከተው። “አ! እነዚያ ፎቶግራፎች በኖሩኝና በሰጠውህ ደስ ባለኝ ነበር” አለው።

“እነዚያን ምስሎች ቀርጸሃቸው ነበር?”

“ሞክሬ ነበር።”

“ሞክሬ ነበር ስትል ምን ለማለት ነው?”

“የተረገሙት ነገሮች! ፍጹም ሊወጡ አልቻሉም።” ማዘርሼድ አንድ ጊዜ አሳለው። “ካሜራዬ በጭጋግ ተዋጠ። የዚህ ዐይነት ነገር ሲደርስብኝ ለሁለተኛ ጊዜ ነው። ሌላው ቀርቶ ኔጋቲቮቹን ጣልኳቸው። ወረወርኳቸው። ጥሩ ካለመሆናቸው የተነሳ የለየለት ፊልም የማበከን ተግባር ነበር። መቼም በአሁኑ ጊዜ ፊልም ምን ያህል ውድ እንደሆነ ታውቃለህ።

‘መጥፎ ቀጣፊ ነው!’ ሲል ሮበርት አሰበ። ‘በሽብር ጠርዝ ላይ ነው ያለው’ ሲል አሰበና በሚያስተዛዝን ድምፅ.....“በጣም መጥፎ አጋጣሚ ነው” አለው። ‘እነዚያ ፎቶግፋፎች ምን ያህል እገዛ የሚያደርጉ በሆኑ ነበር።’ ስለ መንገደኞቹ የሰም ዝርዝር ምንም አልተናገረም። ማዘርሼድ ስለፎቶግራፎቹ ከዋሸ ስለሰም ዝርዝሩም ይዋሻል ማለት ነው። ፎቶግራፎቹና ሊስቱ እዚህ ቤት ውስጥ የሆነ ቦታ ተደብቀዋል ማለት ነው። ለማግኘት ደግሞ ፈጽሞ የሚያስችግሩ አይሆኑም። የመኖሪያ ቤቱ መኝታ ቤት፤ ሳሎን፤ መታጠቢያ ቤትና ዕቃ ቤትን ያካተተ ነው። ሰውዬው ፎቶዎቹንና የሰም ዝርዝር የያዘውን ሊስት እንዲያስረከበው የሚያስገድድበት መንገድ ወይም እውነተኛ ሥልጣን የለውም። ፎቶዎቹንና ሊስቱን የኤስአይኤስ መርማሪዎች መጥተው ከመውሰዳቸው በፊት እሱ ቀድሞ መውሰድ አለበት።

@BOOKALEM

"አዎን" አለና ተነፈሰ ማዘርሼድ። "እነዚያ ፎቶግራፎች አያሌ ንዋይ ባወጡ ነበር" አለው።

"ስለጠፈር መንኮራኩሩ አውራልኝ" አለ ሮበርት።

ማዘርሼድ ሳያውቀው አንገሸገሸው። እንግዳ የሆነው አሸባሪው ትዕይንት አዕምሮው ላይ እንደተቀረጸ ይኖራል። "ከቶም ቢሆን አልረሳውም!" አለው። መንኮራኩሩ ልክ ሕይወት እንዳለው ሁሉ ትርትር የሚል ትርታ ያለው ይመስል ነበር። አንድ የሆነ እርኩሰት ነበረው። እናም እነዚያ ሙታን የሌላ ዓለም ፍጡራን በውስጡ ነበሩ።"

"አውቶቡሱ ውስጥ ስለነበሩት መንገደኞች ልትነግረኝ ትችላላህ?"

'በርግጥ እችለላሁ። አድራሻቸው እና የስም ዝርዝራቸው አለኝ' ሲል በደስታ አሰበና ድምፁን ከፍ አድርጎ "የለም አልችልም። ልረዳህ የማልችልበት ምክንያትም ተሳፍሪዎቹ እኔ በሌለሁበት አውቶቡስ ውስጥ ስለነበሩ ነው። ሁሉም ለኔ እንግዶች ነበሩ" አለው ጭንቀቱን ለመደበቅ እየሞከረ።

"ገባኝ ስለትብብርህ በጣም አመሰግናለሁ ሚስተር ማዘርሼድ። ትብብርህን አደንቃለሁ። ስለፎቶግራፎቹም አዝናለሁ።"

"እኔም እንደዚሁ!" አለ ማዘርሼድ። በሩ ከእንግዳው ጀርባ ሲዘጋ ተመለከተና በደስታ ስሜት 'አደረኩት! ፈፀምኩት! አነዚህን የውሻ ልጆች አታለልኳቸው!' አለ ለራሱ።

ከውጭ በኩል ደግሞ ሮበርት ቁልፉን መረመረው። አሮጌ ሞዴል ሲሆን ይህንን ለመክፈት የተወሰኑ ሴኮንዶች ብቻ እንደሚፈጅበት አረጋገጠ። ቅኝቱን እኩለ ሌሊት አካባቢ ይጀምርና ንጋት ላይ ፎቶግራፍ አንሺው ቤቱን ለቆ እስከሚወጣ ይጠብቃል። 'እንዴ የመንገደኞቹን ስም ዝርዝር ካገኘሁ የቀረው ተልዕኮዬ በጣም የቀለለ ይሆናል' ሲል ወሰነ።

ሮበርት ማዘርሼድ ከሚኖርበት ሕንፃ አካባቢ አንድ አነስተኛ ሆቴል ተከራይቶ ከገባ በኋላ ለጄነራል ሒሊያርድ ስልክ ደወለ።

"የእንግሊዛዊውን ምስክር ስም አግኝቻለሁ ጄነራል።"

"አንድ ጊዜ።.....እሺ ቀጥል ኮማንደር።"

"ሌሊስ ማዘርሼድ። ዋይት ቻፕል 213 ኤ ግሩቭ ጎዳና ይኖራል።"

"እጅግ በጣም ግሩም! የእንግሊዝ ባለሥልጣናት እንዲያነጋግሩት አስፈላጊውን ሁሉ አዘጋጃለሁ።"

ሮበርት የመንገደኞቹን የስም ዝርዝርና የፎቶግራፎቹን ጉዳይ አልጠቀሰም። አነሱ የራሱ ሕመሞች ናቸው።

የሬጊ አሳና የድንች ጥብስ መሸጫ ሱቅ የሚገኘው ከብሩምፕተን ጎዳና ወጣ ብሎ ሲሆን በአብዛኛው ደንበኞቹ በአካባቢው የሚሠሩ ጸሐፊዎችና

@BOOKALEM

የመዝገብ ቤት ሠራተኞቹ ናቸው። ግድግዳው በእግር ኳስ ተጫዋቶች ስዕል የተሸፈነ ሲሆን የተላላጠው የግድግዳ ክፍል ደግሞ ከስዊዝ ካናል ቅራኔ ወዲህ ቀለም ሚባል ነገር ዐይቶ አያውቅም።

ከባንኮኒው ኋላ የተቀመጠው ሰልከ ሁለት ጊዜ እንዳቃጨለ አንድ ቆሸሸ ያለ የሱፍ ሹራብ የለበሰ ግዙፍ ሰው አነሳው። ሰውየው በወርቅ ክፈፍ የተሠራ ክብ መነጽር ግራ ዐይኑ ላይ ከመለጠፉ በስተቀር ማንኛውንም የለንደን ምሥራቃዊ ዳርቻ ነዋሪ ይመስላል። ለአንድ ዐይኑ መነጽር ያደረገበት ምክንያትም ጠጋ ብሎ ለተመለከተው ሰው ግልፅ ነበር። የግራ ዐይኑ ሰማያዊ ቀለም ካለው መስተዋት የተሠራው ነው።

"ሬጊ ነኝ።"

"ይህ ጳጳሱ ነው።"

"አምን ጌታዬ!" አለ ሬጊ ድምፁ ወደ ሹክሹክታ እየተለወጠ።

"የደንበኛችን ስም ማዘርሼድ ይባላል። የክርስትና ስሙ ሌስሊ። የሚኖረው 213 ኤ ግሩቭ ጎዳና ኢ-3 ነው። ይህ ትዕዛዝ በአስቸኳይ እንዲፈፀምልን እንሻለን። ገብቶሃል?

"ልክ እንደተፈፀመ ይቁጠሩት ጌታዬ።"

ምዕራፍ ሃያ

ማዘርሼድ በወርቃማ የቀን ሕልም ውስጥ ተውጦ ነበር። የመላው ዓለም የጋዜጣ ድርጅቶቹ ቃለ-መጠይቅ እያደረጉለት ሲሆን ስኮትላንድ ውስጥ ስለገዛው ጥንታዊ ሀንፃ፤ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ስለገዛው ግዙፍ የጣር ቤት በጣም ትልቅ ስለሆነው የሞተር ጀልባው እየጠየቁት ነበር።

'.....እናም ንግሥቲቱ ኦፌሴላዊ ሮያል ፎቶግራፍ አንሺ እንድትሆንላት ጋብዛሃለች የሚባለው እውነት ነው? አምን! መልሱን አሳውቅሻለሁ ብያታለሁ። እናም ከቡራንና ከቡራት እባካችሁ ይቅርታ ብታደርጉልኝ! በቢ.ቢ.ሲ ጣቢያ ለመታየት ረፈደብኝ።'

የቀን ሕልሙ በበሩ ደወል ተቋረጠበት። የእጅ ሰዓቱን ተመለከተና በጥንቃቄ ከፈተው። በሩ ላይ አንድ ከእርሱ በጣም ያጠረ ከሲታ ፊት ያለውና ቀጫጫ ሰው ቆሞ ተመለከተ። ወፍራም መነፅር አድርጓል።

"ይቅርታ አድርግልኝ። በዚህ ሰዓት በመረበሼ አዝናለሁ! ከዚህ ሕንፃ ዝቅ ብሎ ነው የምኖረው። በርህ ላይ ያለው ጽሑፍ ፎቶግራፍ አንሺ መሆንህን ይናገራል።"

"ታዲያስ?"

"የፖስፖርት ፎቶግራፍ ታነሳለህ?"

@BOOKALEM

እሱ ማዘርሼድ? የፓስፖርት ፎቶፍራፍ ያንሳ? ሰውዬው እኮ የዓለም ባለቤት ሊሆን ነው። ይህ ማይክል አንጀሎን የሚያህል ታላቅ የጥበብ ሰው የመታጠቢያ ቤት ስዕል አንዲሠራ የመጠየቅ ዐይነት ነው።

"የለም አላነሳም!" አለውና በሩን መዝጋት ጀመረ።

"በእውነት ጣልቃ ስለገባሁብህ በጣም ነው የማዝነው። በጣም አሳሳቢ በሆነ የጊዜ ጥበት ውስጥ ነው ያለሁት። ከጥቂት ጊዜ በፊት ፓስፖርቴን ሳወጣ ፎቶው ተገንጥሎ መጥፋቱን አረጋገጥኩ። ፎቶዬ ከፓስፖርቴ ላይ ጠፍቷል። ፎቶ በሌለው ፓስፖርት ማንም አውሮፕላን ላይ የሚያሳፍረኝ የለም።" ሰውየው ሲናገር ዐይኖቹ እምባ አቀረሩ።

"አዝናለሁ" አለ ማዘርሼድ። "ልረዳህ አልችልም።"

"አንድ መቶ ፓውንድ ልከፍልህ ፈቃደኛ ነኝ።"

'አንድ መቶ ፓውንድ? ፎቅ፤ ሕንፃ መርከብ ላለው ሰው? ይህ ሲድብ ነው።'

ድንክዬው ሰውዬ ንግግሩን ቀጠለ። "ከፍያውን እስከ ሁለት ወይም ሦስት መቶ ከፍ ላደርገው እችላለሁ። አየህ እዚያ አውሮፕላን ላይ መሳፈር አለብኝ ወይም ከሥራዬ እባረራለሁ።"

'ሦስት መቶ ፓውንድ? የፓስፖርት ፎቶ ለማንሳት? የማሳደጉን ተግባር እንኳ ቢረሱት አስር ሴኮንዶች ብቻ የሚፈጅ ተግባር ነው።'

ማዘርሼድ ከብሩና ስስቱ ተጋጩበት። በመጨረሻም ከብር ለስስት ሥፈራውን ለቀቀች። 'ጥቂት የኪስ ገንዘብ ባገኝ አይከፋም' አለ በሐሳቡ።

"ግድግዳውን ተጠግተህ ቁም" አለ ማዘርሼድ።

"አመሰግናለሁ። በእውነት አደንቅሃለሁ።"

ማዘርሼድ 'ምነው ፓላሮይድ ካሜራ በኖረኝ' ሲል ተመኘ። እሱ ቢኖረው ሥራውን ቀላል ባደረገለት ነበር። ቢቢታር ካሜራውን ብድግ አደረገና "ቀጥ ብለህ ቁም" አለው። ከአሥር ሴኮንዶች በኋላ ሥራው ተከናወነ። "ፎቶውን ለማሳደግ ጥቂት ጊዜ ያስፈልገኛል። ተመልስህ ብትመጣ።"

"ቅር የማይልህ ከሆነ እዚሁ እጠብቃለሁ።"

"ራስህን አመቻች።"

ማዘርሼድ ካሜራውን ይዞ ጨለማው ቤት ውስጥ ገባ። ከካሜራው ውስጥ ፊልሙን አወጣና ጥቁር ቦርሳ ውስጥ አስቀመጠው። ከዚያም የጠረጴዛውን ቀይ መብራት አበራና ፊልሙን አወጣ።

ይህን ሥራ ያጣድፈዋል። መቼም የፓስፖርት ፎቶ ሥራ ሲባል አስቀያሚ ነው። ከአሥራ አምስት ደቂቃዎች በኋላ በገንዳው ውስጥ ፊልሙን በማሳደግ ላይ እንዳለ ጭስ ይሸተው ጀመር። ግምት ይሆን? የለም አይደለም።

@BOOKALEM

ሽታው እየጠነከረ መጣ። በሩን ለመክፈት ጠመዘዘው። በሩ የተቀረቀረ ይመስላል። ባለው አቅም ሁሉ ገፋው። በጥብቅ ተዘግቷል።

"ሄሎ!" ሲል ተጣራ። "ምንድነው እዚያ ውስጥ የሚደረገው?"

መልስ የለም።

"ሄሎ!" በሩን በትከሻው መግፋት ጀመረ። ግን በሩ ላይ አንድ የተቀረቀረ ነገር ነበር። "ሚስተር!" መልስ አላገኝም። የሚሰማው ነገር ቢኖር ጎላ ያለ የሚንጣጣ ድምፅ ብቻ ነበር። የጢሱ ሽታ እያየለ መጣ። መኖሪያ ቤቱ በእሳት እተንቀለቀለ ነበር። ሰውዬው የሄደው ለዚህ መሆን አለበት። ዕርዳታ ፍለጋ መሆን አለበት የሄደው። ማዘርሼድ በሩን በትከሻው ቢተመትመውም ሊሰብረው አልቻለም። "ዕርዱኝ! ከዚህ ውስጥ አውጡኝ!" ሲል እሪታውን አቀለጠው።

ጢሱ በበሩ እየዘለቀ ሲገባ የነበልባሉ ሙቀት ይሰማው ጀመረ። መተንፈስም ፈጽሞ አስቸጋሪ ሆኖበት ያፍነው ጀመር። ሳምባዎቹ እየነደዱ ሲመጡ አየር ለማግኘት ኮሌታውን በጣጠሰው። ሕሊናውን መሳት ስለጀመረ በጉልበቱ ወደቀ። 'እባክህ አምላኬ! አሁን አትግደለኝ። አሁን ሀብታም እና ዝነኛ በመሆኖዬ አትግደለኝ።'

"ሬጊ ነኝ።"

"ትዕዛዙ ተፈፀመ?"

"አዎን ጌታዬ። ከሚገባው በላይ ቢጠበስም በሰዓቱ ቀርቧል።"

"እጅግ በጣም ጥሩ።"

ሮበርት የስለላ ሥራውን ለመጀመር ልክ ስምንት ሰዓት ከሥፍራው ሲደርስ ከከፍተኛ የትራፊክ መጣበብ ጋር ተጋፈጠ። ጎዳናው በባለሥልጣናት መኪናዎች፤ በእሳት አደጋ መከላከያ ካሚዎኖች፤ በአንቡላንሶችና፤ በሦስት የፖሊስ መኪናዎች ተሞልቷል። ሮበርት በወሬ ተመልካቾች መካከል ተጋፍቶ አለፈና ድርጊቱ ወደሚከናወንበት ማዕከላዊ ሥፍራ ገባ። ሕንፃው በአጠቃላይ በእሳት እየተንቀለቀለ ነበር። ከውጭ በኩል ሲመለከት በፎቶግራፍ አንሺው የተያዘው የመጀመሪያው ፎቅ የወደመ መሆኑን አረጋገጠ።

"እንዴት ሊሆን ቻለ?" ሲል የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኛውን ጠየቀ።

"እስካሁን ድረስ አላወቅንም። እባክህ ወደ ኋላህ ተመለስ።"

"ያንቴ ልጅ እዚያ ላይ ይኖራል። ደህና ነው?"

"አይመስለኝም" አለ በሚያስተዛዝን ድምፅ። "ገና አሁን ከሕንፃው አወጡት።"

ሮበርት ሁለት ሰዎች የተሸከርካሪ አልጋ ቃሬዛ እየገፉ ወደ አንቡላንሱ ውስጥ ሲያስገቡ ተመለከተ።

@BOOKALEM

"የምኖረው ከዚህ ሰው ጋር ነበር። ልብሶቼ በአጠቃላይ ውስጥ ስለሆኑ ገብቼ ለማው....."

የእሳት አደጋ ሠራተኛው አንገቱን አወዛወዘ። "ምንም የሚረባ ነገር የለም ጌታዬ። መኖሪያ ኢፓርተመንቱ ውስጥ ከአመድ በስተቀር የቀረ ነገር የለም።"

'ፎቶ ግራፎቹንና ብርቅዬውን የስም ዝርዝር ጨምሮ!' ሲል ሮበርት በምሬት አዘነ።

ዋሺንግትን ከተማ ደስቲን ቶርንቶን በሚሰቱ አባት በዊላርድ ስተን ጽሕፈት ቤት ምቹ የመመገቢያ ክፍል ውስጥ ምሳ እየበላ ነበር። ደስቲን ቶርንቶን ተሸብሯል። ደስቲን ሁልጊዜ ኃያል አማቱ አጠገቡ ካለ እንደተሸበረ ነው።

ዊላርድ ስተን በደስታ ስሜት ውስጥ ነበር። "ትናንት ማታ ከፕሬዚዳንቱ ጋር እራት አብረን ተመግበናል። በዛን ወቅት ቢሥራህ በጣም እንደተደሰተ ነግሮኛል። በጣም ተደስቻለሁ ደስቲን!" አለ ዊላርድ ስተን።

"በጣም ግሩም ሥራ እያከናወንክ ነው። እኛን ከዘላኖቹ አደጋ ለመከላከል በጣም ግሩም እያደረክ ነው።"

"ዘላኖች?"

አዎን። ይህችን ታላቅ አገር በጉልበቶቿ ለማንበርከክ ጠላት ብቻ ሳይሆን አገራቸውንም የሚያገለግሉ እየመሰሉ ተግባራቸውን ማከናወን ያቃታቸውን፤ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ መፈፀም ያቃታቸውንም ጭምር ነው የምንከላከለው።

"ዘዋሪዎቹን?"

"ትክክል። ዘዋሪዎቹ መቀጣት አለባቸው።"

አንድ ሰው ወደ ምግብ ቤቱ ገባ። "ይቅርታ ሚስተር ስተን። የተከበሩት ሰዎች ደርሰዋል። እርስዎን እየጠየቁ ነው።"

"እሺ!" አለና ወደ ደስቲን ዞር ብሎ "ምሳህን ጨርስ። አንድ የምመለከተው በጣም ጠቃሚ የሆነ ጉዳይ አለ። አንድ ቀን ልነግርህ እችል ይሆናል" አለው።

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሃያ አንድ

የዙሪክ አውራ ጎዳናዎች የተለየ አስቀያሚ ቅርፅ፤ ግዙፍ ቁመና፤ በጣም ትንንሽ ዐይኖችና የተቀቀለ ዓሣ የሚመስል የቆዳ ቀለም ባላቸው እንግዳ ፍጥረታት ተሞልተዋል። ሥጋ ተመጋቢዎች በመሆናቸው ከሰውነታቸው የሚመነጨው ሽታ በጣም የሚከረፋና የሚቀረና ነው። ጥቂቶቹ ሴቶች ከተገደሉ አራዊቶች የተሠሩ የቆዳ ልብሶች ለብሰዋል።

ዘራቸውን ካጠፉት የዱር አራዊት ውስጥ የቀሩትን። እስከ አሁን ድረስ በባልደረቦቿ ላይ ሞት ባስከተለው አደጋ ምክንያት ደንዝዛ ነበር። መሬት ላይ እነዚህ አስቀያሚ ፍጡራን ለአራት "ቀን" ለሚሉት ዑደት ቆይታለች። በውሃ ጥም የተነሳ ራሷን ስታ ነበር። በገበሬው የከብቶች ገንዳ ላይ ከጠጣችው ንጹህ የዝናብ ውሃ ሌላ ምንም አልጠጣችም። ከዚያ ወዲህ መሬት ከደረሰች በኋላ አልዘነበም። ሌላው መሬት ላይ ያለው ውሃ በሙሉ የሚጠጣ አይደለም። ወደ እንግዶች መመገቢያ ሥፍራ ብትሄድም የሰዎቹን ቅርናት ለመቋቋም ካለመቻሏም በላይ ጥሬ አትክልቶቻቸውንና ፍራፍሬአቸውን ለመመገብ ሞከራ በራሷ አገር እንዳሉት ጣፍጭ ሳይሆኑ ጣዕም የለሽና የማይበሉ ሆኑባት።

"ግርማዊቷ" ተብላ ነበር የምትጠራው። ዘለግ ያለችና ውብ ብሩህ አረንጓዴ ዐይኖች ያላት ሴት ናት። አደጋው የደረሰበትን ሥፍራ ከለቀቀች በኋላ የምድራዊያንን አቋም ወይም የሰውነት ቁመና ሁሉ ለመያዝ ስለቻለች ማንም ሳያውቅባት በሕዝቡ መኻል ለመዘዋወር ቢቃት።

አንድ ለሰዎች አካል በተሠራ ጠጣርና ምቾት የለሽ ወንበር ላይ ተቀመጠች። በዙሪያዋ የተቀመጡትን ሰዎች አዕምሮ እያነበበች ነበር።

ሁለቱ ምድራዊያን ፍጡራን አንድ ጠረጴዛ ይዘው አጠገቧ ተቀምጠዋል። አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያወራል።

"ፍራንዝ! ይህ በሕይወት ዘመን አንድ ጊዜ ብቻ የሚገኝ ዕድል ነው። ሃምሳ ሺህ ፍራንክ ከመጀመሪያ ጀምሮ ልታገኝ ትችላለህ። ሃምሳ ሺህ ፍራንክ የለህም?"

በጭንቅላቱ ውስጥ የሚያስበውን አነበበች። ጎይ አንቺ አሞራ። ኮሚሽኑ ያስፈልገኛል' አለ በሕሊናው።

"አዎን ። ግን አላውቅም። ከባለቤቴ መበደር አለብኝ።"

"መጥፎ የካፒታል ምደባ መክሬሃለሁ? ውሳኔህን ስጥ።"

"በጣም ብዙ ገንዘብ ስለሆነ ሚስቴ በፍፁም አትሰጠኝም።"

@BOOKALEM

“ስለመደበኛው ካፒታልስ? ሚሊዮን የማድረግ ዕድል አለ እኮ።” ‘እሺ በል!’ አለ በሐሳቡ።

“እሺ አለሁበት።” በሐሳቡ ደግሞ ‘ጥቂት ጌጣጌጦችንም መሸጥ እችል ይሆናል’ አለ።

‘አገኘሁት!’ አለና በሐሳቡ “በፍጹም አትቆጭበትም ፍራንዝ!” አለው።

ግርማዊቷ የውይይቱ ትርጉም ምን እንደሆነ አልገባትም። ሬስቶራንቱ ውስጥ ራቅ ብሎ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ተቀምጠዋል። በጣም ዝቅ ባለ ድምፅ ይነጋገሩ ስለነበር እነርሱን ለመስማት ግርማዊቷ አዕምሮዋን ወደ ሰዎቹ ዘረጋች።

“እየሱስ ክርስቶስ! እንዴት ልታረግሽ ቻልሽ?” አለ ሰውዬው። በሐሳቡ ደግሞ ‘አንቺ የውሻ ልጅ’ አለ።

እንዴት አረገዘች ብለህ ትገምታለህ? በሐሳቧ ‘ያንተ ብልት ነው ያደረገው’ አለች።

‘ማርገዝ ማለት’ አለች ግርማዊቷ ለራሷ። እነዚህ ፍጡራን (ሰዎች) ልክ እንስሶቻቸው ሜዳ ላይ በብልታቸው በመጠቀም ሌሎች እንስሳትን በሚወልዱበት መንገድ ማለት ነው’ አለች።

‘ስለዚህ ጉዳይ ምን ልታደርጊ ነው ቲና?’ በሐሳቡ.....‘ፅንሱን ማስወረድ አለብሽ።’

“ምን እንዳደርግ ትጠብቃለህ? ስለኔ ለሚስትህ እነግራታለሁ ብለህ አልነበረም?” ‘አንተ ውሸታም ዲቃላ!’ አለች በአዕምሮዋ።

“እየሸ ወለላዬ። ብዬ ነበር። ነገር ግን አሁን ያለንበት መጥፎ ዘመን ነው።” በሕሊናው ደግሞ ‘ካንቺ ጋር እንዲህ ዐይነት ግንኙነት በመፍጠሬ ዕብድ ነኝ። ችግር እንደምታስከትይ ማወቅ ነበረብኝ።’

“ለኔም በጣም መጥፎ ጊዜ ነው” አለች። ሌላው ቀርቶ ትወደኛለህ ብዬ እንኳ አላሰብም። በልቧ.....‘እባክህ እወድሻለሁ ብለህ ተናገር።’

“በእርግጥ እወድሻለሁ። ነገሩ ሚስቴ በአሁኑ ወቅት እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ላይ መሆኗ ብቻ ነው።” በሐሳቡ.....‘ላጣት አልፈልግም’ አለ።

“እኔ ራሴ በአሁኑ ወቅት በጣም አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ላይ መሆኔ አይገባህም? ያንተን ልጅ ተሸክሜያለሁ።” እንባ ከዐይኖቿ ይመነጭ ጀመር። በሕሊናዋ ደግሞ.....‘ደህና አድርገህ እንደምታገባኝ ነው’ አለች።

“እባክሽ ቀዝቀዝ በይ የኔ ወለላ። ሁሉም ነገር ይስተካከላል። አንቺ የምትፈልጊውን ያህል እኔም ልጁን ፈልገዋለሁ።”

በሕሊናው ደግሞ ‘ፅንሱን ለማስወረድ እንድትስማማ አግባባታለሁ’ ይል ነበር።

አንድ ጠረጴዛ አጠገብ አንድ ወንድ ፍጥረት ብቻውን ተቀምጧል። ‘ቃል ገቡልኝ። እሸቅድድሙም ቀደም ሲል የተስተካከለ ስለሆነ እንደማልበላ

@BOOKALEM

አረጋግጡልኝ። ልክ እንደ ቂል እኔም ያለውን ገንዘብ በሙሉ ሰጠኋቸው። ኦዲተሮቹ ከመምጣታቸው በፊት ገንዘቡን ማስመለስ መቻል አለብኝ። ያለዚያ እስር ቤት ከጨመሩኝ ልቋቋመው አልችልም። ራሴን በራሴ አጠፋለሁ' እያለ ያስብ ነበር።

ባለግርማ ምግሲ የሰዎቹን አዕምሮ ዘልቃ ገብታ ሐሳባቸውን ለማንበብ በመቻሏ የተሊያዩ ሰዎች የተሊያዩ ቋንቋዎች እያወሩ መሆኑ አልገባትም።

'ከእናት የጠፈር መንኮራኩራችን ጋር የምገናኝበት መንገድ መፈለግ መቻል አለብኝ' ስትል አሰበች። ብርማ ቀለም ያለውን በእጅ የሚያዝ በጣም ትንሽ አሳላፊና ተቀባይ መገናኛዋን አወጣች። ለሁለት የተከፈለ "ኒውሮኔት" በተባለ ዘዴ የሚሠራ ነበር።

ግማሹ ከፍል ሕይወት ያለው ቅንብር የያዘ ሲሆን ግማሹ ደግሞ ከሌላ ጋላክሲ በተገኘ ብረታማ አካል የተሠራ ነበር። ሕይወት ያለው ከፍል በሺህ የሚቆጠሩ የሴሎቸን ቅንብር የያዘ ሲሆን ሴሎቹ ወዲያው ይወለዳሉ ወይም ይተካሉ። ነገር ግን እንደአለመታደል ሆነና ትራንስሚተሩን የሚያንቀሳቅሰው ዲሊቲየም ከሪስታል ተሰብሮ ጠፋ። ከእናት መንኮራኩሯ ጋር ለመገናኘት ብትሞክርም ያለከሪስታሉ የማይቻል ሆነባት።

ሌላ የቅጠል ምግብ ለመመገብ ሞከረች። ግን ክርፋቱ የማይቻል ነበር። ከመቀመጫዋ ብድግ አለችና ወደ በሩ አመራች። ገንዘብ ተቀባይዋ ከኋላዋ....."አንድ ጊዜ ወይዘሪት!" ስትል ተጣራች። "ለተመገብሽው ምግብ አልከፈልሽም።"

"አዝናለሁ። የናንተ አማካይ የገንዘብ ምንዛሪ የለኝም።"

"ያንን ለፖሊስ ባለሥልጣናት መናገር ትችያለሽ።"

ባለግርማ ሞግሲ የገንዘብ ተቀባይዋን ዐይኖች ትኩር ብላ ስታያቸው ገንዘብ ተቀባይዋ ተዝለፍልፋ ወደቀች። ፊቷን አዙራ ከመመገቢያው ቤት ወጥታ ሄደች።

'ከሪስታሉን ፈልጌ ማግኘት አለብኝ። ከኔ ለመስማት እየጠበቁ ነው።' የስሜት ሕዋሶቿን በትኩረት መሰብሰብ መቻል አለባት። ሁሉም ነገር የተጭበረበረና የተዘበራረቀ ሆነባት። ውሃ ካላገኘች ወደ ሞት እንደምትሸጋገር አውቃዋለች።

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሃያ ሁለት

አምስተኛ ቀን

በርን ስዊዘርላንድ

ሮበርት መሄጃ የሌለው ነጥብ ላይ ደረሰ። የማዘርሼድን የሰም ዝርዝር ለማግኘት ምን ያህል ተማምኖ እንደነበር አላስተዋለም። አሁን የከትትሉ ፍንጭ ቀዝቅዟል። 'የማዘርሼድ ፎቅ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ የሰም ዝርዝሩን በእጄ ማድረግ ነበረብኝ። ይህ ደግሞ ጥሩ ትምሕርት ይሰጠኛል።" ከአዕምሮው ጀርባ ተቀብሮ የቆየ አንድ ሐሳብ ድንገት ብልጭ አለበት። ሐንሰ ቤከርማን እንዲህ ብሎ ነበር። "የተከሰከሰውን ያ.ቢ.አ. እና በውስጡ የነበሩትን ሙታን በማየታቸው ሁሉም መንገደኞች ስሜታቸው በጣም ተጋግሎ ነበር። ይህ ሽማግሌ ሰው ግን ወደ በርን በአስቸኳይ መመለስ እንደሚገባን ምክንያቱም በዩኒቨርስቲው የሚሰጠውን ሌክቸር ማዘጋጀት እንዳለበት ደጋግሞ ይናገር ነበር።" ረዥም መንገድ ቢሆንም ሮበርት ከዚህ ሌላ ምንም አማራጭ አልነበረውም።

ከበርን አየር ማረፊያ መኪና ተከራይቶ ወደ ዩኒቨርስቲው አመራ። ከራቶሲጋል የበርን ከተማ ዋና አውራ ጎዳና ታጥፎ ወጣና የበርን ዩኒቨርስቲ በሚገኝበት በላንጋስ ስትራል ጎዳና ነጎደ። የበርን ዩኒቨርስቲ በርካታ ሕንፃዎችን ያካተተ ሲሆን ዋናው ሕንፃ ከድንጋይ የተሠራ ባለአራት ፎቅና ባለሁለት ክንፍ ሲሆን ከድንጋይ ቡተሠሩ በጣም ትላልቅ የአራዊት ምስል ያላቸው የዝናብ መከላከያዎች ያጌጡ ክፍሎች ሲኖሩት ከዩኒቨርስቲው በስተጀርባ ደግሞ ወንዙን ተንተርሶ በጣም ትልቅ የመናፈሻ ሥፍራ አለ።

ሮበርት የአስተዳደር ሕንፃውን የፊት ለፊት ደረጃዎች ወጥቶ እንግዳ መቀበያው አዳራሽ ውስጥ ገባ። ቤከርማን የሰጠው ብቸኛ ማስረጃ ሽማግሌው ሰው ጀርመናዊ እና በዕለተ ሰኞ ለሚሰጠው ትምሕርት (ሌክቸር) የሚያዘጋጅ መሆኑን ነው።

አንድ ተማሪ የአስተዳደሩን ጽሕፈት ቤት አመለከተው። ከጠረጴዛው ኋላ የተቀመጠችው ሴት አስደንጋጭና አስፈሪ ቁመና ያላት ናት። በአስቀያሚ ሁኔታ የተሰፋ ሙሉ ልብስ ለብሳ ጥቁር ፍሬም በዙሪያው ያለው የዐይን መነፅር አድርጋለች። ጸጉሯ ተበትኗል። ሮበርት ቢሮዋ ሲገባ ቀና ብላ ተመለከተችው።

"ምን ነበር?"

ሮበርት ከኪሱ የመታወቂያ ካርድ እያወጣ "ኢንተርፓል!" አላት። "አንድ ምርመራ በማድረግ ላይ ስላለሁ ዕርዳታሽን ብትለግሺኝ በጣም አመሰግናለሁ። ወይዘሮ.....?"

"ፍሮ ስችራይበር። ምን ዐይነት ምርመራ?"

@BOOKALEM

"አንድ ፕሮፌሰር በመፈለግ ላይ ነበርኩ።"

"ዐይኖቿን እንደመጨፈን አድርጋ....."ስሙን!" አለችው።

"አላውቀውም።"

"ስሙን አታውቅም?"

"የለም። ጎብኚ ፕሮፌሰር ነው። ከጥቂት ቀናት በፊት እዚህ ሥፍራ ሌክቸር አድርጎ ነበር። ሰኞ ዕለት።"

"በርካታ ጎብኚ ፕሮፌሰሮች ሌክቸር ለመስጠት እዚህ ይመጣሉ። ለመሆኑ ትምህርቱ ምንድን ነው?"

"ይቅርታ?"

"የሚያስተምረው ምንድን ነው?" ድምጿ ትዕግስቷን መጨረሷን ያሳያል። "ምን ዐይነት ትምሕርት ነው የሚያስተምረው?"

አላውቅም።

ብስጭቷ እንዲታይ እያደረገች....."ልረዳህ አልችልም!" አለችው። "....እናም እንደዚህ ዐይነት ጥቅም የለሽ ጥያቄ ለማዳመጥ በጣም ሥራ ይበዛብኛል!" አለችና ፊቷን ማዞር ጀመረች።

"እህ! ጥቅም የለሽ አይደለም!" አላትና ጠጋ ብሎ በዝቅተኛ ድምጽ "አየሽ እምነት ልጥልብሽ ነው። ፕሮፌሰሩ በሽርሙጥና ንግድ ውስጥ የሚካፈል ነው" አላት።

የፍሮ ስቸራይበር አፍ በመደነቅ ተከፈተ።

"ኢንተርፖል ለወራት ያህል ጭራውን ሲከታተለው ነበር። ስለእርሱ ያለን ትኩስ መረጃ ፕሮፌሰሩ ጀርመናዊ መሆኑና በወሩ አሥራ አምስተኛ ቀን ላይ እዚህ ሥፍራ ሌክቸር የሰጠ መሆኑን ብቻ ነው።" ሮበርት ቀጥ ብሎ ቆመና "ልትረጂኝ ካልፈለግሽ ግን ዩኒቨርስቲውን ኦፊሺያል የሆነ ጥያቄ ልናቀርብለት እንችላለን። ይህ ማለት ደግሞ የዩኒቨርስቲው ዝና በመገናኛ ብዙሓን....."

"የለም! የለም!" አለች። ዩኒቨርሲቲው ይህን በመሰለ ጉዳይ ውስጥ ስሙ መነሳት የለበትም።" የተጨነቀች መሰለች። "መቼ ነበር አስተማሪ ያልከኝ?"

"አሥራ አምስተኛው ሰኞ።"

ፍሮ ስቸራይበር ተነሳችና ወደ አንድ የዶሴ ማከማቻ ሳጥን አመራች። መሳቢያውን ከፍታ ወረቀቶችን ተመለካከተችና ጥቂት ወረቀቶች ሰባ አወጣች። "ይህ ነው። በወሩ አሥራ አምስተኛው ቀን ላይ እዚህ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ሌክቸር የሰጡ ሦስት ፕሮፌሰሮች አሉ።"

"የምፈልገው ሰው ጀርመናዊ ነው።"

"ሦስቱም ጀርመናዊያን ናቸው" አለችው። "በአጭሩ አንዱ በኢኮኖሚክስ አንዱ በኬሚስትሪና አንደኛው በሳይኮሎጂ ትምሕርት ላይ ነው ሌክቸር ያደረጉት።"

@BOOKALEM

"ልመልከታቸው?"

በዝግታ ያለውዴታዋ ሪፖርቶቹን አቀበለችው። ወረቀቶቹን ተቀብሎ አጠናቸው። የእያንዳቸውን ስምና የመኖሪያ አድራሻ ይዘዋል።

"ከፈለክ የወረቀቶቹን ግልባጭ ላዘጋጅልህ እችላለሁ።"

"የለም አመሰግናለሁ።" ስሞቹንም ቁጥሮቹንም በሚገባ ሊያስታውስ ይችላል። "እንዳቸውም ምፈልገውን ፕሮፌሰር አይደሉም" አላት።

ፍሮ ስችራይበር በአፎይታ ተነፈሰች። "ተመስገን አምላኬ! እኛ ፈጽሞ በዚህ የሽርሙጥና ተግባር ውስጥ አንገባበትም።"

"አዝናለሁ። ለምንም ነገር አስቸገርኩሽ።" ሮበርት ከቢሮዋ ወጣና ወደ ከተማ ስልክ ፍለጋ ሄደ።

የመጀመሪያው ጥሪ ወደ በርን ነበር።

"ፕሮፌሰር ስችራይበር?"

"አዎን።"

"ይህ የሰን ሻይን ቱር አውቶቡስ ኩባንያ ነው። ስዊዘርላንድ ውስጥ በዚህ ወር አሥራ አራተኛ ቀን ከኛ ጋር ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት አውቶቡሳችን ውስጥ ጥንድ መነጽር ረስተው ነበር። እናም....."

የተበሳጨ በሚመስል ድምጽ....."ምን እንደምታወራ አልገባኝም" አለ። "በአሥራ አራተኛው ቀን እኔ በርን ዩንቨርስቲ ሌክቸር እሰጥ ነበር።"

"እናስ በቱሪስቶች አውቶቡሳችን አልተጓዙም?"

"ለዚህ ዐይነቱ የቂሎች ሥራ ጊዜ የለኝም። በጣም ሥራ ሚበዛብኝ ሰው ነኝ" አለና ፕሮፌሰሩ ስልኩን ዘጋው።

ሁለተኛው ጥሪ ወደ ሐምበርግ ነበር። "ፕሮፌሰር ሄንሪክ? ይህ የሰን ሻይን ቱር ኩባንያ ነው። በዚህ ወር አሥራ አራተኛው ቀን ላይ ስዊዘርላንድ ውስጥ ነበሩ?"

"ለምን ለማወቅ ፈለክ?"

"የእጅ ሻንጣዎን ስላኘን ነው። እናም ፕሮፌሰር....."

"የተሳሳተ ሰው ነው ያገኘኸው። እኔ በቱሪስቶች አውቶቡስ ላይ አልነበርኩም።"

"በኛ የጎብኝዎች አውቶቡስ ወደ ጁንግፍሮ አልተጓዙም?"

"ነገርኩህ እኮ! አልተጓዝኩም።"

ሦስተኛው ጥሪ ወደ ሙኒክ ነበር። "ፕሮፌሰር አቶ ስችሚድት?"

"አዎን።"

"ፕሮፌሰር ይህ ሰን ሻይን ቱር ካምፓኒ ነው። ከጥቂት

@BOOKALEM

ቀናት በፊት አውቶቡሳችን ላይ የዘነጉትን መነጽር አግኝተናል። እናም....."

"እንድ ስህተት መኖር አለበት።"

የሮበርት ልብ ቀለጠች። ከዚህ በኋላ የሚሄድበት ሥፍራ የለውም። ድምጹ ንግግሩን ቀጠለ። "መነጽሬ እዚህ ከኔው ጋር ነው ያለው አልጣልኩትም።"

የሮበርት መንፈስ ተጠናከረ። "ፕሮፌሰር እርግጠኛ ነዎት? በወሩ አሥራ አራተኛ ቀን ላይ በተደረገው የጁንግፍሮው ጉዞ በኛ አውቶብስ ውስጥ ነበሩ። አልነበሩም?"

"አዎን ነበርኩ ነገርኩህ እኮ። ግን ምንም የረሳሁት ዕቃ የለም።"

"በጣም አመሰግናለሁ ፕሮፌሰር" አለና ስልኩን ዘጋ። 'ቢንጎ!' ሮበርት አንድ ቁጥር ደወለና ጄነራል ሒሊያርድን ማነጋገር ጀመረ።

"ሁለት ሪፖርት የማደርጋቸው ነገሮች አሉ ጄነራል። ለንደን ስላለው ምስክር ያደረኩልዎት ሪፖርት።

"አዎን።"

"በእሳት ቃጠሎ ትናንት ሞቷል።"

"በእርግጥ? በጣም መጥፎ!"

"አዎን ጌታዬ። ነገር ግን ሌላ ምስክር አግኝቻለሁ ብዬ አምናለሁ። በደንብ ካረጋገጥኩኝ በኋላ አሳውቅዎታለሁ።"

"ካንተ እስክሰማ ድረስ እጠብቃለሁ ኮማንደር።"

ጄነራል ሒሊያርድ ደግሞ ለጃኑስ ሪፖርት አደረገ። "ኮማንደር ቤላሚ ሌላ ምስክር አግኝቷል።"

"ጥሩ! የኮሚቴ አባላት በሙሉ እረፍት የለሽ ሆነዋል። ሁሉም ሰው ኤስ.ዲ.አይ. (የከዋክብት ጦርነት) ከመጀሩ በፊት ይህ ታሪክ ይሰማ ይሆናል ብሎ ሰግቷል።"

"በቅርቡ ተጨማሪ መረጃ አቀርብልዎታለሁ።"

"መረጃ ሳይሆን ውጤት ነው የምፈልገው።"

"አዎን ጃኑስ።"

ሙኒክ ከተማ የሚገኘው ፕላተን ስትራሰ (ጎዳና) ተጠጋግተው በተሠሩ ቡናማ ሕንፃዎች የተሞላ ፀጥ ያለ የመኖሪያ ክልል ነው። ከመኖሪያ ሕንፃዎቹ በአንደኛው የፖስታ ሳጥን ላይ "ፕሮፌሰር ኦቶ ስችሚዲት" የሚል ጹሑፍ ይነበብበታል። ሮበርት ደወሉን ደወለ።

አፓርትመቱ በአንድ ረዥም፤ ቀጭንና በትክክል ያልተበጠረ ሽበታም ፀጉር ባላቸው ሰው ተከፈተ። ሰውዬው ሹራብ ለብሰው ፒፓ እያጨሱ ነበር።

"ፕሮፌሰር ስችሚድት?"

"አዎን?"

@BOOKALEM

"ለአጭር ጊዜ ላነጋግርዎ እችል ይሆን? እኔ ከ....."

"ተነጋግረናል። ዛሬ ጠዋት የደወልክልኝ ሰው ነህ። የሰው ድምጽ በማስታወስ ከፍተኛ ችሎታ አለኝ። ግባ!"

"እመሰግናለሁ!" አለና ሮበርት ወደ ሳሎኑ ገባ። ግድግዳዎቹ ከወለሉ እስከኮርኒሱ ድረስ በመቶዎች በሚቆጠሩ የመጽሐፍ ቅጾች ተጣበዋል። መጽሐፍት በየቦታው ተቀምጠዋል። ጠረጴዛዎቹ፤ ወለሉ ወንበሮቹ ሁሉ በመጽሐፍት ተጣቧል።

"ከስዊስ ቱር ኩባንያ ጋር አይደለህም። ነህ?"

"ደህና.....እኔ....."

"አሜሪካዊ ነህ አይደለህም?"

"አዎን።"

"እናም ይህ ጉብኝት ሳይጠፋ ከጠፋው መነጽሬ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።"

"ደህና.....ጌታዬ የለውም።"

"ያንተ ስሜትና ፍላጎት ያለው ስላየሁት ያ.ቢ.አ ጉዳይ ነው። በጣም የሚያበሳጭ ተሞክሮ ነው። ሁልጊዜ አሉ ብዬ አምን ነበር። ነገር ግን በፍጹም በዐይኔ አያቸዋለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም። በጣም አሰደንጋጭ ነበር።"

"ስለዚህ ጉዳይ አንዳች ነገር ሊነግሩኝ ይችላሉ?"

"ልክ ሕይወት እንዳለው ነገር ነበር። የሚያብረቀርቅ መብራት በዙሪያው አለ። ሰማያዊ.....የለም ግራጫ.....እኔ እርግጠኛ አይደለሁም።"

የማንዴልን አገላለፅ አስታወሰ። 'ቀለሙን ይለዋወጣል። ሰማያዊ ይመስላል.....ቀጥሎም አረንጓዴ.....።'»

".....ተስንጥቆ ተከፍቶ ስለነበር ሁለት የሙታን አካል ይታየኝ ነበር። ትላልቅ ዐይኖች ሲኖሯቸው አንድ ዐይነት ብርማ ልብስ ለብሰው ነበር።"

"ከእርስዎ ጋር ስለተጓዙት መንገደኞችስ ሊነግሩኝ ይችላሉ?"

"በአውቶቡስ ከኔ ጋር ስለተጓዙት?"

"አዎን።"

"ፕሮፌሰሩ ትከሻቸውን ነቀቁ። ስለነርሱ ምንም የማውቀው ጉዳይ የለም። ሁሉም ለኔ ጠጉረ ልውጦች ነበሩ። በማግስቱ ጠዋት መስጠት ስለሚገባኝ ሌክቸር አሰላስል ስለነበር ለመንገደኞቹ የሰጠሁት ትኩረት በጣም አነስተኛ ነበር።"

ሮበርት የፕሮፌሰሩን ገጽታ እየተመለከተ ጠበቃቸው።

"ምናልባት በትንሹም ቢሆን የሚረዳህ ከሆነ ጥቂቶቹ ከየት አገር እንደመጡ ልነግርህ እችላለሁ። የማስተምረው ኬሚስትሪ ቢሆንም የልሳናት አነጋገር ስልት (ፎኖቲክስ) የማጥናት ልማድም አለኝ።"

"ማንኛውም ሊያስታውሱት የሚችሉት ነገር ካለ ይደነቃል።"

@BOOKALEM

"አንድ ኢጣሊያዊ ቄስ፤ አንድ የሁንጋሪያ ዜጋ፤ አንድ ቡቴክሳን ትናጋ የሚናገር አሜሪካዊ፤ አንድ እንግሊዛዊና አንዲት ሩሲያዊት ልጃገረድ።"

"ሩሲያዊት?"

"አዎን። ግን ከሞስኮ አይደለም የመጣችው። ከአነጋገሯ ከኪየቭ ወይም ከአካባቢው የመጣች እንደሆነች ተረድቻለሁ።"

ሮበርት ቢጠብቅም ሌላ ነገር አልነበረም። "ስለስማቸው ወይም ሙያቸው የሆነ ነገር ሲናገሩ አልሰሙም?"

"አዝናለሁ። እንደነገርኩህ በምሰጠው ሌክቸር ላይ ነበር በጣም ያተኮርኩት። ሙሉ ለሙሉ አንድ አቅጣጫ ላይ ለማተኮርም አስቸጋሪ ነበር። ቄሱና የቴክሳሱ ሰው አብረው ነበር የተቀመጡት። ቴክሳሱ ያለማቋረጥ ይለፈልፍ ነበር። ቄሱ ቴክሳኑን ምንያህል እንደተረዱት አይገባኝም።"

"ቄሱስ?"

"የሮማዊያን አነጋገር ዘይቤ ነበራቸው።"

"ስለ አንዳቸው የሚነግሩኝ ተጨማሪ ነገር ይኖራል?"

ፕሮፌሰሩ ትከሻቸውን ነቀነቁና ፒፓቸውን ማጉላት። "አዝናለሁ። ምንም ልረዳህ አልችልም።"

ሮበርት ድንገተኛ ሐሳብ መጣለት። "የኬሚስትሪ ባለሙያ ነኝ ብለውኛል?"

"አዎን።"

"ፕሮፌሰር አንድ ነገር ባሳይዎትስ?" ሮበርት ኪሱ ገባና ቤከርማን የሰጠውን ቁራጭ ብረት አወጣ። "ይህ ምን እንደሆነ ሊያስረዱኝ ይችላሉ?"

ፕሮፌሰር ስችሚድት ነገርዬውን ተቀብለው በትኩረት ሲያጠኑት የፊታቸው ገጽታ መለዋወጥ ጀመረ። "ከየት.....ከየት አገኘህው?"

"መናገር አልችልም ብዬ እሰጋለሁ። ምን እንደሆነ ያውቃሉ?"

"የመግናኛ መሣሪያ አካል ነው።"

"እርግጠኛ ነዎት?"

"በእጃቸው ላይ እያገላበጡት....."ክሪስታል ዲሊቲየም ነው። በጣም በጥቂቱ የሚገኝ ብርቅ ማእድን ነው። እነዚህን ጠባብ ከፍተቶች ታያለህ? እነዚህ የሚያመለክቱት ይህ ማቴርያል ሌላ ከፍ ካለ ነገር ጋር የሚገጠም መሆኑን ነው። ብረቱ ራሱ.....ያምላክ ያለህ! የዚህ ዐይነት ነገር ዐይቼ አላውቅም።" ድምፃቸው ሁሉ በጉጉት ተዋጠ። "ለጥቂት ቀናት ልታውሰኝ ትችላለህ? በስፔክትሮስኮፕ (የብርሃን ጨረር በሚያመነጭ መሣሪያ) ላጠናው እፈልጋለሁ ።"

"የለም ይህ አይቻልም!" አለ ሮበርት።

"ግን....."

"አዝናለሁ" አለና ሮበርት ዕቃውን ወሰደ።

@BOOKALEM

ፕሮፋሰሩ ብስጭታቸውን ለመደበቅ እየሞከሩ.....“ምናልባት መልሰህ ልታመጣው ትችላለህ? ለምን ካርድህን አትሰጠኝም? የበለጠ የማገኘው ጉዳይ ካለ ልደውልልህ እችላለሁ” አሉት።

“አንድም ካርድ የያዝኩ አይመስለኝም” እያለ ሮበርት ኪሶቹን ፈታተሻቸው።

“እዎን እኔም እንዳልያዝክ ገምቻለሁ!” አሉ ፕሮፌሰሩ በጣም ቀስ ብለው።

ኮማንደር ቤላሚ ለጄነራል ሒሊያርድ ስልክ ደወለ። ጀኔራል ሒሊያርድ ስልኩን አነሳና “አቤት ኮማንደር!” አሉት።

“የአዲሱ ምስክር ስም ፕሮፌሰር ስቸሚድት ነው። ፕላተን ስትራስ 5 ሙኒክ ውስጥ ይኖራል።”

“እመሰግናለሁ ኮማንደር። የጀርመንን ባለሥልጣናት ባስቸኳይ አሳውቃቸዋለሁ።”

ሮበርት ላገኘው የምችለው የመጨረሻው ምስክር ይህ ብቻ ነው ለማለት ጥቂት ነበር የቀረው። ግን አንድ የሆነ ነገር ያዘው። ሽንፈትን ማመን እጅግ ይጠላ ነበር። ግን የከተትሉ ፈለግ ቀዘቀዘበት። አንድ ቴክሳንና አንድ ቄስ። ቄሱ የመጡት ከሮም። በሚሊዩን ከሚቆጠሩ ቄሶች ውስጥ ለይቶ ማግኛ መንገድ የለውም። ‘ምርጫ አለኝ’ አለ ሮበርት። ‘መመለስ ወይም ወደ ሮም ተጉዤ አንድ የመጨረሻ ሙከራ አደርጋለሁ’ አለ።

.....

ቡንዳሼር ፋሱንገሶት ዛሞት። (የሕገ መንግሥቱ የመከላከያ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት) በማዕከላዊ የበርሊን ከተማ ኑማርከር ጎዳና ላይ ይገኛል። ትልቅና ግራጫማ ቀለም ያለው በአካባቢው ካሉት ሕንፃዎች የሚለይ ነው። በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ የመሥሪያ ቤቱ ቺፍ ኢንስፔክተር ኦቶ ጆአኪም አንድ መልዕክት እያጠና ነበር። ሁለት ጊዜ በጥንቃቄ አነበበውና ከጠረጴዛው ላይ ቀይ ስልክ አነሳ።

@BOOKALEM

ስድስተኛ ቀን

ሙኒክ ጀርመን

በማግስቱ ጠዋት አቶ ስቸሚድት ለሥራ ወደ ላቦራቶሪያቸው (ቤተ ሙከራ) እየተጓዙ በነበረበት ወቅት ባለፈው ምሽት ከአሜሪካዊው ጋር ስላደረጉት ውይይት እንያስላሰሉ ነበር። 'ያ የብረት ቁራጭ ከየት ነው ሊገኝ የቻለው?' እስከዛሬ ከገጠማቸው ሁሉ በጣም አስደናቂ የሆነው ነገር ነበር። 'በአውቶቡሱ ላይ ስለነበሩት መንደደኞች ለማወቅ እንደጓጓ ተናግሯል። ለምን? ስለበራሪው ዲስክ ምስክሮች በመሆናቸው ነው? ምንም ነገር እንዳያወሩ ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው ነው? ከሆነ ለምን አሜሪካዊው አላስጠነቀቀኝም? አንድ ያልተለመደ ነገር በመከናወን ላይ ነው!' ሲሉ ፕሮፌሰሩ ወሰኑ።

ላቦራቶሪው ውስጥ እንደገቡ ጃኬታቸውን አወለቁና ልብስ መስቀያው ላይ አንጠልጥለው ልብሶቻቸው እንዳይቆሸሹ የሚከላከሉበት ሸርጥ አሸረጡ። ለብዙ ሳምንታት በኬሚካል ሙከራዎች ላይ ጥናት ያደርጉበት ወደነበረ አንድ ጠረጴዛ አመሩ። 'ይህ ውጤት ካስገኘ የኖቤል ሽልማት ማለት ነው!' አሉ። ተለቅ ባለ የመስተዋት ብርጭቆ የተቀመጠ የተጣራ ውሃ አወጡና በአንድ ሌላ ዕቃ ውስጥ የተቀመጠ ቢጫ ፈሳሽ ላይ መጨመር ጀመሩ። 'እንግዳ ነገር ነው!' አሉ ፕሮፌሰሩ። እንደዚህ ብሩህ ቢጫማ ቀለም እንደነበረው አላስተዋሉም።

ጆሮ የሚበጥስ ከባድ ፍንዳታ! ላቦራቶሪ በከፍተኛ ሁኔታ ሲፈነዳ የብርጭቆ፤ የጠርሙስና የሰው ሥጋ በየግድግዳው ላይ ተረጨ ተለጠፈ።

አስቸኳይ መልዕክት

በጣም ከፍተኛ ምሥጢር

የጀርመን መረጃ ድረጅት ለ–ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል

(ቢ.ኤፍ.ቪ) ምክትል ዳይሬክተር ዐይኖች ብቻ

የመልዕክት መጨረሻ

ግልባጭ የለውም

አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ

4- አቶ ስቸሚድት–ተወግዷል

ሮበርት በኢጣሊያ አየር መንገድ አውሮፕላን ወደ ሮም በመጓዝ ላይ ስለነበረ የፕሮፌሰሩን ዜና እረፍት ሳይሰማ ቀረ።

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሃያ ሦስት

ደስቲን ቶርቶን እረፍት የለሽ እየሆነ መጣ። በአሁኑ ጊዜ ሥልጣን ያለው ሰው ነው። ሥልጣን ደግሞ ልክ እንደ እፅ ሱስ የምታስይዝ ናት። የበለጠ ፈለገ። የሚስቱ አባት አንድ ያልታወቀ ምሥጢራዊ ከበብ ውስጥ እንደሚያስገባው ቃል ቢገባለትም እስካሁን አልፈጸመለትም።

ደስቲን ቶርቶን የባለቤቱ አባት ሁልጊዜ አርብ አርብ ያላንዳች ዱካ ይጠፋ እንደነበር የተረዳው እንደዕድል ሆኖለት ነበር። ቶርንቶን ከሰውዬው ጋር ምሳ ለመብላት ፈለገና ደወለለት። የዊላርድ ስተን የግል ጸሓፊው.....አዝናለሁ ሚስተር ስተን በዛሬው ዕለት አይገኙም" አለችው።

"አ! በጣም ያሳዝናል። የሚቀጥለው አርብስ?"

"አዝናለሁ። ሚስተር ስተን የሚቀጥለውም አርብ አይገኙም።"

'ያልተለመደ!' ከሁለት ሳምንታት በኋላም ሲደውል ተመሳሳይ የሆነ መልስ በማግኘቱ ይበልጥ እንግዳ ነገር ሆነበት። 'ሽማግሌው ሁሌ አርብ ዕለት የት ነው የሚሰወረው? የጎልፍ ስፖርት ተጫዋች ወይም የማንኛውም ዐይነት ነገር ልምድ ያለው ሰው አይደለም። ግልጽ የሆነው ጉዳይ ሴት መሆን አለበት!' አለ። የዊላርድ ስተን ሚስት በጣም ማሕበራዊና ሀብታም የሆነች ሴት ናት። በጣም ተግባራዊና በራሷ መንገድ ልክ እንደባሏ ጠንካራ ሴት ናት። 'ባሏ ከሌሎች ሴቶች ጋር የሚያመነዝር ከሆነ ጉሮሮውን አገኘሁት ማለት ነው። ሁኔታውን ማጣራት አለብኝ' ሲል ደስቲን በሐሳቡ ወሰነ። ደስቲን ቶርንቶን እጁ ውስጥ ባለው የስለላ መዋቅር በመጠቀም የሚስቱ አባት ምን በማድረግ ላይ እንደሚገኝ በቶሎ መረዳት ቻለ ነበር። ነገር ግን ቶርንቶን አንድ የተሳሳተ እርምጃ በመውሰድ ራሱን ችግር ውስጥ የሚከት ሞኝ ሰው እንዳልሆነ ሁሉ ዊላርድ ስተን ደግሞ በግል ሕይወቱ ውስጥ ማንም ጣልቃ እንዲገባበት የሚፈቅድ ሰው አይደለም። ስለዚህም ምርመራውን ራሱ ለማካሄድ ወሰነ።

በማግስቱ ልክ ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን ደስቲን ቶርንቶን አንድ ምንም መለያ ምልክት የሌለው ፎርድ ታኑስ አውቶሞቢል ይዞ ከግዙፉ የዊላርድ ስተን ሕንጻ ራቅ ብሎ መጠበቅ ጀመረ። በጣም ውርጫማና አስከፊ ንጋት ነበር። 'ለመሆኑ ምን እያደረኩ ነው?' ሲል ደስቲን ራሱን ጠየቀ። 'ምናልባት ስለስተን ሁኔታ ትክክለኛ የሆነ ምክንያታዊ ገለጻ ሊኖር ይችላልና ጊዜዬን በከንቱ በማጥፋት ላይ ሳልሆን አልቀርም' ሲል አሰበ። ቢሆንም ግን አንድ የማያውቀው ምክንያት እዚያው ጉትሮ ያዘው።

ከጧቱ አንድ ሰዓት የመውጪያው በር ተከፈተና አንድ መኪና ብቅ አለ። ዊላርድ ስተን ራሱ ነበር አሽከርካሪው። በሽንጠ ረዥሙ አውቶሞቢል ፋንታ የቤት

@BOOKALEM

ሠራተኞች የሚጠቀሙበትን አነስተኛ መኪና ነበር የያዘው። ቶርንቶን መላ አከላቱን ከፍተኛ የሆነ የደስታ ስሜት ሲወረው ተሰማው። 'አንድ የምደርስበት ምሥጢር መኖር አለበት። የሰው ልጆች በተስተካከለ ቅደም-ተከተል ይኖራሉ። ዊላርድ ስተን ደግሞ ይህን ቅደም-ተከተል አዛንፏል። የሚሆነው ጉዳይ ከሴት ጋር መሆን አለበት' አለ በሕሊናው።

ደስቲን የማይታይበትን ያህል ርቀት ጠብቆ በጥንቃቄ እያሽከረከረ በዋሺንግተን ጎዳናዎች በማቆራረጥ የሚሰቱን አባት ከኋላው በመከተል ወደ አርሊንግተን ተጓዘ። በሐሳቡ.....'ይህን ጉዳይ ለስለስ አድርጌ ነው መያዝ የሚገባኝ። ሽማግሌውን ጠንከር አድርጌ መግፋት የለብኝም። ስለቅምጡ አስፈላጊውን ሁሉ መረጃ ካገኘሁ በኋላ ይህንን በመያዝ አማቴን እጋፈጠዋለሁ። ብቸኛው ፍላጎቴ ለራሱ ደሕንነት አስፈላጊ የሆነውን መከላከያ ማድረግ መሆኑን ነግረዋለሁ። መልዕክቱም ይገባዋል። በመገናኛ ብዙሓን ዝናውን ማጉደፍ አይፈልግምና።'

ደስቲን በራሱ የግል ሐሳብ ተዘፍቆ ስለነበር ዊላርድ ስተን የተጠመዘዘበትን መንገድ ሊስት ትንሽ ነበር የቀረው። አንደኛ ደረጃ የሆነ የመኖሪያ ሰፈር ክልል ውስጥ ነበሩ።

ጥቁሯ አነስተኛ መኪና ግራና ቀኝ በዛፍ በታጠረ የመኪና መንገድ ውስጥ ተሰወረች።

ደስቲን መኪናውን አቆመና የተሻለ ውሳኔ ለመስጠት ማሰብ ጀመረ። ዊላርድ ስተንን አሁን ከነእምነት ማጉደሉ ይጋፈጠው? ወይም እሰኪወጣ ይጠብቅና መጀመሪያ ውሸማውን ያነጋግራት? ወይስ መጀመሪያ አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ ይሰብስበና ከዚያም አማቱን ያነጋግረው? በመጀመሪያ ወደ ቤቱ ተጠግቶ ለመሰለል ወሰነ። ቶርንቶን መኪናውን ወደ መንገዱ ጠርዝ አቆመና ከቤቱ ጀርባ በሚወስደው መንገድ ሄደ። የእንጨት አጥር የቤቱን ጀርባ ቢዘጋውም ይህ ችግር አልሆነበትም። የአጥሩን በረ ከፈተና ወደ ውስጥ ገባ። በጣም ትልቅ ውበና በከፍተኛ ጥንቃቄ የተያዘ ግቢ ውስጥ ነበር የገባው። በዛፎቹ ጥላ ሥር ምንም ድምጽ ሳያሰማ በፀጥታ ተረማመደና የቤቱ የኋላ በር ሲደርስ የሚቀጥለው እርምጃው ምን መሆን እንዳለበት ለመወሰን ቆመ። ስለሚከናወነው ተግባር በቂ ማስረጃ መያዝ አለበት። ያለዚያ ሽማግሌው ፊቱ ላይ ነው የሚስቅበት። እዚህ ቤት ውስጥ የሚከናወነው ተግባር ምንም ሆነ ምን የወደፊት ዕድሉን የሚከፍት ቁልፍ መሆን አለበት።

ቶርንቶን የኋላውን በር በዝግታ ሞከረው። አልተቆለፈም ነበር። ወደ ውስጥ ሲገባ ያጋጠመው ጥንታዊ ዝግጅት ያለው የምግብ ማብሰያ ክፍል ነው። በአካባቢውም ማንም አልነበረም። ወደ በሩ አመራና ቀስ ብሎ ሲከፍተው በጣም ትልቅ የሆነ የእንግዳ መቀበያ አዳራሽ ተመለከተ። ከአዳራሹ መጨረሻ ላይ ወደ ቤተ መጽሐፍቱ የሚያመራ ሌላ በር አለ። ቶርንቶን በፀጥታ ወደ በሩ ተራመደና

@BOOKALEM

አጠገቡ ሲደርስ ለማዳመጥ ፀጥ ብሎ ቆመ። ምንም ዐይነት የሕይወት ምልክት የለም። ሽማግሌው ምናልባት ፎቁ ላይ መኝታ ቤት ውስጥ ሳይሆን አይቀርም!'

ቶርንቶን ቀ.....ስ ብሎ ይመለከት ጀመር። እከፍሉ ውስጥ በደርዘን የሚቆጠሩ ሰዎች በአንድ ትልቅ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠዋል።

"ግባ ደስቲን!" አለ ዊላርድስተን። "እየጠበቅንህ ነበር።"

ምዕራፍ ሃያ አራት

ሮም የሮበርትን ስሜት አንጠፍጥፋ መጨረስ የቻለች አስቸጋሪ ከተማ ሆነችበት። የጫጉላ ሽርሽሩን ከሱዛን ጋር በዚህች ከተማ ውስጥ ሰላደረገ ትዝታዋ ሁሉ አየለበት። ሮም የእናቱ ንብረት የሆነውን የሐስለርን ሆቴል ንግድ ይመራ የነበረውና ደንቆሮ የነበረው ነገር ግን አምስት ዐይነት ቋንቋዎችን ከሰዎች ከንፈር ላይ ማንበብ የሚችለው የሮቤርቶ ከተማ ነበረች። ሮም ቲቮሊ የሚገኘው የቪላ ዲ ኢስቴ ያትክልት ሥፍራ ነበረች። ሮም በሉክሪዚያ በርጊያ የተመሠረተው የአንድ መቶዎቹ ቆንጆዎች የሱዛን መደሰቻ ከተማ ነበረች። ሮም ከሲፓኝ ደረጃዎች በታች ያለች ኮሎሲየምን፤ ቫቲካንን፤ ፎረምንና የማይክል አንጀሎን የሙሴ ሃውልት የያዘች ከተማ ናት። ሮም የሱዛን የደስታና ሳቅ ከተማ ስትሆን ድምጿም.....'እባክህ ሮበርት ሁልጊዜም እንደዚህ ደስተኞች እንደምንሆን ቃል ግባልኝ!' ይለው ነበር።

'እዚህ ሥፍራ ምን እያደረኩ ነው? ሌላው ቀርቶ ቄሱ እዚህ መሆናቸውን እንኳን አላውቅም። ወደ አገሬ ተመልሼ ሁሉንም ነገር የመርሳዬ ጊዜ አሁን ነው' ሲል አሰበ።

ግን በውስጡ ያለ አንድ ነገር.....ከብዙ ዓመታት በፊት ከሞተ ዝርያው የወረሰው አይበገሬ ባሕርይ ትቶ እንዳይሄድ አደረገው። 'አንድ ቀን ብቻ እሞክራለሁ። የአንድ ቀን ሙከራ ብቻ!' ሲል ወሰነ።

የሊዎናርዶ ዳቪንቺ አየር ማረፊያ እጅግ በጣም ተጣቦ ነበር። እናም እያንዳንዱ ሰው ለሮበርት ቄስ መስሎ ነው የሚታየው። ከሃምሳ? ከአንድ መቶ ሺህ? ቄሶች መኻል ነው አንድ ቄስ የሚፈልገው? በታክሲ ወደ ሐስለር ሆቴል ሲያመራ ረዣዥም ልብሶቻቸውን የተላበሱ በርካታ ቄሶች በጎዳናው ላይ ተመለከተ። 'ይህ የማይቻል ነገር ነው። አዕምሮዬን ሳልስት አልቀረሁም' አለ ሮበርት።

ሐስለር ሆቴል እንግዳ መቀበያ አዳራሽ ውስጥ አቀባበል ያደረገለት ረዳት ሥራ አስኪያጁ ነበር።

"ኮማንደር ቤላሚ! አንተን እንደገና ማየት ምን ያህል ያስደስታል?" አለው።

@BOOKALEM

"አመሰግናለሁ ፔትሮ። ለአንድ ቀን ለኔ የሚሆን መኝታ ክፍል ይኖራችኋል?"

"ላንተ? በእርግጥ ላንተ ምንጊዜም ይኖራል።"

አስተናጋጁ ሮበርትን ከዚህ በፊት ይዞት ወደነበረ ክፍል ወሰደውና "ኮማንደር ምንም ዐይነት የምትፈልገው ነገር ካለ እባክህ አሳውቀኝ!" ብሎት ወጣ።

'ተዐምር ነው የምፈልገው!' ሲል አሰበና አዕምሮውን ለማሳረፍ አልጋው ላይ ጋለል አለ።

'አንድ ቄስ ከሮም ወደ ስዊዘርላንድ የሚጓዘው ለምንድነው? በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ። ለእረፍት ተጉዞ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ በቄሶች ስብሰባ ላይ ለመገኘትም ይሆናል። በቱሪስቶች አውቶቡስ የነበረው ብቸኛው ቄስ መሆኑ ምን ያመለክታል? በቡድን ያልመጣ ከመሆኑ በስተቀር ሌላ ነገር አይጠቁምም። ስለዚህም ጓደኞቹን ወይም የቤተሰቡን አባላት እየጎበኘ ነበር ማለት ነው። ወይም ምናልባት በቡድን ለጉብኝት መጥቶ ጓደኞቹ በዕለቱ ሌላ ፕሮግራም ነበራቸው ማለት ነው።' ሮበርት በሐሳብ ያለ ምንም ዐይነት ውጤት ዙሪያውን ተሽከረከረ። 'እስቲ ወደ ኋላ ከመነሻው ልጀምር። ቄሱ ወደ ስዊዘላንድ እንዴት ሊገባ ቻለ? መኪና አለመያዙ በጣም ጥሩ አጋጣሚ ነው። አንድ ሰው በመኪናው ሊፍት ሰጥቶት ይሆናል። በአውሮፕላን ወይም በባቡር ሊመጣ ሲችል ያለዚያም አውቶቡስ ተሳፍሮ ሊሆን ይችላል። ለእረፍት ጉዞ ሊመጣ ሲችል ያለዚያም አውቶቡስ ተሳፍሮ ሊሆን ይችላል። በእረፍት ጉዞ ላይ የነበረ ከሆነ ደገሞ ያን ያህል ብዙ ጊዜ አይኖረውም። ስለዚህ የተጓዘው በአውሮፕላን ነው ብዬ ልገምት። የዚህኛው መስመር ትንተና የትም አያደርስም። በአየር መንገዶች የመንገደኞች መግለጫ ሊስት ላይ ሌላ ስም ተጠቅሞ ሊሆን ይችላል። ግን የአንድ ቡድን ባልደረባ የነበረ ከሆነ.....'

ቫቲካን የጳጳሱ መደበኛ የመኖሪያ ሥፍራ በቫቲካን ኮረብታ ላይ ወደ ታይበር ምዕራባዊ ዳርቻ ሲል በሰሜን-ምዕራብ ሮማ ከተማ መጨረሻ ላይ በግርማ ሞገስ ተገትራለች። በማይክል አንጀሎ የተነደፈው የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ፍርስራሽ ላይ የሚገኙት ትልልቅ ቆጥ መሰል ግምቦች ቀን ከሌሊት የተለያየ የእምነት መስመር ባላቸው በርካታ ጎብኚዎች እንደተወረሩ ነው።

ፒያዛው ግማሽ ክብ በሆኑ በ667 ዓ.ም. በርኒኒ በተባለ መሐንዲስ በተጠናቀቁ ግምቦች ተከቧል። በተጨማሪም 284 ከአብነ በረድ የተሠሩ ምስሶዎች ሲኖሩት በላዩ ላይ ደግሞ 141 ሃውልቶች በተርታ ተገትረውበታል። ሮበርት ከደርዘን በላይ ለሆነ ጊዜ ሥፍራውን ቢጎበኘውም እንደገና ባየው ቁጥር ትንፋሽ የሚያሳጥር የአድናቆት ስሜት ይወረው ነበር።

የቫቲካን ውስጣዊ አወቃቀር ደግሞ በእርግጥ ከምንም የበለጠ መታየት የሚገባው ተደናቂ ሥፍራ ነው። የሲስቲን ጸሎት ቤትና ሚውዚየም ለመግለጽ የሚያስቸግር ውበት ነበራቸው።

@BOOKALEM

ግን በዚህ ዕለት ሮበርት ለጉብኝት አልነበረም የመጣው። የቫቲካንን የሕዝብ ግንኙነት ጽሕፈት ቤት ፊልጎ አገኘው። ከጠረጴዘው ኋላ የተቀመጠው ወጣት ሰው ትሁት ነበር።

"ምን ልርዳዎት?"

ሮበርት የመታወቂያ ካርድ አወጣና አሳየው። "ከታይም ሜጋዚን ነው የመጣሁት። ባለፈው ሳምንት ወይም በወዲያኛው ስዊዘርላንድ ውስጥ መንፈሳዊ ስብሰባ ስለተካፈሉ ካህናት አንድ አንቀጽ በማዘጋጀት ላይ ነኝ። የሕይወት ታሪክ መረጃ ለማግኘት ነው የመጣሁት።"

ሰውዬው ዐይኖቹን አጨናብሶ ሮበርትን አጠናው። "ባለፈው ወር ቬኒስ ውስጥ ስብሰባ የተካፈሉ ካህናት አሉን። ነገር ግን አንዳቸውም ቢሆኑ ስዊዘርላንድ ውስጥ አልነበሩም። ልረዳህ አልችልም።"

"በእውነት በጣም አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ነው" አለ ሮበርት። "ይህንን መረጃ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?"

"አንተ የምትፈልገው የካህናት ቡድን የትኛውን የቤተ ክርስቲያን ዘርፍ ነው የሚወክሉት?"

"ይቅርታ አልገባኝም?"

"በርካታ የሮማ ካቶሊካዊ ሥርዓቶች አሉ። ፍራንሲስካንስ፤ ሜሪስትስ፤ ቤኔዲክቲስ፤ ትራፒስት፤ ጀስዊትስ፤ ዶሚኒካንስ እና ሌሎችም በርካታዎች አሉ። እነሱ ወደሚወክሉት የቤተክርስቲያን ዘርፍ ሄደህ ብትጠይቅ የተሻለ ነው ስል ሐሳቤን አለግሳለሁ።"

"ሌላ ሐሳብ ይኖርሃል?"

"የለኝም።"

ከቫቲካን ወጣና በሮም አውራ ጎዳናዎች ላይ ሕዝቡን ችላ ብሎ የራሱን ሐሳብ በአዕምሮው እያብላላ መዘዋወር ጀመረ። ፒያዛ ዴል ፓፓሎ አደባባይ ሲደርስ አንድ ቡና ቤት በረንዳ ላይ ሲንዛኖ አዝዞ ተቀመጠ። ትንሽ እንኳ አልነካለትም። መጠጡ እፊቱ ተቀምጧል። 'ካሕኑ ምናልባት አሁንም ስዊዘርላንድ ውስጥ ሊሆን ይችላል። የትኛውን ሥርዐት ነው የሚወክለው? አላውቅም። የማውቀው ነገር ቢኖር ሮማዊ ነው የሚለውን የፕሮፌሰሩን ቃል ብቻ ነው።'

መጠጡን ተጎንጨለት።

'ከሰዓት በኋላ ረፋዱ ላይ ወደ ዋሺንግተን የሚበር አውሮፕላን አለ። መሳፈር አለብኝ። በቃኝ አቁሚያለሁ። የመሰናበቻ ጊዜ ነው!'

"ኢስ ኮንቶ ፔር ፎቤሪ?"

"ሲ ሲኞሬ!"

ሮበርት ፒያዛውን በዐይኖቹ ቃኘ። ከቡና ቤቱ ባሻገር አውቶቡስ መንገደኞች እያሳፈረ ሲሆን በሰልፉ ላይ ሁለት ቄሶች ነበሩ። ሮበርት ሌሎች መንገደኞች

@BOOKALEM

የመጓጓዣ ሒሳባቸውን እየከፈሉ ከአውቶቡሱ ጎላ ሲገቡ ተመለከተ። ቀሳውስቱ ግን ገንዘብ ተቀባዩ ዘንድ ሲደርሱ ፈገግታ ለገሱትና አልፈውት ገንዘብ ሳይከፍሉ ወንበር ላይ ተቀመጡ።

"ቼከዎት ሲኞር!" አለ አስተናጋጁ።

ሮበርት ፈጽሞ አልሰማውም። አዕምሮው እየሮጠ ነበር። 'በዚህ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ማዕከላዊ ልብ በሆነ ከተማ ውስጥ ቄሶች አንዳንድ የተለያዩ ጥቅማ-ጥቅሞች ሊኖራቸው ይችላል። አዎን የሚሆን ነው.....'

የስዊስ አየር መንገድ መሥሪያ ቤት ከቪያ ቬኔቶ የአምስት ደቂቃ ጉዞ አለፍ ብሎ በቪየፓ ጎዳና ላይ ይገኛል። ሮበርት ወደ እንግዳ መቀበያው ዴስክ አመራና....."ሥራ አስኪያጁን ለማነጋገር እፈልጋለሁ" አለ።

"ሥራ አስኪያጁ እኔ ነኝ። ምን ልርዳህ?"

ሮበርት የመታወቂያ ካርድ አውጥቶ እያሳየ....."ሚካኤል ሁድሰን እባላለሁ። የኢንተርፖል ባልደረባ ነኝ" አለ።

"ምን የማደርግልዎ ነገር አለ ሚስተር ሁድሰን?"

"አንዳንድ የጭነት ማመላለሻ አየር መንገዶች አውሮፓ ውስጥ በተለይም እዚህ ሮም ውስጥ አግባብ ያልሆነ ሕገ ወጥ የዋጋ ቅናሽ እየተደረገ ነው በማለት አቤቱታ እያቀረቡ ነው። ከዓለም አቀፍ ስምምነት አንጻር....."

"ይቅርታ ሚስተር ሁድሰን። የሆነው ሆኖ የስዊስ አየር መንገድ ለማንም ቅናሽ አላደረገም። ሁሉም ሰው የተወሰነውን ዋጋ ነው የሚከፍለው።"

"ሁሉም?"

"በእርግጥ ከአየር መንገድ ተቀጣሪዎች በስተቀር።"

"ለቄሶችስ ቅናሽ አታደርጉላቸውም?"

"የለም አናደርግም። በዚህ አየር መንገድ ሙሉ ክፍያ ነው የሚከፍሉት።"

ሮበርት "ጊዜህን ስለሰጠህኝ አመሰግናለሁ" አለና ወጣ። ቀጥሎ የሄደበትና የመጨረሻ ተሰፋው የሆነው የኢጣሊያ አየር መንገድ "አልኢታሊያ" ነበር።

"ሕገ ወጥ የዋጋ ቅናሽ?" አለ ሥራ አስኪያጁ ግራ በመጋባት ሁኔታ ሮበርትን እየተመለከተው። "የዋጋ ቅናሽ የምናደርገው ለሠራተኞቻችን ብቻ ነው።"

"ለካህናትስ የዋጋ ቅናሽ አታደርጉም።"

የሥራ አስኪያጁ ፊት በራ። "አሃ! ያ አዎን። ነገር ግን ሕገ ወጥ አሠራር ሳይሆን ከካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር ባደረግነው ስምምነት መሠረት ነው።"

ሮበርት ልቡ ተኮማተረች። "ከሆነ አንድ ቄስ ከሮም እ.....ለምሳሌ ወደ ስዊዘርላንድ ለመብረር ቢፈልግ ይህን አየር መንገድ ይጠቀማል?"

"አዎን። ርካሽ ስለሚሆንለት።"

"በትክክል ኮምፒውተሮቻችንን ዘመናዊ ወይም ወቅታዊ መረጃዎችን እንዲያከማቹ ለማስቻል ነው የምጠይቅህ። ባለፉት ሁለት ሳምንታት ምን ያህል

@BOOKALEM

ቀላውስት ከሮም ወደ ስዊዘርላንድ በረራ እንዳደረጉ ብትነግረኝ ትልቅ ዕርዳታ በሆነ ነበር። የዚህ ሪኮርድ ይኖራችኋል። አይኖራችሁም?"

"እምን። በእርግጥ ሊታከስ አከፋፈል ስንል ይኖረናል።"

"ይህን መረጃ ባገኝ በእርግጥ አደንቃለሁ።"

"ባለፉት ሁለት ሳምንታት ምን ያህል ቀላውስት ወደ ስዊዘርላንድ እንደበረሩ ለማወቅ ነው የሚሹት?"

"አዎን! ዙሪክ ወይም ጀኔቫ።"

"ጥቂት ቢጠብቁ ከኮምፒውተሮቻችን ጋር ልነጋገር።" ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ ማኔጀሩ የኮምፒውተር የመልስ ንባብ ወረቀት ይዞ መጣ። "ባለፉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ ከሮም ወደ ስዊዘርላንድ የበረረው አንድ ቄስ ብቻ ነው። የኮምፒውተሩን ንባብ (ፕሪንት አውት) እየተመለከተ..... "ከሮም በሰባት ለቀቀ። የመልስ ጉዞው የተሞዘገበው ከሁለት ቀናት በፊት ነው" አለው።

"ሮበርት በረሸሙ ተነፈሰ። ስሙስ?"

"አባ ሮቤርቶ ፓትሪኒ።"

"አድራሻው?"

እንደገና ወረቀቱን ተመለከተና "መኖሪያው ኦሪቬቶ ነው። የኔን ተጨማሪ....." ቀና ብሎ ተመለከተ። ሮበርት ሄዷል።

ምዕራፍ ሃያ አምስት

ሰባተኛ ቀን

ኦሪቬቶ ኢጣሊያ

ቢስክ የመኪና ማቆሚያ መስመር ኤስ 74 ላይ መኪናዋን አቆማት። ከሸለቆው ባሻገር እሳተ ገሞራ በፈጠረው ዓለት ውበት ትንፋሽ የምታሳጥረው ማራኪ ከተማ ተቀምጣለች። ከተማዋ በዓለም ዝነኛ የሆነ ካቴድራል፤ ግማሽ ደርዘን የሚሆኑ አበብያተ ክርስቲያናትና መሬት ላይ የተከሰከሰ ያልታወቀ በራሪ ዲስክ የተመለከተ ምስክር ቄስ በውስጧ ይዛለች።

በጥርብ ድንጋይ የተሠሩ መንገዶች፣ ማራኪ ጥንታዊ ሕንፃዎችና ገበሬዎች ከየአቅጣጫው መጥተው ትኩስ ፍራፍሬያቸውንና ዶሮዎቻቸውን የሚሸጡባት ከፍት የገበያ ሥፍራ የያዘች ጊዜ ያልዳሰሳት ከተማ ናት። ሮበርት ከካቴድራሉ ባሻገር በፒአዛ ዴል ዱም ማቆሚያ ሥፍራ በማግኘቱ መኪናውን እዚያ አቆመና ወደ ካቴድራሉ ገባ። ግዙፉ የምእመናን መቀመጫ አዳራሽ ቅድስቱን ለቀው ከሚወጡ አንድ ቄስ በስተቀር ፀጥ እረጭ ብሏል።

@BOOKALEM

"ይቅርታ አድርጉልኝ አባቴ!" አለ ሮበርት። "ባለፈው ሳምንት ውስጥ ስዊዘርላንድ የነበሩና የዚህ ከተማ ነዋሪ የሆኑ አንድ ቄስ በመፈለግ ላይ ነበርኩ። ምናልባት እርስ....."

"ካሕኑ ፊታቸው ላይ ጥላቻ እየተነበበ ወደ ጓላቸው ራመድ አሉና....."ይህንን ጉዳይ ለመወያየት አልችልም" አሉት።

ሮበርት በመገረም እየተመለከታቸው....."አልገባኝም" አላቸው። "እኔ ለማግኘት የምፈልገው....." ንግግሩን አቋረጡትና....."እርሳቸው የዚህ ደብር ባልደረባ አይደሉም። ከቅዱስ ጀኡቨናሌ ቤተ ክርስቲያን ናቸው።" ቄሱ ይህን ተናግረው እየተጣደፉ ሮበርትን አልፈውት ሄዱ። 'ለምንድነው ጥላቻ ያሳዩት?'

የቅዱስ ጂኡቨናሌ ቤተ ክርስቲያን በሕብረ ቀለማት ያሸበረቁ መካከለኛ ከፍታ ያላቸው ሰገነቶችና ቤተ ክርስቲያናት ባሏት ኮዋርቲሮ ቢቺኦ በተበለች መንደር ይገኛል። ሮበርት የአትክልት ሥፍራ በመኮትኮት ላይ የነበረን አንድ ወጣት ቄስ ሲጠጋው ቀና ብሎ ተመለከተው።

"ቦን ጆርኖ ሲኞር።"

"እንደምን አደሩ። ባለፈው ሳምንት ስዊዘርላንድ ውስጥ የነበሩ ቄስ እፈልግ ነበር። አሳቸው....."

"አዎን! አዎን! ምስኪን አባት ፓትሪኒ። በጣም አሰቃቂ ነገር ነው የደረሰባቸው።"

አልገባኝም። የምን አሰቃቂ ነገር ነው የደረሰባቸው?

"የሰይጣኑን ጋሪ በማየታቸው! ሊቋቋሙት ከሚችሉት በላይ ነው የሆነባቸው። ሕሊናቸውን ስተዋል።"

"ይህንን በመስማቴ አዝናለሁ" አለ ሮበርት። "እሁን የት ነው የሚገኙት? ላነጋግራቸው እወዳለሁ።"

"ፒአዛ ዲ ሳን ፓትሪዚኒ አጠገብ በሚገኘው ሆስፒታል ውስጥ ናቸው። ግን ዶክተሮቹ ማንም ሰው ቢያነጋግራቸው የሚፈቅዱ አይመስለኝም።"

ሮበርት ተቸግሮ ቆመ። ከአዕምሮ ውጭ የመሆን ችግር ያለበት ሰው የሚሰጠው መረጃ ብዙም እርባና የለውም። "ገባኝ በጣም አመሰግናለሁ።"

በጣም ትንሽና የተሟላ የማይመስል ከተማዋ ዳርቻ ላይ የሚገኝ ባለአንድ ፎቅ ሆስፒታል ነበር። መኪናውን አቆመና አነስተኛ የሆነው እንግዳ መቀበያና ማረፊያ አዳራሽ ውስጥ ገባ።

"እንደምን አድረሻል? አባ ፓትሪኒን ለማየት እፈልጋለሁ ።"

"ይህ የማይቻል ነው። ከማንም ሰው ጋር ለመነጋገር አይችሉም።"

ሮበርት ካሁን በኋላ በማንም ላለመቆም ወስኗል። ፕሮፌሰር ስቺሚዲት ያስጨበጠውን ፍንጭ መከተል አለበት። "አልገባኝም" አለ ሮበርት ድምፁን ለስለስ

@BOOKALEM

አድርን። "አባ ፓትሪኒ ራሳቸው ናቸው እኔን ለማየት የጠየቁት። ወደ ኦሪቪቶ የመጣሁት በእርሳቸው ጥያቄ መሠረት ነው።"

"እርሳቸው አንተን ለማየት ጠየቁ?"

"እንዴታ! አሜሪካ ደብዳቤ ጻፉልኝ። እኔም ይህን ሁሉ መንገድ በርሬ ላያቸው መጣሁ።"

ነርሷ ወላወለች። "ምን ለመናገር እንደምችል አላውቅም። በጣም ነው የታመሙት። ሞልቶ!"

"እርግጠኛ ነኝ እኔን ማየቱ ያስደስታቸዋል።"

"ዶክተሩ እዚህ የለም....." ውሳኔ ወሰነች። "በጣም ጥሩ ወደ ክፍሉ ትገባለህ ሲኞር! ቢሆንም የምትቆየው በጣም ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ይሆናል።"

"እሱን ያህል ብቻ ነው የምፈልገው።"

"ፔር ፔኬሪ! በዚህ በኩል።"

ነርሷ ግራ ቀኙ ንፁህ ክፍሎችን በያዘ አጭር ኮሪደር ውስጥ ሮበርትን እየመራች አንድ ክፍል ውስጥ አስገባችው።

"ሲኞር ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ!"

"ግራዜ።"

ሮበርት ትንሿ ክፍል ውስጥ ገባ። አልጋው ውስጥ የተኛው ሰው ነጭ አንሶላ ላይ የተጋደመ የገረጣ ጥላ ይመስል ነበር። ሮበርት ጠጋ አለውና "አባቴ" አለ።

ቁሱ ዘወር ብለው አዩት። ሮበርት በሰው ልጅ ዐይኖች ውስጥ ይህን የመሰለ ሕመም ከቶም ቢሆን ዐይቶ አያውቅም።

"አባቴ ስሜ....."

ሮበርትን ግጥም አድርገው ያዙት። "ዕርዳታ ልታደርግልኝ ይገባሃል። እምነቴ ጠፍቷል። ሕይወቴን በሙሉ እግዚአበርሔርን ቅዱስ መንፈስን ሳመልክ ኖሬ እነሆ አሁን በመጨረሻ እግዚአብሔር አለመኖሩን ተገነዘብኩ። ያለ ነገር ቢኖር ሰይጣን ብቻ ነው። እሱም መጣብን.....!"

"አባ እርስዎ....."

"በዐይኔ ነው ያየሁት። ሁለቱም በሰይጣን ጋሪ ውስጥ ነበሩ። አህ! ሌሎችም በብዛት የኖራሉ። ሌሎችም ይመጣሉ! ሰንበትና ታያለህ!"

"ሁላችንም ገሃነመ_እሳት ውስጥ ሰጥመናል።"

"አባቴ አዳምጡኝ። የተመለከቱት የሰይጣን ጋሪ ወይም ሰረገላ አልነበረም። የጠፈር መንኮራኩር....."

ካህኑ የሮበርትን እጅ ለቀቁና ተመለከቱት። ግልጽ ሆኖ ታያቸው። "ማነህ አንተ? ምንድነው የምትፈልገው?"

"እዚህ የመጣሁት ስዊዘርላንድ ውስጥ በአውቶቡስ ስላደረጉት ጉዞ ልጠይቅልዎት ነው።"

@BOOKALEM

"አውቶቡሱ! አጠገቡ ባልደረስኩ እወድ ነበር።" ቄሱ እንደገና ስላገረሸባቸው ሮበርት ሊጫናቸው ባይወድም ሌላ ምርጫ አልነበረውም።

"እዚያ አውቶቡስ ላይ ከአንድ ቴክሳስ አጠገብ ተቀምጠው ነበር። ከእርሱም ጋር ረዘም ያለ ንግግር አድርገው ነበር። ያስታውሳሉ?"

"ጭውውት? ቴክሳኑ? አዎን አስታውሳለሁ።"

"ቴክሳስ ውስጥ የት ቦታ እንደሚኖር ነግሮዎት ይሆን?"

"አዎን አስታውሳለሁ። ከአሜሪካ ነበር የመጣው።"

"ቤቱ የት እንደሆነ ነግሮዎታል?"

"አዎን ነግሮኛል።"

"የት ነው አባቴ? ቤቱ የት ነው?

"ቴክሳስ። ስለቴክሳስ ነው ያወራው።"

ሮበርት በማበረታታት ዐይነት አንጉቱን ነቀነቀ። "ትክክል ነዎት።"

"በዐይኖቼ ነው ያየኋቸው። እግዚአብሔር አሳውሮኝ ቢሆን እወድ ነበር። እኔ....."

"አባ! የቴክሳሱ ሰውዬ ከየት እንደሆነ ነግሮዎታል? ስም ጠቅሷል?

አዎን ቴክሳስ ፓንዴሮሳ።

ሮበርት እንደገና ሞከረ። "ያ በቴሌቪዥን ነው። አጠገብዎ ተቀምጦ የነበረው ግን በእውን ያለ ሰው....."

ካህኑ እንደገና አዕምሮአቸው ተናወጠ። "መጡብኝ! የፍፃሜው ጦርነት ተጀመረ! መጽሐፍ ቅዱስ ይዋሻል! ምድርን የሚወርሰው ሰይጣን ነው! አሁን በከፍተኛ ድምጽ እያጓሩ ይጮሃሉ። "ተመልከት! ተመልከት! እያቸዋለሁ!"

ነርሷ እየተጣደፈች ገባችና በማንኳስስ ተመለከተችው። "ሲኞር አሁን መውጣት አለብህ!" አለችው።

"አንድ ተጨማሪ ደቂቃ ብቻ ነው የምንፈልገው....."

"አይሆንም ሲኞር። አዲኦ!"

ሮበርት ለመጨረሻ ጊዜ የሚለፈልፉትን ቄስ ተመለከታቸውና ለመውጣት ፊቱን አዞረ። ከዚህ ወዲህ የሚያደርገው ነገር የለም። ቄሱ ወደ ቴክሳስ እንዲጠቁሙት ቆምሮ ተሸንፏል።

ሮበርት መኪናውን አስነሳና ወደ ሮም ጉዞውን አቀና። በመጨረሻም ተፈጸመ። ብቸኛዎቹ ፍንጮች ምናልባት ፍንጭ ተብለው ከተጠሩ የተጠቀሱት ሩሲያዊት ሴት፤ ቴክሳኑና የሁንጋሪያው ተወላጅ ናቸው። ከዚህ በላይ እነሱን ለማሳደድ ምንም መንገድ የለም። ቼከና ቼክ ሜት (መንቀሳቀሻ መንገድ አልቦ)። ይህን ያህል ርቀት መጥቶ ከዚህ በላይ ለመሄድ አልቻለም። የሚያስጨንቅ ጉዳይ ነው። ቄሱ የሚፈልገውን መረጃ እስኪሰጡት ድረስ ሕሊናቸውን ገዝተው ለአድማጭ የሚገባ ነገር መናገር ችለው ቢሆን ኖሮ? ደግሞም ተቃርቦ ነበር!

@BOOKALEM

ምንድን ነበር ቁሱ ያሉት! ፓንዴሮሳ። ሽማግሌው ካህን ቴሌቪዥን በብዛት ተመልከተው ነበር። እናም በቅዠታቸው የቴክሳሱን ተወላጅ በአንድ ወቅት ተወዳጅ ከነበረው "ቦናንዛ" ከተባለው የቴሌቪዥን ፊልም ጋር አመሳስለውታል። ፓንዴሮሳ ዝነኛው የካርትራይት ቤተሰብ የኖረበት ሥፍራ ነው። 'ፓንዴሮሳ!' ሮበርት መኪናውን ዝ.....ግ አደረጋትና ወደ መንገዱ ጠርዝ ወሰዳት። አዕምሮው እየበረረ ነው። ሀ ቅርጽ ሠርቶ መኪናውን አዞራትና ወደ አሪሼቶ ተመልሶ ከነፈ።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ከአንድ አነስተኛ ቡና ቤት አስተናጋጅ ጋር እየተነጋገረ ነበር።

"በጣም ቆንጆና ሰላማዊ ከተማ ነው ያላችሁ።"

"አ! ሲ ሲዎሬ። በዚህች ከተማችን በጣም የምንረካ ሰዎች ነን። ከዚህ በፊት ኢጣሊያን ጎበኙተው ያውቃሉ?"

"ግማሹን የጫጉላ ሽርሽሬን ያሳለፍኩት ሮም ውስጥ ነው።" 'ሕልሜን እውን አረከልኝ ሮበርት። ሕጻን ልጃገረድ ከነበርኩበት ጊዜ ጀምሮ ሮምን ለመጎብኘት በጣም እመኝ ነበር።'»

"አህ! ሮም በጣም ትልቅና ጫጫታ የበዛባት ናት" አለ አስተናጋጁ።

"እስማማለሁ።"

"እዚህ በጣም ቀላል የሆነ ግን ደስተኛ ሕይወት ነው የምንኖረው።"

ሮበርት በጥንቃቄ እንዲህ አለው። "እዚህ ከተማ ውስጥ በአብዛኛዎቹ ቤቶች ጣሪያ ላይ የቴሌቪዥን አንቴና ለማየት ችያለሁ።"

"አዎን። በዚያ መስክ በጣም ዘመናዊ ነን።"

"ማንም ሰው ሊረዳው ይችላል። የከተማው ቴሌቪዥን ሰንት ዐይነት ጣቢያዎችን ይቀበላል?"

"አንድ ብቻ።"

"ብዙና በጣም ጥሩ የሆኑ የአሜሪካ ትዕይንቶች ይቀርብላችኋል ብዬ እገምታለሁ።"

"የለም የለም። ይህ የኛ መንግሥታዊ ጣቢያ ነው። እዚህ በኢጣሊያ ውስጥ የተሠሩ ትዕይንቶችን ብቻ ነው የምንቀበለው።"

'ቢንጎ' አለ ሮበርት ለራሱ። ድምጹን ዘለግ አድርጎ "አመሰግናለሁ" ብሎት ወጣ።

ሮበርት ለአድሚራል ዊታከር ጥሪ አደገረለት። ጸሓፊዋ ስልኩን አንስታ "የአድሚራል ዊታከር ጽሕፈት ቤት" አለች።

ሮበርት የቢሮው ሁኔታ ይታየዋል። 'መንግሥት ላልታወቁና አልባሌ ለሆኑ ብዙም ጥቅም ለማይለግሱት ሰዎች የሚሰጠው ዐይነት ቢሮ መሆን አለበት።'

"ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ነኝ። ለደቂቃ ላናግራቸው?"

@BOOKALEM

“ትንሽ ይጠብቁ ኮማንደር ቤላሚ!”

‘በአንድ ወቅት ኃያል የነበረውን አድሚራል ዛሬ ሰዎች ይፈልጉት ይሆን?’ ሲል ሮበርት ተደነቀ።

“ሮበርት” ድምጽህን በመስማቴ ተደስቻለሁ። ለመሆኑ የት ነው ያለህው? የሸማግሌው ድምጽ የመድከም ቅላጼ ይደመጥበታል።

“ለመናገር አልችልም ጌታዬ!”

ጥቂት ፀጥታ ሆነ። “ይገባኛል! ላደርግልህ የምችለው ነገር አለ?”

“አዎን ጌታዬ። ይህ መቼም አልባሌ ነገር ነው። ከማንም ሰው ጋር ግንኙነት እንዳላደርግ ታዝዣለሁ። ቢሆንም አንድ የውጭ ዕርዳታ ያስፈልገኛል። መቼም ለኔ አንድ ጉዳይ ቢያጣሩልኝ በጣም በወደድኩ።”

“በእርግጥ መሞከር እችላለሁ።”

“ቴክሳስ ውስጥ ፓንዴሮሳ የሚባል የከብት ዕርባታ ሥፍራ መኖር አለመኖሩን ለማወቅ እፈልግ ነበር።”

“ልክ ቦናንዛ ላይ እንዳለው?”

“አዎን ጌታዬ።”

“ማረጋገጥ እችላለሁ። እንዴት ነው የማገኝህ?”

“እኔው ራሴ መልሼ ብደውልልዎት የተሻለ ይመስለኛል አድሚራል።”

“ትክክል። አንድ ወይም ሁለት ሰዓት ስጠኝ። ይህንንም ጉዳይ በሁለታችን መካል አስቀረዋለሁ።”

“አመሰግናለሁ።”

ሮበርት ሽማግሌው ድካሙ ሁሉ የለቀቀው መሰለው። በመጨረሻ ምንም እንኳ የከብት ማርቢያን የመሰለ አልባሌ ነገር ቢሆንም አንድ ነገር እንዲያደርግ ተጠይቋል።

ከሁለት ሰዓት በኋላ ለአድሚራል ዊታከር ጥሪ አደረገ።

“የሰልክ ጥሪህን በመጠባበቅ ላይ ነበርኩ” አለ አድሚራሉ። ድምጹ የረካ ይመስላል። “የምትፈልገውን መረጃ አግኝቼልሃለሁ።”

“እናነ” አለና ሮበርት ትንፋሹን ያዘ።

“ፓንዴሮሳ የሚባል የከብት ዕርባታ ሥፍራ ቴክሳስ ውስጥ አለ። እሱም ዋኮ ከተባለው ከተማ ውጭ ነው የሚገኘው። የባለንብረቱ ስም ዳን ዋይን ይባላል።”

ሮበርት በእፎይታ ትንፋሹን ለቀቀው። “በጣም አመሰግናለሁ አድሚራል! ስመለስ ብድሩን እራት እጋብዝዎታለሁ።”

“እኔም እጠብቃለሁ ሮበርት።” የሚቀጥለው የሮበርት ጥሪ ለጄነራል ሒሊያርድ ነበር።

“ኢጣሊያ ውስጥ አባ ፓትሪኒ የሚባሉ ምስክር አግኝቻለሁ።”

“ቄስ?”

@BOOKALEM

"አዎን። በጣም ታመው ኦሪቬቶ ሆስፒታል ተኝተዋል። የኢጣሊያ ባለሥልጣናት ሊያናግሯቸው አይችሉም ብዬ እሰጋለሁ።"

"ይህንኑ አስተላልፋለሁ። አመሰግናለሁ ኮማንደር።"

ከሁለት ደቂቃዎች በኋላ ጄነራል ሒሊያድ ከጃኑስ ጋር መስመር ላይ ነበር። "ከኮማንደር ቤላሚ እንደገና ሰምቻለሁ። በቅርብ የተገኘው ምስክር ቄስ ነው። አባ ፓትሪኒ ኦሪቬቶ ውስጥ።"

"ጥንቃቄውን ውሰድ።"

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
የብሔራዊ ጸጥታ ወኪል–ለኢጣሊያ መረጃ ድርጅት (ሲፋር)
ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
-5- አባ ፓትሪኒ–ኦሪቬቶ
የመልዕክት መጨረሻ

"ሲፋር" የሚባለው የኢጣሊያ መረጃ ድርጅት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት በሮም ከተማ ደቡባዊ ዳርቻ ላይ በዴላ ቬኒቶ ጎዳና ላይ ዙሪያውን በእርሻ ቤቶች ተከቦ ይታያል። ኢንዱስትሪ የሚመስለውን ሕንጻ አንዳንድ አልፎ ሂያጅ ለሁለተኛ ጊዜ ዞር ብሎ እንዲያየው የሚያደርገው ነገር ቢኖር በያንዳንዱ ጠርዝ ላይ የተዋቀሩት የዘቦች መቆሚያ ማማዎች ብቻ ናቸው።

በወታደራዊ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኘው "ሲፋር" በሚል አጽህሮት የሚጠራው ድርጅት በመላው ዓለም እጅግ በጣም ምሥጢራዊ ከሆኑት የስለላ ድርጅቶች አንዱና በጣም በጥቂቱ የሚታወቀው ነው። ከቅጥር ግቢው ውጭ "ቤታር ፓሳሪ ቦስትሪ ኢ. ሊሚቲ" የሚል ጽሑፍ ተሰቅሎባታል። አንደኛው ፎቅ ላይ በሚገኘው የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ኮሎኔል ፍራንሲስኮ ቄሳር በቅርቡ የተቀበለውን አስቸኳይ መልዕክት በማጥናት ላይ ነበር። ኮሎኔሉ ግንባሩ ላይ ስርጉድ ያለው ጠንካራና ከሃምሳ ዓመት በላይ የሆነው ሰው ነው። መልዕክቱን ለሦስተኛ ጊዜ አነበበው።

'እነሆ የዱምዝዴይ (የፍርድ ቀን) ዘመቻ ተጀመረ ማለት ነው። ለዚህም አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገን መቆየታችን በጣም ግሩም ነው!' መልዕክቱን እንደገና ተመለከተው።

"አንድ ቄስ!"

@BOOKALEM

የአሪቬቶን አነሰተኛ ሆስፒታል ተረኛ ነርሶች መጠባበቂያ ዴስክ አንዲት መነኩሴ አልፋው ስትሄድ ከእኩለ ሌሊት ጥቂት አለፍ ብሎ ነበር።

"ሲኞራ ፊሊፒንን ለማየት ነው የምትሄደው ብዬ እገምታለሁ" አለች ነርስ ቶማሲኖ።

"እርሷን ወይም ሽማግሌው ፈጋሮን ይሆናል!" አለች ሌላዋ ነርስ። ሁለቱም በመጨረሻው የሥራ ሰዓታቸው ላይ ነበሩ፡

መነኩሲቷ ዙሪያውን በቀስታ ተመለከተችና በቀጥታ ቄሱ የተኙበት ክፍል ውስጥ ገባች። ቄሱ ልክ ጸሎት ያደርጉ ይመስል እጆቻቸውን ደረታቸው ላይ አነባብረው በሰላም በአማን ለጥ ብለው ተኝተዋል። የጨረቃዋ ብርሃን በቀጭኑ በተከፈተው መጋረጃ ውስጥ አልፋ ፊታቸው ላይ በማረፍ ወርቃማ ነጸብራቋን ጥላባቸዋለች።

መነኩሲቷ አንዲት ትንሽ ሳጥን ከረጅሙ ልብሷ ውስጥ አወጣችና በጥንቃቄ ከብርጭቆ የተሠራ የመጸለያ መቁጠሪያ አውጥታ በቄሱ እጆች ላይ አኖረችው። አንዱን የመቁጠሪያ ኳስ አውራ ጣታቸው ላይ ልክ በመቁጠር ላይ የነበሩ አስመስላ አስነካችው። ወዲያውኑ ከአውራ ጣታቸው ላይ ቀጭን የደም መስመር ወጣ። መነኩሲቷ ቀጥላ ከሳጥኑ ውስጥ አንድ ፈሳሽ የያዘ ትንሽ ብልቃጥ አወጣችና በዐይን ውስጥ ጠብታ በሚጨመርበት ዕቃ በመጠቀም ሦስት ጠብታዎች የተቆረጠው ጣታቸው ላይ ጨመረችበት።

አደገኛው ገዳይ መርዝ በደማቸው ውስጥ እስኪሰራጭ ድረስ በጣም ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነው የፈጀበት። ከዚያም መነኩሲቷ ሽማግሌው ቄስ አስከሬን ላይ አማተበችና ልክ እንደአመጣጧ ሳትታይ ሹልክ ብላ ወጣች።

አስቸኳይ መልክት
እጅግ በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ሲፋር–ለ ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል
ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
-5- አባ ፓትሮኒ ተወግደዋል
የመልዕክት መጨረሻ

@BOOKAlEM

ምዕራፍ ሃያ ሲድስት

ፍራንክ ጆንሰን የተመለመለው ቬትናም ውስጥ ዘምቶ የነበረ የግሪን ቤሬት ወታደር በመሆኑ ነው። በጓደኞቹ ዘንድ "ገዳይ ማሺን" በመባል ይታወቃል። መግደል በጣም ያፈቅር ነበር። ከዚህም በላይ ለሚያደርገው ንቅናቄ ምክንያታዊ የሆነና በጣም ብሩህ አዕምሮ ያለው ሰው ነው። "ለኛ ፍጹም ተስማሚያችን የሆነ ሰው ነው። በጥንቃቄ አቅርበው። ላጣው አልፈልግም" አለ ጃኑስ።

"ስለመንግሥታችንስ አትጨነቅም?" አለ ሻለቃው። "ልባቸው በሚደማና መጋዘናችንን በሚያራቁቱ ሰዎች የሚመራ መንግሥት ነው። ይህች አገር የኒውክሊየር ኃይል ያስፈልጋታል። ግን እነዚያ የተረገሙ የፖለቲካ ሰዎች ሌሎች ጣቢያዎችን ከመገንባት አስቁመውናል። ነዳጅ ዘይት የምንጠብቀው ከነዚያ የተረገሙ ዐረቦች ነው። ግን የኛ መንግሥት የራሳችንን ዘይት ከባሕር ውስጥ ቆፍረን እንድናወጣ ያደርገናል? የለም አይፈቅዱልንም። ከኛ የበለጠ ለባሕር ዓሣ ነው የሚጨነቁት። ይህ ላንተ ስሜት እየሰጠህ ነው?"

"ነጥብህ ይታየኛል" አለ ፍራንክ ጆንሰን።

"እንደሚገባህ አውቃለሁ። ምክንያቱም አንተ ብሩህ ሰው ነህና።" በሚናገርበት ጊዜ የፍራንክ ጆንሰንን ገፅታ እያጠና ነበር። "ምክር ቤቱ አገራችንን ለማዳን አንድ ነገር ለማድረግ ካልፈለገ አንድ ነገር ማድረጉ የጥቂቶቻችን ጉዳይ ይሆናል ማለት ነው።"

ፍራንክ ጆንሰን ግራ የተጋባ መሰለ። "የጥቂቶቻችን?" ሲል ጠየቀ።

"አዎን። ላሁኑ ይበቃናል" አለ ሻለቃው። "ሌላ ጊዜ እንነጋገርበታለን።"

ቀጣዩ ውይይት ደግሞ የበለጠ ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ነበር። "ዓለማችንን ለመከላከልና ለማዳን የፈቀዱ የአርበኞች ቡድን አለ ፍራንክ። ከፍተኛ የሆነ ሥልጣንና ኃይል ያላቸው የተከበሩ ሰዎች ናቸው። እነርሱም አንድ ኮሜቴ መሥርተዋል። ኮሚቴው ዓላማውን ለማራመድ እንዲችል አንዳንድ ሕጎችን ማጣመም ወይም መጣስ አለበት። በመጨረሻም ተገቢ የሆነ ውጤት ያስገኝለታል። አንተስ አባል የመሆን ፍላጎት አለህ?"

ፍራንክ ጆንሰን ፈገግ አለ። "አዎን በጣም እፈልጋለሁ ።"

ይህ ጅማሬው ነበር። የሚቀጥለው ስብሰባ የተካሄደው አታዋ ካናዳ ውስጥ ነው። በዚም ስብሰባ ፍራንክ ጆንሰን አንዳንድ የኮሜቴውን አባላት ለመገናኘት ቻለ።

በደርዘን የሚቆጠሩ አገሮችን ፍላጎት የሚወክሉ ሰዎች ነበሩበት። "በደምብና በሚገባ የተደራጀን ነን" ሲል አንድ አባል አብራራለት። "በጣም ጥብቅ

@BOOKALEM

የሆነ የእዝ ሰንሰለት አለን። የፕሮፓጋንዳ ክፍል፤ የምልመላና ታክቲክ፤ ምሥጢራዊ የሆነ የግንኙነት ክፍልና.....የጎዳይ ጓድ አለበት። ከሞላ ጎደል የመላው ዓለም የሰለላ ድርጅቶች የዚህ ኮሜቴ አካል ሆነዋል።"

"ማለት የመንግሥታት መሪዎችም?"

"የለም። ርዕሰ ብሔሮች የሉበትም። እጆቻቸው ወደ ሕዝብ ጠልቀው መግባት የቻሉ፤ ምን በመደረግ ላይ እንዳለ የተገነዘቡ፤ አገራችን ምን ዐይነት አደጋ ውስጥ እንዳለች የሚያውቁ ሰዎች ናቸው ያሉበት።"

ሰብሰባው የሚካሄደው በመላው ዓለም ነው። ስዊዘርላንድ፤ ሞሮኮ፤ ቻይና.....እና ፍራንክ ጆንሰንም ሁሉንም ሰብሰባዎች ተሳተፈ።

ከሲድስት ወራት በኋላ ነበር ኮሎኔል ጆንሰን ጃኑስን ለመገናኘት የቢቃው።

"ስላንተ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ ሪፖርት ደርሶኛል ኮሎኔል።"

ፍራንክ ጆንሰን ፈገግ አለና....."ሥራዬን በጣም ነው ምወደው" አለ።

"እኔም ሥራህን እንደምታፈቅር ሰመቻለሁ። እኛን ልትረዳ የምትችልበት ጠቀሜታዊ አቅጣጫ አግኝተሃል?"

ፍራንክ ጆንሰን ቀጥ ብሎ ተቀመጠና....."ማድረግ የምችለውን ማንኛውንም ነገር አደርጋለሁ!" አለ።

"ጥሩ! ጥሩ! በማሠልጠኛ ሥፍራ ከተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች የመጡ ሰላዮችን የሥልጠና ሒደት እንድታጠና ኃላፊነት ተሰጥቶህ ነበር።"

"ትክክል ነው ጌታዬ።"

"እናስ ችሎታቸውንና ራሳቸውንም በደንብ ለማወቅ ችለሃል?"

"በሚገባ።"

"አሁን አንተ እንድታደርግ የምፈልገው ለኛድርጅት በጣም ይጠቅማሉ ወይም ይረዳሉ የምትላቸውን ሰዎች እንድትመለምልልን ነው። በጣም ምርጥ የሆኑትን ብቻ ነው የምንፈልገው።"

"እሱ በጣም ቀላል ነው" አለ ኮሎኔሉ። "ምንም ችግር የለም።" ጥቂት አመነታና እንድ....."

"ምን?"

"እሱኛውን ሥራ በግራ እጄ ላከናወነው እችላለሁ። በእውነት አንድ ተጨማሪ ነገር ከፍ ያለ ሥራ ለመሥራት እፈልጋለሁ ። ወደ ፊት ቀረብ አለና.....ስለ "ፍርድ ቀን ዘመቻ" ሰምቻለሁ። የፍርድ ቀን ዘመቻ አጠገቤ ያለ ኮሪዶር ነው። የሱም አካል ለመሆን እሻለሁ።

ጃኑስ ለተወሰኑ ደቂቃዎች እያጠናው ቁጭ አለ። ከዚያም ራሱን ነቀነቀና "ደህና! አለህበት!" አለው።

ጆንሰን ፈገግ አለ። "አመሰግናለሁ አያዝኑብትም!"

@BOOKALEM

ኮሎኔል ጆንሰን በጣም ተደስቶ የሰብሰባውን ሥፍራ ጥሎ ወጣ። ምን እንደሚሠራ የሚያሳይበት ዕድል አግኝቷልና።

ስምንተኛ ቀን ዋኮ ቴክሳስ

ለዳን ዋይን ቀኑ መጥፎ ነበር የሆነበት። ከዋኮ አውራጃ ፍርድ ቤት ችሎት ውሎ ገና መመለሱ ነበር። ከወጣት ጎኪሚ ጋር የማገጠችው ሚስቱ ካለው ንብረቱ ግማሹን ተረክባ ልትፈታው ነው።

ዳን ዋይን ዕጣ ፈንታ መቀመጫው ላይ በካልቾ እንደመታችው ሆኖ ነው የሚሰማው። ይህን ሁሉ ለመቀበል የሚያስችለው ምንም ዐይነት ወንጀል አልሠራም። ጥሩ ባልና ጥሩ ከብት አርቢ ሆኖ ነው የኖረው።

ጥናት ክፍሉ ውስጥ ቁጭ ብሎ በጨለማ የተዋጠውን የወደፊት ዕድሉን ማንሰላሰል ቀጠለ። ዳን ዋይን ኩሩ ሰው ነበር። ዳን ዋይን በቴክሳኖች ላይ አንዳንድ ጉረኞች ስለሚሰነዝሩት ጉራ የተመላበት ቀልድ ጠንቅቆ ያውቃል። እሱም አንድ ጉራ የሚነዛበት ነገር እንዳለው ይሰማዋል። ዋኮ ውስጥ በአርሻ ከበለፀገው የብራዞስ ወንዝ ሸለቆ አካባቢ ነው የተወለደው። ዋኮ ዘመናዊ የሆነች አገር ብትሆንም በአምስት "ሲ" የተደገፈች የጥንቱን መዓዛ ያለቀቀች አውራጃ ናት። ከብት፤ ጥጥ፤ በቆሎ፤ የኮሌጅ ተማሪዎችና ባሕል። ዳን ዋይን ዋኮን ባለው ሕይወትና ልብ ሁሉ ከመውደዱም በላይ ካሕኑን በስዊስ የጎብኝዎች አውቶቡስ ላይ በተገናኘንበት ወቅት ስለከተማው አምስት ሰዓት ሙሉ በዝርዝር አጫውታቸዋል። ቄሱ የእንግሊዘኛ ቋንቋቸውን ለማሻሻል እንደሚፈልጉ ነግረውት ነበር። ግን ወደ ኋላ እያጠነጠነ ሲያስበው አብዛኛውን ንግግር ያደረገው እርሱ ነበር።

"ዋኮ ሁሉም ነገር አላት" ሲል ለቄሱ አረጋገጠላቸው። "የአየራችን ፀባይ በጣም ጥሩ ነው። ከዚህ የተነሳ እንዲቀዘቅዝ ወይም እንዲሞቅ አንሻም። በትምሕርት በኩል ወረዳው አካባቢ ሃያ ሦስት ትምሕርት ቤቶችና ባይሉር የተባለ ዩኒቨርስቲ አለን። ሦስት ጋዜጦች፤ አሥር የራዲዮና አምስት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች አሉን። ዝነኛ የሆነ የቴክሳስ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ መሥሪያ ቤት አለን። አባቴ! ዓሣ ማስገር የሚወዱ ከሆነ የብራዞስ ወንዝ የማይረሳ ተሞክሮ የሚያገኙበት ነው። እናም የዱር አራዊት ማደኛና ትልቅ የኪነ ጥበብ ማዕከልም አለን። ልንገርዎት! ዋኮ በዓለም ላይ ልዩ ከሆኑት ከተሞች አንዷ ናት። መጥተው ሊጎበኙን ይገባል።"

ኮስማናው ቄስ ፈገግ ብለው ራሳቸውን ነቀነቁ። ዳን ዋይንም 'ምን ያህል እንግሊዘኛ ገብቷቸው ይሆን?' ሲል ተገረመ።

ዳን ዋይን አባቱ አንድ ሺህ ኤከር የከብት እርሻ ቦታ ትቶለት ሲያልፍ ልጁ ደግሞ የከብቶቹን ቁጥር ከሁለት ሺህ ወደ አሥር ሺህ ከፍ አደረጋቸው።

@BOOKALEM

እንደዚሁም አንድ ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣ የርቢ ፈረስም አለው። አሁን ደግሞ ዲቃላዎቹ (ጠላቶቹ) ይህን ሁሉ ንብረቱን ሊወስዱበት ከጀሉ። የከብት ገበያ ዋጋ ወደ ታች ቢወርድ የእርሱ ስህተት አይደለም። ባንኮቹ ደግሞ ለግድያ እየተጠጉት በመምጣት ላይ ናቸው። ራሱን ለማዳን ያለው ዕድል የከብት ዕርባታ ርስቱን ሊገዛ የሚችልና ዕዳውን ከፍሎ እሱን ከመጠነኛ ትርፍ ጋር የሚተወው ሰው ፈልጎ ማግኘት ነው።

ዋይን የከብት እርባታ ሥፍራ ቴክሳስ ውስጥ የሚፈልግ ከበርቴ የስዊስ ዜጋ እንዳለ በመስማቱ ከሰውየው ጋር ለመገናኘት ወደ ዙሪክ በረረ። በመጨረሻም ጉዳዩ ቆቅ ማሳደድ ሆኖ አገኘው። የሰውየው ፍላጎት አንድ ወይም ሁለት ኤከር መሬት ግጦም ከሆነ የጓሮ አትክልት ጋር ብቻ ነበር!

ያ እጅግ በጣም አስደናቂ የሆነ ነገር ሲፈፀም በጉብኝዎቹ አውቶቡስ ላይ ሊገኝ የቻለው በዚህ ምክንያት ነው። ስለ በራሪ ዲስኮች አንብቧል። ግን በፍጹም አምኖ አያውቅም። አሁን ግን በእርግጥ ሊያምን ቻለ። ወደ መኖሪያ ከተማው እንደተመለሰ ወዲያውኑ የመኖሪያ ከተማውን ጋዜጣ ዋና አሳታሚ በስልክ አነጋገረው።

"ጆኒ! አንድ ሃቀኛ በራሪ ዲስክ በውስጡ ሕይወታቸው ያለፈ አስቂኝ መሳይ ሰዎች እንደያዘ አየሁኝ።"

"ፎቶግራፍ አንስተህዋል ዳን?"

"የለም። ጥቂት አንስቼ ነበር። ነገር ግን አንዱም አልወጣም።"

"ግድ የለም። ፎቶግራፍ አንሺ እዚያው ድረስ እንልካለን። ለመሆኑ ያንተ እርባታ ሥፍራ ላይ ነው ያለው?"

"አይደለም። እንዳጋጣሚ ስዊዘርላንድ ውስጥ ነው።"

ፀጥታ ሰፈነ። "ደህና! ምናልባት ሌላ በራሪ ዲስክ ባንተ እርስት አካባቢ ካየህ ስልክ ደውልልን።"

"ቆይ የዚህን ነገር አንድ ሌላ ሰው ፎቶ ግራፍ ይልክልኛል።" ነገርግን ጆኒ ስልኩን ዘግቶታል።

ዳን ዋይን 'ምነው ከሌላ ዓለም የመጡ ፍጡራን ምድራችንን በወረሯት!' ሲል ተመኘ። ምናልባት አበዳሪዎቹን ይገድሉለት ይሆናል። መንገዱ ላይ የመኪና ድምጽ ሰማና ብድግ ብሎ ወደ መስኮቱ ተራመደ። 'ምናልባት ሌላ አበዳሪ? መቼም ዘንድሮ ከየሥርቻው ነው ብቅ ብቅ የሚሉት።' ዳንኤል ዋይን የፊት ለፊቱን በር ከፍተው።

"ዳንኤል ዋይን ነህ?"

"ባልንጀሮቼ ዳን እያሉ ይጠሩኛል። ምን ላድርግልህ?"

ሮበርት ዳን ዋይንን የገመተውን ዐይነት ሰው ሆኖ አላገኘውም። ግዙፍ የቴክሳስ ተወላጅ ነበር የጠበቀው። ዳንዋይን ግን መጠነኛና የመሳፍንት ዐይነት

@BOOKALEM

አቋም ያለው ሰው ነበር። ትውልዱን የሚያመለክትበት የቀረ ነገር ቢኖር የአነጋገር ዘዬው ብቻ ነው። "ካሉህ ጥቂት ደቂቃዎች ለመጋራት እችል ይሆን?"

"የቀረኝ ንብረት ቢኖር ጊዜ ብቻ ነው። በነገራችን ላይ አበዳሪ አይደለህም። ነህ?"

"አበዳሪ አይደለሁም።"

"ጥሩ ወደ ውስጥ ግባ።"

ሁለቱ ሰዎች ወደ ሳሎኑ ገቡ። በጣም ትልቅና በምዕራባዊያን ምቹ የቤት ዕቃ የተደራጀ ከፍል ነው።

"በጣም ድንቅ የሆነ ቦታ ነው ያለህ።"

"አዎን። የተወለድኩትም እዚሁ ቤት ውስጥ ነው። የሚጠጣ ነገር ላቅርብልህ? ምናልባት ለስላሳ መጠጥ?"

"የለም አመሰግናለሁ።"

"ተቀመጥ።"

ሮበርት አንድ ለስላሳ ምቹ የቆዳ ወንበር ላይ ተቀመጠ።

"ለምንድነው ልታየኝ የመጣህው?"

"ባለፈው ሳምንት ስዊዘርላንድ ውስጥ በቱሪስቶች አውቶቡስ ተጉዘህ ነበር ብዬ አምናለሁ።"

"ትክክል ነው። ለመሆኑ የቀድሞዋ ሚስቴ እያስለለችኝ ነው?" ለሷ አይደለም የምትሠራው ። ለሷ ነው?"

"አይደለም ጌታዬ።"

"አሃ!" በድንገት ትዝ አለው። "ፍላጎትህ ያለው በዚያ በራሪ ዲስክ ነገር ላይ ነው። ካየኋቸው ነገሮች ሁሉ የተረገመው! ቀለሙን ዝም ብሎ ይለዋወጥ ነበር። እናም እነዚያ ሙታን ፍጡራን በውስጡ ነበሩ።" ዳን ትዝታው አንገፈገፈው። "በሕልሜ ሁሉ ይመጡብኛል።"

"ሚስተር ዋይን! በአውቶቡሱ ላይ የነበሩት መንገደኞች እንማን እንደነበሩ ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"አዝናለሁ ልረዳህ አልችልም። የምጓዘው ብቻዬን ነበር። እውነቱን ለመናገር አዕምሮዬ በብዙ ነገሮች ተወጥሮ ስለነበረ ለአንዳቸውም ብዙም ትኩረት አልሰጠኋቸውም።"

"ስለአንዳንዶቹ እንኳ አንድ የምታስታውሰው ነገር አለ?"

"አንድ ኢጣሊያዊ ቄስ ነበሩ። በመጠኑም ቢሆን አነጋግሬአቸዋለሁ። ግሩም ሰው ይመስሉ ነበር። አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ ። ይህ በራሪ ዲስክ ነገር በመጠኑም ቢሆን አሸብሯቸው ነበር። ስለሰይጣን ብቻ ነበር የሚያወሩት።"

"ሌላስ ያነጋገርከው ሰው ነበር?"

@BOOKALEM

ዳን ዋይን ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገ። "ቆይ!...ቆይ! በመጠኑም ቢሆን ካናዳ ውስጥ የባንክ ቤት ባለጉበረት ከሆነ ሰው ጋር ተነጋግሬ ነበር" አለና ከንፈሩን በምላሱ አረጠበው። "እውነቱን ለመናገር እዚህ የእርባታ ቦታዬ ላይ መጠነኛ የገንዘብ ችግር ደርሶብኛል። ሁኔታው የሚያሳየው የከብት እርባታዬን እንደማጣው ነው። እነዚህን እግዚአብሔር የረገማቸው ባንከኞች በጣም ነው የምጠላቸው። ሁሉም ደም መጣጮች ናቸው። ቢሆንም ይህ ግለሰብ ከሌሎች የተለየ ሊሆን ይችላል ብዬ ገመትኩ። ባንከኛ መሆኑን እንደተረዳሁ የሆነ እዚህ የምጠቀምበት የገንዘብ ብድር ለማግኘት ያለውን መንገድ ሁሉ ሞከርኩ። ነገር ግን እሱም ልክ እንደተቀሩት ባንከኞች ዐይነት ነበር። ከሌሎቹ ያነሰ ስሜት አላሳየኝም።"

"የመጣው ከካናዳ ነው ያልከው?"

"አዎን። ከፎርት ስሚዝ። ከሰሜን–ምዕራብ ከልል። ልነግርህ የምችለው ይኸው ብቻ ነው ስል እሰጋለሁ።"

ሮበርት ደስታውን ለመደበቅ ተጣጣረ። "አመሰግናለሁ ሚስተር ዋይን። በጣም ነው የረዳህኝ" አለና ተነሳ።

"ይኸው ነው?"

"ይኸው ነው።"

"ለእራት መቆየት ትፈልጋለህ?"

"የለም አመሰግናለሁ። መሄድ አለብኝ። ስለርባታ እርሻህ መልካም ዕድል ይግጠምህ።"

"አመሰግናለሁ።"

<u>ፎርት ስሚዝ። ካናዳ ሰሜን–ምዕራብ ከልል።</u>

ሮበርት ጀነራል ሒሊያርድ በሰልኩ መስመር ላይ እስኪመጣለት ጠበቀ። "እቤት ኮማንደር?"

"ሌላ ምስክር አግኝቻለሁ። ዳን ዋይን የተባለ የፓንዴሮሳ ባለቤት። ከቴክሳስ ወጣ ያለ የከብት እርባታ ሥፍራ።

"በጣም ጥሩ። ቴክሳስ ያለው ቢሯችን እንዲያነጋግረው እደርጋለሁ።

አስቸኳይ መልዕክት

በጣም ከፍተኛ ምሥጢር

የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ለ–ዲ.ሲ.አይ ምክትል ዳይሬክተር

ዐይኖች ብቻ

ግልባጭ የለውም

አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ

-6- ዳንኤል ዋይን–ዋኮ

@BOOKALEM

ላንግሌይ ቨርጂኒያ የሲአይኤ ምክትል ዳይሬክተር መልዕክቱን በጥልቅ ተመለከቱት። ቁጥር -6- ነገሮች በግሩም ሁኔታ እየተከናወኑ ነው። ኮምፕሌር ቤላሚ እፀብ ድንቅ የሆነ ተግባር እያከናወነ ነው። እርሱን ለመምረጥ የተሳሳተው ውሳኔ በጣም ብልህነት ነበር። ጃኑስ ትክክለኛ ነበር። ሰውየው ሁልጊዜ ትክክል ነው። እናም ፍላጎቱን ሁሉ ለማሰፈፀም ኃይል አለው። ታላቅ የሆነ ኃይል። ዳይሬክተሩ እንደገና መልዕክቱን ተመለከቱት። "ድንገተኛ አደጋ" አስመስለው' 'ይህ ብዙም አያስቸግርም አሉ በሐሳ ባቸው። ከዚያም መጥሪያውን ተጫኑት።

ሁለት ሰዎች ወደ እርሻው ሥፍራ የዕቃ መጫኛው በሆነ ጥቁር ሰማያዊ መኪና መጡ። መኪናቸውን አቁመው ዙሪያ ገባውን በጥንቃቄ እየተመለከቱ ወረዱ። የዳን ዋይን የመጀመሪያ ግምቱ የእርሻ ሥፍራውን ለመውሰድ የመጡ መስሎት ነበር። በሩን ከፈተላቸው።

"ዳን ዋይን?"

"አዎን። ምን ላድርግላ....."

ይሆን ያህል ብቻ ነበር የተናገረው። ሁለተኛው ሰው በጥቁር የብረት ኳስ አናቱን ፈለጠው። ሌላው ግዙፍ ደግሞ ሕሊናውን የሳተውን ሰው ወደ እህል መጋዘኑ በትከሻው ተሸክሞ ወሰደው። በመጋዘኑ ውስጥ ሰምንት ፈረሶች ነበሩ። ሰዎቹ ወደሚቀጥለው ጋጣ ተሸክመው ወሰዱት። በውስጡም በጣም የሚያምር ጥቁር የርቢ ፈረስ ነበር።

ግዙፉ ሰውዬ....."የምንፈልገው ይሆን ነው" አለና ዳን ዋይንን መሬት ላይ ጣለው። ሁለተኛው ሰው ከመሬት ላይ የከብት መጎተቻ ብረት ብድግ አደረገ ፈረሱን ባለ በሌለ ኃይሉ አፍንጫው አካባቢ ሲመታው በጠባቡ ጋጣ ውስጥ የተያዘው ፈረስ ነጫጭ ዐይኖቹ ተጎለጎሉ፤ ጥርሶቹ ረገፉ። ትንሹ ሰውዬ....."እሁን" ሲለው ባልደረባው ዳንን ብድግ አደረገና ግማሽ በተከፈተው በር ውስጥ ወደ ጋጣው ከተተው። ረዘም ላለ ጊዜ የቆሰለ ፈረስ በሰው ላይ የሚያደርገውን አሰቃቂ ትዕይንት ሲመለከቱ ከቆዩ በኋላ በውጤቱ ሲረኩ ፊታቸውን አዙረው ወደ መጡበት ተመለሱ።

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ዲሲአይ ለ–ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል
ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርአስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
-6- ዳንኤል ዋይን-ዋኪ- ተወግዷል

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሃያ ሰባት

ዘጠነኛ ቀን

ፎርት ስሚዝ ካናዳ

በሰሜን–ምዕራብ ካናዳ የምትገኘው ፎርት ስሚዝ የተባለችው ከተማ በንግዱ ዓለም በጣም ስኬታማ ውጤት ያላቸው ሁለት ሺህ ሰዎች የሚኖሩባት ስትሆን አብዛኛዎቹ ገበሬዎችና የከብት ዕርባታ የሚመሩ በነጋዴዎች ጎርፍ የሚጥለቀለቁ ናቸው። አየሩ የተራዘመ ግሩም የዝናብ ወራት ያለው ሲሆን የዳርዊንን የ "ጠንካሮች ይዘልቃሉ" መላ ምትን የምታረጋግጥ ከተማ ናት።

ዊሊያም ማን ከጠንካሮቹ አንዱ ነው። የተወለደው ሚቺጋን ውስጥ ሲሆን ገና በለጋ ሠላሳዎቹ ዕድሜ ውስጥ እንዳለ ዓሣ ለማጥመድ ወደ ፎርት ስሚዝ በተጓዘበት ጊዜ የፎርት ስሚዝ ማሕበረ ሰብ ሌላ ጥሩ ባንክ እንደሚያስፈልገው በመወሰን ዕድሉን ተጠቀመበት። በከተማው ውስጥ የነበረው ባንክ አንድ ብቻ ሲሆን ተፎካካሪውንም ከንግድ ውጭ ለማድረግ ዊሊያምን የወሰደበት ከሁለት ዓመት ያነሰ ጊዜ ብቻ ነው። ማን ባንኩን ማንኛውም ባንክ በሚመራበት ዐይነት ሥራውን ይመራው ነበር። ጥሩ ችሎታው ሒሳብ ሲሆን ቁጥሮቹ ደግሞ ከእርሱ ጥቅምና ትርፍ አንፃር እየተቀናጁ መምጣታቸውን አረጋገጠ። በጣም የሚወደው ተረት ቢኖር ልጁ በጣም የታመመበት ሰው ወደ አንድ ባንክ ሄዶ ልጁ አሰቸኳይ ቀዶ ጥገና እንዲደረግለትና ሕይወቱ እንዲተርፍ ያቀረበው የብድር ጥያቄ ነው። አመልካቹ ለብድሩ የሚያሲይዘው ነገር እንደሌለ ሲናገር ባንከኛው ሰውዬውን ከቢሮው አባረረው።

“እወጣለሁ” አለ ሰውዬው። “ከመውጣቴ በፊት ግን አንድ ነገር ልንገርህ። በሕይወቴ ሙሉ እንዳንተ ዐይነት ልበ ቀዝቃዛ ሰው ዐይቼ አላውቅም።”

“አንድ ጊዜ ቆይ!” አለ ባንከኛው። “አንድ ስሜታዊ የሆነ ድርድር አቀርብልሃለሁ። ከዐይኖቼ ውስጥ አንደኛው ከብርጭቆ የተሠራ ነው። የትኛው እንደሆነ ካወከ ብድሩን እሰጥሃለሁ” አለው።

ሰውዬው ወዲያውኑ.....“የግራ ዐይንህ!” ሲል መለሰለት።

ባንከኛው በጣም ተደነቀ። “ይህንን ማንም አያውቅም ነበር። ለመሆኑ እንዴት ለመናገር ቻልክ?”

“በጣም ቀላል ነው!” አለ ሰውዬው። “ለአጭር ጊዜ በግራ ዐይንህ ውስጥ የሐዘኔታ ጭላንጭል በማየቴ እሱ መሆን አለበት ብዬ አሰብኩ።”

@BOOKALEM

ይህን ምሳሌ ዊሊያም ማን ለንግድ ሰው የሚገባ ጥሩ ታሪክ ነው ብሎ ያምናል። አንድ ሰው ንግድን ከሐዘኔታ ጋር ለመምራት አይችልም። ከታችኛው መስመር ጀምሮ መመልከት ይገባል። በካናዳና በአሜሪካ ውስጥ ታላላቅ ባንኮች እንደ መርፌ እየተሰበሩ ሲወድቁ የዊሊያም ማን ባንክ ግን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ እየተጠናከረ መጣ። መመሪያው በጣም ቀላል ነበር። "ለንግድ ጀማሪዎች ብድር የለም። በሕብረት ለሚደረግ ንግድ ብድር የለም። ልጆቻቸው አሰቸኳይ ቀዶ ጥገና ለሚያስፈልጋቸው ጎረቤቶች ብድር የለም።"

ማን ለስዊስ ባንኮች የአሠራር ዘዴ በጣም ከፍተኛ የሆነ ከበሬታ አለው። የዙሪክ መሳፍንት የባንከኞች ሁሉ ባንከኞች ናቸው። ታዲያ ዊሊያም ማን አንድ ቀን ወደ ስዊዘርላንድ ተጉዞ የዙሪክን ባንከኞች በማነጋገር በሥራው ውስጥ የሳተው ነገር ይኖር እንደሆን ለመረዳት ወሰነ። ቢሆንም ከካናዳ ዶላር ውስጥ ብዙ ሳንቲሞችን መጭመቅ ይችላል። ግርማ ሞገስ ያለው አቀባበል ተደረገለት። በጉብኝቱ መጨረሻ ላይ ማን ምንም የተማረው ነገር አልነበረም። የእርሱ የባንክ አመራር ዘዴ በጣም የሚደነቅ ነበር። የስዊስ ባንከኞችም ይህንኑ ሊነግሩት አላመነቱም።

ማን ወደ አገሩ ለመመለስ በተነሳበት ዕለት የአልፕስን ተራራ ለመጎብኘት ወሰነ። ጉብኝቱን አሰልቺ ሆኖ አገኘው። የአካባቢው ትዕይንት የሚስብ ቢሆንም በፎርት ስሚዝ ዙሪያ ካለው የተፈጥሮ ትዕይንት የሚበልጥ አልነበረም። ከመንገደኞቹ አንዱ ቴክሳስ ለሚገኝ የከሰረ የከብት እርባታ እርሻው ብድር ለማግኘት ሞክሮ ነበር። ሰውዬውን ፊቱ ላይ ነው የሳቀበት። ስሜቱን የሳበው ብቸኛ ነገር ቢኖር በራሪ ዲስክ የተባለው ነገር መከስከስ ነው። በዚህ ነገር እውነትነት ለቅንጣት ጊዜ ያህል እንኳ አምኖ አያውቅም። ይህ ጉዳይ ቱሪስቶችን ለመሳብ ሲል የስዊስ መንግሥት ሆን ብሎ ያደረገው እንደሆነ እርግጠኛ ነው። "በዲዝኔይ ዎርልድ" ውስጥ የነበረ ሰው ስለሆነ እውነተኛ የሚመስሉ የማጭበርበሪያ ብዙ ነገሮችን ዐይቷል። "ይህ የስዊዘርላንድ መንግሥት "የብርጭቆ ዐይን" ነው!" አለ በማሸሟጠጥ።

"ዊሊያም ማን ወደ አገሩ ለመመለስ ደስተኛ ነበር።"

"እያንዳንዱ የባንከኛው ደቂቃ በፕሮግራም የተቀናበረች ናት። በመሆኑም ጸሓፊው ቢሮው ገብታ አንድ እንግዳ ሰው ሊያነጋግረው እንደሚፈልግ ስትነግረው የመጀመሪያው ፍላጎቱ ሊያስወግደው ነበር። "ምንድነው የሚፈልገው?" አላት።

"ቃለ መጠይቅ ሊያደርግልህ እንደሚፈልግ ነው የተናገረው። ስለባንክ ባለሙያዎች አንድ ዘገባ በማዘጋጀት ላይ ነው።" ይህ ደግሞ ከመሠረቱ ልዩ የሆነ ነገር ነው። ዊሊያም ማን ኮቱንና ፀጉሩን አስተካከለና "በይ አስገቢው" አላት።

ጎብኚው ሰው አሜሪካዊ ነበር። አለባበሱ በጣም ዘናጭ በመሆኑ ታዋቂ ከሆነ የመጽሔት ወይም ጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት እንደመጣ ያሳያል።

@BOOKALEM

"ሚስተር ማን?"

"አዎን።"

"ሮበርት ቤላሚ እባላለሁ።"

"ስለኔ አንድ ሐተታ ለመጻፍ እንደምትሻ ጸሐፊዬ ነግራኝ ነበር።"

"አዎን! በአጠቃላይ ስለእርስዎ አይደለም። ግን በእርግጥ ከፍተኛውን ሥፍራ የሚይዙት እርስዎ ይሆናሉ። የኔ ጋዜጣ....."

"የትኛው ጋዜጣ ነው እሱ?"

"ዎል ስትሪት ጆርናል የተባለው።"

'አሃ! ይህ ደግሞ እጅግ በጣም ግሩም የሆነ ነው' አለ ባንከኛው በሐሳቡ።

"ጆርናሉ ብዙ ባንከኞች በዓለም ላይ ከሚካሄዱት ነገሮች ውስጥ የተነጠሉ ወይም የተገለሉ ናቸው ብሎ ያምናል። አልፎ አልፎ ነው የሚጓዙት። ወደ ሌሎች አገሮች ለጉብኝት አይሄዱም። በሌላ በኩል እርስዎ ሚስተር ማን ደግሞ በሚገባ የተጓዙ ሰው ለመሆንዎ ዝና ይነግርልዎታል።"

"አዎን ተጉዣለሁ ብዬ እገምታለሁ። እንደእውነቱ ከሆነ ስዊዘርላንድ ውስጥ ጉብኝት ሳደርግ ቆይቼ ባለፈው ሳምንት መመለሴ ነበር።"

"በእውነት? በጉዞውስ ተደስተው ነበር?"

"አዎን። ከበርካታ ባንከኞች ጋር ተገናኝቼ ነበር። ስለዓለም የኤኮኖሚ ጉዳዮችም ተወያይተናል።"

ሮበርት የማስታወሻ ደብተር አውጥቶ ማስታወሻ መያዝ ጀመረ። "ለደስታስ የተወሰነ ጊዜ አግኝተው ነበር?"

"በእውነት አላገኘሁም። ከነዚያ አውቶቡሶች በአንደኛው አጭር የጉብኝት ጉዞ አድርጌ ነበር። የአልፕስን ተራራ ከዚህ ቀደም ዐይቼ አላውቅም ነበር።

ሮበርት ሌላ ማስታወሻ መዘገበ። "ጉብኝት በትክክል የምንፈልገው ዐይነት አርአስት ነበር" አለ ሮበርት በማደፋፈር ዐይነት። "በአውቶቡሱ ላይ አስደሳች ሰዎችን ሳይገናኙ አይቀርም ብዬ እገምታለሁ።"

'አስደሳች?' የገንዘብ ብድር ለማግኘት የሞከረውን ቴክሳስ ተወላጅ አስታወሰ። "የለም በእርግጥ አላጋጠመኝም።

"በእርግጥ?"

ማን ጋዜጠኛውን ተመለከተው። ዘጋቢው ብዙ ይናገራል ብሎ እየጠበቀው ነው። በእርግጥ "ከፍተኛውን ሥፍራ የሚይዙት እርስዎ ይሆናሉ" ብሎታል። "አዎን" አለ ማን። "አንድ ሩሲያዊት ልጃገረድ ነበረች።"

ሮበርት ማስታወሻው ላይ መዘገበና "በእርግጥ ነበረች? እስቲ ስለእርሷ በተጨማሪ ቢነግሩኝ።

@BOOKALEM

"ደህና! መነጋገር ጀመርን። እኔም ሩሲያ ምን ያህል ኋላ ቀር እንደሆነችና ሁኔታውን እስካልለወጡ ድረስ ምን ዐይነት አስከፊ ችግር ውስጥ እንደሚዘፈቁ ገለጽኩላት።"

"መቼም ተመስጣ እንደነበር ነው" አለ ሮበርት።

"አዎን ተመስጣ ነበር። ለሩሲያዊያት ሴቶች በጣም ብሩህ ዐይነት የነበረች በመሆኗ። መቼም እንደምታውቀው በጣም የተሰደቡ ሰዎች ናቸው።"

"ስሚንስ ጠቅሳልዎ ነበር?"

"የለም.....ቆይ.....አልጋ ዐይነት ነገር ነበር።"

"ከየት እንደሆነችስ ተናግራ ነበር?"

"አዎን። በዋናው የኪየቭ ቤተ መዛግብት ቅርንጫፍ ውስጥ በላይብራሪያንነት ትሠራለች። ወደ ውጭ አገር ስገትጓዝ የመጀመሪያዋ ነው ብዬ እገምታለሁ። ይህም ዕድል የተገኘው በግላስኖስት ምክንያት ነው ብዬ እገምታለሁ። አስተያየቴን የምትፈልግ ከሆነ....." ሮበርት በመመዝገብ ላይ መሆኑን ለማረጋገጥ ብሎ ባንከኛው ንግግሩን ቆም አደረገ። "ጎርባቼቭ ሩሲያን በቅርጫት ውስጥ ከተው ወደ ገሃነም ነው የወረወሯት። ምሥራቅ ጀርመን በሳህን ላይ ተቀምጣ ለቦን ተሰጠች። በፖለቲካው ግንባር በኩል ጎርባቼቭ በከፍተኛ ፍጥነት የተንቀሳቀሰ ሲሆን በኤኮኖሚው መስክ ደግሞ በጣም በዝግታ ነው የሚንቀሳቀሰው።"

"በጣም የሚያስደንቅ ነው!" አለ ሮበርት። ለሚቀጥሉት ሠላሳ ደቂቃዎች ሮበርት የባንከኛውን ከተራ ገበያ አስከ ጦር መሣሪያ ቁጥጥር ድረስ ያለ አስተያየት እያዳመጠ ቢቀመጥም ስለአውቶቡሱ መንገደኞች ተጨማሪ ማስረጃ ለማግኘት አልቻለም።

ሮበርት ወደ ሆቴል ከፍሉ እንደተመለሰ ለጄነራል ሒሊያርድ ስልክ ደወለ።

"አንድ ጊዜ ኮማንደር ቤላሚ!" አለች ጸሓፊዋ።

"አቤት ኮማንደር?"

"ሌላ ምስክር አግኝቻለሁ ጄነራል።"

"ስሙ"

"ዊሊያም ማን። ፎርት ስሚዝ ካናዳ ውስጥ የባንክ ባለቤት የሆነ።"

"አመሰግናለሁ የካናዳ ባለሥልጣናት ወዲያውኑ እንዲያነጋግሩት አደርጋለሁ።"

"በነገራችን ላይ ሌላ ፍንጭ ስለሰጠኝ ዛሬ ማታ ወደ ሩሲያ እበራለሁ። ከኢንቱሪስት ድርጅት የመግቢያ ቪዛ እፈልጋለሁ ።"

"ስቶኮልም ቪስጎር ሆቴል ደረስ በል። እንግዳ መቀበያው ዴስክ ላይ አንድ ኤንቨሎፕ ተዘጋጅቶ ይጠብቅሃል።"

@BOOKALEM

"አመሰግናለሁ።"

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ለ–ዲ.ጂ.ኤች.ኪው....
መረጃ ድርጅት ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት– የፍርድ ቀን ዘመቻ
-7- ዊሊያም ማን–ፎርት ስሚዝ
የመልዕክት መጨረሻ

በዚያ ዕለት ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ የዊሊያም ማን የበር መጥሪያ ተደወለ። ማንም የሚጠብቀው ሰው ካለመኖሩም በላይ ቀጠሮ ያላስያዙ ጎብኝዎችን እጅግ ይጠላ ነበር። የቤት ጠባቂው ሥራውን ጨርሶ አርፏል። ሚስቱም ፎቅ ላይ መኝታ ቤት ተኝታለች። ዊሊያም እየተበሳጨ በሩን ከፈተ።

ጥቁር ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በሩ ላይ ቆመዋል።

"ዊሊያም ማን?"

"አዎን።"

አንደኛው የመታወቂያ ካርድ አውጥቶ እያሳየው "ከባንክ ካናዳ ነው የመጣንው። ወደ ውስጥ እንግባ?" አለው።

"ምንድነው የምትፈልጉት?"

"ግድ ካልሰጠህ ይህንን ጉዳይ እቤት ውስጥ ብንነጋገር ይሻላል።"

"በጣም ጥሩ!" አለና ሰዎቹን ወደ ውስጥ መራቸው።

"ቀደም ሲል ስዊዘርላንድ ውስጥ ነበርክ። አልነበርክም?"

ጥያቄው ከግምት ውጭ ሆነበት "ምን?"

"አንተ እዚያ በነበርክበት ጊዜ መዛግብትህን አስመርምረን ነበር። ሚስተር ማን! በባንክህ ውስጥ የአንድ ሚሊዮን ዶላር ጉድለት እንዳለ አውቀሃል?"

ዊሊያም ማን ሁለቱን ሰዎች በፍርሃት ተመለከታቸው። "ምንድን ነው የምታወሩት? እነዚያን መዛግብት ራሴ ነኝ በየሳምንቱ የምመረምራቸው። አንዲት ሳንቲም እንኳ ጎድላ አታውቅም።"

"አንድ ሚሊዮን ዶላር ሚስተር ማን! ገንዘቡንም ለግል ጥቅምህ አባክነህዋል ብለን እናምናለን።"

@BOOKALEM

ዊሊያም ማን ፊቱ በርበሬ መሰለና መንተባተብ ጀመረ። "እንዴት.....ብትቃጡ.....ፖሊስ ከመጥራቴ በፊት ከቤቴ ውጡልኝ።"

"ያ ደግሞ ምንም አይጠቅምህም። አሁን የምንፈልገው የይቅርታና ጸጸት ደብዳቤ እንድትጽፍ ብቻ ነው።"

ግራ ተጋብቶ አፍጥጦ ይመለከታቸው ጀመር። "የጸጸት ማስታወሻ? እናንተ ዕብዶች ናችሁ።"

"አይደለንም ጌታዬ።"

አንደኛው ሰው ሽጉጥ ስቦ አወጣና..... "ተቀመጥ ሚስተር ማን!" ሲል አዘዘው።

'አምላኬ መዘረፌ ነው!' ሲል አሰበ ዊሊያም። "ተመልከቱ! የምትፈልጉትን ነገር ሁሉ ውሰዱ። ብጥብጥ ወይም ረብሻ አያስፈልግም።"

"ቁጭ በል እባክህ!"

አንደኛው ሰው ወደ መጠጥ ማስቀመጫው ቡፌ ተራመደ። ሳጥኑ ቁልፍ ስለነበረ መስታወቱን ሰብሮ አንድ የአልኮል መጠጥ ከብርጭቆ ጋር አወጣና ዊስኪ ግጥም አርጎ ቀድቶ ዊሊያም ወደ ተቀመጠበት ይዞ መጣ።

"ይህንን ጠጣ። ያዝናናሃል!" ሲል አዘዘው።

"ከእራት በኋላ ጠጥቼ አላውቅም ዶክተሬ....."

አንደኛው ሰውዬው ሽጉጡን ዊሊያም ማን ጭንቅላት ላይ ደገነውና "ጠጣው! ያለዚያ መለኪያውን አንጎልህ ውስጥ እከተዋለሁ!" አለው።

ማን ሕይወቱ በሁለት ያበዱ ነፍሰ ገዳዮች እጅ እንደሆነች ገባው። መለኪያውን በሚንቀጠቀጡ እጆቹ ተቀበለና ፉት አለለት።

"ጭልጥ አድርገህ ጠጣው!"

በርከት አደረገና መጠጡን ተጎነጨ። "ምን.....ምንድነው የምትፈልጉት?" አለ ድምጹን ከፍ አድርጎ። ሚስቱ ሰምታ ወደ ታች ትመጣለች ብሎ ተስፋ በማድረግ። ነገርግን ዋጋ የለሽ ተስፋ ነበር። አንዴ አልጋ ላይ ከወደቀች ተሸከመዋት ቢሄዱ እንኳ የማትሰማ እንቅልፋም መሆኗን ያውቃል። 'የመጡበትን ለምን ቶሎ አይፈጽሙም?' አለ በሐሳቡ።

"የምትፈልጉትን ውሰዱ። ላቆማችሁ አልሻም።"

"መለኪያው ውስጥ ያለውን ጨርስ!"

"ይህ አስፈላጊ አይደለም። እ....."

ሰውዬው ኪጆሮው ከፍ ብሎ በጡጫ ነረተው። ማን ከሕመሙ የተነሳ ትንፋሹ አመለጠው።

"ጨርሰው!"

ማን ብርጭቆው ውስጥ የቀረውን ዊስኪ በአንድ ትንፋሽ ሲጨለጠው ጉሮሮውን እያቃጠለው ሲወርድና ሲያዞረው ተሰማው። "ካዝናዬ ፎቅ መኝታ ቤት

@BOOKALEM

ውስጥ ነው ያለው" አላቸው። "ራሴ እከፍትላችኋለሁ።" ምናልባት ይህ ሚስቱን ይቀሰቅሰለትና ፖሊስ ልትጠራለት ትችል ይሆናል።

"ምንም የሚያስቸኩልህ ነገር የለም" አለ ሽጉጥ የያዘው ሰው። "ሌላ መጠጥና ብዙ ጊዜ አለህ።"

ሌላው ሰው ደግሞ ወደ መጠጥ ማስቀመጫው ሄዶ እስከ አፋ ግጥም አድርጎ ሞላውና "እነሆ!" አለው።

"የለም! በእውነት አያስፈልግም!" ሲል ዊሊያም ተቃወመ።

ብርጭቆው እጁ ላይ ተቀመጠለት። "ጨልጥና ጠጣው!"

"በእውነት አልፈ....."

መጀመሪያ የተመታበት ቦታ ላይ በከባድ ቡጢ ደገመው። ማን ከሕመሙ የተነሳ ሕሊናውን ሊስት ምንም አልቀረውም።

"ጠጣት!"

'ደህና የሚፈልጉት ይህንን ከሆነ ምን ቸገረኝ? ይህ ቅዠት ቶሎ ቢያልቅ የተሻለ ይሆናል።'

"ከዚህ በላይ ከጠጣሁኝ እታመማለሁ።"

"ኪታመምክ ደግሞ እገድልሃለሁ!" አለ ሰውዬው።

ዊሊያም ማን አንዴ ባለሽጉጡን አንዴ ጓደኛውን ተመለከታቸው። እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ሰዎች መሰለው ይታዩት ጀመር።

"ሁላችሁም ምንድነው የምትፈልጉት?"

"ነገርንህ ሚስተር ማን። የምንፈልገው የጸጸት ቃልህን እንድትጽፍ ብቻ ነው።" ዊሊያም ማን በስካር "እሺ" በማለት አንገቱን ነቀነቀ።

ሰውዬው ፈገግ አለና....."እየህ የምንፈልገው ይህንን ብቻ ነው።" አንድ ቁራጭ ወረቀት ዊሊያም እጅ ላይ አስቀመጠና....."የምታደርገው ነገር ቢኖር "በጣም አዝናለሁ! ይቅርታ አድርጉልኝ" ብለህ መጻፍ ብቻ ነው።

ዊሊያም ማን ቀና ብሎ እየተጨናበሰ ተመለከተው። "ይኸው ነው?"

"ይኸው ነው። ከዚህ በኋላ ትተንህ እንሄዳለን።"

ድንገተኛ የእፎይታ ደስታ ስሜት ተሰማው። 'ይሄ ሁሉ ሊዚህችው ብቻ ነበር። የሃይማኖት አክራሪዎች ናቸው። ወዲያው ከቤቴ እንደወጡ ፖሊስ ጠርቼ አስይዛቸዋለሁ። ከዚያ እያንዳንዳቸው መሰቀላቸውን አረጋግጣለሁ።'

"ጸፍ ሚስተር ማን!" ለማተኮር በጣም አስቸጋሪ ሆነበት። "ምን ብዬ እንድጽፍ ነበር የፈለከው?"

"አዝናለሁ ይቅርታ አድርጉልኝ።"

ሰውዬው ከዊሊያም እጅ ላይ ጠርዙን ብቻ ይዞ ወረቀቱን ተቀበለው። "በጣም ጥሩ ነው ሚስተር ማን። እንዴት ቀላል እንደሆነ አየህ?" ከፍሉ ይሸከረከርበት ጀመር።

@BOOKALEM

"አዎን" አለ ማን። "ጸጸቴን ጽፌያለሁ። አሁን አትሄዱልኝም?"

"በግራ እጅህ እንደምትሠራ አየሁኝ።"

"ምን?"

"የግራ እጅ ተጠቃሚ ነህ።"

"አዎን።"

"በዚህ አካባቢ ቀደም ሲል በርከት ያለ ወንጀል ተፈጽሟል። ይህንን ሽጉጥ ራስህን እንድትከላከልበት ልተውልህ ነው።"

ሽጉጥ ግራ እጁ ላይ ሲቀመጥለት ተሰማው። "ሽጉጥ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ታውቃለህ?"

"አላውቅም።"

"በጣም ቀላል ነው። ልክ እንደዚህ አድርግ....." አለና ሰውየው ሽጉጡን ወደ ዊሊያም ጆሮ ግንድ ቀና አደረገና ቃታውን ሳበው። የታፈነ ጩኸት ከድምጽ አልባው መሣሪያ ሲሰማ በደም የጨቀየው ወረቀት ደግሞ ወለሉ ላይ ወደቀ።

"ይኸው ነው። ደህና እደር ሚስተር ማን!" አለ ሌላው ሰውዬ።

አስቸኳይ መልዕክት

በጣም ከፍተኛ ምሥጢር

ሲ.ጂ.ኤች.ኪው ለ–ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል

የካናዳ ፀጥታ መሥሪያ ቤት ምክትል ዳይሬክተር

ዐይኖች ብቻ

ግልባጭ የለውም

አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ

-7-ዊሊያም ማን. ፎርት ስሚዝ ተወግዷል

የመልዕክት መጨረሻ

አሥረኛ ቀን

ፎርት ስሚዝ ካናዳ

በማግስቱ ጠዋት የባንኩ መርማሪዎች ከባንኩ ሒሳብ ውስጥ አንድ ሚሊዩን ዶላር መጥፋቱን አስታወቁ። ፖሊስ የዊሊያም ማንን አሟሟት እራስን በራስ ማጥፋት ሲል መዘገበው። የጠፋው ገንዘብም ሳይገኝ ቀረ።

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሃያ ስምንት

ኢሥራ አንደኛ ቀን

ብራስልስ 6300 ሰዓት

የናቶ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት አዛዥ ጄነራል ሺፐሌይ በረዳቱ ከእንቅልፉ ተቀሰቀሰ። "ስለቀሰቀስኩዎት በጣም አዝናለሁ ጄነራል። አንድ ሁኔታ በእጃችን ውስጥ ያለ ይመስላል።"

ጄነራል ሺፐሌይ እንቅልፉን ከዐይኖቹ ላይ እያሻሸ ከአልጋው ቀና ብሎ ተቀመጠ። ከዩናይትድ ስቴትስ የመጡ እንደራሴዎችን ሲያዝናና ነበር ያመሸው። "ምንድነው ችግሩ ቢል?"

"ከራዳር ጣቢያችን አንድ ጥሪ ተቀብዬ ነበር። ራዳሮቻችን በሙሉ አብደዋል ወይም ያልታወቁ እንግዳ ጎብኝዎች መጥተውልናል።"

ጄነራል ሺፐሌይ ከመኝታው ተነሳ። "በአምስት ደቂቃዎች ውስጥ እዚያው እመጣለሁ።"

ፈቃደኛ ተመዝጋቢ ወታደሮች ጨለምለም ባለው የራዳር ክፍል ውስጥ በከፍሉ ማዕከላዊ ሥፍራ ላይ የሚገኝ የራዳር መቆጣጠሪያ አመልካች መሣሪያ ከበው ይመለከታሉ። ጄነራሉ ከፍሉ ውስጥ ሲገባ ዞሩና በተጠንቀቅ ቆሙ።

ጄነራሉ "ተዛና!" አለና አልፏቸው ሻምበል ሙለር ወደተባለው የራዳሩ ኃላፊ ተጠጋ። "ምንድነው የተፈጠረው ሊዊስ?"

ሻለቃ ሙለር ራሱን ቆፈር አከከ አደረገና....."በሰዓት 22 ሺህ ማይልስ የሚበር፤ ድንገት አየር ላይ ቀጥ ብሎ ቆሞ እንደገና በመጣበት ፍጥነት ወደ ኃላው የሚበር አውሮፕላን ያውቃሉ?" ሲል ጄነራሉን ጠየቀው።

ጄነራል ሺፐሌይ አፍጥጦ እየተመለከተው ነበር። "ምንድነው የምታወራው?"

"ከራዳር እስክሪናችን አንጻር ለግማሽ ሰዓት ያህል ይከናወን የነበረው ድርጊት ይህ ነበር። በመጀመሪያ በሙከራ ላይ ያለ አንድ ዐይነት የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ነው ብለን ገምተን ነበር። ነገር ግን ከሩሲያ፤ ከእንግሊዝና፤ ከፈረንሳይ እንዳረጋገጥንው የእነርሱም ራዳሮች የሚያሳዩት እኛ ያየንውን ነገር ነው።"

"ስለዚህ የመሣሪያው (ራዳሩ) ብልሽት ችግር አይደለም ማለትህ ነው?" አለ ጄነራሉ ጠበቅ አድርጎ።

"አይደለም ጌታዬ። በመላው ዓለም ያሉት ራዳሮች በድንገት ቀውሰዋል ብለው ለመገመት ካልፈለጉ በስተቀር።"

"እነዚህ ነገሮች ምን ያህሉ ናቸው ራዳር ላይ የታዩት?"

@BOOKALEM

"ከደርዘን በላይ ይሆናሉ። ፍጥነታቸው እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ለመከታተል እንኳ በጣም አስቸጋሪ ነው። እናገኛቸውና እንደገና ይጠፉብናል። የአየር ንብረት ባሉን፤ የአየር ፀባይ ችግር፤ የእሳት ኳሶች፤ ወይንም ሌላ ለሰው ልጅ የሚታወቁ በራሪ ነገሮች ውስጥ እንዳልሆኑ አረጋግጠናል። ጥቂት አውሮፕላኖችን ላሰማራ ነበር። ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ምንም ሆኑ ምን ልንደርስባቸው ከምንችለው ከፍታ በላይ ነበር የሚበሩት።"

ጀነራል ሺፐሌይ ከራዳሩ ስክሪኖች ወደ አንዱ ሄደና....."አሁን ራዳራችን ላይ የሚመጣ ነገር አለ?" ሲል ጠየቀ።

"የለም ጌታዬ! ግን ተመልሰው እንደሚመጡ ይሰማኛል።"

ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

አታዋ 05500 ሰዓት

ጃኑስ የጄነራል ሺፐሌይን ሪፖርት አንብቦ እንደጨረሰ ኢጣሊያዊው በድንጋጤ ብድግ ብሎ....."ሊወሩን እየተዘጋጁ ነው!" ሲል ጮኸ።

"ምን ቀራቸው? ይኸው ወረውናል እኮ!" አለ ፈረንሳዊው። "በጣም ዘግይተናል። ከፍተኛ ጥፋት ነው የሚደርሰው። በምንም ዐይነት መንገድ....."

"ከቡራን!" አለና ጃኑስ አቋረጣቸው። "ልናስወግደው ወይም ልንከላከለው የምንችለው ጥፋት ነው።"

"እንዴት? ጥያቄያቸው ምን እንደሆነ እያወክ?" እንግሊዛዊው።

"ጥያቄያቸው ከጥያቄአችን ውጭ ነው።" ብራዚላዊው።

"ዛፎቻችንን የፈለገውን ነገር ብናደርጋቸው የራሳችን እንጂ የእነርሱ ጉዳይ አይደለም። ይህ የአረንጓዴ ቤት ውጤት የሚሉት ያልተረጋገጠ የሳይንስ ቁሻሻ መጣያ ነው!"

"የኛስ ጉዳይ?" አለ ጀርመናዊው። "በከተሞቻችን ላይ ያለውን አየር እንድናፀዳ ከጠየቁን ፋብሪካዎቻችንን መዝጋት አለብን ማለት ነው። ምንም የሚተርፍ ኢንዱስትሪ አይኖረንም።"

"እና እኛም መኪና ማምረት ማቆም አለብን ማለት ነው?" አለ ጃፓናዊው። "የሠለጠነው ዓለም የት ሊሆን ነው?"

"ሁላችንም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ነን" አለ ሩሲያዊው። "እነርሱ እንደጠየቁት የተፈጥሮ ሀብት ብክለትን ማቆም ካለብን የዓለምን የኢኮኖሚ አቋም ይደመስሰዋል። የከዋክብት ጦርነት ፕሮጀክታችን ዝግጁ ሆኖ እስኪመታቸው ድረስ ተጨማሪ ጊዜ ማግኘት አለብን።"

"በዚህ ነጥብ ላይ ተስማምተናል!" አለ ጃኑስ በፍጥነት። አፋጣኙ ችግራችን ሕዝብ ፀጥ እንዲል ማድረግና ሽብርና ፍርሃትን መቆጣጠር ነው።"

"ኮማንደር ቤላሚ ምን ዐይነት ዕድገት እያሳየ ነው?" ካናዳዊው።

"እጅግ በጣም ግሩም የሆነ ዕድገት እያሳየ ነው። በሚቀጥለው አንድ ወይንም ሁለት ቀናት ውስጥ ሥራውን ያጠናቅቃል።"

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሠላሳ

ኪየቭ ሶቪየት ሕብረት

እንደአብዛኛው የአገሯ ሰዎች ኦልጋ ሮማንቻንኮ ስለፔሪስትሮይካ ይሰማት የነበረው ደስታ እየቀዘቀዘ መጣ። በመጀመሪያ በእናት ሩሲያ ውስጥ ይከናወናል ተብሎ ቃል የተገባለት ለውጥ ሁሉ በጣም የሚያስደስት ነበር። የነፃነት አየር በጎዳናዎች ሁሉ እየነፈሰ አገሩን ተስፋ ሞልቶት ነበር። ትኩስ ሥጋና አትክልት፤ ውብ ቀሚሶች፤ እውነተኛ የቆዳ ጃኬትና የቆዳ ጫማ በየሱቁ ይገኛል የሚል የተስፋ ቃል ተሰጥቶ ነበር። ነገር ግን ይህ ሁሉ ከተጀመረ ከስድስት ዓመታት በኋላ መራራ የሆነ ቅዠት ሰፈነ። ሸቀጦች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ከገበያ ላይ ጠፉ። ያለጥቁር ገበያ ፈጽሞ ለመኖር አልተቻለም። የሁሉም ነገሮች እጥረት አለ። ዋጋቸውም እየናረ ነው። ዋና ዋና አውራ ጎዳናዎች ላይ ተቃውሞዎች እየተከናወኑ ሲሆን የወንጀል መጠንም እያደገ መጣ። ፔሬስትሮይካና ግላስኖስት እንደነዳፊዎቹ ፖለቲከኞች ባዶ መሆናቸው ይታይ ጀመር። ኦልጋ በኪየቭ መካከል ሌን ኮምሶሞል አደባባይ በሚገኘው ቤተ መጽሐፍት ለሰባት ዓመታት አገልግላለች። የሠላሳ ሁለት ዓመት ወጣት ስትሆን ከሶቪየት ሕብረት ውጭ ተጉዛ አታውቅም። ኦልጋ በመጠኑ ማራኪ የሆነችና በትንሹ ከክብደት በላይ ብትሆንም ይህንን በሩሲያ ብዙም ነገሬ የሚለው አልነበረም። ሁለት ጊዜ ታጭታ ሁለቱም ጥለዋት ሄደዋል። ኦልጋ ከኢቫን ጋር ለመሆን ወደ ሞስኮ ለመሄድ ሞክራ ነበር። ግን ያለሞስኮ መኖሪያ ፍቃድ (ፕሮፒሲካ) የማይቻል ጉዳይ ነበር።

ሠላሳ ሦስተኛው የልደት በዓሏ እየቀረበ ሲመጣ የብረት መጋረጃው ተመልሶ በዙሪያዋ ከመጋረዱ በፊት የዓለምን አንድ ሌላ ገጽታ ለመመልከት ቆረጠች። አክስቷ ወደሆነችው መጽሐፍት ቤት ኋላፊ ሄደች።

"የእረፍት ጊዜዬን አሁን ለመውሰድ እሻለሁ" አለች ኦልጋ።

"መቼ ነው ለመሄድ የምትፈልጊው?"

"የሚቀጥለው ሳምንት።"

"ራስሽን አስደስቺ!"

እንደዚህ ቀላል ነበር። ከፔሬስትሮካ በፊት ቢሆን ኖሮ ግን የእረፍት ፈቃድ መውሰድ ማለት ወደ ጥቁር ባሕር ወይም ወደ ሳማርካንድ ወይም ወደ ቲቢሊስ ወይም ሩሲያ ውስጥ ወዳሉ ሌሎች ደርዘን ሥፍራዎች መሄድ ማለት ነበር። አሁን ግን ፈጠን ካለች መላው ዓለም ክፍት ሆኖላታል። ኦልጋ ከላይብራሪው አንድ አትላስ አወጣችና እላዩ ላይ አቀረቀረች። 'ለካስ ከሩሲያ ውጭ እንደዚህ ዐይነት ሰፊ ዓለም አለ!' ሰሜንና ደቡብ አሜሪካ.....እዚያ ድረስ

@BOOKALEM

ማለፍ አስፈራት። ወደ አውሮፓ ተመለከተች። ስዊዘርላንድ። 'አዎን እዚያ ነው የምሄደው!' አለች።

ለማንም ቢሆን አታምንለትም። ወደ ስዊዘርላንድ ለመሄድ የወሰነችው በአንድ ወቅት የስዊስ ቼኮላት ቀምሳ ቃናውንም ፈጽሞ መርሳት ስላልቻለች ነው። ጣፋጭ ነገሮችን ትወዳለች። የሩሲያ ከረሜላ ሲቀምሱት ስኳር የለሽና አስቸጋሪ ጣዕም ያለው ነው። አልጋ ለቼኮላት ያላት ዝንባሌ ሕይወቷን ሊያስከፍላት ነው።

በኤሮ ፍሎት የሶቭየት አየር መንገድ ወደ ዙሪክ ያደረገችው ጉዞ የደስታ ጅማሬ ነበር። ከዚህ ቀደም በአውሮፕላን በረራ አድርጋ አታውቅም። በከተማውና ባጠቃላዩ ዕይታ ወይም ትዕይንት በጣም ተደንቃ ነበር። በከተማው አውራ መንገዶች ላይ የሚዘዋወሩት ሰዎች በጣም ምርጥ የሆኑ ልብሶችን የለበሱና በአያሌው ውድ የሆኑ መኪኖችን የሚያሽከረክሩ ነበሩ። እያንዳንዱ ዙሪክ ውስጥ የሚገኝ ሰው ሁሉ ለአልጋ ሚሊየነር መስሎ ነው የታያት።

'እና ደግሞ መጋዘኖቹ!' ሳንሆፍስትራሰ ዋናው የመገበያያ ጎዳና ላይ ሽመታ አደረገች። በየመስኮቱ ላይ በተደረደሩት ውብ ሸቀጦች እጅግ ተደነቀች። ቀሚሶች፤ ጫማዎች፤ ጌጣጌጦችና ሳህኖች፤ የቤት ዕቃዎች፤ አውቶሞቢሎች፤ መጽሐፍት፤ ቴሌቪዥን፤ ራዲዮኖች፤ አሻንጉሊቶችና ፒያኖዎች ሁሉ ነበሩ። የሚሸጡት የሸቀጥ ዐይነቶች ሁሉ ማለቂያ የለሽ ሆኑባት። ከዚያም አልጋ በጣፋጭና በቼኮሌት ሸቀጡ በታወቀው ወደ ሰፕሩንግሊ ማዕከል አመራች። ዐይን በሚያጥበረብሩ የጣፋጭ ዐይነቶች ተሞልቷል። በትላልቅ የካርቶን ሳጥን የታሸጉ በልዩ ልዩ ቅርጽ የተሠሩ ቼኮላቶች፤ በቼኮሌት የተጠቀለሉ ፍሬዎች፤ ሌላም ሌላም ሞልቷል። አልጋ ሁሉንም ለመግዛት ተመኘችች። ነገር ግን የዋጋቸውን ውድነት ስትሰማ አንድ የተለያዩ ቼኮሌቶች ቅልቅልና ተለቅ ያለ ቆርቆሮ ውስጥ የታሸገ ከረሜላ ብቻ ሸመተች።

በሚቀጥለው ሳምንት አልጋ የዙሪክ ሆርን ፓርክን፤ የሪትበርግ ሙዚየምን፤ በአሥራ አንደኛው ክፍለ ዘመን የታነፀውን የግሮስ ሙንስተር ቤተ ክርስቲያንና በደርዘን የሚቆጠሩ ሌሎች የቱሪስት መስህብ የሆኑ ሥፍራዎችን ከጎበኘች በኋላ የጉብኝት ጊዜዋ አለቀ።

"የሰንሻይን ቱር ባስ ካምፓኒ ወደ አልፕስ የሚወስድ ጥሩ የጉብኝት ፕሮግራም አለው!" አላት ያረፈችበት የሌአነር ሆቴል ጸሐፊ። "ከመሄድሽ በፊት በዚህ ጉብኝት ብትደሰቺ ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ።"

"እመሰግናለሁ! እሞክራለሁ" አለች አልጋ።

አልጋ ከሆቴሉ እንደወጣች የሄደችው የስፕሩንግሊን የቼኮላት ሱቅ ለማየት ነበር። ቀጥሎ ደግሞ ወደ ሰንሻይን ቱር ባስደጋል ካምፓኒ ቢሮ ሄዳ በጉዞው ለመካፈል ተመዘገበች። ጉዞዋም በጣም አስደሳች መሆኑ ተረጋገጠ። የተፈጥሮው ውበት እይታ ትንፋሽ የሚያሳጥር ነበር። በዚህ ጉዞ ላይ አልጋ በራሪ

@BOOKALEM

ዲስክ ነው ብላ ያመነችበት ነገር ሲፈነዳ ተመለከተች። ነገር ግን አጠገቧ ተቀምጦ የነበረው የካናዳ ባንከኛ "ይህ ሆን ተብሎ የቱሪስቶችን አስተያየት ለመሳብ ሲባል በስዊስ መንግሥት የተዘጋጀ ትዕይንት ነው እንጂ በራሪ ዲስክ የሚባል ነገር የለም" ሲል አብራራላት። ኦልጋ በሰውዬው ንግግር ሙሉ በሙሉ ካለማመኗም በላይ ወደ አገሯ ኪየቭ እንደተመለሰች ጉዳዩን አንስታ ከአክስቷ ጋር ተወያየችበት።

"በእርግጥ በራሪ ዲስኮች አሉ?" "አዎ!" አለቻት አክስቷ። "ብዙ ጊዜ በመላው የሩሲያ ግዛት ላይ ይበራሉ። ታሪኩን ለሆነ ጋዜጣ መሸጥ ትችያለሽ።" ኦልጋ ነገሩን አሰበችበት። ሆኖም ግን ብናገር ይሳቅብኛል ብላ ፈራች። ፓርቲው አባላቱ የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት እንዲስቡ አይፈልግም። በተለይም ወደ አልባሌ ጉዳይ ውስጥ የሚያስገባ ከሆነ። "ሙሉ በሙሉ" አለች ኦልጋ። "ሙሉ በሙሉ ዲምትሪይና ኢቫን ካለመኖራቸው በስተቀር የጉበኝት ጉዞዬ የሕይወቴ ከፍተኛው እርካታ ነው!" ስትል ወሰነች። እንደገና መደበኛ ሥራዋ ላይ የማተኩሩ ጉዳይ አስቸጋሪ ሆነባት።

ከአየር ማረፊያ ወደ ማዕከላዊ ኪየቭ አዲስ በተሠራው ጎዳና ላይ "በኢንቱሪስት" አውቶቡስ የተደረገው ጉዞ አንድ ሰዓት ነበር የፈጀው።

ሮበርት ኪየቭን ሲረገጥ የመጀመሪያ ጊዜው ከመሆኑም በላይ በመንገድ ዳርቻዎች ላይ በሚደረገው የግንባታ (ኮንስትራክሽን) ሥራና በየአቅጣጫው በተገተሩት ትልልቅ የመኖሪያ ሕንጻዎች በጣም ተደነቀ።

አውቶቡሱ ከድኔፐር ሆቴል ፊት ለፊት ቆመና ሁለት ደርዘን መንገደኞች አራገፈ። ሮበርት ሰዓቱን ሲመለከት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ይላል። አሁን ላይብራሪው ዝግ ስለሚሆን የመጣበት ሥራ እስከንጋት መቆየት አለበት። ቀደም ሲል የተያዘለት ትልቅ ሆቴል ውስጥ ገባ። መጀመሪያ ጥቂት የአልኮል መጠጥ ከወሰደ በኋላ በነጭ ቀለም ያሸበረቀው የመመገቢያ አዳራሽ ውስጥ ገብቶ የዓሣ እንቁላል፤ ዝኩኒ እና ቲማቲም ከተመገበ በኋላ ሁለተኛ ዙር ላይ ድንች፤ የተከተፈ ሥጋና ሾርባ ተመግቦ ማሳረጊያውን ቮድካና የጋዝ ውሃ ቀረበለት።

ጄነራል ሒሊያርድ እንደነገረው የመግቢያ ቪዛው ስቶኮልም ሆቴል ነበር የጠበቀው። 'ይህ በመጠኑም ቢሆን ፈጣን የሆነ ዓለም ዓቀፋዊ ትብብር ነው። እኔ ግን ምንም ዐይነት ትብብር የለኝም።'

'ቃሉንም "እርቃን" ይሉታል' ሲል ሮበርት ከሐሳቡ ጋር ተጫወተ። ከእራት በኋላ ሮበርት እንግዳ መቀበያው ላይ ጥቂት መረጃዎችን ጠያየቀና ወደ ሌን ኮምሶሞል አደባባይ አመራ። ጥንታዊ ከሆኑት የሩሲያ ከተሞች አንዱ ኪየቭ በጣም ማራኪ የአውሮፓዊያን ዐይነት ቅያስ ያለው፤ በድኔፐር ወንዝ ደረጃ ላይ የተመሠረተ፤ አረንጓዴ መናፈሻ ሥፍራዎችና በዛፎች የተሰመሩ የመኪና መንገዶች ያሉት ከተማ ነው። በየቦታው በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ከመኖራቸውም በላይ

@BOOKALEM

ለሃይማኖታዊ እነጻ ግሩም የሆኑ ትእይንታዊ ምሳሌዎች ናቸው። የቅዱስ ቭላዳሞር፤ የቅዱስ አንድሪው፤ የቅድስት ሶፊያ አብያተ ክርስቲያናት ሲፕኑ የመጨረሻው ቤተ ክርስቲያን በ 1137 ዓ.ም የተጠናቀቀ ከመሆኑም በላይ ንፁህ ነጭ ቀለም ያለውና ወደ ሰማይ ከፍታው የዘለቀ ሰማያዊ የደወል ፎቅ ያለው ነው። እንዲሁም በከተማው ውስጥ ረዥም የሆነው የፔርቼስክ ጉዳም ይገኝበታል። 'ሱዛን ይሆን ሁሉ ባፈቀረችው ነበር!' ሲል አሰበ። ወደ ሩሲያ ጉብታ አታውቅም። 'ይሆን ጊዜ ከብራዚል ተመልሳ ይሆን?' ሲል አሰበ። ወደ ሆቴሉ እንደተመለሰ በድንገተኛ የስሜት መገፋፋት ተነሳስቶ ሰልክ ደወለላት። ይግረምህ ሲለውም ጥሪው ተላለፈለት።

"ሄ.....ሎ!" ያ ከጉሮሮ የሚወጣ ወሲባዊ ድምጽ።

"ሃይ! ብራዚል እንዴት ነበር?"

"ሮበርት ለእያሌ ጊዜ ደውዬ ላገኝህ ሞከሬ ነበር። መልስ አላገኘሁም። ለመሆኑ የት ነው ያለህው?"

"አገሬ አይደለም ያለሁት።"

"አህ! እንዴት ይሰማሃል? ደህና ነህ?" አለችው። የት እንዳለ ላለመጠየቅ በሚገባ ሠልጥናለች።

"በእርግጥ በጣም ደህና ነኝ። የገንዘብ ከረጢ.....ምንቴ ባንክስ እንዴት ነው?"

"በጣም ደህና ነው ሮበርት። ነገ ወደ ጂብራልታር ልናመራ ነው።"

'በገንዘብ ከረጢት የተረገመ ቀዛፊ የሞተር ጀልባ" አለና ለራሱ ድምጹን ከፍ አድርጎ "ሐልካዮን በተባለችው የሞተር ጀልባ?" አላት።

"አዎን። መርከቧ ላይ ልትደውልልኝ ትችላለህ። ቁጥሩን ታስታውሰዋለህ?"

ያስታውሰዋል። 'ደብሊው ኤስ 337። የሚወክለው ምንድነው? ወንደር ፉል ሱዛን.....ኋይ ስፖርት? ወይስ ዋይፍ ስቲለር?' አለ በሐሳቡ።

"አዎን አስታውሳለሁ። ውስኪ ስኳር 337 ነው።"

"ደህና መሆንህን ለማሳወቅ ትደውልልኛለህ?"

"በእርግጥ እደውልልሻለሁ። ሆኖም ስለተለየሁሽ አዝኛለሁ።"

ሕመም የተመላበት ረዥም ፀጥታ በመኻላቸው ሰፈነ። ለመሆኑ ምን እንድትለው ነበር የፈለገው? "እባክህ ከዚህ ፖል ኒውማንን ከመሰለ አስደሳች ሰው ከዚህ በባለ 250 ሜማ ረዥም ጀልባው አስገድዶ ካሳፈረኝና ምንቴ ካርሎ፤ ሞሮኮ፤ ፓሪስና ለንደን እንዲሁም ሌሎች እግዚአብሔር ብቻ በሚያውቃቸው አስከፊ ቤተ መንግሥቶቻቸው ውስጥ እንድንኖር ካደረገኝ ሰው በርረህ መጥተህ አድነኝ!" ትበለው? ልክ እንደ ቂል ይሆን ትላለች ብሎ ጠበቃት።

@BOOKALEM

"እኔም እንደዚሁ በጣም አጣሁህ ሮበርት። እባክህን ስለራስህ ተጠንቀቅ!" አለችውና ስልኩን ዘጋችው። ሩሲያ ውስጥ ብቻውን ቀረ።

አሥራ ሁለተኛ ቀን

ቤተ መጽሐፍቱ በጠዋት ከተከፈተ ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ሮበርት ግዙፍና የሚያምረው ሕንፃ ውስጥ ገባና ወደ እንግዳ መቀበያው ጠረጴዛ አመራ።

"እንደምን አደርሽ?"

"እንደምን አደርክ? ምን ልርዳህ?" አለች ከጠረጴዛው ኋላ የተቀመጠችው ሴት ቀና ብላ አየችውና።

"ኦልጋ የምትባል እዚህ ቦታ ትሠራለች ብዬ የምገምታት ሴት እየፈለኩ ነበር።"

"ኦልጋ? ለምን አለችን።" ወደሚቀጥለው ክፍል እያመለከተችው....."እዚያ ክፍል ውስጥ መሆን አለባት!" አለችው።

"አመሰግናለሁ።"

"ለካስ እንደዚህ ቀላል ነበር!" አለና ሮበርት በቡድን ተቀምጠው ከልባቸው የሚያጠኑ ተማሪዎችን አልፎ ወደ ተጠቆመው ክፍል አመራ። 'ለምን ዐይነት ሕይወት ይሆን የሚዘጋጁት?' ሲል ሮበርት ተደነቀ። አንዱ አነስተኛ የንባብ ክፍል ደረሰና ወደ ውስጥ ገባ። አንዲት ሴት መጽሐፍት ትደረድራለች።

"ይቅርታሽን" አለ ሮበርት።

ዘወር አለች። "አቤት!"

"ኦልጋ?"

"ኦልጋ ነኝ። ከኔ ምን ትፈልጋለህ?"

ሮበርት በሚማርክ ሁኔታ ፈገግ አለላት። "ፔሬስትሮይካን በተመለከተ የመደበኛው የሩሲያ ዜጋ ሕይወት ላይ ሊያስከትል ስለሚችለው ተጽዕኖ አንድ የጋዜጣ ጽሑፍ በማዘጋጀት ላይ ነኝ። ባንቺ ሕይወት ላይ ብዙ ልዩነት ፈጥሮ ይሆን?" ሲል ጠየቃት።

ሴትዬዋ ትከሻዋን ነቀነቀች። "ከጎርባቾቭ በፊት አፋችንን ለመክፈት እንፈራ ነበር። አሁን አፋችንን መክፈት እንችላለን። ነገር ግን አፋችን የምንከተው ምንም ነገር የለንም።"

ሮበርት ሌላ ዘዴ ሞከረ። "በእርግጥ አንዳንድ የተሻሉ ለውጦች አሉ። ለምሳሌ አሁን ለመጓዝ ችላችኋል።"

"ትቀልዳለህ መሰለኝ። ከባልና ከስድስት ሕፃናት ጋር ማነው ለመጓዝ የሚችለው?"

ሮበርት ቁፈራውን ቀጠለ። "እስካሁን ወደ ስዊዘርላንድ ተጉዘ....."

"ስዊዘርላንድ? በሕይወቴ ሙሉ ወደ ስዊዘርላንድ ተጉዤ አላውቅም።"

@BOOKALEM

"ወደ ስዊዘርላንድ በፍፁም ሄደሽ አታውቂም?" አለ ቀስ ብሎ።

"ነገርኩህ እኮ!" አለችና ጥቁር ፀጉር ወዳላት ሴት እያመለከተች....."ወደ ስዊዘርላንድ ለመሄድ የቻለች ዕድለኛ እርሷ ናት" አለችው።

ሮበርት በፍጥነት አየት አደረጋትና....."ስሟ ማነው?" አላት።

"አልጋ! ልክ እንደኔ" አለችው።

"አመሰግናለሁ!" አላት በረዥሙ ተንፍሶ።

ከአንድ ደቂቃ በኋላ ሮበርት ከሌላዋ አልጋ ጋር ውይይቱን ጀመረ። "ይቅርታ!" አለ ሮበርት። "ስለፔሬስትሮይካና በሩሲያዊያን ሕይወት ላይ ስላስከተለው ተጽዕኖ አንድ የጋዜጣ አንቀጽ በማዘጋጀት ላይ ነኝ።"

ቀና ብላ በጥንቃቄና በስጋት እያየችው....."አቤት?" አለችው።

"ስምሽ ማን ይባላል?"

"አልጋ። አልጋ ሮማንቻንኮ።"

"እስቲ ንገሪኝ አልጋ። ፔሬስትሮይካ ባንቺ ላይ ያመጣው ለውጥ አለ?" ከሰድስት ዓመታት በፊት አልጋ የውጭ አገር ዜጋ ለማነጋገር በጣም ትፈራ ነበር። አሁን ግን ተፈቅዷል። "በእርግጥ ብዙም ለውጥ የለውም። ሁሉም ነገር በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው" አለችው እየተጠነቀቀች።

እንግዳው ሰው አጥብቆ ጠያቂ ነበር። "በሕይወትሽ ውስጥ ምንም የተለወጠ ነገር የለም?"

እራሷ እየነቀነቀች....."የለም!" አለችውና በአርበኝነት መንፈስ ጨመር አድርጋ....."በእርግጥ ወደ ውጭ አገር ለመጓዝ ችለናል!" አለችው።

የተመሰጠ እየመሰለ....."እስካሁን ከአገርሽ ውጭ ተጉዘሻል?" አላት።

"አዎን!" አለችው በኩራት። አሁን በቅርቡ ወደ ስዊዘርላንድ ካደረኩት ጉዞ መመለሴ ነበር። በጣም ውብ የሆነች አገር ናት። ከብዙ ሰዎች ጋር ተገናኝቻለሁ። በአውቶቡስ ተሳፍሬ ወደ ከፍተኛው ተራራ አልፕስ ተጉዤያለሁ።" በድንገት አልጋ እንደዚህ መናገር እንደማይገባት አወቀች። ምናልባት እንግዳው ሰው ስለጠፈር መንኮራኩሩ ሊጠይቃት ይችላልና። ወደ ችግር ሊመራት ስለሚችል ስለዚህ ጉዳይ ለማውራት አትፈልግም።

"እርግጥ? እስቲ እባክሽ አውቶቡሱ ላይ ስለነበሩት ሰዎች ተርኪልኝ።"

በእፎታ ተነፈሰችና ወዲያው መለሰችለት። "በጣም ሀብታ ከመሆናቸውም በላይ አለባበሳቸው....." በእጇ አመለከተችው። "በጣም ሀብታሞች ናቸው። ሌላው ቀርቶ ካንተ አገር ዋና ከተማ ከዋሺንግተን ዲ.ሲ የመጣም ሰው አግኝቻለሁ።"

"ተገናኝተሻል?"

"አዎን። በጣም ግሩም ሰው ከመሆኑም በላይ ካርዱንም ሰጥቶኛል።"

የሮበርት ልብ በጉጉት ዘለለች። "ካርዱ አሁንም አለሽ?"

@BOOKALEM

“የለም ወረወርኩት። እንደዚህ ዐይነት ነገሮችን አለማስቀመጤ የተሻለ ነው።”

‘እርጉም!’ አለ ሮበርት በልቡ።

ቀጠል አደረገችና.....“ስሙን አስታውሰዋለሁ። ፓርከር ይባላል። ልክ እንደናንተ የአሜሪካ ብዕር። ኬቨን ፓርከር ይባላል። በጣም ጠቃሚ የሆነ የፖለቲካ ሰው ነው። እንደራሴዎች (ሴናተሮች) እንዴት ድምጽ እንደሚሰጡም ነግሮኛል።”

ሮበርት ያልጠበቀው መልስ ነው የሆነበት። “ይህንኑ ነው የነገረሽ?”

“አዎን። ብዙ ጉዞዎች ይወስዳቸዋል። ስጦታም ያደርግላቸዋል። ከዚያም የሱ ደንበኞች በሚፈልጋቸው ነገሮች ላይ ድምጽ ይሰጡለታል። አሜሪካ ውስጥ ዲሞክራሲ የሚሠራበት መንገድ እንደዚህ ነው።”

ለሚቀጥሉት አሥራ አምስት ደቂቃዎች አልጋን ቢያስለፈልፋትም ስለተቀሩት መንገደኞች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አልቻለም።

ሮበርት ከሆቴል ክፍሉ ለጀነራል ሒሊያርድ ስልክ አደረገ። “ሩሲያዊቷን ምስክር አግኝቻለሁ። ስሟ አልጋ ሮማንቻንኮ ሲሆን በኪየቭ ዋናው ቤተ መጽሐፍት ውስጥ ትሠራለች።”

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ለ–ጂ.አር.ዩ. ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
-8-አልጋ ሮማንቻንኮ–ኪየቭ
የመልዕክት መጨረሻ

ልክ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ አልጋ ሮማንቻንኮ ቤትሪክ ጎዳና ላይ ከሚገኘው የመኖሪያ አፓርመንቷ ሕንፃ ፊት ለፊት አንድ መኪና ጎማዎቹን ሲ....ጢ.....ጥ! አድርጎ ሲቆም ተሰማት። የአፓርትመንቱ ግድግዳዎች በጣም ስስ ከመሆናቸው የተነሳ በጎዳናው ላይ ያለውን ድምጽ ሁሉ መስማት ትችላለች። ከመኝታዋ ላይ ተነስታ ወደ መስኮቱ ሄዳ ወደ ውጭ ተመለከተች። ሁለት የሲቪል ልብስ የለበሱ ሰዎች የመንግሥት ባለሥልጣናት የሚጠቀሙበት ዐይነት ጥቁር ቻይካ መኪና ውስጥ ወጡና ወደ መኖሪያ አፓርትመንቷ መግቢያ መጡ። ገና ስታያቸው መላ ሰውነቷ በፍርሃት ራደ። ባለፉት ዓመታት ጥቂቶች ጎረቤቶቿ ዳግም ላይታዩ ቀልጠው ጠፍተው ቀርተዋል። አንዳንዶቹ ሳይቤሪያ ወደሚገኘው

@BOOKALEM

"ጉላግ" የግዙት ሠፈር ተግዘዋል። አልጋ 'በአሁኑ ጊዜ እነዚህ የምሥጢር ፖሊሶች ማንን ይሆን የሚያድኑት?' እያለች ስታስብ በሯ ተንኳኳና አስደነበራት። ከኒ ምንድነው የሚፈልጉት? ይህ አንድ ዐይነት ስህተት መሆን አለበት' አለች። በሯን ስትከፍት ሁለት ሰዎች ቆመው ነበር።

"አልጋ ሮማንቻንኮ?"

"አዎን!"

"ገላቭናዬ ራዝቬዳይባ ቴፐራቭ ሌናይ!"

'የተጠላው ጂ.አር.ዩ' አለች በሐሳቧ።

ገፍተዋት ወደ ውስጥ ገቡ።

"ምን.....ምንድነው የምትፈልጉት?"

"ጥያቄውን እኛ እንጠይቃለን። እኔ የሃምሳ አለቃ ዩሪ ግሮሞኮቭ ነኝ። ይህ ደግሞ የሃምሳ አለቃ ቭላድሚር ዜምስኪይ ይባላል።"

አልጋ ድንገት ሽብር ወረራት። "ምን አጠፋሁ? ምን አደረኩ?"

ዜምስኪ ጫን አደረገና....."እናም አንድ ስህተት መሥራትሽን ታውቂያለሽ?" አላት።

"የለም! በእርግጥ የለም!" አለች እየተንተባተበች። "እዚህ ለምን እንደመጣችሁ አላውቅም።"

"ቁጭ በይ!" አለና ግሮሞኮቭ ጮኸባት። አልጋ ተቀመጠች።

"በቅርቡ ወደ ስዊዘርላንድ ሄደሽ መመለስሽ ነው። አይደለም?"

"አዎ። ግ.....ግን ከባለሥልጣን ፈቃድ....."

"አልጋ ሮማንቻንኮ! ስለላ ግን ሕጋዊ አይደለም።"

"ስለላ?" ፍርሃት ወረራት። "ምን እንደምታወራ አላውቅም።"

ግዙፉ ሰውዬ ትኩር ብሎ ይመለከታት ስለነበር በጣም ስስ የሆነ የሌሊት ልብስ ብቻ እንደለበሰች ትዝ አላት።

"እንሂድ! ከኛ ጋር ትሄጃለሽ።"

"ግን በጣም ከፍተኛ የሆነ ስህተት አለ። እኔ የቤተ መጽሐፍት ሠራተኛ ላብራሪያን ነኝ። ማንንም ብትጠይቁ....."

ጎትቶ አነሳት። "በይ ቀጥይ!"

"የት ነው የምትወስዱኝ?"

"ወደ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት። ጥያቄ ሊያቀርቡልሽ ይፈልጋሉ።" በሌሊት ልብሷ ላይ ኮት እንድትደርብ ፈቀዱላትና በደረጃው እያንደረደሩ ወስደው ጥቁር ቮይካ ውስጥ ከተቷት። አልጋ ልክ እንደዚህ በመኪና እየተነዱ ተወስደው ቀልጠው ስለቀሩት ሰዎች ስታስብ ፍርሃት አደነዘዛት።

ግዙፉ ግሮሞኮቭ ነበር መኪናዋን የሚያሽከረክረው። አልጋ ከዜምስኪይ ጋር የኋላው ወንበር ላይ ተቀምጣለች። ምንም እንኳ ዜምስኪ ከግሮሞኮቭ ያነሰ

@BOOKALEM

አስፈሪ መስሎ ቢታያትም በማንነታቸውና ሊደርስባት በሚችለው ነገር ብቻ ተሸብራ ነበር።

"እባካችሁ እመኑኝ!" አለች አልጋ ከልቧ። "ፍጹም ቃሌን....."

"ዝጊ!" ሲል ግሮሞኮቭ ባረቀባት።

"ተመልከት። እሷ ላይ የምትጮህበት ምክንያት የለም። እንደአውነቱ ከሆነ እኔ አምኛታለሁ።"

አልጋ ልቧ በተስፋ ሲዘል ተሰማት።

"ጊዜው ተለውጧል" ሲል ጓድ ዜምስኪ ቀጠለ። "ጓድ ጎርባቼቭ እንደዚህ ንጹሃን ሰዎችን የማንገላታቱን ተግባር አይወዱትም። የዚህ ዐይነቱ ዘመን አልፏል።"

"ማነው እሷን ንፁህ ናት ያለው?" ሲል ግሮሞኮቭ አጉረመረመ። "ምናልባት ላትሆንም ትችላለች። ምንነቷን ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ውስጥ በቶሎ ያረጋግጣሉ።"

አልጋ ባለችበት ተቀምጣ ሁለቱ ሰዎች ልክ እንደሌለች አድርገው ስለእርሷ ሲወያዩ ታዳምጣለች።

"ስማኝማ ዩሪ!" አለ ዜምስኪይ። "ጥፋተኛ ሆነችም አልሆነች ወደ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ከወሰድናት ማመኗ የማይቀር ነው። ይህም ነገር ፈጽሞ አላስደሰተኝም።"

"በጣም መጥፎ ነገር ነው። ማድረግ የምንችለው ምንም ነገር የለም።"

"አዎን! አለ እንጂ።"

"ምን?"

ከአልጋ አጠገብ የተቀመጠው ሰው ለጊዜው ፀጥ አለ። "ስማ!" አለ ቀጠለና። "ለምን አንለቃትም? ቤቷ አላገኘናትም ብለን መናገር እንችላለን። ለአንድና ለሁለት ቀናት ትኩረታቸውን ከእርሷ ላይ እንዲያነሱ እናደርጋቸዋለን። ምክንያቱም ብዙ የሚመረምሯቸው ሰዎች አሉና።" አልጋ አንድ ነገር ለመናገር ሞከረች። ግን ጉሮሮዋ ደረቀባት። አጠገቧ የተቀመጠው ሰው ከርከሩን እንዲረታላት አጥብቃ ተመኘች።

"ለእርሷ ብለን አንገታችንን የምንሰጠው በምን ምክንያት ነው? ከዚህስ ምን እናገኛለን? እርሷስ ምን ታደርግልናለች?" ሲል ግርሞኮቭ አጉረመረመ።

ዜምስኪይ ወደ አልጋ ዘወር ብሎ በጥያቄ ዐይነት አስተያየት ተመለከታት።

አልጋ ድምጽዋ ተመለሰላት። "ምንም ገንዘብ የለኝም!" አለችው።

"እኛ ያንቺን ገንዘብ እንፈልጋለን? እኛ ለራሳችን ብዙ ገንዘብ አለን።"

"አንድ ነገር አላት! አለ ግሮሞኮቭ።"

@BOOKALEM

ኦልጋ መልስ ከመስጠቷ በፊት ዜምስኪ "ቆይ.....ቆይ!" አለ። "ዩሪ ኢቫኖቪች! ይህንን ታደርጋለች ብለህ መጠበቅ የለብህም።"

"የራሷ ጉዳይ ነው። ለኛ ጥሩ ሆኖ መገኘት ወይም ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት መሄድና ለአንድ ወይም ለሁለት ሳምንታት "ወፈ" መገልበጥ! ምናልባትም ቆንጆ ቀዝቃዛ ቤት ውስጥ ሊጨምሯት ይችላሉ!"

ኦልጋ "ስቺዞአ" በመባል ስለሚታወቁት ቀዝቃዛ ቤቶች ብዙ ሰምታለች። ማሞቂያ የሌላቸው፤ አራት በስምንት ጫማ ስፋት ያላቸውና የጣውላ አልጋ ያለብርድ ልብስ የተዘረጋባቸው ከፍሎች ናቸው። 'ለኛ ጥሩ ሆኖ መገኘት ምን ማለት ነው?'

"የራሷ ጉዳይ ነው።"

ዜምስኪይ ወደ ኦልጋ ዘወር አለና "ምን ማድረግ ነው የምትፈልጊው?" አላት።

"እኔ.....እኔ አልገባኝም።"

"ባልደረባዬ እንደሚለው ለኛ ጥሩ ሰው ከሆንሽልን ይህንን ጉዳይ እርግፍ አርገን እንተወዋለን። ከትንሽ ጊዜ በኋላም ምናልባት ያንቺን ጉዳይ ይረሱት ይሆናል።"

"ምን.....ምንድነው ማድረግ ያለብኝ?"

ግሮሞኮቭ ወደ ኋላ በሚያሳየው መስተዋት እያያት ፈገግ አለና "ጥቂት ጊዜሽን ብቻ ስጭን" አላት። አንድ ከዚህ ቀደም ያነበበው ምንባብ ትዝ አለው። ""ዝም ብለሽ ተንጋለይና ስለዘሩ አስቢ!" ፈገግ አለ።

በድንገት ኦልጋ ሰዎቹ ወዴት እያመሩ እንደሆነ ተገነዘበች። ራሷን ነቀነቀችና....."የለም! አላደርገውም!" አለች።

"ትከክል!" አለና ግሮሞኮቭ መኪናውን በፍጥነት ማብረር ጀመረ። "ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ካንቺ ጋር ጥሩ ጊዜ ያሳልፋሉ።"

"ቆይ!" አለች ኦልጋ በድንጋጤ ተውጣና ምን ማድረግ እንዳለባት ባለማወቅ። ስለታሰሩትና ምርመራ ስለተደረገባቸው ሰዎች አሸባሪ ታሪኮችን ሰምታለች። ይህ ሁሉ ያከተመ መስሏት ነበር። ነገር ግን ፔሬስትሮይካ ገና የሕልም እንጀራ ነበር። ጠበቃ እንድትይዝ ወይም ማንንም እንድታነጋግር አይፈቅዱላትም። ባለፉት ጊዜያት ጓደኞቿ በጂ.አር.ዩ. ተይዘው የግዳጅ ግንኙነት እየተፈፀመባቸው ተገድለዋል። እሷም በወጥመድ ተይዛለች። ወደ ዘብጥያ ከወረደች ለአንድ ወይም ሁለት ሳምንታት እየደበደቡና የግዳጅ ግንኙነት እያደረጉባት ወይም የከፋ ነገር እየፈፀሙባት ሊያቆዩዋት ይችላሉ።

ለእነዚህ ሁለት ሰዎች ብቻ ከሆኑ ግን ጣጣው ቶሎ ይፈፀምና ሊለቋት ይችላሉ።

@BOOKALEM

"እሺ!" አለች አልጋ በሐዘን ተኮማትራ። "ወደ አፓርትመንቴ መመለስ ትፈልጋላችሁ?"

"ሌላ የተሻለ ቦታ አውቃለሁ" አለና ግሮሞኩቭ መኪናውን አዙሮ መዳት ጀመረ።

"በጣም ነው የማዝነው። ኋላፊው እርሱ ስለሆነ ላቆመው አልችልም" ሲል ዜምስኪይ ሹክ አላት። አልጋ መልስ አልሰጠችውም።

በመብራት የደመቀውን የሼቭቼንኮ ኦፔራ አዳራሽ አልፈው በዛፎች ወደተከበበ አንድ ትልቅ የመናፈሻ ሥፍራ አመሩ። ግሮሞኩቭ መኪናውን አንድ ትልቅ ዛፍ ሥር አቆመና መብራቶቹን አጠፋ። ወቅቱ በጣም ጭር ብሎ ነበር። "እንውጣ!" አለ።

ሦስቱም ተያይዘው ከመኪናዋ ወጡ።

"በጣም ዕድለኛ ነሽ!" አለ ግሮሞኩቭ አልጋን እየተመለከተ። "በቀላሉ እንለቅሻለን። አንቺም በዚህ ትደሰቻለሽ ብዬ አምናለሁ።"

በፍርሃት ለመናገር ተስኗት እንገቷን ብቻ ወዘወዘች። ግሮሞኩቭ አንድ ግልጽ ሥፍራ እየመራ ወሰዳቸው። "በይ ልብስሽን አውልቂ!"

በጣም ይበርዳል። እኛ.....?

ግሮሞኩቭ ፊቷን በኃይለኛ ጥፊ ኢጋያት። ሐሳቤን ከመለወጤ በፊት እንደተነገረሽ አድርጊ። አልጋ ለደቂቃ አቅማማችና ጥፊውን እንደገና ሊሰነዝር ሲል ኮቷን መፍታት ጀመረች።

"አውልቂው!" አውልቃ መሬት ላይ ጣለችው።

"አሁን ደግሞ የሌሊት ልብስሽን አውልቂ።"

አልጋ በዝግታ የሌሊት ልብሷን ከራሷ በላይ አወለቀችና በጨረቃዋ ብርሃን በውርጭ እየተንዘፈዘፈች እርቃኗን ቆመች።

"ግሩም የሆነ ሰውነት!" አለና ግሮሞኩቭ ጡቷን ጨበጠው።

"እባክህ....."

"አንዳች ድምጽ ብታሰሚ ወደ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ነው የምንወስድሽ!" አለና ወደ መሬት ገፋት።

'ስለዚህ ነገር አላስብም። ስዊዘርላንድ ውስጥ የተፈጥሮውን ውበት በመመልከት ላይ እንዳለሁ አስባለሁ.....'

ግሮሞኩቭ የውስጥ ሱሪውን አወለቀና እግሮቿን ከፈታቸው።

'የአልፕስ ተራራ በበረዶ ተሸፍኖ ይታየኛል። አንዲት ልጃገረድና አንድ ልጅ ቢጋሪ ሲንሸራሸሩ ይታየኛል።'

በእጆቹ ዳሌዋን ጠበቅ አድርጎ ይዞ ሲጫናት ተሰማት።

'በአውራ ጎዳናው ላይ የተዋቡ መኪናዎች ይሽከረከራሉ። በሕይወቴ ሙሉ ካየኋቸው መኪናዎች ሁሉ የበለጡ። ስዊዘርላንድ ውስጥ ሁሉም ሰው የቤት መኪና አለው።'

እላይዋ ላይ ያለው ሰው የእንሰሳት ዐይነት ማቃተት ድምጽ እያሰማ ነበር።

@BOOKALEM

'የስዊስ ሕዝብ ቻሌት የሚላቸውን ዐይነት አነስተኛ መኖሪያ ቤት በተራራው ላይ ይኖረኛል። እናም ሁልጊዜ በሳጥን የተሞሉ ቼኮሌቶች ይኖሩኛል።'

ግሮሞኮቭ በከባዱ እየተነፈሰ ከላይዋ ላይ ተነሳና "ዜምስኪይ! ተራው ያንተ ነው!" አለው።

'ባል አገባና ልጆች ወልጄ በክረምቱ ወራት በአልፕስ ተራራዎች ላይ ለበረዶ ሸርተቴ ጨዋታ እንሄዳለን።'

ዜምስኪይ ተጋደመባት።

'በጣም ማራኪ የሆነ ሕይወት ይኖረኛል። ወደ ሩስያ በፍጹም.....በፍጹም.....'

ሰውየው ከመጀመርያው የበለጠ እየጎዳት ነው።

'በጣም ውብ የአበባ ሥፍራ ባለው ፀጥተኛና ሰላማዊ እርሻ ላይ እንኖራለን.....።' አልጋ ሌላ ነገር ማሰቧን ቀጠለች።

ዜምስኪይ ጉዳዩን ጨርሶ ቀና አለና ወደ ባልደረባው ተመለከተ።

"ተደስታለች ብዬ እገምታለሁ!"

"እጆቹን ወደ አልጋ ላከና አንገቷን ጠምዝዞ ሰበረው።"

በማግስቱ ጠዋት የከተማው ጋዜጣ አንዲት ሴት የግዳጅ ግብረ ሥጋ ከተፈፀመባት በኋላ ተገድላ መገኘቷን የሚያወሳ ዘገባ ይዞ ወጣ። ባለሥልጣናት "በምሽት ሴቶች ብቻቸውን ወደ መናፈሻ ሥፍራ መሄድ በጣም አደገኛ ነው!" ሲሉ አስጠነቀቁ።

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ጂ.አር.ዩ. ለ–ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል
ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
-8-አልጋ ሮማንቻንኮ–ኪየቭ ተወግዳለች
የመልዕክት መጨረሻ

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

ዊላርድ ስተን እና ሞንቴ ባንክስ ተፈጥሮአዊ ጠላቶች ነበሩ። ሁለቱም ሰዎች ጨካኝ ዘራፊዎች ሲሆኑ የሚጋደሉበት ደን "ዎል"ስትሪት""በመባል የሚታወቀው የኒው ዮርክ የንግድ ሥፍራ ነበር።

ሁለቱ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የተጋጩት አንድ ትልቅ የከተማ አገልግሎት መስጫ ኩባንያ ለመያዝ በሚሞክሩበት ጊዜ ነው። ዊላርድ ስተን የመጀመሪያውን የመነሻ ዋጋ ሰነዘረ። ችግር ይገጥመኛል ብሎ አልገመተም። ኃያልና ዝናው የሚያስፈራ ሰው በመሆኑ በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው ሊቀናቀኑት የሚደፍሩት። ታዲያ አንድ ወጣት ጀማሪ ጨረታውን ሲፎካከረው ሲመለከት በጣም ተገረመ። ዊላርድ ስተን የጨረታውን ዋጋ ከፍ ለማድረግ ተገደደ። ተፎካካሪውም አብሮት ከፍ በማድረግ ጨመረ። በመጨረሻ ዊላርድ ስተን ኩባንያውን ለመቆጣጠር ቢችልም እከፍለዋለሁ ብሎ ከገመተው በጣም በላቀ ዋጋ ነበር ያገኘው።

ከስድስት ወራት በኋላም በአንድ ኤሌክትሮኒክስ ኩባንያ ግዢ ጨረታ ላይ ዊላርድ ስተን እንደገና ከሞንቴ ባንክስ ጋር ተፋጠጠ። ጨረታው ወደ ላይ እየናረ ወጣና ሞንቴ ባንክስ አሸነፈ። በሚቀጥለው ጊዜ ዊላርድ ስተን በአንድ የኮምፒውተር ኩባንያ ግዢ ጨረታ ላይ ወጣቱ ሞንቴ ባንክስ ሊፎካከረው እንደተዘጋጀ ሲረዳ 'ባላንጣዬን የማነጋገሪያው ጊዜ አሁን ነው!' ሲል ወሰነ። ሁለቱ ሰዎች ገለልተኛ በሆነው የባሃማስ ፓራዳይስ ደሴት ምድር ላይ ተገናኙ። ዊላርድ ስተን የባላንጣውን የመደብ ጀርባ በሚገባ አስጠንቶ ነበር የመጣው። ታሪኩም እንደሚያስረዳው ሞንቴ ባንክስ በጣም ባለጸጋ ከሆነ የዓሣ ዘይት አምራች ኩባንያ ቤተሰብ የተገኘ ሲሆን ያገኘውን ውርስ እጅግ በጣም ግዙፍ ወደ ሆነ ዓለም አቀፋዊ ውሁድ ኩባንያ ሊያሳድገው የቻለ ሰው ነው።

ሁለቱ ሰዎች ለምሳ ገበታ ላይ ተቀመጡ። ሽማግሌውና ብልሁ ዊላርድ ስተን። ወጣቱና በጉጉት የተሞላው ሞንቴ ባንክስ።

ዊላርድ ስተን ውይይቱን ጀመረ። "የመቀመጫ ውስጥ ሕመም ነው የሆንክብኝ!" አለው ሞንቴ ባንክስን።

"ይህ አነጋገር ካንተ ከተገኘ በጣም ትልቅ አድናቆት አገኘሁ ማለት ነው!" ሲል መለሰለት።

"ምንድነው የምትፈልገው?" ሲል ስተን ጠየቀ።

"ልክ እንዳንተ የዓለም ባለጉብረት መሆን።"

ዊላርድ ስተን አሰብ አደረገና....."አዎን ትልቅ ዓለም ነው!" አለ።

"ይህ ማለት?"

@BOOKALEM

"ለሁለታችንም በቂ የሆነ ሥፍራ አለ።"

ከዚያን ዕለት ጀምሮ ሁለቱ ሰዎች ሽርካዎች ሆኑ። እያንዳንዳቸው የራሳቸውን የንግድ ሥራ በተናጠል ይመራሉ። የርስት ወይም የእንጨት ማምረቻ ጉዳይ ሲመጣ ሁለቱም ቢጋራ በእንድነት ይደራደራሉ። አይፎካከሩም። ብዙ ጊዜ የፍትሕ ሚንስትር ሁለቱ ሰዎች በጋራ ንብረትን በኃይል ለመጠቅለል (ሞኖፖሊ) የሚያደርጉትን የንግድ ስምምነት ለማስቆም ሞክሮ ነበር። ነገር ግን ዊላርድ ስቲን ከባለሥልጣናት ጋር ያለው ግንኙነት ያየለ ነበር። ሞንቴ ባንክስ ደግሞ የተመሠረተበት ክስ በማይታወቅ ምሥጢራዊ ሁኔታ ውድቅ ይሆናል። ሁለቱም የማይለዋወጥ የተዋጣለት ግንኙነት ነበራቸው።

የዱምዝዴይ (የፍርድ ቀን) ዘመቻ ለሁለቱም ሰዎች በጣም ተስማሚ በመሆኑ በጥልቀት ተሳትፈውበታል። እስከዛሬ ድረስ ካደረጉት የንግድ ተሳትፎ ሁሉ እጅግ በጣም አትራፊ የሆነ በአማዞን ሽለቆ ውስጥ የሚገኝ በዛፎች የበለፀገ አሥር ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ መሬት ግዢ ስምምነት ሊያጠናቅቁ ተቃርበዋል። በመንገዳቸው ላይ ምንም ዐይነት መሰናክል እንዲገጥማቸው አይሹም።

ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

አሥራ ሦስተኛ ቀን

ዋሺንግተን ዲሲ

የዩናይትድ ስቴት እንደራሴዎች ምክር ቤት ኃይለኛ በሆነ ጉባኤ ላይ ሲሆን የኡታሁ እንደራሴ መድረኩን ይዞ ነበር።

".....እና በተፈጥሮ ሀብታችን ላይ ብሔራዊ ውርደት እየተፈጸመ ነው። አባቶቻችን ያወረሱንን ብርቅ የተፈጥሮ ሀብት የማዳኑን ቃለ መሃላ መጠበቅ አሁን ነው። ቃለ መሃላ የፈፀምንበት ተግባራችን ብቻ ሳይሆን መሬቱን አየሩን እና ባሕሩን በስግብግብነት በማጥፋት ላይ ካሉት ስስታም ሰዎች መከላከል መብታችንም ጭምር ነው። እናስ ይህንን እያደረግን ነው? በሁሉም ዐይነት መንፈስ የሚቻለንን እያደረግን ነው።"

ኬቨን ፓርከር በንብኝዎቹ አዳራሽ ውስጥ ተቀምጦ በአምስት ደቂቃ ውስጥ ለሦስተኛ ጊዜ የእጅ ሰዓቱን ተመለከተ። 'ንግግሩ ያን ያህል ጊዜ ቆይቶ ይሆን?' ሲል ተገረመ። እዚህ የተቀመጠው ከእንደራሴው ጋር ምሳ ስለተመገበና አንድ የሚፈልገው ውለታ ስላለ ነው። ኬቨን ፓርከር ከእንደራሴዎችና ከምክር ቤት ሰዎች ጋር በወዳጅነት እየተጫወተ የፖለቲካ ውለታ ለማግኘት ሊጋስ እጅጉን በመዘርጋት ወደ ላይ ለመውጣት ይጥራል።

@BOOKALEM

ኢውጌን አሬጎን በተባለ ሥፍራ በድህነት ነው ያደገው። አባቱ አነስተኛ የእንጨት ማምረቻ የነበረው የአልኮል ሱሰኛ ነበር። ስኬታማ የነበረው ንግዱ ወደ ኪሳራ የወረደበት የተሳሳተ የንግድ ሰው ነበር። ወጣቱ ኬቨን እናቱ ከዓመታት በፊት ከሌላ ወንድ ጋር በመኮብለሏ ገና በአሥራ አራት ዓመቱ ወደ ሥራ ለመሰማራት ተገደደ። የቤተሰብ ሕይወት ፈጽሞ አልነበረውም። እንደአባቱ ወድቆ ከመቅረት ያዳነው ነገር ቢኖር የውበቱ ግርማ ሞገስ ብቻ ነበር። ነጣ ያለ ቡናማ ፀጉርና ከብዙ ዓመታት በፊት ከሞተ ዝርያው የወረሰው የሸዦዎች ዐይነት ገጽታ ነበረው። ለልጁ ሐዘኔታ የሚሰማቸው አንዳንድ ሰዎች አነስተኛ ሥራዎችና የሞራል ድጋፍ በመስጠት ይረዱት ጀመር። ጄቭ ጎድስፔል የተባለ የከተማው ታላቅ ሀብታም ሰው ኬቨንን ለመርዳት የተለየ ጉጉት ስላደረሰበት ከኩባንያዎቹ በአንዱ የትርፍ ሰዓት ሥራ ሰጠው። ወንደላጤው ጎድስፔል ወጣቱን ኬቨንን ብዙ ጊዜ ማታ ማታ ለእራት መኖሪያ ቤቱ ይጋብዘዋል።

"በሕይወት ውስጥ በጣም ትልቅ ሰው ልትሆን ትችላለህ። ግን ያለደጋፊ ጓደኛ ሊሳካልህ አይችልም" አለው ጎድስፔል።

"አውቃለሁ ጌታዬ! የእርሶን ወዳጅነት በጣም ነው የማደንቀው። እርሶን ማገልገል በእርግጥ ሕይወቴን ማዳን ማለት ነው።"

ከእራት በኋላ ሳሎኑ ውስጥ ምቹ ወንበር ላይ ተቀምጠው ነበር የሚወያዩት። "ከዚህ የበለጠ ብዙ ነገር ላደርግልህ እችላለሁ!" አለ ጎድስፔል። እጁን በወጣቱ ልጅ ትከሻ ላይ ጣል አድርጎ ትከሻውን ጨመቅ እያደረገ....."ብዙ ነገር!" አለው። "በጣም ግሩም የሆነ ሰውነት እንዳለህ ታውቃለህ?"

"አመሰግናለሁ ጌታዬ!"

"ብቸኛ ሆነህ ታውቃለህ?"

"አዎን ጌታዬ ሁልጊዜ ብቸኛ ነበርኩ።"

"ደህና! ካሁን በኋላ ብቸኛ መሆን የለብህም።" የልጁን እጅ ዳበሰ አደረገው። "ታውቃለህ? እኔም ብቸኛ ነኝ። አንድ ምቾት የሚሰጥ ሰው ያስፈልግሃል።"

"አዎን ጌታዬ!"

"የልጃገረድ ጓደኛ ይዘህ ታውቃለህ?"

"ከሱኤለን ጋር ለጥቂት ጊዜ ወጥቻለሁ።"

"ከሷ ጋር ተኝተህ ታውቃለህ?"

ልጁ ፊቱ ቀላ። "የለም ጌታዬ።"

"ስንት ዓመትህ ነው ኬቨን?"

"አሥራ ስድስት ጌታዬ!"

@BOOKALEM

"እንድ ሙያ ልትጀምር የሚገባበት ታላቅ ዕድሜ ነው።" ለተወሰነ ጊዜ ልጁን በዝምታ አጠናው። "በፖለቲካው መስክ ጥሩ ዝንባሌ አለህ ብዬ እወራረዳለሁ።"

"ፖለቲካ? ስለዚህ ዐይነቱ ነገር ምንም አላውቅም ጌታዬ።"

"አየህ? ለዚህም ነው አንዳንድ ነገሮችን ለማወቅ ወደ ትምሕርት ቤት መሄድ የሚገባህ። እኔም ልረዳህ ነው።"

"አመሰግናለሁ።"

"ሰዎችን ለማመስገን ብዙ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ" አለ ጎድስፔል። የልጁን ጭን ያሻሸው ጀመር።

"ብዙ ዘዴዎች!" አለና በድጋሚ የፓርከርን ዐይኖች እያየ..... "ገባህ?" አለው።

"አዎን ዴቭ!"

አጀማመሩ እንዲህ ነበር።

ኬቨን ፓርከር ከቸርችል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት እንደተመረቀ ጎድስፔል ደግሞ ኬቨን አስፈላጊ ከሆኑ ሰዎች ጋር እንዲገናኝ አደረገ። ሁሉም ሰው ወጣ በሆነው ልጅ ይመሰጥ ነበር። ባለው ግንኙነት መሠረት ፓርከር ለትላልቅ ሰዎች ለመሥራትና ሰዎችን ለመቀራረብ ከመቻሉም በላይ ዋሺንግተን ኮንግረስ ውስጥ በሎቢስትነት ማገልገል አመቺ የሆነ መንገድ ከመሆኑም በላይ ፓርከርም ለሥራው ተስማሚ ሆኖ ተገኘ።

ጎድስፔል ከሁለት ዓመታት በፊት ሲሞት ፓርከር በወቅቱ አስተማሪው ያስተማረውን ችሎታና ዝንባሌ በሚገባ ወርሶ ነበር። ወጣት ወንዶች ልጆችን ወደማይታወቅ ወጣ ያለ ሆቴል በመውሰድ መዝናናት ይወዳል።

የኡታሁ እንደራሴ የመጨረሻ ንግግሩን እያገባደደ ነበር። "አሁን የማሳስባችሁ የቀረውን የተፈጥሮ ሀብታችንን ለማትረፍ ከፈለግን ይህንን ሐሳብ ማሳለፍ እንደሚገባን ነው። አሁን ስለምንጫወተው ሚና ድምጽ እንዲሰጥ እንጠይቃለን።"

'እግዚአብሔር ይመስገን ማለቂያ የለሹ ውይይት በመጨረሻ ተገባደደ።' ኬቨን ፓርከር ከፊቱ የተደቀነውን ምሽት ሲያስበው ስሜቱ ጋለ። ባለፈው ምሽት አንድ ወጣት ወንድ ልጅ በ -ፒ- ጎዳና ላይ ከሚገኝ ታዋቂ የወንዶች ቡና ቤት አግኝቶ ነበር። እንደአለመታደል ሆኖ ልጁ ከሰው ጋር ነበር። ቢሆንም ምሽቱን ሁሉ ሲተያዩ ከቆዩ በኋላ ፓርከር ከቡና ቤቱ ከመውጣቱ በፊት ማስታወሻ ቢጤ ጽፎ የልጁ እጅ ላይ ሊሸጉጥለት ችሏል። "ነገ ማታ" ብቻ ነበር የሚለው። ልጁም ወረቀቱን አየት አድርጎ ፈገግ አለ።

ኬቨን ፓርከር ወደ ውጭ ለመውጣት በችኮላ እየለባበሰ ነበር። ልጁ ሲመጣ ቡና ቤቱ ውስጥ ለመገናኘት ፈልጓል። ወጣቱ ልጅ በጣም ማራኪ ስለሆነ

@BOOKALEM

በሌላ ሰው እንዳይወሰድበት ሰግቷል። የክፍሉ በር ተደወለ። "የተረገመ!" አለና ፓርከር በሩን ከፈተው።

አንድ እንግዳ ሰው ቆሞ ነበር። "ኬቨን ፓርከር?" ሲል ጠየቀ።

"አዎን።"

"እኔ ቤላሚ እባላለሁ። ለአንድ ደቂቃ ያህል ላነጋግርህ እፈልጋለሁ ።"

"ከጸሓፊዬ ጋር ቀጠሮ ማስያዝ አለብህ" አለ ፓርከር ትዕግስቱን ጨርሶ። "ከሥራ ሰዓት ውጭ ስለሥራ ጉዳይ መነጋገር አልሻም።"

"ይህ ስለሥራ ጉዳይ አይደለም ሚስተር ፓርከር። ከሁለት ሳምንታት በፊት ወደ ስዊዘርላንድ ያደረከውን ጉዞ በተመለከተ ነው።"

"ወደ ስዊዘርላንድ ያደረኩት ጉዞ? ስለሱ ምን ተገኘ?"

"የኔ ድርጅት እዚያ ጉዞ ላይ ስለተገናኘሃቸው ሰዎች ለማወቅ ይፈልጋል" አለና ቤላሚ የሐሰት የሲአይኤ መታወቂያውን አሳየው።

ኬቨን ሰውዬውን በጥንቃቄ ተመለከተው። 'ሲአይኤ ከኔ የሚፈልገው ምንድነው? መቼም እግዚአብሔር የረገማቸው አነፍናፊዎች ናቸው።'

ሰውዬውን በመቃረን ምንም የሚጎኝ ነገር የለም። ፈገግ አለና.....ወደ ውስጥ ግባ!" ሲል ጋበዘው። "አንድ በጣም አጣዳፊ የሆነ ቀጠሮ አለብኝ። ቢሆንም ግን ይህ ያንተ ጉዳይ ከአንድ ደቂቃ በላይ አይፈጅም ነው ያልከው።"

"አዎን አይፈጅም። ከዙሪክ ውጭ በአውቶቡስ ለጉብኝት ተጉዘሃል?"

ኬቨን በሐሳቡ.....'ቢቃ ጉዳዩ ይኸው ነው። የዚያ የበራሪ ዲስክ ጉዳይ።' ካያቸው እግዚአብሔር የረገማቸው ነገሮች አንዱ እሱ ነበር። "ስለ ያልታወቀው በራሪ ዲስክ ለማወቅ ትፈልጋለህ አይደል? ደህና ልነግርህ የምፈልገው ያልተለመደ ገጠመኝ መሆኑን ነው።"

"ሊሆን ይችላል። ግን ግልጽ ለመሆን እኛ የሲአይኤ ሰዎች በበራሪ ዲስክ አናምንም። እኔ እዚህ የተገኘሁት በአውቶቡሱ አብረውህ ስለተጓዙት መንገደኞች ለማወቅ ነው።"

ፓርከር ያልጠበቀው ነገር ነው የሆነበት። "ደህና! ልረዳህ አልችልም ብዬ አሰጋለሁ። ሁሉም ለእኔ እንግዶች ነበሩ።"

"ይገባኛል ሚስተር ፓርከር!" አለ ሮበርት በትዕግስት። ግን ስለነሱ አንድ የምታሳውሰው ነገር ይኖራል።"

ፓርከር ትከሻውን ከፍና ዝቅ አደረገ። "ደህና ጥቂት ነገሮችን አስታውሳለሁ። ፎቶግራፋችንን ካነሳ አንድ እንግሊዛዊ ሰው ጋር ጥቂት ቃላት መለዋወጤን አስታውሳለሁ።"

'ማዘር ሼድ ሌላ ማን ይሆናል?' አለ በሐሳቡ።

"አህ!" አለ። "አዎን ከአንዲት ሩሲያዊት ልጃገረድ ጋርም ተነጋግሬያለሁ። ደስተኛ ትመስላለች። አንድ የሆነ ቦታም በላይብራሪነት የምትሠራ ይመስለኛል።"

@BOOKALEM

'አልጋ ሮማንቻንኮ' "በጣም ግሩም ነው። ሌላስ የምታስታውሰው አለ ሚስተር ፓርከር?"

"የለም.....ይመስለኛል.....አህ! አንድ አሜሪካዊ ነበር። ቴክሳን።"

'ዳን ዋይን' "እና ሌላውስ?"

"የሁንጋሪያ ተወላጅ ነው። ሁንጋርያ ውስጥ የካሪኒቫል ይሁን የሰርከስ ባለቤት ነው።" ድንገት ኬቨን ትዝ አለው። "አዎን! ካርኒቫል ነው።"

"እርግጠኛ ነህ ሚስተር ፓርከር?"

"አ! አዎን። ስለካርኒቫል ሥራዎች አንዳንድ ታሪኮችን ነግሮን ነበር። ያንን በራሪ ዲስክ በመመልከቱ በእርግጥ ተደስቶ ነበር። እርግጠኛ ነኝ በራሪው ነገር ቢኖረው ኖሮ በካርኒቫል ትዕይንቱ ውስጥ በተጨማሪነት ያቀርበው ነበር። አስፈሪ የሆነ ትዕይንት እንደነበር አምናለሁ። ሪፖርት ማድረግ ይገባኝ ነበር። ነገር ግን በራሪ ዲስክ ዐይተናል ከሚሉ ሰዎች ጋር ለመቀላቀል አልፈለኩም ነበር።"

"ስሙን ነግሮህ ነበር?"

"አዎን። ግን ለመጥራት በጣም አስቸጋሪ የሆነ የውጭ አገር ሰው ስም ነው። አላስታውሰውም ብዬ እሰጋለሁ።"

"ሌላስ ስለሰውዬው የምታስታውሰው ነገር አለ?"

"ወደ ካርኒቫሉ ለመመለስ መቻኮሉን ብቻ።" ሰዓቱን መልከት አደረገና....."ላደርግልህ የምችለው ነገር አለ?" አለው። "ለቀጠሮዬ እየዘገየሁ ነው።"

"የለም አመሰግናለሁ ሚስተር ፓርከር። በጣም ነው የረዳህኝ።"

"ደስታዬ ነው።" ለሮበርት ውብ የሆነ ፈገግታ አሳየው። "አንድ ቀን ወደ ቢሮዬ ደረስ ብለህ ልታገኘኝ ይገባሃል። ግሩም የሆነ ጨዋታ ይኖረናል።"

"አደርገዋለሁ" አለ ሮበርት።

'ወደ መገቢያዬ ነው!' ሲል ሮበርት አሰበ። ሥራዬን ተቀብለው አሸቀንጥረው ሊወረውሩት ይችላሉ። "የሕይወቴን ቁርጥራጩን ሁሉ አንስቼ እንደገና የምጀምርበት ጊዜ አሁን ነው።!'

ሮበርት ለጄነራል ሒሊያርድ ስልክ አደረገ። አሁን ገና ደረስኩበት ጄነራል። ኬቪን ፓርከር የተባለ ምስክር አግኝቻለሁ። ዋሺንግተን ኮንግረስ ውስጥ ሠራተኛ ነው። የመጨረሻውን ምስክር ለማጣራት መንገድ መጀመሪ ነው።

"በጣም ተደስቼብሃለሁ" አለ ጄነራል ሒሊያርድ። "በጣም ግሩም የሆነ ሥራ ነው ያከናወንከው ኮማንደር። በተቻለህ መጠን በፍጥነት ወደኔ ተመልሰህ እንድትመጣ።"

"አዎን ጌታዬ!"

@BOOKALEM

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
የብሔራዊ ፀትጥታ ወኪል ለ–ሲ. አይ.ኤ. ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
-9-ኬቪን ፓርከር- ዋሺንግተን ዲ.ሲ
የመልዕክት መጨረሻ

ኬቨን ፓርከር በ -ፒ- ጎዳና የሚገኘው ዳኒ ቡና ቤት ሲደርስ ካለፈው ምሽት በበለጠ በሰው ተጣቦ አገኘው። ጠና ጠና ያሉት ሰዎች ወግ አጥባቂ ሙሉ ልብሶችን ሲለብሱ ወጣቶች ደግሞ በጂንስና በቡት ጫማዎች ነበሩ። በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ያለአግባብ የቆዳ ልብሶችን የለበሱ ሲገኙ 'እነዚህኛዎቹ አሳፋሪዎች ናቸው' ሲል ፓርከር አሰበ። የፓርከር መመሪያ "ምን ጊዜም ምሥጢራዊነት" የሚል ነበር። ወጣቱ ልጅ ቡና ቤቱ ውስጥ አልነበረም። ፓርከርም ይኖራል ብሎ አልጠበቀም። ሌሎቹ ከደከማቸውና ካላባቸው በኋላ ንፁህና ውብ ሆኖ ይገባል። ኬቨን ፓርከር ወደ ባንኮኒው ሄዶ መጠጥ አዘዘና ዙሪያውን ተመለከተ። በግድግዳው ላይ የተሰቀሉ ቴሌቪዥኖች የኤም.ቲ.ቪ ጣቢያ ትዕየንቶችን ያሳያሉ። የዳኒ ቡና ቤት ኤስ ኤንድ ኤም (መቆምና ሞዴል) ቡና ቤት ነው። ማራኪ ነን ብለው የሚገምቱት ወጣቶቹ ወንዶች ቆመው ሲታዩ ጠና ጠና ያሉት ወንድ ፈላጊዎች ደግሞ ተቀምጠው መጠጣቸውን እየተጎነጩ ምርጫቸውን ያከናውናሉ። ኤስ እና ኤም ቡና ቤቶች የመደብ ባሕርያቸው የተጠበቀ ቡና ቤቶች ናቸው። በውስጣቸው ፀብና ረብሻ የለም። አብዛኛዎቹ ደምበኞች የውሸት ጥርስ ያስተከሉ ስለሆኑ ሊያስወልቋቸው አይፈልጉም።

አብዛኛዎቹ ሰዎች የምሽቱን ጓደኞቻቸውን መርጠው መጨረሻቸውን ተረዳ። በዙሪያውም የሚካሄደው የተለመደ ጭውውት ይሰማል። ጭውውቱ የሚካሄደው በቪዲዮ ቡና ቤት ወይም በባለቆዳ ወንበሮች ቡና ቤት ወይም በዳንስ ቡና ቤቶች ይሁን በድብቅ ክለቦች ውይይቱ አንድ ዐይነት ተመሳሳይ የመሆኑ ጉዳይ አስደነቀው። የተለመደ ምሥጢራዊ ቋንቋ ነበራቸው።

ልክ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሲሆን ወጣቱ ልጅ ቡና ቤቱ ውስጥ ጥልቅ አለ። ልጁ ፓርከር ከሚያስታውሰው የበለጠ ቆንጆ ሆኖ ነበር። ዙሪያውን ተዟዟመጠና ፓርከርን ሲያየው ወደሱ ተራመደ። እንደምን አመሸህ?

"እንደምን አመሸህ? በመዘግየቴ በጣም አዝናለሁ ።"

"ምንም አይደለም። በመጠበቄ ግድ የለኝም።"

"ወጣቱ ሲጋራ አወጣና ፓርከር እስኪለኩሰለት ጠበቀ።"

@BOOKALEM

"ስላንተ ነበር የማስበው" አለ ፓርከር።

"አስበሃል?"

'የልጁ ዐይን ሽፋሎች በጣም ውብ ነበሩ።' "አዎን! መጠጥ ልጋብዝህ?"

"የሚያስደስትህ ከሆነ።"

"ፓርከር ሳቅ አለና....."እኔን ለማስደሰት ትፈልጋለህ?" አለው።

ልጁ ፓርከርን ዐይን ዐይኑን እያየ....."ይመስለኛል!" አለው በለስላሳ አንደበት፡

"ትናንት ማታ እዚህ አብሮህ የነበረውን ሰው አይቼዋለሁ። ላንተ ተገቢው ሰው አይደለም" አለ ፓርከር።

"እናስ አንተ ለኔ ትከክለኛው ሰው ነህ?"

"ልሆን እችላለሁ። ለምን ሁላታችንም አናረጋግጥም? ወደ ውጭ ለአጭር የእግር ጉዞ ለመውጣት ትፈልጋለህ?"

"ግሩም ይመስላል።"

"ፓርከር መላ አካላቱን ደስታ ሲወረው ተሰማው። "ብቻችንን ልንቆይ የምንችልበት ሞቃትና ምቹ የሆነ ሥፍራ አውቃለሁ።"

"መልካም። መጠጡን እዘለዋለሁ።"

ወደ መውጫው በር ተያይዘው ሲያመሩ በሩ በድንገት ተበረገደና ሁለት ጠብደል ወጣት ወንዶች ቡና ቤቱ ውስጥ ገቡ። ከፓከር ጋር ሊወጣ የነበረውን ወጣት ልጅ መንገዱን ዘግተውበት ቆሙ። "ተገኘህ አንተ የውሻው ልጅ! የተበደርከኝ ገንዘብ የታለ?"

ወጣቱ ልጅ በፍራቻ ተመለከተው። "ምን እንደምታወራ አላውቅም። ከዚህ በፊት ዐይቼህ አላው....."

"ይሆን ቱሻህን አትንፋልኝ!" አለና ጨምድዶ ይዞ ወደ ጎዳናው አወጣው።

ፓርከር እጅግ በጣም ተቆጭቶ ቆመ። ጣልቃ ለመግባት ቃጥቶት ነበር። ግን ወደ ቅሌት ሊለወጥ የሚችል ነገር ውስጥ ሊገባ አልፈለገም። ልጁ በጨለማው ውስጥ ተውጦ ሲጠፋ ቆሞ ተመለከተው። ሁለተኛው ሰው ደግሞ በማስተዛዘን ሁኔታ ፓርከርን በፈገግታ ተመለከተው።

"አጃቢህን በጥንቃቄ መምረጥ ይገባሃል። ያ ልጅ መጥፎ ዜና ነው።"

ፓርከር ጠጋ ብሎ ተናጋሪውን ተመለከተው። ብሩህ ቡናማ ጸጉርና ማራኪ የሆነ ገጽታ ነበረው። አቋሙም የተዋጣለት ቅርፅ አለው። 'ምሽቱ በአጠቃላይ ውድቀት አይደለም!' ሲል ፓርከር አሰበ። "ትክክል ልትሆን ትችላለህ!" አለ ፓርከር።

"ዕጣ በመጋዘኗ ምን እንዳስቀመጠችልን ልናውቅ አንችልም። እናውቃለን?" አለ ልጁ የፓረከርን ዐይኖች እየተመለከተ።

"የለም አናውቅም" አለ ፓርከር። "ስሜ ቶም ነው ያንተስ?"

@BOOKALEM

"ፖል።"

"መጠጥ ለምን አልገዛልህም ፖል?"

"በጣም አመሰግናለሁ።"

"ለምሽቱ የተለየ እቅድ አለህ?"

"ይህ የአንተ ጉዳይ ነው።"

"ምሽቱን ከኔ ጋር ብታሳልፍስ?"

"አስደሳች ይመስላል።"

"በምን ያህል ገንዘብ ነው የምንነጋገረው?"

"ስለወደዱኩህ ሁለት መቶ ዶላር ብቻ ይቢቃኛል።"

"ያን ያህል ተገቢ ይመስላል?"

"ፈጽሞ አታዝንበትም።"

ከሠላሳ ደቂቃዎች በኋላ ፖል ኬሸንን በጀፈርስን ጎዳና ወደሚገኝ አንድ አሮጌ የአፓርታማ ሕንፃ እየመራ ወሰደው። ሦስተኛው ፎቅ ላይ የሚገኝ አንድ አነስተኛ ክፍል ውስጥ እንደገቡ ፓርከር ዙሪያውን ተመለከተ። "ብዙም አጥጋቢ አይደለም። ነው? የሆቴል ክፍል ሳይሻል አይቀርም።"

ፖል ሳቅ አለና....."እዚህ ምሥጢራዊ የሆነ ሥፍራ ከመሆኑም ባሻገር የምንፈልገው አልጋውን ብቻ ነው" አለ።

"ትክክል ነህ። ለምን ልብስህን አታወላልቅም? የገዛሁትን ለማየት እሻለሁ።"

"በእርግጥ!" አለና ፖል ማወላለቅ ጀመረ። ግሩም የሆነ ሰውነት ነበረው።

"በል አንተም ቶሎ አወላልቅ። እፈልግሃለሁ!" ሲል ፖል ሹክ አለ። "ከንፈር ነው ወይንስ ጭን የምትፈልገው?" ሲል ፖል ጠየቀ።

"አፐሬቲቭ ብናደርገውስ?"

"መታጠቢያ ቤት ልግባ። ቶሎ እመለሳለሁ" አለ ፖል።

ፓርከር የሚቀጥለውን መጪ ደስታ እያሰበ ራቁቱን ተጋደመ። ባልደረባው ከመታጠቢያ ቤት ወጥቶ መኝታውን ሲጠጋ ተሰማ።

እጆቹን ዘረጋና....."ናልኝ ፖል!" አለው።

"መጣሁልህ!"

ፓርከር ሥለታም ጩቤ ደረቱን በጥርቆት ሲገባ የፍንዳታ ዐይነት ሕመም ተሰማው። ዐይኖቹን ከፈታቸውና እያቃሰተ ወደ ላይ ተመለከተ። "አምላኬ ምንድነው.....?"

ፖል እየለባበሰ ነበር። "ስለገንዘቡ አትጨነቅ በምከር ቤቱ ሒሳብ ነው።"

@BOOKALEM

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ሲ.አይ.ኤ. ለ–ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል
ምክትል ዳይሬክተር ዐይኖች ብቻ
ግልበጭ የለውም
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
-9-ኬቪን ፓርከር–ዋሺንግተን ዲ.ሲ
ተወግዷል።
የመልዕክት መጨረሻ

ሮበርት ቤላሚ የካርኒቫል ባለቤት የሆነውን ሰው ለመፈለግ በምሽቱ አውሮፕላን ወደ ሁንጋሪያ እየበረረ ስለነበር የምሽቱ የዜና ዕትም አመለጠው።

ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት

ቡዳ ፔስት

ከፓሪስ ወደ ቡዳፔስት በማሌቭ አየር መንገድ አውሮፕላን የተደረገው በረራ ሁለት ሰዓት ከአምስት ደቂቃ ነበር የፈጀው። ሮበርት ስለሆንጋሪ የሚያውቀው በጣም ውስን የሆነ ነገር ቢኖር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የአክሲስ ኃይሎች አጋር እንደነበረችና ከዚያ በኋላ የሩሲያ ሳተላይት የርዕዮት ዓለም ተከታይ መሆኗን ነው። ሮበርት ከአየር ማረፊያው ወደ ከተማዋ ማዕከል በሚያየው ነገር ሁሉ እየተመሰጠ በአውቶቡስ ተጓዘ። ሕንፃዎቿ አሮጌዎችና ምሕንድስናቸው ጥንታዊ ሥነ–ጥበብ የሚታይበት ነው። የሩዶልፍን የውሃ ዳርቻ ተንተርሶ ግዙፍ የፓርላማ ሕንፃ ሲገኝ ከከተማዋ በላይ ደግሞ የሮያል ቤተ መንግሥት ይገኛል። መንገዶቹ በመኪናዎችና በገበያተኞች ተጣበዋል። አውቶቡሱ ሆቴል ዱና ኢንተርናሽናል ፊት ለፊት ሲቆም ሮበርት ወደ እንግዳ መቀበያው አስተናጋጅ ሄደ።

"ይቅርታ አድርግልኝ። እንግሊዘኛ መናገር ትችላላህ?"

"ኢግና! (አዎን) ምን ልርዳዎት?"

"ጓደኛዬ ከጥቂት ሳምንታት በፊት እዚህ ቡዳ ፔስት ውስጥ ነበር። በጣም ግሩም የሆነ የካርኒቫል ትርዒት መመልከቱን ነግሮኛል። የት እንደማገኘው ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"ካርኒቫል?" አለና አስተናጋጁ አንድ ወረቀት አወጣ። "እስቲ እንመልከት።" ቡዳ ፔስት ውስጥ በአሁኑ ጊዜ አፔራ፤ የተለያዩ ቲያትሮች፤ የባሌ ዳንስ

@BOOKALEM

ትርኢት፤ የምሽትና የቀን የከተማ ጉብኝት.....ቀና ብሎ ሮበርትን ተመለከተና.....“አዝናለሁ! የካርኒቫል ትርዒት የለንም” አለው።

“እርግጠኛ ነህ?”

“ራስዎ መመልከት ይችላለሉ” አለና ወረቀቱን ለሮበርት አቀበለው። የተጻፈውን በሁንጋሪያን ነበር።

ሮበርት ወረቀቱን መለሰለት። “ትክክል! ስለዚህ ጉዳይ የማነጋግረው ሰው ይኖራል?”

“የባሕል ሚንስቴር መሥሪያ ቤት ሊረዳዎት ይችላል።”

ከሠላሳ ደቂቃዎች በኋላ ሮበርት በባሕል ሚንስቴር ጽሕፈት ቤት ከአንድ ጸሓፊ ጋር እየተነጋገረ ነበር።

“.....ሀንጋሪ ውስጥ ካርኒቫል የለም። እርግጠኛ ነህ ባልንጀራህ ቡዳ ፔስት ውስጥ ነው ያየው?”

“እዎን።”

“ግን ቦታውን ለይቶ አልተናገረም?”

“አልተናገረም።”

“አዝናለሁ ልረዳህ አልችልም።” ጸሓፊው ትዕግስት የለሽ ነበር። “ሌላ የምረ.....”

“የለም!” አለና ሮበርት ከመቀመጫው ተነሳ። ጥቂት አመነታና “እንድ ተጨማሪ ጥያቄ አለኝ። ሰርከስ ወይንም ካርኒቫል ወደ ሀንጋሪ ለማሰገባት ብፈልግ የመግቢያ ፈቃድ ማግኘት አለብኝ?”

“በእርግጥ አለብህ።”

“ለዚህ የምሄደው ወዴት ነው?”

“ወደ ቡዳፔስት የፈቃድ መስጫ አስተዳደር።”

የፈቃድ መስጫው ሕንፃ የቆመው ቡዳፔስት ውስጥ ከመካከለኛው ክፍለ ዘመን ግንብ አጠገብ ነው። ሮበርት ባለሥልጣኑ ቢሮ ከመቅረቡ በፊት ሠላሳ ደቂቃ መጠበቅ ነበረበት።

“ልረዳህ እችላለሁ?”

ሮበርት ፈገግ አለ። “ይችላሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በዚህ ዐይነት አልባሌ ነገር ጊዜዎን በማባከኔ በጣም አዝናለሁ። እዚህ የመጣሁት ከወንድ ልጄ ጋር ነው። እሱም እዚህ ሀንጋሪ ውስጥ የሆነ ቦታ የካርኒቫል ትዕይንት እንደሚካሄድ ስለሰማ እኔም አሳይሃለሁ ብዬ ቃል ገብቼለት ነበር። መቼም ሕፃናቶች አንድ ሐሳብ ጭንቅላታቸው ውስጥ ከገባ እንዴት እንደሚሆኑ ያውቃሉ።”

ባለሥልጣኑ ግራ ተጋብቶ ሮበርትን ያየው ጀመር። “ልታየኝ የፈለከው ለምን ጉዳይ ነው?”

@BOOKALEM

“ደህና። እውነቱን ለመናገር ካርኒቫሉ የት እንደሚገኝ ማንም የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም። ሆንጋሪ ደግሞ ትልቅና በጣም ውብ የሆነች አገር ናት። ሆንጋሪ ውስጥ የሚደረጉ ነገሮችን ልቅም አድርጎ የሚያውቅ ሰው አለ ከተባለ እርስዎ መሆን አለብዎት።”

ባለሥልጣኑ አንገቱን ነቀነቀ። “እዎን። የዚያን ዐይነት ነገር ፈቃድ ሳይሰጠው ሁንጋሪያ ውስጥ ሊከፈት አይችልም።” መጥሪያ ሲጫን አንድ ጸሓፊ ገባች። በሆንጋሪያን ፈጣን የንግግር ልውውጥ ከተደረገ በኋላ ጸሓፊዋ ወጣች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጥቂት ወረቀቶች ይዛ ገባችና ለባለሥልጣኑ አስረከባ ወጣች። ሰውዬው ወረቀቶቹን ተመለከተና ለሮበርት እንዲህ አለው። “ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ለሁለት ካርኒቫሎች ፈቃድ የሰጠን ሲሆን አንደኛው ከአንድ ወር በፊት ተዘግቷል።”

“ሌላውስ?”

“ሌላው ደግሞ ሶፕሮን ውስጥ በመታየት ላይ ነው። ጀርመን ድንበር አካባቢ የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ናት።” ባለሥልጣኑ እንደገና ወረቀቶች ተመለከተ። “ቡሽፌኬት። ላስሎ ቡሽፌኬት።”

ላስሎ ቡሽፌኬት በሕይወቱ ምርጥ የሆነ ቀን ነበር የገጠመው። በሕይወታቸው ውስጥ በጣም የሚያስደስታቸውን ነገር ማድረግ የሚችሉ ሰዎች በጣም ጥቂት ሲሆኑ ከጥቂት እድለኞች አንዱ ላስሎ ቡሽፌኬት ነበር። ላስሎ ቡሽፌኬት ስድስት ጫማ ከአራት ኢንች ርዝመትና ሦስት መቶ ፓውንድ ክብደት ያለው ግዝፍ ሰው ነው። በዐልማዝ ያጌጠ የእጅ ሰዓት፤ የዐልማዝ ቀለበትና የወርቅ አምባር በማድርግ ያጌጣል። አባቱ የአነስተኛ ካርኒቫል ባለቤት ነበር። እሱ ሲሞት ልጁ ካርኒቫሉን ወረሰ። ከካርኒቫሉ ሌላ ሕይወት ጨርሶ አያውቅም።

ላስሎ ቡሽፌኬት በጣም ትልቅ የሆነ ሕልም አለው። በጣም ትንሽ የሆነችውን ካርኒቫል አውሮፓ ውስጥ ወደታላቅና ምርጥ ካርኒቫልነት ሊለውጠው ያቅዳል። እንደ ፒ.ቲ ቨርኑና ካርኒቫሎች ታዋቂ ለመሆን ነው ፍላጎቱ። ለጊዜው ግን ማቅረብ የሚችለው አነስተኛ ትርዒቶችን ብቻ ነው። ወፍራሟ ወይዘሮና ባለንቅሳቱ ሰው፤ የሲአሜዝ መንትዮች፤ የአንድ ሺህ ዓመት ዕድሜ ያለው ከግብጽ የመቃብር ሥፍራ ተቆፍሮ የወጣ ያልበሰበሰ አስከሬን (መሚ)፤ ጎራዴ የሚውጠው ሰው፤ ነበልባል በሊታው፤ ትንሿ እባብ አጫዋች ማሪካ ይገኙበታል።

አሁን በአንድ ምሽት የላስሎ ቡሽፌኬት ሕልም ወደ ገሐድነት ሊለወጥ ነው። ከዚህ በፊት ዝናውን ስለሰማለት አንድ አምላጭ (ከእስር የማምለጥ ትርዒት የሚያሳይ አርቲስት) ለመመርመር ወደ ስዊዘርላንድ ተጓዘ። ትርዒቱ የተለመደው ዐይነት ነበር። አርቲስቱ ዐይኖቹ ታሰሩ። እጆቹ በካቴና ታሰሩ። ከዚያም እንደ ትንሽ ሳጥን ውስጥ ጉብጉ ከተቆለፈበት በኋላ እንደገና ከነትንሹ ሳጥን በውሃ

@BOOKALEM

የተሞላ ገንዳ ውስጥ ተከተተ። ላስሎ በስልክ ሲነገረው ነገሩ በጣም ማራኪ ነበር። ነገር ግን ጉዳዩን ለማየት ወደ ስዊዘርላንድ ከበረረ በኋላ አንድ ችግር መኖሩን ተገነዘበ። አምላጩን አርቲስት ሠላሳ ደቂቃዎች ወሰደበት። በዓለም ላይ ውሃ ውስጥ የተከተተ ሳጥን ለሠላሳ ደቂቃዎች በትዕግስት አፍጥጦ የሚያይ ተመልካች አይኖርም።

ጉዞው በአጠቃላይ ጊዜ ማባከን መስሎ ታየው። ላስሎ ቡሽፌኬት አውሮፕላን የሚሳፈርበት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ በአውቶቡስ ጉብኝት ለማድገረግ ወሰነ።

እንደተቀሩት መንገደኞች ቡሽፌኬት የአውሮፕላን ብሎ የገመተውን ፍንዳታ በዐይኑ አይቷል በጆሮውም ሰምቷል። እሱም እንደሌሎቹ መንገዱን አቋርጦ የተረፉ ተሳፋሪዎች ካሉ ለመርዳት እየሮጠ ሄደ። በሥፍራው ያየው ትዕይንት ግን ከቶም ቢሆን ሊመስል የማይችል ዐይነት ነበር።

በራሪ ዲስክ ለመሆኑ የሚያጠያይቅ ነገር የለም። በውስጡ የማይታወቁ ሁለት ተንንሽ ሙታን ፍጡራ ነበሩበት። መንገደኞቹ አፋቸውን ከፍተው ባሉበት ቀሩ። የበራሪው ዲስክ የኋላ አካል ምን እንደሚመስል ለማየት ላስሎ ወደ ኋላ ዞረ።

ከስብርባሪው በስተኋላ አሥር ጫማ ያህል ከሌሎች መንገደኞች ዕይታ ራቅ ብሎ ሁለት ተቃራኒ አውራ ጣቶችን የያዘ ባለስድስት ጣት የተቆረጠ ትንሽ እጅ ወድቋል። ቡሽፎኬት ያለምንም ማወላወል ከኪሱ መሐረብ አውጥቶ የተቆረጠውን እጅ ብድግ አደረገና እኪሱ ከተተው።

ልቡ እጅግ በጣም ይመታበት ነበር። የሌላ ዓለም ፍጡር ትክክለኛ እጅ በእጁ አስግብቷል። ካሁን በኋላ ወፍራም ወይዘሮውን፤ ንቅሳታሙን ሰው፤ ጎራዴ የሚውጠውን፤ እሳት የሚበላውን፤ መርዘኛ እባብ የምታጫውተውን ሁሉንም መርሳት እችላለሁ!' አለ በሐሳቡ። 'ከቡራንና ከቡራት! የሕይወታችሁን ሙሉ ደስታ ለማየት ወደ ፊት ተራመዱ። አሁን ልታዩት የተቃረባችሁት ትዕይንት ማንም ሚች የሆነ ፍጡር ዐይቶት የማያውቀው ዐይነት ትርዒት ነው። በሕዋው ውስጥ ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ነገር እየተመለከታችሁ ነው። እንሰሳ አይደለም። አዝርዕት አይደለም። ማዕድንም አይደለም። ታዲያ ምንድን ነው? ይህ የሌላ ዓለም ፍጡር ትክክለኛ ቅሬተ አካል ነው። ይህ የሳይንስ ልቦለድ አይደለም! ይህ ትክክለኛ የሆነ ነገር ነው። 500 ፎሮንቲስ ከከፈላችሁ ፎቶግራፍ ከዚህ.....'

ይህ ደግሞ አደጋው በደረሰበት ሥፍራ የነበረውን ፎቶግራፍ አንሺ አስታወሰው። እልክላችኋለሁ ብሎ ቃል የገባለትን ፎቶግራፍ አስታወሰው። 'በላከ!' ሲል ተመኘ። በትልቁ አሳድጎት ከኤግዚቢሽኑ አጠገብ ያስቀምጠዋል። ይህ ደግም ግሩም የሆነ የትዕይንት ሰውነት ችሎታ ነው። ሕይወትም የትዕይንት ሰውነት

@BOOKALEM

ችሎታ ማለት ናት። ወደ ሀንጋሪ ተመልሶ ታላቅ የሆነ ሕልሙን በተግባር ለመተርጎም መታገስ አቃተው።

አገሩ እንደደረሰ ከኪሱ የተቆረጠውን የሌላ ዓለም ፍጡር እጅ አውጥቶ መሐረቡን ሲዘረጋው እጁ ተኮማትሮ አገኘው። ነገር ግን አቧራውን ከላዩ ላይ ሲያራግፈው ቀደሞ የነበረውን ጥንካሬ ሲይዝ በአድናቆት ተመለከተ። ቡሽፌኬት የፍጡሩን እጅ ከደበቀ በኋላ በጣም ትልቅ የሆነ በውስጡ ልዩ የሆነ የአየር እርጥበትን የሚቆጣጥር መሣሪያ ያለው የመስተዋት ሳጥን በትእዛዝ አሠራ። በካርኒቫሉ ውስጥ ለኤግዜቢሽን አቅርቦት እንዳበቃ በመላው አውሮፓ ይዞት ለመጓዝ ወሰነ። የግል የሆነ የማስጎብኛ ትርዒት ደግሞ ለሳይንቲስቶች ምናልባትም ለርዕሰ ብሔሮች ያቀርባል። በዕርግጥ ሁሉንም የመግቢያ ዋጋ ያስከፍላል። ፊት ለፊቱ ማለቂያ የሌለው ንዋይ እየጠበቀው ነው።

ይህን የገጠመውን መልካም ዕድል ለማንም አልተናገረም። ሌላው ቀርቶ ለሴሰኛዋ ዳንስኛና ፍቅረኛው ለሆነችው ማሪካ እንኳ አልነገራትም። ማሪካ የምትሠራው ከኮብራና እጅግ በጣም መርዘኛ ከሆነው "አፊዲያ" ከተባለው እባብ ጋር ነው። በእርግጥ አፊዲያው የመርዝ ከረጢቱ እንዲወጣ ተደርጓል። ሆኖም ከተመልካቾች አንድም ሰው ይህን የሚያውቅ የለም። ምክንያቱም የመርዝ ከረጢቱ ያልወጣ ኮብራ እባብ ስላለውና እሱም አይጦቹን ሲገል ለተመልካቹ ያለምንም ክፍያ ስለሚያሳይ ነበር። ተመልካቹ አይጦቹ በኮብራው እየተነደፉ ሲሞቱ ማየት በጣም ያስደስተዋል። ተመልካቹ ሕዝብ መርዘኛ እባቦች በቆንጆዋ ማሪካ ስሜትን የሚያነሳሳ ገላ ላይ ሲንሸራሸሩ ማየት በጣም ያስደስተው ነበር። በሳምንት ሁለት ወይም ሦስት ምሽት ማሪካ ወደ ቡሽፌኬት ድንኳን ሾልካ ትመጣለች። ልክ ለማዳ እባቦቿ እንደሚያደርጉት በምላሷ መላ ሰውነቱን ትልሰዋለች። ባለፈው ምሽት ፍቅር ሲሠሩ ያደሩ ከመሆኑም በላይ በማሪካ ጂምናስቲክ ቡሽፌኬት አሁንም እንደተዳከመ ነበር። የቀን ሕልሙ በአንድ እንግዳ ጎብኚ ተቋረጠ።

"ሚስተር ቡሽፌኬት ነህ?" አለ ኮማንደር።

"ከእርሱ ጋር እየተነጋገርክ ነው! ምን ልርዳህ?"

"ባለፈው ሳምንት ውስጥ ስዊዘርላንድ እንደነበርክ አምናለሁ።"

በሽፌኬት ወዲያውኑ 'ምን ችግር ሊመጣ ይሆን?' ሲል ጠንቀቅ አለ። አንድ ሰው ያንን እጅ ሲያነሳ አይቶ ይሆን?

"ስለጉዞዬ ምን ተገኘ?" ሲል ጠየቀ።

"ባለፈው ሳምንት እሁድ ለጉብኝት በአውቶቡስ ተጉዘሃል?"

"አዎን" አለ እየተጠነቀቀ። ቤላሚ.....'እናም.....መጨረሻ ላይ ተፈፀመ!' አለ በሐሳቡ። ይህ የመጨረሻው ምስክር ነው። የማይቻል ተልዕኮ ተሰጥቶት እጅግ በጣም ግሩም የሆነ ሥራ ለማከናወን ቻለ። "የት እንዳሉ አናውቅም" ነበር የተሰጠው መግለጫ። እሱ ግን አድኖ አገኛቸው። አንድ ኃያል የሆነ ሽክም

@BOOKALEM

ከትከሻው ላይ ሲወርድ ነበር የተሰማው። አሁን በነጻነት ወደ አገሩ ተመልሶ አዲስ ሕይወት የሚመሠርትበት ወቅት ነው።

"ስለጉዞዬ ምን ተገኘ ሚስተር?"

"ይህን ያህል አስፈላጊ ጉዳይ አይደለም" ሲል ሮበርት መለሰለት። "አብረውህ ተጉዘው ስለነበሩት መንገደኞች አንዳንድ መረጃ ለማግኘት እፈልጋለሁ ብዬ አምናለሁ።"

"አ! ስለሁሉም መንገደኞች ልነግርህ እችላለሁ" አለ ላስሎ ቡሽፌኬት። "ከኢጣሊያ የመጡ እንድ ቄስ ነበሩ። የኬሚስትሪ ፕሮፌሰር የሆነ ጀርመናዊ ከሙኒክ፤ ኪየቭ ቤተ መጽሐፍት ውስጥ የምትሠራ ሩሲያዊት ልጃገረድ፤ ከብት አርቢ ከዋኮ ቴክሳስ፤ ካናዳዊ ባንከኛ ድንበሮቹ አካባቢ፤ የኮንግረስ ሎቢስት ከዋሺንግተን ዲ.ሲ።"

'ያምላክ ያለህ!' አለ ሮበርት በሐሳቡ። 'መጀመሪያ እርሱን አግኝቼ ቢሆን ኖሮ አያሌ ጊዜ በቆጠብኩ ነበር። ሰውየው በጣም የሚያስደንቅ ነው። ሁሉንም ማስታወስ ይችላል።'

"በጣም ጥሩ የማስታወስ ችሎታ አለህ!" አለው ሮበርት።

"አዎን!" አለና ቡሽፌኬት ፈገግ አለ። "እናም ደግሞ አንዲት ሌላ ሴት ነበረች።"

"ሩሲያዊት?"

"የለም! የለም! ሌላ ነጭ ልብስ የለበሰች ረዥም ቀጭን ሴት ነበረች።"

ሮበርት ለተወሰነ ጊዜ ያሰላሰል ጀመር። የተቀሩት ምስክሮች አንዳቸውም አልጠቀሷትም። "ተሳስተሃል ብዬ እገምታለሁ።"

"የለም አልተሳሳትኩም። እዚያ ቦታ ላይ ሁለት ሴቶች ነበሩ።"

ሮበርት በአዕምሮው ያሰላ ጀመር። በሐሳቡ ሊመጣለት አልቻለም። "በፍፁም ሌላ ሴት ልትኖር አትችልም።"

ቡሽፌኬት የተሰደበ ያህል ነበር የተሰማው። "ያ ፎቶግራፍ አንሺ ከተከሰከሰው ዩ.ኤ.ፍ.አ ፊት ለፊት ፎቶግራፋችንን ሲያነሳ አጠገቤ ቆማ ነበር። እውነተኛ ቆንጆ ነበረች!" አለና ንግግሩን ቆም አደረገ። "የሚገርመው አውቶቡሱ ላይ እንደነበረች አለማስታወሴ ነው። ምናልባት የተቀመጠችው ወደ ኋላ ሊሆን ይችላል። የበሸተኛ ወይም ሕመምተኛ ዐይነት ገጽታ ይታይባት ስለነበር ተጨንቄ ነበር።"

ሮበርት ፊቱን ጭፍግግ እያደረገ....."ለመሆኑ ተመልሳችሁ አውቶቡሱ ላይ በተሳፈራችሁበት ጊዜ እሷም አብራ ነበረች?"

"እስቲ ላስብበት። ከዚያ በኋላ እሷን ስለማየቴ የማስታውሰው ነገር የለም። ግን በዚያ ዩ.ኤ.ፍ.አ. በሚባል ነገር በጣም ተደንቄ ስለነበር ብዙም ትኩረት አልሰጠኋትም።"

@BOOKALEM

'እዚህ ቦታ ላይ የማይገጣጠም አንድ ነገር አለ። ከአሥር ይልቅ አሥራ አንድ ምስክሮች ነበሩ ማለት ነው? ይህንን ማጣራት አለብኝ' አለ በሐሳቡ።

"በጣም አመሰግናለሁ ሚስተር ቡሽፌኬት።"

"በጣም ደስተኛ ነኝ!" አለ ቡሽፌኬት።

"መልካም ዕድል!" አለው ሮበርት።

ቡሽፌኬት ገለፈጠ። "አመሰግናለሁ!" ዕድል አያስፈልገውም። ካሁን በኋላ እውነተኛ የሌላ ዓለም ፍጡር እጅ ባለንብረት ስለሆነ ዕድል አያስፈልገውም።

በዚያ ምሽት ሮበርት ቤላሚ ለጄነራል ሒሊያርድ የመጨረሻ ዘገባውን አቀረበ።

"ስሙን አግኝቼዋለሁ። ላስሎ ቡሽፌኬት። ሲባ ከሶፕሮን ከሀንጋሪ ወጣ ብሎ አንድ አነስተኛ የካርኒቫል ትርዒት እየመራ ነው።"

"እርሱ የመጨረሻው ምስክር ነው?"

ሮበርት ለቅጽበት ያህል አመነታና....."እዎን ጌታዬ.....!" ስለስምንተኛዋ ምስክር ለመጥቀስ ጀመር አደረገና ተወው። 'እስኪጣራ ድረስ መጠበቅ ይሻላል' ሲል ወሰነ። የሌላ ምስክር መኖር ጉዳይ ፈጽሞ የማይመስል ነው።

"እመሰግናለሁ ኮማንደር። በጣም ግሩም ሥራ!"

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
የበሔራዊ ፀጥታ ወኪል
ለ–ኤች.አር.ኪው የሀንጋሪ መረጃ ድርጅት ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
-10-ላስሎ ቡሽፌኬት -ሶፕሮን
የመልዕክት መጨረሻ

ካርኒቫሉ ከተዘጋ በኋላ እኩለ ለሊት ላይ ሁለት ሰዎች ሶፕሮን ደርሰው ከአሥራ አምስት ደቂቃዎች በኋላ ልክ እንደአመጣጣቸው ማንም ሳያያቸው ተመልሰው ሄዱ።

ላስሎ ቡሽፌኬት ሕልም እያለመ ነበር። አንድ በጣም ግዙፍ የሆነ ነጭ ድንኳን በር ላይ ቆሞ ሕዝቡ አንድ ሳጥን ላይ ባለ 5 ፍሮንቲ ዋጋ ያለው ቲኬት ለመግዛት ተሰልፎ ይታየዋል። 'እባካችሁ በዚህ በኩል ኑ! አሁን የምታዩት ትክክለኛ የሆነ የሌላ ዓለም ሰው አካል ነው። ስዕል መሳል ወይም ፎቶግራፍ ማንሳት የተከለከለ ነው። በ500 ፎሮንቲ የሕይወት ዘመን ደስታ ሽምቱ። ዕድሜ

@BOOKALEM

ልካችሁን የማትረሱት ተዕይንት ነው።' እንደገና ከማሪካ ጋር አልጋ ውስጥ ነበር። በመላ ሰውነቱ ላይ እየተሳበች በምላሷና በእጆቿ ስትዳስሰው እጁን ይስማዋል። አሱም ወደ እርሷ ቀሰ ብሎ እጁን ሰደደ። አንድ ቀዝቃዛና የሚለሰልስ ነገር እጁ ላይ ተሰማው። ከእንቅልፍ ሰመመኑ ነቃና ዐይኖቹን ገለጣቸው። ወዲያው ጩኸቱን አቀለጠው። ልክ በዚያች ቅጽበት መርዘኛው ኩብራ ጥቃቱን ሰነዘረ።

ጠዋት አስከሬኑ ሲገኝ መርዘኛው እባብ የነበረበት ጎጆ ግን ባዶ ነበር።

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ኤች.አር.ኪው. የሁንጋሪያ መረጃ ድርጅት
ለ–ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
–ነዐ–ላስሎ ቡሽፌኬት –ሶፐሮን– ተወግዷል
የመጨረሻ መልዕክት

ጀነራል ሒሊያርድ በቀዩ ስልክ ጥሪ አደረገ። "ጃኑስ! የመጨረሻውን ሪፖርት ከኮማንደር ቤላሚ ተቀብያለሁ። የመጨረሻውን ምስክር ፈልጎ ያገኘ ሲሆን በሙሉ አስፈላጊው የጥንቃቄ እርምጃ ተወስዶባቸዋል።"

"እጅግ በጣም ጥሩ። ሌሎቹንም አሳውቃቸዋለሁ። በቀሪው ፕላናችን መሠረት ወዲያው አስፈላጊውን ሥራ እንድትጀምር እፈልጋለሁ ።"

"ወዲያውኑ ጌታዬ!"

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ኤን.ኤስ.ኤ (ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል)
ለ–ሲ.ጄ.ኤች.አር.ኪው
ለ– ቢ.ኤፍ.ቢ
ለ–ኤም.አይ.6
ለ– ሲ.አይ.ኤ
ለ– ኮምሴክ
ለ–ዲ.ሲ.አይ
ለ– ሲፋር
ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርዕስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
ዘ–ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ–ይወገድ!
የመልዕክት መጨረሻ

@BOOKALEM

ክፍል ሁለት

ታዳኙ

ምዕራፍ ሠላሳ አራት

አሥራ አምስተኛ ቀን

ሮበርት ቤላሚ በሁለት ሐሳቦች መካል እየዋለለ ነው። 'ሌላ አሥራ አንደኛ ምስከር ነበረች ማለት ነው? ከነበረችስ ለምንድነው ከምስክሮቹ አንዳቸው እንኳ ያልጠቀሷት?'

የአውቶቡስ ቲኬት የሚሸጠው ጸሓፊ ሰባት መንገዱኞች ብቻ እንደነበሩ ነው የነገረው። 'የሀንጋሪው ካሪኒቫል ባለቤት ተሳስቷል!' ሲል ሮበርት አመነ። ትክክል እንዳልሆነ ወይም እውነት እንዳልሆነ ገምቶ እዚያ ላይ ዘግቶ መተው ይችል ነበር። ነገር ግን የሮበርት ሥልጠና እንዲህ ያለውን ነገር አይፈቅድም። ቡሽፌኬት ያመጣውን ታሪክ ማጣራት አለበት። 'ግን እንዴት?' ሲል አሰበ። 'የአውቶቡሱ ሾፌር ሐንስ ቤከርማን ማወቅ አለበት።'

ወደ ሰንሻይን ቱርስ ኩባንያ ስልክ ደወለ። ቢሮው ዝግ ከመሆኑም በላይ ካፔል ውስጥ ሐንስ ቤከርማን የተበለው ሰው ስልክ አልተመዘገበም ነበር። 'ወደ ስዊዘርላንድ ሄጄ ለዚህ ነገር አንድ መደምደሚያ ማበጀት አለብኝ። ያልተቋጨ መጨረሻ እንዲኖር አልሻም' ሲል ወሰነ።

ሮበርት ዙሪክ ሲደርስ በጣም መሸቶ ነበር። መኪና ተከራየና አሁን ወደሚያወቀው ወደ ካፔል መንደር ጉዞውን ቀጠለ። ካፔል እንደደረሰም ቤተ ክርስቲያኑን አለፍ አለና ሐንስ ቤከርማን ቤት ፊት ለፊት መኪናውን አቆመ። 'መቼም የሌለ ነገር ነው በማደን ላይ ያለሁት' አለ በሐሳቡ። ቤቱ ጨልሟል። ሮበርት በሩን አንኳኳና በምሽቱ ውርጭ እየተንቀጠቀጠ ይጠባበቅ ጀመር።

ወይዘሮ ቤከርማን በሩን ከፈተችው። ቀለሙ የለቀቀ የጥጥ ልብስ ለበሰ ነበር። "ምንድን ነው?" አለችው።

"ወይዘሮ ቤከርማን አስታወሱኝ? ስለሐንስ ዘገባ አዘጋጅ የነበርኩት ጋዜጠኛ ነኝ። በዚህ ወቅት በማስቸገሬ አዝናለሁ። እባክዎትን በጣም አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ ባለቤትዎን ለማነጋገር ፈልጌ ነበር።"

ለንግግሩ ያገኘው መልስ ቢኖር ፀጥታ ብቻ ነው። "ወይዘሮ ቤከርማን?" አለ ሮበርት።

"ሐንስ ሞቷል!"

ሮበርት በሰውነቱ ውስጥ ድንጋጤ ሲሰራጭ ተሰማው። "ምን?"

"ባለቤቴ ሞቷል። ፖሊሶች ብዙ መድኃኒት ስለወሰደ ነው ብለዋል።"

@BOOKALEM

"መድኀኒት?" ሮበርት የሐንስ ንግግር ትዝ አለው። 'አዝናለሁ መጠጥ ላቀርብልህ አልችልም። የአልሰር በሽተኛ ነኝ። ሌላው ቀርቶ ሕመሜን ለማስታገስ እንኳ ሐኪሞች መዱኀኒት ሊሰጡኝ አልቻሉም። ለሁሉም ዐይነት መድኀኒት አለርጂክ ነኝ።'

"ፖሊስ ድንገተኛ አደጋ ነው አለ ነው የሚሉኝ?"

"አዎን።"

"የአስከሬን ምርመራ አድርገዋል?"

"አድርገው በደሙ ውስጥ መድኀኒት አግኝተዋል። በፍፁም ስሜት የማይሰጥ ጉዳይ ነው።"

ምንም መልስ አልነበረውም። "በጣም አዝናለሁ ወይዘሮ ቤከርማን። እኔ....." የጀመረውን ሳይናገር ፊቱ ላይ በሩን ደርግማ ዘጋችበት። ሮበርት በምሽት ቀዝቃዛ አየር እየተንዘፈዘፈ ብቻውን ቆሞ ቀረ።

'አንድ ምስክር ተሰናብቷል። የለም ሁለት ናቸው። ሌስሊ ማዘርሼድም በአሳት አደጋ ሞቷል። ሁለት ምስክሮች ሞተዋል።' አለ በሐሳቡ። ሮበርት የአስተማሪው ንግግር በሕሊናው ውስጥ አቃጨለበት። 'በዛሬው እለት ልንወያይበት የምፈልገው አንድ ተጨማሪ ነገር አለ። "ኢጋጣሚ" ማለት ሁልጊዜ ትርጉሙ አደጋ ማለት ነው። ከዚያው ሰውዬ ጋር ደጋግማችሁ መንገድ ላይ የምትገናኙ ከሆነ ወይም ያችኑ መኪና በእንቅስቃሴ ላይ እያላችሁ በድጋሚ ካያችኋት ራሳችሁን ደብቁ። ምናልባት አደጋ ላይ ልትሆኑ ትችላላችሁና።'

የመጀመሪያው የስልክ ጥሪ ወደፎርት ስሚዝ ካናዳ ነው። በሐዘን የተኮማተረ የሴት ድምፅ ስልኩን መለሰ። "አቤት?"

"ዊልያም ማንን አቅርቡልኝ እባክዎ።"

እንባ እየተናነቃት....."አዝናለሁ። ባሌ ካሁን በኋላ ከኛ ጋር አይደለም!" አለችው።

"አልገባኝም" አለ ሮበርት።

"ራሱን በራሱ ገድሏል።"

'ራሱን በራሱ ገደለ? ያ ባለጠንካራ ጭንቅላቱ ሰው? ምን ዐይነት ገሃነማዊ ተግባር ነው በመከናወን ላይ ያለው?' ሲል አሰበ። ሮበርት የስልክ ጥሪ በስልክ ጥሪ ላይ እያካታተለ ይደውል ጀመር።

"እባክዎን ፕሮፌሰር ስቸሚዲትን አቅርቡልኝ።"

"ፕሮፌሰሩ ላቦራቶሪያቸው ውስጥ በፍንዳታ ሞተዋል።"

"ዳን ዋይንን ለማነጋገር እፈልግ ነበር።"

"ምስኪን! የርቢ ፈረሱ በእርግጫ ቀጥቅጦ ገደለው።"

"ፍሪትዝ ማንዶልን ፈልጌ ነበር።"

"ፍሪትዝ ማንዶል በድንገተኛ አደጋ ተገደለ።"

@BOOKALEM

"አልጋ ሮማንቻንኮን እባክዎ።"
"ምስኪን ልጃገረድ! ገና በወጣትነቷ ተቀጨች።"
"ስለአባ ፓትሪኒ ለመጠየቅ ነበር የደወልኩት።"
"ምስኪኑ ቄስ እንደተኙ ተሰናብተዋል።"
"ኬቨን ፓርከርን ማነጋገር አለብኝ።"
"ኬቪን ተገድሏል"

እያንዳንዱ ምስክር ሞቷል። ፈልጎ ያገኛቸውና የጠቆመባቸው ደግሞ ሮበርት ነው። የሚደረገው ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ያልቻለው ለምንድነው? እነዚያ ዲቃላዎች ምስክሮች ከመግደላቸው በፊት ሮበርት ከእያንዳንዱ አገር መውጣቱን በቅድሚያ ያረጋግጣሉ ወይም ይጠብቃሉ። ሪፖርት የቀረበለት ብቸኛው ሰው ደግሞ ጀኔራል ሒሊያርድ ብቻ ነው። 'ከዚህ ግዳጅ ውሰጥ ማንንም ጣልቃ ማስገባት የለብህም!'

ምስክሮቹን ፈልጎ እንዲጠቁማቸው ተጠቀሙበት። 'ከዚህ ጉዳይ በስተጀርባ ያለው ምሥጢር ምንድነው?'

'አቶ ስቭሚድት ጀርመን ውስጥ ተገደለ። ሐንስ ቤከርማን ፊሪትዝ ማንዶል ስዊዘርላንድ ውስጥ። አልጋ ሮማንቻንኮ ሩስያ። ዳን ዋይንና ኬቨን ፓርከር አሜሪካ። ዊሊያም ማን ካናዳ። ሌስሊ ማዘርቬድ እንግሊዝ። አባ ፓትሪኒ ኢጣሊያ። ላስሎ ቡሽፌኬት ሁንጋሪያ። ይህ ሁሉ የሚያሳየው ከደርዘን በላይ የሆኑ መንግሥታት የስለላ ድርጅቶች በታሪክ ውስጥ በጣም ግዙፍ የሆነ የሽፋን እንቅስቃሴ ሴራ ውስጥ አባሪ ተባባሪ ሆነዋል ማለት ነው።

አንድ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ባለሥልጣን የበራሪ ዲስኩን መከስከስ የተመለከቱ የዐይን ምስክሮች በሙሉ እንዲገደሉ ወስኗል። ግን ማን? እናስ ለምን?'

'ቅድሚያ ሽፋን ግባ!' አለ ሮበርት። እኔንም ሊገድሉኝ ይቃጣሉ ብሎ ማመኑ በጣም አስቸጋሪ ሆነበት። ከመካከላቸው አንዱ ነውና። ግን ነገሩን አጣርቶ አስካላወቀ ድረስ ምንም ዐይነት ዕድል መውሰድ (መዘናጋት) አይችልም። ማድረግ የሚገባው የመጀመሪያው ተግባር የሐሰት ፓስፖርት ማግኘት ነው። ይህንንም ሊያዘጋጀለት የሚችለው ሮም የሚገኘው ሪኮ የተባለ ሰው ነው።

ሮበርት በቀጣዩ የሮም በረራ አውሮፕላን ተሳፍሮ እንቅልፍ እንዳይጥለው እየታገለ ጉዞውን ቀጠለ። ያለፉት ኢሥራ አምስት ቀናት ውጣ ውረድ ሁሉ ከአውሮፕላን መናጥ ጋር ተደማምሮ ምን ያህል እንዳደከመውና ያለውን አካለዊ ጥንካሬ ሁሉ እንዳንጠፈጠፈ የተገነዘበው አሁን ነው።

የተሳፈረበት ጄት ሊአናርዶ ዳቪንቺ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ካረፈ በኋላ ወደ ተርሚናሉ ሲገባ በመጀመሪያ ያየው ሰው ሱዛንን ነበር። በድንጋጤ ተውጦ ቀጥ ብሎ ቆመ። ጀርባዋ ወደ እርሱ ስለነበር በመጀመሪያ 'ተሳስቼ ይሆን?' እያለ ሲያስብ ድምጿን ሰማ።

@BOOKALEM

"አመሰግናሁ የሚጠብቀኝ መኪና አለ።" ሮበርት ከጎኗ ራመድ አለና....."ሱዛን!" አላት።

ፊቷን ዞር አድርጋ ስታየው ድንግጥ አለች። "ሮበርት! ምን ዐይነት አጋጣሚ ነው? ደስ የሚል አጋጣሚ።"

"ጅብራልታር ነሽ ብዬ ገምቼ ነበር።"

"እዎን ወደዚያው በመጓዝ ላይ ነበርን። ሞንቴ በቅድሚያ እዚህ የሚያጠናቅቃቸው ጉዳዩች ስላሉ ነው ቆም ያልንው። ዛሬ ማታ ጉዞአችንን እንቀጥላለን። ሮም ውስጥ ምን እያደረክ ነው?"

ሮበርት በሐሳብ ተመሰጠ። 'ሕይወቴን ለማዳን በመሮጥ ላይ ነኝ። አንድ አስቸጋሪ ሥራ ገና መጨረሴ ነው። ይህም የመጨረሻ ተልዕኮዬ ነው። ሥራውን ትቻለሁ ፍቅሬ። ካሁን በኋላ አብረን መኖር የምንችል ሲሆን ምንም የሚነጣጥለን ነገር አይኖርም። ሞንቴን ተይውና ወደኔ ነይልኝ።'

ነገር ግን ሮበርት እነዚህን ቃላት መናገር አልቻለም። የሚበቃውን ያህል በድሏታል። እሷም በአሁኑ ጊዜ በአዲሱ ሕይወቷ ደስተኛ ናት። 'ልተወው ይቅር' አለ በሐሳቡ።

ትኩር ብላ እያየችው ነበር። "የደከመህ ትመስላለህ ሮበርት።"

ፈገግ አለና "እዎን! ትንሽ ጊዜ ዙሪያውን ስሯሯጥ ነበር።" ሁለቱ ዐይኖቻቸው ተያዩ። ያ በመካከላቸው ያለ ምትሃታዊ ስበት አሁንም ነበር። የሚያቃጥለው መፈላለግ፤ ትውስታው፤ ሳቅ ፈገግታው፤ መተሳሰቡ ሁሉ ነበር።

ሱዛን የሮበርትን እጆች በእጆችዋ ለስለስ አድርጋ ያዘችና "ሮበርት አህ! ሮበርት ምን ያህል....."

"ሱዛን....."

እና ልክ በዚህ ሰዓት አንድ የሾፌሮች የደንብ ልብስ የለበሰ ግዙፍ ሰው ወደ ሱዛን ተራመደና....."መኪናው ዝግጁ ነው ሚስ ባንክስ!" አለና ንግግራቸውን አቋረጠው።

"አመሰግናለሁ" አለችና ወደ ሮበርት ዘወር አለች። "እዝናለሁ ሮበርት አሁን መሄድ አለብኝ። እባክህን ስለራስህ ተጠንቀቅ።"

"መልካም" አለና ጥላው ስትሄድ በትኩረት ተመለከታት። ሊነግራት የሚፈልገው እጅግ በጣም ብዙ ነገር ነበር። ሕይወት አልባሌ የሆኑ አጋጣሚዎች አሏት። ሱዛንን ማግኘት በጣም የሚያስደስት ጉዳይ ነው። ግን ታዲያ ምንድነው የሚረብሸው ነገር? 'በእርግጥ «አጋጣሚ?» በ አጋጣሚ የሚሆን ነገር አለ?'

ወደ ሐስለር ሆቴል በታክሲ ተሳፈረ።

"እንኳን ደህና መጣህ ኮማንደር።"

"አመሰግናለሁ።"

"ተላላኪው ሻንጣህን እንዲወስድልህ አደርጋለሁ።"

@BOOKALEM

"ቆይ!" አለና ሮበርት ሰዓቱን ተመለከተ። ከምሽቱ አራት ሰዓት ይል ነበር። ወደ ፎቅ ወጥቶ ጥቂት ለማንቀላፋት ዳድቶት ነበር። ነገር ግን በመጀመሪያ የፓስፖርቱን ጣጣ ማከናወን አለበት። "አሁን ወደ መኝታዬ አልሄድም። ሻንጣዎቼን ወደ መኝታ ከፍል ብታስልከልኝ በጣም አድንቅሃለሁ።"

"በእርግጥ አልከልሃለሁ ኮማንደር።"

"እዚያጋ! እንደምን አለህ? ጥሩ ቀን እያሳለፍክ ነው?"

"በጣም ግሩም!" አለ ሮበርት። በቡድን የሚጠጡ የተሳከሩ ቱሪስቶች ነበሩ።

ሮበርት በእንግዳ መቀበያው አዳራሽ ውስጥ አቋረጠና ወደ ታክሲ ማቆሚያ ሥፍራ አመራ። ልክ ታክሲው ውስጥ ሊገባ ሲል አንድ ግራጫማ ቀለም ያላት ትኩረት የማትስብ አፔል መኪና ከጎዳናው ባሻገር ቆማ ተመለከተ። ብዙም እይታ የማትስብ ነበረች። የቆመችውም በጣም ዘናጭ የሆኑ የቅንጡት መኪኖች መኻል ነው።

"ቪአ ሞንቴ ግራፓ!" አለና ሾፌሩን አዘዘው። በጉዞአቸውም ላይ ሮበርት በጓላ መመልከቻው መስታወት ተመለከተ። ምንም ዐይነት ግራጫማ አፔል ከጓላው አልነበረም። 'በጣም ተጠራጣሪ እየሆንኩ ነው!' አለ በሐሳቡ። ሞንቴ ግራፓ ጎዳና እንደደረሱ ወደ ጎን አጮልቆ ሲመለከት ከጎዳናው በታች ከአንድ ሕንፃ ዝቅ ብሎ ግራጫማዋ አፔል መኪና ቆማ ተመለከታት። እንዳልተከተለችው በእርግጠኝነት ይምል ነበር። ግን ይኸው በዐይኑ እያያት ነው። በዝግታ እየተራመደ ከመኪናዋ እየራቀ ሲሄድ በሰቅ መስታወት ነፀብራቅ ውስጥ አፔሏ በጣም ቀስ ብላ ስትከተለው ተመለከተ። የሚቀጥለው ጎዳና ላይ ሲደርስ ባለአንድ አቅጣጫ ቀጥተኛ መንገድ መሆኑን ተገነዘበ። ፊቱን ወደተጣበበው የጎዳና ትራፊክ አዞረ። አፔሏ ጥቂት አመነታችና የመንገዱ ጠርዝ ላይ ሮበርትን ለመያዝ ወደ ፊት ከነፈች። አካሄዷ ዙሮ ለመመለስ መሆኑ ያስታውቃል። ሮበርት እንደገና ፊቱን አዞረና ወደ መጣበት ሞንቴ ግራፓ አመራ።

አፔሏ በአካባቢው አልነበረችም።

ሌላ ታክሲ ላይ ተሳፈረና ለሾፌሩ....."ወደ ሞንቴ ቼሊ" አለው። ሕንፃው አሮጌና ብዙዎቹ ከፍሎች ያልተያዙ፤ የጥሩ ዘመን ቅሪት ማስታወሻ፣ነበር። በተለያዩ ተልዕኮዎች ላይ ሮበርት ሕንፃውን ደጋግሞ ጎብኝቶታል። ወደ ሕንፃው ምድር ቤት የሚወስዱ ሦስት ደረጃዎችን ወረደና አንድ በር ላይ አንኳኳ። አንድ ዐይን በትንሿ የመመልከቻ መስኮት ውስጥ አጮቆ ተመለከተውና በሩ ተከፈተለት።

ሰውዬው "ሮበርት!" ብሎ ጮኸና እጆቹን ዘርግቶ እቅፍ አድርጎ ይዞት....."እንደምን ነህ ጓደኛዬ?" አለው።

@BOOKALEM

ተናጋሪው ወደ ስልሳ ዓመት የሚሆነው፣ ፂሙን ያልተላጨ፣ ነጭ የዐይን ቅንድብ ያለው፤ ጥርሶቹ የበለዙና የጉንጩ ሲጋ የተንጠለጠለ ሰው ነበር። በሩን ከውስጥ በኩል ዘጋና ቆለፈው።

"በጣም ደህና ነኝ ሪኮ" አለ ሮበርት።

ሪኮ ሁለተኛ ስሙ አይታወቅም። እርሱም ጉራውን ሲነዛ....."እንደኔ ዐይነት ሰው አንድ ስም በቂው ነው" ይላል።

"ዛሬስ ምን ላድርግልህ ጓደኛዬ?" ሲል ጠየቀው።

"በአንድ የሆነ ጉዳይ ላይ ነው ያለሁት። ደግሞም በጣም ቸኩያለሁ። አንድ ፓስፖርት ልታዘጋጅልኝ ትችላለህ?"

ሪኮ ፈገግ አለና....."ጳጳሱ ካቶሊክ ነውን? የዚህ ዐይነት ተራ ጥያቄ እንደጠየቅከ ቁጠረው።" አንድ መሳቢያ በቁልፍ ከፈተና "የየት አገር ዜጋ ልትሆን ትፈልጋለህ?" ብሎት በርካታ የተለያዩ ቀለሞች ያሏቸው ፓስፖርቶች አውጥቶ መምረጥ ጀመረ። የግሪክ፤ የቱርክ፤ ዩጎዝላቪያ፤ የእንግሊዝ፤ ፓስፖርቶች አሉኝ....."

"አሜሪካ" አለ ሮበርት።

ሪኮ ሰማያዊ ሽፋን ያለው ፓስፖርት አወጣ። "ይኸውና! አርተር በተርፊልድ የሚል ስም ላንተ ተስማሚ ይሆንልሃል።"

"በጣም ግሩም!" አለ ሮበርት።

"ግድግዳውን ተጠግተህ ብትቆምልኝ ፎቶግራፍ አነሳሃለሁ።"

ሮበርት ወደ ግድግዳው ተጠግቶ ሲቆም ሪኮ መሳቢያውን ሳበና ፖላሮይድ ካሜራውን አወጣ።

ከአንድ ደቂቃ በኋላ ሮበርት የተነሳውን ፎቶግጋፍ ተመለከተ። "በመሳቅ ላይ አልነበርኩም" አለ ሮበርት።

"ምን?" አለው ሪኮ ግራ ተጋብቶ።

"በመሳቅ ላይ አልነበርኩም። ሌላ ፎቶ አንሳ።"

ሪኮ በምን ቸገረኝነተ ትከሻውን ነቀነቀና....."እንዳልከ!" አለው። ሁለተኛውን ፎቶ ሲያነሳው ሳቅ ብሎ ተነሳ። "ይህ የተሻለ ነው!" አለ ሁለተኛውን በፈገግታ የተነሳውን ፎቶ እየተመለከተ። የመጀመሪያውን ፎቶግራፍ እንደዋዛ አድርጎ እኪሱ ውስጥ ከተተው። "አሁን ደግሞ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠይቀው የሥራ ደረጃ ነው!" ሲል ሪኮ ተናገረ። ሪኮ አንድ የመጠረዣ ማሺን ወደያዘ ጠረጴዛ ሄደና ፎቶግራፉን ፓስፖርቱ ውስጥ ጨምሮ ማሸግ ሲጀምር ሮበርት ደግሞ ቀለምና ሌሎች ቁሳቁሶችን ወደያዘ ጠረጴዛ ሄደና የወረቀት መቁረጫ ስለትና የወረቀት ማጣበቂያ ማስቲሽ አንስቶ ኪሱ ከተተ።

ሪኮ የእጅ ሥራ ውጤቱን አጠናው። አይከፋም። ፓስፖርቱን ለሮበርት አሰጨበጠና....."ዋጋው አምስት ሺህ ዶላር መሆኑ ነው!" አለው።

@BOOKALEM

ሮበርትም.....“በትክክል ያወጣል!” ሲል ለሪኮ አረጋገጠለትና አሥር ባለአምስት መቶ ዶላር ኖቶች አወጣ።

“ካንተ ዐይነት ሰዎች ጋር የንግድ ሥራ መሥራት በጣም የሚያስደስት ነው!” አለ ጫማ አዳሹ። “ስላንተ ምን አደሚስማኝ ታውቃለህ።”

አዎን። ሪኮ ምን እንደሚሰማው ሮበርት በትክክል ያውቃል። ሪኮ ለበርካታ መንግሥታት የሚሠራ የተዋጣለት «“ጫማ አዳሽ”» ሲሆን ለአንዳቸውም ታማኝነት የለውም። ሮበርት ፓስፖርቱን እኪሱ ውስጥ ከተተ።

“መልካም ዕድል ሚስተር በተርፊልድ!” አለና ሪኮ ፈገግ አለ።

"አመሰግናለሁ” አለና ሮበርት ክፍሉን ጥሎ ወጣ።

በሩ ከሮበርት ኋላ እንደተዘጋ ሪኮ ስልኩን ብድግ አደረገና የሆኑ ቁጥሮችን መደወል ጀመረ። ‘ለአንድ ሰው መረጃ ማቀበል ደግሞ ሌላ የገንዘብ ማግኛ ምንጭ ነው።’

ከሕንፃው ውጭ ሃያ ያርድ ያህል ራቅ ብሎ ሮበርት አዲሱን ፓስፖርቱን ከኪሱ አወጣና የቆሻሻ መጣያ ገረወይና ውስጥ ቀበረው። «አስቂኝ ቀልድ! ፓይለት በነበረበት ጊዜ ለጠላት ሚሳይል የማሳሳቻ "ዱካ" የሙተው ዘዴ ነበር። ‘እዎን! ሐርተር በተርፊልድን ያሳዱ።’»

ግራጫማዋ አፔል መኪና አንድ ሕንፃ ዝቅ ብላ ሮበርትን እየጠበቀች ቆማለች። ሮበርትን በመከታተል ላይ ያለችው ብቸኛዋ አሳዳጅ መኪና እንደሆነች እርግጠኛ ነው። ደግሞም በሄደችበት እያነፈነፈች ታገኘዋለች። ፈልገው የሚያገኙበት አንድ መንገድ አላቸው ማለት ነው። የዚህ እንቆቅልሽ መልሱ አንድ ብቻ ነው። ይኸውም ሮበርት የሚሄድበትን አቅጣጫ የሚጠቁም የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ እየተጠቀሙ ነው ማለት ነው። መሣሪያውን ራሱ እንዲይዘው ተደርጎ ተለጥፎበታል። ከልብሱ ጋር ተጣብቆበት ይሆን? ልብሱን ባዘጋጀበት ሰዓት ሻምበል ዱገርቲ አብሮት የነበረ ቢሆንም የትኛውን ልብስ እንደሚይዝ አያውቅም ነበር። ሮበርት የያዘውን ቁሳቁሶች በአዕምሮው መቁጠር ጀመረ። ገንዘብ፤ ቁልፎች፤ የገንዘብ ቦርሳ፤ መሐረብ፤ የዱቤ መሸመቻ (ክሬይዲት ካርድ) ‘.....እሱ እንኳ አስፈላጊነቱ ያጠራጥረኛል ጄነራል። ‘ግድ የለም ውሰደው። እናም ምንጊዜም ካንተ ሳትለይ ያዘው።’

‘የውሻ ልጅ! እንዲህ በቀላሉ እኔን ፈልገው ማግኘታቸው ምንም አያስደንቅም’ አለ ሮበርት።

አሁን ግራጫማዋ አፔል አትታይም ነበር። ሮበርት ክሬይዲት ካርዱን አወጣና በደንብ መረመረው። ከአንድ መደበኛ የዱቤ ካርድ በመጠኑ ወፈር ያለ ነበር። በጣም ጫን ሲያደርገው በካርዱ ውስጥ የተደበቀ ሌላ ነገር እንዳለ ይሰማዋል። ‘ይህን ለማሠራት የሚችል የርቀት መቆጣጠሪያ (ሪሞት ኮንትሮል) አላቸው ማለት ነው።’

@BOOKALEM

'በጣም ጥሩ! እስቲ እነዚህን ዲቃላዎች በሥራ በዛት ላጣድፋቸው!' አለ ሮበርት። ዕቃ የሚጭኑና የሚያራግፉ በርካታ የጭነት ካሚዮኖዎች በመንገዱ ላይ ተደርድርው ነበር። ሮበርት የካሚዮኖዎቹን ሰሌዳ እየተመለከተ መጣና አንድ በቀይ ቀለም የተፃፈ የፈረንሳይ ሰሌዳ ቁጥር ያለው ካሚዮን ሲያገኝ ዙሪያውን ተመልከቶ ማንም ሰው እንደማያየው ካረጋገጠ በኋላ ከሬይዲት ካርዱን በኋላ በኩል ዕቃ መጫኛው ላይ ወረወረው።

ሮበርት ወዲያው ታክሲ አስቆመና "ሐሰለር ሆቶል!" አለው። እንግዳ መጠበቂያ ክፍል ውስጥ እንደገባ ወደ እስተናጋጁ አመራ። "እስቲ እባክህን ዛሬ ወደ ፓሪስ የሚበር አውሮፕላን ይኖር እንደሆነ አረጋግጥልኝ።"

"በሚገባ ኮማንደር። በተለይ የምትፈልገው አውሮፕላን ይኖር ይሆን?"

"ችግር የለም። የመጀመሪያውን በራሪ አውሮፕላን ነው የምፈልገው።"

"ይህንን ላንተ በማዘጋጀቴ ደስታ ይሰማኛል።"

"አመሰግናለሁ!" አለና ሮበርት ወደ ሆቴሉ ጸሐፊ ሄደና..... "እባክህ የቁጥር 314 ክፍሌን ቁልፍ ስጠኝ። ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ ክፍሌን እለቃለሁ" አለው።

"በጣም ጥሩ ኮማንደር ቤላሚ!" ጸሐፊው አንድ የዕቃ ማስቀመጫ ውስጥ እጁን ከተተና ቁልፍና አንድ ፖስታ ይዞ ወጣ። "አንድ ደብዳቤ አለህ" አለው ጸሐፊው።

ሮበርት ነቃ አለ። ኤንቬሎፑ የታሸገ ሲሆን ለኮማንደር ሮበርት ቤላሚ የሚል አድራሻ ተጽፎበታል። 'በውስጡም የሚፈነዳ ፕላስቲክ ወይም ብረታማ ነገር ይኖረው ይሆን?' ብሎ በጣቱ ጫን ጫን እያለ ፈተሸና ከፈተው። በውስጡ ያገኘው ነገር የአንድ የኢጣሊያ ሬስቶራንት ማስታወቂያ ብቻ ነበር። ከላይ የሮበርት ስም ከመጻፉ በስተቀር ፍፁም ተራ ፖስታ ነበር

"ይህን ማን እንደሰጠህ ታስታውሳለህ?"

"አዝናለሁ!" አለ ጸሐፊው ይቅርታ በመጠየቅ ዐይነት። በዛሬው ምሽት በሥራ ብዛት ተወጥረን ስለነበር ለማስታወስ አልችልም።"

አዎን አስፈላጊ አይደለም። ሰውዬው ፊቱን ማሳየት የለበትም። ካርዱን ከሆነ ቦታ ወስዶ ኤንቬሎፕ ውስጥ ይጨምረውና እንግዳ መቀበያው ዴስክ ላይ ጥሎ እርሱ ራቅ ብሎ ይጠብቃል። ጸሐፊው የትኛው ሳጥን ውስጥ ፖስታውን እንደከተተ ካየ የሮበርተን ክፍል ቁጥር አወቀ ማለት ነው። አሁን ሰውዬው ፎቁ ላይ የሮበርት መኝታ ክፍል ውስጥ ገብቶ እየጠበቀው ነው ማለት ነው። ሮበርት የጠላቱን ፊት የሚያይበት ጊዜ አሁን ነው። ቀደም ሲል ያያቸውን በቡድን ሆነው የሚመጡ ደስተኛ ሰዎች ድምፅ ሰማና ዘወር አለ። ከቅድሙ የበለጠ መሳከራቸው በሚገባ ያስታውቃል። አንደኛውን ሰውዬ ሮበርትን....."እንደምን ዋልክ? ምን ዐይነት ፓሪ አመለጥህ መሰለህ" አለው።

@BOOKALEM

የሮበርት አዕምሮ እየበረረ ነበር። "ፓሪዎችን ትወዳላችሁ?"

"አዎን!.....አዎን!"

"እውነተኛ ፈንጠዚያ ፎቅ ላይ እየደመቀ ነው። ልጃገረዶችና የምትወዱት ማንኛውም ነገር አለ። ተከተሉኝ!" አለና ሮበርት ይመራቸው ጀመር።

"ይህ ነው ትከክለኛ የአሜሪካኞች መንፈስ! አለና" ሰውዬው የሮበርትን ጀርባ መታ መታ አደረገው። "ሰምታችኋል ጓደኞቼ? ይህ ሰው ፓሪ ጋብዞናል" አለ። ሁሉም አሳንሰሩ ውስጥ ታጭቀው ገቡና ወደ ሦስተኛው ፎቅ ወጡ።

የደስታው ምሽት መሪ የሆነው ሰው....."እያችሁ እነዚህ የጣሊያን ሰዎች እንዴት እንደሚኖሩ ያውቃሉ። አንድ ዐይነት የደስታ በዓል አዘጋጅተዋል ብዬ እገምታለሁ" አለ።

"እውነተኛ ደስታ ምን እንደሚመስል አሳያችኋለሁ!" ሲል ሮበርት ቃል ገባላቸው። በረዥሙ ኮሪደር ውስጥ ሮበርትን ወደ መኝታ ክፍሉ ተከተሉት። ሮበርት ቁልፉን ቀዳዳው ውስጥ ጨመረና ወደ ሰዎቹ ዘወር አለ። "ጥቂት ደስታ ለማግኘት ሁላችሁም ዝግጁ ናችሁ?"

በብዛት የደስታ "አዎንታ!" መልስ ተሰጠው።

ሮበርት ቁልፉን ጠምዝዞ በሩን በርግዶ ከፈተውና ወደ ጎን ዘወር አለ። ክፍሉ ጨለማ ስለነበረ መብራቱን ቦግ አድርጎ ሲያበራው አንድ ቀጭን ፈዝም እንግዳ ሰው አፉ ላይ ድምፅ የለሽ ሲሊንደር የታሰረበት መውዜር ሽጉጥ ግማሽ በግማሽ ወጣ አድርጎ ይዞ እከፍሉ ማዕከላዊ ሥፍራ ላይ ቆሞ ነበር።

ሰውዬው በቡድን የመጡትን ሰዎች በድንጋጤ ተመለከተና ሽጉጡን ቶሎ ከተተው።

"ሄይ! የታለ የመጠጡ መደርደሪያ?" ሲል አንደኛው ጠየቀ።

ሮበርት ወደ ሰውዬው አለመከተና....."ሰውዬው አለው። ሂዱና ተቀበሉት" አላቸው።

ቡድኑ በአጠቃላይ ወደ ሰውዬው አመራ። "የታል መጠጡ ወንድም? በል አምጣው። ልጃገረዶቹስ የታሉ? ይህንን ፓሪ አውራ ጎዳናው ላይ ብናካሂደው ይሻላል።"

ሰውዬው ወደ ሮበርት ለመጠጋት እየታገለ ነው። ግን የሰው መንጋ መንግዱን ዘግቶት ነበር። ሮበርት ከውጭ ከፍሉን ዘግቶ ሲወጣ የሚያደርገው ነገር አጥቶ ይመለከት ጀመር። ሮበርት ሁለቱን ደረጃ አንዴ እየሳበ ቁልቁል በረረ።

በእንግዳ መቆያው አዳራሽ ውስጥ አቋርጦ ወደ ሆቴሉ መውጫ በር ሲያመራ አስተናጋጁ ከኋላው ጠራው።

"ኮማንደር ቤላሚ በኤር ፍራንስ አውሮፕላን ላይ ቦታ አስይዤልሃለሁ። የበረራ መስመር ቁጥር 321 ወደ ፓሪስ የሚያመራ ነው። ከጧቱ አንድ ሰዓት ጉዞውን ይጀምራል!" አለው።

@BOOKALEM

"አመሰግናለሁ" አለ ሮበርት።

በሩን አልፎ የስፓኒሽ ደረጃዎች ፊት ለፊት ወዳለው አነስተኛ አደባባይ ወጥቶ ታክሲ አስቆመና "ቪያ ሞንቴ ግራፓ" ብሎት ገባ።

አሁን ሮበርት ለጥያቄው መልስ አግኝቷል። ሊገድሉት እንደሚፈልጉ አረጋጧል። 'ግን በቀላሉ የሚፈፀም ወይም የሚወጡት አይሆንም!' አለ በሐሳቡ። አሁን ከአዳኝነት ፋንታ በታዳኝነት መድረክ ላይ ይገኛል። አሳዳጆቹ ራሳቸው በሚገባ አሠልጥነውት ዘዴአቸውን፤ ብልሃታቸውን፤ ጥንካሬአቸውን፤ ድክመታቸውን ሁሉ በሚገባ አብጠርጥሮ ያውቀዋል። በእርሱ ላይ የሚያደርጉትን የግድያ ሙከራ ለማስቆም ደግሞ ይህንን ዕውቀቱን በሚገባ መጠቀም እንዳለበት ተገነዘበ።

በመጀመሪያ ከእነርሱ ከትትል ውጭ ዱካውን የሚያጠፋበት መንገድ መፈለግ አለበት። እርሱን የሚያድኑት ሰዎች አንድ የማሳመኛ ታሪክ ተነግሮአቸዋል። ማለት እንደአደንዛዥ እጽ ያመላልሳል፤ ወይም የሰው ነፍስ አጥፍቷል፤ ወይም ሰላይ ነው ተብለው ሊሆን ይችላል። በጣም አደገኛ ሰው ስለሆነ ምንም ዕድል አትሰጡት። በቀጥታ ለመግደል ተኩሱ ተብለው ማስጠንቀቂያ ተሰጥተውም ሊሆን ይችላል።

"ሮማ ተርሚኒ!" ሲል ሮበርት የታክሲ አሽከርካሪውን አዘዘው። አሁን እያደኑት ቢሆንም ፎቶግራፉን ለማሰራጨት ጊዜ የላቸውም። ስለዚህ እስካሁን ድረስ ፊት የለሽ ሰው ነው የሚያድኑት።

ታክሲው ቪአ ጆቫኒ ጆአ ቲ 36ተኛ ጎዳና ላይ ደረሰ። ባለታክሲው ወደ ሮበርት ዞረና "ስታዚፋኒ ተርሚኒ ሰኞር!" ሲል አስታወቀው።

"እዚህ ጥቂት እንጠብቅ" አለውና ሮበርት ታክሲው ውስጥ ተቀምጦ የባቡር ጣቢያውን የፊት ለፊት አካባቢ በሚገባ ማጥናት ቀጠለ። ሁሉም ነገር ጤናማ ከመምሰሉ በላይ የሚከናወነው ሁሉ የተለመደው ዕለታዊ እንቅስቃሴ ብቻ ይመስላል። ታክሲዎችና ሸንጠ ረዣዥም አውቶሞቢሎች (ሊመዚን) መንገደኞችን እያራገፉና እያሳፈሩ ይመጣሉ ይሄዳሉ። የባቡር ጣቢያው ሠራተኞች ዕቃ ያራግፋሉ ይጭናሉ። አንድ የፖሊስ ባልደረባ ከተከለከለ የማቆሚያ ሥፍራ ላይ መኪኖችን ለማስነሳት እየተጣደፈ ነበር። በድንገት በሚካሄደው የተለመደው ጤናማ እንቅስቃሴ ውስጥ ምን የተበላሸ ነገር እንዳለ ተረዳ።

በቀጥታ ከባቡር ጣቢያው ፊት ለፊት "መቆም ክልክል ነው!" የሚል ምልክት በተደረገበት ቦታ ላይ ምንም ዐይነት የመለያ ምልክት ያልተደረገባቸው ሦስት ሸንጠ ረዥም መኪኖች የቆሙ ሲሆን ፖሊሱ ደግሞ እነሱን በተመለከተ ምንም የወሰደው እርምጃ የለም። ሮበርት ለታክሲው ሾፌር....."ሐሳቤን ለውጫለሁ። ወደ ቪአ ቬኔቶ 510 ኤ ውሰደኝ" አለው። ማንም ሰው እሱን ሊፈልግ የማይችልበት የመጨረሻው ሥፍራ ነው። የአሜሪካን ኤምባሲና ቆንስላ

@BOOKALEM

ከቪአ ቬኔቶ ፊት ለፊት የሮዝ ቀለም ባለው ሕንፃ ውስጥ ተዋቅረዋል። የኤምባሲው ጸሐፊት ቤት በአሁኑ ሰዓት የተዘጋ ሲሆን የቆንስላው ፓስፖርት ክፍል ግን ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ የደንበኛ አደጋ ችግሮችን በተመለከተ አገልግሎት ለመስጠት ሲባል ክፍት ነው። የመጀመሪያው ፎቅ ላይ አንድ የባሕር ኃይል ወታደር ከጠረጴዛ ኋላ ተቀምጦ ነበር።

ሮበርት ሲጠጋ ወታደሩ ቀና ብሎ ተመለከተውና....."ምን ልርዳዎት ጌታዬ?" ሲል ጠየቀው።

"ፓስፖርቴን ስለጣልኩ አዲስ ለመጠየቅ ነበር የመጣሁት" አለ ሮበርት

"አሜሪካዊ ዜጋ ነህ?"

"አዎን።"

አከፍሉ ውስጥ በርካታ ሰዎች ፓስፖርታችን ጠፍቷል እያሉ አዲስ ፓስፖርትና ቪዛ ለማግኘት ወይም ፓስፖርታቸውን ለማሳደስ እያመለከቱ ነበር።

"አልባኒያን ለመጎብኘት ቪዛ ያስፈልገኛል? እዚያ ዘመዶች ነበሩ....."

"በዛሬው ምሽት ፓስፖርቴ እንዲታደስልኝ እፈልጋለሁ። የምሳፈርበት አውሮፕላን....."

"ምን እንደደረሰ አላወቅም። ምናልባት ሚላን ውስጥ ሳልጥለው አልቀርም....."

"ፓስፖርቴን ከኪስ ቦርሳዬ ውስጥ ነው የወሰዱብኝ....."

ሮበርት ሁሉንም እያዳመጠ ቆመ። የፓስፖርት ሌብነት ኢጣሊያ ውስጥ ሞቅ ያለ ገቢ የሚያስገኝ የጎጆ ኢንዱስትሪ ነው።

'እዚህ ቦታ አዲስ ፓስፖርት የሚያወጣ ሰው መኖር አለበት' አለ በሐሳቡ። በሰልፉ የመጀመሪያ ረድፍ ላይ ዝንጥ ብሎ የለበሰ በመካከለኛ ዕድሜ ውስጥ የሚገኝ አንድ ሰው የአሜሪካ ፓስፖርት እየተሰጠው ነበር።

"ይኸው አዲሱ ፓስፖርትዎ ሚስተር ኮዋን! እንዲህ ዐይነት መጥፎ ነገር ስለገጠመዎት በጣም አዝናለሁ። እዚህም በርካታ ኪስ አውላቂዎች አሉ ብዬ እሰጋለሁ።"

"እርግጠኛ ነኝ ይህኛውን ፓስፖርቴን በፍጹም አላሰርቅም!" አለ ሚስተር ኮዋን።

"ልክ እንዲዚያ ያድርጉ ጌታዬ!"

ሰውየው ፓስፖርቱን የጃኬቱ ኪስ ውስጥ ጨምሮ ለመውጣት ሲዞር ተመለከተው። ሮበርት ቀደም ብሎት ተራመደ።

አንዲት ሴት ሮበርትን ነካ አድርጋው ስታልፍ ወደ ኮዋን ገድገድ አለና ገጨው። "በጣም አዝናለሁ። ይቅርታ!" አለና ሮበርት የኮዋንን ጃኬት አስተካከለለት።

"ምንም ችግር የለም" አለ ኮዋን።

@BOOKALEM

ሮበርት የሚስተር ኮዋንን ፓስፖርት በኪሱ ይዞ በአዳራሹ ውስጥ እያቋረጠ ወደ ወንዶች መፀዳጃ ክፍል ገባ። ብቻውን መሆኑን ለማረጋገጥ ዙሪያውን ከተመለከተ በኋላ አንድ ክፍል ውስጥ ገባ። ከዚያም ከሪኮ የሰረቀውን የወረቀት መቁረጫ ስለትና ማጣበቂያ ከኪሱ አውጥቶ በከፍተኛ ጥንቃቄ የፐላስቲኩን ሽፋን ቆረጠውና የኮዋንን ፎቶግራፍ ከፓስፖርቱ ላይ አንስቶ ሪኮ ያነሳውን ፎቶግራፍ በኮዋን ፓስፖርት ላይ አጣበቀው። በመጨረሻም ፕላስቲኩን መልሶ በማጣበቂያ ማስቲሽ አጣበቀና የእጅ ሥራውን ውጤት ተመለከተው። ፍፁም የተዋጣለት ነበር። አሁን ሮበርት ሚስተር ሄንሪ ኮዋን ሆነ። ከሠላሳ ደቂያዎች በኋላ ወደ ቪያ ቬኒስ ጎዳና ወጥቶ ታክሲ አስቆመና "ሊዎናርዶ ዳቪንቺ አየር ማረፊያ!" ብሎ ተሳፈረ።

ሮበርት አየር ማረፊያው ሲደርስ ከምሽቱ ስድስት ሰዓት ተኩል ሆኖ ነበር። ከአየር ማረፊያ ወጣ ብሎ ቆመና ያልተለመደ ነገር እንዳለ ለማጣራት መመልከት ጀመረ። ላይ ላዩን ሁሉም ነገር የተለመደና ትክክለኛ ይመስላል። የፖሊስ መኪና ወይም አጠራጣሪ ሰዎች አልነበሩም። ሮበርት ተርሚናሉ ውስጥ ገባና ዋናው በር ላይ ቆም አለ። በግዙፉ ተርሚናል ውስጥ በርካታ የተለያዩ የአየር መንገድ ባንኮኒዎች አሉ። በማንኛውም ሥፍራ የተደበቀ አጠራጣሪ ሰው አይታይም። ሆኖም ግን ሁኔታው ሁሉ ከሚገባው በላይ ሰላማዊ በመምሰሉ የሆነ ችግር ሊከሰት ይችላል በማለት ባለበት ቆሞ ይሰልል ጀመር።

አዳራሹን አቋርጦ የፈረንሳይ አየር መንገድ ዴስክ ነበር። አንድ ነገር ትዝ አለው። ‹"የፈረንሳይ አየር መንገድ የበረራ ቁጥር 312 ወደ ፓሪስ አስመዝግቤሃለሁ!"› ሮበርት የኤር ፍራንስን ዴስክ ላይ ወደ ቆሙች ሠራተኛ አመራ። "እንደምን አመሸሽ?"

"እንደምን አመሹ ሲኞር! ልረዳዎት እችላለሁ?"

"አዎን። እባክሽን በድምፅ ማጉያ ኮማንደር ቤላሚንን ወደ ስልኩ ብትጠሪልኝ።"

"በእርግጥ!" አለችና ድምጽ ማጉያውን አነሳች።

ሮበርት ጥቂት ራቅ ብሎ አንዲት በመካከለኛ ዕድሜ ላይ የምትገኝ ወፍራም ሴት ከአየር መንገድ ሠራተኛ ጋር በርካታ ሻንጣዎችን በተመለከተ ከሚፈቀደው ክብደት በላይ መከፈል ስላለበት ተጨማሪ ክፍያ ሞቅ ያለ ክርክር ስታደርግ ተመለከተ።

"አዝናለሁ ማዳም! ግን ይህ ሻንጣ እንዲሳፈር ከፈለጉ የትርፍ ጭነት ክፍያውን መክፈል ይኖርብዎታል።"

ሮበርት ጠጋ አለ። የሴትዮዋን ድምፅ በማይክሮፎኑ ሰማ። "ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ እባክህ ወደ ስልኩ ብትመጣ!" ጥሪው በመላው አየር ማረፊያ ውስጥ አስተጋባ።

@BOOKALEM

አንድ የመንገደኛ ሻንጣ በትከሻው የተሸከመ ሰው ሮበርትን አለፈው። "ይቅርታ!" አለ ሮበርት። ሰውዬው ዞር አለና "አቤት?" አለው።

"ባለቤቴ በድምፅ ማጉያ ስታስጠራኝ ሰማሁ። ሆኖም ግን....." አለና ወደ ሴትየዋ ሻንጣ እያመለከተ....."እነዚህን ሻንጣዎቼን ትቼ ለመሄድ አልቻልኩም።" ባለአሥር ዶላር ኖት አወጣና ለሰውዬው አቀበለው። "እባክህ ወደዚያ ነጭ ቴሌፎን ሄደህ በአንድ ሰዓት ውስጥ ሆቴላችን ድረስ ሄጄ እንደምወስዳት ብትነግርልኝ ትብብርህን አደንቅ ነበር።"

ሰውዬው በእጁ የጨበጠውን የአሥር ዶላር ኖት ተመለከተና "በሚገባ!" አለው።

ሮበርት ሰውዬው ወደ ስልኩ ሄዶ ብድግ ሲያደርገው ተመለከተ። መነጋገሪያውንም ጆሮው ላይ ለጥፎ....."ሄሎ.....ሄሎ?" ሲል ሰማው።

በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አራት ግዙፍ ሰዎች ከየት እንደመጡ ሳይታወቅ ሰውዬውን ተረባረበው ከግድግዳው ጋር አጣብቀው ያዙት።

"ሄይ ምንድን ነው ይሄ?"

"ይህንን በፀጥታ እናከናውነው" አለ ከሰዎቹ አንዱ።

"ምንድነው የምታደርጉት? እጃችሁን ከላዬ ላይ አንሱ!"

"አትቀልድ ኮማንደር ሮበርት። ምንም....."

"ኮማንደር? የተሳሳተ ሰው ነው የያዛችሁት። የኔ ስም ሜልቪን ዴቪስ ሲሆን የመጣሁት ከአሃማ ነው።"

"ድብብቆሽ ባንጫወት ጥሩ ይመስለኛል!" አለ አንዱ የፀጥታ ሠራተኛ።

"ቆዩ ቆዩ! የተዘጋጀልኝ ወጥመድ ነው። የምትፈልጉት ሰው እዚያ ነው" አለና ሮበርት ቆሞ ወደነበረነት ሥፍራ አመከለታቸው። በሥፍራው ማንም አልነበረም።

ከተርሚናሉ ውጭ አንድ የአየር መንገድ አውቶቡስ ለመልቀቅ እየተዘጋጀ ነበር። ሮበርት ከሌሎች መንገደኞች ጋር እየተጋፋ ተሳፈረበት። የሚቀጥለውን እንቅስቃሴውን በትኩረት እያሰበ የኋላው ወንበር ላይ ተቀመጠ።

እናያለን ብለው ያልገመቱትን ነገር በማያቸው ብቻ ለሞቱ ሰዎች ተጠያቂው ማን እንደሆነ ለማወቅ አሁን በመደረግ ላይ ስላለው ነገር ትክክለኛ መልስ ለማግኘት ሲል ሮበርት አድሚራል ዊታከርን ለማነጋገር ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ ተመኘ። 'ተጠያቂው ማን ይሆን? ጀኔራል ሒሊያርድ? ደስቲን ቶርንቶን? አማቱ ዊላንድ ስተን ምሥጢራዊው ሰው? እዚህ ሴራ ውስጥ በሆነ መልኩ ተሳትፎ ይኖረው ይሆን? ወይስ የብሔራዊ ፀጥታ ኤጀንሲ ዳይሬክተር የሆነው ኤድዋርድ ሳንደርስ ነው ለዚያ ወንጀል ኃላፊ? ወይስ ጉዳዩ እስከፕሬዚዳንቱ ድረስ ይዘልቅና ይነካካ ይሆን?' ሮበርት መልስ ይሻ ነበር። ወደ ሮም ከተማ በአውቶቡስ

@BOOKALEM

የተደረገው ጉዞ አንድ ሰዓት ያህል ሲወስድ አውቶቡሱ ኤደን ሆቴል ፊት ለፊት ሲቆም ሮበርት ወረደ።

«ከዚህ አገር መውጣት አለብኝ» አለ ሮበርት በሐሳቡ። ሮም ውስጥ ሊያምነው የሚችል አንድ ሰው ብቻ ነው ያለው። እሱም ኮሎኔል ፍራንሴስኮ ቄሳር የተባለ የኢጣሊያ መንግሥት የምሥጢር አገልግሎት (የመረጃ ድርጅት) የበላይ የሆነ ሰው ነው።

ኮሎኔል ቄሳር ሁልጊዜ ዘግይቶ ወይም አምሽቶ ይሠራል። ከውጭ አገር የመረጃ ድርጅቶች ወደ ውጭና ወደ ውስጥ የመልዕክት ዐይነቶቹ ይጎርፋሉ። ታዲያ ሁሉም የሚመለከቱት ኮማንደር ሮበርት ቤላሚን ነው። ኮሎኔል ቄሳር ባለፉት ዓመታት ከሮበርት ጋር ጎን ለጎን ከመሥራቱም በላይ በጣም ይወደውና ያስብለትም ነበር። ቄሳር አጠገቡ ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን ትኩስ መልዕክት ተመለከተና በረጂሙ ተነፈሰ። "ይገደል!" ነበር የሚለው። መልእክቱንም በማንበብ ላይ እንዳለ ጸሐፊው ቢሮ ውስጥ ገባች።

"ኮማንደር ቤላሚ በቁጥር አንድ መስመር ላይ ይጠብቅሃል።"

ኮሎኔል ቄሳር ትክ ብሎ ተመለከታት። "ግድ የለም እሺ!" አለና ጸሐፊው እስክትወጣለት ጠበቀና ስልኩን ብድግ አደረገ።

"ሮበርት?"

"ቻው! ፍራንሲስኮ። ምንድን ነው እየተከናወነ ያለው?"

"አንተው ንገረኝ እንጂ ጓደኛዬ። ስላንተ ብዙ ዐይነት መልዕክቶችን ስቀበል ነበር የቆየሁት። ለመሆኑ ምንድነው ያጠፋህው?"

"በጣም ረዥም ታሪክ ስለሆነ የማስረዳበት ጌዜ የለኝም። ለመሆኑ አንተ የሰማህው ምንድን ነው?"

"ወደ ግል መግባትህና መከዳትህ እንዲሁም ምሥጢር በማውጣት ላይ እንደሆንክ....."

"ምን?"

"ከቻይናዎቹ ጋር ስምምነት ማድረግህን ከመስማቴም በላ....."

"የክርስቶስ ያለህ! ይህ ሁሉ አልባሌ ወሬ ነው።"

"ነው? ለምን?"

"ምክንያቱም ከአንድ ሰዓት በፊት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በጣም ተርበው ነበርና።"

"ስለእግዚያብሔር ሮበርት። ይህ የሚቀለድበት ነገር አይደለም እኮ!"

"ቀደም ሲል ኢሥር ንፁሃን ሰዎችን ወደ መቃብራቸው ሰድጃለሁ። እኔ ደግሞ በኢሥራ አንደኛነት ተራ ተይዞልኛል። እስቲ ስለዚህ ጉዳይ አስረዳኝ ፍራንሲስኮ።"

"አሁን የት ነው ያለህው?"

@BOOKALEM

"እዚህ ሮም ውስጥ ነኝ። ከዚህ የተረገመ ከተማህ ለመውጣት የምትችል አልመሰለኝም።"

ለጥቂት ደቂቃዎች በሐሳብ የተሞላ የፀጥታ ጊዜ አለፈ። "አንተን ለመርዳት ምን የማደርገው ነገር አለ?"

"ልንነጋገር ወደምንችልበት አስተማማኝ ቤት ውሰደኝ። ከዚያም እንዴት ለመውጣት እንደምችል እቅድ አወጣለሁ። ይህንን ማመቻቸት ትችላለህ?"

"እዎን ግን በጣም መጠንቀቅ አለብህ። እኔ እራሴ መጥቼ እወስድሃለሁ።"

ሮበርት በረዥሙ በእፎይታ ተነፈሰ። "አመሰግናለሁ ፍራንሴስኮ። በእውነት አደንቅሃለሁ።"

"እናንተ አሜሪካዊያን እንደምትሉት....."ብድር አለብህ!"› አሁን የት ነው ያለህው?"

"ትሬስቴቬር ውስጥ ሊዶ ቡና ቤት።"

"እዚያው ጠብቀኝ። በአንድ ሰዓት ውስጥ አገኝሃለሁ።"

"አመሰግናለሁ አሚኮ!" አለና ሮበርት ስልኩን አስቀመጠ። 'በጣም ረዥም ሰዓት ሊሆን ነው አለ በሐሳቡ።'

ከሠላሳ ደቂቃዎች በኋላ ሁለት ምልክት የሌላቸው መኪናዎች ከሊዶ ቡና ቤት አሥር ያርድ ያህል ራቅ ብለው ቆሙ። እያንዳንዱ መኪና ውስጥ አራት አራት ሰዎች ሲኖሩ በሙሉ አውቶማቲክ መሣሪያዎች ታጥቀዋል።

ኮሎኔል ቄሳር ከመኪናው ውስጥ ወጣና....."ይህንን ጉዳይ በፀጥታ እንፈጽመው! ማንም ሰው እንዲጎዳ ማድርግ የለብንም" አለ። "አልዳንቴ አልዳይትሮ ሱቪቶ!" ግማሾቹ የሕንፃውን ጀርባ ለመሸፈን ሮጡ።

ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ከመንገዱ ባሸገር የአንድ ሕንፃ የመጨረሻ ጣራ ላይ ሆኖ ሰዎቹ መሣሪያቸውን ደግነው ያለ የሌለ ጥይታችውን ቡና ቤቱ ላይ ሲያዘንቡበት ተመለከተ።

'ጥሩ እናንተ ዲቃሎች! ጨዋታውን በናንተ ዐይነት መንገድ እንጫወተዋለን!' አለ በሐሳቡ በይቅርታ የለሽነት።

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሠላሳ አምስት

ኣሥራ ስድስተኛ ቀን

ሮም ኢጣሊያ

ሮበርት ፒያዛ ዴል ዳሞ ከሚገኝ የቴሌፎን ጣቢያ ሆኖ ለኮሎኔል ፋራንሴስኮ ቄሳር ስልክ አደረገለት። "በጓደኝነት ላይ ምን ተፈጠረ?" ሲል ሮበርት ጠየቀው።

"ጓደኛዬ የዋህ አትሁን። እኔም ልክ እንዳንተ በትእዛዝ ስር ነው ያለሁት። የምታደርገው የማምለጥ ሙከራ ምንም ጥቅም የለውም ስል ላረጋግጥልህ እችላለሁ። በመላው ዓለም የመረጃ ድርጅቶች ሊስት ላይ የአንደኛ ደረጃ "በጣም ተፈላጊ!" ማዕረግ ተሰጥቶሃል። ግማሹ የዓለም መንግሥታት ናቸው እያደኑህ ያሉት።"

"በከሃዲነቴ ታምናለህ?"

ቄሳር በረጅሙ ተነፈሰ። "እኔ የማምንበት ጉዳይ ምንም ዋጋ የለውም ሮበርት። ይህ ፈጽሞ የግል ጉዳይ አይደለም። ትዕዛዝ ነው።"

"እኔን ለመግደል?"

"እጅህን በመስጠት ጉዳዩን ልታቀለው ችችላለህ።"

ሮበርት "አመሰግናለሁ" አለና ስልኩን ደረገመው።

ሮበርት ብዙ በቆየ ቁጥር የሚደርስበት አደጋ የሰፋ እንደሚሆን አውቆታል። ከግማሽ ደርዘን በላይ ከሚሆኑ አገሮች የሚላኩ የስለላ ሠራተኞች ዙሪያውን እያጠበቡበትና እየዘጉበት እንደሚመጡ ተገንዝቧል። 'አንድ ዛፍ መኖር አለበት!' ሲል ሮበርት አሰበ። ይህ አነጋገር የመጣው ሽርሽር ላይ ታሪኩን ካወራ አንድ አዳኝ ነው።

"ይህ ግዙፍ አንበሳ ወደኔ እየጋለበ በመምጣት ላይ ነው። አጠገቤ የነበሩት ጠመንጃ አቀባዬቼ በሙሉ ነፍሳቸውን ለማዳን በረሩ። እኔም ያለጠመንጃና ያለምንም መደበቂያ ሥፍራ ቀረሁ። አንዲት ቁጥቋጦ ወይም አንድ ዛፍ ካለመኖሩም በላይ አውሬው ወደኔ እየበረረ በመምጣት ላይ ነበር። "እንዴት አመለጥክ?" ሲል አንድ አድማጭ ጠየቀው። "ቅርብ ወዳገኘሁት አንድ ዛፍ ሩጬ ሄድኩና ተንጠላጥዬ ወጣሁ።"

"ግን ምንም ዛፍ የለም ነበር ያልከው?" አለ አድማጩ።

"አልገባህም?" አለ ተራኪው። "አንድ ዛፍ መኖር አለበት!" 'አምን ዛፉን መፈለግና ማግኘት አለብኝ!' አለ ሮበርት በሐሳቡ።

@BOOKALEM

የጢያሳውን ዙሪያ ገባ ተመለከተ። በዚህ ሰዓት ፈፅሞ ጭር ብሎ ነበር። አሁን ለዚህ ሁሉ ቅዠት የዳረገውን ‘ጄነራል ሒሊያርድን የማነጋገሪያ ሰዓት ነው ሲል ወሰነ። ግን መጠንቀቅ እንደሚገባውም አልዘነጋም። ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ የስልክ አቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያዎች እጅግ በጣም ቅፅበታዊ በሆነ ፍጥነት አንድ ሰው የት አገር የት ቦታ ሆኖ እንደሚደውል ለመጠቆም ይችላሉ። ሮበርት በአቅራቢያው የሚገኙ ሁለት የቴሌፎን መደወያ ሳጥኖች ያለመያዛቸውን ተመለከተ። ጄነራል ሒሊያርድ የሰጠውን የግል የስልክ ቁጥር ተወና ወደ ኤንኤስኤ (national security agency) የስልክ ኦፕሬተር ደወለ። ጥሪውን አንድ ኦፕሬተር እንደመለሰ.....“እባክህ ከጄነራል ሒሊያርድ ቢሮ ጋር አገናኘኝ” አለ።

ከተወሰነ ጌዜ በኃላ.....“የጄነራል ሒሊያርድ ጽሕፈት ቤት!” የሚል የጸሐፊዋ መልስ መጣ።

“እባክሽን ለአገር አቋራጭ ጥሪ ትንሽ ጠብቂ!” አለና ስልኩን ሳይዘጋው ወደ ሁለተኛው የስልክ ሳጥንበፍጥነት ሄዶ ያንኑ ቁጥር ደገመና ደወለ። “ሌላ ጸሐፊ.....“የጄነራ ሒሊያርድ ቢሮ!” ስትል መለሰች።

“እባክሽን ለአገር አቋራጭ ጥሪ ጥቂት ጠብቂኝ!” አለና ስልኩን እንደተንጠለጠለ ትቶት ወደ ሦስተኛው የስልክ ቤት እየሮጠ ሄዶ የቀድሞውን ቁጥር በመደወል.....“ይህ ከማንደር ሮበርት ቤላሚ ነው። ጄነራል ሒሊያርድን ለማነጋግር አፈልጋለሁ” አለ።

የመደናገጥ ድምፅ ተሰማ። “ጥቂት ጊዜ ኮማነደር!” አለችና ጸሐፊዋ የውስጥ መገናኛ መሣሪያውን ጫን ብላ.....“ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ በመስመር ላይ ነው ጄነራል!” አለች።

ጄነራል ሒሊያርድ ወደ ሐሪስን ዞር አለና.....“ኮማንደር ቤላሚ በመስመር ሦስት ላይ ነው። የአቅጣጫ ፍለጋ ሥራውን በአስቸኳይ ጀምር!” አለው።

ሐሪስን ኬለር ጠረጴዛ ላይ ወዳለ ስልክ እየተጣደፈ ሄደና ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ የመልዕክት ስርጭት ቁጥጥርና ፍተሻ ለሚደረግበት የግንኙነት ማዕከል ደወለ። የማዕከሉ የበላይ መኮንን አዳምስ የተባለ ሰው ነው።

“ኤንኤቢ አዳምስ!”

በወጪና ገቢ የስልክ ጥሪ ላይ የአቅጣጫ ጥቆማ ሥራ ለማከናወን ምን ያህል ጊዜ ይወስድባችኋል?” ሲል ሐሪስን ኬለር በዝግታ ሹክ አለ።

“አንድ ወይም ሁለት ደቂቃዎች።”

“የጄነራል ሒሊያርድ ቢሮ ውስጥ መስመር ቁጥር ሦስት ላይ ሥራህን ጀምር። እኔም እጠባበቃለሁ” አለና ለጄነራል ሒሊያርድ ምልክት ሰጠው።

“ጄነራል ሒሊያርድ ስልኩን አነሳ። “ኮማደንር አንተ ነህ?”

“እርስዎና እኔ የምንነጋገርበት ጌዜ አሁን ነው ብዬ አስባለሁ ጄነራል።”

@BOOKALEM

"ስለደወልክ በጣም ተደስቻለሁ ኮማንደር። ለምን ወደዚህ መጥተህ ስለሁኔታው አንነጋገርበትም? የምትመለስበት አውሮፕላን ላዘጋጅልህ እችላለሁ። በጥቂት ጊዜ ውስጥ....."

"የለም አመሰግናለሁ። በአውሮፕላኖች ላይ በጣም በርካታ «አደጋዎች» ይደርሳሉ ጄነራል።" አለ ሮበርት።

በመገናኛው ማዕከል ውስጥ (ኤን.ኢ.ሲ) የኤሌክትሮኒክስ መቆጣጠሪያ መሣሪያው ሥራውን ጀምሯል። የኮምፒተሩ ስክሪን ላይ ኤ.ኢ.ዲ.ኤስ.121 ቢ122 ሲ 123 ሲ የሚል ጽሑፍ እየበራ ነው።

"ምንድነው ነገሩ?" አለና ኬለር በስልኩ ውስጥ ሹክ አለ።

"ኒው ጀርሲ ያለው የግንኙነት ማዕከል ዋሺንግተን ዲሲ ውስጥ የሚገኙ የስልክ ሳጥኖችን በመፈተሽ ላይ ስለሆነ ትንሽ ይጠብቁ።" የኮምፒተሩ ስክሪን ባዶ ሆነ። ከዚያም አገር አቋራጭ የስልክ ሳጥን መስመር አንድ የሚል ጽሑፍ ኮምፒተሩ ላይ በራ።

"ጥሪው የመጣው አውሮፓ ውስጥ ከሆነ ሥፍራ ነው። አገሩን ለመለየት እየሞከርን ነው።"

ጄነራል ሒሊያርድ ንግግር እያደረገ ነበር። "ኮማንደር ቤላሚ! አለመግባባት አለ ብዬ እገምታለሁ። አንድ አስተያየት አለኝ ሮበርት።"

ሮበርት ጄነራሉን ሳያስጨርሰው ስልኩን ዘጋው። ጄነራል ሒሊያርድ ወደ ኬለር ዘወር አለና "አገኘህው?" ሲል ጠየቀው።

ሐሪስን ኬለር ደግሞ ከአዳምስ ጋር በስልክ እየተነጋገረ ነው። "ምን ተፈጠረ?"

"ጠፋብን።"

ሮበርት ወደ ሁለተኛው የስልክ ሳጥን አመራና አነሳው።

ጸሐፊዋ ጄነራል ሒያርድን....."ኮማንደር ቤላሚ መስመር ሁለት ላይ እየጠራ ነው" ስትለው ጄነራሉ ከመስመር ሁለት ጋር የሚያገናኘውን ቁልፍ ተጫነው።

"ኮማንደር?"

"አንድ ሐሳብ ላቅርብ" አለ ሮበርት።

ጄነራል ሒሊያርድ መናገሪያውን በመዳፍ ሸፈነና....."እቅጣጫ ፍለጋውን እንደገና ቀጥል" አለው።

ሐሪስን ኬለር ስልኩን አነሳና....."መስመር ሁለት ላይ ነው ያለው። በፍጥነት ተንቀሳቀስ!" አለው አዳምስን።

"ቀጥል" አለው ጄነራሉ ሮበርትን።

"የኔ ሐሳብ ጄነራል! ያሰማራህብኝን ሰዎች አሁኑኑ አስነሳ። አሁን!"

@BOOKALEM

"ሁኔታው የገባህ አይመስለኝም ሮበርት። ይህን ችግር ለመፍታት አንተ....."

"እንዴት እንደምትፈታው እኔ እነግርሃለሁ። እኔን የማስገደል ትዕዛዝ ወጥቷል። አሁኑኑ እንድታሰርዘው እፈልጋለሁ ።"

በመገናኛ ማዕከሉ ውስጥ አዳምስ በስልክ....."ሮም ከተማ ውስጥ መሆኑን አውቀናል" አለው።

"ቁጥሩንና አቅጣጫውን አሁኑኑ ስጠኝ" አለ ኬለር።

ሮበርት የእጅ ስዓቱን ተመለከተና....."አንድ ተልዕኮ ሰጠኸኝ እኔም ተወጣሁት" አለ።

"በጣም ግሩም ሥራ ነው የሠራህው ሮበርት። እኔ የምለው ለ....." ስልኩ ተዘጋ።

ጄነራሉ ወደ ኬለር ዘወር አለና....."እንደገና ዘጋው!" አለው።

ኬለር አዳምስን በስልኩ ወስጥ እንዲህ ሲል ጠየቀው። "አቅጣጫውን አገኘህው?"

"አላገኘሁትም" ሲል መለሰ።

ሮበርት ወደሚቀጥለው ስልክ ሄደና አነሳው። በውስጥ መገናኛው ማሣሪያ (ኢንተርኮም) ጸሓፊዋ....."ኮማንደር ቤላሚ በመስመር አንድ ላይ ይጠራል" ሰትል አስታወቀች።

ጄነራል ሒሊያርድ....."ይህንን ዲቃላ ፈልግልኝ!" ብሎ ጮኸና ስልኩን ብድግ አደረገው። "በጥንቃቄ እንድታዳምጠኝ እፈልጋለሁ ጄነራል ሒሊያርድ። በርካታ ንፁሃን ሰዎችን ገድለሃል። በኔ ላይ ያሰማራሃቸውን ገዳዮች ካላነሳህ ወደ መገናኛ ብዙሃን ሄጄ በመደረግ ላይ ያለውን ጉድ ለዓለም ሕዝብ አሳውቃለሁ።"

"ዓለም አቀፍ የሆነ ሽብርና ፍርሃት እንዲነሳ ካልፈለክ በስተቀር ይህንን አድርግ ብዬ አልመክርህም። ከዓለማችን ውጭ ያሉት ፍጡራን በገሃድ ወይም በእርግጥ ያሉ ናቸው። እኛ ደግሞ በነሱ አንፃር መከላለያ የለሾችን ነን። እንቅስቃሴአቸውን ለመጀመር ዝግጁ ሆነዋል። የዚህ ጉዳይ አንዲት ቃል እንኳ ወደ ሕዘቡ ጆሮ ቢወጣ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ፈጽሞ አታውቅም።"

"እንተም እንደዚሁ! አለ ሮበርት። እኔ ላንተ ምርጫ እያቀረብኩልህ አይደለም። በኔ ላይ የሰጠህውን ትዕዛዝ አንሳ። ካሁን በኋላ አንድ ተጨማሪ የመግደል ሙከራ ቢደረግብኝ ወደ መገናኛ ብዙሐን መሄዴ ነው።"

"እሺ በጣም ጥሩ አሸንፈሃል። ትእዛዙን አነሳለሁ። ለምን እንዲህ አታደደርግም? እኛ....."

"የአቅጣጫ መፈለጊያው አሁን በጥሩ ሁኔታ በመሥራት ላይ ነው ጄነራል! መልካም ቀን ይሁንልህ!" ስልኩ ተዘጋ።

"አገኘህው?" አለና ኬለር በስልኩ ውስጥ ጮኸ።

@BOOKALEM

"ተቃርቤ ነበር ጌታዬ። ጥሪ የሚያደርገው ከሮም መዕካለዊ ሥፍራ አካባቢ ነበር። ስልኮችን ይለዋወጥብን ስለነበረ አላገኘንውም።"

ጀኔራሉ ወደ ኬለር ተመለከተ። "ታዲያስ?"

"አዝናለሁ ጄነራል። የምናውቀው ሮም ውስጥ መሆኑን ብቻ ነው። የተናገረውን ማስፈራሪያ ያምኑበታል? የተሰጠበትን ትዕዛዝ ማንሳት አለብን?"

"የለም አይነሳም እናጠፋዋለን።"

ሮበርት የነበረውን የመውጫ አማራጭ እንደገና ሲመረምረው በሚያሳዝን ሁኔታ በጣም ጥቂት ነበር። በአሁኑ ጊዜ የአየር ማረፊያዎችን፤ የባቡር ጣቢያዎችን፤ የአውቶቡስ ጣቢያዎችን፤ የመኪና አከራይ ወኪሎችን ሁሉ በመቆጣጠር ላይ ናቸው። ሆቴል ቤት ተከራቶ መግባት አይችልም። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ "ሲፋር" ቀይ የማስጠንቀቂያ መልዕክት አሰራጭቶ መሆን አለበት። የሆነው ቢሆን ግን ሽፋን አግኝቶ ከሮም መውጣት አለበት። አሳዳጆቹ የሚመለከቱት ወንድና ሴት ጣምራዎችን አይደለም። ጅማሬው ይህ ነበር።

አንድ ጥግ ታክሲ ቆሞ ነበር። ሮበርት ፀጉሩን በተን በተን ከራሳቱን ዝቅ አደረገና እንደሰከረ ሰው እየተንገዳገደ ወደ ታክሲው ሄዶ "ሃይ አንተ!" አለና ተጣራ።

አሽከርካሪው በጥላቻ ተመለከተው።

ሮበርት የአሥር ዶላር ኖት አወጣና ለሹፌሩ አስጨበጠውና አንዲት የምታጋድመኝ እፈልጋለሁ ። "ምን ማለቴ እንደሆነ ገባህ?"

ሮበርት ታክሲ ውስጥ ሲገባ መኪናዋ ተፈተለከች። ወደ ኋላው ዞር አለና ተመለከተ። የሚከታተለው አልነበረም። ፍርሃት ከመቸውም በበለጠ እየተሰራጨበት ነበር። ከዓለም መንግሥታት ግማሹ እያሳደዱት ነው። ይግባኝ የሌለው የግድያ ትዕዛዝ ነበር የተሰጠበት።

ከሃያ ደቂቃዎች በኋላ ቶር ዲ አንቶን የተባለው የሴትኛ አዳሪዎችና የእቃጣሪዎች ቀይ መብራት ሰፈር ደረሰ። አሽከርካሪው መኪናውን ጥግ አስይዞ አቆማት።

"የፈለካትን ሴት እዚህ ማግኘት ትችላለህ።"

"አመሰግናለሁ!" አለና ሮበርት ቆጣሪው የሚያሳየውን ሒሳብ ከፍሎ ከታክሲው ወረደ። ሮበርት ታክሲው ከሄደ በኋላ የነበረበትን አካባቢ ዙሪያውን ተመለከተ። የፖሊስ መኪናዎች አይታዩም። በጣም ጥቂት የሆኑ መኪናዎችና እግረኞች ብቻ ናቸው የሚታዩት። ከደርዘን በላይ የሚሆኑ ሴትኛ አዳሪዎች መንገዱን ወረውታል። ከመካከላቸው አንዲት የሮበርትን ዐይን የሳበች ነበረች።

ገና በመጀመሪያዎቹ ሃያ ዓመታት ውስጥ ያለች ትመስላለች። ረዥም ጥቁር ፀጉር አላት። ጥቁር ቀሚስ በነጭ ሸሚዝ ለብሳ በላዩ ላይ ከግመል ፀጉር

@BOOKALEM

የተሠራ ኮት ጣል አድርጋበታለች። ሮበርት በትርፍ ሰዓቷ በሞዴልነት ወይም በተዋናይነት ሳትሠራ አትቀርም ብሎ ገመተ። እሷም ሮበርትን በትኩረት እየተመለከተቸው ነበር።

ሮበርት እንደመንገዳገድ እያለ ወደ እርሷ ሄደ። "ሄይ ቤቢ! እንግሊዘኛ መናገር ትችያለሽ?" አላት።

"አዎን።"

"በጣም ጥሩ! እስቲ እኔና አንቺ ግሩም የሆነ ፓርቲ እናድርግ" አላት።

እርግጠኛ ባለመሆን ፈገግ አለችለት። 'ሰካራሞች ምንጊዜም ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ።'

"መጀመሪያ ስካርህ ቢለቅህ ሳይሻል አይቀርም!" አለች ለስለስ ባለ የጣሊያኖች ያነጋገር ዘይቤ።

"ሄይ! ስካሩ በሚገባ ለቆኛል" አላት።

"አንድ መቶ ዶላር ያስወጣሃል።"

"አ.....ዎ አመሰግናለሁ ወለላዬ።"

"ባ ቤኔ! ና እንሂድ" አለችው። "ከዚህ ጥቂት አለፍ ብሎ አንድ ሆቴል አለ።"

"ጥሩ! ማነው ስምሽ ልጂት?"

"ፒየር።"

"የኔ ሔነሪ ነው" አላት። አንድ የፖሊስ መኪና መንገዱን ይዞ ወደ እነርሱ አቅጣጫ መጣ። "ከዚህ አካባቢ እንውጣ" አለች። ሴትኛ አዳሪዎቹ ፒየርና አሚሪካዊ ደንበኛዋ ተያይዘው ሲሄዱ በቅናት አዩአቸው። ሆቴሉ የሐሰለር ዐይነት አይደለም። የአቃጣሪ ዐይነት ገጽታ ያለው ዴስኩ ላይ የቆመው አስተናጋጅ ፓስፖርት አልጠየቀውም። የመኝታ ቤቱን ቁልፍ ለፒየር ሲሰጣት በጨረፍታ ቀና ብሎ ተመለከታትና....."ሃምሳ ሺህ ሊሬ" አላት። ፒየር ሮበርትን አየት ስታደርገው ፖንዘቡን ከኪሱ አወጣና ለልጁ አሰረከበው። የገቡበት ክፍል ወደ ጥግ ላይ አንድ አልጋ፤ ጠረጴዛና ሁለት ወንበሮች እንዲሁም የፊት መታጠቢያ ከመስተዋት ጋር አለው። ከበሩ በስተኋላ ደግሞ የልብስ ቁም ሳጥን ነበረው። ሒሳቤን በቅድሚያ መክፈል አለብህ" አለች ፒየር።

"በሚገባ" አለና ሮበርት አንድ መቶ ዶላር አውጥቶ ሰጣት።

"ግራዜ!" አለች።

ፒየር ልብሷን ማወላለቅ ስትጀምር ሮበርት ወደ መስኮቱ ሄዶ የመጋረጃውን አንድ ጫፍ ገለጠና ወደ ውጭ መመልከት ጀመረ። ሁሉም ነገር ሰላማዊ ይመስላል። 'በአሁኑ ጊዜ ፖሊሶች የጭነት መኪናውን ፈረንሳይ ውስጥ እየተከታተሉ ነው' ሲል ገመቶ። ሮበርት መስኮቱን ጋርዶ ሲዞር ፒየርን እርቃኗን

@BOOKALEM

ቆማ አያት። በጣም ውብ የሆነ ሰውነት አላት። ጥብቅና አነስ ያሉ ጡቶች፤ ከብ የሆነ ዳሌ፤ አነስ ያለ ሽንጥና ጥሩ ቅርፅ ያላቸው ረዣዥም እግሮች ተጎናፀፋለች።

ሮበርትን እያየችው....."ልብስህን አታወልቅም እንዴ?" ስትል ጠየቀችው።

"እውነቱን ለመናገር በጣም በርከት አድርጌ ስለጠጣሁ ብዙም እንቅስቃሴ ልሰጥሽ የምችል አይመስለኝም።"

በጠንቃቃ ዐይኖቿ እያየችው....."ታዲያ ለምን.....?

"አሁን ከተኛሁኝና ስካሩን ካበረድኩት ሲነጋ መዳራት እንችላለን።"

በምንቸገረኝነት ትከሻዋን ነቀነቀችና....."መሥራት አለብኝ። ለ.....ገንዘብ ያስወጣኛል" አለችው።

"አትጨነቂ!" አለና በርካታ የአንድ መቶ ዶላር ኖቶች አውጥቶ ይህ ይሸፍነዋል?" አላት።

አሥራ ሰባተኛ ቀን

ሮም ኢጣሊያ

ሮበርት የማለዳ ፀሓይ ፊቱን እየመታች ስታሞቀው ነበር ከእንቅልፉ የነቃው። ግራ ተጋብቶ አደጋ ይኖራል በማለት በፍጥነት ዙሪያውን ተመለከተ። ፒየርን ሲመለከታት የማታው ትዝታ ሁሉ ተመልሶ መጣለትና ሰውነቱ ዘና አለ።

ፒየር መስታወቱ ላይ ቆማ ፀጉሯን እየቦረሸች ነበር። "ቦን ጆርኖ! አላንኮራፈህም!" አለችው።

ሮበርት የእጁ ሰዓቱን ሊመለተከት ከጧቱ ሦስት ሰዓት ሆኖ ነበር። እንደዓልማዝ ውድ የሆነ ሰዓት ነው የባከነው።

"አሁንስ ፍቅር መሥራት አትፈልግም? ገንዘብህን ከፍለህበታል እኮ።"

"አይ ምንም አይደለም!" አላት። 'ብፈልግም አልችልም የኔ ልጅ' አለ በሐሳቡ።

"ቤኔ!" አለችና ልብሷን እየለበሰች....."ለመሆኑ ሱዛን ማናት?" አለችው እንደዋዛ። "በአንቅልፍ ልብህ ስለእርሷ ስታወራ ነበር።"

ሕልሙ ትዝ አለው። ሱዛን ተመልሳ መጥታለት ነበር። ወይም ምንአልባት ይህ የመመለሷ ምልክት ነበር። "ጓደኛዬ ናት" አላት ባጭሩ። «ቢሐሳቡ....."ሚስቴ ናት። የገንዘብ ከረጢትን ትሰለችና አንድ ቀን ትመለስልኛለች። አስከዚያው ድረስ በሕይወት ከቆየሁ።'»

ሮበርት ወደ መስኮቱ ተራምዶ መጋረጃውን ገለጥ አደረገና ወደ ውጭ ተመለከተ። መንገዶቹ በእግረኞችና ሱቃቸውን በሚከፍቱ ነጋዴዎች ተጣበዋል። ምንም ዐይነት የአደጋ ምልክት የለም። ወደ ልጅቷ ዘወር አለና....."ፒየር ከኔ ጋር አጭር ጉዞ ብትሄጅ ምን ይመስልሻል?" አላት።

"ጉዞ ወዴት?" አለች በጥርጣሬ እያየችው።

@BOOKALEM

"ለንግድ ሥራ ጉዳይ ወደ ቬኒስ መሄድ አለብኝ። ብቻዬን መጓዝ አስጠልቶኛል። ቬኒስ ከተማን ትወጃታለሽ?"

"አዎን።"

"ጥሩ! ለምታባክኝው ጊዜ እከፍልሻለሁ። እናም ጥሩ የበዓል ጊዜ አብረን እናሳልፋለን።" በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከተ ነበር። "ቬኒስ ውስጥ ሲፒሪያኒ የተባለ ተወዳጅ ሆቴል አውቃለሁ" አላት።

"በቀን አንድ ሺህ ዶላር ያስወጣሃል" አለችው። ከተከራከራት በአምስት መቶ ዶላር ለመስማማት ዝግጁ ነበረች።

"ተስማምተናል!" አለና ሮበርት ሁለት ሺህ ዶላር ቆጥሮ እየሰጣት....."በዚህ እንጀምራለን" አላት።

ፒየር አመነታች። 'ችግር የሚያስከትል አንድ ስህተት አለ' የሚል ስሜት አደረባት። ቢሆንም አንድ ትንሽ ሚና ትጫወትበታለች ተብሎ ተስፋ የተሰጣት የፊልም ተወኔት በመዘግየቱ ገንዘብ ያስፈልጋት ነበርና....."በጣም ጥሩ እንሂድ!" ስትል ተስማማች።

በእንግዳ መቀበያው አዳራሽ በር ወደ ውጭ ወጥተው ታክሲ ከመከራየታቸው በፊት ሮበርት ጎዳናውን በጥንቃቄ ሲቃኝ ተመለከተችው።

'ለአንድ ለሆነ ሰው ዒላማ ሳይሆን አይቀርም። ከዚህ ጣጣ ውስጥ መውጣት አለብኝ'አለች በሐሳቧ።

"ተመልከት" አለች ፒየር። "ካንተ ጋር ወደ ቬኒስ በመሄዴ እርግጠኛ አይደለሁም። እኔ....."

"በጣም አሰደሳች የሆነ ጊዜ እናሳልፋለን" አላት ሮበርት።

አውራ ጎዳናውን አቋርጦ ከፊታቸው አንድ የጌጣ ጌጥ መሸጫ ሱቅ ተመለከተ። ወዲያው የፒየርን እጅ ያዘና....."ነይ አንድ ውብ የሆነ ነገር እገዛልሻለሁ" አላት።

"ግን....."

ወደ ጌጣ ጌጥ ሱቁ መንገዱን አቋርጦ እየመራ ወሰዳት።

ከባንኩኒው በስተኋላ የቆመው ጸሓፊ....."ቦን ጆርኖ ሲኞሬ! ልረዳዎት እችላለሁ?" አለው።

"አዎን" አለ ሮበርት። ለወይዘሪቷ የሚስማማ ቆንጆ ነገር እየፈለግን ነው" አለና ወደ ፒየር ዘወር ብሎ....."ሉል ትወጃለሽ?" አላት።

"እኔ.....አዎ።"

ሮበርት ወደ ጸሓፊው ዘወር አለና....."ከሉል የተሠራ የእጅ አምባር አለህ?" አለው።

"ሲኞሬ! በጣም ውብ የሆነ የሉል አምባር አለኝ።" ወደ ማስቀመጫው ሄደና ከሉል የተሠራ የእጅ አምባር ብድግ አድርጎ....."ይህ የመጨረሻው ውብ

@BOOKALEM

ከሉል የተሠራ የእጅ አምባር ነው። ዋጋው አሥራ አምስት ሺህ ዶላር ነው" አለው።

ሮበርት ወደ ፒየር እያየ....."ወደድሺው?" አላት።

መናገር ተሰኗት ራሷን በአወንታ ወዘወዘች።

"እሺ እንወስደዋለን!" አለና ሮበርት የኢኤንኢይ ከሬዲት ካርዱን ለጸሓፊው ሰጠው።

"አንድ ጊዜ እባክዎን!" አለና ጸሓፊው ካርዱን ተቀብሎ አንድ ክፍል ውስጥ ገባ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተመልሶ መጣና ....."ልጠቅልልላችሁ ወይስ.....?" አለ።

"የለም ጓደኛዬ ታደርገዋለች" አለና ሮበርት አምባሩን ተቀብሎ እጇ ላይ አጠለቀላት። ፒየር ፍዝዝ ብላ አምባሩን ታየው ነበር።

"ቬኒስ ውስጥ ደግሞ በጣም እንደሚያምርብሽ ነው። አይደለም?" አላት ሮበርት።

ፒየር ሳቅ አለችና....."በጣም ውብ ይሆናል!" አለችው።

መንገድ ላይ እንደወጡ....."ምን ያህል ላመሰግንህ እንደምችል አላውቅም!" አለችው።

"ጥሩ ጊዜ እንድታሳልፊ ስለፈለኩ ብቻ ነው። ለመሆኑ መኪና አለሽ?" ሲል ጠየቃት።

"የለኝም። አንዲት አሮጌ ነበረችኝ። እሷም ተሰረቀች።"

"አሁን የመንጃ ፈቃድ አለሽ?"

ግራ ገብቷት ተመለከተችው። "እዎን አለኝ። ታዲያ ያለመኪና መንጃ ፈቃድ ብቻውን ምን ይሠራል?"

"ታያለሽ! አሁን ከዚህ ቦታ እንውጣ።" ታክሲ አስቆመና....."ቪያ ፓ እባክህ" አለ።

ታክሲው ውስጥ ተቀምጣ ታጠናው ጀመር። የእርሷን እጅባ ለማግኘት የተጨነቀው ለምንድን ነው? ሌላው ቀርቶ ጫፏን አልነካትም። 'ይህ ሰው ምን ይሆን?'

"ዊ!" ሲል ተጣራ ለሾፌሩ። አሁን ከማጆሪ የመኪና አከራይ ድርጅት አንድ መቶ ያርድ ያህል ርቀት ላይ ናቸው። ሒሳቡን ከፈለና ታክሲው ከዐይናቸው አስኪጠፋ ጠበቀ። ወዲያው ለፒየር ወፈር ያለ የገንዘብ ጥቅል አሸጋገራትና....."መኪና እንድትከራይልን ኢፈልጋለሁ። ፊያት ወይም አልፋ ሮሜኦ መኪና ብለሽ ጠይቂ። ለአራት ወይም ለአምስት ቀናት መኪናውን እንደምንፈልግ ንገሪያቸው። የሰጠሁሽ ገንዘብ ለዲፖዚት (ለመያዣ) በቂ ሲሆን መኪናውን በሰምሽ ተከራይው። እኔ ከመንገዱ ባሸገር ያለው ቡና ቤት ውስጥ እጠብቅሻለሁ።"

@BOOKALEM

ሰምንት ሕንፃዎች ያህል ራቅ ብሎ ሁለት መርማሪዎች የፊረንሳይ ሰሌዳ ቁጥር ያለው የጭነት መኪና የሚያሽከረክረውን ዕድለ ቢስ ሾፌር በጥያቄ እያጣደፉት ነበር።

"ምንም የማውቀው ነገር የለም። ይህንን ካርድ ማን ካሚዎኔ ላይ እንደጣለው አላውቅም። ምናልባት አንድ ወፈፌ ጣሊያን ሳያስቀምጠው አይቀርም።"

ሁለቱ መርማሪዎች ተያዩ። "ሁኔታውን በሰልከ ሪፖርት አደርጋለሁ" አለ ከሁለት አንዱ መርማሪ።

ፍራንሲስኮ ቄሳር አዲስ ስለተገኘው ዕድገት እያሰላሰለ ከጠረጴዛው ኋላ ተቀምጧል። ገና በጊዜ የተሰጠው ተልዕኮ በጣም ቀላል ይመስል ነበር "እሱን ፈልጎ ለማግኘት ምንም ችግር አይገጥምህም። ጊዜው ሲደርስ ካርዱ ውስጥ የታሸገውን የኤሌክትሮኒክ ጠቋሚ መሣሪያ በርቀት መቆጣጠሪያ (ሪሞት ኮንትሮል) ሥራውን እናስጀምረዋለን። መሣሪያውም በቀጥታ ወደ ሮበርት ይመራሃል" ነበር የተባለው። ነገር ግን አንድ ሰው ሮበርትን ዝቅ አድርጎ እንደገመተው ፍራንሲስኮ አሁን ተረዳ።

ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን በግዙፍ ሰውነቱ ወንበሩን ሞልቶት ጀኔራል ሒሊያርድ ፊት ተቀምጧል።

"በአውሮፓ ውስጥ ካሉት ምርጥ ተከታታዮች ግማሹን ያህል አሰማርተንበታል። እስካሁን ምንም ዕድል አልገጠማቸውም!" አለ ጄነራል ሒሊያርድ።

"ነገሩ ከዕድልም በላይ እንደሚጠይቃቸው ነው። ቤላሚ በጣም ምርጥ የሆነ ሰው ነው!" አለ ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን።

"ሮም ውስጥ እንዳለ እናውቃለን። ያ የውሻ ልጅ ለአንድ የእጅ አምባር አሥራ አምስት ሺህ ዶላር ነው ያስከፈለን። አሁን ጠርሙስ ውስጥ እንደገባ እባብ ሆኖ ነው ያገኘነው። ከጣሊያን አገር የሚወጣበት ምንም መንገድ የለም። ፓስፖርቱ ላይ የሚጠቀምበት ስም አርትር በተርፊልድ መሆኑንም አውቀናል።"

ኮሎኔል ጆንሰን ራሱን በአሉታ ነቀነቀ። "ቤላሚን እስከማውቀው ድረስ ምን ዐይነት ስም እንደሚጠቀም ፈጽሞ ማወቅ አትችልም። ተስፋ ማድርግ የሚቻለው ቤላሚ ያደርጋል ብለህ የምትጠብቀውን አለማድረጉ ብቻ ነው። አሁን የምናሳድደው ሰው በስለላው ዓለም ውስጥ ምርጥ የሆነውን ነው። ማድርግ የምንችለው ነገር በጭስ አፍነን ከጉድጓዱ ወደ ገላጣው ሥፋራ እንዲወጣ ማድርግ ነው። በአሁኑ ጊዜ ሁሉንም ዐይነት እንቅስቃሴ በበላይነት እየተቆጣጠረ ነው። ተነሳሽነቱንና የበላይነቱን ከላዩ ነጥቀን መውሰድ መቻል አለብን።"

"በመገናኛ ብዙሃን ስምና ፎቶውን ማሰራጨት ማለት ነው?"

@BOOKALEM

"በትክክል።"

ጀኔራል ሒሊያርድ ከንፈሩን መጠጠና....."ይህ የሚጎዳ ጉዳይ ነው። ራሳችንን ማጋለጥ አንችልም!" አለ።

"ያንን ማድረግ የለብንም። በአደንጓሯ ዕፅ ንግድ ከሰ እንደሚፈለግ አድርገን መግለጫ እናወጣበታለን። በዚህ ዐይነት መንገድ ኢንተርፖልና የመላው አውሮፓ የፓሊስ ኃይል እኛ እጃችንን ሳናስነካ ከኋላው እንዲሰማራበት ለማድረግ እንችላለን።"

ጄነራል ሒሊያርድ በዚህ ሐሳብ ላይ ለጥቂት ጊዜ ሲያስብ ቆየና "ጥሩ! ሐሳቡን ወድጄዋለሁ" አለ።

"በጣም ጥሩ! እኔም ወደ ሮም ሄጄ ራሴ አደኑን በበላይነት እመራለሁ" አለ ኮለኔል ጆንሰን።

ኮሎኔል ጆንሰን ወደ ቢሮው እንደተመለሰ ቤሐሳብ ባሕር ሰጠመ። አደገኛ የሆነ የድብብቆሽ ጨዋታ ነበር በመጫወት ላይ ያለው። አደገኛነቱ የማያጠያይቅ ነው። ኮማንደር ሮበርት ቤላሚን መፈለግ አለበት።

ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት

ሮበርት ስልኩ ደግሞ ደጋግሞ ሲጮህ ይሰማዋል። አሁን ዋሺንግተን ውስጥ ከማለዳው አሥራ ሁለት ሰዓት ነው። ሽማግሌውን ሁልጊዜ እንደቀስቀስኩት ነው' ሲል አሰበ።

አድሚራሉ በስድስተኛው ጥሪ ስልኩን አነሳ። "ሄሎ....."

"አድሚራል እኔ....."

"ሮበርት ምን?"

"ምንም ነገር አይናገሩ አድሚራል። ምናልባት ስልክዎ የማዳመጫ መሣሪያ ተደርጎበት ይሆናል። በፍጥነት እናገራለሁ። ስለኔ የሚነገረውን ነገር ሁሉ በፍጹም እንዳያምኑ። ምን በመደረግና በመከናወን ላይ እንዳለ እንዲያጣሩልኝ አፈልጋለሁ ። ዘግይቶ ዕርዳታዎን ሳልፈልግ አልቀርም።"

"ማድረግ የምችለውን ሁሉ ሮበርት!" አለ አድራሚሉ።

"አውቃለሁ። ቆይቼ እደውላለሁ" አለና ሮበርት ስልኩን አስቀመጠው። ለአቅጣጫ መጠቆሚያ መሣሪያ ምንም ጊዜ አልሰጠም ነበር። አንድ ሰማያዊ ቀለም ያላት ፊያት መኪና ወደ ቡና ቤቱ ስትመጣ ተመለከተ። መሪውን የያዘችው ፒየር ነበረች።

"ወዲያኛው ወንበር ላይ እለፊ! እኔ አሽከረክራለሁ" አላት ሮበርት። ፒየር ቦታውን ስትለቅለት እሱ መሪውን ያዘ።

"አሁን ወደ ቬኒስ ነው የምንጓዘው?" ስትል ጠየቀቸው ፒየር።

@BOOKALEM

"መጀመሪያ አንድ ሁለት ቦታ እንቆማለን" አላት።

በመጀመሪያ ጥቂት የማደናገሪያ ዘዴዎችን ይበትናል። ወደ ቪአሌ ሮዚና መኪናውን ጠምዝዞ ማሽከርከር ጀመረ። ጥቂት ራቅ ብሎ ሮዚና የጉዞ አገልግሎት የተባለ ድርጅት አለ። ሮበርት ኩርባውን ዞር አድርጎ መኪናውን አቆመና "ከደቂቃ በኋላ እመለሳለሁ" ብሏት ወጣ። ከመኪናው ወጥቶ ሲሄድ ፒየር ተመለከተችው። 'አሁን መኪናዋን አስነስቼ መሄድና ገንዘቡን ለራሴ ማስቀረት እችል ነበር። ግን የተረገመውን መኪና በኔ ስም ነው የተከራየው። ናቺአ!' ስትል ራሷን ሰደበች።

ወደ ወኪሉ ጽሕፈት ቤት እንግዳ መቀበያ ዴክስ አመራ። "እንደምን ዋሉ ምን ልርዳዎት?" አለችው።

"ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ እባላለሁ። ጥቂት ጉዞ ለማድርግ አቅጃለሁ። የጉዞ ቦታ ለማስመዝገብ እፈልግ ነበር" አላት።

ጸሓፊዋ ፈገግታ አሳየቸውና....."እዚህ የተገኘንው ለዚህ ዐይነቱ ጉዳይ ነው ሲኞር! ለመሆኑ ወዴት ለመጓዝ ነው ያቀዱት?"

"ወደ ቤጂንግ የአንድ ጉዞ ብቻ የአውሮፕላን ቲኬት ለማገኘት እፈልጋለሁ ።"

ማስታወሻ ላይ መዘገበችና....."መቼ ነው ለመነሳት የሚፈልጉት?" አለችው።

"በመጪው አርብ ቀን።"

"በጣም ጥሩ!" አለችና ኮምፒተር ላይ የተወሰኑ ቁልፎች በጣቷ ጠቁማ....."አርብ ዕለት ምሽት አንድ ሰዓት ከአርባ ደቂቃ ላይ ወደ ቻይና የሚበር የቻይና አየር መንገድ በረራ አለ" አለችው።

"ያ በጣም ግሩም ነው" አላት።

ሌሎች ቁልፎችን እንደገና ነካካችና....."ይኸውና ለእርስዎ ቦታ ተይዞልዎታል። ክፍያው በጥሬው ነው ወይስ.....?

"እ! ይቅርታ ገና አልጨረስኩም። ወደ ቡዳፔስት የባቡር ቲኬት እንዲያዝልኝ እፈልጋለሁ::"

"ይህ ደግሞ ለመቼ ነው ኮማንደር?"

"በሚመጣው ሰኞ።"

"በማን ስም?"

"በመጀመሪያው።"

ግራ በመጋባት ተመለከተችውና....."አርብ ዕለት ወደ ቤጂንግ ይበራሉ። እንደገና....."

"አልጨረስኩም" አለ ሮበርት በደስተኛ ስሜት። ለዕሁድ ደግሞ ወደ ማያሚ ፍሎሪዳ የደረሰ መልስ የአውሮፕላን ቲኬት እፈልጋለሁ ።"

አሁን በግልጽ አፍጣ እያየችው ነው። "ሲኞር ይህ የሆነ ቀልድ....."

@BOOKALEM

ሮበርት የኢኤንኢይ ክሬይዲት ካርድ አውጥቶ ሰጣትና ....."የቲኬቶቹን ዋጋ በዚህ ካርድ ገቢ አድርጊ" አላት።

ለደቂቃ ያህል አየችውና....."ይቅርታ!" ብላው ሌላ ቢሮ ካርዱን ይዞ ገባች። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተመልሳ ወጣች። "በጣም ጥሩ ነው። ያዘዙንን የቲኬት ሽያጮች ሁሉ ለመፈጸም በጣም ደስተኞች ነን። ሁሉም ምዝገባ በአንድ ስም እንዲሆን ነው የፈለጉት?"

"አዎን በኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ስም።"

"በጣም ጥሩ።"

ሌሎች ተጨማሪ ቁልፎችን ኮምፒተሩ ላይ ስትነካ ሮበርት ይመለከታት ነበር። ጸሓፊዋ ሦስት ቲኬቶችን በኮምፒተር አዘዘችና ከማተሚያው መሣሪያ ላይ ቀዳ አነሳቻቸው።

"እባክሽ ቲኬቶቹን በተለያዩ ፓስታዎች ውስጥ አሽጊልኝ" አላት ሮበርት።

"በሚገባ። የሆነ ቦታ እንድልክልዎ ይፈ....."

"የለም ራሴ እወስዳቸወለሁ።"

"ሲ ሲኞሬ" አለች ጸሓፊዋ።

ሮበርት የዱቤ መሸመቻ ካርዱን ወረቀት ሲፈርምላት ሴትዮዋ ደግሞ ደረሰኙን አስረከበችው።

"ይኸው ጌታዬ መልካም ጉዞ.....ጉዞዎች ይሁንልዎ።"

"አመሰግናለሁ" አለ ሮበርት በፈግታ። ከአንድ ደቂቃ በኋላ የመኪናውን መሪ ጨብጦ መንገድ ከመጀመሩ በፊት መንገዱን በንቁ ዐይኖቹ ሲስልል ፒየር በትኩረት ነበር የምታየው።

"አንድ ነገር እንድታደርጊልኝ እፈልጋለሁ" አላት ሮበርት።

'አሁን ነገር ተጀመረ። አንድ መጥፎ ነገር አንዳደርግ ሊጠይቀኝ ነው' ስትል አሰበችና....."ምንድን ነው?" አለችው።

መኪናውን ቪክቶሪያ ሆቴል ፊት ለፊት አቆመና ከኤንቬሎፓቹ አንዱን አቀበላት። "ወደ እንግዳ መቀበያው ዴስክ ሄደሽ መኝታ ክፍል በኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ስም ካስመዘገብሽው በኋላ ሮበርት ከአንድ ሰዓት በኋላ እንደሚመጣና አንቺም ጸሓፊው መሆንሽን አሳውቀሽ በቅድሚያ የሆቴሉን ክፍል ማየት እንደምትፈልጊ ንገሪያቸው። ወደ ክፍሉም እንደገባሽ ይህን ፓስታ ጠረጴዛው ላይ ጥለሽው ትወጫለሽ።"

ግራ በመጋባት ሁኔታ እያየችው....."ይኸው ነው?" አለችው።

"ይኸው ነው።"

'ሰውዬው ፈፅሞ ስሜት አይሰጥም።' "ቤኔ!" አለችና ከመኪናው ወረደች።

'ይህ ወፈፌ አማሪካዊ ምን ለማድርግ እንዳቀደ ለማወቅ ጓጓች። 'ኮማንደር ሮበርት ቤላሚስ ማን ይሆን?' ስትል አሰበች። የታዘዘችውን ለመፈፀም በቀጥታ ወደ

@BOOKALEM

እንግዳ መቀበያው ዴስክ አመራች። ይህን የዝሙት አዳሪነት ሥራዋን ስታካሂድ በጣም ለተወሰነ ጊዜ ነው ትልቅ ሆቴል ውስጥ የመግባት ዕድል ያገኘችው። እንግዳ ተቀባዩ በትህትና ነበር የተቀበላት። "ምን ልርዳሽ ሲኞራ?"

"የኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ጸሐፊ ነኝ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ስለሚመጣ የሆቴል ክፍል ላስይዝለት እፈልጋለሁ ።"

የሆቴሉ ጸሐፊ መዝገቡን ተመለከተና....."አንድ በጣም ግሩም የሆነ ክፍል አለን" አላት።

"መጀመሪያ ላየው እችላለሁ?" አለች ፒየር።

"በእርግጥ ይቻላል። አንድ ሰው እንዲያሳይሽ አደርጋለሁ።"

አንድ ረዳት ሥራ አስኪያጅ ፒየርን አጅቧት ወደ ፎቅ ወጣ። ወደ ክፍሉ ሳሎን ቤት እንደገቡ ፒየር ዙሪያውን መመልከት ጀመረች።

"ይህ የሆቴል ክፍል አጥጋቢ ይሆን ሲኞራ?" አላት።

ፒየር ምንም ዕውቀት አልነበራትም። "አዎን አጥጋቢ ነው" አለችና ከቦርሳዋ ውስጥ ኤንቬሎፑን አውጥታ ጠረጴዛ ላይ እያስቀመጠች....."ይህንን ለኮማንደሩ እዚህ እተውሊታለሁ" አለች።

"ቤኔ!" አላት ረዳት ሥራ አስኪያጁ።

ፒየር የማወቅ ጉጉት አደረባትና ኤንቬሎፑን ከፍታ ተመለከተችው። በውስጡ በኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ስም የተዘጋጀ ወደ ቤጂንግ የሚወስድ የአንድ ጉዞ ብቻ የአውሮብላን ቲኬት ነበር። ትኬቱን መልሳ ፖስተው ውስጥ ከተተችና ፖስታውን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣ ከፎቅ ወደ ታች ወረደች።

ሰማያዊዋ ፊያት መኪና ሆቴሉ ፊት ለፊት ቆማ ነበር። "እንዳች ችግር ነበር?" አለ ሮበርት።

"የለም።"

"ሁለት ቦታዎች ላይ ከቆምን በኋላ መንገዳችንን አንቀጥላለን" ሲል በደስታ አሳወቃት።

ቀጥሎ የቆሙት ሆቴል ባላዲየር ነበር። "በኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ስም አንድ የሆቴል ክፍል ታስመዘግቢያለሽ። እሱ ከአንድ ሰዓት በኋላ እንደሚገባ ነግረሽ ክፍሉን በቅድሚያ ለማየት ጠይቂ። ቀጥሎም....."

"ክፍሉ ውስጥ ኤንቨሎፑን እተወዋለሁ" አለችና አቋረጠችው።

"ትክክል! "አላት።

"ፒየር ወደ ሆቴሉ ከቅድሙ የበለጠ በራስ የመተማመን ስሜት እየተሰማት ገባች። 'ልክ እንደሴት ወይዘሮ ክብርን ጠብቆ መንቀሳቀስ ነው። ምሥጢሩ ይኸው ነው!' ስትል በሐሳቧ አውጠነጠነች።

አንድ ረዳት ሥራ አስኪያጅ ፒየርን አጅቧት ፎቅ ወጣ። "ይህ ካሉን የመጨረሻው ምርጥ የማረፊያ ቤት ነው" ሲል አሳወቃት። እውነትም ውብ ነበር።

@BOOKALEM

"አዎን ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። አየህ ኮማንደሩ በጣም የተለየ ሰው ነው" አለችውና ኤንቬሎፑን ከቦርሳዋ ከፍታ ተመለከተችው። በውስጡ በኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ስም የተመዘገበ የባቡር ቲኬት ነበረበት። ፒየር ፍፁም ግራ ተጋብታ ቲኬቱን ተመለከተችው። 'ምን ዐይነት ጨዋታ ነው?' ቲኬቱን ከፍሉ ውስጥ ትታ ወጣች።

ፒየር ወደ መኪናው ስትመለስ "እንዴት ሆነ?" አለና ሮበርት ጠየቃት።

"መልካም ነበር" አለችው።

አሁን ደግሞ የቆሙት ሊአናርዶ ዳቪንቺ ሆቴል ነበር። ሮበርት ትኬቱን ከሰጣት በኋላ መናገር ሲጀምር "አውቃለሁ" አለችና አቋረጠችው።

"አዎን በሚገባ ሲኞራ! በጣም ተወዳጅ የሆነ የማረፊያ ቤት አለን!" አላት የሆቴሉ ጸሓፊ። "ኮማንደሩ መቼ ነው ይመጣል ያልሺኝ?"

"በአንድ ሰዓት ውስጥ። በመጀመሪያ ከፍሉን ተመልከቼ አጥጋቢነቱን ለማረጋገጥ እወዳለሁ" አለች።

"በእርግጥ ይቻላል ሲኞራ!"

ከፍሉ ቀደም ሲል ከተመለከተቻቸው የሆቴል ከፍሎች የበለጠ በቅንጦት ዕቃዎች ያበደ ነበር። ረዳት ሥራ አስኪያጁ መኻል ሥፍራ ላይ በትልቅ መጋረጃ የተጋረደ ትልቅ አልጋ ያለበት ሰፊ የመኝታ ክፍል አስጎበኛት። 'ምን ዐይነት ብኩንነት ነው? በአንድ ምሽት አዚህ የመኝታ ክፍል ውስጥ አያሌ ንዋይ ይፈሳል'ን ስትል አሰበችና ሦስተኛውን ኤንቬሎፕ አውጥታ ከፈተችው። በውስጡም በኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ስም ወደ ማያሚ ፍሎሪዳ የተዘጋጀ የአንድ ጉዞ የአውሮፕላን ቲኬት ነበረበት። ፒየር ኤንቬሎፑን አልጋው ላይ ጥላው ወጣች።

ረዳት ሥራ አስኪያጁ ፒየርን ወደ ሳሎኑ አጅቦ ወሰዳት። "ባለቀለም ቴሌቪዥን አለን" አላትና ቴሌቪዥኑን ከፈተው። ወዲያው የሮበርት ምስል የቴሌቭዥኑን መስተዋት ሞላው።

".....እናም!" አለ ዜና አንባቢው። "ኢንተርፖል ሮም ውስጥ ነው ያለው ብሎ ያምናል። በዓለም አቀፍ አደንዛዥ እጽ አዘዋዋሪነት ምክንያት ለጥያቄ ይፈለጋል። የሲ.ኤን.ኤን. ዜና አገልግሎት ዘጋቢ በርናርድ ሾው ነኝ።"

ረዳት ሥራ አስኪያጁ ቴሌቪዥኑን አጠፋውና....."ሁሉም ነገር የሚያረካ ነውን?" አላት።

"አዎን!" አለችው በዝግታ። 'እጽ አመላላሽ?'

"ኮማንደሩን ለማየት በናፍቆት እንጠባበቃለን" አለ ሥራ አስኪያጁ።

ፒየር ወደ መኪናው እንደተመለሰች ሮበርትን በተለየ ዐይን ነበር የተመለከተችው።

ቪክቶሪያ ሆቴል ውስጥ ሙሉ ጥቁር ልብስ የለበሰ ሰው የእንግዶችን መዝገብ ስም ዝርዝር እየተመለከተ ነበር። የሆቴሉን ጸሓፊ ቀና ብሎ

@BOOKALEM

ተመለከተውና.....“ኮማንደር ቤላሚ በስንት ሰዓት ነው ክፍሉን የያዘው?” ሲል ጠየቀው።

“እስካሁን አልመጣም። ክፍሉን ጸሓፊው ካስመዘገበችለት በኋላ በአንድ ሰዓት ውስጥ እንደሚመጣ ተናግራለች።”

ሰውዬው ወደ ባልደረባው ዘወር አለና.....“ተጨማሪ የሰው ኃይል አስመጣና ሆቴሉን በተጠናከረ መልኩ አስጠብቅ። እኔ ፎቅ መኝታ ቤቱ ውስጥ እጠብቃለሁ” አለውና ወደ ሆቴሉ ጸሓፊ ዘወር ብሎ.....“ክፍሉን ክፈትልን” አለና አዘዘው።

ከሦስት ደቂቃዎች በኋላ የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ ሰውዬውን ለሮበርት የተያዘው ክፍል ውስጥ አስገባው። ሙሉ ጥቁር ልብስ የለበሰው ሰው በእጁ ሽጉጥ ይዞ በጥንቃቄ ወደ ክፍሉ ገባ። ክፍሉ ባዶ ነበር። ዙሪያውን ሲቃኝ ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን ፖስታ ተመለከተ። አነሳውና ከፍቶ ተመለከተው። የፖስታውን ይዘት እንደተረዳ ወዲያውኑ ወደ ጣሊያን መረጃ ጠቅላይ ቤሮ ሲፋር ስልክ መደወል ጀመረ።

ፍራንሲኮ ቄሳርና ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን ሞቅ ያለ ስብሰባ ይዘዋል። ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን ሊዎናርዶ ዳቪንቺ አየር ማረፊያ ካረፈ ገና ሁለት ሰዓት የሆነው ቢሆንም ምንም ዐይነት የድካም ምልክት አይታይበትም ነበር። “እኛ እስከምናውቀው ድረስ ቤላሚ አሁንም ሮም ውስጥ ነው ያለው” አለ ፍራንሲስኮ። “ስለሚገኝባቸው ሥፍራዎች ከሥልሳ የበለጡ ሪፖርቶች ደርሰውናል።”

“እስካሁን ሰንቱን አጣርታችኋል?”

“አላጣራንም።”

ሰልኩ አቃጨለ። “ሉዊጂ ነኝ ኮሎሌል። አግኝተነዋል። ሆቴል ቪክቶሪያ የተከራየው ክፍል ውስጥ ነው ያለሁት። እንደዚሁም ወደ ቤጂንግ ለመሄድ የገዛውን የአውሮፕላን ቲኬት አግኝቻለሁ። ከሮም ለመውጣት ያቀደውም አርብ ቀን ነው።”

የኮሎኔል ቄሳር ድምፅ በደስታ ተሞላ። “በጣም ጥሩ! እኛ እስክንመጣ ድረስ አዚያው ጠብቅ!” አለና ሰልኩን ዘግቶ ወደ ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን ዘወር አለ። “እዚህ ሮም ድረስ ያደረከው ጉዞ ከንቱ ድካም ነው ብዬ እፈራለሁ ኮሎኔል ጆንሰን። ሮበርት ሆቴል ቪክቶሪያ ውስጥ ተመዘገበ አግኝተንዋል። እንዲሆም ወደ ቤጂንግ የሚወስደው የአውሮፕላን ቲኬትም ሆቴሉ ውስጥ አግኝተናል።”

“ቤላሚ ሆቴል ቪክቶሪያ ውስጥ በስሙ ተመዝግቦ?” ሲል ኮሎኔል ጆንሰን ድምፁን ለስለስ አድርጎ ጠየቀ።

“እንዴታ!”

“እናስ የአውሮፕላን ቲኬቱም በስሙ ነው የተዘጋጀው?”

@BOOKALEM

"አዎን!" አለና ኮሎኔል ቄሳር ከመቀመጫው እየተነሳ....."እዛው ድረስ እንሂድ" አለ።

ኮሎኔል ጆንሰን አንጉቱን ነቀነቀና....."ጊዜህን አታባክን" አለው።

"ምን?"

"ቤላሚ በፍጹም....."

የኮሎኔል ጆንሰን ንግግር በስልክ ጩኸት ተቋረጠ። ቄሳር ስልኩን አነሳና ፊቱን ወደ ጆንሰን አዞረ። "ወደ ቡዳፔስት የሚወስድ የባቡር ቲኬት በቤላሚ ስም ተዘጋጅቶ አገኙ? አልገባኝም....."

ስልኩ እንደገና አቃጨለ። "አቤት?" አለ ዘለግ ባለ ድምፅ ኮሎኔል ቄሳር።

"ብሩኖ ነኝ። ቤላሚ ያለበትን ቦታ አግኝተናል። ሌአናርዶ ዳቪንቺ ሆቴል የተመዘገበ ከመሆኑም በላይ አሁድ ዕለት ወደ ማያሚ ለመጓዝ አቅዷል። ምን ላድርግ?"

"ወደ ቢሮ ተመልሰህ ና!" አለና ቄሳር ስልኩን ዘጋው። "ይህ ምን ዐይነት ጨዋታ ነው?" አለ ቄሳር።

"አያሌ የሰው ኃይል በከንቱ ማባከንህን እያረጋገጠ ነው። አይደለም?"

"እሺ! አሁን ምንድነው የምናደርገው?"

"ዲቃላውን እናጠምደዋለን።"

በፓሳጂኤታ አጠገብ አድርጎ በቪያ ጎዳና ላይ እየነዳ ወደ ቬኒስ በመጓዝ ላይ ነበረ።«'በአሁኑ ሰዓት ፖሊሶች የኢጣሊያን ዋና ዋና የመውጫያ ኬላ ይዘጋሉ። ግን በስተምዕራብ በኩል ፈረንሳይ ወይም ስዊዘርላንድ ይሄዳል ብለው ነው የሚጠብቁት። ከቬኒስ በጀልባ ወደ ቴሪስቲ እሄድና ከዚያም ወደ ኦስትሪያ እዘልቃለሁ።'

"ከዚያ በኋላ....."»

የፒየር ድምፅ ከሐሳቡ አነቃው። "ርቦኛል!" አለችው።

"ምን?"

"ምሳም ሆነ ቁርስ አልቀመስንም እኮ!"

"አዝናለሁ!" አለ ሮበርት። ስለምግብ ለማሰብ እንዳይችል አዕምዕሮው በብዙ ነገር ተወጥሮ ነበር። "የሚቀጥለው ሬስቶራንት ስንደርስ እንቆማለን" አላት።

መኪናውን ሲነዳ ፒየር ትመለከተው ነበር። ሁኔታው ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ግራ አጋባት። በአቃጣሪዎች፤ በሌቦችና የእጽ አመላላሾች ዓለም ውስጥ ነው የኖረችው። የዚህን ሰው ሁኔታ በትኩረት ስታጤነው ግን 'ፈፅሞ ወንጀለኛ አይደለም!' አለች።

ሮበርት አንድ አነስተኛ ምግብ ቤት ፊት ለፊት ቦታ ፈልጎ መኪናዋን ሲያቆም ፒየር ወረደች። ሬስቶራንቱ በደንበኞቹ ጫጫታ የተመላበት ንግግርና በምግብ ሳህን ኳኳታ ተሞልቷል። ሮበርት አስቀድሞ የምግብ ቤቱን መግቢያ በር ለማየት እንዲመቸው ግድግዳ የተጠጋ ጠረጴዛ መርጦ ከፒየር ጋር ወንበር ስበው

@BOOKALEM

እንደተቀመጡ አስተናጋጁ መጣና ለእያንዳንዳቸው የምግብ ዝርዝር ማውጫ አደላቸው። ጂብራልታር

ሮበርት በሐሳብ ተመስጦ ነበር። 'ሱዛን በአሁኑ ሰዓት ጀልባዋ ላይ ተሳፍራለች። ይህ ደግሞ እሷን ለማነጋገር የምችልበት የመጨረሻው ዕድሌ ነው።'ፒየር ማውጫውን ተመለከተችና ምግብ ሲታዘዝ ሮበርት....."ቶሎ እመለሳለሁ" ብሏት አጠገባቸው ወዳለ የሕዝብ ስልክ ሄደና መነጋገሪያውን ካነሳ በኋላ ሳንቲም ሲጨምር ፒየር ተመለከተችው።

"የጂብራልታሩን የባሕር መስመር ለማነጋገር እፈልጋለሁ" አለ።

'ጂብራልታር ውስጥ ለማነው ጥሪ የሚደርገው? የማምለጫ መስመሩ ይሆን?' ስትል ፒየር ተደነቀች።

"ኦፕሬትር! ከጂብራልታር የባሕር ወደብ የምትርቅ "ሐልካዮን" የተባለች የአሜሪካ የሞተር ጀልባ ላይ ቁጥሩ ደበሊው ኤስ (ዊስኪ ስኩዌር) 337 ነው። አመሰግናለሁ።"

በኦፕሬተሮቹ መካከል ጥቂት ደቂቃዎች የፈጀ የንግግር ልውውጥ ከተደረገ በኋላ ጥሪው መልስ አገኘና የሱዛን ድምፅ መጣለት።

"ሱዛን....."

"ሮበርት ደህና ነህ?"

"ደህና ነኝ። ልነገርሽ የፈለኩት....."

"ምን ልትነግረኝ እንደፈለክ አውቃለሁ። ዜናው በቴሌቪዥንና በራድዩ ተሰራጭቷል። ኢንተርፖል የሚያድንህ ለምንድን ነው?"

"በጣም ረዥም ታሪክ ነው።"

"ጊዜ ውሰድና ንገረኝ! ለማወቅ እፈልጋለሁ ።"

ጥቂት አመነታና....."የፖለቲካ ጉዳይ ነው ሱዛን" አላት። "እንዳንድ የዓለም መንግሥታት ሕዝብ ማወቅ የሚገባውን ነገር እንዳይታወቅ ለማድረግ እንደሚጥሩ ማስረጃ አግኝቻለሁ። ለዚህም ነው ኢንተርፖል የሚያሳድደኝ።"

ሮበርት የሚናገራትን አንዳንዱን ቃላት ፒየር ጆሮዋን አቁማ እያዳመጠች ነው። "እንተን ለመርዳት ማድረግ የምችለው ነገር አለ?"

"ምንም ነገር የለም ወለላዬ። ምናልባት ከታዳኝነቱ በሕይወት ካልመጣሁ ድምፅሽን ለመስማት ብቻ ብዬ ነው የደወልኩልሽ።"

"እንደሱ አትበል" አለች ሱዛን የመሸበር ቅላጼ ባለው የተደናገጠ ድምፅ። "የት አገር እንዳለህ ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"ኢጣሊያ።"

ከአጭር ፀጥታ በኋላ....."ደህና! አንተ ካለህበት ብዙም ሩቅ አይደለንም። ከጂብራልታር ገና መልቀቃችን ስለሆነ አንተ የጠራህው ቦታ ድርስ መጥቶን ልናነሳህ እንችላለን።"

@BOOKALEM

"የለም እኔ....."

"ስማኝ! ምናልባት ይህ ለማምለጥ ያለህ ብቸኛ አማራጭ ነው።"

"ይህንን እንድታደርጊ አልፈቅድም ሱዛን። ብዙ የተምታታ ነገር ውስጥ ልትገቢ ትችያለሽ።"

በመነጋገር ላይ ሳሉ ሞንቴ ሱዛን ስልክ የያዘችበት ክፍል ውስጥ ሲገባ የተወሰነ ውይይታቸውን በመስማቱ ..... "ላነጋግረው ስልኩን ስጪኝ!" አላት።

"አንድ ጊዜ ሮበርት ሞንቴ ሊያነጋግርህ ይፈልጋል።"

"ሱዛን እኔ....." ብሎ ሳይጨርስ የሞንቴ ድምፅ በስልኩ ውስጥ ንግግር ጀመረለት። "ሮበርት! በጣም ከፍተኛ ችግር ውስጥ መግባትህ ይገባኛል።"

"አዎን እንደዚያ ማለት ትችላለህ።"

"ከዚህ ችግር ውስጥ ልናወጣህ እንወዳለን። ማንም ሰው እኛ ጀልባ ላይ የሚፈልግህ የለም። ለምን ከሆነ ቦታ ላይ እንድናሳርፍህ ኢታደርግም?"

"አመሰግናለሁ ሞንቴ። ሐሳብህን እደንቃለሁ። መልሴ ግን አይሆንም ነው።"

"ተሳስተሃል ብዬ እገምታለሁ። እኛ ጀልባ ላይ ብትሆን ደህንነትህ የተጠበቀ ይሆን ነበር ብዬ አስባለሁ።"

'ለምነድነው እኔን ለመርዳት የጓጓው?' አለ ሮበርት በሐሳቡ። "ቢሆንም አመሰግናለሁ ሞንቴ። የራሴን ዕድል እሞክራለሁ። ሱዛንን እንደገና ለማነጋገር እፈልግ ነበር።"

"በእርግጥ ይቻላል!" አለና ሞንቴ ስልኩን ለሱዛን እያቀበለ ....."ሐሳባችንን እንዲቀበል አሳምኚው!" አላት።

ሱዛን ስልኩን ተቀብላ....."እባክህን ዕርዳታችንን ተቀበል" ስትል ለመነችው።

"ረድተሽኛል ሱዛን። አንቺ የሕይወቴ ምርጥ አካል ነሽ። ምንጊዜም እንደማፈቅርሽ እንድታውቂልኝ እፈልጋለሁ ።"

"እንደገና ጥሪ ታደርግልኛለህ?"

"የምችል ከሆነ።"

"ቃል ግባልኝ።"

"እሺ ቃል ገብቻለሁ።"

በዝግታ ስልኩን አስቀመጠና ወደ ጠረጴዛው ተመልሶ ፒየርን....."በይ እንመጣብ!" አላትና የመረጡትን ምግቦች አዘዙ።

"የተነጋገርከውን ሰምቻለሁ። ፖሊሶች እየፈለጉህ ነው። አይደለም?"

ሮበርት ትንሽ እንደመሸማቀቅ አለና በሐሳቡ"ግዴለሽ ሆኜ ነበር"። ይህቺ ሴት ችግር ልትፈጥርብኝ ነው'» አለና....."ትንሽ ያለመግባባት ጉዳይ ነው እኔ....."

"ልክ እንደቂላቂል አትመልከተኝ። እኔ ልረዳህ እፈልጋለሁ ።"

ሲጋት በተመላበት ጥንቃቄ እየተመለከታት....."ለምን ብለሽ ትረጂኛለሽ?" ሲል ጠየቃት።

@BOOKALEM

ፒየር ወደ ሮበርት ጠጋ አለችና.....“ምክንያቱም ለኔ በጣም ሊጋስ ስለሆንክ ነው። ከዚህም ባሻገር ፖሊስ ሲባል በጣም ነው የምጠላው። ጎዳናዎች ላይ ገቢያ ፍለጋ ተጉትሮ በፖሊሶች መባርር ምን ማለት እንደሆነ አታውቅም። ልክ እንደቆሻሻ መታየት ምን እንደሆነ አታውቅም። በዝሙት አዳሪነት ወንጅለው ከያዙኝ በኋላ ከእስር ከፍል አውጥተው በስተኋላ ወዳለ ሌላ ከፍል አስገብተው ተፈራርቀውብኛል። እንተን ለመርዳት ስል ምንም ዐይነት ነገር አደርጋለሁ።”

“ፒየር አንቺ ልታደርጊልኝ የምትችው ምንም.....”

“ቬኒስ ውስጥ ፖሊሲች በቀላሉ ሊይዙ ይችላሉ። ሆቴል ውስጥ ልረፍ ብትል ያገኙሃል። መርከብ ላይ ልሳፈር ብትል በቀላሉ ያጠምዱሃል። እኔ ግን ፖሊሶች ሊያገኙህ የማይችሉበት አስተማማኝ የመደበቂያ ሥፍራ አውቃለሁ። ወንድሜና እናቴ ኔፕልስ ከተማ ውስጥ ይኖራሉ። ማንም ሰው እዚያ መጥቶ ሊፈልግህ ስለማይችል እነሱ ቤት ውስጥ መቆየት እንችላለን።”

ሮበርት ለተወሰነ ጊዜ በነገሩ እያሰበበት ፀጥ ብሎ ቆየ። ፒየር የምትነግረው ነገር ስሜት የሚሰጥ ነው። ኔፕልስ በጣም ትልቅ ወደብ ከመሆኗም በላይ የግል ቤት የበለጠ አስተማማኝ የመደበቂያ ሥፍራ ነው። ከዚህም ሌላ መርከብ በቀላሉ ለማግኘት ይችላል። ፒየርን አደጋ ውስጥ ለመክተት ስላልፈለገ መልስ ከመስጠቱ በፊት ጥቂት አመነታ።

“ፒየር! ፖለሶች ካገኙኝ በቀጥታ እንዲገድሉኝ ነው የታዘዙት። አንቺም ልክ እንደግብረ አበሬ ነው የምትወሰጂውና ራስሽን ችግር ውስጥ ልትጨምሪ ትችያለሽ።”

ፒየር ፈገግ አለች። ነገሩ በጣም ቀላል ነው። እንዲያገኙህ አናደደርግም!” አለችው።

ሮበርት ውሳኔውን አሳለፈ። ፈገግታዋን በፈገግታ መለሰላትና.....“በጣም ግሩም! በይ ምሳሽን ተመገቢ። ወደ ኔፕልስ እንጓዛለን” አላት።

“ያሰማራሃቸው ሰዎች በሙሉ ሮበርት ወዴት እንደሚያመራ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም?” ሲል ኮሎኔል ፈራንክ ጆንሰን ጠየቀ።

ፍራንሲስኮ ቄሳር በረጅሙ ተነፈሰና.....“ለጊዜው አያወቁም። ግን የጊዜ ጉዳይ.....”

“ጊዜ የለኝም!” ሲል አቋረጠው ጆንሰን። “የቀድሞ ሚስቱ የት እንደምትገኝ አጣርተሃል?” አለው።

“የቀድሞ ሚስቱ? የለም አላጣራሁም። ጥቅሙ አልታየኝም።”

“ስለዚህ የተሰጠህን የቤት ሥራ አልሠራህም ማለት ነው!” ሲል ፍራንክ ጆንሰን ቧረቀበት። “ሞንቴ ባንክስ የተባለ ሰው አግብታለች። አሁን ያሉበትን ቦታ በአስቸኳይ ፈልገህ እንድታገኝ ሐሳብ አቀርባለሁ።”

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት

ግማሽ በግማሽ በደነዘዘ ሕሊናዋ በአውራ ጎዳናው ላይ እየተንከራተተች ነው። 'አሰቃቂው የመከሰከሰ አደጋ ከደረሰ ስንት ቀን ሆነው?' ቁጥሩንም ሰታዋለች። እጅግ በጣም ከመድከሟ የተነሳ አንድ ነገር ላይ ለማተኮር አሰቸጋሪ ሆኖባታል። ይህ ምድራዊ ሰዎች የሚጠጡት የተበከለ ውሃ ሳይሆን ንፁህ ለመጠጥ የሚሆን የዝናብ ውሃ በጣም አስፈልጓታል።

የሕይወት ሕልውናዋን የሚያንሰራራላትና ጥንካሬዋን መልሳ ከሪስታሉን ፊልጋ ለማግኘት የሚረዳት ንጹህ ውሃ ያስፈልጋታል።

ተንገዳገደችና ከአንድ መንገደኛ ጋር ተጋጨች።

"ሄይ! ተመልከቺ....." አሜሪካዊው የሽያጭ ሠራተኛ ጠጋ ብሎ ተመለከታትና ፈገግታ ሰጣት። "ይታይሽ ካንቺ ጋር እንደዚህ መጋጨት! ምን ዐይነት አሻንጉሊት ነሽ?"

"አዎን ይታየኛል።"

"ከየት ነው የመጣሽው ወለላዬ?"

"ከጠፋችው ፕላይዴዝ ከተባለች ሰባተኛዋ ኮከብ።"

ከት ብሎ ሳቀና....."ቅንነት የመላበት ቀልድ ደስ ይለኛል። ለመሆኑ ወዴት ነው የምትሄጂው?"

ራሷን እያወዛወዘች....."እኔ እዚህ ቦታ እንግዳ ነኝ። ወዴት እንደምሄድ አላውቅም!" አለችው።

'ኢየሱስ! ጥሩ ዕድል ሳይገጥመኝ አልቀረም!' ፣"ለመሆኑ እራት ተመግበሻል?"

"የለም። የናንተን ምግብ መብላት አልችልም።"

'እንግዳ የሆነች ግን ውብ ሴት አገኘሁ'፣ "ማረፊያሽስ የት ነው?"

"ምንም ማረፊያ ቦታ የለኝም።"

"ሆቴልም የለሽም?"

'ሆቴል?' ትዝ አላት። 'ለመንገደኛ እንግዶች የተዘጋጁ ሳጥኖች።'

"የለኝም። ለመኝታ የሚሆን ቦታ ማግኘት አለብኝ። በጣም ደክሜአለሁ።"

ፈገግታ በፈገግታ ሆኖ ፊቱ በራ። "ደህና! ለምን ወደኔ የሆቴል ክፍል አንሄድም? እዚያ በጣም ግሩም የሆነ ትልቅ የመኝታ አልጋ አለኝ። ሐሳቤን ወደድሽው?"

"አ! በጣም ወድጀዋለሁ!" አለችው።

@BOOKALEM

የገጠመውን መልካም ዕድል ለማመን አልቻለም። 'በጣም ግሩም። እጭዱ ውስጥ በጣም ግሩም መሆን አለባት!' አለ በሐሳቡ።

ግራ ጉብቷት ተመለከተችው። "አልጋህ የተሰራው ከጭድ ነው?"

ደንገጥ ተመለከታት። "ምን? የለም! የለም! መቼም መቀለድ ትወጃለሽ። አንሄድም?"

ዐይኖቿን በጥቂቱ ነው መክፈት የቻለችው። "አሁን ወደ አልጋው አንሄድም?"

እጆቹን አሻሸና....."ሆቴሉ ልክ መጠምዘጎው አጠገብ ነው" አላት።

የሆቴሉ እንግዳ መቀበያ ዴስክ ላይ የመኝታ ቤቱን ቁልፍ ተቀበለና በአሳንሱር ወደ ፎቅ ይዟት ወጣ። መኝታ ክፍሉ ውስጥ እንደገቡም....."የሆነ የሚጠጣ ነገር ትፈልጊያለሽ?" አላት።

መጠጥ ተሰፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ አሰፈልጓታል። ግን ምድራዊያን ሊያቀርቡ የሚችሉትን ዐይነት ፈሳሽ አልነበረም። "የለም አልፈልግም። አልጋው የት ነው?" ስትል ጠየቀችው።

"እዚያ ውስጥ ነው ወለላዬ!" አለና ወደ መኝታ ክፈሉ እየመራ አስገባት። "መጠጥ እንደማያስፈልግሽ እርግጠኛ ነሽ?"

"እርግጠኛ ነኝ።"

ከንፈሩን በጉምሹት....."ላስና ታዲያ ለምን ልብስሽን አታወልቂም?" አላት።

አንገቷን በአዎንታ ነቀነቀች። 'የምድራዊያን ልምድ ነው' አለች በሐሳቧ። የለበሰችውን ቀሚስ ስታወልቀው ከውስጥ በኩል ምንም አለበሰችም ነበር። መላ አከላቷ እጅግ በጣም የተዋበ ነው።

ሰውዬው በደስታ ተመለከታትና 'ይህ የኔ ዕድለኛ ቀኔ ነው። ላንቺም እንደዚሁ። ከዚህ በፊት ካደረግሽው ሁሉ የበለጠ ፍቅር እንሥራለን' አለ በሐሳቡ። በተቻለው ፍጥነት ልብሱን ሁሉ አወላለቀና እንኗ አልጋው ላይ ዘሎ ወጣ። እንደገና ዘወር አለና....."የተረገመ!" መብራቱን ሳላጠፋው መጣሁ! አለና ከአልጋው መነሳት ጀመረ።

እንቅልፍ በተጫነው ስሜት....."ተወው ግድ የለም! እኔ አጠፋዋለሁ!" አለችው።

ሰውዬው አፍጥጦ እየተመለከታት እጁን ስትዘረጋው እየረዘመ.... እየረዘመ.....ወደ ቅጠልያ አረንጓዴነት እየተለወጠ በሰፊው ከፍል ውስጥ አቋርጦ ሄደና ማጥፊያውን በጣቶቿ ተጭና አጠፋችው።

በጨለማው ውስጥ እሪታውን አቀለጠው!

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሠላሳ ስምንት

አውቶ ስትራዳ ዴል ሶል በተባለው ነፃ አውራ ጎዳና ላይ በከፍተኛ ፍጥነት እየበረሩ ነው። ሁለቱም በየራሳቸው ሐሳብ ተውጠው ላለፉት ሠላሳ ደቂቃዎች በዝምታ ነበር የተጓዙት።

በመጨረሻም ፒየር ፀጥታውን አደፈረሰችው። "ለመሆኑ እናቴ ቤት ውስጥ ምን ያህል ጊዜ መቆየት ትፈልጋለህ?" አለችው።

"ችግር የማይፈጠር ከሆነ ለሦስት ወይም ለአራት ቀናት።"

"በጣም ጥሩ!።"

ሮበርት እዚያ ቤት ከአንድ ወይም ቢበዛ ከሁለት ምሽት የበለጠ ለመቆየት ፈጽሞ ፍላጎት የለውም። እቅዱን ግን ለራሱ በልቡ ነበር የያዘው። አስተማማኝ የሆነ መርከብ ካገኘ ወዲያውኑ ከኢጣሊያ ለመውጣት መንገዱን ይጀምራል።

"ቤተሰቤን ለማየት ቸኩያለሁ!" አለች ፒየር።

"አንድ ወንድም ብቻ ነው ያለሽ?"

"አዎን። ካርሎ የተባለ ታናሽ ወንድሜ ነው።"

"ፒየር እስቲ ስለቤተሰብሽ አጫውችኝ።"

ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገችና....."ብዙም የሚነገር የለውም" አለች። "አባቴ ሕይወቱን በሙሉ የሠራው ወደቡ ላይ ሲሆን የአሥራ አምስት ዓመት ልጅ በነበርኩበት ጊዜ የዕቃ ማንሻ ክሬን ወድቆበት ገደለው። እናቴም በሽተኛ ስለነበረች ካርሎንና እናቴን መደገፍ ነበረብኝ። በዚህም የተነሳ በጎዳናዎች ላይ የተሻለ ገንዘብ ማግኘት እችላለሁ ብዬ ወሰንኩ። አሁን ሁለቱንም እየሠራሁ ነው" አለችው ለራሷ ማሰተዛዘን በማይታይበት ድምፅ።

"ፒየር እርግጠኛ ነሽ እናትሽ እንግዳ ሰው ወደ ቤታቸው ይዘሽ የመምጣቱን ጉዳይ? ቅር አይላቸውም?"

"እርግጠኛ ነኝ አታውቅም። በጣም ነው የምንቀራረበው" አለችውና በድንገት....."ታፈቅራታለህ?" ስትል ጠየቀችው።

ሮበርት በድንጋጤ ዞሮ ተመለከታት። "እናትሽን?"

"ሬስቶራንቱ ውስጥ በስልክ ያነጋገርካትን ሴት.....እ.....ሱዛንን።"

"ይወዳታል ብለሽ እንድታስቢ ያደረገሽ ምንድን ነው?"

"የድምጽህ ቅላጼ። ለመሆኑ እሷ ማን ናት?"

"ጓደኛዬ።"

@BOOKALEM

"በጣም ዕድለኛ ሴት ናት። እኔም እንደዚህ የሚጠነቀቅልኝ ሰው ባገኝ በጣም እመኛለሁ። ሮበርት ቤላሚ ትከክለኛ ስምህ ነው?"

"አዎን" አላት።

"እና ማዕረግህ ኮማንደር ነው?"

ይህ ደገሞ ለመመለስ በጣም አስቸጋሪ ነበር። "እርግጠኛ አይደለሁም ፒየር። በአንድ ወቅት ነበርኩ።"

"ኢንተርፖል ለምን እንደሚከታተልህ ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"ምንም ነገር ባልነግርሽ የተሻለ ነው!" አላት በጣም እየተጠነቀቀ። ከኔ ጋር በመሆንሽ ብቻ በቂ ችግር ውስጥ ልትገቢ ትችያለሽ። በትንሹ ካወቅሽ የተሻለ ነው።"

"እሺ ሮበርት!" አለችው።

ሁለቱን ያገናኛቸውን እንግዳ አጋጣሚዎች አሰበ። "እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅሽ። በጠፈር መንኮራኩር የሚመጡ የሌላ ዓለም ፍጡራን መኖራቸውን ብታውቂ በፍርሃት ትሸበሪያለሽ?"

ለተወሰነ ጊዜ ፒየር በጥናት ተመለከተችው። "ከልብህ ነው?"

"በጣም።"

አንገቷን ነቀነቀችና....."የለም! አልሸበርም" አለችው። "እንዲያውም የሚያጓጓ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። የዚህ ዐይነት ነገሮች አሉ ብለህ ታምናለህ?"

"ሊኖር የሚችልበት መንገድ አለ" አላት በጥንቃቄ።

የፒየር ፊት በደስታ በራ። "እውነተኛ.....ማለቴ.....ልክ የሰው ዐይነት ተክለ-ሰውነት ነው ያላቸው?"

ሮበርት ሳቀና....."አላውቅም" አላት።

"ይህ ነገር ፖሊሶች ከሚያሳድዱን ጉዳይ ጋር ግንኙነት አለው?"

"የለውም!" አለ ሮበርት በፍጥነት። "ምንም ግንኙነት የለውም።"

"አንድ ነገር ብነግርህ እንደማትናደድብኝ ቃል ትገባልኛለህ?"

"ቃል ገብቼልሻለሁ።"

ሰትናገር ድምጿ የሹክሹክታ ያህል ስለነበረ በችግር ነው የሰማት። "ካንተ ጋር በፍቅር የወደኩኝ ይመስለኛል።"

"ፒየር....."

"ሞኝ ወይም ቂል እንደሆንኩ አውቃለሁ። ከዚህ በፊት ለማንም ሰው እንደዚህ ብዬ እንደማላውቅ እንድትረዳልኝ እፈልጋለሁ ።"

"በጣም ነው የከበሽኝ ፒየር።"

"እያሾፍክብኝ አይደለም?"

"የለም አይደለም" አላት። የነዳጅ መጠን አመልካች መሣሪያውን ተመለከተና....."የነዳጅ ማደያ ብንፈልግ የተሻለ ነው" አላት። ከአሥራ አምስት

@BOOKALEM

ደቂቃዎች በኋላ የነዳጅ ማደያ ጣቢያ ሲደርሱ....."መኪናቸንን እዚህ ነዳጅ እንሞላለን" አለ ሮበርት።

ፒየር....."መልካም!" ብላ ፈገግ አለችና....."ለእናቴ ስልክ ደውዬ መልክ መልካም እንግዳ ይገዬ በመምጣት ላይ መሆኔን አሳውቃታለሁ" አለችው።

ሮበርት ወደ ነዳጅ ማደያው ቢሮ ገብታ የስልክ መደወያ ፍራንክ ስትዘረዝር ተመለከታት። 'በእውነት ማራኪ የሆነች ልጅ ናት። ስሜቷን ላለመንካት መጠንቀቅ አለብኝ።'»

ቢሮው ውስጥ ስልኩን መደወል ጀመረችና ወደ ሮበርት ዘወር ብላ ፈገግ እያለች እጇን አውለበለበችለት። ወዲያው በስልኩ ውስጥ ድምፅ ሲመጣላት....."ኪኢንተርፖል አገናኝኝ! በፍጥነት!" አለች።

ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ

ስለ ሮበርት ቤላሚ የተሰራጨውን የዜና ዘገባ ፒየር ካየችበት ጊዜ ጀምሮ አዱኛ በሯን ከፍታ እንደተቀበለቻት አረጋገጠች። ዓለም አቀፍ የፖሊስ ኃይል (ኢንተርፖል) ሮበርትን የሚያሳድድ ከሆነ እሱን ላገኘለትና ለጠቆመው ሰው ከፍተኛ የሆነ ሽልማት ይሰጣል ማለት ነው። ሮበርት ያለበትን ቦታ የምታውቀው እርሷ ብቻ ስለሆነች ሽልማቱ የእርሷ ብቻ ይሆናል። በዐይነ ቁራኛ ልትጠብቀው ወደምትችልበት ቦታ ወደ ኔፐልስ ለመሄድ እንዲስማማ ማድረግ መቻሏ አቻ የሌላት ብልህ መሆንዋን ያሳያል።

"ኢንተርፖል! ምን ልርዳዎት?" የሚል የወንድ ድምፅ ተሰማት።

የፒየር ልብ መዝለል ጀመረ። ሮበርት አሁንም ቤንዚን ማደያው ውስጥ መሆንኑ ለማረጋገጥ በመስኮት ወደ ውጭ ተመለከተችና....."አዎን!" አለች ፒየር በስልኩ። "አዎን! ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ የተባለው ሰው በመፈለግ ላይ ናቸሁ። አይደለም?"

ከአጭር ጊዜ ፀጥታ በኋላ....."ደዋዩ ማነው እባክዎን?" አላት።

"ግድ የለም! ትፈልጉታላችሁ ወይስ አትፈልጉትም?"

"እባክዎን አንድ ጊዜ ቢጠብቁ! ወደ ሌላ ሰው አስተላልፍዎታለሁ" አለና ወደረዳቱ ዞር ብሎ....."የአቅጠጫ መጠቆሚያ መሣሪያውን ማሠራት ጀምር! ቶሎ!" አለው።

ከሠላሳ ሴኮንድ በኋላ ፒየር ከአንድ ከፍተኛ መኮንን ጋር መነጋገር ጀመረች።

"አቤት ሲኞራ! ልረዳሽ እችላለሁ?"

"ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ከኔ ጋር ነው። ትፈልጉታላችሁ ወይስ አትፈልጉትም?"

"አዎ ሲኞራ! በጣም ነው የምንፈልገው። እና ከእርሶ ጋር ነው ያሉት?"

@BOOKALEM

"ትክክል ከኔ ጋር ነው ያለው። እርሱን ለማግኘት ምን ያህል ትከፍላላችሁ?"

"ስለ ሽልማት ገንዘብ ነው የሚያወሩት?"

"እርግጥ! ስለ ሽልማቱ ገንዘብ ነው የማወራው" አለችና በመስኮት ወደ ውጭ ገልመጥ ብላ ተለመከተች። 'እነዚህ ምን ዐይነት ደደብ ፖሊሶች ናቸው?'

ባለሥልጣኑ ወደ ረዳቱ ዘወር ብሎ ፍለጋውን እንዲያቀላጥፍ ምልክት ሰጠው። "ሲኞራ አስካሁን ሰውዬውን ዋጋ አልመደብንለትም።"

"ስለዚህ.....ደህና! አንድ የሆነ ዋጋ አሁኑኑ መድቡ! በጣም እቸኩላለሁ።"

"ምን ያህል ሽልማት ነው የሚጠይቁን?"

"አላውቅም" አለችና ለተወሰኑ ሴኮንዶች አሰባ....."ሃምሳ ሺህ ዶላር በቂ ነው?" አለች።

"ሃምሳ ሺህ ዶላር በጣም ብዙ ገንዘብ ነው። አሁን ያለበትን ሥፍራ ቢነግሩኝ ወደ እርስዎ መጥተን ተገቢ የሆነ ዋጋ ከተደራደርን በኋላ....."

«'ሞኝ ናት ብሎ ነው መሰል የገመተኝ።'» ሮበርት ወደ ቢሮው ሲመጣ ተመለከተችና....."የለም! አሁን የጠየኩትን ከፍያ ለመከፈል ትስማማላችሁ ወይም.....ፍጠን! ቸኩያለሁ።"

"በጣም ጥሩ ሲኞራ! የጠየቁትን ለመከፈል ተስማምተናል....."

ሮበርት በበሩ ገብቶ ወደ ፒየር ሲመጣ አርዕስቱን ቀየረችና....."እሺ እማዬ! ልክ በእራት ሰዓት እዚያው እንደርሳለን" አለችና ስልኩን ዘጋችው።

የኢንተርፖል ዋና መሥሪያ ቤት ውስጥ ባለሥልጣኑ መኮንን....."የስልክ ጥሪ የተደረገበትን ቦታ አገኘህው?" ሲል ረዳቱን ጠየቀው።

"አዎን! ጥሪው አውቶ ስትራዳ ዴል ሶል የተባለ ቦታ ከሚገኝ አንድ የነዳጅ ማደያ ጣቢያ ነው የተደረገው። ወደ ኔፐልስ በመጓዝ ላይ ያሉ ይመስላል።"

ኮሎኔል ፍራንኮ ቄሳርና ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን የቄሳር ቢሮ ውስጥ ግድግዳ ላይ የተሰቀለ ትልቅ ካርታ እያነበቡ ነው። "ኔፐልስ በጣም ትልቅ የሆነች ከተማ ናት። በሺህ የሚቆጠሩ የመደበቂያ ሥፍራዎች ሊያገኙ ይችላሉ" አለ ቄሳር።

"ሴትየዋስ?"

"ስለማንነቷ ምንም ሐሳብ የለንም።"

"ለምን አናጣራም?"

"እንዴት?" አለ ቄሳር ግራ ገብቶት።

"ቤላሚ ለሽፋን የምትሆነው ሴት በአስቸኳይ ካስፈለገችው ምንድነው የሚያደርገው?"

"ምናልባት ሴትኛ አዳሪ ሴት ሊይዝ ይችላል።"

"ትክክል! ከየት ነው የምንጀምረው?"

"ከቶር ዲ አንቶን።"

@BOOKALEM

በፓሳጂኤታ አርኪኦሎጂካ ኢድርገው ሱቅ በደረቴዎች ሽቀጣቸውን በጎዳናው ላይ ሲያዘሩ ኢያዩ ተጓዙ። መኪናዋ ውስጥ ከኮሎኔል ፍራንሲስኮ ቄሳር እና ከኮረኒል ፍራንክ ጆንሰን ጋር የቀጣናው ፖሊስ ኢንስፔክተር ሻምበል ቤሊኒ ነበር።

"አሁን የሚጠብቀን ሥራ በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆን ነው! እነዚህ ሴትኛ አዳሪዎች በመካከላቸው ከፍተኛ የሆነ ፉክክር አለ። ነገር ግን ፖሊስን በተመለከተ ልክ እንደአህትማማቾች አንድ ነው የሚሆኑት። በፍጹም መረጃ አይሰጡም።"

"እናያለን!" አለ ፍራንክ ጆንሰን። ቤሊኒ ሾፌሩን መኪናዋን ጥግ አስይዞ እንዲያቆም አዘዘውና ሦስቱም ሰዎች ከመኪና ወረዱ። መንገዱ ላይ የተደርደሩት ሴተኛ አዳሪዎች ሰዎቹን በሲጋት ሲመለከቷቸው ኢንስፔክተር ቤሊኒ ወደነርሱ እየተጠጋ ሄደ።

"እንደምን ዋልሽ ማሪያ? ገበያው እንዴት ነው?" አላት።

"እናንተ ስትሄዱ የተሻለ ይሆናል።"

"እኛም ለመቆየት አላቀድንም። አንድ ጥያቄ ብቻ ልጠይቅሽ እፈልጋለሁ። ባለፈው ምሽት ከናንተ መካል አንዷን ሴት ይዞ የሄደ አንድ አሜሪካዊ በመፈለግ ላይ ነን። ማን እንደሆነች ማወቅ እንፈልጋለን። ልትረጂን ትችያለሽ?" አለና የሮበርትን ፎቶግራፍ ከኪሱ አውጥቶ አሳያት።

ሌሎች በርካታ ሴተኛ አዳሪዎች ወሬውን ለመስማት በዙሪያቸው ተሰባሰቡ። "እኔ ልረዳህ አልችልም! ግን ሊረዳህ የሚችል ሰው አውቃለሁ!" አለች ማሪያ።

ቤሊኒም በማደፋፈር ዐይነት ራሱን ወዘወዘና....."ጥሩ ማነው?" አላት።

ማሪያ ከመንገድ ባሻገር ወዳለ አንድ ሱቅ አመለከተችው። በሩ ላይ "የወደፊት ዕድል ተናጋሪ። የእጅ መዳፍ አንባቢ።"፣ የሚል ጹሑፍ ተሰቅሎበታል። "ማዳም ሉቺያ ልትረዳህ ትችላለች!" አለችው።

የተሰበሰቡት ሴቶች በሣቅ አውካኩ።

ሻምበል ቤሊኒ ዙሪያውን ተመለከታቸውና....."ቀልድ ትፈልጋላችሁ? ጥሩ! የምትወዱት ዐይነት ጥሩ ጥሩ ቀለድ እንቀልዳለን!" አላቸው። "እነዚህ የተከበሩ ሁለት ሰዎች ከአሜሪካዊው ጋር የሄደችውን ሴት ለማገኘት በጣም ተጨንቀዋል። ማን እንደሆነች የማታውቁ ከሆነ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋግራችሁ ስሟን የሚያውቅ ሰው ካገኛችሁና ማንነቷን ከተረዳችሁ በኋላ ሰልክ እንድትደውሉልኝ ስል ሐሳብ አቀርባለሁ።"

"ለምን ብለን?" አለች አንደኛዋ በተቃውሞ።

"በኋላ ትረዱታላችሁ።"

ከአንድ ሰዓት በኋላ የሮም ከተማ ዝሙት አዳሪዎች በሙሉ ተከበቡ። ፓትሮል መኪኖች በከተማዋ ጎዳናዎች ላይ እየተዘዋወሩ በየመንገዱ ላይ ገበያ ፍሊጋ የቆሙትን ሴትኛ አዳሪዎች በሙሉ አሰሯቸው። እሪታ የተሞላበት ተቃውሞ ተደረገ።

"እኔ ለፖሊስ ጥበቃ አከፍላለሁ! በኔ ላይ ይህን ማድረግ አትችልም።"

@BOOKALEM

"ይሄ ለአምስት ዓመታት መተዳደሪያዬ ነው።"

"ለናንተና ለጓደኞቻችሁ በነፃ ሰጥቻለሁ። ምስጋናዬ ይሄ ነው?"

በማግስቱ ጠዋት ጎዳናዎች በሙሉ ከሴተኛ አዳሪዎች ነፃ ሲሆኑ እስር ቤቶች ግን ጢም ብለው ሞሉ።

ቄሳርና ጆንሰን በቤሊኒ ቢሮ ውስጥ ተቀምጠው በመወያየት ላይ ነበሩ። "እነዚህን ሴቶች እስር ቤት ውስጥ ማቆየቱ አስቸጋሪ ይሆናል። እንደዚሁም ለቱሪዝም ሥራችን መጥፎ መሆኑን ለመጨመር እፈልጋለሁ።"

"እትጨነቅ! አንድ ሰው መናገሩ አይቀርም። ግፊቱን መጨመር ብቻ ነው ያለብህ።" በመጨረሻም ከእኩለ ቀን በኋላ ፍንጭ ተገኘ። የቤሊኒ ጸሓፊ ወደ ቢሮው ገባችና....."ሚስተር ሎሬንዞ የተባለ ሰው ሊያይህ ይፈልጋል!" አለችው።

"እስገቢው" አላት።

ሚስተር ሎሬንዞ በጣም ውድ የሆነ ሙሉ ልብስ ከመልበሱም በላይ በሦስት ጣቶቹ ላይ የዐልማዝ ቀለበት አጥልቋል። ሚስተር ሎሬንዞ ሥራው የዝሙት አዳሪዎች አገናኝ ወይም አቃጣሪ ነው።

"ምን ልርዳህ?" ሲል ቤሊኒ ጠየቀው።

ሎሬንዞ ፈገግ አለና....."እኔ ነኝ ልረዳችሁ የምችለው ከቡራን! ከአንድ አሜሪካዊ ጋር የሄደች ሴት እንደምትፈለጉ ነግረውኝ ነበር። እኛም ከባለሥልጣኖች ጋር ለመተባበር ምንጊዜም የምንጓጓበት ጉዳይ በመሆኑ ስሟን ልሰጣችሁ ይገባል ብዬ እገምታለሁ።"

"ማን ትባላለች?" አለ ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን።

ሎሬንዞ ጥያቄውን ችላ አለውና....."እንደተለመደው ያላችሁን አድናቆት ሽርካዎቼንና ጓደኞቻቸውን በመልቀቅ እንደምትገልጹልኝ እተማመናለሁ።"

"እኛ ከአንዷም ሽርሙጣችሁ ጋር ምንም ጉዳይ የለንም" አለ ኮሎኔል ቄሳር። "እኛ የምፈልገው የልጅቷን ሰም ብቻ ነው።"

"ይህ በጣም ምስጋና የተሞላበት ዜና ነው ጌታዬ! ኃላፊነት ከሚሰማቸው ሰዎች ጋር መደራደር ምን ጊዜም ያስደታል። እኔ የማውቀው....."

"ስሟን ሲኞር!" ሎሬንዞ አቋረጠው።

"አዎን በርግጥ! ፒየር ቫሊ ነው። አሜሪካዊው ከእርሷ ጋር ሌሊቱን በሆቴል ሌ ኢንክሮቺዎ ካሳለፈ በኋላ በማግስቱ ሄደዋል። እንደዚህ ከተናገርኩኝ....."

ቤሊኒ በፍጥነት ሰልኩን አንስቶ መደወል ጀምሮ ነበር። "በፒየር ቫሊ ላይ ያለውን ሪኮርድ በሙሉ አምጣልኝ! በአስቸኳይ!" ሲል አዘዘ።

"ከቡራን! ምስጋናችሁን ሴቶቹን በመልቀቅ እንደ....."

ቤሊኒ ቀና ብሎ ተመለከተውና....."እናም "አፕሬሽን ቡታና"ን (ዘመቻ ሴትኛ አዳሪ) ይሰረዝ!" ሲል ተጨማሪ ትእዛዝ ሰጠ።

ሎሬንዞ በደስታ እየፈነደቀ "ግራዜ!" አላቸው።

@BOOKALEM

ከአምስስት ደቂቃ በኋላ የፒየር ቫሊ ሪኮርድ ቤሊኒ ጠረጴዛ ላይ ቀረበ። "የአውራ መንገዱን ሥራ የጀመረችው በአሥራ አምስት ዓመቷ ነው። ከደርዘን ለበለጠ ጊዜ ተይዛ ታሥራለች።"

"ከየት ነው የመጣችው?" ሲል ኮሎኔል ጆንሰን አቋረጠው።

"ከኔፐልስ።" ሁለቱ ሰዎች እርስ በእርሳቸው ተያዩ። "ኔፐልስ ውስጥ አንድ ወንድምና ወላጅ እናት አላት።"

"የት አካባቢ እንደሆነ ማጣራት ትችላለህ?"

"እችላለሁ።"

"አሁኑኑ አድርገው።"

ምዕራፍ አርባ

የኔፐልስን አጎራባች መንደሮች እየተጠጉ ነበር። የታጠቡ ልብሶች የተሰጠባቸው መስኮቶች የሚታይባቸው አሮጌ ህንፃዎች በመንገድ ተደርድረው ህንፃዎቹን በባለቀለም ባንዲራዎች ያሸበረቁ የኮንክሪት ተራሮች አስመስሏቸዋል።

"ወደ ኔፐልስ መጥተህ ታውቃለህ?" ስትል ፔዬር ጠየቀችው።

"አንድ ጊዜ" አለ ሮበርት። ድምፁ ረገጥ ያለ ነበር። ይህን ጊዜ ሱዛን አጠገቡ ተቀምጣ ትሰቃለች። 'ኔፐልስ የተኮነነች ከተማ መሆኗን ሰምቻለሁ። እኛስ እዚህ አንዳንድ የተኮነኑ ነገሮች ማድርግ አንችልም የኔ ፍቅር?' 'ጥቂት አዳዲስ ነገሮችን እንፈጥራለን" ሲል ሮበርት ቃል ገባላት።

ፒየር አተኩራ እየተመለከተችው ነበር። "ደህና ነህ?" አለችው።

ሮበርት ከሐሳብ ሰመመኑ ተመልሶ....."እዎን ደህና ነኝ" አላት። በባሕሩ ውሃ ዳርቻ ላይ የሚገኘውን ጥንታዊ ሕንፃ ዲልህ አቦን፤ ቶሌዶን፤ ጥንታዊውን የኔፐልስ ከፍለ ከተማ እየተቃረቡ መጡ። "ከዚህ ጥቂት ከፍ ብሎ ነው ያለው። በግራ በኩል ወደ ቪአ ቬኔቶ ሮስ ታጠፍ" አለችው።

ሮበርት መኪናውን ጠምዞ ይነዳ ጀመር። አካባቢው በመኪና የተጨናነቀ ከመሆኑም በላይ የጡሩንባው ድምፅ ጆሮ የሚያደነቁር ነበር። ሰዎች ላለመግጨት ሲል ሮበርት በዝግታ ይነዳ ጀመር።

"እዚህጋ ወደ ቀኝ ታጠፍና ወደ ፒያዛ ዴል ፕሌቢሰቶ ግባ" ስትል ፒየር መራችው። የትራፊኩ መጨናነቅ የባሰ ከመሆኑም በላይ አካባቢው በፊት ከሚያውቀው በበለጠ ተለውጧል።

"ቁም!" ስትል ፒየር

ሮበርት ወደ ኩርባው ተጠግቶ የተደርጉና አነስተኛ ሱቆች ፊት ለፊት መኪናውን አቆማትነና ዙሪያውን ተመልከቶ....."እናትሽ የሚኖሩት እዚህ ነው?" አላት።

@BOOKALEM

"አይደለም አለችና ተንጠራርታ የመኪናውን ጡሩምባ ተጫነችው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንዲት ወጣት ልጃገረድ ከሱቅ ስትወጣ ፒየር ከመኪናው ወረደችና ወደ ልጅቷ በረረች። ሁለቱ ሴቶች ተቃቀፉ።

"እጅግ በጣም አምሮብሻል። በጣም ሳይሳካልሽ አይቀርም!" አለች።

"አዎን! የእጅ አምባሬን ተመልከቺ!" አለቻት ፒየር።

"እውነተኛ ዕንቁ ነው?"

"አዎን ነው።"

ልጅቷ ወደ ሱቁ ዘወር አለችና....."ወደዚህ ነይና ማን እንደመጣ ተመልከቺ" ስትል ጠራቻት።

"መጣሁ ፍቅሬ! ጓደኞቼን ሰላም ልበል" አለች የተጠራችው ሴት። በደቂቃ ውስጥ ከግማሽ ደርዘን በላይ የሆኑ ሴቶች በፒየር ዙሪያ ተሰብስበው እምባሯን ሲያደንቁ ሮበርት የሚያደርገው ጠፍቶት ጥርሱን ነክሶ ይመለከት ጀመር።

"ስለኔ አብዶልኛል!" አለችና ፒየር ወደ ሮበርት ዘወር ብላ ....."አይደለም ካሮ?" ስትል ተጣራች። ሮበርት ቢያንቃት ደስ ባለው ነበር። ነገር ግን ምንም ሚድረግ የሚችለው ነገር አልነበረም።

"አዎን! አሁን መሄድ አንችልም ፒየር?" አለ ጮክ ብሎ።

"በደቂቃ ውስጥ" አለችው።

"አሁን!" አለ ሮበርት።

"አህ! በጣም ጥሩ!" አለችና ፒየር ወደ ሴትዮዋ....."ዞራ በጣም አሰፈላጊ የሆነ ቀጠሮ ስላለን አሁን መሄድ አለብን። ቻው!" አለቻት።

"ቻው!"

ፒየር መኪናው ውስጥ ገብታ ሮበርት አጠገብ ከተቀመጠች በኋላ መኪናቸውን አስነስተው ሲሄዱ ሴቶቹ ቆመው ተመለከቷቸው።

"በሙሉ የዱሮ ጓደኞቼ ናቸው!" አለች ፒየር በደስታ ስሜት።

"በጣም ግሩም። የናትሽ ቤት ወዴት ነው?"

"ከተማ ውስጥ አይደለም የምትኖረው።"

"ምን?"

"ከከተማው ውጭ የግማሽ ሰዓት መንገድ ወጣ ብሎ በአንድ የእርሻ ሥፍራ ላይ ያለ ቤት ውስጥ ነው የምትኖረው።"

የእርሻው ቤት በደቡባዊ የኔፐልስ ከተማ ዙሪያ የሚገኝ ሲሆን ከመንገድ ወጣ ያለ አሮጌ የድንጋይ ሕንፃ ነው።

"ያውና! ቆንጆ ቤት አይደለም?" አለች ፒየር በደስታ።

"አዎን!" አለ ሮበርት። ቤቱን የወደደበት ምክንያት ከከተማ የወጣ በመሆኑ ነው። ማንም ሰው እዚህ ድረስ መጥቶ እሱን የሚፈልግበት ምክንያት አይኖረውም። ፒየር ትከክል ነበረች። አስተማማኝ የመደበቂያ ሥፍራ ነው። የቤቱ ፊት በር ደርሰው

@BOOKALEM

ቆሙ። የፒየር እናት ቀጭን፤ ግራጫ ፀጉርና ከጥንቃቄ ብዛት የተጨማደደ የፊት ገፅታ ያላት ሴት ወይዘሮ ከመሆኗም በላይ ያረጀች የሴት ልጂ አምሳያ ነበረች።

ፒየር! በጣም ነበር የናፈቅሺኝ።

"እኔም በጣም ነው የናፈኩሽ እማማ! ወደ ቤት አመጣዋለሁ ብዬ በስልክ የነገርኩሽ ወዳጄ ይህ ነው!" አለች ፒየር።

እማማ አንዲንም ነጥብ አልሳቱም። "አሃ? እንኳን ደህና መጣህ ሚስተር.....?"

"ጆንሰን!" አለ ሮበርት።

"ግባ.....ግባ" አሉ አሮጊቷ።

ወደ ሳሎን ተያይዘው ገቡ። ክፍሉ በጣም ትልቅ፤ በቤት ዕቃዎች የተሞላ፤ ምቹና የመኖሪያ ቤትነት ወግ ያለው ነው።

ገና በለጋዎቹ ሃያ ዓመታት ውስጥ የሚገኝ ወጣት ልጅ ወደ ክፍሉ ገባ። ልጁ አጭርና ቀጫጫ የሆነ ተክለ–ሰውነት ሲኖረው ፀጥተኛና አሳቢ የሚመስሉ ቡናማ ዐይኖች ነበሩት። ጂንስ ሱሪና "ቀይ ሰይጣን"› የሚል ጽሑፍ የተሰፋበት ጃኬት ለብሷል። እህቱን ሲያያት ፊቱ በደስታ በራና "ፒየር!" ብሎ ጮኸ።

"ሄሌ ካርሎ!" አለቸውና ወንድምና እህት ተቃቀፉ።

"እዚህ ምንድነው የምታደርጊው?"

"ለአጭር ጊዜ ጉብኝት ለማድረግ ነው የመጣነው።" ወደ ሮበርት ዘወር አለችና....."ይህ ታናሽ ወንድሜ ካርሎ ነው። ይህ ደግሞ ሚስተር ጆንስ ይባላል!" ብላ አስተዋወቀቻቸው።

"ሄሎ ካርሎ!"

ካርሎ ሮበርትን እያጠናው....."ሄሎ!" አለ።

"እማዬ ለእናንተ ለሁለት ፍቅረኛ ወፎች በስተኋላ ካሉት ክፍሎች ውስጥ መኝታ አዘጋጅላቸው ብላኛለች።"

"ችግር የማይፈጥርብህ ከሆነ ምናልባት ትርፍ ክፍል ካላችሁ የመኝታ ክፍል ለብቻዬ ቢዘጋጅልኝ እመርጣለሁ።"

ለጥቂት ጊዜ ያህል የሚረብሽ ዐይነት ዝምታ ሰፈነ። ሦስቱም ሰዎች ሮበርትን ትክ ብለው እየተመለከቱት ነው።

አሮጊቷ ወደ ፒየር ዘወር ብለው....."ፍናፍንት (ግብረ ሰዶማዊ) ነው እንዴ?" አሏት። ፒየር ትከሻዋን ነቀነቀችና....."አላውቅም" አለች። ግን ሮበርት የግብረ ሰዶም ልማደኛ እንዳልሆነ እርግጠኛ ነበረች።

እማማ ወደ ሮበርት እየተመለከቱ....."ደስ እንዳለህ!" አሉና ልጃቸውን....."እንደገና ስላየሁሽ በጣም ተደስቻለሁ!" አሏት። "ነይ እስቲ ወደ ምግብ ማብሰያው ክፍል እንሂድና ቡና እናዘጋጅ" አሏት።

@BOOKALEM

ምግብ ማብሰያው ውስጥ እንደገቡ....."ቤኒሲሞ! እንዴት ብለሽ አገኘሽው? በጣም ሀብታም ሰው ይመስላል" አሏት። "ይሄ ያደረግሽው የእጅ አምባር ደግሞ በርካታ ንዋይ የፈሰሰበት መሆን አለበት። አምላኬ! ዛሬ ምሽት በጣም ታላቅ የሆነ እራት ነው የማዘጋጀው። ጎረቤቶቼን በሙሉ እንጋብዝና እንደ....."

"የለም እማማ። ይህንን ማድረግ የለብሽም።"

"ግን ካራ!" አሏት በቤት ስሟ። "ለምንድነው ስለገጠመሽ መልካም ዕድል ዜናውን የማናሠራጨው? ወዳጆቻችን በሙሉ ይደሰታሉ።"

"እማማ ሚስተር ጆንስ ለጥቂት ቀናት ብቻ ነው ለማረፍ የሚፈልገው። ምንም ዐይነት ፓርቲም ሆነ ጎረቤት አያስፈልግም።"

እማማ በረሸሙ ተነፈሱና....."እሺ! እንደፈለግሽ" አሉ።

'እማማ እንዳትረበሽ ከቤት ውጭ እንዲያዝ አድርጌ ሁኔታዎችን አመቻቻለሁ' አለች በሐሳ ቧ።

ካርሎ የእጅ አምባሩን በጣም ነው አተኩሮ የተመለከተው። "የእጅ አምባሩ እውነተኛ ሉል ነው። አንተ ነህ ለእሁቴ የገዛህላት?"

ሮበርት ስለልጁ የጠላው ነገር አለ። "ጠይቃት!" አለው።

ፒየርና እማማ ከኩሽና ወደ ሳሎን ገቡ። እማማ ሮበርትን እያዩ....."እርግጠኛ ነህ ከሷ ጋር መተኛት አትፈልግም?" ሲሉ ጠየቁት።

ሮበርት ሃፍረት ተሰማው። "የለም አመሰግናለሁ አልፈልግም" አለ።

"እሺ መኝታ ቤትህን አሳይሃለሁ" አለቸና ፒየር ሮበርትን እየመራች በስተኋላ ወዳለ አንድ ክፍል ወሰደችው። መኝታ ቤቱ በጣም ሰፊና ምቹ ሲሆን እከፍሉ መኻል ላይ ሁለት አልጋዎች አሉት።

"ሮበርት እኔና አንተ አብረን ብንተኛ እማማ ምን ታስባለች ብለህ ፈርተህ ነው? ምን እደምሠራ ታውቃላች እኮ።"

"እሱ አይደለም" አለ ሮበርት። ምክንያቱን ሊያስረዳ የሚችልበት ምንም መንገድ አልነበረውም። "አዝናለሁ! እኔ....."

የፒየር ድምጽ ቀዝቀዝ ያለ ሆነ። "ግድ የለም" አለችው። በጣም የተዋረደች መስሎ ነበር የተሰማት። ሁለት ጊዜ ከእርሷ ጋር ላለመተኛት እምቢተኛ ሆነ። 'እሱን ለፖሊስ አሳልፌ መስጠት ትክክለኛ ዋጋው ነው!' ስትል አሰበች። በአንፃሩ ደግሞ መጠነኛ የሆነ የሚከነክን የጥፋተኛነት ስሜት ተሰማት። 'በጣም ጥሩ ሰው ነው። ግን ሃምሳ ሺህ ዶላር ደግሞ ሃምሳ ሺህ ዶላር ነው።'»

እራት በሚመገቡበት ጊዜ እማማ ከመጠን ያለፈ ለፍላፊ ሆነው ሲገኙ ሮበርት ደግሞ የማምለጫ እቅዱን በጥድፊያ እያሰላሰለ ነበር። ወደ ወደብ ሄጄ ከዚህ አገር የሚያወጣኝ መርከብ እፈልጋለሁ ።'»

ፒየር ደግሞ ስለምታደርገው የስልክ ጥሪ እያሰላሰለች ነበር። 'ፖሊሶች አቅጣጫችንን እንዲያውቁ ከተማ ገብቼ እደውላለሁ።'

@BOOKALEM

ካርሎ ደግሞ እህቱ እቤት ያመጣችውን እንግዳ እያጠናው ነው። 'በጣም ቀላል ዒላማ ሊሆን ይችላል።'

የእራት ገበታ ከፍ ካለ በኋላ ሁለቱ ሴቶች ወደ ምግብ ማብሰያው ክፍል ሲገቡ ሮበርትና ካርሎ ብቻቸውን ቀሩ። "እህቴ ወደ ቤት ያመጣችው የመጀመሪያው ሰው አንተ ብቻ ነህ። መቼም በጣም ሳትወደህ አይቀርም።"

"እኔም በጣም እወዳታለሁ።"

"አስፈላጊውን ሁሉ ጥንቃቄ ልታደርግላት ነው?"

"እህትህ ለራሷ አስፈላጊውን ሁሉ ጥንቃቄ ማድረግ ትችላለች።"

ካርሎ በእርካታ ፈገግ አለ። እፊቱ የተቀመጠው እንግዳ ዝንጥ ብሎ የለበሰ ከመሆኑም በላይ ሀብታም መሆኑ በግልጽ ያስታውቃል። 'ያሸበረቀ ሆቴል ውሰጥ ለማረፍ ሲችል ለምንድን ነው እዚህ ማረፍን የመረጠው?' ካርሎ ሊያስበው የቻለው ብቸኛ ምክንያት ሰውዬው በመደበቅ ላይ መሆኑን ብቻ ነው። ይህም ደግሞ አንድ የሚያጓጓ ነጥብ አስነሳ። 'አንድ ሀብታም ሰው በሚሸሸግበት ጊዜ ከሁኔታው በሆነ መንገድ ገቢ የሚያደረግ ገንዘብ አለ።'

'ከየት ነው የመጣህው?' ሲል ካርሎ ጠየቀ።

'በተለይ የመጣሁበት ሥፍራ የለም። ብዙ ጉዞ አደርጋለሁ።'

"በንግድ ሥራ ላይ ነው የተሰማራህው?"

"በጡረታ ተገልያለሁ።"

'ይህን ሰው እንዲያወራ ለማስገደድ ብዙም አያስቸግርም።' "የቀይ ሰይጣን" ቡድን መሪ የሆነው ሉቻ በጥቂት ጊዜ ውሰጥ ምሥጢሩን ሊያስለፈልፈው ይችላል።'" "ለመሆኑ ከኛ ጋር ምን ያህል ጊዜ ትቆያለህ?"

"ይህን ያህል ጊዜ ለማለት በጣም ያስቸግረኛል" አለ ሮበርት። የልጁ የማውቅ ጉጉት እየነካው መጣ።

ፒየርና እናቷ ከኩሽና ተያይዘው መጡ። "ጥቂት ቡና ትፈልጋለህ?"

"የለም አመሰግናለሁ። በጣም ግሩም የሆነ እራት ነበር የጋበዙኝ።"

"ያ ምንም አይደለም። ነገ ከዚህ የበለጠ የበዓል ድግስ ነው የማዘጋጅልህ።"

"ጥሩ" አለ ሮበርት። በዚያ ወቅት ሮበርት አይገኝም። ከመቀመጫው እየተነሳ....."ቅር የማይላችሁ ከሆነ በጣም ሰለ ደከመኝ መተኛት እፈልጋለሁ" አለ።

"በእርግጥ ትችላላህ። በደህና እደር!" አሉ እማማ!

"ደህና ይደሩ!"

ሮበርት ወደ መኝታው ከፍል ሲያመራ ተመለከተች። ካርሎ ሳቅ "አለና አንቺ ከእርሱ ጋር ለመተኛት ብቁ ነሽ ብሎ አያስብም" አላት። ትችቱ ልክ የታለመለትን ያህል እንደመርዝ ነደፋት። ሮበርት የግብረ ሰዶም ሴሰኛ መሆኑን ቢታውቅ ሰሜት አይሰጣትም ነበር። ግን ከሱዛን ጋር ሲያወራ ሰምታዋለች። ምን እንደምታደርግ ታውቃለች። 'ይህንን ሰትሮንዞ» አሳየዋለሁ!' አለች።

@BOOKALEM

ሮበርት አልጋው ውስጥ ጋደም ብሎ ቀጣይ እንቅስቃሴውን ማንሰላሰል ጀመረ። ከሬይዲት ካርዱ ውስጥ ታሽጎ በነበረው የአቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያ አማካይነት የሐሰት ፈለግ ለመተው መቻሉ መጠነኛ የሆነ ጊዜ እንዲያገኝ ረድቶታል። ቢሆንም ግን እዚህ ላይ ብዙም ሊተማመን አይችልም። ምናልባት በአሁኑ ጊዜ ቀዩን የጭነት ካሚዎን ይዘውት ሊሆን ይችላል። ከኋላው የሚያሳድዱት ሰዎች ጨካኝና ቀልጣፎች ናቸው። 'የዓለም መንግሥታትና ርዕሰ ብሔሮች በዚህ ግዙፍ እውነትን የመሸፈን ዘመቻ ውስጥ ተካፍለው ይሆን? ወይስ በአንድ ድርጅት ውስጥ የሚገኝ ሌላ ድርጅት በስለላው ማሕበረሰብ ውስጥ በላኤ ሰብ የሆነ ሕገ ወጥ የግል ንቅናቄ እያደረገ ይሆን?' ሮበርት ሁኔታውን የበለጠ ባሰበበት ቁጥር የተለያዩ አገሮች መራሔ መንግሥታት ስለጉዳዩ የሚያውቁት ነገር አይኖርም የሚለው ሐሳብ የሚያሳምን ሆነበት። አንድ ሐሳብ ድንገት አዕምሮው ውስጥ ተከሰተ። የአድሚራል ዊታከር ከባሕር ኃይሉ የመረጃ ጽሕፈት ቤት ኋላፊነት በድንገት በጡረታ መገለላቸውና ወደ ግዙት ዐይነት ሥራ መመደባቸው እንግዳ ነገር ሆኖበት ነበር የቆየው። ግን አንድ የዚህ ሴራ አባሪ ሊሆኑ እንደማይችሉ የሚያውቅ ሰው ሥራቸውን እንዲለቁ ያስገደዳቸው ከሆነ ነገሩ ስሜት ይሰጣል። 'አድሚራሉን ማግኘት አለብኝ!' አለ። ስለሚደረገው ሴራ እውነቱ ላይ ለመድረስ ሊያምነው የሚችለው ሰው ቢኖር አድሚራሉ ብቻ ናቸው። ጎግ አለ ሮበርት በሐሳቡ። 'ነገ.....' ዐይኖቹ ተጨፈኑ እንቀላፋ።

የመኝታ ቤቱ በር ሲንሳጠጥ ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው። ወዲያውኑ በተጠንቅ ከተጋደመበት ቀና ብሎ ተቀመጠ። የሆነ ሰው ወደ አልጋው እየቀረበ ነበር። ሮበርት ሰውነቱን አስቆጥቶ ለመወርወር እንደተዘጋጀ ያርከፈከፈችው ሽቶዋ ሸተተው። ቀጥሎ ጎኑ አልጋው ውስጥ ስትገባ ተሰማው።

"ፒየር.....ምንድን ነው.....?

"እሽ....ሽ....ሽ" በሰውነቷ ሰውነቱን ተጫነችው። ፍጹም እርቃኗን ነበረች።

"እ.....አዝናለሁ ፒየር። ምንም ነገር ላደርግ አልችልም።"

"ምንም ነገር የለም? እንግዳው እኔ አንድ ነገር ላድርግልህ!" አለችው በለሆሳስ ድምፅ።

"ምንም ጥቅም የለውም። አትችይም!" አላት ጥልቅ የሆነ ፍራቻ እየተሰማው። ሊሆን በማይችለው ነገር ከሚመጣው ሃፍረት ሁለታቸውንም ለማዳን ፈለገ።

"ሮበርት ትወደኛለህ? ቆንጆ ሰውነት አላት ብለህ ታስባለህ?"

"አዎን!"

እሷም ሥራዋን ቀጠለች። የሰውነቷ ሙቀት ሰውነቱን ተሰማው። በለስላሳ ጣቶቿ በደረቱ ላይ ከታች ወደ ላይ እየተመላለሰች አሻሸችው።

@BOOKALEM

ከሌላ ሴት ጋር የደረሰበት ውርደት ከመደገሙ በፊት ማስቆም አለብኝ አለ በሐሳቡ። "ፒየር! እኔ ፍቅር መሥራት አልችልም። ከረዥም ጊዜ በፊት ጀምሮ ከሴት ጋር ተኝቼ አላውቅም።"

"እንተ ምንም ማድርግ የለብህም ሮበርት። እኔ ትንሽ መጫወት እፈልጋለሁ። ሲጫወቱብህ አትወድም?" ምንም ስሜት አልነበረውም። የተረገመች ሱዛን ከራሷ በላይ ነበር ይዛ የሄደቸው። ወንድነቱንም ጭምር ነበር ይዛ የሔደችው።

ፒየር በሰውነቱ ላይ ወደ ታች እየተንሸራተተች ወረደች። "ዙርና ተኛ!" አለችው። "ምንም ጥቅም የለውም ፒየር። እኔ....." ራሷ ገልብጣ አስተኛችው። ሱዛንና ሙት ስሜቱን እየረገመ ተጋደመ። አሁን የፒየር ምላስ በጀርባው ላይ ሞቃትና ውብ የሆነ እንቅስቃሴ እያደረገ ወደ ታች..... ወደ.....ታች እያለ ሲወርድ ተሰማው።

"ፒየር....."...

"እሽ...ሽ...ሽ...ሽ" .....

ምላሷ ለሰላላ ከመሆኑም በላይ ጡቶቿ ከምላሷ ጋር በሰውነቱ ላይ እየታከኩ ወደ ታች ሲወርዱ ተሰማው። የሰውነቱ ንዝረት እየጨመረ ሲሄድ ተሰማው። ወንድነቱ አድጎ ተነስቶ እንደ አለት ሲነጠነክር....። በመጨረሻም ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰዳቸው።

አሥራ ሰምንተኛ ቀን

ጎህ ቀዶ የማለዳ ብርሃን በመስኮት ሲገባ ሮበርት ከእንቅልፉ ነቃ። ፒየርን እቅፍ አድርጎ ያዛትና....."አመሰግናለሁ!" ብሎ ሹክ አላት።

ፒየር የሸር ፈገግታ ሳቅ አለችና....."እንዴት ይሰማሃል?" ስትል ጠየቀችው።

"በጣም ግሩም!" አላት። በርግጥም ግሩም እርካታ ተሰምቶታል። ፒየር እላዩ ላይ ልጥፍ አለችና....."አውሬ!" አለችው።

ሮበርት ፈገግ አለና....."አንቺ ለኔ ተሞክሮ በጣም ግሩም ነሽ!" አላት።

ፒየር አልጋው ላይ ተቀመጠችና ኮስተር ብላ....."አንተ የአደንዛዥ እጽ አመላላሽ አይደለህም። ነህ?" አለችው

የዋህ ጥያቄ ነበር። "አይደለሁም።"

"ግን ኢንተርፖል እያሳደደህ ነው።"

"አዎን።"

ፊቷ በድንጉተኛ ፀዳል በራ። "አውቄአለሁ! ሰላይ ነህ አይደለም?" አለች እንደሕፃን ልጅ በሰሜት ጓጉታ።

@BOOKALEM

ሮበርት ሳቀ። "ነኝ?" አለና በሐሳቡ 'ውብ ቆንጆ ልጃገረድ አፍ ውስጥ' ብሎ ቆዘመ።

"እመን!" አለች ፒየር እየገፋፋችው። "ሰላይ ነህ አይደለም?"

"አዎን!" አለ ሮበርት። "ሰላይ ነኝ።"

"አውቄአለሁ!" አለች ፒየር ዐይኗ እየበራ። "ጥቂት ምስጢሮችን ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"ምን ዐይነት ምሥጢሮችን?"

"ታውቃለህ? የሰላይ ምሥጢሮችን። የምሥጢር ምልክቶችንና የዚያን መሰል ነገሮችን። የስለላ ልብ ወለዶችን ማንበብ እወዳለሁ። ሁል ጊዜ አነባለሁ።"

"ታነቢያለሽ?"

"አዎን! ግን እነሱ የፈጠራ ታሪኮች ናቸው። እውነተኛ ነገሮችን ግን አንተ ታውቃለህ። አይደለም? ለምሳሌ ሰላዮች ከሚጠቀሙባቸው ምልክቶች አንዱን ልትነግረኝ አትፈቅድም?"

ሮበርት ኮስተር ብሎ....."ደህና! መናገር እንኳ አይገባኝም። አንድ ግን መናገር ምንም አይደለም።" "ልታምን የምትችለውን ነገር ምን ልትነግራት?""አዎን! የመጋረጃው ብልሃት!" አለ።

ዐይኗ ፍጥጥ ብሎ....."የመጋረጃው ብልሃት?" አለችው።

"አዎን" አለና ሮበርት ወደ መኝታ ቤቱ መስኮት አመለከታት። "ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር የዋለና አስተማማኝ ከሆነ መጋረጃውን ወደ ላይ እንደተገለጠ ትተይዋለሽ። ይህ ሰላይ ባልደረባሽን ከአደጋ ለማራቅ የምትጠቀሚበት ምልክት ነው።"

ፒየር በጣም ተደስታ "በጣም ግሩም ነው! የዚህ ዐይነት ዘዴ ከመጽሐፍ አላነበብኩም" አለችው።

"ማንበብ አትችይም። በጣም ምሥጢር ነው!" አላት።

"ለማንም አልናገርም!" ብላ ቃል ገባችለት። "ሌላስ?"

'ሌላስ?' አለ በሐሳቡ። "ደህና! የስልኩ ዘዴም አለ።" ፒየር ልጥፍ አለችበትና....."ስለሱም ንገረኝ" አለችው።

"ባልደረባሽ የሆነ ሰላይ ነገሮች አስተማማኝ መሆናቸውን ለማወቅ ደወለ እንበል። ፒየር እንድትቀርብለት ጠየቀ። ሁኔታው ጥሩ ወይም አስተማማኝ ከሆነ "እኔ ፒየር ነኝ"ትያለሽ። የተበላሸ ሁኔታ ካለ ግን "የተሳሳተ ቁጥር ነው"ትያለሽ።

"በጣም ያሚያስደስት ነው!" አለች በአድናቆት።

'ይህን ዐይነት አልባሌ ታሪክ ሳወራ ማሠልጠኛው እርሻ ላይ ያሉት አለቆቼ ቢሰሙ የልብ ድካም ይይዛቸዋል' አለ በሐሳቡ።

"ሌላስ ልትነግረኝ ትችላለህ?" አለች ፒየር።

@BOOKALEM

ሮበርት ሳቀና.....“የለም። እነዚህ ለአንድ ቀን ጠዋት በቂ ምሥጢሮች ናቸው” አላት።

“እህ!” አለች ፒየር ሰውነቱን በሰውነቷ እየታከከች። “አሁን ገላህን ለመታጠብ ትፈልጋለህ?” አለችው።

አዎን።።

የሞቀው ውሃ ውስጥ እንዱ ሌላውን በሳሙና እየሙቱ ይታጠቡ ጀመር። ፒየር የሮበርትን እግሮች ከፍታ ሳሙና መቀባት ስትጀምር ነገርዬው እንደገና መጋል ጀመረና ባኞ ውስጥ ፍቅር ሠሩ።

ሮበርት ልብሱን ሲለባብስ ፒየር ፒጃማ ጣል አደረገችና.....“እስቲ የቁርሱን ጉዳይ ልመልከት” ብላው ሄደች። ምግብ ቤቱ ውስጥ ካርሎ እየጠበቃት ነበር።

“ስለጓደኛሽ ንገሪኝ” አላት ወንድሟ።

“ስለሱ ምን ልንገርህ?”

“የት ነው ያገኘሽው?”

“ሮም ውስጥ።”

“ያንን የሉል አምባር ከገዛልሽ በጣም ሀብታም መሆን አለበት።”

ትከሻዋን ነቀነቀችና.....“ይወደኛል!” አለችው።

“ምን እንደማስብ ታውቂያለሽ?” አለ ካርሎ። “ጓደኛሽ ከአንድ ከሆነ ነገር በመሸሽ ወይም በማምለጥ ላይ ያለ ይመስለኛል። ለትክክለኛው ቦታ ሁኔታውን ብናሳውቅ ዳጎስ ያለ ሽልማት ልናገኝ እንችላለን።”

ዐይኗ እንደእሳት እየተንቀለቀለ ወደ ወንድሟ ተጠጋችና .....“ካርሎ! ከዚህ ነገር ብትርቅ ይሻልሃል!” አለችው።

“እና በመሸሽ ላይ ነው ያለው?”

“ስማ! አንተ ዲቃላ! አሁንም የራስህን ጉዳይ ብቻ ተከታተል ስል አስጠነቅቅሀለሁ!” አለችው። ሽልማቱን ከማንም ጋር የመካፈል ፍላጎት የላትም።

“ትንሿ እህቴ ሁሉንም ሽልማት ለብቻሽ ነው የፈለግሽው?” አላት።

“የለም አልገባህም ካርሎ።”

“የለም?”

ፒየር ከልቧ እንዲህ አለች። “አንድ ነገር እነግርሃለሁ። ሚስተር ጆንስ ከሚስቱ በመሸሽ ላይ ነው ያለው። የሚከታተለው መርማሪ ተከራይታበታለች። ጉዳዩ ይኸው ነው።”

ካርሎ ሳቀና.....“ታዲያ ለምንድነው ይህንን ከዚህ በፊት ያልነገርሽኝ? ስለዚህ ይህ ትልቅ ንግድ (ቢዝነስ) አይደለም ማለት ነው። እሺ! እኔም ጉዳዩን ትቼዋለሁ” አለ።

“ጥሩ!” አለች ፒየር።

@BOOKALEM

ካርሎም በሐሳቡ.....“ይህ ሰው ማን እንደሆነ ማጣራት አለብኝ!” አለ።

ጃኑስ በስልክ እየተነጋገረ ነበር። “.....እስካሁን ያገኛችሁት ዜና አለ?”

“ኮማንድር ቤላሚ ኔፐልስ ውስጥ መሆኑን እናውቃለን።

“እስካሁንስ ድረስ የተገኘ ውጤት አለ?”

“አሁንም እየተከታተሉት ነው። መሪ የሆኑ ጭብጦች አሉን። ከቤተሰቦቿ ጋር ኔፐልስ ውስጥ ነዋሪ ከሆነች አንዲት ሴተኛ አዳሪ ጋር በመጓዝ ላይ ነው። ወደ ኔፐልስ እየተጓዙ ነው ብለን ሰለምናምን እዚያው ድረስ እንከተላቸዋለን።”

“በየጊዜው የተገኘውን እድገት አሳውቀኝ።”

የኔፐልስ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ቢሮ የፒየር ወላጆች የት እንደሚገኙ ለማወቅ በመጣደፍ ላይ ነው። በደርዘን የሚቆጠሩ ሰላዮችና የኔፐልስ ከተማ ፖሊሶች ሮበርትን ለማግኘት ከተማዋን በማበጠር ላይ ናቸው።

ካርሎ በሮበርት ላይ እቅዱን እያዘጋጀ ሲሆን ፒየር ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢንተርፖል ለመደወል ተዘጋጅታለች።

ምዕራፍ አርባ አንድ

በአየሩ ላይ የሰፈነው ውጥረት ተጨባጭ አካለዊ ገሃድነት ያለው ከመምሰሉ የተነሳ ሮበርት እጁን ቢልክ የሚነካው መሰሎ ነበር የተሰማው። ወደቡ በሠራተኞች ብዛት እንደጉብ ቀፎ ተወሮ የጭነት መርከቦችን የመጫንና የማራገፍ ተግባር በከፍተኛ ጥድፊያ እየተከናወነበት ነው። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ማን አንድ ሌላ ትርጓትም ተጨምሮበታል። መርከቦች የሚቆሙበትን የውሃ ዳርቻ የፖሊስ መኪኖች ወደ ላይ እና ወደ ታች ይመላለሱበታል። የምሥጢር መርማሪዎች መሆናቸው በግልጽ የሚታወቅባቸው ሰዎችም ባሕረኞችንና የወደቡን ሠራተኞች እያስቆሙ በጥያቄ ያጣድፋሉ። እጅግ የተጠናከረው የሰው አደን ለሮበርት ያልታሰበ አስደንጋጭ ዱላ ሆነበት። ሁኔታው ሲታይ መጀመሪያ የሮበርትን ኔፐልስ ውስጥ መኖር ያወቁ ይመስላል። ያለዚያ በእያንዳንዱ የኢጣሊያ ከፍተኛ ከተማ ውስጥ ሁሉ የዚህ ዐይነት የተጠናከረ የአደን ዘመቻ ማድረግ ፈፅሞ የማይቻላቸው ነው። ሮበርት ከነበረበት መኪና ውስጥ ለመውጣት እንኳ አልቃጣም። መኪናውን አዞረና ከመርከቦች ማቆሚያው ሥፍራ ወጣ። በጣም ቀላል ነው ብሎ አሰቦት የነበረው ዕቅድ ማለትም ወደ ፈረንሳይ የሚወጣ መርከብ የመሳፈሩ ጉዳይ አሁን እጅግ በጣም አደገኛ ሆነበት። የነበሩትን አማራጮች በሙሉ እንደገና ተመለከታቸው። ወጣም ወረደ አሁን ኔፐልስ ውስጥ መኖሩን አነፍንፈው ደርሰውበታል። የመርከብ ማቆሚያ ሥፍራዎች ስለሚጠብቁ

@BOOKALEM

እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ በየመንገዱ ላይ ፍተሻና የመቆጣጠሪያ መሰናክል ስለሚኖር የሆነውን ያህል ርቀት በመኪና መጓዝ እጅግ አደገኛ ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት የባቡር ጣቢያው መስመርና የአየር ማረፊያውም ይጠበቃል። ሮበርት በአሁኑ ወቅት ልክ ሞርሳ ላይ የታሰረ ሲሆን ማሰሪያው ብረት ደግሞ በላዩ ላይ እየጠበቀበትና እየጨፈለቀው ነው።

ሮበርት የሱዛንን ግብዣ አሰበበት። ከጅብራልታር የባሕር ወሽመጥ ገና በመልቀቅ ላይ ነን። የፈለክበት ቦታ ድረስ መጥተን ልናነሳህ እንችላለን።' ምናልባት ይህ የመጨረሻ ማምለጫ መንገዱ ሊሆን ይችላል። ሮበርት ሱዛንን በዚህ ጉዳይ ውስጥ ለመጨመር ባይፈልግም ሌላ ምርጫ ሊመጣለት አልቻለም። አዳኞቹ ሮበርትን በአንድ የግል ጀልባ ላይ የሚፈልጉበት ምክንያት አይኖራቸውም። 'ሐልካዮን ጀልባ ላይ ልሳፈር የምችልበት መንገድ ካገኘሁ በማርሴ የባሕር ዳርቻ አካባቢ ሊያወርዱኝ ይችላሉ። እናም ወደ ወደቡ በራሴ ጥረት እገባና እነሱዛንን ከችግር ነፃ ላደርጋቸው እችላለሁ።'

መንገድ ዳርቻ ላይ የሚገኝ አንድ ምግብ ቤት ፊት ለፊት መኪናውን አቆመና ስልክ ለመደወል ወደ ውስጥ ገባ። በአምስት ደቂቃዎች ውስጥ ከሐልካዮን መርከብ ጋር ለመገናኘት ቻለ።

"እባክዎ ወይዘሮ ባንክስን?"

"የሚጣራው ማነው ልበል?"

"የዱሮ ጓደኛዋ መሆኔን ይንገሩልኝ።"

ከአንድ ደቂቃ በኋላ የሱዛን ድምፅ መጣለት። "ሮበርት አንተ ነህ?"

"አዎን።"

"እስካሁን አላሰሩህም?"

"የለም ሱዛን አልያዙኝም" አላት። ጥያቄውን ለመስንዘር ግን በጣም አስቸጋሪ ሆነበት። "ሱዛን የዕርዳታ እጅሽ አሁንም ክፍት ነው?"

"በእርግጥ ነው! መቼ?"

"ዛሬ ማምሻውን ኔፕልስ መድረስ ትችያለሽ?"

"አላውቅም" አለችና ለትንሽ ጊዜ ካመነታች በኋላ....."አንድ ጊዜ ጠብቅ" አለችው። ሱዛን ስታወራ ድምጿ ይሰማዋል። እንደገና መስመሩ ላይ ተመልሳ መጣች። "ሞንቴ የሞተር ብልሽት ችግር አለብን ይላል። ግን ቢሆንም ኔፕልስ በሁለት ቀን እንደርሳለን።"

'የተረገመ!' አለ ሮበርት በልቡ። በየቀኑ እዚህ ያለው የመያዝ ዕድሉ እየጨመረ ነው። "እሺ በጣም ጥሩ!" አላት ሱዛንን።

"እንዴት እናገኝሃለን?"

"እኔ አገኛችኋለሁ።"

"ሮበርት እባክህን ተጠንቀቅ!"

"እሞክራለሁ! በእርግጥ እየሞከርኩ ነው።"

"ምንም ነገር እንዲደርሰብህ አታደርግም?"

@BOOKALEM

"የለም ምንም እንዲደርስብኝ አላደርግም። ባንቺም እንደዚሁ።"

ሱዛን ስልኩን ዘግታ ወደ ባሏ ዘወር ብላ ፈገግ አለች። "መርከቧ ላይ ሲሳፈር ነው!" አለችው።

ሮም ውስጥ ከአንድ ሰዓት በኋላ ፍራንሲስኮ ቄሳር ለኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን አንድ ቴሌግራም አቀበለው። ከሐልካዮን ላይ የመጣ ነበር። "እናሳውቃለን!"ይላል። ከዚህ በላይ ምንም ዐይነት ፊርማ ወይም ምልክት አልነበረውም።

"ከሐልካዮንላይ የሚወጡትንም ሆነ የሚገቡትን የስልክ ጥሪዎች በሙሉ እንዲጠለፍ አድርጌአለሁ" አለ ፍራንሲስኮ ቄሳር። "ልክ ቤላሚ መርከቧ ላይ እንደተሳፈረ ወዲያውኑ እንይዘዋለን።"

ምዕራፍ አርባ ሁለት

ካርሎ ቫሊ በጉዳዩ የበለጠ ባሰበበት ቁጥር አንድ ትልቅ ነጥብ እንደሚመታ የበለጠ እርግጠኛ ሆነ። አሜርካዊው ከሚስቱ በመሸሽ ላይ ነው ብላ ፒየር የነገረችው መቼም የለየለት ተረት ነው። ሚስተር ጆንስ በሸሸት ላይ መሆኑ እርግጠኛ ጉዳይ ነው። በመሸሽ ላይ ያለው ከባለቤቱ ሳይሆን ከፖሊሶች ነው። ምናልባት ሰውዬውን ላስያዘ ሰው የተመደበ ሽልማት ሊኖር ይችላል። ምናልባትም ዳንስ ያለ ትልቅ ስጦታ። ይህ ጉዳይ በጣም በጥንቃቄ መያዝ ያለበት ስለሆነ ካርሎ ቫሊ ሁኔታውን ከቀይ ሰይጣንቡድን መሪ ከማሪዮ ሉቺያ ጋር ሊነጋገርበት ፈለገ።

ጠዋት በማለዳ ካርሎ ቫሊ ቬስፓ የተባለችውን ሞተር ብስክሌቱን አስነሳና ከፒያዛ ጋሪባልዲ በስተጀርባ ወደሚገኘው ቪአ ሰርሰሌላ ወደ ተባለ ሥፍራ አመራ። አንድ የመኖሪያ አፓርታማ ሕንፃ ፊት ለፊት ዶቅዶቄውን አቆመና የመኖርያ ሕንፃውን በር ደወል ተጫነ።

ከደቂቃ በኋላ....."የማነው እርጉም!" የሚል ድምፅ ተሰማ።

"ካርሎ ነኝ። ለአንድ ደቂቃ ላናግርህ እሻለሁ ማሪዮ!" አለው።

"በጠዋት መሆኑ ጥሩ ነው። በል እሺ ወደ ላይ ና" አለው።

የበሩ መጥሪያ ድምጽ ሲያሰማ ካርሎ ወደ ላይ መውጣት ጀመረ።

ማሪዮ ሉቻ እርቃኑን የተከፈተው በር ላይ ቆሞ ነበር። እከፍሉ መጨረሻ ካርሎ አልጋ ላይ የተኛች ልጃገረድ ትታየዋለች።

"ቼ ኮዛ? በጠዋት ምን ልታደርግ መጣህ?"

"በጣም ከመጓጓቴ የተነሳ ሙትኛት እንኳ አልቻልኩም። አንድ የደረሰኩበት ትልቅ ጉዳይ አለ ብዬ እገምታለሁ።"

"አሃ! በል ግባ።"

@BOOKALEM

ካርሎ ትንሿ የተዘበራረቀች ኢፓርትመንት ውስጥ ገባ። "ትናንተና ማታ አህቴ አንድ ዒላማ ወደ ቤት ይዛ መጥታለች።"

"ታዲያ ምን ይሁን? ፔየር ሸርሙጣ ናት።"

"አዎን! ግን ይህኛው ሀብታም ከመሆኑም በላይ በመሸሸግ ላይ ነው ያለው።"

"ከማነው የሚሸሸገው?"

"አላወቅሁም። ግን ጉዳዩን እንደማጣራው ነው። አንድ ትልቅ ሽልማት ሳይኖርው አይቀርም ብዬ አስባለሁ።"

"ለምን እህትህን አትጠይቃትም?"

ካርሎ ፊቱን ጭፍግግ አደረገና....."እሷም ሽልማቱን ለብቻዋ ለማስቀረት ነው የፈለጉችው። የገዛላትን የእጅ አምባር ማየት አለብህ። እውነተኛ ሉል ነው።"

"የእጅ አምባሩ ምን ያህል ያወጣል?"

"ዛሬ ጠዋት ልሸጠው ስለሆነ ዋጋውን አሳውቅሃለሁ።"

ሉቻ በሐሳብ ተውጦ ከመቀመጫው ተነሳ። "ካርሎ የምነግርህ ምን መሰለህ?" አለው። "እኔ የምለው የእህትህን ጓደኛ ለምን አናናግረውም? ዛሬ ጠዋት ካለበት ቦታ ወደ ክበባችን እንውሰደው። ከበቡ ፓስካሊ ፖርተሪ ሳኒታ የሚገኝ ድምፅ የለሽ የሆነ ከፍል ያለው የመጋዘን ቤት ነው።"

ካርሎ ፈገግ አለና...."ቤኔ!" አለ። እዚህ ድረስ በቀላሉ አመጣዋለሁ።"

"እኛም እንቀበለዋለን" አለ ሉቻ። "ጥቂት ወሬም እናወራለን። ደግሞም ጥሩ ድምፅ ይኖረዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ምክንያቱም ጥቂት ዘፈን ልናዘፍነው ነውና!"

ካርሎ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲመለስ ጆንስ ለቆ ስለነበር በፍርሃት ተሸበረ። "ጓደኛሽ ወዴት ሄደ?" ሲል ፒየርን ጠየቃት።

"ወደ ከተማ ለአጭር ጊዜ ወጣ እላላሁ ብሎ ነው የሄደው። ለመሆኑ ለምን ጠየከኝ?"

የግዳጅ ፈገግታ እያሳያት....."እንግዳውን ለማወቅ ስለጓጓሁ ነው" አላት።

ካርሎ እህቱና እናቱ ምሳ ለማዘጋጀት ወደ ኩሽና እስኪገቡ ጠበቀና በጥድፍያ ወደ ፒየር መኝታ ቤት ገባ። የእጅ አምባሩን በአንድ የውስጥ ልብስ ማስቀመጫ ውስጥ አገኘው። ጌጡን በፍጥነት ወደ ኪሱ ጨመረና እናቱ ከኩሽና ሲወጡ እሱ መንገዱን በመቀጠል ላይ ነበር።

"ካርሎ ለምሳ አትቆይም እንዴ?"

"የለም እማማ። ቀጠሮ አለብኝ። ወደ ኋላ እመለሳለሁ።" ሞተሩ ላይ ተሳፈረና ወደ ካርቴር እስፓኞሎ ከነፈ። 'ምናልባትም አምባሩ አርቲፊሻል ሊሆን ስለሚችል ሉቻ ፊት ሞኝ መሆን የለብኝም' ሲል አሰበ። ሞተር ብስክሌቱን አሮጌያ የሚል ጽሑፍ ያለበት አነስተኛ የጌጣጌጥ መሸጫ ሱቅ ፊት ለፊት አቆማት። ባለቤቱ ጋምቢኖ ጠና ያለ፤ በትክክል ያልገጠመ ጥቁር የውሸት ፀጉር ያጠለቀና በአፉ ሙሉ

@BOOKALEM

የውሸት ጥርስ የተተከለለት ሰው ነው። ካርሎ ወደ ሱቁ ሲገባ ቀና ብሎ ተመለከተው።

"እንደምን አደርክ ካርሎ! በጠዋት ነው ከቤት የተነሳህው?"

"አዎን።"

"ዛሬ ምንድን ነው ያመጣህልኝ?"

ካርሎ የእጁ አምባሩን ከኪሱ አወጣና ባንኮኒው ላይ አጋደመው።

ጋምቢኖ ብድግ አደረገና እያገላበጠ ሲመረምረው ዐይኖቹ እየተጎለጎሉ ወጡ። "ይህንን ከየት አመጣህው?"

"ሀብታም አክስቴ አውርሳኝ ሞተች። ደህና ዋጋ ያወጣል?"

"ሊያወጣ ይችላል" አለ ጋምቢኖ በጥንቃቄ።

"ከኔ ጋር ድብበቆሽ አትጫወት።"

ጋምቢኖ የተቀየመ መሰለ። "አታልዬህ አውቃለሁ?"

"ሁልጊዜ።"

"እናንተ ልጆች ሁልጊዜ ትቀልዳላችሁ። የማደርገውን ነገር እነግርሃለሁ ካርሎ። ይህ ዕቃ በጣም ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣ ስለሆነ ብቻዬን የምችለው አይመስለኝም።"

የካርሎ ልብ በመጠኑ ዘለለ። "በእርግጥ?" ሲል ጠየቀው።

"አንድ የሆነ ቦታ ላሳየው እሞክራለሁ። ዛሬ ማታ ስልክ ደውዬ አሳውቅሃለሁ።"

"እሺ!" አለና ካርሎ የእጅ አምባሩን ከሸማግሌው እጅ ላይ መንጭቆ ወሰደው። "እስክትደውልልኝ ድረስ ዕቃው ከኔ ጋር ይቆያል!"

ካርሎ በአየር ላይ እየተንሳፈፈ ነበር ከሱቁ የወጣው። 'ትክክል ነኝ!' አለ ለራሱ። 'ሰውዬውም ሀብታም ነው። እናም ደግሞ ወፈፌ ነው። ለምን ብሎ ነው ለአንዲት ሽርሙጣ የዚህ ዐይነት ውድ ዕቃ የሚገዛው?'

ካርሎ ከሱቁ ውስጥ ሲወጣ ጋምቢኖ በፀጥታ ይመለከተው ነበር። 'እነዚህ አህዮች ራሳቸውን ምን ዐይነት ጣጣ ውስጥ ነው የጨመሩት?' ከባንኮኒው ስር ለመላው የጌጣጌጥ ዕቃዎች ማስያዣና መሸጫ ሱቆች የተላለፈውን መመሪያ አነሳው። ካርሎ የያዘውን ትክክለኛ አምባር መግለጫ ነበረበት። ግን በተለመደው የፓሊስ ጣቢያ ስልክ ቁጥር ፈንታ በግርጌው "በአስቸኳይ ለኢጣሊያ የመረጃ ድርጅት (ሲፋር) አሳውቁ!" ይላል። ስለኢጣሊያ የመረጃ ድርጅት እንደሚያውቀው ማንም ሰው የሚያታልላቸው አይደሉም። ከአምባሩ ሊያገኘው የሚችለው ወፈር ያለ ትርፍ ሊያመልጠው ቢሆንም አንገቱን በጣመድ ውስጥ ለማስገባት አልቃጣም። ያለውዲታው መግለጫው ላይ የተፃፈውን ቁጥር በዝግታም ቢሆን መደወል ጀመረ።

@BOOKALEM

ምዕራፍ አርባ ሦስት

የሞት ጥላዎች ያጠሉበት የፍርሃት ወቅት ነበር። ከዓመታት ቀደም ብሎ ሮበርት አንድ ከሃዲ ለማሳደድ ግዳጅ ተሰጥቶት ጥቅጥቅ ወዳሉት የቦርኔዎ ደኖች ገብቶ ነበር። ባህላዊው "የጭንቀት አደን(ሙዚም ተኩት)" የተባለው ወርሃ ጥቅምት ነው። ይህ ወቅት የአገሬው ተወላጆች "ባሊሳላንግ" በተባለ ሽብር ውስጥ የሚኖሩበት ጊዜ ነው። ባሊሳላንግ በተወላጆቹ ዕምነት ሰዎችን ደማቸውን ለመጠጣት ሲል የሚያሳድድ መንፈስ ነው። ወቅቱ የነፍስ ግድያ የሚበረክትበት ጊዜ ሲሆን ለሮበርትም ኔፐልስ በድንገት የቦርኔአ ደን የሆነችበት። ሞት በአየሩ ውስጥ ሰፈኗል። 'እንዴት እዚህ መኖሬን ሊያውቁ ቻሉ? ፒየር! አዎን በፒየር አማካይነት ብቻ ነው ሊያውቁ የቻሉት። ወደ ፒየር ቤት ተመልሼ እሷን ማስጠንቀቅ አለብኝ። መጀመሪያ ግን ከዚህ አካባቢ ማምለጫ መንገድ ማግኘት አለብኝ።' መኪናውን አዞረና የመንገድ መሰናክሉ ወደ ሚጀምርበት የከተማው መውጫ አመራ። 'በሆነ ተዓምር መሰናክሉ በሌለ' እያለ ተመኘ። መግቢያው አጠገብ አምስት መቶ ያርድ ያህል ሲቀረው የፖሊሶቹን መሰናክል አየው። እንደገና መኪናውን አዞረና ወደ ከተማው ማዕከል አመራ። ሮበርት መኪናውን በዝግታ እያሽከረከረ በሐሳቡ እራሱን በሚያሳድዱት ሰዎች ቦታ አስቀምጦ ማሰብ ጀመረ። ከኢጣሊያ የሚያስወጡትን መንገዶች በሙሉ ዘግተዋል። አገሪቱን ለቆ የሚወጣ ማንኛውም መርከብ ይፈተሻል። እዚህ ላይ በድንገት አንድ እቅድ ብልጭ አለለት። 'ከኢጣሊያ የማይወጡ መርከቦች አይፈትሹም። መልካም ዕድል ነው!' አለና በሐሳቡ እንደገና ወደ ወደቡ ተጓዘ።

የሱቁ በር ላይ የተንጠለጠለች አነስተኛ ቃጭል ስታቃጭል ጋምቢኖ ቀና ብሎ ተመለከተ። ሁለት ጥቁር ሙሉ ልብስ የለበሱ ሰወች ወደ ሱቁ እየገቡ ሲሆን ሰዎቹም ደንበኞቹ አልነበሩም።

"ምን ልርዳችሁ?"

"ሚስተር ጋምቢኖ?"

በውሸት ጥርሱ እየሳቀ....."አዎን!" አለ።

"የሉል አምባርን በተመለከተ የስልክ ጥሪ አድርገህልን ነበር።"

'ሲፋር!' አለ በሐሳቡ። ካሁን አሁን ይመጣሉ እያለ ሲጠባበቃቸው ነበር። "አዎን ደውዬ ነበር" አለ ጋምቢኖ። "እንደ ማንኛውም አርበኛ ዜጋ ግዴታዬ መሆኑ ስለተሰማ....."

@BOOKALEM

“አልባሌ ወሬህን አቁም! ማነው አምባሩን ያመጣው?”

“ካርሎ የተባለ ወጣት ልጅ።”

“አምባሩን እዚህ ትቶታል?”

“የለም ይዞት ነው የሄደው።”

“ካርሎ የመጨርሻ ስሙ ማነው?”

“የመጨረሻ ስሙን አላውቀውም። "የቀይ ሰይጣን" አባል ከሆኑት ልጆች አንዱ ነው። የከተማችን አንዱ የወሮ በሎች ቡድን ሲሆን ሉቻ በተባለ ልጅ ነው የሚመራው።”

“ይህ ሉቻ የተባለ ልጅ የት ነው የሚገኘው?”

ጋምቢኖ አመነታ። የጋምቢኖን ምሥጢር ማውጣት ሉቻ ከደረሰበት ምላሱን ቆርጦ እንደሚጥለው ያውቃል። እነዚህ ሰዎች ለማወቅ የፈለጉትን ነገር ካልተናገረ ደግሞ አንጎሉን እንደሚያፈርጡት ያውቃል። በመጨረሻም ጋምቢኖ.....“ከፒያዛ ጋሪባልዲ በስተጀርባ ቪአ ሰርቬላ በተባለ ቦታ ይኖራል” አላቸው።

“እናመሰግናለን ሚስተር ጋምቢኖ! በጣም ነው የረዳህን።”

“ሁልጊዜ ተባባሪ ለመሆን.....” ንግግሩን ሳይጨርስ ጥለውት ሄዱ።

ሁለቱ ሰዎች የመኝታ ቤቱን በር በርግደው ሲገቡ ሉቻ አልጋው ውስጥ ከፍቅረኛው ጋር ተኝቶ ነበር። ከመኝታው ወስጥ ተወርውሮ ወጣ። “ምንድነው እሱ? እናንተ እነማን ናችሁ?”

ከሁለቱ አንዱ የመታወቂያ ካርድ አወጣና አሳየው። “ሲፋር!”አለና ሉቻ ምራቁን ዋጠ። “ሄይ! ምንም ያጠፋሁት ነገር የለም። እኔ ሕግ አክባሪ የሆንኩ ዜጋ.....”

“እናውቃለን ሉቻ! ካንተ ምንም ጉዳይ የለንም። እኛ ካርሎ የተባለ ልጅ ነው የምንፈልገው።”

‘ካርሎ!” ጉዳዩ ይኸው ነው? ያ የተረገመ የእጅ አምባር!’ አለ በሐሳቡ። ‘ካርሎ ራሱን ምን ዐይነት ችግር ውስጥ ነው የጨመረው? መቸም የተሰረቀ የእጅ አምባር ፍለጋ ሲፋር ሰዎቹን እዚህ ድረስ አይልከም።’»

“ደህና ታውቀዋለህ ወይስ.....አታውቀውም?”

“እውቀው ይሆን?”

“እርግጠኛ ካልሆንክ ወደ ጠቅላይ መምሪያ ወስደን የማስታወስ ችሎቻህን እናድስልሃለን።”

“ቆዩ! አሁን አስታወስኩት” አለ ሉቻ። “ካርሎ ቫሊን ነው መሰል የምትፈልጉት። ስለሱ ምን ተገኘ?”

“ልናነጋግረው እንፈልጋለን። የት ነው የሚኖረው?”

እያንዳንዱ የቀይ ሳይጣን አባል ጓደኛውን አስከሞት ድረስ አሳልፎ ላለመስጠት የደም ቃለ መሃላ ገቢቷል። የቀይ ሰይጣን ድርጅትን በጣም ጠንካራ

@BOOKALEM

ከበብ ሊያደርገው የቻለው ይህ እምነት ነበር። አንዱ ካንዱ ጋር የተዋሃዱ ናቸው። "አንዱ ለሁሉም ሁሉም ለአንዱ።"

"ወደ ጠቅላይ መምሪያ መሄድ ትፈልጋለህ?"

ለምን ብሎ? የካርሎን የመኖሪያ አድራሻ ሰጣቸው።

ከሠላሳ ደቂቃዎች በኋላ ፒየር የበሯን ደውል ስምታ ስትከፍት ሁለት እንግዳ ሰዎች ተገትረው አገኘች።

"ሲኞሪና ቫሊ?"

'ችግር!'፣ "አዎን!"

"ወደ ውስጥ እንግባ?"

አይሆንም ማለት ብትፈልግም አልቻለችም። "እናንተ እነማን ናችሁ?"

አንደኛው የመታወቂያ ካርዱን አወጣ። 'ሲፋር!'፣ ስምምነት ያደረገችው ከእነዚህ ሰዎች ጋር አልነበረም። ፒየር 'ከማገኘው ሽልማት አጭበርብረው ያደናቅፋኛል' ስትል ስጋት ያዛት።

"ከኔ የምትፈልጉት ምንድንው?"

"ጥቂት ጥያቄዎች ልንጠይቅሽ እንደወዳለን።"

'እግዚያብሔር ይመስገን! ሮበርት ከቤት በመውጣቱ አሁንም መደራደር እችላለሁ' አለች ቤሐሳቧ።

"ትናንት ከሮም በመኪና ነው የመጣሽው አይደለም?"

"አዎን። ይህ ታዲያ ሕግ መጣስ ነው? ከተፈቀደው ፍጥነት በላይ ነው የነዳሁት?"

ሰውዬው ፈገግ አለ። የፊቱን ገጽታ ግን አለወጠውም። "አብሮሽ የተጓዘ ሰው ነበር?" አላት።

"አዎን!" አለች ፒየር በጥንቃቄ።

"ማነው እሱ ሲኞሪና?"

ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች። "መንገድ ላይ ያገኘሁት ሰው ነው። ከኔ ጋር ወደ ኔፕልስ ለመምጣት ፈልጎ ነው።"

"አሁን እዚህ ካንቺ ጋር አለ?" ሲል ሁለተኛው ሰው ጠየቃት።

"የት እንዳለ አላውቅም። ከተማ እንደገባን ወዲያውኑ አወረድኩት። ሰውየም የት እንደገባ ጠፋ።"

"የመንገደኛሽ ስም ሮበርት ቤላሚ ነበር?"

"ቤላሜ?" አለችና የምታሰብ ለመምሰል ግንባሯን አኮማተረችው። "አላውቅም! ስሙን የነገረኝ አይመስለኝም።"

"አህ! የነገረሽ ይመስለናል። ከቶር ዲአንቶን አግኝቶ ወሰደሽና ለሊቱን በኤል ኢንከሮቺአ ሆቴል አሳለፍሽ። እናም በማግስቱ ጠዋት አንድ የሉል አማባር ገዛልሽ።

@BOOKALEM

ከዚያም አንዳንድ ሆቴሎች የአውሮፕላንና የባቡር ቲኬት አስይዞ ላከሽ። ከዚያም መኪና በስምሽ ተከራየልሽና ወደ ኔፐልስ ይዘሽው መጣሽ። ትክክል?" አላት።

'ሁሉንም ነገር ያውቃሉ።' ፒየር በአዎንታ ራሷን አወዛወዘች። ዐይኖቿ በፍርሃት ተሞሉ።

"ጓደኛሽ ተመልሶ ይመጣል? ወይስ ኔፐልስን ለቋል?"

ትክክለኛው መልስ የቱ እንደሆነ ለመወሰን አመነታች። ሮበርት ከተማውን ለቆ ወጥቷል ብላ ብትነግራቸውም በምንም ዐይነት አያምኗትም። እዚሁ እቤት ውስጥ ይጠብቁትና ሲመለስ እሱን ይዘው እሷንም በመዋሸትና የሮበርት ግብረ አበር በመሆን ይይዟታል። ስለዚህ እውነቱን መናገር የተሻለ ይጠቅማል ስትል ወሰች።

"ወደ ቤቴ ይመለሳል" አለችው፡

"በቶሎ?"

"እርግጠኛ አይደለሁም።"

"በጣም ጥሩ! እዚሁ እራሳችንን እናመቻቻለን (እንቆያለን።) ዙሪያውን ብንቃኝስ ቅር ይልሻል?" ሽጉጦቻቸውን ለማሳየት ኮቶቻቸውን ከፈቱ።

"እ.....አይለኝም።" ቤቱ ውስጥ መዘዋወር ሲጀምሩ እማማ ከኩሽና ወጡና....."እነዚህ እነማን ናቸው?" አሉ።

"የሚስተር ጆንስ ጓደኞች ናቸው እማማ። እሱን ለማየት ነው የመጡት።"

እማማ ፊታቸው በደስታ ፈካ። "የዚህ ዐይነት ግሩም ሰው!" አሉና....." ጥቂት ምሳ ትፈልጊያለሽ?" አሏት።

የፒየር አዕምሮ እየተተራመሰ ነበር። 'ለኢንተርፖል እንደገና መደወል አለብኝ።' ሃምሳ ሺህ ዶላር እንከፍላለን ብለው ተስማምተዋል። እስከዚያ ድረስ ግን አሳልፋ እስክትሰጠውና ገንዘቡን ገቢ እስክታደርግ ድረስ ሮበርት ከቤቷ እንዲርቅ ማድረግ አለባት። 'ግን እንዴት?' በድንገት ጠዋት ያደረጉት ጭውውት ትዝ አላት። 'ችግር ካለ ግን አንዱን ጥላ ወደ ታች ትሰቢዋለሽ።'ሁለቱ ሰዎች ሳህን ሙሉ ካፔሊኒ እየተመገቡ ተቀምጠዋል።

"እዚህ ከፍል ውስጥ ብርሃን በጣም በዛ!" አለች ፒየር ከመቀመጫዋ ተነስታ በቀጥታ ወደ መስኮቱ ተራመዳ እንደኛውን መጋረጃ ወደ ታች ሰባ ጋረደችው። ከዚያም ወደ ገበታ ጠረጴዛው ተመለሰች። 'ሮበርት የማስጠንቀቂያ ምልክቱን እንዳየው ያስታውሳል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።'

ሮበርት የማምለጫ እቅዱን እንደገና እያሰላሰለ ወደ ቤት በመንዳት ላይ ነበር።

የተዋጣለት እቅድ አይደለም። ቢሆንም ግን የተወሰነ ጊዜ ለማግኘትና ዱካውን ሊያጠፋባቸው ጊዜ ሰጥቶታል። ወደ ፒየር ቤት እንደደረሰ መኪናውን በጣም ቀ...ስስሰ እያደረገ በመንዳት ዙሪያውን ይለመከት ጀመር። ሁሉም ነገር የተለመደው እርጋታ ይታይበታል። ፒየር እንድትወጣ ካስጠነቀቀ በኋላ ተመልሶ

@BOOKALEM

ይጠፋል። ሮበርት መኪናውን ቤቱ ፊት ለፊት ሊያቆም ሲል አንድ ያልተለመደ ነገር ተመለከተ። የፊት ለፊት መጋረጃ በሙሉ ወደ ላይ ሲሰበሰብ አንደኛው ብቻ ወደ ታች ተስቧል። አጋጣሚ ሊሆን ይችላል። ግን ቢሆንም የማስጠንቀቂያ ደወል ጭንቅላቱ ውስጥ አቃጨለበት። 'ፒየር ትንሿን ቀልድ በቁም ነገር ወስዳት ይሆን?' የፈለገውን ያህል የራቀ ቢሆንም በዕድሉ ለመቆመር አልፈለገም።

መኪናውን አዞረና ከፒየር ቤት አንድ ማይል ርቀት የሚገኝ ቡና ቤት በር ላይ አቁሞ ስልክ ለመደወል ወደ ውስጥ ገባ።

ስልኩ ሲያቃጭል ሁሉም በመመገቢያ ጠረጴዛው ዙሪያ ተቀምጠው ነበር። ከሰዎቹ አንዱ ከመቀመጫው መነሳት ጀመረ። "ቤላሚ ሊደውል ይችላል?"

ፒየር በማንጓጠጥ አመለካከት አየችውና....."በእርግጥ አይደውልም። ለምን ብሎ?" ከወንበሯ ተነሳችና የስልኩን መነጋገሪያ ብድግ አድርጋ....."ሄሎ?" አለች።

"ፒየር የመስኩቱን መጋረጃ አየሁና....."

ማድረግ የሚገባት "ሁሉም ነገር ትክክል ነው" ብላ መናገር ብቻ ነው። ከዚያም ሮበርት ወደ ቤት ሲመለስ ፖሊሶቹ ከያዙት በኋላ የሽልማት ገንዘቧ እንዲሰጣት መጠየቅ ነው። 'ግን በእርግጥ ይይዙታል?' ድምፅ ተሰማት። 'ፖሊሶች ካገኙኝ እንዲገሉኝ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸዋል!'»

በጠረጴዛው ዙሪያ የተቀመጡት ሰዎች እየተመለከቷት ነው። በሃምሳ ሺህ ዶላር ልታደርግ የምትችለው ብዙ ነገር አለ። በጣም ውብ የሆኑ ቀሚሶች ይገዛሉ። ሽርሽሮች ይደረጋሉ። ውብ የሆነ መኖሪያ አፓርትመንቶች ሮም ውስጥ። ሮበርት ይሞታል። በሌላ ጎን ደግሞ የተረገሙትን ፖሊሶች በጣም ትጠላቸዋለች።

ፒየር በስልኩ ውስጥ....."የተሳሳተ ቁጥር ነው የደወሉት!" አለች።

ሮበርት መኪናውን አዞረና ከፒየር ቤት ርቆ ወደ መርከቦቹ ሥፍራ አመራ። መጣም ትልልቅ ለሆኑት የጭነት መርከቦችና የሕዝብ ማመላለሻዎቹ አገልግሎት ወደሚሰጠው ዋናው ወደብ ከመሄድ ይልቅ ሳንታ ሉቺያን አልፎ "ካን ሪአና ኢስቺያ" የሚል ምልክት ወደተለጠፈበት አነስተኛ ወደብ ነዳና መኪናውን በቀላሉ ልትታይ የምትችልበት ቦታ ላይ አቁሞ ቲኬት ወደሚሸጠው ሰው አመራ።

"የሚቀጥለው ጀልባ ወደ ኢስቺያ የሚለቀው መቼ ነው?"

"በሠላሳ ደቂቃ ውስጥ።"

"ወደ ካፕሪስ?"

"በአምስት ደቂቃዎች ውስጥ።"

"ወደ ካፕሪ የአንድ ጉዞ ቲኬት ስጠኝ።"

"ሲ ሲኞር!"

"ምንድነው ይህ ሲ ሲኞር! የሚሉት አልባሌ? እናንተ ሰዎች ለምንድነው እንግሊዘኛ የማትናገሩት?"

የሰውዬው ዐይኖች በድንጋጤ ተጎለጎሉ።

@BOOKALEM

"እናንተ እግዜየር የረገማችሁ አሳማዎች! ሁላችሁም አንድ ዐይነቶች ናችሁ። ስቲዩፒዶች! ወይም እናንተ ሰዎች እንደምትሉት ስቱፒድ!" አለ ሮበርት። የሰውዬው እጅ ላይ ገንዘቡን ወሸቀለትና ትኬቱን ተቀብሎ ቤት ወደምትመስለው አነስተኛ መርከብ አመራ።

ከሦስት ደቂቃዎች በኋላ ካፐሪ ወደተባለች የወደብ ከተማ ጉዞውን ቀጠለ። መርከቧ በካናሉ ውስጥ በጥንቃቄ በማለፍ ዝግ ብላ ጉዞዋን ጀመረች። የካናሉን መጨረሻ እንደወጣች ሞተሯ አጉረመረመና እንደባሕር ዶልፊን በግርማ ሞገስ ባሕሩን በፍጥነት እየሰነጠቀች ትቀዝፍ ጀመር። ጀልባዋ ደስታ በተሞላበት ስሜት በተለያየ ልሳን በሚንጫጩ አገር ጎብኝዎች ታጭቃለች። ሮበርትን ማንም ዘወር ብሎ የተመለከተው የለም። መጠጥ ወደሚሸጥበት አነስተኛ ባንኮኒ አመረና የቡና ቤቱን አስተናጋጅ....."ፕሮስካ ቶኒክ ስጠኝ!" ብሎ አዘዘው።

"እሺ ጌታዬ!"

መጠጥ ቀጂው አልኮሉን አቀላቅሎ አመጣና....."ይኸውሎት ሲኞሬ!" ብሎ አስቀመጠለት።

ሮበርት መለኪያውን አንስቶ ከመጠጡ ተንነጨለትና ብርጭቆውን ባንኮኒው ላይ በኃይል መትቶ አስቀመጠው። "ስለ ክርስቶስ! አሁን ይህን መጠጥ ብላችሁ ትጠሩታላችሁ? ጣዕሙ ልክ የፈረሰ ፍግ ነው የሚለው። እናንተ እግዜር የረገማችሁ ጣሊያኖች! ምን ነካችሁ?"

በዙሪያው ያሉ ሰዎች እየዘሩ ተመለከቱት።

"አዝናለሁ ሲኞር!" አለ አስተናጋጁ። የመጨረሻውን ምርጥ....."

"አጉል ልፍለፋህን አቁም!"

አንድ እንግሊዛዊ ወደ ሮበርት ጠጋ አለና....."ዙሪያውን ሴት ወይዘሪት አሉ። ለምን የምትናገረውን ቃል አትመርጥም!" አለው።

"የምናገረውን ነገር መምረጥ የለብኝም!" ሲል ሮበርት ጮኸ። "እኔ ማን እንደሆንኩ ተውቃለህ? እኔ ኮማንደር ሮበት ቤላሚ ነኝ። እና ደግሞ ይህን ጀልባ ብለው ይጠሩታል? ይሄ ግን አንድ የታንኳ ቁራጭ ነው።"

የመጠጡን ሠፈር ለቀቀና ከእንጨት የተሠራ ወንበር ላይ ሄዶ ተቀመጠ። የመንገደኞች ዐይን በሙሉ በትኩረት እንደሚያየው ይሰማዋል። ልቡ በፍጥነት ድ...ው!...ድ...ው!... እያለ ይመታል። የሆነው ሆኖ የቃላት ጨዋታው ገና አላለቀም።

በቤት ቅርጽ የተሠራችው ከብ የሞተር ጀልባ ካፐሪ ደርሳ ስትቆም ሮበርት በተወጠረ ካቦ ላይ መንገደኞችን ወደሚያጓጉዘው የአየር ላይ መኪና ጣቢያ የመግቢያ ቲኬት መሸጫ ሱቅ አመራ። አንድ ጠና ያለ ሰው ቲኬት በመሸጥ ላይ ነበር።

@BOOKALEM

"አንድ ቲኬት!" ሉለና ጮኸ። "ደሞ ፍጠን! ሙሉ ቀን የለኝም። ቢሆንም ደግሞ አንተ ቲኬት ለመሸጥ በጣም አርጅተሃል! እቤት መዋል ነው የሚገባህ። ይሄን ጊዜ ሚስትህ ከመላው ጎረቤቶችህ ጋር እያመነዘረች ነው።"

ሽማግሌው በቁጣ መነሳት ጀመረ። አላፊ አግዳሚው ሮበርትን በቁጣ እየተመለከተው ነው። ሮበርት ቲኬቱን ተመለከተና መኪናው ውስጥ ገባ።

'እምን! ሰው ሁሉ በሚገባ ያስታውሰኛል!' አለ። ማንም ሰው ሊስተው የማይችል ፈለግ እየተወ ነው። በአየር ላይ በተወጠረ ካቦ የሚጓዘው መንኮራኩር እንደቆመ ሮበርት በተጣበበው ሕዝብ መኻል እየተጋፋ ወጣና በቪያ ቪቶሪ ኢማኑኤል ጎዳና አድርጎ ወደ ኩዊዛና ሆቴል ሄደ።

"የመኝታ ክፍል እፈልጋለሁ" አለው ከዴስኩ ጓላ ያለውን ጸሓፊ።

"በጣም አዝናለሁ! ያሉን ክፍሎች በሙሉ ተይዘዋል። ሌላ....."

ሮበርት ስልሳ ሺህ ሊሬ ለጸሓፊው አሸገውና....."ማንኛውም ክፍል ይሆናል" አለው።

"ደህና! እንደዚህ ከሆነ ልናስተናግድዎ እንችላለን። ሲኞር እባክዎን ቢመዘገቡ!" አለ ጸሓፊው።

ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ብሎ ፈረመ።

"ከኛ ጋር ለምን ያህል ጊዜ ይቆያሉ ኮማንደር?"

"አንድ ሳምንት።"

"በጣም ግሩም ነው! ፓስፖርትዎን ይስጡኛል?"

"ሻንጣዬ ውስጥ ነው። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ይደርሳል።"

"ተላላኪ ክፍልዎን እንዲያሳይዎት አደርጋለሁ።"

"አሁን አይደለም። ለጥቂት ደቂቃዎች ወደ ውጭ ወጣ ብዬ ቶሎ እመለሳለሁ።"

ሮበርት ከእንግዳ ማረፊያው ክፍል ወደ ጎዳና ሲወጣ ትዝታ እንደፈጣን ነፋስ መታው። በዚህ ሥፍራ በነዚህ መንገዶች ላይ ከሱዛን ጋር ተንሸራሽሯል። ግሮታ አዙራን ጎብኝተው ፒአዛ ኡምቤርቶ ቡና ጠጥተዋል። በማሪና ርኮላ እንደሉል አረንጓዴ በሆነው ውሃ ውስጥ ዋኝተዋል። ቪያ ቪቶሪዎ አማኑኤል ጎዳና ሱቆች ውስጥ ገብይተው ወደ ሞንቴ ሰላሮ አሻቅበዋል። በባርባሮሳ ሬስቶራንት ቡና ጠጥተው እናካፕሪ በሚገኘው ቤተመቅደስ ውስጥ በመግባት አምላካቸውን ስለባረካቸው አመስግነዋል። ሮበርት ምትሃቷ ካፕሪ ናት ብሎ አስቦ ነበር። ምትሃቷ ሱዛን ነበረች። ምትሃተኛዋ ደግሞ አሁን መድረኩን ለቃለች።

ሮበርት እንደገና ወደ ፒአዛ ኡምቤርቶ ተመልሶ የኤሌክትሪኩን መኪና ተሳፈረ። ከመንገደኞቹ ጋር ድምጹን አጥፍቶ በፀጥታ ነበር የመልስ ጉዞውን የተያያዘው። የመድረሻ ነጥቡ ላይ ሲደርስ ከመኪናው ወጣና ቲኬት ሻጩ እንዳያየው በከፍተኛ ጥንቃቄ ከጣቢያው ወጣ። ከዚያም ጀልባዎች ወደሚቆሙበት ሌላ ዳርቻ

@BOOKALEM

ሄዶ በሲፓኝ ያነጋገር ዘይቤ ድምጹን ቀይሮ.....“ወደ ኢችያ የሚሄደው ጀልባ መቼ ይነሳል?” ሲል ጠየቀ።

“በሠላሳ ደቂቃዎች ውስጥ።”

“አመሰግናለሁ!” አለና ሮበርት አንድ ቲኬት ገዛ። ከዚያም የባሕር ዳርቻ ላይ የሚገኝ ቡና ቤት ውስጥ ገብቶ ወደ ጥጉ አንድ ወንበር ላይ ተቀመጠና ዊስኪውን መጎንጨት ጀመረ። በአሁኑ ሰዓት ያለምንም ጥርጥር መኪናዋን አግኝተው የአደን ቀጠናቸውን እያጠበቡ ነው። የአውሮፓን ካርታ በአዕምሮው ውስጥ ዘርግቶ ማየት ጀመረ። የሚመስለው ርምጃ ወደ አገረ እንግሊዝ መግባትና ከዚያም አሜሪካ የመግቢያ መንገድ መፈለግ ነው። ወደ ፊረንሳይ የመመለሱ ጉዳይ ስሜት የማይሰጥ ነው። ‘አሁን’ አለ ሮበርት።.....‘ፈረንሳይ በጣም የተጣበበ መሆን አለበት። ስለዚህ ኢጣሊያን ለመልቀቅ ሲቪታቬቼያ። አዎን ሲቪታቬቼያ መድረስ አለብኝ። ሐልካዮን ጀልባ።’

ከቡና ቤቱ ባለቤት ዝርዝር ፍራንክ ወሰደና ስልክ ደወለ። የባሕር አጥሬተሩ ጥሪውን እስኪያስተላልፍለት ድረስ አሥር ደቂቃዎች ወሰደበት። በመጨረሻም ሱዛን በስልኩ መስመር ተደመጠችለት።

“ካንተ ለመስማት ስንጠባበቅ ነበር። ጎህ ሲቀድ ኔፐልስ መድረስ እንችላለን። ከየት ነው የምናሳፍርህ?”

“የሐልካዮን መርከብ ወደዚህ መምጣት በጣም አደገኛ ነው” አለ ሮበርት። “ፖሊንድሮሙን” ታስታውሻለሽ? ለጫጉላ ሽርሽራችን ወደዚያ ሄደን ነበር።”

“ማንን?”

“በጣም ደክሞኝ ስለነበር ስለሱ ቦታ የሆነ ቀልድ ተናግሬ ነበር።”

መሥመሩ ላይ ለተወሰነ ጊዜ ፀጥታ ከሰፈነ በኋላ ሱዛን ለስለስ ባለ ድምፅ.....“አዎን አስታውሳለሁ!” አለች።

“ሐልካዮን ነገ እዚያ ልትጠብቀኝ ትችላለች?”

“አንድ ጊዜ ጠብቀኝ!” አለች ሱዛን።

ሱዛን ወደ ስልኩ ተመለሰች። “አዎን! እዚያ እንመጣለን።”

“ጥሩ! ብዙ ዕርዳታ ነው የጠየኩሽ። አኔን መርዳትሽን ከደረሱበት በጣም ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ነው የምትገቢው።”

“አትጨነቅ እዚያው እንገኛለን። ተጠንቀቅ!”

“አመሰግናለሁ።” ስልኩ ተዘጋ።

ሱዛን ወደ ሞንቴ ባንከስ ዘወር አለችና.....“ይመጣል!” አለችው።

ሮም በሚገኘው የሲፋር” ጠቅላይ መምሪያ ውስጥ የሮበርት ንግግር እየተደመጠ ነበር። በክፍሉ ውስጥ አራት ሰዎች ነበሩ። “እንደገና ለማዳመጥ ከፈለጉ ንግግሩን ቀድተነዋል ጌታዬ!” አለ የራዲዮ አጥሬተሩ።

@BOOKALEM

ኮሎኔል ቄሰር ፍራንክ ጆንሰንን በጥያቄ ተመለከተው። "እዎን ስለቀጠሮው ቦታ ለመስማት እፈልጋለሁ ። ፓሊንድሮም ያለ መሰለኝ። ኢጣሊያ ውስጥ የሚገኝ ሥፍራ ነው?"

ኮሎሌል ቄሳር ራሱን በአሉታ ነቀነቀ። "በፍጹም እንደዚህ የሚባል ቦታ አልሰማሁም።" ወደ ረዳቱ ዞረና....."ካርታው ላይ ፈልገው። እንደዚሁም ከሐልካዮን ጋር የሚደረገውን ግንኙነትም ጥለፍ!" አለው።

"እሺ ጌታዬ!"

ኔፐልስ በሚገኘው የእርሻ ቤት ውስጥ ስልኩ ሲያቃጭል ፒየር ለመመለስ ተነሳች።

"ቆይ!" አለና እንደኛው ወደ ስልኩ ሄዶ እንስቶ....."ሃሎ!" አለ። ለጥቂት ጊዜ ሲያዳምጥ ቆየና ስልኩን ጥሎ ወደ ጓደኛው በመዞር....."ቤላሚ በጀልባ ወደ ካፕሪ አምርቷል!" አለው።

ፒየር ሁለቱ ሰዎች እየተጣደፉ በበሩ ሲወጡ ተመለከተቻቸው። በሐሳቧም.....'እግዚአብሄር ይህን ያህል ገንዘብ እንዳገኝ አልፈቀደም። ለማንኛውውም ሮበርት እንዲያመልጥ ተስፋ አደርጋለሁ!' አለች።

ጀልባዋ ኢስቺያ ደርሳ እንደቆመች ሮበርት በተቻለው መጠን መልኩ እንዳይታይ ከመንገደኞቹ ጋር እየተጋፋ ከወረደ በኋላ ወደቡ ዳር ወዳለች አንዲት ኪዎስክ አመራ። ወደ ስሪንቶ የምትሄደው መርከብ በአሥር ደቂቃ ውስጥ እንደምትነሳ የሚያስታወቅ ምልክት ተለጥፏል።

"የደርሶ መልስ ቲኬት ወደ ስሪንቶ!" አለ ሮበርት።

ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ወደ ዋናው ባሕር ጉብ ምድር ወደ ስሪንቶ መንገድ ጀመረ። 'አሁን ከትንሽ ዕድል ጋር አሰሳው ወደ ካፕሪ ይዞራል' አለ። 'ከትንሽ ዕድል ጋር።'

ስሪንቶ የሚገኘው የምግብ ገበያ እጅግ ተጣቧል። ገበሬዎች ከገጠሩ ከፍል ትኩስ አትክልትና የጥጃ ሥጋ ይዘው በመምጣት የመንገዱን ገበያ ሞልተውታል። መንገዱ በሸቀጥ ላኪዎችና በሸማቶች ተጣቧል።

ሮበርት አንድ ቆሻሻ ሸርጥ ለብሶ የጭነት መኪና ላይ ሸቀጥ የሚጭን ጠብደል ሰው ተጠጋ። "ይቅርታ ሞንሹር!" አለ በትከከለኛ የፊረንሳይ አነጋገር ዘይቤ። "ወደ ሲቪታቬቺያ የሚሄድ መኪና እፈልግ ነበር። ወደዚያ ይሆን የሚሄዱት?"

"አይደለም" አለና ሰውየው ሌላ ካሚዎን እያመለከተው....."ወደ ሳሌርኖ ነው የምሄደው። ምናልባት ጁሴፔ ሊረዳህ ይችላል" አለው።

"አመሰግናለሁ" አለና ሮበርት ወደ ሁለተኛው ሰው ሄደ። "ሞንሹር! በኢጋጣሚ ወደ ሲቪታቬቺያ ትሄድ ይሆን?"

@BOOKALEM

"እሄድ ይሆን?" አለ ወዲው።

"ብታሳፍረኝ በደስታ እከፍልሃለሁ።

"ምን ያህል?"

ሮበርት አንድ መቶ ሺህ ሊሬ አቀበለው።

"በዚህን ያህል ገንዘብ ወደ ሮም የሚወስድ የአዎሮፕላን ቲኬት መግዛት ችላለህ!" አለ ሰውየው ተደንቆ።

ሮበርት ወዲያው ስህተቱን ተገነዘበና ዙሪያውን በጭንቀት ተመለከተ። "እውነቱን ለመናገር አንዳንድ አበዳሪዎቼ አየር ማረፊያ የሚጠብቁኝ መሆኑ ነው። ለዚህ ነው በጭነት መኪና መሄዱን የመረጥኩት።"

ሰውየው ተስማማ። "አዎ ገባኝ!" በጣም ጥሩ! ግባ። ለመነሳት ዝግጁ ነን።

ሮበርት አፋሸከ። "በጣም ነው የደከመኝ። ከጀርባ በኩል ብተኛ ቅር ይልሃል?"

"ጉዞው መቼም በጣም የሚንጥ ነው የሚሆነው። በል እንደተመቸህ አድርግ" አለው።

"ሜርሲ!"

የካሚዎኑ ዕቃ መጫኛ ጋሪ በባዶ ካርቶኖችና ዕቃ መያዣዎች ተሞልቷል። ሮበርት ተሳቢው ውስጥ ከገባ በኋላ ጆሴፔ መዝጊያውን ሲዘጋው ከባዶዎቹ ሳጥኖች ጎላ ተደበቀ። ምን ያህል ደክሞት እንደነበር የተገነዘበው አሁን ነው። መሲደዱ ጨርሶ ሊጥለው ደርሷል። ከተኛ ምን ያህል ጊዜ ሆነው? ፒየር ሌቭት ወደመኝታው መጥታ እንዴት ጤናማ ወንድ መሆኑን እንዲገነዘብ እንዳደረገችው ትዝ አለው፡ና 'ደህና በሆነች!' ሲል ተመኘ። ከዚያም ጭልጥ ያለ እንቅለፍ ወሰደው።

በካሚዎኑ ጋቢና ውስጥ ጆሴፔ ስላሳፈረው መንገድኛ እያሰላሰለ ነበር። ባለሥልጣናት ስለሚፈልጉት አንድ አሜሪካዊ ወሬው ተሰራጭቷል። 'ግን ሰውየው የፈረንሳዩች የአነጋገር ለዛ አለው። አለባበሱ ደግሞ እንደአሜሪካኖች ነው። አሜሪካዊ ይመስላል። ጥሩ የገንዘብ ሽልማት ሊኖር ስለሚችል ማጣራቱ አይከፋም።'

ከአንድ ሰዓት ጉዞ በኋላ ጆሴፔ ጎዳናው ዳርቻ የሚገኝ ነዳጅ ማደያ ላይ አቁሞ "ነዳጅ ሙላልኝ!" ሲል አዘዘና ወደ መጫኛው ጫፍ ሄዶ አጮልቆ ተመለከተ። መንገደኛው ለሽ ብሎ ተኝቷል።

ጆሴፔ ወደ ምግብ ቤቱ ገባና ለቀጣናው ፖሊስ ጣቢያ ስልክ ደወለ።

@BOOKALEM

ምዕራፍ አርባ አራት

የስልክ ጥሪው ለኮሎኔል ቄሳር ተላለፈለት። "እዎን" አለው ጁሴፔን። "የኛን ሰው ይመስላል። በጥንቃቄ አዳምጠኝ። በጣም አደገኛ የሆነ ሰው ነው። ስለዚህ ልክ እንደነገርኩህ ማድርግ አለብህ። ገባህ?"

"አዎን ጌታዬ።"

"አሁን የት ነው ያለህው?"

"ወደ ሴቪታቬቺያ በሚወስደው ጎዳና የካሚዎን ነዳጅ ማደያ ላይ።"

"እሱ አሁን የካሚዎንህ መጫኛ ላይ ነው ያለው?"

"አዎን!" አለ ጁሴፔ። ቃለ ምልልሱ አስጨነቀው። 'ምናልባት አርፌ ሥራዬን ብሠራ ይሻል ነበር።'

"ሰውየው እንዲጠራጠር የሚያደርገው ምንም ነገር አታድርግ። ወደ ካሚዎንህ ተመለስና ወደ ሲቪታቬቺያ መንዳትህን ቀጥል። የካሚዎንህን የሰሌዳ ቁጥርና የመኪናውን ቀለም ንገረኝ።"

ጁሴፔ ነገረው።

"መልካም! አስፈላጊውን ርምጃ እንወስዳለን። አሁን ተንቀሳቀስ!" ኮሎኔል ቄሳር ወደ ኮሎኔል ጆንስን ዞረና ራሱን ነቀነቀ። "አገኘንው! የመንገድ መሰናክል እንዲደረግ አዛለሁ። በሠላሳ ደቂቃዎች ውስጥ እቦታው ላይ በሄሎኮፕተር መድረስ እንችላለን።"

"እንሂድ።"

ጁሴፔ ስልኩን ከዘጋ በኋላ ላቡን እየጠራረገ ወደ ጭነት መኪናው ተመለሰ። 'መቼም ተኩስ እንደማይከፈት ተስፋ አደርጋለሁ። ማሪያ ትገለኛለች። በሌላ በኩል ደግሞ ሽልማቱ ብዙ ከሆነ.....'ጋቢና ገባና በቀጥታ ወደ ሲቢታቬቺያ ማሽከርከር ጀመረ።

ከሠላሳ አምስት ደቂቃዎች በኋላ ጁሴፔ ከአናቱ በላይ የሄሊኮፕተር ድምጽ ተሰማውና ቀና ብሎ ተመለከተ። የፖሊስ አርማ ነበረበት። ከፊት ለፊቱ ደግሞ ራቅ ብሎ ሁለት የፖሊስ መኪኖች መንገዱን ዘግተው ቆመዋል። ሄሊኮፕተሩ ከመንገድ ጠርዝ ላይ ሲያርፍ ኮሎኔል ፍራንክ ጆንስን እና ኮሎኔል ቄሳር ከሄሊኮፕተሩ ወረዱ።

@BOOKALEM

ጁሴፕ ወደ መሰናክሉ ሲቃረብ የመኪናውን ፍጥነት ቀንሶ የሞተሩን ቁልፍ አጥፍቶ ዘሎ ወረደና ወደ መኮንኖቹ በሩጫ እየበረረ ሄዶ.....“ከኋላ በኩል ነው ያለው!” ሲል ጮኸ።

የጭነት መኪናው በዝግታ ተሸከርክሮ ቆመ። የዚያን ጊዜ ሎሎኔል ቄሳር.....“ከበቡት! ብሎ ጮኸ።”

ፖሊሶቹ መሣሪያዎቻቸውን በጥንቃቄ ደግነው ከበቡት።

“አትተኩሱ! እኔ እይዘዋለሁ!” አለና ኮሎኔል ፍራንክ ጮኸ። ጆንሰን ወደ ካሚዩኑ ተጠጋና.....“ና ውጣ ሮበርት! ተፈጽሟል!” ሲል ተጣራ።

መልስ አልነበረም።

”ሮበርት አምስት ሴኮንዶች ብቻ ነው ያለህ!”

ፀጥታ ብቻ። አሁንም ጠበቀ።

ቄሳር ወደ ፖሊሶቹ ዘወር አለና ምልክት ሰጣቸው።

“የለም!” አለና ኮሎኔል ጆንሰን ጮኸ። ቢሆንም ዘግይቶ ነበር።

ፖሊሶቹ ከካሚዎኑ የኋላ መጫኛ ውስጥ ጥይታቸውን ያራግፉት ጀመር። የአውቶማቲክ መሣሪያው ጩኸት ጆሮ ያደነቁራል። የሳጥንና የካርቶን ቁርጥራጮች በአየር ላይ ይንሳፈፍ ጀመር። ከአሥር ሴኮንድ በኋላ ተኩሱ ፀጥ አረጭ እንዳለ ኮሎኔል ጆንሰን ጋሪው ላይ ዘሎ ወጣና ከመንገዱ ላይ ካርቶኖችንና ሳጥኖችን በእግሩ እየመተረ ወደ ፊት ሄደ። በመጨረሻም ወደ ኮሎኔል ቄሳር ዘወር አለና.....“የለም!” አለው።

አሥራ ዘጠነኛ ቀን

ሴቪታቬቺያ ኢጣሊያ

ሲቪታቬቼያ በ537 ዓ.ም በማይክል አንጀሎ ተጠናቆ የተሠራ ግዙፍ ሕንጻ ዘብ የቆመባት የኢጣሊያ ጥንታዊ የባሕር ወደብ ናት። ወደቡ ወደ ኢጣሊያንና ሳርዲኒያ የሚመላለሰውን ትራፊክ የሚያስተናግድ በአውሮፓ ውስጥ በጣም እንቅስቃሴ የበዛበት ወደብ ነው። ገና ማለዳ ቢሆንም ወደቡ ግን በሥራ ብዙት ይጣደፋል። ሮበርት የባቡር ሃዲዱን አቋረጠና አፍንጫ የሚሰብ የምግብ ሽታ ወዳለበት አነስተኛና ሬስቶራንት ውስጥ ገብቶ ቁርስ አዘዘ።

ጀልባዋ ሐልካየን በቀጠሮው ቦታ ኤልባ ትመጣለች። ሱዛን ስላስታወሰችው በጣም ነው ያመሰገናት። በጫጉላ ሽርሽራቸው ወቅት እዚያች ከተማ የሆቴል ክፍላቸው ውስጥ ለሦስት ቀናት ፍቅር እየሠሩ ቆይተዋል። ‹ወደ ውሃ ዋና መሄድ ትፈልጋለህ የኔ ፍቅር?› አለችው ሱዛን። ሮበርት ራሱን እየነቀነቀ.....‘የለም መንቀሳቀስ አልችልም’ አላት። ቀጠለናም በእንግሊዘኛው ቋንቋ.....‘እይ ወዝ ኤብል (able–elba)’ የሚል ቃል ወደ ግራ ሲነገር አይ ወዝ ኤልባ የሚል ድምጽ ስለሰጠ ሱዛን ከልቧ

@BOOKALEM

ሳቀች። እናም አሁን ከቀኝ ወደ ግራ የማንበቡን የቃላት ጨዋታ «"ፖሊንድረም"» አስታወሰችለት።

አሁን ማድረግ ያለበት ወደ ኤልባ የሚወስደው ጀልባ መፈለግ ብቻ ነው። ወደ ወደቡ በሚመስደው መንገድ ላይ ይራመድ ጀመር። ወደቡ በሞተር ጀልባዎችና በባሕር ትራንስፖርት እንቅስቃሴ ተወጥሯል። በሕዝብ ማመላለሻ ጀልባ ኤልባ ለመሄድ አስተማማኝ የሆነው መንገድ ይህ ብቻ ነበር። ራሱን በሕዝቡ መኻል ማቅለጥ ይችላል።

ሮበርት ወደ ጀልባዎቹ ማቆሚያ ሥፍራ ሊሄድ ሲል ከአንድ ሕንጻ ባሻገር አንድ መለያ ምልክት የሌለው ሽንጠ ረዥም አውቶምቢል ቆሞ አየ። የመንግሥት ሰሌዳ ቁጥር የተለጠፈበት ሲሆን ውስጡ ሁለት ሰዎች ተቀምጠው የመርከቦችን ማቆሚያ ወደብ ይቃኛሉ። ሮበርት ፊቱን አዞረና ወደ ሌላ አቅጣጫ ጉዞውን ጀመረ።

ሮበርት በመርከብ ጭነት ሠራተኞች መካከል የሲቪል ልብስ ለብሰው ተመሳስለው የሚሰልሉ ተከታዩችን ልክ ኮረብታ ላይ ለምልክት እንደሚበራ እሳት ነው ለይቶ የሚያውቃቸው። ልቡ ይመታበት ጀመር። 'እንዴት አድርገው ነው እዚህ ሥፍራ መኖሩን ለማወቅ ያቻሉት?' እናም ስህተቱ በድንገት ተገለጸለት። 'አምላኬ! ለካስ የምሄድበትን ቦታ ለሾፌሩ ነግሬው ነበር። ምን ዐይነት ደደብ ነኝ? በጣም ደክሞኝ ነበር ማለት ነው።'

የካሚዋኑ ዕቃ መጫኛ ጋሪ ላይ ተኝቶ በነበረበት ወቅት የመኪናው እንቅስቃሴ የለሽነት ከእንቅልፉ አነቃው። ወዲያው ከተኛበት ብድግ ብሎ ወደ ውጭ ሲመለከት የካሚዎኑ ሾፌር ነዳጅ ማደያው ውስጥ ስልክ ሲደወል ተመለከተና ቀሰ ብሎ ሾልኮ ከወጣ በኋላ ወደ ሲቪታቬቺያ የሚያመራ ሌላ መኪና ላይ ተንጠልጥሎ ለመግባት ቻለ።

ራሱን ወጥመድ ውስጥ ነው የከተተው። ሰዎቹ በከፍተኛ ሁኔታ እያሰሱት ነው። ጥቂት መቶ ያርድ ርቀት ላይ ማምለጫ የሚሆኑ ጀልባዎች ነበሩለት። ካሁን በኋላ ግን አጠገባችው መድረስ አይችልም።

ሮበርት ፊቱን ከወደቡ አዞረና ወደ ከተማ ገሰገሰ። በተለያዩ ሕብረ ቀለማት "ወደ መዝናኛ ሥፍራ ይምጡ!"» የሚል ማስታወቂያ የተሰቀለበት ሕንጻ አልፎ ሄደ። "ደስታ ለሁሉም"፣ "ምግብ፣ የተለያዩ፣ ጨዋታዎች፣ ግልቢያ" እንዲሁም "ታላቁን እሽቅድድም ይመልከቱ" የሚሉ ማስታወቂያዎች ተለጥፈዋል። ሮበርት ቆም አለና ማስታወቂያውን ተመለከተ። አሁን የማምለጫ መንገድ አገኘ!

@BOOKALEM

ምዕራፍ አርባ አምስት

ከሲቪታቬቺያ አምስት ማይልስ ርቆ በተዘጋጀው የመዝናኛ ዝግጅት ላይ በተለያዩ ሕብረ ቀለማት ያሸበረቁ የአየር ላይ ተንሳፋፊ ባሉኖች በሜዳው ላይ ተገጥግጠዋል። እያንዳንዱ ባሉን በገመድ ከጭነት መኪኖች ጋር ታስሮ ሠራተኞቹ ባሉኖቹን በቀዝቃዛ አየር (ቀዝቃዛ ሃይድሮጂን ጋዝ) እየሞሉ ነው። ከግማሽ ደርዘን በላይ የሚሆኑ ባሉን ተከታይና ፈላጊ መኪኖች የተደረደሩ ሲሆን እያንዳንዱ መኪና ውስጥ አንድ አሽከርካሪና አንድ የባሉን ተመልካች ወይም ፈላጊ ተቀምጠዋል።

ሮበርት የበላይ ወደሚመስል ሰው ሄደና.....“ለታላቁ እሽቅድምድም ዝግጁ የሆነከ ትመስላለህ” አለው።

“አዎን!” አለ ሰውዬው። ለመሆኑ ባሉን ላይ ወጥተህ ታውቃለህ?

“አላውቅም” አለ ሮበርት። አንድ ትዝታ መጣበት።

‘በካም ሐይቅ ላይ በባሉኑ እየተንሳፈፉ ነበር። ሮበርት ተንሳፋፊውን ባሉን የሐይቁን ውሃ እስኪነካ ድረስ ወደ ታች አወረደው። “ባሕሩ ላይ መከስከሳችን ነው!” ብላ ሱዛን ጮኸች። “የለም አንከሰከስም” አላት ሮበርት እየሳቀ። የባሉኑ የታችኛው አካል በውሃው ሞገድ ላይ እየደነሰ ነበር። አንድ የአሸዋ ከረጢት ወደ ውጭ በመጣል ክብደት ሲቀንስለት ተንሳፈው ባሉን እንደገና ወደ ላይ መነሳት ጀመረ። ሱዛን በደስታ ፍልቅልቅ ብላ እየሳቀች አቀፈችውና.....::’

ሰውየው ሮበርትን እያናገረው ነበር። “አንድ ቀን ልትሞክረው የሚገባህ በጣም ታላቅ የሆነ ስፖርት ነው።”

“አዎን። ለመሆኑ የእሽቅድድሙ ጉዞ ወዴት ነው?”

“ወደ ዩጎዝላቪያ። በአሁኑ ጊዜ በጣም ግሩም የሆነ የምሥራቅ ነፋስ በመንፈስ ላይ ነው። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ከምድር እንሊቃለን። ምንጊዜም በማለዳ አየሩ ቀዝቃዛ በሆነበት ሰዓት መብረር በጣም የተሻለ ነው።”

“በእውነት?” አለ ሮበትት በትሁት አንደበት። ዩጎዝላቪያ ውስጥ በቢጋው ወራት ያሳለፈው አንድ ተልዕኮ ትዝ አለው። ኮማንደር ከዚህ አገር አስጠፍተን የምናወጣቸው አሥር ሰዎች አሉን። አየሩ አስኪቀዘቅዝ ድረስ መጠበቅ አለብን። በከረምት አየር አራት ሰዎች ሊያንሳፍፍ የሚችል ባሉን በቢጋ አየር ሁለት ሰዎችን ብቻ ያነሳል።’

@BOOKALEM

ሠራተኞቹ ባሉኞቹን በአየር ሞልተው ከጨረሱ በኋላ የተሞላውን አየር ለማሞቅ በቀስታ ወደ ባሉኑ የተነጣጠረውን እሳት ማቀጣጠያ ውልብልቢት ለመለኮስ ሲዘጋጁ አያቸው። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አየሩ ሞቆ ባሉኑን ሲወጥረው ተሳፍሪዎቹ የሚቆሙበት ቅርጫትም ቀጥ ብሎ ተዘረጋ።

"ባሉኑን እየተዘዋወርኩ ባይ ቅር ይልሃል?" አለ ሮበርት።

"ቀጥል! ግን ማንም ሰው እንዳያይህ ተጠንቀቅ" አለው።

ሮበርት አንድ ቢጫና ቀይ ቀለም ያለው በፕሮፔን ጋዝ የተሞላ ባሉን ተጠጋ። ባሉኑ በገመድ ከካሚዎን ጋር ታስሯል። የባሉኑ ሠራተኛ ከሆነ ሰው ጋር ለመነጋገር ስለሄደ በአካባቢው ማንም አልነበረም።

ሮበርት ተንጠላጥሎ ቅርጫቱ ላይ ወጣና የባሉኑን የተለያዩ መሣሪያዎች መመርመር ጀመረ። የባሉኑን አየር ሙቀት መለኪያ፤ የከፍታ መቆጣጠሪያውን እንዲሁም የመፍቻ ማስቀመጫ ሳጥኑን ተመለከታቸው። ባሉኑ ሙሉ በሙሉ ተነፍቶ ተወጥሯል። የመፍቻውን ሳጥን ከፈተና አንድ ስለታም ቢለዋ አውጥቶ ባሉኑ ከካሚዩኑ ጋር የታሰረበትን ገመድ ገዝግዞ ቆረጠው። በሴኮንዶች ውስጥ ባሉኑ ወደ ሰማይ መንሳፈፍ ጀመረ።

"ሄይ! ምንድን ነው እሱ? ወደ መሬት መልሰኝ!" አለና ሮበርት ጮኸ።

"አይዞህ አትፍራ!" አለ ሠራተኛው። "የከፍታ መለኪያውን መሣሪያ እየተቆጣጠርክ አንድ ሺህ ሜትር ከፍታ ላይ ውጣ። ዩንቨርሳቨያ ውስጥ እንገናኛለን! ስምተህኛል?" አለው።

"አዎን ሰምቼሃለሁ።"

ባሉኑ ሮበርትን ከምዕራብዊ ኤልባ ወደ ምሥራቁ አቅጣጫ ወደ ላይ እያንሳፈፈ ወሰደው። ሌሎች ባሉኖች ገና መሬት አለቀቁም። የሮበርት ባሉን ከፍታ በጨመረ ቁጥር አቅጣጫውን ይቀያይራል። እርሱ ግን ደንታ አልነበረውም። የባሉን ፈላጊ ከሆኑት መኪኖች አንዱ ሲነሳ ሮበርት ተመለከተው። ወዲያው ሚዛን ጠብቂያውን ዝቅ ሲያደርገው ባሉኑ ከፍታውን እየጨመረ መጣ። ስድስት መቶ....ዘጠኝ....መቶ....አንድ ሺህ አንድ መቶ ጫማ.....።

አንድ ሺህ አምስት መቶ ጫማ ከፍታ ላይ ሲደርስ የአየሩ ግፊት በጣም እየቀዘቀዘ በመምጣቱ ባሉኑ ሰማይ ላይ ቀጥ ብሎ የቆመ ይመስል ነበር። አሁን ሮበርት የባሉኑን ከብደት የበለጠ በመቀነስ የንፋሱን አቅጣጫ መቆጣጠር ጀመረ።

ሁለት ሺህ ጫማ ከፍታ ላይ ሲደርስ አየሩ እየለሰለሰ መጣና ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ይዞት ይንሳፈፍ ጀመረ። ከቢታቹ እጅግ በጣም ዝቅ ብሎ ሌሎች ባሉኖች መሬት እየለቀቁ ወደ ዩንዝላቪያ ሲያመሩ ተመለከታቸው። በጆሮው ስር ከሚያፏጨው ነፋስ በስተቀር ሌላ ምንም የሚሰማ ድምፅ አልነበረም። ፍጹም ፀጥታ። ሌላ ትዝታ.....ከሱዛን ጋር ያሳለፈው ትዝታ ታወሰው። «'በደመና ላይ የምንሳፈፍ መስሎ ነው የሚሰማኝ! ዝንተ ዓለም እዚህ አየር ላይ ብንንሳፈፍ ደስ ይለኝ

@BOOKALEM

ነበር።' እቅፍ አደርጋ ያዘቸውና 'ሮበርት ተንሳፋፊ ፊኛ ላይ ፍቅር ሠርተህ ታውቃለህ? እስቲ እንሞክረው!' ቆይታም.....'ሮበርት አስከዛሬ ድረስ ባሉን ላይ ፍቅር የሠራንው አኔና አንተ ብቻ ሳንሆን አንቀርም!' አለችው።»

አሁን ሮበርት በተረጋጋ አየር እየተረዳ በቱስካኒ ወደብ ዳርቻ በታፍሪኒያን ድምቅ ሰማይ ላይ እየተንሳፈፈ ነው። ከባሕር ዳርቻው ራቅ ብሎ ትልቁን ኤልባ ጨምሮ በርካታ ደሴቶች ይታያሉ።

ሮበርት የኤልባ ደሴት ሌላ ትውስታ ቀሰቀሰችበት። ናፖሊዮን የታሰረው እዚህ ኤልባ ደሴት ላይ ነበር። ናፖሊዮን ኤልባን የመረጠበት ምክንያት ምናልባት በጠራ ቀን ተወዳጁን የትውልድ ደሴቱን ኮርሲካን ለማየት ስለሚያስችለው ይሆናል። የናፖሊዮን ሐሳብ ከታሰረባት ከኤልባ ደሴት አምልጦ ፈረንሳይ መግባት ነበር።

'የኔም ሐሳብ ይኸው ነው' አለ ሮበርት። ልዩነቱ ግን ናፖሊዮን ለማምለጥ የሚረዱት ሱዛንና ሐልካዮን የሞተር ጀልባ ስለሌሉት ነው።

በርቀት ሞንቴ ካፓኒ ከምድር ሦስት ሺህ ጫማ ከፍ ብላ ታየችው። ከባሉኑ ውስጥ የሞቀውን አየር ለማተንፈስ የሚረዳውን ቫልቭ ሲስበው ባሉኑ ወደ ታች መውረድ ጀመረ። ወደ ምድር ዝቅ እያለ ሲመጣ ደግሞ መሬት ላይ በሚያስደስት ሁኔታ የበቀለው አትክልትና ሳር፤ ከመሬት አናታቸውን ብቅ ብቅ ያደረጉት የባልጩት ዐለቶችችና የቱስካን የውሃ ዳርቻ ቤቶች ጎልተው ይታዩት ጀመር። በደሴቶቹ ዙሪያ ዘመናት ያልለወጧቸው ነጫጭ የውሃ ዳርቻዎች ይታያሉ።

ሮበርት በተቻለው መጠን የሰዎችን ዕይታ ላለመሳብ ሲል ባሉኑን ከተራራው ስር አሳረፈው። ካረፈበት ቦታ ጥቂት ራቅ ብሎ አንድ አውራ ጎዳና ስላየ መኪና እስኪመጣ ለመጠበቅ ወደ መንገዱ ገባ።

"ወደ ከተማ በመኪናህ ልታሳፍረኝ ትችላለህ?"

"እምን ግባ።"

የመኪናው አሽከርካሪ ወደ ሰማኒያ ዓመት የሚጠጋቸው ፊታቸው የተጨማደደ ሽማግሌ ሰው ነበሩ።

"ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ሰማይ ላይ አንድ ባሉን እንዳየሁ እምላለሁ። ለመሆኑ አንተ አይተህዋል?" ሲሉ አሽከርካሪው ጠየቁት።

"የለም አላየሁም" አለ ሮበርት።

"ለጉበኝት ነው የመጣህው?"

"የለም። ወደ ሮም ለማለፍ በመንገዴ ላይ ነኝ።"

"እኔም አንዴ ሮም ውስጥ ነበርኩ" አሉ ሽማግሌው።

ቀሪውን ጉዟቸውን የጨረሱት በዝምታ ነበር። ፖርቶሬራዬ የተባለችው የኤልባ ብቸኛ ዋና ከተማ ሲደርሱ ሮበርት ከመኪናው ወረደ።

"መልካም ቀን ይሁንልህ!" አሉት በእንግሊዘኛ ቋንቋ።

@BOOKALEM

ሮበርት በከተማዋ ዋና አደባባይ በቪያ ጋሪቫልዲ አልፎ በሄደበት ጊዜ ጎዳናዎቹ በሙሉ በቤተሰብ ቱሪስቶች ተጣበው ነበር። ለሮበርት ጊዜ ልክ ባለበት ነጥብ ላይ የቆመ መስሎ ነው የታየው። 'ግማሹ የዓለም መንግሥታት እኔን ለመግደል ከማሳደዳቸውና ሱዛንን ከማጣቴ በስተቀር ሁሉም ነገር እንዳለ ነው። የተለወጠ ነገር የለም' አለ በሐሳቡ።

ሮበርት ከአንድ የስጦታ ሱቅ ውስጥ የሩቁን አቅርቦ የሚያሳይ መነጽር ገዛና የባሕሩን ወደብ በግልጹ ለማየት እንዲችል ስቴላ ማሪነር ሬስቶራንት በረንዳ ላይ አንድ ወንበር ስቦ ተቀምጦ አካባቢውን በደንብ ቃኘው። አጠራጣሪ መኪኖች፤ የፖሊስ ጀልባዎች ወይም ዩኒፎርም የለበሱ ፖሊሶች አይታዩም። የሚያሳድዱት ሰዎች በዋናው ከርስ ምድር ላይ እንዳጠመዱት አድርገው ስለሚገምቱ «ሐልካንዮን» ጀልባ ላይ ለመሳፈር ሁኔታው አስተማማኝ ነው ሲል ወሰነ። አሁን ማድረግ ያለበት ጀልባዋ አስከትመጣ ድረስ መጠበቅ ብቻ ነው።

ሮበርት እቅዱን እንደገና እየመረመረ «ፕሮካንኒኮ» የተባለውን የአካባቢውን ባሕላዊ ነጭ የወይን ጠጅ እየተጎነጨ ተቀመጠ። ጀልባዋ ማርሴ ወደብ ካደረሰችው በኋላ በራሱ ጥረት ፓሪስ ከተማ ይገባል። ከዚያም ሊ ፖ የተባለውን ሊረዳው የሚችል ቻይናዊ ጓደኛውን ይፈልጋል። ነገሩ ፈዝ ነበር። የፍራንሰስኮ ቄሳር ድምጽ ተሰማው። 'ከቻይናዎቹ ጋር ስምምነት ማድረግህን ሰምቻለሁ።'»

ሮበርት ሊ ፖ እንደሚረዳው ያውቃል። ምክንያቱም ሊ ፖ በአንድ ወቅት የሮበርትን ሕይወት አድኖለታል። ይህም ማለት በጥንታዊው የቻይናዎች ባሕል ዊን.ዩ ከብር መሠረት ሊ ፖ ለሮበርት ሕይወት ኃላፊ ሆኗል ማለት ነው።

ከዚህ በፊት ሊ ፖ "ጎጂ" እና "አንካቡ" የተባለው የቻይና የምሥጢር ፖሊስ ድርጅት ውስጥ ይሠራ ነበር። ይህ ድርጅት በይበልጥ የስለላ ሥራን የሚመለከት ነበር። ከዓመታት ቀደም ብሎ ሮበርት አንድ የቻይናን መንግሥት የሚቃወም የአገሬው ተወላጅ ለማስኮብል ሲሞክር ተያዘና ኩዊን ቼንግ»በተባለው የቻይና የመጨረሻው ጥብቅ እስር ቤት ታሰረ። ሊ ፖ ደግሞ በወቅቱ ከሮበርት ጋር ግንኙነት የነበረው የሁለት ዓለም ሰላይ ነበርና የማምለጫ መንገድ አዘጋጀለት።

ልክ የመጨረሻው የቻይና ድንበር ላይ ሲደርሱ "አሁን በሕይወት ባለሕበት ወቅት ነው ከቻይና መውጣት ያለብህ። ይህን ዕድል ለዘለዓለም አታገኘውም" አለው ሮበርት።

ሊ ፖ የሮበርትን ሐሳብ እንደሰማ ፈገግ አለና....."እኔ በቻይናዊያን አነጋገር "ሬን" ወይም ሰቃይን እስከመጨረሻ የመቋቋምና ከስቃይ የመትረፍ ችሎታ አለኝ" አለው። ከአንድ ዓመት በኋላ ደግሞ ሊ ፖ ፓሪስ የሚገኘው የቻይና ኤምባሲ ተዛወረ።

ሮበርት የመጀመሪያ እርምጃውን አሃዱ ለማለት ቡና ቤቱን ለቀቀና የውሃው ዳርቻ ላይ መዘዋወር ጀመረ። ባሕሩ ዳርቻ ፓርቶ ፊራያን በሚለቁና በሚገቡ

@BOOKALEM

ትናንሽና ትላልቅ መርከቦች ተጣቧል። ዙሪያውን በደንብ ተመለከተና አንድ ሞተር ጀልባ ወደሚወለውል ሰው ተጠጋ። ዲንዚት የተባለች ባለሰምንት ሲሊንደር ሞተር ጀልባ ናት።

"በጣም ግሩም ጀልባ!" አለው ሮበርት።

ሰውየው ራሱን እየነቀነቀ....."ሜርሲ!" አለው።

"ይህችን ጀልባ ተከራይቼ በወደቡ አካባቢ ብዘዋወር ደስ ይለኝ ነበር።"

ሰውየው ሥራውን አቋረጠና ቀና ብሎ ሮበርትን ተመለከተው። "ይቻል ይሆናል። ግን ከሞተር ጀልባዎች ጋር እውቂያ አለህ?" አለው።

"አዎን ዶንዚ ሞተር ጀልባ አገሬ አለኝ።"

ሰውየው ራሱን ነቀነቀና....."ከየት ነው የመጣህው?" አለው።

"ከኦሬጎን" አለው ሮበርት።

"እሺ በሰዓት አራት መቶ ፍራንክ ትከፍላለህ። በተጨማሪም የመያዣ ገንዘብ ታስይዛለህ።"

"በጣም ግሩም!" ሲል ሮበርት ተስማማ።

ጀልባዋ ለመንቀሳቀስ ዝግጁ ሆናለች። "አሁን ነው ልትወስዳት የምትፈልገው?"

"የለም። አሁን እንኳ የማደርሳቸው ጥቂት መልዕክቶች ሰላሉ ነገ ጠዋት እወስዳታለሁ።"

"በሰንት ሰዓት?" አለ ባለጀልባው።

"ሰዓቱን አሳውቅሃለሁ....." አለና "ይሽውልህ ግማሹን ከፍያ ያዝ" ብሎ ጥቂት ገንዘብ አስጨበጠው።

ሐልካዮን መርከብ ወደ ወደብ መግባቷ በጣም አደገኛ ሊሆን ይችላል ሲል ወስኗል። የወደቡ ኃላፊ ለእያንዳንዱ ጀልባ የመግቢያ ፈቃድ በማውጣትና የቆይታ ጊዜአቸውን እንዲመዘግብ በማዘዙ ሮበርት ከሐልካዮን ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በጣም ጥቂት እንዲሆን ስለወሰነ ወደ ወደቡ ከምትገባ ይልቅ እሱ ወደ ጥልቁ ባሕር በጀልባ ሄዶ ሊሳፈራት ወሰነ።

በፊረንሳይ የባሕር ሚንስትር ቢሮ ውስጥ ኮሎሊል ቄሳርና ኮሎኔል ጆንሰን የባሕር አፐሬተሩን በማነጋገር ላይ ነበሩ። "እስካሁን ድረስ ከሐልካዮን ጋር ተጨማሪ ግንኙነት ላለማደረጉ እርግጠኛ ነህ?"

"የለም ጌታዬ! መጨረሻ የተደረገውን ግንኙነት ሪፖርት ካደረኩ በኋላ ሌላ የሰልከ ጥሪ አልተደረገም።"

"ማዳመጥህን ቀጥል!" አለና ኮሎኔል ቄሳር ወደ ኮሎኔል ጆንሰን ዞሮ ሳቀና....."አትጨነቅ! ልከ ጀልባው ላይ እንደተሳፈረ እንይዘዋለን!" አለው።

"እኔ ግን የምፈልገው ከመሳፈሩ በፊት ነው።"

@BOOKALEM

የባሕር መስመሩ አፐሬተር ደግሞ ለኮሎኔል ቄሳር.....“በኢጣሊያ ካርታ ላይ ፖሊንድረም ተብሎ የተመዘገበ ቦታ የለም። ግን አግኝተንዋል ብዬ እገምታለሁ” አለ።

“የት ነው እሱ?”

“የቦታ ስም አይደለም ጌታዬ! ነገሩ ቃል ነው።”

“ምን?”

“አዎን ጌታዬ ፖሊንድረም ማለት አንድ ቃል ወይም አረፍተ ነገር ከቀኝ ወደ ግራ ሲነበብ ማለት ነው። ለምሳሌ “ማዳም አይ አም አዳም” የሚል ሃረግ ውሰዱ። ከዚህም በመነሳት ጥቂት ቃላትን በኮምፒተራችን መርምረናል” አለና አንድ ረዘም ያለ ሊስት ለኮሎኔሉ ሰጠው።

ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰንና ኮሎኔል ፍራንስስኮ ቄሳር ሊስቱን ተቀብለው ተመለከቱት። “ብዙም የሚረዳ አይመስለኝም” አለ ኮሎኔል ቄሳር።

“ሊረዳን ይችል ይሆናል” አለ አፐሬተሩ። “አንድ የሆነ የምሥጢር ቃል ተጠቅመው እንደነበር ግልፅ ነው። አንድ ዝነኛ የሆነ ፖሊንድረም የተነገረው በናፖሊዎን ነበር።” ይሽውም “ኤልባ” የሚለውን የደሴቷን ስም ወደ ግራ አዙሮ ኤበል ብሎታል።”

ኮሎኔል ቄሳርና ኮሎኔል ጆንሰን ተያዩ። “ኤልባ! የክርስቶስ ያለህ! ሮበርት አሁን ያለው ኤልባ ደሴት ላይ ነው!”

ሃያኛ ቀን

ኤልባ ደሴት

በመጀመሪያ በባሕሩ አድማስ ላይ አንድ ነጥብ መስላ ነበር የምትታየው። ቀስ በቀስ በንጋቱ ፀሓይ እየጎላችና እየገዘፈች መታየት ጀመረች። ሮበርት አቅርቦ በሚያሳየው መነጽሩ ሐልካዮንን ተመለከታት። ስለጀልባዋ ምንም የሚያሳስት ነገር የለም። ባሕሩ ላይ ካሉት ሁሉ የተለየች ናት።

ሮበርት ለሥራ ዝግጁ የሆነችውን ጀልባ ለመከራየት ወደ ባሕር ወደብ ወረደና.....“እንደምን አደርክ?” አለው።

የጀልባዋ ባለቤት ቀና ብሎ ተመለከተው። “ሞንዝር ሞንሹር! ጀልባዋን ለመውሰድ ዝግጁ ነህ?”

“አዎን” አለ ሮበርት ራሱን እየነቀነቀ።

“ለምን ያህል ጊዜ ነው የምትፈልጋት?”

“ከአንድ ወይም ከሁለት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ።”

ሮበርት ቀሪውን ገንዘብ ለባለቤቱ አስረከበና ወደ ጀልባዋ ወረደ።

“በጥንቃቄ ያዛት!” አለ ሰውዬው።

“አትጨነቅ አጠነቀቅላታለሁ!” ሲል ሮበርት አረጋገጠለት።

@BOOKALEM

የጀልበዋ ባለቤት የታሰረችበትን ገመድ ሲፈታ ጀልባዋ በደቂቃዎች ውስጥ በባሕር ላይ ሞተሯን እያጮኸች ወደ ሐልካዮን ከነፈች። ሮበርት ወደ ትልቋ ጀልባ ለመድረስ የተወሰኑ ደቂቃዎች ፈጀበት። እየቀረባት ሲመጣ መርከቧ በረንዳ ላይ ሱዛን እና ሞንቴ ባንከሰን ቆመው አያቸው። ሱዛን እጁን አውለበለበችለት። ምን ያህል እንደተጨነቀች ፊቷ ላይ ማየት ይችላል።

ሮበርት የሞተር ጀልባዋን ወደ ትልቋ ጀልባ አሰጠጋና በመሰላሉ ላይ መንጠላጠል ጀመረ።

"ጌታዬ! ጀልባዋን እንድንጭንልዎ ይፈልጋሉ?" ሲል አንድ ሠራተኛ ተጣራ።

"ተዋት ትሂድ። ባለቤቷ በቶሎ ያገኛታል።"

ሮበርት በመሰላል እየተንጠለጠለ እንኳን የለሽ የሆነው የመርከቧ በረንዳ ላይ ወጣ። በአንድ ወቅት ሱዛን ስለሐልካዮን መርከብ ገልጻለት በነበረበት ጊዜ በሁኔታው በጣም ተመስጦ ነበር። አሁን በአካል ሲያያት ደግሞ የበለጠ ማራኪ ሆና አገኛት። ሐልካዮን የሞተር ጀልባ ሁለት መቶ ሰማኒያ ጫማ ርዝመት ያላት በቅንጦት ያበደ የባለቤቱ ከፍል፤ ስምንት እንገዳ ማረፊያ ክፍሎች እና ለአሥራ ስድስት የጀልባዋ ሠራተኞች የሚሆኑ ክፍሎች አሏት።

ከዚህም ሌላ ጀልባዋ ሳሎን፤ የመመገቢያ ክፍል፤ ጽሕፈት ቤትና የመዋኛ ገንዳም አላት።

መርከቢቱ እያንዳንዳቸው አሥራ ስድስት ሲሊንደር እና አንድ ሺ ሁለት መቶ ሃምሳ የፈረስ ጉልበት ያላቸው በካተር ፒላር ኩባንያ የተሠሩ ዲ ሦስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ በተባሉ በሁለት የናፍጣ ሞተሮች የምትነዳ ስትሆን ሌሎች ለሰው ማመላለሻ የሚሆኑ ስድስት አነስተኛ ጀልባዎችንም ጭናለች። የመርከቧ ውስጣዊ ክፍል የተጌጠው በሉዊጂ ስቱርቺዎ ሮም ኢጣሊያ ውስጥ በሚገኘው ኩባንያ ነው። መርከቧ በአጠቃላይ ተንሳፋፊ ቤተ መንግሥት ነች።

"እዚህ ለመድረስ በመቻልህ በጣም ተደስቻለሁ!" አለች ሱዛን። ሱዛን የመንፈስ አለመረጋጋት ይታይባታል። ሮበርት አንድ የተበላሸ ነገር እንዳለ ይሰማዋል። ወይስ እንዳው ነገር የማሸተት ጠርጣሪነቱ ይሆን?

እጅግ በጣም ተውጣ ነበር ያገኛት። በዚህም ምክንያት ኃይለኛ ብስጭት ተሰማው። እንዴ ምን መሰላ ሊያገኛት ነበር የጠበቃት? ገመምተኛ መስላ ጠውልጋ?

ወደ ሞንቴ ዘወር አለና....."ይህን ያደረከልኝን ዕርዳታ ምን ያህል እንደማደንቀው እንድትረዳልኝ እፈልጋለሁ" አለው።

ሞንቴ ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና....."አንተን ለማውጣት መርዳቴ በጣም ያስደስተኛል" አለው።

"የሚቀጥለው ዕቅድህ ምንድን ነው?"

"መርከቧን አዙረህ ወደ ምዕራብ ማርሴ ብታመራ እወዳለሁ። ከዚያም የባሕር ወደብ ላይ ታወርዱኝና.....።"

@BOOKALEM

አንድ ነጭ የባሕርኛ ደንብ ልብስ የለበሰ ሰው መጣ። ሰውዬው በሃምሳዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ግዙፍና በሚገባ የተከረከመ ጢም ያለው ሰው ነው።

"ይህ ካፕቴን ሲምፕሰን ይባላል። ይህ ደግሞ....."አለና ሞንቴ ባንክስ ለዕርዳታ ወደ ሮበርት ዘወር ብሎ ሲያየው ሮበርት ፈጠን አለና....."ስሚዝ! ቶም ስሚዝ እባላለሁ" አለና ራሱን አስተዋወቀ።

"ወደ ማርሴ ነው የምናመራው ካፕቴን" አለ ሞንቴ ባንክስ።

"ወደ ኤልባ አንሄድም ማለት ነው?"

"የለም አንሄድም።"

"በጣም ጥሩ!" አለ ካፕቴን ሲምፕሰን። ግራ የገባው ይመስላል።

ሮበርት የባሕሩን ዙሪያ ቃኘው። ሁሉም ንጹህ ነበር።

"ወደ ታች እንድንወርድ ሐሳብ አቀርባለሁ" አለ ሞንቴ ባንክስ። ሦስቱም መርከቧ ሳሎን ውስጥ ተመቻችተው እንደተቀመጡ....."አንድ ማብራሪያ ልትሰጠን የሚገባ አይመስልህም?" አለ ሞንቴ።

"እውን ይገባኛል። ነግር ግን ምንም የምሰጠው ገለጻ አይኖርም። ምክንያቱም አጠቃላይ ጉዳዩን በትንሹ ካወቅህ የተሻለ ይሆናል። ወንጀል ያልሠራሁ ንፁህ ሰው መሆኔን ብቻ ነው ልናገር የምችለው። አንድ ፖሊቲካ ነክ በሆነ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ በመግባቴ ብዙ ነገር ስላወቅሁ እነሆ እየታደንኩ ነው። ካገኙኝ ደግሞ ይገድሉኛል።"

ሱዛንና ሞንቴ ተያዩ።

"እነሱ እኔን ኩሐልካዮን መርከብ ጋር የሚያገናኙበት ምክንያት የላቸውም" ሲል ሮበርት ንግግሩን ቀጠለ። "ሞንቴ እመነኝ! ሌላ ማንኛውም ዐይነት የማምለጫ መንገድ ቢኖረኝ ኖሮ እጠቀምበት ነበር።"

ሮበርት እሱ ፈልጎ ስላገኛቸውና ስለተገደሉት ንፁሓን ሰዎች አሰበ። አሁን ደግሞ ሱዛን አንድ ነገር ብትሆን ሐዘኑን ፈጽሞ አይቋቋምም። ድምጹን ለማረጋጋት እየሞከረ....."ስለራሳችሁ ደሕንነት ስትሉ እዚህ መርከብ ላይ መሳፈሬን ለማንም ባትናገሩ በጣም አደንቃችኋለሁ" አላቸው።

"በእርግጥ አናደረገውም!" አለ ሞንቴ።

መርከቧ በዝግታ ዞራ ወደ ማርሴ አቅጣጫ መቅዘፍ ጀመረች። "አንድ ጊዜ ይቅርታ ብታደርጉልኝ ካፕቴኑን ለማነጋገር እፈልጋለሁ ።"

እራት ፈጽሞ አሰደሳች አልነበረም። ሮበርት ፈጽሞ ሊገባው ወይም ሊረዳው ያልቻለ የሚረበሽ ውጥረት ነበር። በሞንቴና በሱዛን መኻል ያለ ነገር ነው? ወይስ የእርሱ መርከቧ ላይ መገኘት ነው? ወይስ ሌላ ነገር ነው? 'ከዚህ ቦታ ቶሎ ብጠፋ ነው የተሻለ የሚሆነው' አለ በሐሳቡ።

@BOOKALEM

ከእራት በኋላ ካፕቴን ሲምፕሰን ተመልሶ ሲመጣ ሳሎን ውስጥ ተቀምጠው መጠጥ በመጎንጨት ላይ ነበሩ። "ማርሴ የምንደርሰው መቼ ነው?" አለ ሮበርት።

"ሚስተር ስሚዝ! የአየር ንብረቱ የተረጋጋ ከሆነ ነገ ከሰዓት በኋላ እንደርሳለን" አለ ካፕቴኑ።

ስለካፕቴን ሲምፕሰን ባሕርይ ሮበርትን ሚያስቆጣ አንድ ነገር ነበረበት። ካፕቴኑ ወደ ብልግና ያደላ እስኪመስልበት ድረስ ድምጹና ንግግሩ የሻከረ ነበር። 'መቼም ጥሩ ሰው ባይሆን ኖሮ ሞንቴ አይቀጥረውም ነበር' አለ በሐሳቡ። 'ሱዛን ይህ መርከብ ይገባታል። ሱዛን ምርጥ የሆነው ነገር ሁሉ ይገባታል።'»

ከምሽቱ አምስት ሰዓት ሲሆን ሞንቴ ሰዓቱን ተመለከተና....."አሁን ብናርፍ የተሻለ ይመስለኛል የኔ ፍቅር!" አላት ሱዛንን።

ሱዛን ወደ ሮበርት ሰረቅ አድርጋ ዐይታ....."አዎን" አለች። ሦስቱም ከመቀመጫቸው ተነሱ።

ሞንቴ ወደ ሮበርት ዘወር ብሎ....."መለወጫ ልብስ ከፍልህ ውስጥ ታገኛለህ። የሰውነታችን መጠን እኩል ነው" አለው።

"አመሰግናለሁ!" አለ ሮበርት።

"ደህና እደር ሮበርት።"

"ደህና እደሪ ሱዛን።"

ሮበርት በዓለም ላይ እጅግ በጣም የሚያፈቅራት ሴት ከተፎካካሪው ጋር ጥላው ስትሄድ ተመለከተ። 'ተፎካካሪዬ? ማንን ነው የማታልለው? አሸናፊው እርሱ ነው። ተሸናፊው ደግሞ እኔ ነኝ።'

እንቅልፍ የማይጨበጥ ቅዠት ነበር። ሮበርት የሚያስበው ከሚቀጥለው ግድግዳ ኋላ ስለተኛችውና ከምንም ነገር በላይ ስለሚያፈቅራት ሴት ነው። ሱዛን እርቃኗን አልጋ ውስጥ ተጋድማ ታየችው። 'የሌሊት ልብስ ፈጽሞ አትለብስም' አለ በሐሳቡ። ወዲያው በ ዐይነ–ሕሊናው እየታየችው ሰሜቱ ሲነሳሳ ተሰማው። 'በአሁኑ ሰዓት ሞንቴ ከርሷ ጋር ፍቅር እየሠራ ነው? ወይስ ብቻዋን ናት? እና እርሷስ ከዚህ በፊት ከእርሱ ጋር ስላደረገቻቸው እጹብ ድንቅ ነገሮች እያስታወሰች ይሆን? ምናልባት አይደለም።' ደህና! ለማንኛውም ከሕይወቷ ውስጥ በቶሎ ወጥቶ ይሄድላታል። ምናልባትም ከአሁን በኋላ ፈጽሞ አያያትም ይሆናል።

የ "ሲፋር" መገናኛ ከፍል ራዳር ሐልካዮንን በመፈለግ ላይ ነው። ኮሎኔል ቄሳር ወደ ኮሎኔል ጆንስ ዘወር አለና....."ኤልባ ደሴት ላይ ልንጠልፈው አለመቻላችን በጣም መጥፎ አጋጣሚ ነው። ለማኘውም አሁን አግኝተንዋል። ከሐልካዮን መርከብ መልዕክት አስኪደርሰን ድረስ አንድ ፈጣን የሞተር ጀልባ በተጠንቀቅ አቁመናል" አለው።

@BOOKALEM

ሃያ አንደኛ ቀን

ጎሕ ከመቅደዱ ሮበርት መርከቧ በረንዳ ላይ ወጥቶ ፀጥተኛውን ባሕር በመቃኘት ላይ ነበር። "እንደምን አደርክ!" ብሎ ካፕቴን ሲምፕሰልን ተጠጋው። "አየሩ የተሻሻለ ይመስላል ሚስተር ስሚዝ።"

"አዎን"።

"ከሰዓት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ማርሴ እንደርሳለን። እዚያስ ብዙ እንቆይ ይሆን?" አለ ካፕቴኑ።

"አላወኩም" አለ ሮበርት በደስተኛ ስሜት። "እስቲ እናያለን።"

"እሺ ጌታዬ!"

ሲምፕሰን ተመልሶ ሲሄድ ሮበርት በፀጥታ ተመለከተው። 'ስለሰውየው የሚሰማኝ ምንድን ነው?' እያለ።

ሮበርት ወደ መርከቧ የኋላ ጫፍ ሄደና ባሕሩንና ዙሪያ ገባውን መቃኘት ጀመረ። ምንም የሚታየው ነገር የለም። ሆኖም ግን ባለፉት ዓመታት ደመ_ነፍሳዊው የማነጻጸር ችሎታው ሕይወቱን ከአንድ ጊዜ በላይ ታድጎለታል። ከረዥም ጊዜ በፊት በደመ_ነፍስ ስሌቱ ላይ የመመካት ትምሕርት አግኝቷል። አንድ የተሳሳተ ነገር እንዳለ እርግጠኛ ነው።

ከዕይታ ውጭ በጣም ርቆ የኢጣሊያ ባሕር ኃይል ፈጣን መርከብ ስትሮምቦሊ ሐልካዮንን ማሳደድ ጀመረች

ሱዛን ለቁርስ ብቅ ስትል ገርጥታና ተጎሳቁላ ነበር።

"መልካም እንቅለፍ ተኛሽ ፍቅሬ?" ሲል ሞንቴ ጠየቃት።

"መልካም ነው" አለች ሱዛን።

'ለካስ አንድ የመኝታ ክፍል አይጋሩም' አለ ሮበርት ቤሐሳቡ። ይህንንም በመረዳቱ ምክንያት የለሽ የሆነ ደስታ ተሰማው። እሱና ሱዛን ግን ምንጊዜም አንድ መኝታ ውስጥ ነው የሚተኙት። ለስላሳና የተራቆተው ገላዋ የሱን ገላ እየቀዘፈ ነበር የሚተኙት። 'እየሱስ! እንደዚህ ማሰቤን ማቆም አለብኝ' አለ ሮበርት ለራሱ።

ከመርከቧ በስተቀኝ በኩል ከማርሴ ትኩስ የተጠመደ ዓሣ በማምጣት ላይ የነበርች የአሳ ማጥመጃ ጀልባ ትታያለች።

"ለምሳ ዓሣ ቢያዘጋጁላችሁ ትወዳለችሁ?"

ሁለቱም ወንዶች ራሳቸውን በአዎንታ ነቀነቁ።

@BOOKALEM

ዓላ አጥማጅ ጀልባዋ አጠገብ ደርሰው ነበር። ካፕቴን ሲምፕሰን ወደነሱ ሲመጣ....."ማርሴ መድረሻ ሰዓታችን ስንት ነው?" ብሎ ሮበርት ጠየቀው።

"በሁለት ሰዓት ውስጥ እንደርሳለን ሚስተር ስሚዝ።"

"ማርሴ በጣም ደስ የምትል ወደብ ነች" አለ ሮበርት።

በሲፋር የመገናኛ ክፍል ውስጥ ሁለት ኮሎኔሎች ከሐልካዮን የመጣ መልዕክት እያነበቡ ነበር። መልዕክቱ "አሁን" ብቻ ነበር የሚለው። "የሐልካዮን አቅጣጫ ወዴት ነው?" ሲል ኮሎኔል ቄሳር አምባረቀ።

"ከማርሴ ሁለት ሰዓት ወጣ ብለው ወደ ወደቡ እያመሩ ነው።"

ስትሮሞቦሊ በፍጥነት አሳዳ እንድታቆማቸውና እንድትይዝ አዘዘ።

ከሠላሳ ደቂቃ በኋላ ፈጣኗ የኢጣሊያ ባሕር ኃይል የጦር መርከብ ሐልካዮንን አሳዳ ደርሰችባት። የጦር መርከቧ እየከነፍች ወደነሱ ስትመጣ ሱዛንና ሞንቴ በመርከቧ ጫፍ ላይ ሆነው ይመለከቷት ነበር።

የጦር መርከቧ ድምጽ ማጉያ ትዕዛዝ መስጠት ጀመረ። "አሆይ! ሐልካዮን! አቁም! ልንሳፈር ነው" አለ።

ሱዛንና ምንቴ ሲተያዩ ካፕቴኑ ወደነርሱ እየተጣደፈ መጣ። "ሚስተር ባንክስ....."

"ሰምቻለሁ! እንዳዘዙት አድርግ። የመርከባችንን ሞተር አጥፋ።"

"እሺ ጌታዬ።"

ከአንድ ደቂቃ በኋላ የሞተሩ ድምጽ ፀጥ አረጭ አለና መርከቧ ውሃው ላይ በፀጥታ ቆመች። ከጦር መርከቧ ላይ የታጠቁ የባሕር ኮማንዶዎች በመንሳፈፊያ ታንኳ ወደ ባሕር ሲወርዱ ሱዛንና ሞናቴ ይመለከቷቸው ነበር። ከአሥር ደቂቃ በኋላ በደርዘን የሚቆጠሩ ወታደሮች የሐልካዮንን የመውጫ መሰላል ወረሩት።

የቡዱኑ መሪ የሆነው የባሕር ኃይል መኮንን ሌፍተናንት ኮማንደር....."ስላስቸገርንዎ በጣም አዝናለሁ ሚስተር ባንክስ!" አለ። "የኢጣሊያ መንግሥት አንድ በመሸሸ ላይ ያለ ወንጀለኛ አሳፍረዋል ብሎ ያምናል። መርከብዎን ለመፈተሽ ታዘናል።"

ሱዛን በፀጥታ ቆማ ባሕረኞቹ የመርከቧን በረንዳና የታች ክፍሎች ለመፈተሽ ሲበታተኑ ተመለከተች።

"አንድ ቃል እንዳትናገሪ!"

"ግን....."

"አንዲት ቃል!"

የመርከቧ የላይኛው ወለል ላይ ቆመው አሰላው ሲጠፍ ይመለከታሉ። ከሠላሳ ደቂቃዎች በኋላ ወታደሮቹ እንደገና መርከቧ በረንዳ ላይ ተሰበሰቡ።

@BOOKALEM

"ምልክቱም የለም ኮማንደር!" አለ አንዱ ባሕረኛ።

"እርግጠኛ ነህ?" አለ ኮማንደሩ።

"ፍጹም እርግጠኛ ነኝ ጌታዬ!" መርከቧ በረንዳ ላይ ምንም ተሳፍሪ የሌለ ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱን ሠራተኛም ተመልከተናል።

ኮማንደሩ ባለበት ሥፍራ ተሸብሮ ቆመ። የበላይ አለቆቹ በጣም ከፍተኛ የሆነ ስህተት ሠርተዋል። ወደ ሞንቴ ሱዛንና ካፕቴን ሲምፕስን ፊቱን አዞረና....."ይቅርታ መጠየቅ ይገባኛል። ስላሰቸገርናችሁ እጅግ በጣም አዝናለሁ። አሁን መርከባችሁን እንለቃለን!" አለና ለመሄድ ፊቱን አዞረ።

"ኮማንደር" አለው ሞንቴ።

"አቤት"

"እናንተ ምትፈልጉት ሰው ከሠላሳ ደቂቃዎች በፊት በዓሣ ማጥመጃ ጀልባ ሄዷል። እሱን ለመያዝ ምንም ችግር አይገጥማችሁም።"

ከአምስት ደቂቃ በኋላ የጦር መርከቧ ስትሮሞቦሊ ወደ ማርሴ አቅጣጫ ትበር ጀመር። ሊውተናንት ኮማንደሩ የሚደሰትበት ብዙ ምክንያት ነበረው። ኮማንደር ሮበርት ቤላሚን ግማሹ የዓለም መንግሥታት እያሳደዱት ሲሆን የሚያገኘው ግን እሱ ነው። 'ግሩም የሆነ የማዕረግ ዕድገት አገኛለሁ' አለ በሐሳቡ።

ከመርከቧ ድልድይ ላይ ባሕረኛው መኮንን ተጣራ። "ኮማንደር እባክህን አንድ ጊዜ ወደዚህ ብትመጣ።"

'ዓሣ አጥማጁን ጀልባ አገኛት ማለት ነው?' ኮማንደሩ እየተጣደፈ ሄደ።

"ይመልከቱ ጌታዬ!"

ኮማንደሩ አንዴ ብቻ ሁኔታውን ተመለከተና ልቡ ቀለጠችበት። ከፊት ለፊቱ ራቅ ብሎ አጠቃላዩ የማርሴ ዓሣ አጥማጅ ጀልባዎች ባሕሩን እንደአሸን ሸፍነውታል። ከነሱ ውስጥ ደግሞ በመቶ የሚቆጠሩት አንድ ዐይነት ሲሆኑ ወደ ወደብ በመመለስ ላይ ነበሩ። ኮማንደር ቤላሚ የተሳፈረባትን ጀልባ ለማወቅ በዓለም ላይ ምንም ዐይነት ዘዴ ለም።

@BOOKALEM

ምዕራፍ አርባ ስድስት

ማርሴ ውስጥ ሞዴል 18ዘ የሆነች ፊያት መኪና ጨለም ካለ ጎዳና ሰርቆ ወሰደ። ምንም እንኳ መኪናዋ የተቆለፈችና የተዘጋች ብትሆንም ይህ ለሮበርት ብዙም የሚያስቸግር ጉዳይ አልነበረም። ዙሪያውን ተመለካከታትና ማንም እንደማያየው ካረጋገጠ በኋላ የመኪናውን ጣራ የሸራ ሽፋን ሸርክቶ ቀደደውና እጁን አሾልኮ አስገብቶ በሩን ከፈተው። መኪናዋ ውስጥ ከገባ በኋላ ከአመልካች ሰሌዳው በታች አጎንብሶ በርከት ያሉ የማስነሻና የማቀጣጠያ ሽቦዎችን ሰቦ አወጣቸው። ከመካከላቸውም አንድ ወፍራምና ቀይ የኤኬክትሪክ ሽቦ መርጦ በአንድ እጁ ያዘና ሌሎቹን ሽቦዎች በቀዩ ተራ በተራ መንካት ጀመረ። በዚህ ዐይነት በቀዩ ሽቦ ፍተሻውን በማድረግ ላይ እንዳለ በድንገት የመቆጣጠሪያ ሰሌዳው መብራቶች በሩለት።

ቀዩን ሽቦና ሰሌዳውን ያበራለትን ሌላ ሽቦ አንድ ላይ ሰበሰቦ አሰረና ያዘ። በመቀጠልም ሁለቱን አንድ ላይ የተቋጠሩ ሽቦዎች የመኪናው ሞተር እስኪነሳለት ድርስ ከሌሎች ሽቦዎች ጋር ተራ በተራ ማነካካት ቀጠለ።

የመጀመሪያው አሰቸኳይ ሥራው ሊ ፖ የተባለውን ሰው ፈልጎ ማግኘት ነው። ፓሪስ እንደደረሰ የሕዝብ ስልክ ያለበት አካባቢ ፈልጎ የ ሊ ፓን ስልክ ቁጥር ደወለ። ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ የ ሊ ፖ ድምጽ በመልስ መስጫው መሣሪያ (አንሰሪንግ ማሺን) ላይ ተሰማ።

"እንደምን አደሩ እቤት ልገኝ ባለመቻሌ አዝናለሁ። ቢሆንም ግን ለጥሪዎች መልስ ባለመስጠቴ ምንም አደጋ የለም። ድምጽ ለመስማት ሲጠብቁ ይጠንቀቁ።"

ሮበርት የመልክቱን ምሥጢር ለመፍታት እያንዳንዷን ቃል ተራ በተራ መቁጠር ጀመረ። ቁልፍ የሆኑት ቃላት "አዝናለሁ፣ አደጋ፣ ጥንቃቄ" የሚሉት ናቸው።

'እሷን! ስልኩ ተጠልፏል ማለት ነው።' ሊ ሮበርት እንደሚውልለት ጠብቆ ነበር ማለት ነው። እናም ለሮበርት በዚህ ዐይነት መንገድ ማስጠንቀቂያ አስተላለፈለት። ሮበርት ከዚህ በፊት ሁለቱ የተጠቀሙበትን የምሥጢር ቃል በመጠቀም በቶሎ ሊን ማግኘት አለበት።

ሮበርት በሩ ቤንት አኖሬ ጎዳና ላይ መራመድ ጀመረ። አንድ የጋዜጣ መሸጫ ሱቅ አካባቢ ሲደርስ አንድ ወጣት ልጅ ተጣራና አስቆመ። "ልጅ! ሃምሳ ፍራንክ ለማግኘት ትወዳለህ?"

@BOOKALEM

ልጁ ሮበርትን በጥርጣሬ ተመለከተውና.....“ምን ሰርቼ?” አለው። ሮበርት አንድ ወረቀት ላይ የሆነ ነገር ጫር ጫር አድርጎ ለልጁ ከሃምሳ ፍራንክ ገንዘብ ጋር አንድ ላይ አቀብለውና.....“ይሀን ወደ ጋዜጣው ቢሮ የማስታወቂያ ክፍል ወስደህ ስጥልኝ” ሲል አዘዘው።

“በጣም ጥሩ!”

ልጁ ወደ ሕንጻው ሲገባ ቆሞ ተመለከተው። ይህ በማግስቱ ጠዋት ለሚወጣው ጋዜጣ ጽፎ የላከው ማስታወቂያ እንደሚከተለው ይነበባል።

«“ቲሊ አባባ በጣም ስለታመመ ይፈልግሻል። እባክሽን በቶሎ አግኚው። እናትሽ።”»

ከዚህ በኋላ ሮበርት ከመጠበቅ ሌላ የሚያደርገው ምንም ነገር የለም። የሆቴል ክፍል ለመያዝ አያስበውም። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ መላው የፓሪስ ሆቴሎች ስለሮበርት መግለጫ ይሰጣቸዋልና። ፓሪስ እንደሆነ የተሞላች የሰዓት በምብ ናት።

ሮበርት አንድ የተጣበበ የቱሪስቶች አውቶቡስ ላይ ተሳፈረና ከኋለ በኩል ድምጹን አጥፍቶ ዝቅ ብሎ ተቀመጠ። የጉብኝቱ ቡድን የሉክሰምበርግን የአትክልት ሥፍራ ሌስ ኢንቫሊድስ የሚገኘውን የናፖሊዎን የመቃብር ሥፍራ እንዲሁም ሌሎች በደርዘን የሚቆጠሩ የቱሪስት መስህቦችን እየተዘዋወረ ጎበኘ። እናም በጉብኝቱ ወቅት ሮበርት በቱሪስቶቹ መኻል ሆኖ ነበር የሚንቀሳቀሰው።

ሮበርት ከጉብኝቱ በኋላ ከሌላ የቱሪስቶች ቡድን ጋር የቲያትር መመልከቻ ቲኬት ሸመተ። በሁለት ሰዓት የተጀመረው ትርዒት እንደተጸፈመ በሞንትማትሪ ጎዳና ከትንሽ ቡና ቤት ትንሽ ቡና ቤት እየተዘዋወረ ጊዜውን አሳለፈ።

ሃያ ሁለተኛ ቀን

ፓሪስ ደፊንስ

የንጋቱ ጋጌጦች እስከአምስት ሰዓት ድረስ አይወጡም። ለአምስት ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩት የጋዜጣ መሸጫ አካባቢ ቆሞ እየተጠባበቀ ነበር። አንድ ቀይ ካሚዎን ደረሰ። ከካሚዎኑ ላይ አንድ ልጅ የታሰሩ ጋዜጦችን ወደ መንገዱ ጠርዝ ወርውሮ ሲጥል ሮበርት ተሸቀዳድሞ አንዱን ብድግ አረገውና ወዲያውኑ “ይፈለጋል” ማስታወቂያ የታተመበትን አንቀጽ ገልጦ ተመለከተ። የእርሱ ማስታወቂያ ታትሟል። አሁን ምንም የሚያደርገው ነገር የለም። መጠበቅ ብቻ።

ከሰዓት በኋላ ሮበርት የትምባሆ መሸጫ ሱቅ አመራና በርካታ የግል መልዕክቶች የተለጠፉበትን ሰሌዳ ተመለከተ። የዕርዳታ ፈላጊዎች ማስታወቂያ፤ የሚከራዩ ኢፓርትመንቶች ማስታወቂያ፤ የክፍል ጓደኛ የሚፈልጉ ተማሪዎች ማስታወቂያ፤ የሚሸጡ ብስክሌቶች። በሰሌዳው መካከለኛ ሥፍራ ላይ ሮበርት

@BOOKALEM

የሚፈልገውን መልዕክት አገኝ። “ቲሊ እስክታገኝሽ ቸኩላለች። እባክሽ በስልክ ቁጥር 154126451 ደውይላት።”

ሊ ፖ በመጀመሪያው ጥሪ ነው መልስ የሰጠው። “ሮበርት ነህ?”

“አዎን ሊ።”

“አምላኬ! ሰውዬ ምንድነው እየተደረገ ያለው?”

“እንተ ትነግረኛለህ ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር።”

“ጓደኛዬ!” አለ ሊ። “በአሁኑ ጊዜ ከፈረንሳይ ፕሬዚዳንት የበለጠ ከፍተኛ ትኩረት እየሳብክ ያለህው አንተ ነህ። የመገናኛ ብዙሓን በሙሉ ባንተ ጊዜ እየነደዱ ነው። የሆነው ቢሆን አንተ አሁን ከፍተኛ ችግር ውስጥ ነው ያለህው። ቻይና ኤምባሲ ውስጥ ያለውን የኔን ስልክ ጠልፈውታል። የመኖሪያ ቤቴን ስልክ የጠለፉት ሲሆን ቤቴን በዐይነ ቁራኛ እየተመለከቱ ነው። ስላንተ ማለቂያ የሌለው ጥያቄ ሲጠይቁኝ ነው የከረሙት።”

“ሊ! ይህ ሁሉ የሚከናወነው ለምን እንደሆነ የምታውቀው ነገር አለ?”

“በስልክ ልነግርህ አልችልም። ለመሆኑ የሱንግ አፓርትመንት የት እንደሆነ ታስታውሳለህ?”

“አዎን” አለ ሮበርት። የሊ ወዳጅ የሆነች ሴት ናት።

“በግማሽ ሰዓት ውስጥ እዚያ እንገናኝ።”

“አመሰግናለሁ” አለ ሮበርት። ሊ ራሱን ምን ዐይነት ችግር ውስጥ እየከተተ እንዳለ በሚገባ ተገንዝቧል። ከዚህ በፊት ኤፍ.ቢ.አይ ውስጥ የሚሠራ ጓደኛው ምን እንደደረሰበት በሚገባ ያስታውሳል። ‘የተረገምኩ ገፊ ነኝ! የቀረብኩት ሁሉ ይሞታል’ አለ በሐሳቡ።

አፓርትምንቱ ፀጥተኛ በሆነው የፓሪስ ከተማ ክልል ቤንቢሉ በተባለ ሥፍራ ላይ ይገኛል።

ሮበርት ወደ አፓርትምንቱ ሕንጻ በደረሰ ጊዜ ስማዩ ዝናብ ባዘሉ ጥቋቁር ደመናዎች ተጋርዷል። ከዚህም ሌላ የመብረቅና ነጎድጓድ ድምጽ ከርቀት ይሰማው ነበር። የአፓርትመንቱን መጥሪያ ሲደውል ሊ ፖ ወዲያውኑ በሩን ከፈተለት።

“ወደ ውስጥ ግባ ቶሎ በል!” አለ ቻይናዊው። ከውስጥ በኩል በሩን ዘጋና ቆለፈው። ሮበርት ለመጨረሻ ጊዜ ካየው ቀጭንና ዕድሜ የለሽ ሆኖ ነበር የታየው። ሁለቱ ሰዎች እጅ ለእጅ ተጨባበጡ።

“ሊ! ለመሆኑ ምን እየተከናወነ እንደሆነ ታውቃለህ?”

“ሮበርት ተቀመጥ!” አለ ሊ።

ሮበርት ወንበር ላይ ተቀመጠ። ሊ ለተወሰነ ጊዜ ሮበርትን እያጠናው ቆየና.....“ለመሆኑ “አፕሬሽን ዱምዝዶይ›(የፍርድ ቀን ዘመቻ)” የተባለ ነገር ሰምተህ ታውቃህ?”

@BOOKALEM

ሮበርት ፊቱን ጭፍግግ አደረገና.....“የለም አላወቅም። ለመሆኑ ካልታወቁ በራሪ ዲስኮች ጋር ግንኙነት አለው?”

“ከያ.በ.አ. ጋር ሁሉም ዐይነት ግንኙነት አለው” አለ ቻይናዊው። “ዓለም ከጥፋት ጋር እየተፋጠጠች ነው ሮበርት።”

ሊ ከመቀመጫው ተነሳና መንጎራደድ ጀመረ። “የጠፈር (የሌሎች ዓለማት) ፍጡራን እኛን ለማጥፋት ወደ ምድር ሊመጡ ነው። ከሦስት ዓመታት በፊት ፍጡራኑ በመንኮራኩራቸው እዚህ ምድር ላይ አርፈው ከባለሥልጣናት ጋር ከተገናኙ በኋላ ኃያላኑ ባለኢንዱስትሪ አገሮች የኒውክሊየር ጣቢያቸውን እንዲዘጉና ቅሪተ አካል ነዳጅ ማንደዳቸውን እንዲያቆሙ! የሚል ጥያቄ አቅርበው ነበር።”

ሮበርት እጅግ በጣም ግራ ገብቶት ነበር የሚያዳምጠው። ሊ ንግግሩን ቀጠለ። “የነዳጅ፤ የኬሚካል፤ የኅማ፤ የፐላስቲክ፤ ምርቶች ሁሉ የማምረት ተግባር በአስቸኳይ እንዲቆም ጠይቀዋል።” ይህ ማለት በመላው ዓለም በሺህ የሚቆጠሩ ፋብሪካዎች ይዘጉ ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የአውቶሞቢልና የብረታ–ብረት ፋብሪካዎች እንዲዘጉ ይገደዳሉ። የዓለም ምጣኔ ሀብት ፈራረሰ ማለት ነው። ባጠቃላይ “ሕዋውን ትመርዛላችሁ!” ነው የሚሉት። “መሬትንና ባሕርን እየበከላችሁ ነው!” ይላሉ። የጦር መሣሪያዎችን ማምረትና ጦርነትን ማፍፋም እንደናቆም ይፈለጋሉ።”

“ሊ.....”

ሊ ሮበርትን አቋረጠውና ንግግሩን ቀጠለ። “ከበርካታ አገሮች የተውጣጡ ኃያላን ሰዎች ማለትም ከፍተኛ የኢንዱስትሪ ባለቤቶች ከአሜሪካ፤ ከጃፓን፤ ከሩሲያ፤ ከቻይና የተውጣጣ ቡድን ከመመሥረታቸውም በላይ «ጃኑስ» በሚል የምሥጢር ሰም የሚጠራ ሰው በመላው ዓለም ዙሪያ የሚገኙ የስለላና የመረጃ ድርጅቶችን በአንድነት በማቀናጀት እነዚህን ከጠፈር ወይም ከሌላ የከዋክብት ዓለም የሚመጡ ፍጡራንን ለማቆም እንዲቻል ‹“የፍርድ ቀን ዘመቻ”› (ኦፐሬሺን ዱምዝደይ) የተባለውን ንቅናቄ ፈጥረዋል። ወደ ሮበርት ዘወር አለና....“ኤስ.ዲ.አይ. የተባለ ነገር ሰምተሃል?” ሲል ጠየቀው።

“የከዋክብት ጦርነት (ስታር ዋርስ)” አለ ሮበርት። “የሶቪዬትን ኢሕጉር አቋራጭ ባሊስቲክ ሚሳይል ተኩስ ለማክሸፍ የተፈጠረ በሳተላይት ቴክኖሎጂ የታገዘ ዕቅድ ነው።”

ሊ በአሉታ ራሱን ነቀነቀ። “አይደለም። ይህ የማስመሰያ ሽፋን ነው። ኤስ.ዲ.አይ. የተፈጠረው ሩሲያዊያንን ለመውጋት አይደለም። ንድፉ የወጣው ያ.በ.አ. (ያልታወቁ በራሪ አካለት) የተባሉትን በራሪ ዲስኮች እየመቱ ለመጣል እንዲቻል ነው። “እነሱን ለማቆም ያለው ብቸኛ ዕድል ይህ ብቻ ነውና!” ሮበርት በሰማው ሁሉ በተቀመጠበት ደንዝዞ ቀረ። ሊ የተናገረውን ለመዋጥና ለማዋሃድ

@BOOKALEM

እየሞከረ ነው። ከውጭ በኩል የነጎድጓዱ ጩኸት የበለጠ እያስገመገመ አገሩን ያደባልቀዋል።

"ሊ! አንተ የምትለኝ መንግሥታቱ ሁሉ ከዚህ ነገር በስተጀርባ አሉበት ነው?"

"በእያንዳንዱ መንግሥት ውስጥ ሰው በላዎች አሉ እንበል። ከዚህም በመነሳት የፍርድ ቀን ዘመቻ የሚመራው ወይም የሚቀላጠፈው በግል ነው። አሁን ተረዳህኝ? ገባህ?"

"ያምላክ ያለህ! መንግሥታቱ በመደረግ ላይ ስላለው ነገር የሚያውቁት ነገር የለም?" አለና ቀና ብሎ ሊን እየተመለከተው....."ሊ! ለመሆኑ አንተ ይህን ሁሉ እንዴት ደረስክበት?" ሲል ጠየቀው።

"የፍርድ ቀን ዘመቻ"፣ በተባለው ንቅናቄ እኔ የቻይና ተወካይ ወይም የቻይና አገናኝ ነኝ!" ይህን በተናገረበት ወቅት ሊ በእጁ "ቤሬታ"፣ የተባለ ሽጉጥ ይዞ ነበር። ሮበርት ሽጉጡን በድንጋጤ ተመለከተው።

"ሊ....."

ሊ የሽጉጡን ቃታ ተጫነው። ልክ በዚህ ሴኮንድ የጥይቱ ጩኸት ጆሮ ከሚያደነቁር የነጎድጓድ ድምጽና የመብረቅ ብልጭታ ጋር ተደባለቀ።

ምዕራፍ አርባ ሰባት

እላይዋ ላይ የተንጠባጠቡት የመጀመሪያዎቹ ንፁሕ የዝናብ ውሃ ጠብታዎች ሲቀሰቀሷት አንድ የመናፈሻ ቦታ አግዳሚ ወንበር ላይ ተኝታ ነበር። ለመንቀሳቀስ በማትችልበት ሁኔታ እጅግ ከመዳከሚም ሌላ ባለፉት ሁለት ቀናት ውስጥ የቀራት የሕይወት እንጥፍጣፊ ኃይል ሁሉ ከውስጧ ሲያልቅ ይሰማት ነበር። 'እዚህ ፕላኔት ላይ ሞቼ ልቀር ነው'፣ አለችና የዘለዓለም እንቅልፏ ነው ብላ ወደገመተችው መኝታ ሄደች። ከዚህ በኋላ ዝናብ መዝነብ ጀመረና ሕሊናዋን መግዛት ስትጀምር ራሷን ወደ ሰማይ ቀና አደረገችና ቀዝቃዛው ውሃ በፊቷ ላይ እንዲንቆረቆር አደረገች። ይህ የተቀደሰ ዝናብ ይዘንባል ብላ በፍጹም አላመነችም ነበር። ንፁሁና ቀዝቃዛው የዝናብ ውሃ የበለጠ ኃይሉን ጨምሮ ጥንካሬ እየሰጣት በላይዋ ላይ መዝነቡን ቀጠለ።

የዝናቡን ውሃ በላይዋ ላይ እንዲወረድ እያደረገች ውሃውን ወደ ጥልቁ የሕይወቷ መሠረት እየመጠጠች ድካሙና ዝለቱ ሁሉ ፈፅሞ እስኪለቃት ድረስ ቀጥ ብላ ቆመች። ጥንካሬዋ የበለጠ እየጨመረ በመጨረሻም ሙሉ በሙሉ ዝገጁ መሆኗ እስኪታወቃት ድረስ ብርታቷ ሲመለስ ተሰማት። 'አሁን ዝግጁ ነኝ፣ በትክክል ማሰብ ማመዛዘን እችላለሁ። ወደ መጣሁበት ዓለም ለመመለስ እንድችል ማን ሊረዳኝ እንደሚችል አሁን በግልጽ አወኩት!' አለችና አነስተኛዋን የመገናኛ መሣሪያ አውጥታ ዐይኖቿን ጨፈነችና በከፍተኛ ትኩረት አዕምሮዋን ማሠራት ጀመረች።

@BOOKALEM

ምዕራፍ አርባ ስምንት

የሮበርትን ሕይወት ያዳነው የመብረቁ ብልጭታ ነበር። ልክ ሊ ፖ ቃታውን መሳብ በጀመረበት ቅጽበት ከውጭ በኩል በመስኮት የገባው የመብረቅ ብልጭታ ብርሃን ስላስበረገገው ሮበርት በአጋጣሚ ወደ ጎን ተነቃነቀ። በዚህ ምክንያት ከአፈሙዙ የወጣቸው ጥይት ከደረቱ ይልቅ የቀኝ ትከሻውን መታችው።

ሊ እንደገና ሽጉጡን ከፍ ለማድረግ ሲሞክር ሮበርት የጎን ስንዘራ ምት በመጠቀም ሽጉጡን ከሊ እጅ አስጣለው። ሊ ደግሞ ወደ ፊት ተወረወረና ሮበርትን የቆሰለው ትከሻው ላይ በኃይለኛ ቡጢ ነረተው። ሕመሙ ፈጽሞ ማይቻል ነበር። የሮበርት ጃኬት በደም ተበከለ። ሮበርት የፊት ለፊት ስንዘራ በመጠቀም ከርኑን በፍጥነትና በኃይል ሊ ፖ ላይ አነዘረበት። ሊ በደረሰበት ሕመም ጮኸና ተመልሶ ሚዛኑን ጠብቆ በመቆም "ሹት" የተባለውን ገዳይ የአነዛዘር ዘዴ ሮበርት አንገት ላይ አነዘረበት።

ሮበርት ዱላውን በቀላሉ አስወገደው። ሁለቱም ሰዎች ዐይን ለዐይን ትክ.....!ብለው እየተያዩ የማጥቂያ ክፍተት ለማግኘት ዙሪያውን ይዞሩ ጀመር። ለዘመናት በቆየው አደገኛና ገዳይ የእጅ በእጅ ውጊያ ጥበብ በፀጥታ ተዋጉ። ከዚህ ውሰጥ በሕይወት የሚወጣው አንድ ሰው ብቻ እንደሆነ ሁለቱም በሚገባ ያውቁታል።

ሕመሙ እየጨመረ ሲመጣ ደሙ ወለሉ ላይ ሲወርደድ ይታየው ነበር። ጊዜ በ ሊ ፓ ጎን ነው የቆመው። 'ይህን ፍልሚያ በቶሎ እንዲያበቃ ማድረግ አለብኝ!'አለ ሮበርት በሐሳቡ። የፊት ለፊት እግር ምት በመጠቀም ሮበርት ወደ ፊት ተነቃነቀ። ሊ ደግሞ ምቱን ከማስወገድ ይልቅ ሙሉ በሙሉ ተቀብለውና የሮበርትን የቆሰለ ትከሻ በክርኑ የጎንና የኋላ ምት ሲያወርድበት ሮበርት ለመውደቅ አዘመመ። ወዲያውኑ ሊ እላዩ ላይ ተከመረበትና የቆሰለ ትከሻውን አሁንም አሁንም ደጋግሞ በክፍሉ ዙሪያ እያዞረ በጡጫ ጠበጠበው።

ሮበርት የሚወርድበትን ጡጫ ለማቆም ምንም ኃይል አልነበረውም። በጣም ደከመ። ዐይኖቹ እየጨለሙ መጡበት። ብቻውን ወለሉ ላይ ተነጠፈ። ሁለቱም ሰዎች በሞት-ሽረት ግብግብ ተያይዘው ሲወድቁ ከመስተዋት የተሠራውን ጠረጴዛ እንክትክቱን አወጡት። ሮበርት የቀረውን የኃይል እንጥፍጣፊ ሁሉ ጨርሶ 'ተፈጸመ አሸንፏል!'አለ በሐሳቡ።

ግማሽ ሕሊናውን ስቶ በወደቀበት ቦታ ካሁን አሁን ሊ ይጨርሰኛል እያለ ተጋድሞ ጠበቀ። ግን ምንም የተፈጠረ ነገር አልነበረም። ሮበርት በሕመም እየተሰቃየ በዝግታ አንገቱን ቀና ሲያደርግ ሊ ከአጠገቡ ተጋድሞ ዐይኖቹ ሙሉ በሙሉ

@BOOKALEM

ተጎልጉለው የቤቱን ኮርኒስ ወደ ላይ እየተመለከተ ተጋድሟል። ከተሰበረው ጠረጴዛ ላይ አንድ ግዙፍ የመስተዋት ስባሪ ደረቱ ላይ ተቀብቅቦበት ነበር።

ሮበርት ለመቀመጥ ታገለ። እጅግ ብዙ ደም ስለፈሰሰው ከመድከሙም በላይ ትከሻው ላይ ከፍተኛ ሕመም ይሰማዋል። 'ወደ ሐኪም ዘንድ መሄድ አለብኝ!' አለ በሐሳቡ። 'አንድ የሆነ ስም ነበር.....በፓሪስ የአሜሪካ ሆስፒታል ውስጥ ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል የሚጠቀምበት ዶክተር.... አዎን እሱ ነው! ሌዊን ሔልሲንገር።'

ስልክ ሲደውል ዶክተር ሔልሲንገር ከቢሮው ለመውጣት በመዘጋጀት ላይ ነበረ። ረዳት ነርሷ ደግሞ ወደ ቤቷ ሄዳ ስለ ነበር ዶክተሩ ስልኩን አነሳው። በስልኩ ውስጥ የሚሰማው ድምጽ ደካማ ነበር።

"ዶክተር ሔልሲንገር?"

"አዎን።"

"እኔ ሮበርት ቤላሚ ነኝ። ዕርዳታህን እፈልጋለሁ። በመጥፎ ሁኔታ ተጎድቻለሁ። ትረዳኛለህ?"

"በእርግጥ እረዳሃለሁ። የት ነው ያለህው?"

"ስለሱ ግድ የለም። አሜሪካን ሆስፒታል ከግማሽ ሰዓት በኋላ እንገናኝ።"

"እሺ እዚያው እመጣለሁ። አንተ በቀጥታ ድንገተኛ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል ግባ።"

"ዶክተር...ስለዚህ ስልክ ጥሪ ለማንም እንዳታወራ።"

"ቃል እገባልሃለሁ!" አለና ዶክተሩ ስልኩን ዘጋ።

ዶክተር ሔልሲንገር ወዲያውኑ ስልክ ደወለ። "ኮማንደር ቤላሚ አሁን ስልክ ደውሎልኝ ነበር። በግማሽ ሰዓት ውስጥ አሜሪካን ሆስፒታል ልንገናኝ ነው።"

"አመሰግናለሁ ዶክተር!" አለ መልዕክቱን የተቀበለው ሰው። ዶክተር ሔልሲንገር ስልኩን ሲያስቀመጠው ልክ በዚህች ቅጽበት የእንግዳው መቀበያ በር ሲከፈት ተሰማውና ቀና ብሎ ተመለከተ። ሮበርት ቤላሚ በእጁ ሽጉጥ ይዞ ቆሟል።

"በድጋሚ ሳስበው" አለ ሮበርት። "እዚሁ የሕክምና ዕርዳታ ብታደርግልኝ የተሻለ ይሆናል።"

ዶክተሩ ድንጋጤውን ለመደበቅ ሞከረ። "አንተ.....አንተ ሆስፒታል ብትገባ ይሻላል።"

"ለሬሳ ቤት በጣም ይቀርባል!" አለው ሮበርት። "በአስቸኳይ ቁስሌን ለጥፍልኝ!" አለ ለመናገር እያዳገተው።

ዶክተር ሔልሲንገር ለመቃወም ፈለገና 'መተው የተሻለ ነው' ሲል አሰበ። "እሺ እንደፈለክ ሮበርት። ማደንዘዣ ብሰጥህ የተሸለ ነው።"

"ይህን በፍጹም አታስበው! ማታለል የለም።" ሽጉጡን በግራ እጁ እንደያዘ....."እኔ ከዚህ ቤት በሕይወት ካልወጣሁ አንተም አትወጣም። ጥያቄ አለህ?" አለው። ሕሊናውን ሊስት የተቃረበ መሰለው።

@BOOKALEM

ዶክትር ሔልሲንገር ምራቁን ዋጠና.....“የለኝም!” አለው።

“እሺ ሥራህን ቀጥል!” ሲል ሮበርት አዘዘው።

ዶክተር ሔልሲንገር ሮበርትን እየመራ አንድ በሕክምና መርጃ መሣሪያዎች የተሟላ ክፍል ውስጥ ይዞት ገባ። ሮበርት በዝግታና በጥንቃቄ ጃኬቱን አወለቀውና ሸጉጡን እንደያዘ ጠረጴዛው ላይ ተቀመጠ። ዶክተር ሔልሲንገር የቀዶ ጥገና ሴንጢው ይዞ ስለነበር ጣቱን ቃታው ላይ ጠበቅ አደረገው።

“ተዝናና!” አለ ዶክተር ሔልሲንገር በጭንቀት። “ጥይቱ አሁንም ሰውነትህ ውስጥ ነው። ማደንዘዣ እስካልሰጠሁህ ድረስ ሕመሙን.....”

“የለም!” አለና ሮበርት ጮኸ። የፈለገው ቢሆን ራሱን ለማደንዘዣ አሳልፎ አይሰጥም። “እንዲሁ በደረቁ ንትተህ አውጣው!”

“እንዳልክ!” አለ ዶክተሩ። ሮበርት ዶክተሩ ከረቂቅ ተዋሲያን ነጻ የሆነ ዕቃ ማስቀመጫ ሄዶ መቆንጠጫ መሰል መቀስ ብድግ ሲያደርግ ተመለከተው። ጠረጴዛው ላይ ተቀምጦ ሙሉ በሙሉ ሊያጥለቀልቀው የተቃረበውን የመደንዘዝ ስሜት ይታገል ጀመር። ዐይኖቹን ለሰኮንድ ጨፍኖ ሲገልጣቸው ዶክተር ሔልሲንገር መቆንጠጫውን መቀስ ይዞ አጠገቡ ቆሞ ነበር። “ይኸው እንቀጥላለን!” መቆንጠጫ የሚመስለውን መቀስ ሮበርት ቁስል ውስጥ ከተተው። ሮበርት ከሕመሙ ከባድነት የተነሳ እሪታውን አቀለጠው። ብሩሕ የሆነ የብርሃን ብልጭታ ዐይኖቹ ላይ በራበት።

“እርሳሱ ወጥቷል!” አለ ዶክተር ሔልሲንገር።

ሮበርት ለተወሰነ ጊዜ ባለበት ቦታ እየተንዘፈዘፈ ተቀምጦ በጥልቀት እየተነፈሰ እንደገና ራሱን ለመቆጣጠር ሞከረ።

ዶክተር ሔልሲንገር በትኩረት እያየው.....“ደህና ነህ?” አለው።፤ መልስ ለመስጠት ሮበርት የተወሰነ ጊዜ ወሰደበት።

“አዎን! በል ጠግነው።”

ዶክተሩ ቁስሉ ላይ ፔሮክሳይድ (ማጠቢያ መድኀኒት) ሲጨምርበት ከሕመሙ የተነሳ ሮበርት እንደገና ሕሊናውን ሊስት ተቃረቦ ጥርሱን ነከሰ። “ቆይ አሁን መጨረሳችን ነው.....እግዚአብሔር ይመስገን ይኸው አስከፊው ጉዳይ ተፈጸመ” አለና ዶክተሩ ቁስሉን መሸፈን ጀመረ።

“ጃኬቴን ሰጠኝ!” አለ ሮበርት።

ዶክተር ሔልሲንገር በመደነቅ ተመለከተው። “አሁን ከዚህ መውጣት አትችልም። ሌላው ቀርቶ መራመድ እንኳ አትችልም።”

“ጃኬቴን አቀብለኝ።” ድምጹ በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ንግግሩ በችግር ነበር የሚሰማው። ዶክተሩ ጃኬቱን ለማምጣት ክፍሉን አቋርጦ ሲሄድ ሮበርት ይመለከተዋል። ልክ ሁለት ዶክተር የሚያይ ነበር የመሰለው።

“በጣም ብዙ ደም ስለፈሰሰህ ከዚህ መውጣት በጣም አደገኛ ነው የሚሆንብህ!” ሲል ዶክተሩ አሰጠነቀቀው።

@BOOKALEM

'መቆየቱ ደግሞ ለኔ የበለጠ አደገኛ ነው'አለ በሐሳቡ። ጃኬቱን በጥንቃቄ ለበሰና ተነስቶ ለመቆም ሞከረ። እግሮቹ መብረክረክ ሲጀምሩ ቶሎ ብሎ የጠረጴዛውን ጠርዝ ያዘው።

"በፍጹም አትወጣም!" ሲል ዶክተሩ አሰጠነቀቀው። ሮበርት የደበዘዘውን የዶክተሩን ምስል ተመለከተና ..... "እወጣዋለሁ" አለው። ነገር ግን ገና ከዚህ ክፍል እግሩ እንደወጣ ዶክተር ሔልሲንገር ስልኩን እንደሚያነሳ ያውቃል። የሮበርት ዐይኖች ዶክተሩ የተጠቀመበት ፕላስተር ላይ አረፉ።

ግልፅ በሆነ የማስጠንቀቂያ ድምፅ "ተቀመጥ!" አለው ዶክተሩን።

"ለምን? ምን ልታደር.....?"

"ተቀመጥ!"

ሔልሲንገር ወንበሩ ላይ ሲቀመጠ ሮበርት የፕላስተሩን ጥቅል አነሳ። ጠቀሜታ የለውም። መጠቀም የሚችለው በአንድ እጁ ብቻ ነው።

ሰፊውን ፕላስተር እየተረተረ ወደ ዶክተር ሔልሲንገር ሄደና "ፀጥ ብለህ ከተቀመጥክ ምንም ጉዳት አይደርስብህም!" አለው። የፕላስተሩን ጫፍ የወንበሩ እጀታ ላይ አሰረና የዶክተሩን እጅ ዙሪያውን ከወንበሩ እጀታ ጋር ይጠመጥም ጀመር።

"ይህ አላስ....."

"አፍክን ዝጋ!" ሮበርት ዶክተሩን ከወንበሩ ጋር ማሰሩ ሕመሙን ሁሉ እነደገና ይቀሰቅስበት ጀመር። ዶክተሩን በፀጥታ ተመለከተውና....."ሕሊናዬውን አልሰትም!" አለው። ከጨረሰ በኋ ግን ሕሊናውን ስቶ ወደቀ።

ሕዋው ውስጥ እየተንሳፈፈ ነበር። በነጭ ዳመናዎች ውስጥ ከብደት የለሽ ሆኖ በሰላም እየተንሳፈፈ ነበር። "ንቃ!"። ግን ለመንቃት አልፈለገም። ይህ በጣም ድንቅ የሆነ ስሜት ዘለዓለም እንዲቀጥል ፈለገ። "ንቃ!" አንድ ጠጣር ነገር ጎኑን ሲጫነው ተሰማው። ዐይኖቹ እንደተጨፈኑ እጁን የጃኬቱ ኪስ ውስጥ ከተተና ያዘው። ክሪስታሉ ነበር። ወደ እንቅልፉ ተመለሰ።

ሮበርትን ለስላሳና እውነተኛ የሆነ የሴት ድምጽ ነበር የሚጠራው። እጅግ በጣም የሚያምር ደረቅ ሳር ላይ የተቀመጠ ሲሆን አየሩ ደግሞ በሙዚቃ ተሞልቷል። በሰማዩ ላይ ደግሞ ብሩሕ ብርሃን ይታያል። አንዲት ሴት ወደ እርሱ እየመጣች ነው። ረዘም ያለች ውብ ሴት ስትሆን ረጋ ያለች የእንቁላል ቅርጽ ያለው ፊት ያውም ብርሃን በውስጡ ማሳለፍ የሚችል የሚመስል ገጽታ ያላት፤ እንደ ሀጫ በረዶ የነጣ ረዥም ቀሚስ የለበሰች ስትሆን ድምጿ ረጋ ያለና ቀስ ብሎ የሚሰማ ነው።

"ካሁን በኋላ ማንም አይጎዳህም ሮበርት። ወደኔ ና! እየጠበቅኩህ ነው!"

ሮበርት ዐይኖቹን በቀስታ ከፈታቸው። ረዘም ላለ ጊዜ ተጋድሞ ቆየና በቀስታ ቀና ብሎ ተቀመጠ። መንፈሱ በድንገተኛ እርካታና መነሳሳት ተሞልቷል። አሁን አሥራ አንደኛዋ ምስክር ማን እንደሆነችና የት እንደሚያገኛት በትክክል ተረዳ።

@BOOKALEM

ምዕራፍ አርባ ዘጠኝ

ሮበርት ዶክተሩ ቢሮ ውስጥ ሆኖ ለአድሚራል ዊታከር ስልክ ደወለለት።

"አድሚራል! እኔ ሮበርት ነኝ።"

"ሮበርት! ምንድነው እነሱ የነገሩኝ?"

"አሁን ስለሱ ግድ የለም አይጨነቁ አድሚራል። አሁን የእርሶን ዕርዳታ እፈልጋለሁ ። ለመሆኑ ጃኑስ የሚባል ስም ሰምተው ያውቃሉ?"

አድራሚሉ በቀስታ"....."ጃኑስ?" የለም በፍጹም አልሰማሁም!" አለ።

ጃኑስ በአሁኑ ጊዜ ንፁሃን ሰዎችን በመግደል ላይ ያለ አንድ ዐይነት ምሥጢራዊ ድርጅት በመምራት ላይ መሆኑን ደርሼበታለሁ። እኔንም ለመግደል እየሞከረ ነው። ይህን ሰው ላቆመው ይገባል! አለ ሮበርት።

"እንዴት ነው ልረዳህ የምችለው?"

"ከፐሬዚዳንቱ ጋር መገናኘት እፈልጋለሁ ። ስብሰባ ሊያዘጋጁልኝ ይችላሉ?"

ከአጭር ጊዜ ዝምታ በኋላ አድሚራሉ መልስ ሰጠ። "አዎ! እርግጠኛ ነኝ እችላለሁ" አለ።

"ከዚህም የበለጠ ነገር አለ። በዚህ ነገር ውስጥ ጄነራል ሒሊያርድ አለበት።"

"ምን?.....እንዴት?"

"እና ሌሎችም አሉበት። አብዛኛዎቹ የአውሮፓ የስለላ ድርጅቶች በዚህ ሴራ ውስጥ በአባሪነት አሉበት። አሁን ከዚህ የበለጠ ልገልጽልዎት አልችልም። ከእርስዎ የምፈልገው ለጄነራል ሒሊያርድ ደውለው ሌላ ኦሥራ አንደኛ ምስክር ማግኘቴን እንዲነግሩልኝ ነው።"

"አልገባኝም። ኦሥራ አንደኛ ምስክር ለምን?

"አዝናለሁ አድሚራል። አሁን ልነግርዎት አልችልም። ነገሩን ሒሊያርድ ያውቀዋል። ስዊዘርላንድ ውስጥ እንድንገናኝ እፈልጋለሁ ።"

"ስዊዘርላንድ?"

"ኦሥራ አንደኛው ምስክር የት እንደሚገኝ የማውቀው እኔ ብቻ መሆኔን ንገሩት። አንድ የተሳሳተ እርምጃ ከወሰደ ስምምነቱ እንደሚሰረዝ ንገሩት። ዶልደር ግራንድ ሆቴል የእንግዳ መቀበያው ባንኮኒ ላይ ሄዶ አንድ ማስታወሻ እንዲወስድ ንገሩት። እንደዚሁም ከጃኑስ ጋር ስዊዘርላንድ ውስጥ በግል ለመገናኘት እንደምፈልግ ንገሩት።"

"ሮበርት እርግጠኛ ነህ የምታደርገውን ነገር ታውቃለህ?"

"የለም ጌታዬ! እርግጠኛ አይደለሁም። የሆነው ሆኖ ያለኝ አማራጭ ይህ ብቻ ነው። አሁን ያለሁበት ሁኔታ ለድርድር የማይቀርብ መሆኑን ለጄነራል

@BOOKALEM

ሒሊያርድ ንገሩት። አንደኛ ወደ ስዊዘርላንድ አስተማማኝ የሆነ የማለፊያ መንገድ እሻለሁ።
ሁለተኛ ጄነራል ሒሊያርድና ጃኑስ እዚያው እንዲያገኙኝ እፈልጋለሁ። ሦስተኛ ከዚህ በኋላ ከዩናይትድ ስቴት ፕሬዚዳንት ጋር ስብሰባ ማድረግ እፈልጋለሁ ።"

"ማድረግ የምችለውን ነገር ሁሉ አደርጋለሁ ሮበርት። በምን መንገድ ነው ላገኝህ የምችለው?"

"እኔ እደውልልዎታለሁ። ለመሆኑ ምን ያህል ጊዜ ነው የሚፈልጉት?"

"አንድ ሰዓት ያህል ስጠኝ።"

"እሺ።"

"እና ሮበርት....."

በጄነራሉ ድምጽ ውስጥ ያለው ስጋት ተሰማው። "አቤት ጌታዬ?"

"ተጠንቀቅ!"

"አይጨነቁ ጌታዬ። ከዚህም ከበለጠ አደጋ ተርፌአለሁ። ያስታውሳሉ?"

ከአንድ ሰዓት በኋላ ሮበርት እንደገና ከአድሚራሉ ጋር እየተነጋገረ ነበር።

"ስምምነት አግኝተሃል። ጄነራል ሒሊያርድ በአሥራ አንድኛው ምስክር ዜና የተሸበረ ይመስላል። ባንተ ላይ ምንም ዐይነት ጉዳት እንደማይደርስብህ ቃል ገብቶልኛል። ነገ ጠዋት ወደ ስዊዘርላንድ በአውሮፕላን ይመጣል።"

"ጃኑስስ?"

"ጃኑስም አብሮ በአውሮፕላን ይመጣል።"

ሮበርት ታላቅ እፎይታ ተሰማው። "እና ፕሬዚዳንቱስ?"

"እኔ እራሴ አነጋግራቸዋለሁ። ረዳቶቻቸው አንተ ዝግጁ በሆንክበት ጊዜ ስብሰባውን ያዘጋጁልሃል። ጄነራል ሒሊያርድ ደግሞ የምትሄድበት አውሮፕላን....."

"በፍጹም!" አለ ሮበርት። አሁን ያለሁት ፓሪስ ውስጥ ነው። እራሴ የማሽከረክረው መኪና እፈልጋለሁ። መኪናው ሞንቴ ፓርነስ በሚገኘው ሊትሬ ሆቴል ፊት ለፊት ቆሞ እንዲጠብቀኝ እንዲያደርግ እፈልጋለሁ።"

"አስፈጽምልሃለሁ።"

"አድሚራል?"

"አቤት ሮበርት?"

ድምጹን ለመቆጣጠር እየተቸገረ....."አመሰግናለሁ!" አለ።

አሁንም ሮበርት የሚሰማው ሕመም በጣም ጠንካራ ስለነበር በሩ ሊትሬ ጎዳና ላይ በዝግታ ይራመዳል። በዝግታና በጥንቃቄ። ከሆቴሉ ሕንጻ ፊት ለፊት አንድ ጥቁር ሜርሰዲስ መኪና ቆሟል። መኪናው ውስጥ ማንም አልነበረም። ከመንገድ ባሻገር አንድ ጥቁርና ነጭ የተቀባ የፖሊስ መኪና ውስጥ ሁለት የደንብ ልብስ የለበሱ ፖሊሶች ተቀምጠዋል። በመንገዱ ጠርዝ የእግረኛ መቆሚያ ሥፍራ ላይ ደግሞ ሁለት

@BOOKALEM

የሲቪል ልብስ የለበሱ ሰዎች ሮበርት ወደ ሆቴሉ ሲቃረብ በጥንቃቄ ይመለከቱታል። ሰዎቹ የፈረንሳይ ፀጥታ ፖሊስ ሠራተኞች ናቸው።

ሮበርት መተንፈስ አቅቶት ነበር። ልቡ ከሚገባው በላይ ይመታል። ወጥመድ ውስጥ እየገባ ይሆን? ያለው ብቸኛ ዋስትና አሥራ አንደኛው ምስክር ነው። ጄነራል ሒሊያርድ አምኖት ይሆን? በቂስ ነበር?

ሮበርት ሰዎቹ አንዳች ዐይነት እንቅስቃሴ ያደርጉ እንደሆነ እየተቆጣጠረ በቀጥታ ወደ ሜርሰዲሱ አመራ። ነገር ግን ሰዎቹ ባሉበት ቦታ ተገትረው ይመለከቱት ነበር።

ሜርሰዲሱን ተጠጋና በሾፌሩ መቀመጫ በኩል ዞሮ ወደ ታች ተመለከተ። ቁልፉ ማስነሻው ላይ እንደተሰካ ተትቷል። በሩን ከፍቶ መኪናው ውስጥ ገባና የሾፌሩ ወንበር ላይ ሲቀመጥ የሰዎቹ ዐይኖች እላዩ ላይ ተለጥፎ እንደነበር ተሰምቶታል። ለተወሰነ ደቂቃ ባለበት ተቀምጦ ቁልፉን በትኩረት ይመለከተው ጀመር። ምናልባት ጄነራል ሒሊያርድ አድሚላር ዊታከርን አታሎት ከሆነ ሁሉም ነገር በአሰቃቂ ፍንዳታ የሚደመደምበት ወቅት አሁን ነው።

በረዥሙ ተነፈሰና በግራ እጁ የማስነሻውን ቁልፍ አዞረው። ሞተሩ ነፍስ ዘርቶ ተነሳ። የጸጥታ ሠራተኞቹ ባሉበት ቦታ ተገትረው ሜርሰዲሱን እየነዳ ሲሄድ በፀጥታ ተመለከቱት። ልክ በመንገዱ መንታ መገናኛ ላይ ሲደርስ አንድ የፖሊስ መኪና ቀደመውና ከፊቱ ገባበት። ለተወሰነ ጊዜ ሮበርት 'በቃ ሊያስቆሙኝ ነው' እያለ አሰበ። ነገር ግን የፖሊስ መኪናው ቀዩን መብራት ብልጭ ድርግም እያደረገ ሲያበራለት መንገዱን አጨናንቆት የነበረው ትራፊክ እየገለጠለት ሄደ። 'አሃ! ለካ እያጀቡኝ ነው' አለ።

ከመኪናው አናት በላይ ደግሞ የሄሊኮፕተር ድምጽ ተሰማውና ወደ ላይ ሲመለከት ሄሊኮፕተሩ የፈረንሳይ ፖሊስ አርማ እንዳለው ተረዳ። ጄነራል ሒሊያርድ ሮበርት በደህና ስዊዘርላንድ እንዲደርስ አሰፈላጊውን ትብብር ሁሉ እያደረገለት ነው። "አምን!" አለ ሮበርት በሐሳቡ። ‹አምን የመጨረሻውን ምስክር ካሳየሁት በኋላ እገድለዋለሁ ብሎ ያስባል። ነገር ግን እራሱ ያላሰበውና ያልጠበቀው ነገር ይደርስበታል።'»

ልክ ከቀኑ በ10.00 ሰዓት ስዊስ ድንበር ላይ ሮበርትን አጀቦ የመጣው የፈረንሳይ ፖሊስ መኪና ወደ መጣበት ተመሰና በምትኩ የስዊስ መንግሥት ፖሊስ መኪና በአጃቢነት ተተካለት። ጉዞውን ከጀመረ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘና ማለት ጀመረ። 'እግዚአብሔር ይመስገን አድሚራል ዊታከር በከፍተኛ ሥፍራዎች ላይ ወዳጆች አሉት' አለ። አሁን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ራሳቸው ሮበርትን ለስብሰባ ስለሚፈልጉት ጄነራል ሒሊያርድ ዝንቡን እንኳ እሽ ለማለት አይቃጣም። በሐሳቡ ነጭ ልብስ ወደ ለበሰችው ሴት ሄደ። ልክ በዚህ ቅጽበት ድምጿን ሰማው። መኪናው ውስጥ ድምጿ ማስተጋባት ጀመረ። "ፍጠን ሮበርት። ሁላችንም እየጠበቅንህ ነው!"

@BOOKALEM

'ሁላችንም? ሌሎችም አሉ ማለት ነው። እስቲ በቶሎ ደርስበታለሁ' አለ በሐሳቡ።

ዙሪክ ውስጥ ዶልደር ግራንድ ሆቴል ላይ ቆም አለና ለጄነራልድ ሒሊያርድ ማስታወሻ ጽፎ ተወለት። እባክህን "ጄነራል ሒሊያርድ እኔን ሲጠይቅህ ይህንን ማስታወሻ ስጥልኝ!" አለው የሆቴሉን ጸሐፊ።

"እሺ ጌታዬ!"

ከሆቴሉ እንደወጣ በቀጥታ ያጅበው ወደነበረው የፖሊስ መኪና አመራ። መኪናው ውስጥ ለተቀመጠው ፖሊስ ዝቅ አለና....."ካሁን በኋላ አጅብ አልፈልግም! ብቻዬን ነው የምጓዘው" አለው።

ፖሊሱ ጥቂት አመነታና....."በጣም ጥሩ ኮማንደር" አለው።

ሮበርት መኪናውን አስነሳና ከሌላ ዓለም የመጣው ያልታወቀ በራሪ አካል ወደተከሰከሰበት ቦታ ወደ ኡተንዶርፍ መንገዱን ቀጠለ። መኪናውን እያሽከረከረ በዚህ በራሪ ነገር ምክንያት ስለተፈጠሩት አሳዛኝ ድርጊቶችና ስለጠፋው ሕይወት ሁሉ ያሰላስል ጀመር። ሐንስ ቤከርማንና አባ ፓትሪኒ። ላስሎ ቡሽፌኬትና ፍሪቲዝ ማንዴል። አልጋ ሮማንቻንኮና ኬቨን ፓርከር። ሙት! በሙሉ ሙታን! 'ጃኑስን ለማየት እፈልጋለሁ' ሲል በሐሳቡ ተናገረ። 'ዐይኖቹን ማየት አለብኝ።' ሮበርት መኪናውን እያሽከረከረ ሲሄድ መንደሮቹ ወደ ኋላ እየበረሩ የሚያልፉ ይመስሉ ነበር። ቀደም ሲል እዚህ ሥፍራ ላይ የተጀመረው ሽብርና የደም መፍሰስ አሁን በግዙፉ የአልፕስ ተራራ ውበት ተዋጠ። ሮበርት ወደ ቱን ከተማ እየተቃረበ በመጣ ቁጥር መላ አካላቱን የመሸበር ስሜት ወረረው። ከፊቱ እሱና ሐንስ ቤከርማን የአየር ንብረት ባሎኑን ወድቆ ያገኙበትና እስካሁን ያሳለፈው ቅዠት ሁሉ የተጀመረበት ሥፍራ ነው። መኪናውን ወደ መንገዱ ጠርዝ አውጥቶ አቆመና ሞተሩን አጠፋው። መኪናው ውስጥ እንደተቀመጠ በፀጥታ ጸልዮ ሲያበቃ ከመኪናው ወጣና መንገዱን አቋረጠ መስኩ ውስጥ ገባ።

ሮበርት በመስኩ ላይ በሚራመድበት ጊዜ በሺህ የሚቆጠር ትውስታ በአዕምሮው ይመላለስበት ጀመር። በመጀመሪያ ትዝ ያለው ነገር ቢኖር ከንጋቱ አሥር ሰዓት የተቀበለው የስልክ ጥሪ ነው። 'ፎርት ሚድ በሚገኘው የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል መሥሪያ ቤት ጄነራል ሒሊያርድ ዘንድ ከንጋቱ 0600 ሰዓት ሪፖርት እንድታደርግ ታዘሃል። መልዕክቱ ገብቶሃል ኮማንደር?'

በወቅቱ መልእክቱን ምን ያህል በትንሹ እንደተረዳው የገባው አሁን ነው። የጄነራል ሒሊያርድን ንግግር አስታወሰ። 'እነዚያን ምስክሮች ፈልገህ ማግኘት አለብህ። እያንዳንዳቸውን።' እናም አሰሳው ሮበርትን ከዙሪክ ወደ በርን፤ ለንደን፤ ሙኒክ፤ ሮም እና ኦሪቬቶ፤ ከዋኮ ወደ ፎርት ስሚዝ፤ ከኪዬቭ ወደ ዋሺንግተንና ቡዳፔስት አንከራትቶታል። እናም ይህ የተረገመ አሰሳ እዚህ የተጀመረበት ሥፍራ ላይ ተፈጸመ።

@BOOKALEM

እሷም እየጠበቀችው ነበር። ሮበርት ልክ በሕልሙ እንደተመለከታት ነበር ያገኛት። እናም እርሱም ወደ እርሷ እርሷም ወደ እርሱ ይሄዱ ጀመር። ብሩህ አንጸባራቂ ፈገግታ ፊቷ ላይ ተላብሳ ወደ ሮበርት ስትመጣ በአየር ላይ የምትንሳፍ ትመስል ነበር።

"ስለመጣህ አመሰግናለሁ ሮበርት።"

በሚገባ ስምቷታል ወይንስ ሐሳቧን ነው እየሰማ ያለው? አንድ ሰው እንዴት ከሌላ ዓለም ከመጣ ፍጡር ጋር ሊያወራ ይችላል?

"መምጣት ነበረብኝ!" አላት እንደዋዛ አድርጎ። ስለሁኔታው እውነትነት ማመን አቅቶታል። 'እዚህ ሥፍራ ቆሜ ከሌላ ዓለም ከመጣች ፍጡር ጋር እያወራሁ ነው። መፍራትና መሸበር ይገባኝ ነገር። ነገር ግን በሕይወቴ ሙሉ እንዲህ ዐይነት የተዝናና መንፈስ አድሮብኝ አያውቅም።' "ላስጠነቅቅሽ ይገባኛል!" አላት ሮበርት። በአንቺ ላይ ጉዳት ለማድረስ የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች ወደዚህ እየመጡ ነውና ከመድረሳቸው በፊት መሄድ ይገባሻል።"

"መሄድ አልችልም።"

ሮበርት ምክንያቷን ተረዳላት። በግራ እጁ ኪሱ ውስጥ ገባና ከሪስታሉን የያዘውን ብረታማ ዕቃ አውጥቶ ሰጣት።

ፊቷ በደስታ በራ። "አመሰግናለሁ ሮበርት!" አለችው።

"አሁን የሚሆነው ምንድነው?" አላት።

"አሁን ከጓደኞቼ ጋር መገናኘት እችላለሁ። ከዚያም ወደዚህ ይመጡልኛል" ስትል መለሰችለት።

'በዚህ ንግግሯ ውስጥ አንድ ዐይነት መጥፎ መልዕክት ወይም ምልክት ነበረበት?' ሮበርት አሁንም የጄነራል ሒሊያርድን ንግግር አስታወሰ። 'ይህችን ፕላኔታችንን ይዘው እኛንም በባርነት ቀንበር ሊያገቡን ይሻሉ።' ጄነራል ሒሊያርድ እውነቱን ቢሆንስ? ትክክል ቢሆንስ? ምናልባት ፍጡራኑ መሬትን የመያዝ ፍላጎት ቢኖራቸውስ? ማነው ሊያቆማቸው የሚችለው?', ሮበርት ሰዓቱን ተመለከተ። አሁን የጃኑስና የጄነራል ሒሊያርድ መድረሻ ሰዓት ነው። እናም ሮበርት ልክ ይህንኑ በሚያስብበት ወቅት አንድ ግዙፍ ሄሊኮፕተር በስተሰሜን በኩል ብቅ ሲል ድምጹን ሰማው።

"ጓደኞችህ እየመጡ ነው!" አለችው።

'ጓደኞች?' እነሱ የለየላቸው ጠላቶቹ ስለሆኑ በነፍስ ገዳይነታቸው ሊያጋልጣቸውና ሊያጠፋቸው ቆርጦ ተነስቷል። ሄሊኮፕተሩ መሬት ላይ ሲያርፍ ሳሩና አበቦቹ በነፋሱ ኃይል ይርገበረቡ ጀመር። አሁን ከጃኑስ ጋር ፊት ለፊት የሚተያይበት ወቅት ደረሰ። የመተያየቱን ነገር ሲያስበው ግደል ግደል የሚል ደም ፍላት ያዘው። የሄሊኮፕተሯ በር ተከፈተ።

ሱዛን ከሄሊኮፕተሩ ወጣች!

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሃምሳ

ከምድር እጅግ በጣም ከፍ ብላ በምትንሳፈፈው እናት የጠፈር መንኮራኩር ውስጥ ከፍተኛ ደስታ ተፈጠረ። በመቆጣጠሪያ መሣሪያዎቹ ላይ ያሉት መብራቶች በሙሉ አረንጓዴ ማብራት ጀመሩ።

"አገኘናት!"

"አሁን መፍጠን አለብን።"

ግዙፏ የጠፈር መንኮራኩር እጅግ በጣም ወደ ታች እርቃ ወደምትገኘው መሬት ተምዘገዘገች።

@BOOKALEM

ምዕራፍ ሃምሳ አንድ

ለአንድ ለተወሰነ ቅጽበት ጊዜ ባለበት ቦታ ፀጥ ብሎ ቆመ። ቀጠለናም ሺህ ጊዜ ተፈረካክሶ ብትንትኑ ወጣ። ሱዛን ከሄሊኮፕተሩ ውስጥ ስትወጣ ሮበርት ባለበት ቦታ ደንዝዞ ተመለከታት። እሷም ባለችበት ቦታ ለተወሰኑ ሴኮንዶች ቆም አለችና ወደ ሮበርት መንቀሳቀስ ስትጀምር ከኋላዋ ቆሞ የነበረው ሞንቴ ባንክስ ቀብ! አድርጎ ያዘና ወደ ኋላ አስቀራት።

"ሮበርት ሩጥ! አምልጥ! ሊገድሉህ ነው!" ስትል ጮኸች።

ሮበርት ወደ ሱዛን መራመድ በጀመረበት ቅጽበት ጄነራል ሒሊያርድና ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን ከሄሊኮፕተሩ ወጡ።

"እኔ እዚህ ነኝ ኮማንደር። የስምነታችንን ቃል አክብሬአለሁ" አለና ጀኔራል ሒሊያርድ ወደ ሮበርትና ነጭ ልብስ ወደ ለበሰችው ሴት መጣ።

"አሥራ አንደኛዋ ምስክር ይህች ሴት ናት ብዬ ገምታለሁ። የጠፋችው የሴላ ዓለም ፍጡር። ማራኪ ሆና እናገኛታለን ብዬ አስባለሁ። የዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በመጨረሻ ተፈፀመ!"

"እስካሁን አልተፈጸመም። ጃኑስን አመጣዋለሁ ብለህ ነበር።"

"አ! አዎን። ጃኑስም አንተን ለማየት እንደሚሻ አሳውቋል።"

ሮበርት ፊቱን ወደ ሄሊኮፕተሩ መለስ ሲያደርግ የመውጫው በር ላይ አድሚራል ዊታከርን ቆሞ ሲያየው ባለበት ቦታ ደንዝዞ ዐይኑን ማመን አቅቶት አድሚራሉን ይመለከተው ጀመር።

"እኔን ለማየት ጠይቀህ ነበር ሮበርት?"

"ሮበርት ዓለም በላዩ ላይ የተደፋችበት መስሎ ታየው። "ለምን? ለምን? ስለእግዚአብሔር ለምን?"

አድሚራሉ ወደ ሮበርት ተንቀሳቀሰ። "አይገባህም ሮበርት። ይገባሃል? በፍፁም አይገባህም። አንተ በጣም ጥቂት ለሆኑ ረብ የለሽ ሕይወት ነው የምትጨነቀው። እኛ ደግሞ የምንጨነቀው ይህችን ዓለም ለማዳን ነው። ይህች ዓለም ይህች መሬት የምትገባው ለኛ ነው።"

አድሚራሉ ነጭ ልብስ ወደ ለበሰችው ሴት ዘወር አለ። "እናንተ ፍጥረታት...ጦርነትን የምትሹ ከሆነ ታገኙታላችሁ። እናም ድል እንመታችኋለን!" አላትና ወደ ሮበርት ዘወር አለ። "አንተ ደግሞ ከዳህኝ። ልክ እንደልጄ ነበርክ። የልጄን የኤድዋርድን ሥፍራ ሰጠሁህ። አገርህን ለማገልገል የሚያስችል ዕድል ሰጠሁህ። እናስ

@BOOKALEM

እንዴት አድርገህ ነበር የከፈልከኝ? እያለቀስክ መጣህና እሚስትህ ጉያ ስር ለመሆን እንድትችል ከሚስትህ እንዳትርቅ ጠየከኝ።" ጀነራሉ ይህን ሲናገር ድምጹ በጥላቻ ተሞልቶ ነበር። "የኔ ልጅ ቢሆን ኖሮ እንዲህ አያደርግም ነበር። አንተ ልትሰጥ የምትችለው ፋይዳ ምን ያህል የተምታታ እንደነበር ቀደም ብዬ ማወቅ ይገባኝ ነበር።"

ሮበርት መንቀሳቀስ ተስኖት ለመናገር ልሳኑን ይዞት ቀረ። "ቢሆንም ግን አሁንም ባንተ ላይ ያለኝ እምነት ባለማለቁ ጋብቻህ እንዲፈረስ አደረኩ። ግን....."

"እርሶ? ጋብቻዬን አፈረሱ?"

ሲ.አይ.ኤ "ቀበሮውን" እንድታሳድድ የላከህ ጊዜ ታስታውሳለህ? ይህንን ተልዕኮ ያዘጋጀሁት እኔው ራሴ ነበርኩ። ወደ ልቦናህ ሊመልስህ ይችላል ብዬ ገምቼ ነበር። አንተም በተልዕኮህ ወደክ። ምክንያቱም "ቀበሮው" የሚባል አልነበረምና። እኔ ያቃናሁህና ከመካከላችንም አንዱ ነህ ብዬ አሰቤ ነበር። ከዚህ በኋላ ኤጀንሲውን ለመልቀቅ እንደምትፈልግ ነገርከኝ። ልክ በዚህ ወቅት ነበር አንተ ፈጽሞ አርበኛ ያለመሆንህን የተረዳሁት። መደምሰስ መወገድ የሚገባህ መሆኑን ያወኩት በዚህ ወቅት ነው። ከመወገድህ በፊት ግን እኛ ለምናራምደው ዓላማ አገልግሎት መስጠት ይገባሃል።"

"ዓላማ? ንጹሓን ሰዎችን መግደል? እርሶ ዕብድ ነዎት።"

"ፍርሃትና ሽብርን እንዳይነዙ ለማስቆም እንዲቻል መገደል ነበረባቸው። አሁን እንግዶቹን የሌላ ዓለም ሰዎች ለማቆም ዝግጁ ነን። እኛ የምንፈልገው በጣም ትንሽ ጊዜ ነበር። እሱንም አንተ ሰጠህን።"

ነጭ ልብስ የተጎናፀፈችው ሴት ምንም ሳትናገር ባለችበት ሥፍራ ቆማ ሰዎቹ የሚናገሩትን ስታዳምጥ ቆየችና በመጨረሻም አስተሳሰቧን ሜዳው ላይ በቆሙት ሰዎች አእምሮ ውስጥ እንዲሰርጽ አደረገች።

"እኛ ወደዚህ የመጣነው የምትኖሩባትን የራሳችሁን ፕላኔት እንዳታጣፏት ለመከላከል ነው። ሁላችንም የአንድ ጠፈር አባላት ነን። እስቲ ወደ ላይ ተመልከቱ።"

ሁሉም ራሳቸውን ወደ ሰማይ ቀና አደረጉ። እጅግ በጣም ግዙፍ የሆነ ነጭ ደመና ነበር። ደመናውን በዐይኖቻቸው እያዩት መልኩን መቀየር ጀመረና ወደ ዋልታ በረዶ ክምርነት ተለወጠ። በረዶው መቅለጥ ጀመረ። እናም ውሃው በመላው ዓለም የሚገኙ ወንዞችና ውቅያኖሶች ውስጥ መሙላት ጀመረ። ለንደን፤ ሎስ ኤንጀለስ፤ ኒው ዮርክ እና ቶኪዮን እንዲሁም በወደቦች ዳርቻ ላይ የተቆረቆሩ ታላላቅ ከተሞችን አጥለቀለቃቸው። እንደገናም ትዕይንቱ ጨርሶ የወደመ የእርሻ መሬትነት ተለወጠ። በገነተረ የፀሓይ ኃይል የተቃጠለ ጥራጥሬ፤ ሜዳው ላይ የተከመረ የከብቶችና የእንስሳት ጥንብ ታያቸው። አሁንም ትዕይንቱ ዐይናቸው ላይ ተለወጠ። እመፅ በቻይና፤ ረሃብና ችጋር በሕንድ፤ በመጨረሻም አጥፊ ከሆነ የኒውክሊየር ጦርነት በኋላ ሰዎች በዋሻ ውስጥ ሲኖሩ ታያቸው። በኋላም ትዕይንቱ ሁሉ ቀሰ እያለ ከዐይናቸው ላይ ጠፋ።

@BOOKALEM

አድናቆትና ፍርሃት የተሞላበት ፀጥታ ለተወሰነ ጊዜ ሰፈነ። "አሁን በያዛችሁት ጉዞ ከቀጠላችሁ የወደፊት ዕጣችሁ ይህ ነው!" አለቻቸው።

መጀመሪያ ራሱን መቆጣጠር የቻ ለው አደሚራል ዊታከር ነበር። "ይህ የሰውን አዕምሮ የማደንዘዝና የመቆጣጠር ዘዴ ነው" አለ። "ሌሎች ማራኪ የሆኑ የማታለያ ዘዴዎችንም ልታሳይን እንደምትችይ እርግጠኛ ነኝ" አላትና ወደ እንግዳዋ ሴት እየተጠጋ....."ወደ ዋሺንግተን ከኔ ጋር አወሰድሻለሁ። ካንቺ የምንፈልገው በርካታ መረጃ አለ!" አላት። አድሚራሉ ይህን ተናግሮ ወደ ሮበርት ዞረ። "ያንተ ነገር አበቃ!" አለውና ወደ ፍራንክ ጆንሰን ዞሮ....."ግደለው!" አለው። ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን ሽጉጡን ከማህደሩ ውስጥ አወጣ። ይህን ግዜ ሱዛን ከሞንቴ ባንክስ እጅ አምልጣ እየሮጠች ሮበርት አጠገብ ቆመችና...."የለም! አይሆንም!" ስትል ጮኸች።

ኮሎኔል ጆንሰን ሽጉጡን አድሚራሉ ላይ ደገነና....."አድሚራል በቁጥር ስር ውለሃል!" አለው።

አድሚራል ዊታከር አፍጥጦ እየተመለከተው ነበር። "ምን.....ምንድነው የምታወራው? ግደለው ብዬ ነግሬሃለሁ። አንተም ከኛ መካከል አንዱ ነህ።"

"ተሳስተሃል። በፍጹም የናንተ አባል ሆኜ አላውቀም። ከረዥም ጊዜ በፊት ድርጅታችሁ ውስጥ ሰርጌ የገባሁት ኮማንደር ቤላሚን ለመግደል ሳይሆን ለማዳን ነው!" ወደ ሮበርት ዞሮ አለና....."አዝናለሁ በወቅቱ ፈጥኜ ልደርስልህ አልቻልኩም!" አለው።

የአድሚራል ዊታከር ፊት አመድ መሰለ። "ይህ ከሆነ አንተም ትደመሰሳለህ። ማንም ሰው በመንገዳችን ለመቆም አይቻለውም። ድርጅታችን....."

"ከአሁን በኋላ ድርጅት የሚባል ነገር የላችሁም" አለ ጆንሰን አድሚራሉን አቋረጠውና። "አባሎቻችሁ በሙሉ ተከበዋል። ተፈጸመ አድሚራል!" አለው።

ከበላያቸው ሰማዩ በብርሃንና በድምጽ ይርገበገብ ጀመር። ግዙፏ የጠፈር መንኮራኩር ከውስጧ ብሩህ አረንጓዴ ሙብራት እያበራች በቀጥታ ወደነሱ ወረደች።

መሬት ላይ ስታርፍ ፍርሃትና አድናቆት በተሞላበት ፀጥታ ተመለከቷት። ቀጥሎም ከውስጧ ሌላ አነሰተኛ የጠፈር መንኮራኩር ወጣ።... ቀጥሎ ሌላ.....ቀጥሎ ሌላ.....ሰማዩ በሙሉ በበራሪ ዲስኮች ከመሸፈኑም በላይ አየሩ ሁሉ ከተራራ ተራራ በሚያስተጋባ ጥዑም ሙዚቃ ተሞላ። የግዙፏ መንኮራኩር በር ተከፈተና አንድ እንግዳ ፍጥረት ብቅ አለ።

ባለነጭ ልብሷ ሴት ወደ ሮበርት ዘወር አለች። "አሁን መሄዴ ነው!" አለችውና ወደ አድሚራል ዊታከር ጄነራል ሒሊያርድና ሞንቴ ባንክስ እየሄደች....."እናንተ ደግሞ ከኔ ጋር ትሄዳለችሁ!" አለቻቸው።

አድሚራል ዊታከር ወደ ኋላው ሸሸት አለና....."የለም! መሄድ አልፈግም!" ሲል ጮኸ።

@BOOKALEM

“አዎን ምንም ጉዳት አናደርስባችሁም!” አለችና እጇን ወደ ሦስቱ ሰዎች ዘረጋች። ለተወሰነ ግዜ ምንም የተፈጠረ ነገር አልነበረም። ከጥቂት ሰኮንዶች በኋላ ግን ሌሎቹ እየተመለከቱ ሦስቱ ሰዎች በደነዘዘ ሕሊናቸው ወደ ጠፈር መንኮራኩሯ መሄድ ጀመሩ።

“አይሆንም! አለና አድሚራል ዊታከር እሪታውን አቀለጠው። ሦስቱም መንኮራኩሯ ውስጥ ገብተው እስኪሰወሩ ድረስ እሪ... እያሉ ነበር።”

ነጭ ልብስ የለበሰችው ሴት ወደ ሌሎቹ ዘወር አለች። “ምንም ዐይነት ጉዳት አይደርስባቸውም። ብዙ የሚማሩት ነገር ይኖራል። ትምሕርታቸውን ሲጨርሱ ወደዚህ እንዲመለሱ ይደረጋል።” ሱዛን ሮበርትን ጠበቅ አድርጋ ይዛው ነበር።

“ሮበርት! ሰዎች ይህችን የምትኖሩባትን ፕላኔት መግደል እንዲያቆሙ ንገራቸው አስረዳቸው!”

“እኔ አንድ ሰው ብቻ ነኝ።”

“ያንተ ዐይነት በሺህ የሚቆጠሩ አሉ። በየዕለቱም ቁጥራችሁ እየጨመረ ነው። አንድ ቀን የናንተን ዐይነት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ይኖሩና በአንድ ድምጽ መናገር ትችላላችሁ። ይህንን ታደርጋለህ?”

“እሞክራለሁ! እሞክራለሁ።” አላት ደገመና።

“አሁን መሄዳችን ነው። ነገር ግን እናንተን መመልከታችንን አናቋርጥም። እናም ተመልሰን እንመጣለን።”

ባለነጭ ልብሷ ሴት ፊቷን አዞረችና መንኮራኩሯ ውስጥ ገባች። በውስጡ ያሉት መብራቶች ሰማዩን አስኪያበሩት ድረስ እጅግ በጣም ብሩህ እየሆኑ መጡ። እናም በድንገት ያላንዳች ማስጠንቀቂያ ግዙፏ እናት የጠፈር መንኮራኩር በግልገሎቹ በራሪ መንኮራኩሮች ተከታይነት ወደ ሰማይ መጠቁና ከዐይን ተሰወሩ።

‘ሰዎች ይህችን ፕላኔት እንዳይገድሏት ንገራቸው! ትከክል!’› አለ ሮበርት በሐሳቡ። ‘ካሁን በኋላ በቀሪው የሕይወት ዘመኔ ምን እንደምሠራ አወቃለሁ!’ ሱዛንን ተመለከተና ፈገግ አለ።

ጅማሬው!

@BOOKALEM

የደራሲው ማስታወሻ

የህንን መጽሓፍ ለመጻፍ የሚያስችል ግንዛቤ ለማግኘት ከምንኖርባት ዓለም ውጭ የሆነ ተሞክሮ ያላቸው ጠፈርተኞችን የሚመለከቱ በርካታ መጽሓፍትን፤ ሜጋዚኖችን እና የጋዜጣ አንቀጾችን አንብቤአለሁ። ኮሎኔል ፍራንክ ቦርማን የተባለ ጠፈርተኛ ጀሚኒ -7- በተባለች መንኮራኩር በጠፈር ውስጥ ጉዞ ሲያደርግ ያጋጠመውንና ይከተለው የነበረውን አንድ ያልታወቀ በራሪ አካል (ዩ.ኤፍ.ኦ) ፎቶግራፍ አንስቷል። ኔል አርምስትሮንግ ሉፓሎ፣ነበተባለችው መንኮራኩር ጨረቃ ላይ ባረፈበት ጊዜ ሁለት ያልታወቁ የጠፈር መንኮራኩረሮችን ዐይቷል። በዝ አልድሪን የተባለ ጠፈርተኛም ጨረቃ ላይ አንድ ያልታወቀ በራሪ መንኮራኩር ፎቶ አንስቷል። ኮሎኔል ኤል ጎርዲን በ "ፕሮጀክት ሜርኩሪ" በረራው በጣም ግዙፍ የሆነ ያ.በ.አ አውስትራሊያ ፐርዝ ላይ ከማየቱም በላይ ከዚህ በፊት በምድራችን ላይ ተሰምቶ በማያውቅ ያልታወቀ ቋንቋ የተደረገ የንግግር ልውውጥ ለመቅዳት ችሏል።

እነዚህንና ሌሎችንም ሰዎች አነጋግሬ ያረጋገጡልኝ ነገር ቢኖር ታሪኩ ከግልጽ እውነትነት ይልቅ አጠራጣሪ ወይም የሐሰት ዜና መሆኑን እና እነሱም ያ.በ.ኢዎችን በተመለከተ ምንም ዐይነት ገጠመኝ የሌላቸው መሆኑን ነው። ከኮሎኔል ጎርደን ኩፐር ጋር ውይይት ካደረኩኝ ከጥቂት ቀናት በኋላ ስልክ ደወለልኝ። እኔም ጥሪውን መለስኩለት። ነገርግን እንደገና ሰወዬው የማይገኝ ሆነ። ከአንድ ዓመት በኋላ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ኖቬምበር 9 ቀን 1987 ዓ.ም የሚል በኮሎኔሉ የተጻፈና ስለ ያ.በ.አ. ያሚያወሳ ደብዳቤ ለማግኘት ቻልኩ።

እኔም የደብዳቤውን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ስል ለኮሎኔል ኩፐር ስልክ ደወልኩለት። በዚህ ወቅት ፈቃደኛ ሆኖ ተገኘ። ደብዳቤው በትክክል ከርሱ የተጻፈ መሆኑን አረጋገጠልኝ።

እርሱ ራሱ ወደ ሕዋው ባደረጋቸው ጉዞዎች በርካታ የያ.በ.ኢዎችን በረራ ከማየቱም በላይ ሌሎች የእርሱ ብጤ ጠፈርተኞችም ተመሳሳይ የሆነ ገጠመኝ እንዳላቸውና ይህንንም በተመለከተ ከማንም ጋር እንዳይወያዩ ወይም እንዳይናገሩ ማሰጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑን አስረዳኝ። በራሪ ዲስኮች መኖራቸውን የሚያስረዱ በርካታ መጽሓፍት አንበቤያለሁ። እንዲሁም በራሪ ሳህን መሰል መንኮራኩሮችን የሚያሳይ የቪድዮ ፊልም ከመመልከቴም በላይ በ ያ.በ.አ ወደ ሌላ ዓለም ተወስደን ነበር የሚሉ ሰዎችን አዕምሮ በማደንዘዝ ሕክምና (Hypnosiss) የተራቀቁ ሰዎችን ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭና ውስጥም አነጋግሬአለሁ።

@BOOKALEM

ሐኪሞቹ የዚህ ዐይነት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ምርመራዎችን ከማድረጋቸውም በላይ የእያንዳንዱ ተመርማሪ ገጠመኝ በሚያስደነግጥ ሁኔታ ተመሳሳይ ከመሆኑም በላይ ተወሰድን የሚሉት ሰዎች ሁሉ በሰውነታቸው ላይ አንድ ዐይነት የሆነ ምንነቱ የማይታወቅ ምልክት እንደነበረባቸው ይናገራሉ።

አንድ የበራሪ ዲስኮችን ጉዳይ ለመመርመር በ ዩ.ኤስ መንግሥት የተቋቋመ "ብሉ ቡክ ፕሮጀክት" የተባለ ቡድን ኃላፊ የሆነ የአየር ኃይል ጄነራል እንዳረጋገጠልኝ ከሆነ "በራሪ የጠፈር መንኮራኩሮች ወይም እንግዳ የሆኑ የሌላ ዓለም ፍጡራን ስለመኖራቸው ምንም ዐይነት ጠጣር የሆነ ማስረጃ ተገኝቶ አያውቅም" ብሎኛል።

በቲሞቲ ሎርድ ሒል ኖርተን የባሕር ኃይል አድሚራልና ከ 1971–1973 በብሪቲሽ መከላከያ ሚንስትር ስታፍ የተጻፈ "አበቭ ቶፕ ሴክሬት" የተባለ ድንቅ መጽሐፍ መቅድም ላይ የሚከተለውን ጽፏል።

"በከባቢው አየራችን ላይና በምድራችን ላይ የሚታዩት መንኮራኩሮች በሰው ልጅ ለመሠራታቸውና ቁሳዊ ኃይል ለመሆናቸው ሳይንሳዊ ማረጋገጫ በሳይንስ ሊቃውንቶች ሊገኝላቸው ያልቻሉት ነገሮች ለኔ ግራ የሚያጋቡ ሆነው ነው የሚታዩኝ። የነዚህ ነገሮች በርካታ ዕይታዎች ለኔ ተአማኒነታቸው አጠራጣሪ ባልሆኑ ሰዎች ተመስክሯል። አብዛኛዎቹ የዐይን ምስክሮች የፖሊስ መኮንኖች፤ የአየር መንገድ፤ ወይም የአየር ኃይል ፓይለቶችን የመሳሰሉ የሠለጠኑ ተመልካቾች ይገኙባቸዋል።"

በ1933 ዓ.ም አራተኛው የስዊዲሽ በራሪ ጓድ በስካንዲኔቪያ የአየር ክልል ላይ ስለተገኘ ያልታወቀ ምሥጢራዊና ምንም ዐይነት የመለያ ምክት ወይም አርማ የሌለው በራሪ ነገር ምርመራ ጀመረ። በኤፕሪል 31/1934 ዓ.ም ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ሪውተርስዊርድ የሚከተለውን ቃል ለጋዜጠኞች ሰጠ።

"የነዚህ ሁሉ ዘገባዎች ትንተና የሚያሳየው በምሥጢራዊ ወታደራዊ ጦር ሰፈሮቻችን ላይ ሕገ ወጥ የሆነ የአየር ትራፊክ መኖሩን ነው። ተአማኒነት ባላቸው ሰዎች ስለነዚህ ምሥጢራዊ በራሪዎች የቅርብ ርቀት ዕይታ የቀረቡ በርካታ ሪፖርቶች አሉ። እናም ደግሞ እያንዳንዱ ዘገባ ላይ ተመሳሳይ የሆኑ በርካታ ሪፖርቶች አሉ። በመንኮራኩሮቹ ላይ ምንም ዐይነት አርማ ወይም የመለያ ምልክት የለባቸውም።...ጥያቄው ታዲያ እነማን ወይም ምንድን ናቸው? የአየር ድንበራችንን የሚጥሱትስ ለምንድነው? የሚል ነው።"

በ1947 ዓ.ም ፕሮፌሰር ፖል ሳንቶሪኒ የተባሉ ታዋቂ የግሪክ ሳይንቲስት በግሪክ ሰማይ ላይ የሚበሩ ሚሳይሎችን እንዲመረምሩ ተጠይቀው ነበር። "ሚሳይሎች አለመሆናቸውን በፍጥነት አረጋገጥን። ነገርግን ከዚህ በላይ ከመራመዳችን ወይም ሌላ ነገር ከማድረጋችን በፊት ጦር ሠራዊቱ ከውጭ መንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ተነጋግሮ የምናደርገውን ምርመራ እንድናቆም

@BOOKALEM

ትዕዛዝ ሰጠ። የውጭ አገር ሳይንቲስቶች ከኔ ጋር ምሥጢራዊ ንግግር ለማድረግ ወደ ግሪክ በረሩ። (ገቡ) የ ያ.ቢ.አን (ዩ.ኤፍ.አ) ጥያቄ ዓለም አቀፋዊ የምሥጢር ብርድ ልብስ ጀቡኖታል። ለዚህም ምክንያት ከሆኑት ውስጥ ባለሥልጣናት ሊከላከሉ የማይችሉት ኃይል መኖሩን ለማመን ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ነው!" ሲሉ ፕሮፌሰሩ በተጨማሪ አረጋግጠዋል።

ከ1947 እስከ 1952 ዓ.ም ድረስ ኤ.ቲ.አይ.ሲ. (ኤር ቴክኒካል ኢንቴሊጀንስ ሴንተር) የአየር ቴክኒካዊ መረጃ ማዕከል በግምት ከ 15ዘ በላይ የሚሆን ሕጋዊ ዕይታ (ያ.ቢ.አዎችን አየን የሚሉ ሪፖርቶችን) ተቀብሏል። ከዚህም ውስጥ ሃያ በመቶ የሚሆኑትን አየር ኃይሉ "ሳይታወቁ የቀሩ" ብሎ አስቀምጧቸዋል።

ኤር ቺፍ ማርሻል ሎርድ ዶውዲንግ የሮያል ኤር ፎርስ (የእንግሊዝ አየር ኃይል) ተዋጊ እዝ አዛዥ ሆነው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ያገለገሉ እንዲህ ብለው ጽፈዋል።

"ከአሥር ሺህ የሚበልጡ የበራሪ መኮራኩሮች ዕይታዎች ከዚህ ውስጥ አበዛኛዎቹ ሳይንሳዊ ማብራሪያ ያልተገኘላቸው ዘገባዎች ቀርበዋል። እነዚህ በራሪ ነገሮች በራዳር ላይ የታዩ ሲሆን ፍጥነታቸውም በሰዓት 9000 (ዘጠኝ ሺህ) ማይልስ ድረስ ነበር። እኔም እነዚህ ነገሮች በእርግጥ ያሉ ለመሆናቸውና በምድራችን ላይ ከሚገኙ መንግሥታት በአንዱም ያልተመረቱ ለመሆናቸው አምናለሁ።"

በቅርብ ጊዜ ኤልምውድ ዊስኮንሲን ውስጥ የከተማው ነዋሪዎች በአጠቃላይ በራሪ ዲስኮች በከተማቸው ሰማይ ላይ ለበርካታ ቀናት ሲበሩ ተመልክተዋል።

የፈረንሳይ አየር ኃይል ዋና አዛዥ ለመሆን የበቁትና ማዕከላዊ አውሮፓ ውስጥ የሕብረቱ (ናቶ) አየር መከላከያ አስተባባሪ በመሆን ያገለገሉ ጄነራል ሊኦኔል ማክስ ቻዚን እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል። "እንግዳ የሆኑት በራሪ ነገሮች የመታየታቸው ጉዳይ በአሁኑ ጊዜ የማያጠያይቅ ሆኗል።...አሳቢ፤ ብሩህ አዕምሮ ያላቸው፤ የተማሩና በትክክል ራሳቸውን የሚቆጣጠሩ ሰዎች እንግዳ የሆኑ ነገሮችን ያዩና እነሱንም በትክክል መግለጽ የቻሉ በየዕለቱ ቁጥራቸው እየጨመረ ነው።

ከዚህ ቀጥሎም የ1947 ዓመተ ምሕረቱ ዝነኛው የሮዝዌል አደጋ ተከሰተ! የዐይን ምስክሮች ከሰጡት የምስክርነት ቃል አንጻር በጁላይ 2-1947 ዓ.ም አንድ የዲስክ ቅርጽ ያለው ብሩህ በራሪ አካል በሮዝዌል ኒው ሜክሲኮ ላይ ሲያንዣብብ ታየ። በማግስቱ ደግሞ በስፋት የተበታተነ የዚሁ በራሪ መኮራኩር ስብርባሪ አካል በአንድ የአካባቢው የእርሻ ሥራ አስኪያጅና በሁለት ልጆቹ ተገኘ። ሁኔታው ለባለሥልጣናት ተነገረና የበራሪ ዲስክ ስብርባሪ መገኘቱን የሚገልጽ ሕጋዊ የሆነ የዜና መግለጫ ወጣ። ከዚህ ቀጥሎ ወዲያውኑ የተገኘው ስብርባሪ የአየር ንብረት

@BOOKALEM

ባሉን እንጂ ሌላ ነገር አለመሆኑን የሚገልጽ ሌላ የዜና መግለጫ (ፕሬስ ኮንፍረንስ) እንዲቀርብና እንዲታይ ተደረገ። ይህ በዚህ እንዳለ እውነተኛው ስብርባሪ ወደ ራይት ፊልድ መላኩ ይነገራል።

በአንድ ምስክር አገላለጽ መሠረት ስብርባሪ መንኮራኩሩ ውስጥ የተገኘው የአብራሪዎቹ ሙት አካል "ሰዎችን የመሰሉ ግን ሰብአዊ ሰው ያልሆኑ!" ተብሎ ተገልጿል። የራስ ቅላቸው ክብና ፀጉር የለሽ፤ ዐይኖቻቸው ትንንሽና ቅዱ ሰፋ ያለ፤ ከኛ ከሰዎች ቁመና አንጻር ትናንሾች፤ ከራሳቸው ሰውነት ጋር ሲነፃፀር ጭንቅላታቸው በጣም ትልልቅ፤ አንድ ወጥ የሆነ ግራጫማ ቀለም ያለው ልብስ ለብሰዋል። ሁሉም ወንዶች ሲመለሱ ቁጥራቸው በርካታ ነበር። ወዲያው ወታደራዊ ባለሥልጣናት መጥተው ከተረከቡ በኋላ ስላየንው ነገር ለማንም ምንም እንዳናወራ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶን ሥፍራውን እንድንለቅ ታዘዝን።"

በ1948 ዓ.ም ከአንድ የመረጃ ምንጭ ከተገኘ ሰነድ ለመረዳት እንደተቻለው እጅግ በጣም ምሥጢራዊ የሆነ እና የምሥጢር መጠሪያው "ማጀስቲክ 12""የተባለ ስለ ያ.በ.አ.ዎች ምርመራ የሚያደርግና ግኝቶቹንም በቀጥታ ለፕሬዚደንቱ የሚያቀርብ ቡድን በፕሬዚደንት ትሩማን ተቋቋመ። ኖቬምበር 18/1952 ዓ.ም የተዘገበና "Top secret Majic eyes only (በጣም ከፍተኛ ምሥጢር ለማጂክ ዐይኖች ብቻ)" በሚል ርዕስ በወቅቱ የአሜሪካን ፕሬዚደንት ሆነው የተመረጡት ፕሬዚደንት ድዋይት አይዘንአወርን ለማሳመን ተብሎ በአድሚራል ሔሊንኮተር የተዘጋጀው ሰነድ እንደሚለው "የመከስከስ አደጋው ከደረሰበት ክሮዝዌል ሁለት ማይልስ ያህል ራቅ ብሎ ከሌላ ዓለም የመጡ አራት እንግዳ ፍጡራን ተገኝተዋል" የሚል እጅግ በጣም አስደናቂ የሆነ ሐተታ ዘግቧል። "የብሔራዊ ፀጥታን ቀጣይ አስፈላጊነትን በማስመልከትና በዚህም አነሳሽነት የእነዚህ እንግዳ ፍጡራን ጉብኝት ከፍተኛ ዓላማ ምን እንደሆነ ሳይታወቅ በመቅረቱ.....በዚህና ግልጽ በሆነው የዓለም አቀፍ ቴክኖሎጂካዊ ግንዛቤ እንዲሁም ሕዝባዊ ፍርሃትና ሽብርን በማናቸውም ዐይነት ዋጋ ሁሉ ከማስወገድ አስፈላጊነት የተነሳ በአዲሱም አስተዳደር ውስጥ ጥብቅ የሆነ የፀጥታ (ምሥጢር) ጥበቃ ያለአንዳች መቋረጥ መቀጠል አለበት።" ሲል የማጀስቲክ 12 ቡድን አንድ ዐይነት የሆነ አስተያየቱን ያቀርባል። ይህ በዚህ እንዳለ ከባለሥልጣናት የተሰጠው ሕጋዊ ማስተባበያ ግን የዚህ ሰነድ ተአማኒነት አጠያያቂ መሆኑን ነው።

የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ያ.በ.አ.ን በተመለከተ ከአንድ መቶ በላይ ሰነዶችን በምሥጢር መያዙ ሲነገር ሲ.አይ.ኤ ደግሞ በግምት ሃምሳ የሚሆኑ ዲ.አይ.ኤ. (ዲፌንስ ኢንቴሊጀንስ ኤጀንሲ) ስድስት ሰነዶችን በከፍተኛ ምሥጢር ደብቀው ይዘዋል። ሻለቃ ዶናልድ ኪሆ የተባሉ የቻርለስ ሊንድበርግ የቀድሞ ረዳት "የአሜሪካ መንግሥት ሕዝባዊ ሽብርና ፍርሃትን ለመከላከል ሲል የ ያ.በ.አ.ን መኖር ይክዳል" ሲሉ በግልፅ ከሰዋል። በአገስት 1948 ዓ.ም የአየር ኃይል

@BOOKALEM

ቴክኒካዊ መረጃ ማዕከል በጣም ምሥጢራዊ በሆነውና "ሁኔታውን መገመት" በሚለው ሰነዱ "ያ.በ.አ. ከሌላ ፕላኔት የሚመጡ ሕዋው አቋራጭ ጎብኚዎች ናቸው!" ብሎ አስተያየቱን በሰጠበት ጊዜ በወቅቱ የአየር ኃይሉ ቺፍ አፍ ስታፍ የነበሩት ጄነራል ባንደንበርግ ሰነዱ እንዲቃጠል አዘዋል። እውነቱን ከሕዝብ ጆሮ ለመደበቅ የተቀነባበረ ዓለም አቀፍ የመንግሥታት ሴራ ይኖር ይሆን? ከስድስት ዓመታት አነስ ባለ ጊዜ ውስጥ በከዋክብት ጦርነት (ስታር ዋርስ) ዐይነት ፕሮጀክት ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ሃያ ሦስት እንግሊዛዊያን ሳይንቲስቶች አጠያያቂ በሆነ ሁኔታ ሞተዋል። የሚቾቹ ስም ቀንና ያሟሟት ሁኔታ ከዚህ የሚከተለው ነው።

1982- ፕሮፌሰር ኪዝ ቦውደን። በመኪና አደጋ የተገደለ።

ሐምሌ 1983- ጃክ ወልፈንደን። በአውሮፕላን ስፖርት በረራ አደጋ የተገደለ።

ጎዳር 1982- ስቴፈን ድሪንክወተር። ራስን በራስ አንቆ መግደል።

ሚያዚያ 1983-ሌ/ኮሎኔል አንቶኒ ጉድሌይ። የጠፋ። በኋላ ሞቷል የተባለ።

ሚያዚያ 1984-ጆርጅ ፍራንክስ። ራሱን ሰቅሎ የገደለ።

1985- ስቴፈን አክ። ራሱን ሰቅሎ የገደለ።

ጎዳር 1985- ጆናታን ዋሽ። ራሱን ከድልድይ ላይ በመወርወር የገደለ።

1986- ዶክተር ጆን ብሪታን። ራሱን በካርቦን ሞኖክሳይድ በመመረዝ የገደለ።

ጥቅምት 1986- አርሻድ ሸሪፍ። ብሪስቶር በተባለ ሥፍራ ከመኖሪያ ቤቱ ፲ ማይልስ ርቀት ላይ ገመድ አንገቱ ላይ አስሮ ሌላውን ጫፍ ዛፍ ላይ ካሰረ በኋላ በከፍተኛ ፍጥነት በመወርወር ራሱን የገደለ።

ጥር 1987-ፒተር ፔፔል። ጋራዥ ውስጥ መኪና ሥር ገብቶ ራሱን የገደለ።

ታሕሣስ 1987- ዴቪድ ሳንድስ። መኪናውን በከፍተኛ ፍጥነት እያሽከረከረ ቡና ቤት ጥሶ በመግባት ራሱን የገደለ።

ሚያዚያ 1987- ማርክ ዊዝነር። ራሱን አንቆ የገደለ።

ሚያዚያ ፲፩-198-7 ዴቪድ ስቱዋርት ጉዲንግ። ሳይፕረስ ውስጥ የተገደለ።

ሚያዚያ ፲፩-1987- ዴቪድ ግሪንሃል። ከድልድይ ላይ መውደቅ።

ሚያዚያ ፲፩-1987- ሻኒ ዋረን። ውሃ ውስጥ በመስጠም ራሱን የገደለ።

ግንቦት 1987- ሚካኤል ቤከር። በመኪና አደጋ የተገደለ።

ግንቦት 1988- ትሪቨር ናይት። ራሱን በራሱ የገደለ።

ነሐሴ1988- አሊስተር ቤክሃም። በኤሌትሪክ ራሱን የገደለ።

ነሐሴ 1988- ብርጋዲየር ፒተር ፊሪ። በኤሌክትሪክ ራሱን የገደለ።

ቀኑ ያልታወቀ- ቪክቶር ሙር። ራሱን የገደለ።

@BOOKALEM

ይህ ሁሉ ሞት አጋጣሚ ነው? ባለፉት ሦስት አሥርተ ዓመታት ውስጥ ከሰባ ሺህ በላይ የሚሆኑ ያልታወቁ መንኮራኩሮች መታየታቸው ሲዘገብ ከዚህም ሌላ ለቁጥር አዳጋች የሆኑ ያልታወቁ በራሪ ነገሮች ዕይታዎች ምናልባትም ከዚህ አሥር እጥፍ የሆኑት ሪፖርት ሳይደረጉ ቀርተዋል። የያ.ኢ.ቢ.አ ዕይታ ሪፖርቶች በመላው ዓለም ከመቶ በሚበልጡ አገሮች ይቀርባል።

ስፔይን ውስጥ – Ojectos foladerod No. Identitiecados.

ፈረንሳይ ውስጥ – Soucuops Volahtes

ጀርመን ውስጥ – Fliegehd Unetertassch

ቼኮዝላሎቫኪያ ውስጥ – Letajici Talire ተብለው ይጠራሉ።

ታዋቂው አስትሮኖመር ካርል ሳጋን በኛ ጋላክሲ ሚልኪ ዌይ ውስጥ 25ነ ቢሊዮን ከዋክብት ይኖራሉ ብሎ ሲገምት ከዚህ ውስጥ አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ አንድ ዐይነት ሥልጣኔ የያዙ ፕላኔቶች ይኖራሉ ብሎ ያምናል።

የኛ መንግሥት (አሜሪካ) ሌላ የውጭ ዓለም ሥልጣኔ መኖሩን ይክዳል። ቢሆንም ግን በኮሎምበስ መታሰቢያ ቀን 1992 ዓ.ም ካሊፎርኒያ እና ፖርቶሪኮ ውስጥ ናሳ (የአሜሪካ የጠፈር ምርምር ድርጅት) በሕዋው ውስጥ የሠለጠነ ሕይወት መኖሩን ማወቅ የሚያስችል በአሥር ሚሊዮን የሚቆጠሩ የራዲዩ ቻናሎችን የሚተነትን ልዩ የራዲዮ ሞገድ ተቀባይ መሣሪያና ኮምፒተር ያለው ራዲዮ ቴሌስኮፕ ወደ ጠፈር ይልካል።

ናሳ (NASA) ይህንን ተልዕኮ "ሞፕ mop" (Micriwave observing Project) የሚል የቅጽል መጠሪያ ሰጥቶታል። ነገር ግን የሥነ–ከዋክብት ሊቃውንቶች "ሴቲ seti" (Search for extra terstrial Intelignce) ብለው ይጠሩታል።

ሁለት የአሜሪካ የቀድሞ ፕሪዚደንቶች ስለ ያ.ቢ.አ ወይም ስለሌላ ዓለም ፍጡራን የሚያወቁት ነገር እንዳለ ጠይቂያቸው ነበር። መልሳቸው ግን አሉታዊ ነበር። አንድ ዐይነት የሚያውቁት መረጃ ቢኖርስ ይነግሩኝ ነበር? ይህንን አርእስት በተመለከተ ከተጋረደው የምሥጢር ብርድ ልብስ እንጻር የሚነግሩኝ አይመስለኝም።

በራሪ ዲስኮች ወይም ኳሶች በእርግጥ አሉን? ከሌላ ዓለም በሚመጡ እንግዳ ፍጡራን እየተጎበኘን ነውን? የሠለጠነ ሕይወት በጠፈር ውስጥ መኖሩን ለማወቅ አዳዲስ ቴክኖሎጂ በጥልቁ ሕዋው ውስጥ ከሚያደርገው ፍተሻ አንጻር ምናልባት መልሱን ከገመትንው የጊዜ ርዝመት ቀደም ብለው እናገኝ ይሆናል።

በጠፈር አሰሳ፤ በሥነ–ከዋክብት ምርምር፤ በሕዋው አፈጣጠር ላይ ጥናትና ምርመር የሚያደርጉና ከላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የማይጠበቁ በርካታ ሰዎች ሲኖሩ እነሱም ጥናታቸውን በአንድ ጭብጥ ላይ በማንጠልጠል የራሳቸው የሆነ መላ ምት ወይም ጥቆማ እየሰጡ ነው። አዩዋ

@BOOKALEM

አሜስ በሚገኝው "አሜስ ምርምር ማዕከል" በሚባለው የናሳ የምርምር ማዕከል ውስጥ የኤስ.ኢ.ቲ.አይ. ሳይንቲስትና አስትሮ ፊዚሲስት የሆኑት ጂል ታርታርል ከነዚህ ሰዎች አንዱ ናቸው።

"በጋላክሲያችን (ሚልኪ ዌይ) ውስጥ 400 ቢሊዮን ከዋክብት አሉ። እኛ የተሠራነው በጣም ተራ ከሆነው የከዋክብት አቧራ ነው። በከዋክብት አቧራ ከተሞላው ሕዋው ውስጥ ብቸኛዎቹ ፍጡራን እኛ ነን ብሎ ለማመን በጣም ያስቸግራል።"

ኮሎኔል ኤል ጎርደን ኩፐር ለአምባሳደር ግሪፊዝ ከጻፈው ደብዳቤ የተወሰደ።

አምባሳደር ግሪፊዝ
በተባበሩት መንግሥታት የግሬናዳ ተወካይ
866 2ተኛ ጎዳና
ክፍን ቁጥር 502
ኒው ዩርክ–ኒው ዩርክ
ውድ አምባሳደር ግሪፊዝ

U.F.O (ያ.በ.ኢ) ተብለው በሕዝብ ዘንድ ስለሚታወቁ ከሌላ ዓለም (ፕላኔት) የሚመጡ ጎብኚዎቻችንን በተመለከተ ያለኝን አስተያየትና እነሱን በተመለከተ መወሰድ ስለሚገባው ትክክለኛ ነገር ሐሳቤን ላቀርብልዎ እወዳለሁ።

እነዚህ ፕላኔታችንን (መሬትን) የሚጎበኙ የጠፈር መንኮራኩሮችና አብራሪዎቻቸው ከሌላ ዓለም ወይም ከምድራችን ውጭ የሚመጡና በግልጽ ለመረዳት እንደሚቻለውም ከቴክኒካዊ ሙያ አንጻር እዚህ መሬት ካለንው ሰዎች የበለጠ የሠለጠኑ ናቸው ብዬ አምናለሁ። ይህንን በተመለከተ ከመላው ዓለም ገጠመኞችን በሳይንሳዊ መንገድ የሚሰበብና የሚተነትን እንዲሁም በእነዚህ ጎብኚዎች ዘንድ እንዴት በወዳጅነት መንፈስ ጣልቃ መግባት የሚቻልበትን የተሻለ ዘዴ የሚወሰን በከፍተኛ ደረጃ የተቀነባበረ ፕሮግራም እንዲኖረን የሚያሰፈልግ መሆኑን አምንበታለሁ። እኛ በእነሱ ዘንድ ሙሉ በሙሉ ብቃት ያለን የሕዋው አባል የመሆን ተቀባይነት ከማግኘታችን በፊት ችግሮቻችንን ሁሉ ከጦርነት ይልቅ በሰላም ለመፍታት መቻላችንን ልናሳያቸው (ልናሳምናቸው) ይገባል። ይህንን ተቀባይነት ማግኘት ደግሞ ዓለማችንን በሁሉም ዐይነት መስክ ለማምጠቅ (ማሠልጠን) የሚያስችል ዕድል ይሰጠናል። ይህ ከሆነ በኋላ በእርግጥ የተባበሩት ምንግሥታት ድርጅት ይህንን ጉዳይ በፍጥነትና በብቃት ለመምራት የሚያስችል ሥልጣን ይኖረዋል።

እኔ በቂ ልምድ ያለኝ የያ.በ.ኢ. ጉዳይ ተመራማሪ አለመሆኔን ላሳውቅ እወዳለሁ። እስካሁን ያ.በ.ኢ. የማብረርም ሆነ ከአብራሪዎች ከአንዱም ጋር የመገናኘት ዕድል አልገጠመኝም። እነዚህ ጎብኚዎች በሚጓዙበት ሰፊ ድንበር

@BOOKALEM

ውስጥ እስካለሁ ድረስ ስለነርሱ ለመወያየት ብቃት አለኝ ብዬ አምናለሁ። እንደዚሁም ደግሞ በ1951 ዓ.ም በምድረ አውሮፓ ላይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ በተዋጊ የበረራ ሠልፍ ገብተው የተለያየ መጠን ያላቸውን መንኮራኩሮች ለሁለት ቀናት ያደረጉትን በርካታ በረራ የማየት ዕድል አጋጥሞኛል። በዚያን ጊዜ የኛ ተዋጊ ጀቶች ሊደርሱ ከሚችሉበት ከፍታ እጅግ በጣም ርቀው (ከፍ ብለው) ነበር የሚበሩት።

ከዚህም በማያያዝ ለማመልከት የምፈልገው በርካታ ጠፈርተኞች የያ.በ.አ.ን ጉዳይ በተመለከተ ለመወያየት ወይም ለመናገር በጣም ዝግተኞች ናቸው። ምክንያቱም በርካታ የሆኑ ሰዎች በግድ የለሽነት የማታለያ ታሪኮችንና የሐሰት ሰነዶችን በመሸጥ ስማቸውንና ዝናቸውን ያለማወላወል ስለሚያጠፉባቸው ነው። የ ያ.በ.አ.ን ጉዳይ በተመለከተ ቀጣይ ተሳትፎ ያላቸው ጥቂት ጠፈርተኞች ሥራቸውን በከፍተኛ ጥንቃቄ ማከናወን አለባቸው። በያ.በ.አ. መኖር የምናምን እና ያ.በ.አዎችን መሬት ላይ ወይም ከአውሮፕላን ላይ የማየት ዕድል ያጋጠመን በርካታ ሰዎች አለን። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ይህንን ፕሮጄክት ለማንቀሳቀስ ከተሰማማ ምናልባት በርካታ ብቃት ያላቸው ሰዎች ፊት ለፊት ቀርበው በጉዳዩ ላይ ሊገኝ የሚችል ማስተማመኛ እገዛና መረጃ ሊለግሱ ይችላሉ።

በቅርቡ ላይዎት እሞክራለሁ።

በእውነት

ኤል ጎርደን ኩፐር

ኮሎኔል የ.ኤስ ኤር ፎርስ ጠፈርተኛ።

ቡክዓለም በቴሌግራም ያቀረበው መጽሐፍ
@BOOKALEM

@BOOKALEM



በስዊስ የአልፕስ ተራራ ላይ አንድ የአየር ንብረት መመርመሪያ ባሉን ተከስክሶ ተገኘ። እዚህ ላይ መላው ዓለም ከዚህ በፊት አይቶትም ሰምቶትም የማያውቀው ቅዠት ተጀመረ...!

እጅግ በጣም አስደንጋጭና አስፈሪ የሆነ ከፍተኛ ምስጢር በዓይናቸው የተመለከቱ አሥር የተለያዩ አገር ዜጎችን አድኖ እንዲይዝ ኮማንደር ቤላሚ ተመረጠ።

ግዳጁን በመወጣት ላይ እንዳለ የመላው ዓለም መረጃ ድርጅቶች እሱን በማደን ላይ መሆናቸው ይሰማው ጀመር። ግን ለምን...?

እንደገና ኤዲት ተደረጎ ለ12ኛ ጊዜ የታተመ። የሲዲኒ ሼልደን የመጨረሻው ምርጥ መጽሐፍ!!

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ
0113 691933

12150 ብር

@BOOKALEM